የአማርኛ ሰዋስው

የተሻሻለ ሁለተኛ እትም

ለዲ/ር አንዷለም
ከመለሰችላቸው ምኞት ጋር
ገሌ ያሚገኙ
መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ባየ ይማም

© የደራሲው መብት በህግ የተከበረ ነው

የመጀመሪያ እትም 1987
የተሻሻለ ሁለተኛ እትም 2000

ISBN 978 – 99944 – 999 – 8 - 4

ባየ ይማም

መታሰቢያነቱ፣

ለይማም መኩንን አግደው

ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ አፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ) በባህልና ጥበብ ሙያዎች ውስጥ ባሉ ሰዎች የተመሰረተ መንግስታዊ ያልሆነ ማሕበር ነው።

የሶሳይቲው አላማ የኢትዮጵያን ሰፊ የባሕልና የልዩ ልዩ ጥበባት ሃብት፣ የሕዝቦቿን ነባር ልማዶች፣ ሀገር በቀል እውቀት፣ አመለካከት፣ ማህበራዊ አስተዳደር፣ የተፈጥሮ ሃብትና ይህን ሃብት በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅና ለመንከባከብ ያሏቸውን ጥቡበና ዘዴዎች፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኛ ናቸው የሚሏቸውን የእውቀት፣ የባሕልና የጥበብ ሃብት በመንከባከብ፣ በማልማትና ዘላቂነታቸው እንዳይደናቀፍ በማድረግ ረገድ ጠቃሚ የሆነ አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው።

ይህን አላማ ለማሳካት ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ ሀገርኛ የሆኑ ባለሙችና ኪነጥበባዊ ከዋኔዎች እንዲበለፅጉና እንዲከበሩ የሚረዱ ስራዎችን ማገዝ ነው። ይህን የአማርኛ ስዋስው መጽሐፍ የማሳተሙን ስራ ለመደገፍ ሲወስንም የቋንቋው ተናጋሪ ህዝብ ባህል ህያው ሆኖ ለተከታይ ትውልድ እንዲሸጋገር ይረዳል በሚል እምነት ነው።

ዋና መስሪያ ቤቱ በዩናይትድ ስቴትስ ካሊፎርኒያ የሚገኘውና የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ነባር እውቀትና ባህላዊ ህይወት በመደገፍ ላይ የሚገኘው «ዘ ክሪስተንሰን ፈንድ» ድርጅት ኬዝ በልዩ ልዩ መስኮች ለሚያደርጋቸው ጥረቶች ያልተቋረጠ እገዛ በመስጠት ላይ ነው። የአገራችን ማህበረሰቦች የተፈጥሮአዊ አካባቢ ብዝሀ ህይወትን ዘለቄታዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ያሏቸውን ልማዳዊ የአስተዳደር ብልሃት ተንከባክቦ ለማቆየት መጠነ ሰፊ እርዳታም ያደርጋል። ድርጅቱ የዚህን መጽሐፍ የአርትአትና የሕትመት ሙሉ ወጪ በመደገፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓልና በዚህ አጋጣሚ ምስጋናችንን ልናቀርብ እንወዳለን።

እንዲሁም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለበርካታ አመታት ምርምር በማካሄድ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባስተማሩባቸው አያሌ አመታት በመስክ በርካታ ምሁራንን በማፍራት ለአገራቸውና ለአለም የላቀ አገልግሎት ላበረከቱትና ዛሬም ይህንን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውንና እጅጉን አድካሚ የሆነውን መጽሐፍ ላዘጋጁት ለፕሮፌሰር ባዬ ይማም፣ ከርሳቸው ጋርም ባህላዊና ስነልሳናዊ እውቀታቸውን በማካፈል ለመጽሐፉ ዝግጅት ትልቅ ድርሻ ለነበራቸው የቋንቋው ተናጋሪዎችና የባህል አዋቂዎች ሁሉ ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ አፍ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል።

ይህ የአማርኛ ስዋስው መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋም ሆነ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለሚደረጉ ምርምሮችና ተከታታይ ጥናቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውና ሰሌሎች ተመሳሳይ ሰራዎችም አርኣያ ሊሆን እንደሚችል ተስፋችን የላቀ ነው።

ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ አፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ)

ጥቅምት 2000፣አዲስ አበባ

ማውጫ

ምህፃረ-ቃል viii
ምሊጋና x
መቅድም xi
መግቢያ xvii

ምዕራፍ አንድ 1
ስነ-ድምፅ 1
መግቢያ 1
ተናባቢ 2
እግድ 7
ፍትግ 8
ፍግድ 9
ስርናዊ 10
ጎናዊ 10
ከፍናቢ 11
አናባቢ 13
ርኒም 17
አቀነጻጀት 20
ቀለም 23

ድምፀ ልሳናዊ ሂደት 27
ምስለት 29
ከናፍራዊነት 30
ከፊል ላንቃዊነት 33
ሙሉ ላንቃዊነት 35
ትናጋዊነት 37
ማንቁርታዊነት 38
ከበት 39
ድምፀት 40
ኢድምፀት 42
ግድፈት 44
ጥብቀት 54
ልለት 56
ኢምስለት 58
ስርገት 59
ቅየራ 65

ቅፅላዊ ሀረግ 273
ስማዊ ቅፅል 274
ግሳዊ ቅፅል 276
ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ 279
መስተዋድዳዊ ሀረግ 284
መስተዓምራዊ ሀረግ 292

አረፍተ ነገር 304
የአረፍተ ነገር አይነቶች 307

ተራ አረፍተ ነገር 312
ሀተታዊ አረፍተ ነገር 318
ሁነታዊ አረፍተ ነገር 319
ገቢር አረፍተ ነገር 323
ተገብሮአዊ አረፍተ ነገር 335
መጠይቃዊ አረፍተ ነገር 340
አሉታዊ አረፍተ ነገር 348
ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር 361

ውስብስብ አረፍተ ነገር 368
ውስብስብ ሀተታዊ አረፍተ ነገር 369
ውስብስብ ስማዊ ሀረግ 369
መሙሊያ አረፍተ ነገር 369
አዛማጅ አረፍተ ነገር 374
ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ 385
ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ 408
ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረግ 416
ውስብስብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር 420

ሙዳየ ቃላት 448

ዋቢ መፃህፍት 458

ምህፃረ ቃል

273	ሀ	ሀረግ
274	ሁዋ	ሁዋለኛ
276	ላ	ላዩኛ
279	ል	ልክኛ
284	ታ	ታቸኛ
292	መ	መሀለኛ
	መሙ	መሙሊያ
304	መስ	መስተዋድድ
307	መስተ	መስተዓምር
	ማ	ማእከል
312	ማንቅ	ማንቁርት
318	ም	ምሰሶ
319	ስ	ስርን
323	ስ	ስም
335	ስሀ	ስማዊ ሀረግ
340	ባ	ባህሪ
348	ተ	ተናባቢ
361	ተግ	ተውሳክ ግስ
	ተግሀ	ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ
368	ቅ	ቅፅል
368	ቅሀ	ቅፅላዊ ሀረግ
369	ቅጣ	ቅጣይ
369	ንሀ	ንኡስ ሀረግ
374	(ኢ)ነ	(ኢ)ነዛሪ
385	ከ	ከፋች
408	አ	አናባቢ
416	አነ	አረፍተ ነገር
420	አን	አንስታይ
	አጎ	አንላግሽ
448	ድ	ድድ
	ግ	ግስ
	ግሀ	ግሳዊ ሀረግ
458	ፊ	ፊተኛ
	ጨ	ጨራሽ

ልዩ ምልክቶችና ፊደሎች

[ ] በድምፅ ደረጃ ንበታዊ አፃፃፍን፣ በሀረግ ደረጃ መዋቅራዊ አንድነትን ያሳያል።

/ / ፎኒማዊ አፃፃፍን ያመለክታል።

* በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ ሲገኝ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያመለክታል።

? ተቀባይነቱ አጠራጣሪ የሆነ አባባልን ያመለክታል።

ብ [β] <u>አበባ</u> ስንል የምንለማውን ልል ወይም ፍትግ "ብ" ይወክላል።

ም [ɱ] <u>ከም</u>ፈር ስንል የምንለማውን የከንፈርና የጥርስ የሆነ ውሁድ ድምፅን ይወክላል።

ን [ŋ] <u>አንጥት</u> ስንል የምንለማውን የትናጋ "ን" ይወክላል።

ምስጋና

ይህን መፅሀፍ በማዘጋጅበት ጊዜ በሀሳብም ሆነ በተግባር የተባበሩኝና የረዱኝ ብዙ ናቸው። ዝርዝሩ በድህረ ምረቃው ክፍል በተለያየ ጊዜ ያስተማርኩዋቸውን የስነ-ልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ተማሪዎችን፣ የስነ-ልሳን ትምህርት ክፍል ባልደረቦቼንና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ወዳጆቼን ያጠቃልላል። ለሁሉም ምስጋናዬ ክፍ ያለ ነው።

መፅሀፉን ለሁለተኛ ጊዜ ለህትመት ሳዘጋጅ፣ ረቂቁን በማንበብና የማሻሻያ አስተያየት በመስጠት ለረዱኝና ላበረታቱኝ ለሰለሞን ተሰማ፣ ለጌታቸው እንዳላማው፣ ለእያሱ ነጋ፣ ለደበላ ጎሽ፣ ለደረጀ ገብሬ፣ ለሙሉሰው አስራቴ፣ ለደርብ አዶ፣ ለዶ/ር ግርማ አውግቸው፣ ለዶ/ር ዘለዓለም ልየው፣ ለዶ/ር ሂሩት ወ/ማርያም፣ ለዶ/ር ሀይለየሱስ እንግዳሸት፣ ለዶ/ር ሞገስ ይገዙ፣ ለዶ/ር አበበ ገ/ፃድቅ፣ ለአቶ ሽመልስ ማዘንጊያ፣ ለብንያም ምትኩ፣ ለኑላ ጥሳሁን፣ እንዲሁም የመጨረሻውን ቅፅ በማተም ለተባበሩኝ ለዶ/ር ዮናስ አድማሱ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። በመፅሀፉ ውስጥ ለሚታይ ግድፈትም ሆነ ስህተት ተጠቃሽና ተወቃሹ ማንኛቸውም ሳይሆኑ፣ እኔው ራሴ መሆኔን በአፅንዖት እገልፃለሁ። ለዚህም ምክንያቱ የችግሩ መንስዔ ምናልባት የተሰጠኝን አስተያየት ሙሉ በሙሉ አለመቀበሌ ሲሆን ይችላል ብዬ ስለማምን ነው።

የመጨረሻውን ረቂቅ ለህትመት በማዘጋጅበት ጊዜ አስፈላጊውን ሁሉ በማቅረብ ክፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለሚሽገን ስቴት ዩኒቨርሲቲና ለኪዮቶ ዩኒቨርሲቲ ሀላፊዎችና ባልደረቦች ክልብ የመነጨ ምስጋናዬን እገልፃለሁ። የኪዮቶ የኒቨርሲቲዋ ታካኮ ኑማታ ስላደረገችልኝ ያላሰለስ የቴክኒክ እገዛም እንደዚሁ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በዚህም ሆነ በማንኛውም ስራዬ ላይ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ትብብርዋ ምን ጊዜም ለማይለየኝ ባለቤቴ ለስናይት ለማ፣ የተለየ ትዕግስታቸውና ፍቅራቸው ጉልበት ለማይሆነኝ ለቃለአብ፣ ለፀጋዘአብና ለምኒልክ ባየ ያለኝ ፍቅርና አድናቆት ከቃላት በላይ ነው።

በመጨረሻ የህትመቱን ወጭ ለሽፊነልኝ ለክርስትንስን ፈንድ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

መቅድም

ቁዋንቁዋ ሁለት የተያያዙ ዋና ዋና ተግባራት አሉት። አንደኛው ሀሳብን ማስተላለፍ ሲሆን፣ ሁለተኛውና የዚሁ ነፀብራቅ የሆነው ማንነትን ማመልከት ነው። የመጀመሪያውን ለነ-ልሳናዊ፣ ሁለተኛውን ማህበራዊ ተግባር ልንለው እንችላለን። ከዚህ አንፃር ማንኛውም ሰው ለለ አንድ ጉዳይ ሲናገር፣ የሚያስተላልፈው መልዕክት ሁለት ነው። አንደኛው፣ በቀጥታ ለለ ጉዳዩ የሚሰጠው አስተያየት ሲሆን፣ ሁለተኛውና ከዚህ የሚሰርፀው፣ ይህንን ሀሳብ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ ባድማጩ ላይ ስለራሱ ማንነት የሚያሳድረው ግምት ነው። ስለዚህም ንግግሩ ብሉም ቁዋንቁዋው የሀሳቡ ብቻ ላይሆን፣ የማንነቱም መግለጫ ነው።

"ካነጋገር ይፈረዳል ካያያዝ ይቀደዳል" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከዚህ ላይ ሲጠቀስ ይችላል። አንድ ቡቲፕ የተቀረፀን ንግግር በመስማት፣ ከንግግሩ ፍሬ ሀሳብ፣ ካነጋገሩ ለዛ፣ ማለትም ከቃላት አመራረጡ፣ ከድምፅ እወራረዱ፣ ወዘተ፣ ስለ ተናጋሪው አንዳንድ ነገሮችን ከሞላ ጎደል በትክክል መናገር ይቻላል። ይኸውም ተናጋሪው ገጠሬ ወይም ከተሜ፣ ወጣት ወይም ሽማግሌ፣ ሴት ወይም ወንድ፣ ገበሬ ወይም ነጋዴ፣ ወዘተ፣ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመለየት ነው። ከዚህም አልፈን፣ አንዳንድ ጊዜ "ይሽማ እገሌ አይደለም እንዴ!" እስከ ማለት ልንደርስ እንችላለን። ይህ አንግዲህ የአንድን ግለሰብ ንግግር ብሉም ማንነት ቦሚመለከት ነው።

ከግለሰብ አልፈን፣ ባንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ቁዋንቁዋ ተናጋሪዎችንም በወንዝና በተራራ ተለይተው፣ ራቅ ባለ ሌላ አካባቢ ከሚኖሩ የዚያው ቁዋንቁዋ ተናጋሪዎች እንደዚሁ ባነጋገር ዘይቤያቸው ለይተን ልናውቃቸው እንችላለን። ለምሳሌ አማርኛ ተናጋሪዎችን ብናይ፣ <u>ዴዴብ</u> የሚሰውን ወሎየ፣ <u>አልበልቶም</u> ከሚለው ጎጃሜ፣ <u>ባዔላ</u> የሚለውን መንዜ፣ <u>የግዳስ ጨቅሎቹን ከውናቸው</u>[1] ከሚሰው ጎንደሬ በቃል አመራረጡና አጠቃቀሙ መለየት ይቻላል። አያንዳንዱ አካባቢ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት ክልላዊ ዘይቤ አለው ማለት ነው[2]። ይሁን እንጅ፣ ይህ ዘይቤ የዚያው የአንድ አማርኛ የተለያየ ገፅታ ስለሆነ፣ ተናጋሪዎቹን በሀሳብ ከመግባባት አያግዳቸውም። እነሱም ቢሆኑ ቁዋንቁዋችሁ ምንድን ነው? ሲባሉ፣ በጥቅሉ "አማርኛ" ይላሉ

---

[1] ይልቅስ ህፃናቱን ሰብስባቸው ማለት ነው።
[2] ይህን በተመለከተ ሀይሉ፣ ጌታቸውና ኮውሌ (1976)ን፣ ህብተማርያም (1973)ን እንዲሁም ጌታሁን (1983)ን ይመልከቱ።

እንጅ፣ በከልላዊ መልኩ መንዝኛ፣ ጎጃምኛ፣ ወዘተ፣ አይሉም[3]። ከሌሎች ህዝቦች ተሰይተው <u>በተጨባጭ</u> የሚታወቁትም ከማንኛውም ሌላ መሰፈርት ይልቅ፣ በዚሁ ቁዋንቁዋ ተናጋሪነታቸው ነው።

ይህ ግን በአንድ ቁዋንቁዋ ተናጋሪዎች መካከል የሚታይ ሁኔታ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባለ <u>ልሳነ ብዙ</u> ሀገር ደግሞ ዜጎች ካንድ ቁዋንቁዋ በላይ ሊናገሩ ይችላሉ። የሚናገሩዋቸው ቁዋንቁዋዎች የሰርጭት ሰፋትና የአድገት ደረጃም የተለያየ ነው። እንዳንዱ ቁዋንቁዋ ሰፋፊ ክልል የሚሸፍንና የዚያኑ ያህልም ብዙ ተናጋሪ ያሰው ሲሆን፣ አንዳንዱ ደግሞ በጠባብ ክልልና በዚያው ውስጥ ብቻ በሚኖሩ ህብረተሰቦች የተወሰነ ነው። አንዳንዱ ለፅሁፍ የበቃና ሰፊ የሰነ-ፅሁፍ ቅርስ ያለው ሲሆን፣ ሌላው ገና ሰዚህ ያልደረሰና በንግግር ቁዋንቁዋነት ብቻ የተወሰነ ነው። እንደዚህ ያሉ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ቁዋንቁዋዎች በመናገር ዜጎች ብሄረሰባዊ ወይም ከልላዊ ማንነታቸውን ይገልፃሉ።

ይሁን አንጅ፣ እንደዚህ ያሉ ልሳነ ብዙ ዜጎች ከልል-አለፍ በሆነ ደረጃ የሚግባቡበት አናም በጋራ የሚታወቁበት አንድ የጋራ ቁዋንቁዋ ያስፈልጋቸዋል፣ ይኖራቸዋልም። በሀገራችን በዚህ ደረጃ በማገልገል ላይ ያለው ቁዋንቁዋ አማርኛ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ቁዋንቁዋው ከሌሎቹ ቁዋንቁዋዎች የሰፋ ሰርጭትና ከሁሉም የበዛ ተናጋሪ ያለው መሆኑ ነው። ባንድ ክልል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ ብዜራዊ ሰርጭትና ይዘት ያለው ቁዋንቁዋ ነው። ወደ የትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ቢኪድ፣ አማርኛ ተናጋሪ ማግኘት እያሰቸግርም። ርግጥ፣ የተናጋሪው ችሎታና ብዛት ከመሀል ሀገር እየራቁ በሄዱ ቁጥር፣ የዚያኑ ያህል እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል። ይህም ሆኖ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቁዋንቁዋ ይበልጥ ዜጎችን የማገናኘት አድሉ የተሻለ ነው።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ቁዋንቁዋ የህሳብ ብቻ ሳይሆን፣ የተናጋሪዎችን ማንነት መግለጫም ነው። ይህ ከሆነ፣ ብዙ ቁዋንቁዋ የሚናገሩ ሰዎች በልሳነ ብዙነታቸው አንድ ቁዋንቁዋ ብቻ ከሚናገሩት ተለይተው ይታወቃሉ ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉ ዜጎች እንደ ባለ ብዙ መታወቂያ ሰዎች ሊቆጠሩ ይችላሉ። ርግጥ፣ የመታወቂያው አይነትና አገልግሎት የተለያየ ሊሆን ይችላል። በአንድ በኩል፣ በከልላቸው በሚናገሩት ቁዋንቁዋ ብሄረሰባዊ ወይም ከልላዊ ማንነታቸውን ሲያሳውቁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብሄራዊ ደረጃ በጋራ በሚናገሩት ቁዋንቁዋ ብሄራዊ ዜግነታቸውን ያሳውቃሉ። በቀበሌ መታወቂያችን ጠባቡን ሰፈራችንን፣ በፓሰፖርታችን ኢትዮጵያዊነታችንን እንደምናሳውቀው ማለት ነው።

---

[3] በአንዳንድ የደቡብ ክፍል ህዝቦች፣ በተለይም በወላይታ፣ በጋሞ፣ በጎፋና በዳውሮ መካከል የዚህ አይነት አመለካከት አንዳለ በማስተማሪያ ቁዋንቁዋ ምርጫ ላይ በግልፅ ተከስቶአል። የወቅቱ ፖለቲካም አመለካከቱን የበለጠ አጠንክሮታል።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ለዚህ ብሄራዊ አገልግሎት የበቃው ቁዋንቁዋ አማርኛ ነው። በለሆነም ብሄራዊ ምልክት ነው፤ ሊባል ይችላል። ይህ አባባል ግን ሌሎቹ ቁዋንቁዋዎች ብሄራዊ ምልክት አይደሉም ወደሚል ድምዳሜ ሊወስደን አይገባም። ርግጥ፣ ሌሎቹም ቁዋንቁዋዎች ብሄራዊ ምልክቶች ናቸው። ብሄራዊነታቸው ግን እንደሚሸፍኑት ክልል የተወሰነ ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ አማርኛ ከሁሉም የሰፋ ስርጭትና አገልግሎት ስላለው፣ ከሁሉም የበለጠ ብሄራዊ ነው። ይህን በንልም ብዙ ክልል ያጻርሳል፣ የዚያኑ ያህልም ብዙ ህዝብ ያገናኛል ማለታችን ነው። ይህ ባንድ በኩል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቁዋንቁዋውን ብሄራዊነት የሚያሳዩ ስነ-ልሳናዊ ባህሪያትም አሉ።

የሀገራችንን ቁዋንቁዋዎች በጥቅሉ ከሌሎች ቁዋንቁዋዎች የሚለዩዋቸው በርካታ ስነ-ልሳናዊ ባህሪያት አሉ[4]። ከነዚህም ባህሪያት መካከል አብዛኞቹ የሚገኙት በአማርኛ ውስጥ ነው። ለምሳሌ፣ በድምፅ ደረጃ ብናይ፣ አንደ ትግርኛ ባሉ የሴም ቁዋንቁዋዎች ውስጥ ከሚገኙት አራት የጉሮሮ ድምፆች፣ አንደ ኦሮምኛ ባሉ የኩሽ ቁዋንቁዋዎች፣ እንዲሁም አንደ ባስኬቶ ባሉ የአሞ ቁዋንቁዋዎች ውስጥ ከሚገኙ አንዳንድ ለየት ያሉ የድድና የከናፍር ድምፆች በስተቀር፣ ሌሎቹን ባህሪያት በሙሉ የያዘ ቁዋንቁዋ ነው። በዚህ ረገድ ብዙ አናባቢና በርካታ የላንቃ ድምፆች ካሉዋቸው የአባያዊ ቁዋንቁዋዎች የሚጋራው ባህሪ በጣም ውሱን ነው። ለዚህ ምክንያቱ የአባያዊ ቁዋንቁዋዎች አፍሮኢሲያዊ ከሆኑት ከኩሽ፣ ከኦሞና ከሴም ቁዋንቁዋዎች በታሪክም ሆነ በዘር ህረግ የተለዩ መሆናቸው ነው።

በሰዋሰው ደረጃም ያለው ሁኔታ እንደዚሁ ነው። አንደ ትግርኛ ባሉ ቁዋንቁዋዎች ውስጥ ከሚገኘውና <u>በግዒ</u> ብሎ፣ <u>ዓባግዕ</u> ከሚለው አይነት የብዙ ቁጥር ስርዓት በስተቀር፣ ሌሎቹን ባህሪያት በሙሉ ያካተተ ቁዋንቁዋ ነው። ይህም በመሆኑ፣ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቁዋንቁዋ ይልቅ፣ ከአማርኛ ቁዋንቁዋ ስነ-ልሳናዊ ቅርፅና ይዘት በመነሳት፣ ሰለ ኢትዮጵያ ቁዋንቁዋዎች አጠቃላይ ባህሪ ከሞላ ጎደል በትክክል መናገር ይቻላል። ሰለ ሀገሪቱ ስነ-ልሳናዊ ባህሪያት አማርኛ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቁዋንቁዋ የበለጠ የተሙዋላ መረጃ ይሰጣል ማለት ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ታሪካዊ ምክንያት አለው።

ታሪኩ ከቁዋንቁዋው ውልደትና አድገት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ውልደቱና አድገቱ ደግሞ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው። ታሪካችን ባመዛኙ የወረራና የፍልሰት ታሪክ ነው፣ ሲባል ይችላል። በድርቅና በቸነፈር ምክንያት የትውልድ "አገሩን" እየለቀቀ ወደሌላ የተሻለ "አገር" በመሄድና በዚያው በመኖር ህዝብ ከህዝብ ሲቀላቀል፣ ሲወልድና ሲዋለድ ኖሮአል። ደጋው ሲራብ ቆላ ወርዶ፣ ቆላው ሲራብ ወይም በወባ

[4] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ፈርገሰን (1976)ን ይመልከቱ።

ሲረፈረፍ፣ ደጋ ወጥቶ "ከፋ ቀን" ማለስፍና መመለስ፣ አለያም በዚያው ለምዶ መቅረት፣ የተለመደ ነው። ለግዳይና ለእደን አገር አቁዋርጦ፣ መልካ ተሻግሮ መሄድና በለስ እስኪቀና ድረስ በሄዱበት መቆየት፣ ካልቀናም በዚያው ለምዶ መቅረት አስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረ ባህል ነው። እንደዚህ ያለው የህዝብ እንቅስቃሴና ተራክቦ አንዱ የታሪካችን ፈርጅ ነው።

ሴላው ፈርጅ ፖለቲካዊ ቅርፅና ይዘት ያለው ነው። ይህም ከግዛትና ከዕምነት ማስፋፋት ጋር የተያያዘ ስፊ እንቅስቃሴ ነው። በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት፣ በሰላም ብቻ ሳይሆን በህይልም ጭምር የሚፈፀም ተግባር ነው። በዚህ ረገድ፣ መጀመሪያ ከስሜን ወደ መህል አገር በሴማዊያን፣ በሁዋላም ከደቡብ ወደ ስሜን በኩሻዊያን፣ በተለይም በአሮሞ፣ በመጨረሻም አንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ለመመስረት ሊባል፣ ከመህል ህገር ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አንዲሁም ምስራቅ የተደረጉት ወረራዎችና ዘመቻዎች ጎላ ጎላ ብለው የሚጠቀሱት ናቸው።

በማንኛውም አይነት አንቅስቃሴ ቢሆን፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀስው፣ ህዝብ ከህዝብ ጋር እጅግ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ተቀሳቅሱአል። ወራሪ ሰራዊት ከወረረው ህዝብ ጋር አየተጋባ በዚያው ለምዶ ይቀራል እንጅ፣ ወደመጣበት አጅግም አይመለስም። ባለበት ሆኖ፣ የዘር ሀረጉን ከመጣበት አካባቢ ጋር ማጣቀስ ይቀናዋል።

በነዚህና እነዚህን በመሳስሉ እንቅስቃሴዎች ሳቢያ፣ ህዝብ ከህዝብ አንደተቀሳቀለ ሁሉ፣ ቁዋንቁዋ ከቁዋንቁዋ፣ ባህልም ከባህል ሊቀሳቀል ናሮአል። በዚህም ሂደት ውስጥ ቁዋንቁዋዎች ተወልደዋል፣ ቁዋንቁዋዎችም ሞተዋል። በአክሱማዊያን ዘመን ሰፊ ክልል ያዳርስ የነበረውና ስነ-ፅሁፋዊ ቅርሱ እንደ አማርኛ ላሉ ለዛሬዎቹ ቁዋንቁዋዎች መሰረት የሆነው የግዕዝ ቁዋንቁዋ ዛሬ የለም። ይህንንም ስንል፣ በግዕዝ አፉን የፈታና በአሱም የሚታወቅ የግዕዝ ብጄረስብ ወይም ህብረተስብ የትም አይገኝም ማለታችን ነው። ቁዋንቁዋውም ቢሆን በትምህርት አንጅ <u>በልምደት</u> አይታወቅም። ለትምህርት ሊበቃ የቻለውም ቃላቱ በመዝገብ፣ ሰርዓቱ በስዋስው፣ ስነ-ፅሁፉ በገድልና በዜና መዋዕል መልክ ተመዝግቦና ተደርሶ ለትውልድ በመተላለፉ ነው። ይህም ብመሆኑ ቁዋንቁዋው ተወላጅ ተናጋሪ ማህበረሰብ አንጅ፣ አንባቢና ተርጉዋሚ ምሁር ግለሰብ ዛሬም ቢሆን አላጣም።

የግዕዝ ፅድል ያላጋጠማቸው ሴሎች ቁዋንቁዋዎችም በዚያው ዘመንም ሆነ ከዚያ በፊት ኖረው ሊሆን ይችላል። ይሁን አንጅ፣ ፅሁፍ ለላነበራቸው ዛሬም ሆነ ወደፊት ስለነሱ የሚታወቅ ነገር የለም። አነዚህ ቁዋንቁዋዎች ትንሳዔ የሌለው የዘላለም ሞት ሞተዋል። ያልተፃፈና ስርዓቱ በወጉ ያልታወቀ ቁዋንቁዋ ተቆፍሮ ሊወጣ የሚችል ዕፅም የለውምና።

የቁዋንቁዋ ሞቱም ሆነ ልደቱ ባንድ ጀምበር የሚፈፀም አይደለም። ቀናትን ሳይሆን፣ ዘመናትን ይወስዳል። ምጡም ሆነ ጣዕሩ ረዥም ነው። ልደቱ የሚበሰረው በርካታ ተወላጅ ተናጋሪዎችን ሲያገኝና ጠንካራ ማህበራዊ መሰረት መያዝ ሲጀምር ሲሆን፣ መርዶው የሚነገረው ደግሞ ማህበራዊነቱ አክትሞ የመጨረሻ ግለሰብ ተናጋሪውን ሲያጣ ነው። የግዕዝ አሙዋሙዋትም ሆነ የአማርኛና የሴሎቹ ኢትዮሴማዊ ቁዋንቁዋዎች አፈጣጠር ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ የተለየ አይደለም።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ሰሚናዊያን የሴም ወገኖች ግዛታቸውን እያስፋፉ ወደ መሀል ሀገር የመጡት ልዩ ልዩ የኩሽ፣ የኦሞና የአባያዊ ቁዋንቁዋዎችን በሚናገር ዘማች ሰራዊትና ከግዕዝ ትንሽ ሰየት የሚል የሴም ቁዋንቁዋ ይናገሩ በነበሩ አዝማቾች አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል[5]። አዝማችና ዘማች ባቀኑት የአገው መሬት ላይ ከህዝቡ ጋር መኖር ይጀምራሉ። የተለያየ ቁዋንቁዋ ይናገር የነበረው ሰራዊትም፣ ቀሰ በቀሰ ያዝማቹቹን ሴማዊ ቁዋንቁዋ መልመድ ይጀምራል። አጀማመሩም ቁዋንቁዋውን እንዳስ በመማር ሳይሆን፣ ከራሱ ቁዋንቁዋ ጋር አያቀላቀለና አያዋሀደ በመናገር ነው። ዛሬ ታይፕ የሚሰውን የአንግሲዝኛ ቃል ወሰደን፣ ተየበ፣ ተያቢ፣ ትየባ፣ ትይብ፣ ወዘተ፣ አያልን አማርኛ አያሰመሰልን እንደምንጠቀምበት ሁሉ፣ ሴማዊያኑ የሚናገሩትን ቃላትም ሰራዊቱ በዚሁ አይነት ከራሱ ቁዋንቁዋ ጋር አያመሳሰለና አያዳቀለ ይናገር ነበር።

ይህ በቃላት ደረጃ ሊሆን፣ በመዋቅር ደረጃ ደግሞ በግስ ይጀምር የነበረውን ያዝማቾቹን ቁዋንቁዋ የራሱን ቁዋንቁዋ በማሰመሰል በግስ እንዲጨርስ ያደርገው ጀመር። በዚህም ምክንያት ዛሬ አማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹም ኢትዮሴማዊ ቁዋንቁዋዎች፣ ከግዕዝ በስተቀር፣ አንደ ዐረብኛና አንደ ዕብራይስጥ ካሉ በግስ ከሚጀምሩ ሴሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች ሊለዩ ችለዋል። የቃላቱ ቅርፅና የመዋቅሩ ስርዓት በዚህ አይነት ቀስ በቀስ እየተሰወጠ የመጣው ያዝማቾቹ ቁዋንቁዋ፣ ከጊዜ ብዛት ሴማዊ ባህሪውን አየተወ፣ በዚያው ልክም የኩሽና የኦሞ ቁዋንቁዋዎችን (ኩሾኦሞአዊ) አየመሰለ መጣ። ወደ አራተኛው ከፍለ ዘመን አካባቢም ባብዛኛው መልኩ ከጥንቱ የሴም ቁዋንቁዋ የተለየ ይሆንና

---

[5] ቤንደር (1983)ን አንዲሁም ታደሰ ታምራት (1972)ን ይመልከቱ። የግዛት ማስፋፋቱ እንቅስቃሴና የህዝቦች የፍልሰት አቅጣጫ ከመሀል ወደ ዳር፣ ከኢትዮጵያ ወደ ባህር ማዶ ሊሆን አንደሚችል የሚጠቁሙ ስነ-ልሳናዊ መረጃዎች አሉ። ሆኖም ጉዳዩ አሁንም አከራካሪ ስለሆነ ከታሪክና ከቅድመ ታሪክ አንፃር በስፋትና በጥልቀት ሊታይ ይገባዋል። ለጊዜው ግን ነባሩንና ውጭ - ተኮር የሆነውን የአንኡለንዶርፍ (1955)ን አመለካከት ለመነሻም ቢሆን መውሰድ ይቻላል። ወስጥ-ተኮር ስለሆነው ዘመናዊ አመለካከት ሀድስን (1978)፣ ኤረት (1988)፣ አንዲሁም አየለ በክሪ (1997)ን ይመልከቱ።

የተለየ ሰም ይፈልጋል። ስለዚህም ይነገርበት ከነበረው ያካባቢ ሰም በመነሳት "እማርኛ" ተብሎ መጠራት ይጀምራል[6]።

ሁኔታው ባንድ የተለየ ብሄረሰብ ሳይሆን፣ የተለያየ ቁዋንቁዋ ይናገር በነበረ ዘማችና አዝማች የተፈጠረ የሰራዊት ቁዋንቁዋ ነበር ለማለት ያስችላል። መሰረታዊ መድበለ ቃላቱ፣ ዛሬም ቢሆን ባብዛኛው ሴማዊ ሲሆን፣ በመጠኑ ደግሞ ኩሻዊ ነው። ለዚህ እንደ ውሻ፣ ስጋ፣ ካራ፣ ውሀ፣ ሽከና፣ አኩሌ፣ አሬራ፣ ኮርቻ፣ ሰንጋ፣ ቀብድ፣ ዱላ፣ ወዘተ፣ ያሉትን ቃላት አንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ በሙሉ ኩሻዊ ናቸው። እንደ ብርሌ፣ አረቄ፣ ቆላስ፣ ዲያቆን፣ ዲያቢሉስ፣ ወዘተ፣ ያሉት ደግሞ በሀይማኖት ሳቢያ የመጡ የግሪክ ቃላት ናቸው። እንደተጠቀሱት ባሉ የኩሽ ቃላት ተጋቦት ምክንያት ዛሬ ከሌሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች የሚለዩትን እንደ [ሽ፣ ች፣ ጅ፣ ጭ፣ ኝ] ያሉትን የላንቃ ድምፆችና እንደ [ጵ፣ ፕ] ያሉትን ከግሪክ ቃላት ጋር የመጡትን የከናፍር ድምፆች ሲይዝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በጥንቱ የሴም ቁዋንቁዋ ውስጥ የነበሩትንና ዛሬም ቢሆን እንደ ትግርኛ ባሉ ቁዋንቁዋዎች ውስጥ የሚገኙትን እንደ [ሕ፣ ኽ፣ ዕ፣ ኧ] ያሉትን የጉሮሮ ድምፆች ሊያጣ ችሎአል። ድምፆቹን ይጣ እንጅ፣ የነሱ መለያ የሆኑትን ፊደሎች በከፊል እንደያዘ ቀጥሎአል። በዚህም ምክንያት፣ እነዚህ ፊደሎች (ምልክቶች) በራሱ በእማርኛ ውስጥ የሚወከሉት ድምፅ ስለሌለ፣ ትርፍ ፊደሎች እየተባሉና የስርዓተ ፅሀፈቱም ችግር እየተባሉ ዘወትር ይጠቀሳሉ። ስርዓተ ፅሀፈቱ ግን በማንኛውም መስፈርት ቢለካ ከማንኛውም ስርዓተ ፅሀፈት ቢሻል እንጅ አይብስም፣ (ዝርዝሩን ከባየ (1984)፣ ከባየና እና ቲም (1989) ይመልከቱ)።

ቃላቱ ባብዛኛው ሴማዊ የሆነውን ያህል፣ ስዋሰዋዊ ስርዓቱ ኩሽ-እሞእዊ ሊሆን ችሎአል። በዚህም ምክንያት፣ የብዙዎቹ ቅጣይ ምዕላዶች ቅርፅና የህረግ እመቃቀር ስርዓት ከሌሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች ይልቅ፣ እንደ እሮምኛ ላሉ የኩሽና እንደ ወላይትኛ ላሉ የእሞ ቁዋንቁዋዎች ይቀርባል። ለዚህ አንደ <u>ቀበ-ኛ</u> እና <u>ጢኑ-ኛ</u> ያሉትን የኦሮምኛ ቃላትና በዚሁ አምሳያ /-ኧኛ/ የሚለውን ቅጣይ <u>ምዕላድ</u> እየጨመሩ የተፈጠሩትን እንደ ህይለኛ፣ ጥፋተኛ፣ ተንኮለኛ፣ ፈረሰኛ፣ ወዘተ፣ ያሉትን ቃላት መጠቃቀስ ይቻላል። ይህ እይነት የቃላት እመሰራረት በመሰረቱ የኩሽ አንጅ የሴም ቁዋንቁዋ ባህሪ አይደለም።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ አረፍተ ነገርን በባለቤት ጀምሮ በግስ መጨረስም የሴም ላይሆን፣ እንደ ኦሮምኛና እንደ ወላይትኛ ያሉ የኩሽና የእሞ ቁዋንቁዋዎች ባህሪ ነው። በድምፁ፣ በምዕላዱና በህረግ እመቃቀሩ ሴማዊነትን እየለቀቀ፣ ኩሽእሞእዊነትን እየያዘ የመጣ ቁዋንቁዋ ነው። ሴማዊነቱን ከእዝማቹ፣ ኩሽአሞአዊነቱን ደግሞ ከዘማቹ ሰራዊትና ከተዘመተበት የአገው

[6] <u>ዝኒ ከማሁ</u>

ህዝብ ይዘ የመጣ ትይጥ ቁዋንቁዋ ነው፣ ሲባል ይችላል። የሰራዊት ቁዋንቁዋ በመሆኑም ከሰራዊቱ ጋር መዝመት የጀመረው በዚያው ዘመን ነው፣ ለማለት ይቻላል።

በእክሱምም ሆነ በተከታዩ የዛጉዌ ዘመን የቤተ መንግስቱ ቁዋንቁዋ ግዕዝ ነበር። ይሁን እንጅ፣ በተለይ በዛጉዌ ዘመን ቤተ መንግስቱ እንደ ጥንቱ ግዕዝን ሲጠቀም፣ ሰራዊቱና ህዝቡ አማርኛን ከአገውኛ ጋር ሻሚያ፣ ግስትም ጎን ለጎን፣ ይጠቀም ነበር[7]። የሁዋላ ሁዋላ ግን አገዎች በመካከላቸው በነበረው የሰልጣን ሽኩቻ ሳቢያ፣ አማርኛ ከልሳነ ሰራዊትነት ወደ ልሳነ ንጉስነት ሲሸጋገር እንደቻለ ይነገራል። ይኸውም በንጉስ ላሊበላ ዘመን አካባቢ ሲሆን፣ ምክንያቱ ደግሞ አማርኛ ተናጋሪ የነበረውን ሰራዊት ድጋፍ ላለማጣት ሲባል እንደሆነ የሚገልፅ አፈ ታሪክ አለ።

ይህ ባንድ በኩል የሚሰጥ አስተያየት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቁዋንቁዋው በርግጥ ልሳነ ንጉስ የሆነው የዛጉዌ ዘመን አከትሞ፣ ሰልጣን ወደ ሸዋ ሲሻገርና የሰሎሞናዊያኑ ሰርወ መንግስት እንደገና በ1272 ሲጀመር እንደሆነ የሚጠቅሰ ፅሁፋዊ ማሰረጃ አለ። ይህም በዓፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት ነው[8]።

በላሊበላም ይሁን በይኩኖ አምላክ ዘመን ቁዋንቁዋው ልሳነ ንጉስ ይባል እንጅ፣ አንደ ግዕዝ ልሳነ ፅሁፍ አልነበረም። ለዚህ የበቃው በ14ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ የሚጠቅሱ ማሰረጃዎች አሉ። ለፅሁፍ የበቃውም የግዕዝን ፊደል በተጥታ በመውረሰና በማሻሻል ነው። ቀደም ሲል ለጠቀሰናቸው ከኩሽ ቁዋንቁዋዎች ላገኛቸው ድምፆች ምልክት የሆኑትንና፣ ዛሬ አንዳንድ ጊዜ አረቢ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዲቃላ እየተባሉ የሚጠሩትን እንደ [ሸ፣ ኀ፣ ቈ፣ ወዘተ፣] ያሉትን ፊደሎች ሲፈጥር፣ በግዕዝ የጉሮሮና የጥብቅ ድምፆች ምልክት የነበሩትን ፊደሎች በሙሉ ሊወስድ ችሎአል። እነዚህም ዛሬ ትርፍ ፊደል የሚባሉትና የሰርዓተ ፅሀፈታችንም ችግር እየተባሉ የሚጠቀሱት እንደ [ዕ፣ ፅ፣ ሕ፣ ኅ፣ ሥ] ያሉት ፊደሎች ናቸው። እነዚህን ፊደሎች አስወግዶና ሌሎችንም ማሻሻያዎች አድርጎ የፊደሉን ቁጥር መቀነሰና ሰርዓቱንም የበለጠ ቀላል ማድረግ ይቻል ነበር። ይሁን እንጅ፣ ፊደሉ ተራ የፅሀፈት ምልክት ወይም መሳሪያ ብቻ ሳይሆን፣ ታሪካዊና ባህላዊ አሌት ያለው ብሄራዊ ቅርሰ ስለሆነ፣ በዚህ በኩል ሊደረግ የሚታሰብ የማሻሻያ ርምጃ ሁሉ በተላሉ ተግባራዊ ላይሆን ይችላል። በተለይም ከጥንት ጀምሮ፣ ፊደሉን አስቆጥሮ፣ ቅኔውን ከነዜማው አስተምሮ፣ ህይማኖቱን፣ ፍልሰፍናውን፣ ዓለማዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ታሪካችንን መዝግቦ ያቆየችውና ቅርሰ ጠባቂ የሆነችው ቤተ ክህነት በዚህ በኩል የጠነከረ አቁዋም አላት።

---

[7] ዝኒ ክግሁ

[8] በዕምነት ገብረ እምላክ (1947)ን ይመልከቱ።

ልሳነ ንጉስ ብሉም ልሳነ ፅሁፍ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ፣ በትረ መንግሰቱ የትም ይሂድ የት፣ ዙፋኑ ሳይ ማንም ይቀመጥ ማን፣ ቁዋንቁዋው የህዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የመንግስትም ቁዋንቁዋ እንደሆነ ሊቀጥል ችሉአል። በዚህም ምክንያት መንግስት በዘመተበት ሁሉ ሊዘምት፣ ባለሲሶ መንግስት የነበረችው ቢተ ክህነትም በደረሰችበት ደብር ሁሉ ሊደርስና ፊደሉም ሊቆጠር ችሉአል። በሁዋላም ዘመናዊ ትምህርት ሲስፋፋ፣ መጀመሪያ የትምህርት፣ በሁዋላ ደግሞ በተወሰነ ደረጃ የግስተግሪያም ቁዋንቁዋ ሊሆንና፣ የበለጠ ስፋት ያለው ክልል ሊያዳርስና የተለያየ ቁዋንቁዋ የሚናገሩ ዜጎችን ሁሉ ሊያነጋግር ችሉአል። ባጭሩ ልሳነ ብዜር ለመሆን በቅቶአል።

በመልክዓ ምድራዊ ስርጭቱ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ በስነ-ልሳናዊ ትርፅና ይዘቱም ብዜራዊ ባህሪ ያለው ቁዋንቁዋ ነው። ሊግዊ ብቻ ሳይሆን፣ ከሊሉት የሲም ቁዋንቁዋዎች የበለጠ ኩሾአሞአዊ በመሆኑ፣ የሁሉንም የቁዋንቁዋ ዘርፎች ባህሪያት አካቶ ሊይዝ ችሉአል። ስለዚህ ነው፣ አማርኛ ከሌሉት ቁዋንቁዋዎች የበለጠ ብዜራዊ ባህሪ ያለው ቁዋንቁዋ ነው የምንለው። በመሆኑም በእኔ ግምት በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ለማሳየት የምሞክረው ባህሪ የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የብዙዎቹ የኩሽና የኦሞ ቁዋንቁዋችም ጭምር ነው። ከዝርዝር ጉዳዮች በመለስ፣ የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ቁዋንቁዋዎች ሰዋስው ሊባል የሚችል መፅሀፍ ይመስለኛል። ይህን በሚመለከትም ሪቻርድ ሄይምርድ የተባሉ የኢትዮጵያ ቁዋንቁዋዎች ሊቅ እንዲህ ያሳሉ፡

> ...I have for some time been engaged in compiling a Gamo-English-Amharic dictionary. Time and again, I have been impressed hy *the general lack of difficulty in finding exact relation equivalents in Amharic for Gamo lexemes;* this facility has certainly not been in evidence in trying to find appropriate English glosses. Earlier, when working with Enid Parker on Qafar lexicography, I have received the same overall impression of how much simpler it would have been to find Amharic equivalents than English ones. (1991:143)

ይህ አንግዲህ አማርኛ አንደ ጋሞኛ እና አንደ አፋርኛ ካሉ ቁዋንቁዋዎች ጋር በፅንሰ ሀሳብ አገላለፅ ደረጃ ምን ያህል ተመሳሳይ አንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን፣ በሰዋስው ደረጃ ደግሞ አንደ ኦሮምኛ ካሉ የኩሽ ቁዋንቁዋዎች ጋር ያለውን ተመሳሳይነት አስመልክተው ሁለት የስነ-ልሳን ተሰጥዎ የነበራቸው አንግሊዛዊያን ከዛሬ ሰማኒያ ዓመት በፊት በፃፉት የኦሮሞ ሰዋስው መፅሀፍ ውስጥ አንዲህ ይላሉ።

> Considering that this grammar could be *translated almost literally into Amharic,* it is not surprising that they talk it well. The constant intercourse between Semitic and Hamitic elements in Abyssinia is naturally reflected in the Amharic and Oromifa languages and a comparative study of the two would be most profitable, though it is beyond the scope of this book. At the same time knowledge of Amharic is of the greatest use in learning Oromo, and in enabling one to grasp the delicacy of its verbal formation and other idioms. (Hodson, A.A., and Walker, C.H. 1922:8)

አሁን በቅርቡም፣ በኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች ላይ ከፍተኛ ምርምር የሚያካሂዱት ፕሮፌሰር አልጋ ካፒልዩክ፣ የቋንቋዎቹን ተመሳሳይነት አለመልክተው የሚከተለውን ፅፈዋል፡፡

> Whereas the vocabulary and the phonological and morphological features of the modern languages vary considerably, their syntax is almost identical, and this is in addition to the similarity in word order. A text in Tigrinya can be translated correctly into Amharic or Gurage, and vice versa, by changing only the lexemes and maintaining the same constructions and idiomatic expressions. (Kapeliuk, 1989:6)

ይህ አባባል ምን ያህል ውነት እንደሆነ፣ ፍርዱን ይህን መፅሀፍ ከራሳቸው ቋንቋዎ ጋር እያገናዘቡ ለሚያነቡ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ እተዋለሁ፡፡ በእኔ እምነት ግን ኢትዮጵያዊያንን ከሊሎች የቅርብም ሆነ የሩቅ ህዝቦች ለይቶ አንድ የሚያደርጋቸው ለነ-ልሳናዊ ብቻ ላይሆን፣ ባህላዊና የእሱ ነፀብራቅ የሆነው <u>*ለነ-ልቦናዊ*</u> ባህሪም ጭምር ይመስለኛል፡፡ ተረቶቻችን፣ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮቻችን፣ አንቆቅልሹና እንኳ-ሰላንትያው ሁሉ የቅርፅ አንጅ የይዘት ልዩነት ያለው አይመስልም፡፡ የጠሣና የቀበሮ ብልጥነት፣ የጅብ ሆዳምነትና የአንበሳ አስፈሪነት ባንድ ብዜረሰብ ተረት ውስጥ ብቻ የሚታይ ክስተት ነው ለማለት የሚቻል አይመስልም፡፡ ርግጥ፣ ነገሩ ሰፋ ያለ ንፅፅራዊ የለነ-ቃልና የባህል ጥናት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

መግቢያ

በመቅድሙ ላይ ለማሳየት እንደሞከርነው፣ እግርኛ ብሄራዊ ቅርፅና ይዘት ያለው ቁዋንቁዋ ነው። ክልላዊ ስፋቱና ማህበራዊ መሰረቱ ጠንካራ ነው። ለነ-ፅሁፋዊ ሀብቱም ቢሆን ተመሳሳይ ባህሪ የሚታይበት ነው። የአንድን ብሄረሰብ ታሪክና ለነ-ፅሁፍ ብቻ የሚያደስ ላይሆን፣ የመላውን ህዝብ ህይወት ለመዳሰስ የሚሞክር ነው[1]። ከእነዚህ ሁኔታዎች ስንነሳ፣ ቁዋንቁዋው የጋራ እንጅ የእንድ ብሄረሰብ ግላዊ መሳሪያና መለያ ነው ለማለት ያስቸግራል። ውልደቱና እስተዳደጉም የሚያመለክተው ይህንኑ ሀቅ ነው። በህዝቦች እንጅ ባንድ ህዝብ ብቻ የተፈጠረ የእንድ ህዝብ ልሳንና የግል መለያ እይደለም።

ይህን የጋራ መሳሪያ ደግሞ በስርዓቱ ግወቅ ብሄራዊ ጠቀሜታውን የበለጠ ቀና ያደርገዋል። ስለዚህም ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ በየትምህርት ቤቱ በትምህርትነት ሲሰጥና ወደ ሁዋላም ለእንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቶአል። ዛሬም ቢሆን ከሞላ ጎደል በዚሁ ደረጃ እንደቀጠለ ነው። ትምህርቱ እንዳንድ ጊዜ በስርዓት፣ ግለትም በሰዋሰው፣ እንዳንድ ጊዜ ደግሞ በክህሎት፣ ግለትም ባጠቃቀም ችሎታ ላይ ሲያተኩር ኖሮአል። ዓላማው በግልፅ ምን እንደነበርና ምን ያህልም እንደተሳካ በርግጥ ለመናገር ያስቸግራል። የግያስቸግር ነገር ቢኖር፣ አብዛኛው ህዝብ በትምህርት ቤት ውስጥም ይሁን ከዚያ ውጭ፣ ከቁዋንቁዋው ጋር ስለሚተዋወቅና በእሱም ቢያንስ በአደባባይ እዘውትሮ ስለሚጠቀም፣ በንግግር ደረጃ <u>ልሳነ ክልዔ</u> ሊሆን መቻሉ ነው።

አብዛኛው ህዝብ የራሱን ቁዋንቁዋ፣ ያጎራባቹን ህዝብ ቁዋንቁዋና እግርኛን ስለሚናገር <u>ልሳነ ሳልስ</u> ነው። እንደ ስሜን ግእ ያሉ ንዑሳን ብሄረሰቦች ለዚህ ምሳሌ ናቸው። ከግእኛ ሌላ እሮምኛንና እግርኛን ስለሚናገሩ ልሳነ ሳልስ ናቸው። ኦሮሞዎቹ ደግሞ እሮምኛንና እግርኛን ስለሚናገሩ ልሳነ ክልዔ ናቸው። የፅቆጣ እገዎችም እንደዚሁ የራሳቸውን ቁዋንቁዋ ሀምጣንጋን፣ የጎረቤታቸውን ቁዋንቁዋ ትግርኛን፣ ከዚያም አልፈው እግርኛን ይናገራሉ። ትግራዮች ደግሞ የራሳቸውን ቁዋንቁዋና እግርኛን ስለሚናገሩ ልሳነ ክልዔ ናቸው። በዚህ አያያዝ <u>ልሳነ ምህደ</u> የሆነው እግራው ብቻ ነው። እሱም ቢሆን ወደ ደቡብ ያለው ኦሮምኛን፣ ወደ ሰሜን ያለው ደግሞ ትግርኛን ስለሚናገር በመጠኑም ቢሆን ልሳነ ክልዔ ነው። ሁኔታው ሀገሪቱ ቢያንስ ልሳነ ክልዔ እንደሆነች ያሳያል። ለዚህም ምክንያቱ የእግርኛው ብሄራዊነት ነው፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ቁዋንቁዋው ያልደረሰበት ክልል የለም። ርግጥ፣ የልሳነ ክልዔነቱ ደረጃ ከመሀል እስከ ዳር እኩል አይደለም። ከመሀል በራቅን ቁጥር መጠኑ እያነሰ ይሄዳል። የምናገኘው ተናጋሪ ችሎታም እንደዚሁ።

---

[1] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ባየ (1984)ን ይመልከቱ።

ቀደም ባለው ዘመን ይሰጥ የነበረው ትምህርት የሰዋሰው፣ የድርሰትና የንባብ ነበር። እንዲህ ወደ ሁዋላ ግን አትኩሮቱ በከሀሎት ላይ አየሆነ ሰለመጣ፣ የሰዋሰው ድርሻ ሊመናመን ችሎአል። በዚህም ምክንያት በታላላቆቹ የትምህርት ተቋማት ሳይቀር፣ ዛሬ ባለቤትንና አንቀፅን የሚለይ ተማሪ ለማግኘት እያስቸገረ ነው። ርግጥ ነው፣ ከሀሎት እንዱና ምናልባትም ዋነኛው የቋንቋችን አጠቃቀም ትምህርት ዘርፍ ነው ሊባል ይችላል። ይሁን እንጅ፣ በዚህም በኩል ቢሆን ተማሪዎቻችን የሚደርሱበት ደረጃ ከፍተኛ ነው ለማለት በፍፁም አያስደፍርም። ሁለተኛ ደረጃን የጨረሰ ተማሪ፣ ዛሬ ጥሩ የሰራ ግመልክቻ ቀርቶ፣ ተራ ደብዳቤ እንኩዋ በወጉ ለመፃፍ እየተሳነው መጥቶአል። ከሁለት ያጣ ጎመን አየሆነ ነው፤ ከስርዓቱም ሆነ ከከሀሎቱ የለበትም።

በማንኛውም የሰነ ልሳን ባለሙያ እምነት ከማንኛውም የከሀሎት ትምህርት በሰተጀርባ ማንኛውም የቋንቋዋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅና ረቂቅ የሆነ ዕውቀት አለ። ይኸውም ከፍ ሲል የተጠቀሰውና የቋንቋዋው ስርዓት ወይም ሰዋሰው በመባል የሚታወቀው ክፍል ነው። ይህ ትምህርት የአንድን ቋንቋዋ ሰርዓት ከድምፅ አሰካክ አሰከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው። ይዙቱ የሰርዓት ነው። ሰለዚህም ከአጠቃቀም ይለያል። ዋነኛ ዓላማው በቀጥታ የመፃፍ፣ የማንበብ፣ የመናገርና የመረዳት ችሎታን ማዳበር ሳይሆን፣ በሚነበበውም ሆነ በሚነገረው ቃል፣ ሀረግ፣ አረፍተ ነገርና ድርሰት ጀርባ የሚገኘውን ረቂቅ ስርዓት ደረጃ በደረጃ ለተማሪው ማሳየት ነው። ይህን በማድረግ ተማሪውን በከሀሎት ትምህርት ውስጥ ትክክል ወይም ስህተት፣ መደበኛ ወይም <u>ኢመደበኛ</u> እየተባለ የሚነገረውን አባባል፣ ለምን ትክክል ወይም ስህተት፣ ለምን መደበኛ ወይም ኢመደበኛ እንደሆነ ከሰርዓቱ አንፃር እንዲገነዘብ ማስቻል ነው። በትክክል መጠቀምን ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛነትን ራሱን መግለፅና በዚያ ችሎታም መሰረት ትክክለኛ የሚባለውን አጠቃቀም መረዳትና መተግበር ነው።

ትምህርት የቀመሰ ቀርቶ፣ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ቢሆን የአንድን አረፍተ ነገር ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት የማወቅ ችሎታ አለው። ለምሳሌ አንዱን ፊደል ያልቆጠረ መንዜ ጠርተን፣

አኔ ራሴን አዋረደው፤

ብንልስትና፣ አባባሉ ትክክለኛ አግርኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ብንጠይቀው፣ ያለምንም ማወላወል አባባሉ ትክክለኛ አንዳልሆነ ይነግረናል። ከዚያም አልፎ፣

አኔ ራሴን አዋረድኩት፤

ነው የሚባለው ብሎ፣ ትክክለኛውን እባባል ሊነግረን ይችላል። ይኸኛው እባባል ለምን ትክክል እንደሆነ፣ ላይኛው ለምን ትክክል እንዳልሆነ ብንጠይቀው ግን፣ "እይባልማ!" ከማለት በስተቀር ምክንያቱን ሊነግረን ከቶ አይችልም። "እይባልማ!" ከማለት አልፎ ለምን እንደሚባል ወይም እንደማይባል ሊነግረን የሚችለው፣ የቁጥጥሮውን ስርዓት በወጉ ሊገነዘብ ብቻ ነው። ቁጥጥሮን መናገር መቻልና የሚናገሩትን ቁጥጥሮ ስርዓት ስውል መገንዘብ የተለያዩ ችሎታዎች ናቸው። መናገር መቻል ባመዛኙ ማህበራዊ ሲሆን፣ ስርዓትን መገንዘብ ግን ሰነ-ልሳናዊ ነው። ይህም ሰዋስው የምንለውን ትምህርት ያካትታል።

እንግዲህ እንዱ የሰዋስው ትምህርት ዓላማ የአንድን ቁጥጥሮ ስርዓት ግለፃትና የንግግርም ሆነ የፅሁፍ ከሀሎት ከዚሁ ስርዓት ጋር ምን እይነት ቁርኝት እንዳለው ግለፃት ነው። የትክክለኛ እጠታተም፣ ግለትም የከሀሎት መለኪያ <u>በመሰረቱ</u> ስርዓት ነው። ከዚህ ካለፈ፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ ማህበራዊ ብሎም ባህላዊ ነው። በዚህም ምክንያት አንዳ ማህበረሰቡ መዋትር፣ አካባቢና ባህል፣ እጠታቀሙም ሊለያይ ይችላል። በአንዱ አካባቢ ትክክለኛ የሚባለው፣ በሌላ አካባቢ እንዳ ስህተት ሊታይ ወይም እንዳ ነውር ሊቆጠር ይችላል። ፍርዱ አንደየአስተግሪው <u>ዳራ</u> እና የግል ችሎታ ይለያያል፤ በተስይ የቁጥጥሮው የመደበኛነት ደረጃ ዝቅተኛ ከሆነ። በየብሄረሰቡ ቁጥጥሮ በሚሰጠው ትምህርት ላይ የሚታየው ችግር በከፊል ከዚህ የመነጨ ነው። በከፊል ደግሞ የስርዓቱን ትምህርት የሚያስተምር የሰለጠነ መምህር፣ በወጉ የተሰናዳ ሰዋስውና የንባብ መዛፍት አለመኖር ነው። እንደነዚህ ያሉትን ችግሮች በወጉ እየተረዱና አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ ተግሪውን ጥሩ የቁጥጥሮ ተጠቃሚና በመጠኑም ቢሆን <u>አሰላላይ</u> እና ተመራማሪ እንዲሆን ማስቻል እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሌላው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ደግሞ ከዘመናችን አቢይ የሰነ-ልሳን ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው። ይኸውም የሰው ልጅ የእፍ መፍቻ ቁጥጥሮውን የሚያውቀው እንዲት ነው? የሚል ሲሆን፣ መሰረቱም ግንኛውም ጤነኛ ህፃን፣ ዙሩ ምንም ይሁን ምን፣ ትውልዱ የትም ይሁን የት፣ ግንም ስው ስራየ ብሎ ላያስተምረው የተወለደበትን ህብረተሰብ ቁጥጥሮ ከአምስት እስከ ስድስት አመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በሚገባ ሊያውቅ መቻሉ ነው። ምይና ውስጥ የተወለደ አማራና እዲስ አበባ ውስጥ የተወለደ ምይናዊ ህፃን የየተወለዱበትን ህብረተሰብ ቁጥጥሮ ለማወቅ የሚወስድባቸው ጊዜ ባማካይ እኩል ነው። በሁለቱ መካከል በአዕምር የመብሰል ልዩነት ምናልባት ቢኖርም እንኩዋ፣ በዚህ ምክንያት ቁጥጥሮን በማወቅ ረገድ ምንም ልዩነት እይታይም። ሞኙም ሆነ ብልሁ እኩል ያውቁታል፣ እኩልም ህሳቤውን ይገልፁበታል። በሁለቱ መካከል የሚኖረው ልዩነት በሚገልፁት ህሳብ ክብደትና ቅለት ላይ ነው። ይህም ከአዕምር ብስለት ልዩነት የመጣ ሊሆን ይችላል። የቁጥጥሮ ዕውቀታቸውንና እስተዋፅዖቸውን በተመለከተ ግን ልዩነት የለም። ሌላው ተርቶ ቁጥጥሮውን

የሚያውቁበት ሂደት፣ ደረጃና ጊዜ ተመሳሳይ ነው። በምን ጀምረው በምን እንደሚፈርሱና መቸ ጀምረው መቸ እንደሚጨርሱም ከሞላ ጎደል ሊታወቅ ተችሉአል። ለምሳሌ፣ በድምፅ ደረጃ ያለውን ሂደት ብንመለከት፣ አንድ ህፃን "አ፣ ጥ፣ ፅ፣ ቅ" ማለት የሚችለው "ፐ፣ ት፣ ስ፣ ክ" ማለት ከቻለ በሁዋላ ነው። ታዲያ፣ ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ይህ እንዲት ሊሆን ቻለ? የሚል ነው።

ይህን በተመለከተ ሁለት <u>መላምታዊ</u> መልሶች ሊሰነዘሩ ቆይተዋል። አንደኛው የህፃናት አንጎል እንደ ንፁህ ወረቀት ከምንም ነገር የፀዳ በመሆኑ፣ ማንኛውም ጤነኛ ህፃን የሚነገረውን ነገር ሁሉ ቶሎ የመቀበል ችሎታ አለው። ከሀፍረትም ሆነ ከይሉኝታ ነፃ ስለሆነ፣ የሚሰማውን ነገር ሁሉ እያስመሰለ የመድገም እድሉ የሰፋ በመሆኑ፣ ቁዋንቁዋውን በቀላሉ ለመልመድ ያስችለዋል፤ የሚል ነው። ይህ መላምት አለማመዱን በአመዛኙ ማህበራዊ ያደርገዋል። ይህም ህፃኑ፣ የተወለደበት ማህበረሰብ የሚናገረውን ብቻ እየሰማ አስመስሎ በመድገም ቁዋንቁዋን ይለምዳል የሚል ነው። ለጋ አዕምሮውም ይህን ለማድረግ ዝግጁ ለለሆነ ልምዱን ፈጣን ያደርገዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የመጀመሪያ ቁዋንቁዋ ዕውቀት ከላይ እንደተገለፀው ማህበራዊ ብቻ ሳይሆን አዕምሮአዊም ነው፤ የሚል ነው። ማህበራዊ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ዕውቀቱ ከማህበረሰቡ በሚገኘው <u>ግብዓት</u> ብቻ ይወሰን ነበር። የህፃናትን ንግግር ስናይ ግን ህብረተሰቡን በመስማት ከሚያገኙት ያለፈ ነው። ለምሳሌ፣ የእኔ መንታ ልጆች ርስበርሳቸው ሲነጋገሩም ሆነ ከኔ ጋር ሲያወሩ፣ "መብራቱ ጥፍት ነው፣ ብርቱካን ነብሮአል፣ አንዲት ልጄት፣ ከእንደገና[2]፣ አልቀጭጥም ለማለትም አልቀጭም፣ ወዙተ፣ ወዙተ" ይሉ ነበር። በሌተሰብም ሆነ በህፃናተሰብ ደረጃ እንደነዚህ ያሉ አባባሎች አይሰሙም። ልጆቹ ታዲያ ከየት ሰሙዋቸውና ሊጠቀሙባቸው ቻሉ?

ሁለተኛም ቁዋንቁዋ የሚሰሙትን ነገር በመደጋገም ብቻ የሚታወቅ ቢሆን ኖሮ፣ ብዙ እየተናገሩ ብዙ ጊዜ በማስደገም የግወቂያ ጊዜውን ማሳጠር ይቻል ነበር። ብልህ ህፃናትም በአጭር ጊዜ አውቀው በጨረሱ ነበር። ህፃናት ግን ምንም ያህል ቢነገራቸውና እየደጋገሙ እንዲሰሙ ቢደረጉ፣ የግወቂያ ጊዜውን ማሳጠር አይችሉም። እንዲያውም አንዳንዱን አንዲደግሙት የሚነገራቸውን ነገር በትክክል አንዳልደገሙት ሲረዱ፣ ከናካቴው ያኮርፉና ንግግር ያቆማሉ። ይህ የሚያመለክተው የሚነገራቸውን ሁሉ በትክክል ለመድገም የሚችሉት ወላጅ በሚፈልገው ፍጥነትና መጠን ሳይሆን፣ አካላዊና አዕምሮአዊ በሆነ የብቃት ደረጃ ልክ ነው። የብቃት ደረጃቸው ያልደረሰበትን ነገር በሉ ቢሉዋቸው አይሉም።

---

[2] በነገራችን ላይ፣ <u>ከእንደገና</u> ማለት መደበኛ አማርኛ አየሆነ ነው። ብዙ የአዲስ አበባ ወጣቶች ሲጠቀሙበት ይሰማል። እንደነዚህ ያሉ አባባሎች የቁዋንቁዋ <u>ልውጠት</u> ምልክት ናቸው።

ለምሳሌ [ፐ] ማለት የማይችል ልጅ፣ [ጵ] ለማለት አይችልም። [ጵ] ማለት የሚችል ልጅ ግን [ፐ] ማለት ይችላል። እንደነዚህ ያሉ ድምፆች የሚገኙባቸውን ቃላት ትርጉም የማወቅ ሂደትም እንደዚሁ ቃላትን በመደጋገም ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ አጠቃላይ የአዕምሮንና የአንደበት አካላትን ድምፅ የመፍጠር ብቃት ይጠይቃል።

ሌላው ከዚሁ ጋር አየተያያዘ የሚነሳው ጉዳይ ህፃናት ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች እንዲሁም ከአጠቃላዩ ማህበረሰብ የሚሰሙት የቁዋንቁዋ አይነት ነው። ቁዋንቁዋው የፅሁፍ ሳይሆን የንግግር ነው። የንግግር ቁዋንቁዋ ደግሞ ዝብርቅርቃም ነው። በፅሁፍ እንደሚቀርበው የተሰተካከለ አረፍተ ነገር ሳይሆን፤ በተለያየ ምክንያት በሚፈጠሩ ሰህተቶች የተሞላና የተቆራረጠ ነው። አቀራረቡም ለህፃናት እንደሚሆን አየተደረገ ሳይሆን፤ ተናጋሪው እንደሚፈልገው እየሆነ ነው። በዚህ አይነትና ሁኔታ የሚሰሙትን ቁዋንቁዋ ነው፤ ህፃናት በአምስትና በስድስት እመት ጊዜ ውስጥ የሚለምዱት። አነዚህን ሁኔታዎች ይዘን ሰንነሳ፤ ቁዋንቁዋ የሚለመደው የሚሰሙትን በመደጋገም ነው የሚለው አካሄድ ትክክል አይመስልም።

ይህ ካልሆነ፤ ሊሆን የሚችለው ማንኛውም ሰው በተፈጠሮው ቁዋንቁዋን ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያውቅ የሚያስችለው አዕምሮአዊ ችሎታ አለው፤ ብሎ መነሳት ነው። ይህ ችሎታ በማንኛውም ጤነኛ ሰው አንጎል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ ተግባሩም ቁዋንቁዋን በአጭር ጊዜ ማሳወቅ ብቻ ነው። ችሎታው የሚገኝበት ያንጎል ክፍል ጉዳት ሲደርስበት ቁዋንቁዋን ማወቅ አይቻልም፤ ያወቁት ቁዋንቁዋም እንደ ጉዳቱ ደረጃ በሙሉ ወይም በከፊል ሊጠፋ እስበሰዚያም ሊቃወስ ይችላል። ማዳመጥ አየቻሉ፤ መናገር ያቅታል። መናገር እየቻሉ፤ የሚናገሩትን ነገር ትርጉም ማዘበራረቅ ይከሰታል። እንደነዚህ ያሉ ሁኔታዎች ቁዋንቁዋ ውስጥም አዕምሮአዊ እንደሆነ በቂ ምልከት ናቸው።

የዚህ አዕምሮአዊ ችሎታ ቅርፅና ይዘት ምን እንደሆነና አሰራሩም እንዴት እንደሆነ ለማወቅ የሚደረገው ጥናት መነሻ የተለያዩ ቁዋንቁዋዎች ሰርዓት ወይም ሰዋሰው የምንለው ነው። ይህን ሰርዓት በማየትና ሁለንተናዊ የሆኑ ባህሪያትን እያነጠሩ በማውጣት በየቁዋንቁዋውም እንዴት እንደሚከሰቱ በመገንዘብ ወደ ጥያቄው መልሰ መረማመጃ የሚሆኑ ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል የሚል እምነት አለ። የሰዋሰው ትምህርት የምንለውም ይኸው የእያንዳንዱ ቁዋንቁዋ ሰርዓት ነው። ከዚህ አኩዋያ ሲታሰብ፣ የሰዋሰው ትምህርት ሁለት ፈርጅ እንዳለው መረዳት ይቻላል። እንደኛው ከሰው አዕምሮአዊ ባህሪ ማሰትም <u>ከተበበ ነገር</u> ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ሌላው ፈርጅ ደግሞ <u>ከነቢበ ነገር</u> ጋር የተገናዘበ ነው። የመጀመሪያው ከማሰብና ከማወቅ፣ ሁለተኛው ያሰቡትንና ያወቁትን ነገር ከመተንፈሰ ማለትም ከመናገር ጋር የተያያዘ ሰብዓዊ ባህሪ ነው። ይህም ባብዛኛው ግህበራዊ ነው። ያሰቡትን ለመናገር እድማው መኖር አለበት። በአካል ወይም በሙናብ።

በዚህ ረገድ በመቅድሙ ላይ እንደተገለፀው፣ ቁዋንቁዋ ማህበራዊ አገልግሎትና መሰረት ያሰውን ያህል፣ አዕምሮአዊ ተፈጥሮም አንዳሰው ለመረዳት ይቻላል። ማህበራዊ አገልግሎቱን ከማህበራዊ ተራክቦና ከመደበኛ የክህሎት ትምህርት ማግኘት ይቻላል። ማንኛውም ወላጅ "ባሰጌ! እንደዚህ አይባልም፣ ነውር ነው!" አያሰ ልጁን ሲቆጣና ሰርዓት እንዲይዝ ሲያደርግ፣ የሚያሰተምረው ማህበራዊነትን ብቻ ሳይሆን፣ የዚሁ መግለጫ የሆነውን የቁዋንቁዋውን መደበኛ አጠቃቀም ጭምር ነው። በትምህርት ቤት የሚሰጠውና መደበኛ የቁዋንቁዋ ትምህርት የሚባለውም በመሰረቱ የዚሁ ተክታይ ነው። ልዩነቱ የአደረጃጀት፣ የአቀራረብና የምዘና ነው።

በዚህ አይነት ባጠቃቀም፣ ማለትም በክህሎት ትምህርት አማካኝነት የቁዋንቁዋን አዕምሮአዊነት በውል ማሳየት አይቻልም። ይህን ማድረግ የሚቻሰው፣ በትምህርትነት የሚሰጥን ቁዋንቁዋ ሰርዓት ራሱን በቻሰ መርህ ግብር፣ በራሱ ዘዴና ዓላማ መሰረት በወጉ በሰለጠነ መምህር በማስተማር ነው። ይህ የሰርዓት ትምህርት ለክህሎቱ ትምህርት አጋር ሊሆንም፣ ላይሆንም ይችላል። ይህን የሚወሰነው ክህሎቱን የሚያሰተምረው ባሰሙያ ነው። ለዚያውም ከሰ<u>ነ-ዘዴ</u> ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከሰነ-አዕምሮና ከሰነ-ልሳን ጋር ትውውቅ ያሰው ከሆነ ነው።

ባጠቃላይ ግን የቁዋንቁዋን ትምህርት በሚመለከት አንድ ነገር ያሰጥርጥር መናገር ይቻላል። ይኸውም የአንድን ቁዋንቁዋ አጠቃቀም ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ፣ አጠቃቀሙን፣ ማለትም ክህሎቱን ከነሰርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ ክህሎትና ሰነ-ልሳናዊ ዕውቀት ያሰው መሆኑ ነው። ይህ ዕውቀትም ከቁዋንቁዋው አልፎ፣ ከቁዋንቁዋው ጋር ተያያዥነት ካላቸው እንደ ሳይኮሎጅ፣ ሶሲዮሎጅና ፍልሰፍና ካሉ የትምህርት ዘርፎች ጋር ተማሪው በቀላሉ እንዲተዋወቅ ይረዳዋል። ቁዋንቁዋ አዕምሮአዊ እንደሆነ ሁሉ ማህበራዊ ብሎም ባህላዊ ነውና። በዚህ መልኩ ቁዋንቁዋ ባህልም የባህል መግለጫም ነው።

የቁዋንቁዋውን አጠቃቀም ከነሰርዓቱ የሚያውቅ ሰው መኪና አነዳድንና የመኪና አካላትን አሰራር እንደሚያውቅ መካኒክ ሾፌር የሚቆጠር ነው። እንዲህ አይነቱ ሾፌር ደግሞ የትራፊክን ህግ ጠብቆ እንዲያሽከረክር ከሰለጠነ ሾፌር የበለጠ የመኪና ሰርዓትና ያነዳድ፣ ማለትም ያጠቃቀም ችሎታ ይኖረዋል። ስለዚህም ከተራ አሽከርካሪ ጋር አይመደብም። ሊመደብም አይገባም።

ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፣ ማንኛውም የቁዋንቁዋ ተማሪ የተሙዋላ የቁዋንቁዋ ዕውቀት ሊያገኝ የሚችለው፣ ክህሎቱን ብቻ ሳይሆን ሰርዓቱን፣ ማለትም የቁዋንቁዋውን ሳይንስ ጭምር ሲገነዘብ መሆኑን ነው። ክህሎቱን ብቻ ያገኘ ተማሪ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ተራ አሽከርካሪ ብዙም አይሰይም። ሁለቱም አጠቃቀሙን እንጅ ሰርዓቱን መግለፅ አይችሉምና። ሰርዓቱን ብቻ የተካነ ተማሪም ያጠቃቀም ድህ ከመሆን አያመልጥም። ሳይንሱን ከማነብነብ አልፎ፣

ጥሩ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። ሁለቱን ትምህርቶች አጣጥሞ የያዘ ተማሪ ብቻ ነው፣ ከፍ ሲል እንደጠቀስነው ባለሙያ ሾፌር የሚቆጠረው። ስርዓቱን ከነአጠቃቀሙ ይዞአልና።

የቁዋንቁዋ ትምህርት ሲባል ስርዓት ብቻ የሚመስላቸው እንዳሉ ሁሉ፣ ከሀሎት ሲባልም ከማንበብ፣ ከመፃፍ፣ ከመናገርና ከመረዳት የማይዘል የሚመስላቸው እይጠፉም። ይህ <u>ድንገሬ</u> የሚከሰተው ከሀሎትን፣ ማለትም አጠቃቀምንና ስርዓትን ለያይቶ ከማየት ነው። ሁለቱ የተዛመዱ ግን ደግሞ የተለያየ ዓላማና ዘዴ ያላቸው የቁዋንቁዋ ዘርፎች ናቸው። ዝምድናቸው ሁለቱም በቁዋንቁዋ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ሲሆን፣ ልዩነታቸው ደግሞ እንደኛው የስርዓት፣ ሌላው ያጠቃቀም ዘርፍ መሆኑ ነው። አጠቃቀሙ በአብዛኛው ማህበራዊና ባህላዊ ሲሆን፣ ስርዓቱ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ አዕምሮአዊና ማህበራዊ ነው።

ይህን አንድነትና ልዩነት በመረዳት አንዳግባቡና አንዳስፈላጊነቱ ሁለቱንም ዘርፎች ባንድ ላይ አካቶና አጣጥሞ፣ እስያም ለያይቶ ማስተማር ይቻላል። በመሰረቱ ግን ስርዓት ስነ-ልሳናዊ ሲሆን፣ አጠቃቀም ግን ከፍ ሲል እንደተገለፀው ማህበራዊ ነው። የመጀመሪያው የቁዋንቁዋ ግንዛቤን፣ ሁለተኛው ያጠቃቀም ችሎታን የሚያዳብር ትምህርት ነው። የአጠቃቀሙ ችሎታ ግን የስርዓቱ ነፀብራቅ ነው። ስለዚህ የስርዓቱ ግንዛቤ ለአጠቃቀሙ ከሀሎት ወሳኝ ነው ባይባልም፣ እጅግ እስፈላጊ ነው።

በመሰረቱ የቁዋንቁዋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ድርሰት ሲያርሙ ዋናው ትኩረታቸው በአረፍተ ነገሮቹ ትክክል መሆን ወይም አለመሆን ላይ ነው። የሀሳብ ጥንካሬ፣ ቅደም-ተከተላዊ አቀነጃጀት፣ የቃላት አመራረጥ፣ ግልፅት፣ ወዘተ፣ የአረፍተ ነገሩን ስርዓት ያህል አይተኮርባቸውም ለማለት ይቻላል። በእረፍተ ነገሩ ላይ የሚደረገው ትኩረትም ያልሰጡትን አንደመሻት የሚቆጠር ነው። ትክክለኛ የሀረግ አወቃቀር ስርዓትን ላያስተምሩ፣ አረፍተ ነገርህ በትክክል አልተዋቀረም ብሎ አስተያየት መስጠትና ደብተርን ቀይ ስቀይ ማድረግ ተገቢ አይሆንም። ሀሳቡን አስከገለፀ ድረስ የአረፍተ ነገሩ ትክክለኛ አለመሆን አያስጨንቀንም ማለትም፣ ተማሪውን ለስራ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ አንዳይቀርብ የሚያደርግ አደገኛ አመለካከት ነው። በየጊዜው የሚሰማው የቀጣሪዎች አሮሮ የሚያመለክተው በየደረጃው እየተመረቁ የሚወጡት ተማሪዎች ተራ ዘገባ (ሪፖርት) ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት አንደሌላቸው ነው። ባጭሩ ሀሳብን አስተካክሎ በተስተካከለ አረፍተ ነገር የመግለፅ ብቃት የላቸውም። ይህ አየታወቀ፣ ለዚህ የሚረዳውን ትምህርት ችላ ማለት ተገቢ አይመስለንም። ትክክልም አይደለም። ትክክል የሚሆነው ከስነ-ልሳኑና ከስነ-ዘዴው ሳይንስ ጋር አብሮ እየተራመዱም ባይሆን፣ ከስር ከሰሩ እየተከተሉ የከሀሎቱንም ሆነ የስርዓቱን ትምህርት ማነልበት ነው።

ሰርዓቱንም ሆነ አጠቃቀሙን በወጉ ለማሰተማር ደግሞ ከሞላ ጎደልም ቢሆን የተጠናቀረ የማስተማሪያና የማገናዘቢያ መፅሀፍ ያስፈልጋል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አማርኛ በትምህርትነት መሰጠት የጀመረው ገና ዱሮ ነው። በዚያን ዘመን፣ ችግሩ የተሰማቸው እንደ ብላታ መርሰዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስና አንደ ተክለማሪያም ፋንታዬ ያሉ ሊቃውንት ካዘጋጁዋቸው ሁሰት መፃህፍት ሌላ፣ ዛሬ ምንም ነገር የለም ለማለት ይቻላል። እነዚህም ቢሆኑ በይዘታቸውም ሆነ ባመሰካከታቸው ለዛሬው ዘመን ትምህርት በቂ አይደሉም። ብዙ ይጎድላቸዋል። ርግጥ፣ ይህ የአሁኑ መፅሀፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወጣ በሁዋላ፣ የዚህኑ ፈለግ የተከተሰ አንዳንድ የሰዋሰው መፃህፍት ወጥተዋል። በጣም ጥሩ ዕድገት ይመስሰኛል። ስሊሎች ቁዋንቁዋዎችም መልካም አርአያ ስለሆነ ሊበረታታ ይገባዋል። በየትምህርት ቤቱ በትምህርትነት እየተሰጡ ያሉት የሀገራችን ቁዋንቁዋዎች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሰራ ይጠይቃሰ። የየቁዋንቁዋው መምህራንም ከዚህ መፅሀፍ ብዙ ይጠቀማሰ የሚል አምነት አሰኝ።

የሰርዓቱ ትምህርት ካንደኛና ከሁሰተኛ ደረጃ አልፎ በየኮሌጁ መሰጠት ከጀመረ በርካታ እመታትን ቢያሰቆጥርም፣ በዚሁ ቁዋንቁዋ ተዘጋጅቶ የቀረበ መደበኛ ማስተማሪያም ይሁን መመሪያ ወይም ማጣቀሻ መፅሀፍ አሁንም በብቃት የለም። ባሰመኖሩም ትምህርቱ የሚሰጠው የተሰያዩ የስነ-ልሳን ሰዎች በልዩ ልዩ የውጭ ቁዋንቁዋዎች ሰለ ቁዋንቁዋው ከፃፉዋቸው የምርምር ሰራዎች ላይ እየተቀነጨበ በሚወጣ ተበታኝ ወረቀት አማካኝነት ነው። ይህም በመሆኑ፣ መምህራን በተቀያየሩ ቁጥር የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ እንደ መምህራኑ <u>ዳራ</u> እና እንደሚያጋጥማቸው የምርምር ሰራ ሲቀያየር ኖሮአል። በዚህም ምክንያት የአንዱ ዘመን ተማሪ የተማረውን፣ የሌላው ዘመን ተማሪ አያገኘውም። ሰለዚህም ተመጣጣኝ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸውን ተማሪዎች ማፍራት ሲያስቸግር ቆይቶአል። ከዚህ ችግር ስመውጣት የሚቻለው፣ አንድ ወጥ የሆነ የማስተማሪያ መፅሀፍ በባዕድ ሳይሆን፣ በዚሁ ቁዋንቁዋ ሲዘጋጅና ሁሉም በዚሁ መነሻነት እያስተማረ ተፈላጊውን ግንዛቤና የአጠቃቀም ክህሎት ሲያዳብር ነው።

እነሆ፣ በዚህ መፅሀፍ ለማድረግ የተሞከረውም ይኸው ነው። አንድ ወጥና አጠቃላይ የሆነ የአማርኛ ስዋስው ማዘጋጀት። በሶስተኛ ደረጃና ከዚያም ዝቅ ብሎ የሚሰጠውንና መሰጠትም የሚገባውን አጠቃላይ የአማርኛ ትምህርተ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የቁዋንቁዋው ስርዓት በሶስት ምዕራፎች ተካቶ እንዲቀርብ ተደርጎአል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የአማርኛን ድምፆች አይነትና ያሰካከ ባህሪ የሚያሳይ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ከድምፆቹ የሚመሰረቱትን ቃላት የርባታና የምስረታ ስርዓት የሚያካትት ሲሆን፣ ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ የሀረግንና የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ያወቃቀር ባህሪ የሚያሳይ ነው። ሰስቱም ምዕራፎች ስስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቢቻል በሶስት፣ አለያም በሁለት መንፈቅ ተጠቃለው ሊሰጡ ይችላሉ።

ሶስቱም ምዕራፎች መፅሀፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወጣ ከነበራቸው ይዘት በእጅጉ ተለውጠዋል። ተጨማሪ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሂደቶችና ስነ-ምዕላዳዊ ስርዓቶች ተካተዋል። ከዋና ዋናዎቹ የቃሳት ክፍሎች በተጨማሪ፣ መስተጓምር የሚል ራሱን የቻለ የቃል ክፍል ተካቶአል። በመዋቅሩ ክፍል አድራጊና አስደራጊ አረፍተ ነገሮችን የሚመሰክት ክፍል ተጨምሮአል። በዚህም ምክንያት የመፅሀፉ ይዘት ሰፍቶአል። በመጀመሪያው ዕትም ተጠቅሰው የነበሩ አንዳንድ ምሳሌዎች ወጥተዋል ወይም በሌሎች ተተክተዋል። ይህም የተደረገው ፅንሰ-ሀሳቦችን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ሲባል ነው። በያንዳንዱ ንዑስ ክፍል መጨረሻ ላይ ለሙከራ የሚሆኑ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ዝግጅቱ ከመሰረተ ጉዳዮች ተነስቶ ቀስ በቀስ ጥልቅና ውስብስብ ወደሆኑ ነገሮች የሚሄድ ነው። ለስሆነም ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ሆነ ከዚያ በታች ላሉት እንደ አስፈላጊነቱ ከያይነቱ አየተጨለፈና ቀጠንጠን አየተደረገ ሊቀርብ ይችላል፣ የሚል ግምት አለኝ። ከዚህም አልፎ፣ ከትምህርት ቤት ውጭ መፅሀፉን በግል በማንበብ ብቻ ስለ አማርኛ ቁዋንቁዋ ስርዓት፣ ብሎም ስለ አጠቃላይ የስነ-ልሳን ሳይንስ መሰረታዊ ግንዛቤ ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ መፅሀፉ ጥሩ መነሻ ሊሆን የሚችል ይመስለኛል። ይሁን እንጅ በዚህ ደረጃ በግል ለሚያነቡ ሰዎች አንድ ማሳሰቢያ አለኝ። ይኸውም መፅሀፉ እንደ ተራ ልቦለድ ተዝናንቶ የሚነበብ ሳይሆን፣ ቀስ ተብሎ እየታሰበና እየተጠና የሚነበብ መሆኑን ነው። አንዳንድ ፅንሰ-ሀሳቦችን ለመረዳት አንዳንድ ጊዜ አረፍተ ነገሮቹን ደጋግሞ ማንበብ ሊያስፈልግ ይችላል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ፅንሰ-ሀሳቦቹ አዕምሮአዊ የሆኑ ነገሮችንና ግንኙነቶችን የሚሸፍኑ ስለሆኑና አነዚህንም ለመግለፅ የተጠቀምኩባቸው ቃላት አንግዳ፣ አረፍተ ነገሮቹም ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። የቃላቱን ችግር ለማቃለል፣ ይከብዳሉ ብዬ ለገመትኩዋቸው ቃላት፣ ሙዳየ ቃሳት ተዘጋጅቶአል። በሙዳየ ቃሳቱ ውስጥ የገቡት በግርጌያቸው ሳይ የተሰመረባቸውና ተንጋደው የተፃፉት ብቻ ናቸው። ተጨማሪ ንባብና ምርምር ለማካሄድ ለሚፈልጉ ደግሞ አስካሁን ድረስ በቁዋንቁዋው ስርዓት ሳይ የተፃፉትንና የታተሙትን የስነ-ልሳንና ሌሎችም ተዛማጅ መረጃዎች ከሞላ ጎደል የሚያሳይ መዘርዝር ቀርቦአል።

መፅሀፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታተም የህትመት ደረጃው የታቀደውን ያህል አንዳልነበረ ግልፅ ነው። ለዚህም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩ። ይህም ከፍተኛ ቅሬታን ቢያሳድርብኝም ለበለጠ ስራ እንድነሳሳ ረድቶኛል። ይህ ያሁኑ ዕትም በአይነቱም ሆነ በይዘቱ ከመጀመሪያው የተሻለ እንደሆነ በየደረጃው ረቂቁን ያነበቡ ባልደረቦቼና ተማሪዎቼ ጠቁመውኛል። ያም ሆኖ በበኩሌ አሁንም "እንዲህ ቢሆኑስ" የምላቸው ጉዳዮች አሉ። የምርምር ስራ ማሰቂያ የለውምና ስጊዜው ባለበት ትቻቸዋለሁ። ወደፊት ግን "አንዲያ" አደርጋቸው ይሆናል።

መልካም ንባብ

ምዕራፍ አንድ

ስነ-ድምፅ

መግቢያ

ማንኛውም ቁዋንቁዋ መሰረቱ ድምፅ ነው። ድምፅ ስንል በንግግር ጊዜ በአንደበት የሚፈጠረውን ማለታችን ነው። ድምፅ በአንደበት የሚፈጠረው በመደበኛ የስትንፋስ ሂደት ላይ ከሳንባ የሚነሳ ወይም ወደ ስንባ የሚገባ አየር በተለያዩ የአንደበት አካላት፣ በተለያየ ቦታ ላይ እየታገደና አየተለቀቀ፣ ወይም ላይታገድ እንደልቡ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ነው።[1] አንድ ሰው በቁዋንቁዋ ሀሳቡን የሚያስተላልፈውም በመሰረቱ የተለያዩ ድምፆችን በቅደም-ተከተል በተለያዩ ያንደበት ክፍሎች በመፍጠር ነው። ለምሳሌ አንድ ልጅ፣

መፅሀፍ ማንበብ አፈልጋለሁ 1

በማለት፣ የመፅሀፍ ማንበብ ፍላጎቱን የሚገልፀው፣ የሚከተሉትን ድምፆች ተራ በተራ፣ በተለያየ ቦታና ሁኔታ በመፍጠር ነው።

ም-ኧ-ፅ-እ-ሀ-አ-ፍ-ም-አ-ን-ብ-ኧ-ብ-አ-ፍ-ኧ-ል-አ-ግ-ሉ-ል-ኧ-ሀ-ኡ

እነዚህ ድምፆች ባብዛኛው የተለያዩ ናቸው። የልዩነታቸው ምክንያት የሚፈጠሩበት ቦታና ያፈጣጠራቸው ሁኔታ የተለያየ መሆኑ ነው። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ድምፆች ብንመለከት፣ [ም] ከንፈሮቻችንን በመዝጋት ከሳንባችን የሚወጣው አየር በሰርን በኩል እድርጎ በአፍንጫ እንዲወጣ ስናደርግ የሚፈጠር ሲሆን፣ [ኧ] ደግሞ ከንፈሮቻችንን አላቀን አፋችንን ስንከፍትና አየሩ በአፍ በኩል እንዲወጣ ስናደርግ የሚፈጠር ድምፅ ነው። በዚሁ ሁኔታ የሌሎቹንም ድምፆች የተለያየ የመፈጠሪያ ቦታንና የአፈጣጠር ሁኔታን መዘርዘር ይቻላል።

ርግጥ፣ ከላይ የተጠቀሰው ልጅ የመፅሀፍ ማንበብ ፍላጎቱን የሚገልፀው ድምፆቹን በተደረደሩበት መልካቸው እያንዳንዳቸውን በተናጠል በመፍጠር ብቻ አይደለም። ቅደም-ተከተላቸውን ላያፋልስ፣ በቡድን በቡድን በመከፈልና አንዱን ቡድን ከሌላው ጋር እንደሚከተለው አያደረገ በመለየት ነው።

---

[1] ዋናው ከሳንባ የሚወጣው አየር ይሁን እንጅ በማንቁርትና በትናጋ ላይ በሚገኝ አየር አማካኝነትም ሊፈጠር ይችላል።

መ - ፅ - ሀፍ - ማን - በብ - እ - ፈል - ል - ጋ - ልለ - ሁ (2)

በዚህ አይነት ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን 24 ድምፆች በ11 ሊመድባቸው ይችላል። ይህም ሆኖ፣ አንደዚህ እያደረገ በመከፈል ብቻ ሀሳቡን በሚገባ ሳያስተላልፍ ይችላል። ይህን ለማድረግ የሚችለው እነዚህን 11 ቡድኖች አንደገና በአራት በማጠቃለል፣

መፅሀፍ - ማንበብ - እፈልግ - ኣለሁ (3)

ሲል፣ ወይም ደግሞ ከላይ በተራ ቁጥር (1) በቀረቡበት ሰርዓተ ፅሀፈታዊ መልካቸው በሶስት ቡድኖች ብቻ እካቶ፣

መፅሀፍ - ማንበብ - እፈልጋለሁ (4)

ሲል ነው።

በመሰረቱ ግን እነዚህ ከሁሰት እስከ አራት የቀረቡት ቡድኖች ከላይ የተዘረዘሩት የ24ቱ ተናጠል ድምፆች ቅንጅት ናቸው። በሁለቱ፣ ማለትም በዝርዝሮቹና በቅንጅቶቹ (ቡድኖቹ) መካከል ያለው ልዩነት የቅንጅት ነው። 24ቱ ነጠላ ድምፆች ወደ 11፣ 11ዱ ደግሞ ወደ አራት፣ ከዚያም አልፎ፣ ወደ ሶስት እየተቀናጁ በተዋረድ ሊመጡ ችለዋል። ከዚህም ሁኔታ የምንረዳው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ድምፆች <u>ተናጠላዊ</u> እና ቅንጅታዊ ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው። ተናጠላዊ ባህሪያቸው ካፈጣጠራቸው ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ቅንጅታዊ ባህሪያቸው ካገባባቸው የሚመጣ ነው። በድምፅ ደረጃ የሚደረግ የእንድ ቁዋንቁዋ ጥናትም በነዚህ ሁለት ባህሪያት ላይ የሚያተኩር ነው። እኛም በዚህ ከፍል የምናደርገው ይህንኑ ነው። የአማርኛን ድምፆች ተናጠላዊና ቅንጅታዊ ባህሪያት መመርመር።

ተናባቢ

ባህሪያቱን ለመመርመር መነሻችን ከላይ አንደተጠቀሰው ልጅ ያሉ አንደበተ ጤነኛ ሰዎች ንግግር ነው። ለምሳሌ፣ የተጠቀሰው ልጅ "መፅሀፍ ማንበብ እፈልጋለሁ" ከማለት አልፎ፣ ሰሰ መፅሀፍ ንባብ ጠቃሚነት ረዘም ያለ ንግግር ቢያደርግና፣ ያን ንግግሩንም በቴፕ ቀርፀን፣ በውስጡ የሚገኙትን ድምፆች እየሰየን በተናጠል ስማውጣት ብንሞክር፣ ከምናገኛቸው ዋና ዋና ድምፆች መካከል አብዛኞቹ የሚከተሉት እንደሆኑ እንረዳለን።

ነ	ፍ	ጥ	ር	ጅ	ሹ	ኝ	ግ	(5)
ም	ድ	ስ	ን	ች	ሽ	ክ	ፅ	
ው	ት	ዝ	ል	ጭ	ይ	ቅ	ሀ	

እነዚህ 24 የተለያዩ ድምፆች ናቸው። ልጁ ከተማ- አና/ወይም ግዕዝ-ቀመስ ከሆነ፣ በንግግሩ ውስጥ፣ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ [ጵ-ፕ-ፅ] የሚሉትን ድምፆች ልናገኝ እንችላለን። እነዚህ ከላይኞቹ ጋር ሲደመሩ፣ የድምፆቹ ጠቅላላ ቁጥር 27 ይሆናል። እነዚህ ተራ ድምፆች ናቸው። ተራ የሚያሰኛቸው በአንድ በተወሰነ ቦታና በአንድ በተወሰነ የአንደበት አካል አንቅስቃሴ አማካኝነት የሚፈጠሩ መሆናቸው ነው።

ከነዚህ በተጨማሪ፣ በልጁ ንግግር ውስጥ ውስብስብ ሊባሉ የሚችሉ ድምፆችንም ልናገኝ እንችላለን። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፣

[ኮ ግ ቅ][2] 6

እነዚህ ሶስት ድምፆች ከላይ በተራ ቁጥር አምስት አንደተዘረዘሩት፣ በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው። ይሁን እንጅ፣ የሚፈጥሩት ሁለት የተለያዩ ያንደበት አካላት ባንድ ጊዜ ሲንቀላቀሉ ነው። በዚህም ምክንያት የሁለት ተራ ድምፆች <u>ቅናጅ</u> ይመስላሉ። ለምሳሌ [ኮ]ን ብንመለድ፣ የሚፈጠረው ትናጋ ላይ ሲሆን፣ አፈጣጠሩ ደግሞ የምላስ የሁዋላ ከፍል ወደ ትናጋ ወጥቶ ከለንባ የሚወጣውን አየር ሲያግደውና፣ ከናፍርም መደበኛ ዝርግ ቅርፃቸውን ትተው ክብ ሲሆኑ ነው። ሁለቱ ተንቀሳቃሽ የአንደበት አካላት የምላስ የሁዋላ ከፍልና ከናፍር ናቸው። የከናፍር <u>ክበት</u> [ው] የሚለውን ተራ ድምፅ ስንፈጥርም የሚታይ ስለሆነ፣ [ኮ] የሚለው የትናጋ ድምፅ የ[ክ] አና የ[ው] ቅናጅ ይመስላል። አንዳንድ ሊቃውንትም ሁኔታው በርግጥ ይህ እንደሆነ ያምናሉ[3]።

ይሁን እንጅ፣ የሚንቀሳቀሱት አካላት ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በአንድ ጊዜ እንጅ፣ በቅደም-ተከተል አይደለም። አንቅስቃሴያቸው ቅደም-ተከተላዊ ቢሆን ኖሮ፣ ድምፆቹ ውነትም የሁለት ተከታታይ ድምፆች ማለትም፣ የ[ክ] አና የ[ው] አይነት ድምፆች ውህደት የፈጠራቸው ናቸው ሊባሉ ይችሉ ነበር። ይህ ግን አይደለም። ድምፆቹ የሁለት ተከታታይ ድምፆች ውጤት ሳይሆኑ፣ የተለያዩ የአንደበት አካላት መሳ (አኩል) አንቅስቃሴ ውጤት ናቸው። ከከናፍር አንቅስቃሴ ከበትን፣ ምላስ ወደ ትናጋ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ደግሞ ትናጋዊነትን የያዙ ባሰሁለት ባህሪ ድምፆች ናቸው። በዚህም ምክንያት ድምፆቹ ተራ ሳይሆኑ፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ውስብስብ ናቸው። እነዚህ ድምፆች ከላይ ከተዘረዘሩት 27 ተራ ድምፆች ጋር ሲደመሩ፣ የምናገኘው ጠቅላላ የድምፅ መጠን 30 ይሆናል።

---

[2] የዚህ አይነት የአፈጣጠር ባህሪ ያላቸው የትናጋ ድምፆች ብቻ ናቸው። ከነዚህ ውጭ ግንኛውም ተናባቢ ለምሳሌ፣ [ሀ] [ሆ]፣ [ም] [ሞ] ሆኖ ሊከሰት ይችላል። ይህ የሚሆነው ግን በአፈጣጠር ሳይሆን ድምፁ ከብ ከሆነ አናባቢ ጋር ሲሰለፍ በሚመጣ የባህሪ ተጋቦት ነው። አንደ [ግ] አይነቱ አማፍም ንበታዊ (ፎነቲክ) ነው። ሰርዓተ ፅሀፈታዊ አማፋቸው ኩ፣ ጉ፣ አና ጕ ነው።

[3] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቤንደር (1976)ን፣ ፖዶልስኪ (1977)ን ታደሰ (1972)ን፣ ሙሉጌታ (2001)ን ይመልከቱ።

እነዚህ በሙሉ ተናባቢ ድምፆች ይባላሉ። ተናባቢ የሚባሉበት ምክንያት፣ ተንቀሳቃሽ በሚባሉት ያንደበት ክፍሎች ከሳንባ የሚወጣው አየር እየታገደና እየተለቀቀ ሲወጣ የሚፈጠሩ በመሆናቸው ነው። ተንቀሳቃሽ የአንደበት ክፍሎች የሚባሉት ከናፍር፣ ምላስ፣ የትናጋ ጫፍ (ቬለም) እና ማንቁርት ውስጥ የሚገኙ ተርገብጋቢ አካላት ናቸው።

ድምፆቹ በጥቅሉ ተናባቢ ይባሉ እንጅ፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ በመካከላቸው የሚታዩ ልዩነቶች አሉ። እነዚህም ልዩነቶች የሚመነጩት ከድምፆቹ <u>መካነ ፍጥረት</u> እና <u>ባህርየ ፍጥረት</u> ነው። መካነ ፍጥረት አንድ ድምፅ የሚፈጠርበት ቦታ ሲሆን፣ ባህረየ ፍጥረት ደግሞ፣ ድምፁ የሚፈጠርበት ሁኔታ ነው። መካነ ፍጥረት የሚባሰው፣ በመሰረቱ ከከናፍር ጀምሮ እስከ ማንቁርት ድረስ ያለው የላይኛው ያፋችን ከፍል ነው። ይህም የላይኛውን ከንፈር፣ ጥርሰን፣ ድድን፣ <u>ድኅረ ታን</u> (የድድና የላንቃ ድንበር) ላንቃን፣ ትናጋን፣ እንጥልን፣ ጉሮሮንና ማንቁርትን ያጠቃልላል።

በመሰረቱ በነዚህ በያንዳንዳቸው ላይ በተንቀሳቃሾቹ ክፍሎች አማካኝነት አየር እየታገደ ሲለቀቅ፣ የተሰያየ ድምፅ ሲፈጠር ይችላል። ከዚህ አኩዋያ ሲታይ፣ በየቁዋንቁዋው መካከል ሊኖር የሚችለው የድምፅ ልዩነት፣ እነዚህን ቦታዎች በከፊል ከመጠቀም ወይም ካለመጠቀም የሚመጣ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ለምሳሌ፣ አማርኛን ብንመለድ፣ እንጥልንና ጉሮሮን አይጠቀምም። ለዚህም የእንጥልና የጉሮሮ ድምፆች የሉትም። በዚህ ምክንያት፣ የእንጥል ድምፅ ካሉዋቸው እንደ ሀምጣንጋ ካሉ የአገው ቁዋንቁዋዎችና የጉሮሮ ድምፅ ካላቸው እንደ ትግርኛ ካሉ የሴም ቁዋንቁዋዎች ይለያል። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በቁዋንቁዋዎች መካከል ያለው የድምፅ አይነት ልዩነት፣ አንድም ከመካነ ፍጥረት ምርጫ እና/ወይም ከባህርየ ፍጥረት ልዩነት የሚመጣ ነው፣ ለማለት ይቻላል።


ባህርየ ፍጥረት ካየር ጋር የተገናዘበ ፅንሰ-ሀሳብን ያዘለ ሰያሜ ነው። በመሰረቱ ድምፅ የሚፈጠረው አየር ሲናር ነው። አየር ከሌለ ሰውም አይናርም። ይናራል እንኩዋ ቢባል፣ ድምፅ መፍጠር ስለማይችል፣ በንግግር ሀሳብን ማሰተላለፍ አይችልም። ድምፅ የሚፈጠረው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ባብዛኛው ከሳንባ በሚወጣ አየር ነው። ባብዛኛው የምንልበት ምክንያት ባንዳንድ ቁዋንቁዋዎች ወደ ሳንባ በሚገባ አየርም የሚፈጠሩ ድምፆች ስላሉ ነው። በሀገራችን ለምሳሌ እንደ ኦሮምኛ ያሉ የኩሽና እንደ ባስኬቶ ያሉ የኦሞ ቁዋንቁዋዎች በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ድምፆች አሉዋቸው። ከነዚህም አንዱ [ድ] ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ድምፅ የሚፈጠረው ከሳንባ የሚነሳው አየር በማንቁርት አልፎ፣ በጉሮሮ አድርጎ፣ በአፍ ወይም ባፍንጫ በኩል ወደ ውጭ ይወጣል። በዚህ ጉዞው ላይ ከላይ በተዘረዘሩት ቦታዎች ማለትም፣ መካነ ፍጥረቶች ላይ እየታገደ ወይም ሳይታገድ እንደልቡ ሊወጣ ይችላል። የሚታገደውም ተንቀሳቃሽ ባልናቸው የአንደበት ክፍሎች ነው። እነዚህ ክፍሎች ከተጠቀሱት መካነ ፍጥረት ጋር በሚያደርጉት ንክኪ አማካኝነት፣ አየር እየታገደ ሲወጣ የሚፈጠሩት ድምፆች፣ ሳይታገድ ሲወጣ ከሚፈጠሩት ሌሎች ድምፆች የተለዩ ናቸው። ስለሆኑም ሲታገድ የሚፈጠሩትን በጥቅሉ እግድ፣ ሳይታገድ የሚፈጠሩትን ልቅ ድምፆች

አንላቸዋለን፡፡ አግዶቹ በጥቅሉ ከፍ ሲል ተናባቢ ያልናቸው ሲሆኑ፣ ልቆቹ ደግሞ አናባቢ የሚባሉትና ወደፊት የምናያቸው ናቸው፡፡

በአንድ መካነ ፍጥረት ላይ አየር የሚታገደው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት የሚፈጠሩትን ድምፆች አንደ እግዱ ደረጃ ሙሉ ወይም ከፊል እግድ በማለት በሁለት ብቻ አንከፍላቸዋለን፡፡ ሙሉ እግድ የሚባሉት፡ አየሩ ሙሉ በሙሉ ከታገደ በሁዋላ ባንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሲለቀቅ የሚፈጥሩት ሲሆኑ፣ ከፊል እግድ የሚባሉት ደግሞ ያየሩ መውጫ በተንቀሳቃሹ የአንደበት አካል በከፊል ሲዘጋ ወይም ሲጠብና ከዚህም የተነሳ አየሩ በጠበበው በር እየተሹለከለከና አየተፋተገ ሲወጣ የሚፈጠሩት ድምፆች ናቸው፡፡

1-ሰርን
2-ከናፋር
3-ጥርስ
4-ድድ
5-ድላንቃ
6-ትናጋ
7-እንጥል
8-የምላስ ጫፍ፡
9-የምላስ መሀል
10-የምላስ ሁዋላ
11-እፋ፡
12-ጉሮሮ
13-የማንቁርት ክዳን
14-ማንቁርት
15-ርግብግቢት
16-አየር ማለፊያ
17-መዋጫ



የአንደበት አካላት

አየር መታገድ የሚጀምረው ከሳንባ ወጥቶ፣ በአየር ማስፊያ ቱቦ (16) አድርጎ፣ ግንቁርት (15) ሲደርስ ነው። አዚህ ውስጥ የሚገኙ ተርገብጋቢ ሰስ ሙንቻዎች መውጫ ቀዳዳውን ሊዘጉበት ይችላሉ[4]። በር እንዲሰቁ አየሩ ሲገፋቸው ይወጠሩና መንዘር ይጀምራሉ። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ድምፆች ይህ ሁኔታ በሌሰበት፣ ማለትም እግድ ብሎም ውጥረትና ንዝረት በሌሰበት ከሚፈጠሩት ድምፆች የተሰዩ ናቸው። በዚህም መሰረት ሙንቻዎቹ ሲወጠሩና ሲነዝሩ የሚፈጠሩትን ነዛሪ፣ ሲረግቡና ሳይነዝሩ የሚፈጠሩትን ደግሞ ኢነዛሪ በማለት ድምፆችን በጥቅሉ በሁለት እንከፍላለን። ጆሮአችንን በመዳፋችን በመዝጋት [ብ] ብንል፣ ሙንቻዎቹ ሲነዝሩ ይሰማናል። ባንዛሩ ደግሞ ጆሮአችንን ተጭነን [ፕ] ብንል፣ ምንም ንዝረት አይሰማንም። ቢሰማንም ሰሚቱ አጅግ ደካማ ነው። በዚህ አይነት ነዛሪ ድምፆችን ከኢነዛሪ ድምፆች በቀላሉ ሰመሰየት እንችላለን። እሰቲ አርሰዎም [ክ]፣ [ግ]፣ [ት]፣ [ድ]፣ ወዘተ፣ እያሉ ነዛሪውን ከኢነዛሪው ስመሰየት ይሞክሩ።

አየር ከግንቁርት ወጥቶ፣ በጉሮሮ አድርጎ በአፍ በኩል፣ ወይም በሰርን አድርጎ ባፍንጫ በኩል ሊወጣ ይችላል። በአፍ በኩል የሚወጣው የትናጋ ጫፍ (ቬለም) ወደ ስርን የሚወሰደውን በር ሲዘጋበት ነው። ባፍንጫ በኩል የሚወጣው ደግሞ ወደ አፍ የሚወሰደውን በር ይሽው አካል ማሰትም (ቬለም) ሲዘጋበት ነው። ከዚህም የመውጫ በር ልዩነት የተነሳ፣ ድምፆች የስርንና የአፍ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ሰምሳሌ፣ ቀደም ሲል ከዘረዘርናቸው ድምፆች መካከል እንደ [ም፣ን፣ኝ] ያሉት የሰርን ሲሆኑ፣ እንደ [ል፣ድ፣ቅ] ያሉት ደግሞ የአፍ ናቸው። አንድ ድምፅ የስርን መሆኑን ወይም አሰመሆኑን ሰማረጋገጥ ሁሰቱንም የአፍንጫ ቀዳዳ ተጭኖ በመያዝ፣ ድምፁን ስማሰት (ሰማሰማት) መሞከር ነው። ድምፁን ስማሰት ከተቻሰ፣ ድምፁ የአፍ ነው፣ ካልተቻሰ የሰርን ነው።

አየሩ በአፍ በኩል የሚወጣ ከሆነ፣ አንጥል ላይ በምላስ ሰር፣ ትናጋ ላይ በምላስ የሁዋላ ክፍል፣ ላንቃ ላይ በምላስ የመሀል ክፍል፣ ድድ ላይ በምላስ የፊት ክፍል፣ ጥርሰ ላይ በምላስ ጫፍ፣ እንደዚሁም በመጪረሻ በከናፍር በከፊል፣ ወይም በሙሉ፣ እየታገደና እየተሰቀቀ ይወጣል። በዚህ ሁኔታ አንደ ቦታውና አንደ አግዱ ልዩነት፣ የተሰያዩ ተናባቢ ድምፆች ይፈጠራሉ። ከዚህ ላይ አንድ ልንነነዘበው የሚገባ ነገር አለ። ይሽውም ስድምፅ ፈጠራ ምላስ ምን

[4] ካሁን በፊት እነዚህ አካላት ከር-መላይ ሙንቻዎች ተብለው ነበር። አንዳንድ ጊዜም ሀብለ ድምፅ ይባላሉ። ሙንቻዎቹ ከር ወይም በግዕዙ አጠራር ሀብል አይደሉም። ሰላልሆኑ ስያሜው መስተካከል አለበት። በአየር ሲገፉ የሚርገበገቡ ሰስ አካል አንጅ ከር አይደሉም። በዚህ ምክንያት ርግብግቢት ብያቸዋለሁ። ሰሰነታችው ርግብግብ ያደርጋቸዋል።

ያህል እሰፈላጊ እንደሆነ ነው። ለዚህም ነው፤ እንዳንድ ጊዜ ቁዋንቁዋንና ምላስን አንድ እድርገን የምንወሰደው።

እንግዲህ ከዚህ አጠቃላይ የድምፅ እፈጣጠር ሁኔታና ቦታ ተነስተን ቀደም ሲል የዘረዘርናቸውን ተናባቢ ድምፆች በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን።

	መካነ ፍጥረት						
ባህርየ ፍጥረት	ከናፍር	ስነፈር	ድድ	ድላንቃ	ላንቃ	ትናጋ	ማንቁርት
እግድ፡ ነ	ብ		ድ			ግ ግ	
ኢ	ፕ		ት			ክ ክ	ዕ
ፈ	ጵ		ጥ			ቅ ቅ	
ፍትግ፡ ነ			ዝ	ዥ			
ኢ		ፍ	ስ	ሽ			ሀ
ፈ			ፀ				
ፍግድ፡ ነ				ጅ			
ኢ				ች			
ፈ				ጭ			
ሰርናዊ፡	ም		ን		ኝ		
ጎናዊ፡			ል ር				
ከፍናቢ፡	ው				ይ		

የፎኒም ሰጠረዥ[5]

በጥቅል አነጋገር፡ እነዚህ ድምፆች በሙሉ አግድ ናቸው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፤ እንዳው ከፊል ወይም ሙሉ ሲሆን ይችላል። ዝርዝር እፈጣጠራቸውን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

[5]ከዚህ ለተሰየ የፎኒም ዝርዝር፤ ሙሉጌታ ስዩም ገበያው፤ (2001)ን ይመልከቱ።

እግድ

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ድምፆች [ብ፣ፕ፣ጵ]፣ ድ፣ት፣ጥ]፣ [ግ፣ግ፣ቅ፣ቅ፣ክ፣ኮ] እና [ዕ] ናቸው። ሁሉም ከሳንባ የሚመጣው አየር ሙሉ በሙሉ ከታገደ በሁዋላ ሙሉ በሙሉ ሲለቀቅና ቡልቅ! እያለ በአፍ በኩል ፈሙጣ የሚፈጠሩ ናቸው። አየሩ የሚታገደው ለመጀመሪያዎቹ፣ ላይኛው ከንፈር ላይ በታችኛው ከንፈር፣ ለሚቀጥሉት የላይኛው የፊት ጥርሰ ሰር ላይ በምላስ የፊት ክፍል፣ ለሶስተኞቹ፣ ማለትም ለ[ግ፣ግ፣ክ፣ኮ፣ቅ] እና [ቅ] ትናጋ ላይ በምላስ የሁዋላ ክፍል ሲሆን፣ ለ[ዕ] ደግሞ ማንቁርት ውስጥ በሚገኙት ተርገብጋቢ ሙንቻዎች እማካኝነት ነው። ሰለዚህም ድምፆቹ በሚፈጠሩበት ቦታ ሰም የከናፍር፣ የጥርሰ[6]፣ የትናጋና የማንቁርት እግድ ድምፆች ይባላሉ። ከነዚህ ድምፆች መካከል [ብ፣ድ፣ግ]እና [ግ] ብቻ ነዛሪ ናቸው። ይህም ማለት፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ድምፆቹ ሲፈጠሩ ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ተርገብጋቢ ሙንቻዎች ስለሚወጠሩ ይነዝራሉ ማለት ነው። ሌሎቹ በሙሉ ኢነዛሪ ናቸው። [ጵ፣ጥ፣ቅ] እና [ቅ] ደግሞ ከሌሎቹ የሚለዩበት ተጨማሪ ባህሪ አላቸው። ይኸውም እነዚህ ድምፆች ሲፈጠሩ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ከሳንባ የሚወጣው አየር የሚታገደውና የሚለቀቀው በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ ብቻ ላይሆን፣ ማንቁርት ውስጥም ነው። ለምሳሌ [ቅ]ን ብንወሰድ፣ ከሳንባ የሚወጣው አየር በአንድ ጊዜ፣ ማንቁርት ውስጥና ትናጋ ላይ ይታገዳል። ማንቁርት ውስጥ በክሮቹ፣ ትናጋ ላይ በምላስ የሁዋላ ክፍል በአንድ ጊዜ ይታገድና፣ በሁለቱም ቦታዎች ላይ የታገደው አየር በቅደም-ተከተል ላይሆን፣ እንደዚሁ በአንድ ጊዜ ይለቀቃል። ስለዚህም በሚለቀቅበት ጊዜ ጠሽ! የሚል ድምፅ ያሰማል። ከዚህም የተነሳ፣ በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ድምፆች በሙሉ ፈንጅ ይባላሉ። አንዳንድ ጊዜም ማንቁርታዊ እየተባሉ ይጠራሉ።

ፍትግ

ፍትግ ድምፆች የሚባሉት [ፍ]፣ [ዝ፣ሰ፣ፅ]፣ [ሽ፣ኧ] እና [ህ] ናቸው። በአራት የተከፈለቡት ምክንያት የሚፈጠሩበት ቦታ እንደዚሁ የተለያየ ሰለሆነ ነው። የመጀመሪያው፣ ማለትም [ፍ]፣ የላይኛው የፊት ጥርሰ ላይ፣ የሚቀጥሉት ድድ ላይ፣ ሶሰተኞቹ ድላንቃ ላይ፣ የመጨረሻው ደግሞ ማንቁርት ላይ ይፈጠራል። በዚህም ምክንያት እንደ ቅደም-ተከተላቸው የጥርሰ፣ የድድ፣ የድላንቃና

[6] በእኔ አነጋገር [ሰ] እና [ዝ] የሚፈጠሩት በላይኛው የፊት ጥርሰ ጀርባና በድድ መካከል ላይ ነው። ይህም እግድ ከሆኑት ከ[ት፣ድ፣እና ጥ] አፈጣጠር ጋር ተመሳሳይ ነው። በመካከላቸው ያለው ልዩነት የአፈጣጠር አንጅ የመካነ ፍጥረት አይደለም። ይህን ማረጋገጥ የሚቻለው በመሳሪያ ነው።

የማንቁርት ፍትግ ድምፆች ይባላሉ። ፍትግ የሚባሉበት ምክንያት ከሳንባ የሚወጣው አየር በተጠቀሱት ቦታዎች እድርጎ ሲያልፍ፣ መንገዱ በከፊል ሰለሚዘጋበትና ከዚህም የተነሳ ሰለሚጣበብ፣ እንደልቡ ሳይሆን፣ እየተፋተገና እሽሽሽ... የሚል ድምፅ እያሰማ ሰለሚወጣ ነው[7]። መንገዱን የሚዘጉበት ቀደም ሲል ተንቀሳቃሽ ያንደበት ክፍሎች ያልናቸው፣ ማለትም ከንፈር፣ ምሳስና ማንቁርት ውሰጥ የሚገኙት ከሮች ናቸው። ሰምሳሌ የ[ፍ]ን አፈጣጠር ብንመለከት፣ ከሳንባ ተነሰቶ በአፍ በኩል የሚወጣው አየር ጥርሰ አካባቢ ሲደርስ፣ የታችኛው ከንፈራችን ወደ የላይኛው የፊት ጥርሳችን በመሄድ መውጫ መንገዱን ሲያጣብብበት፣ የግድ እየተፋተገና እየተሹለከለከ እንደሚወጣ እንረዳለን።

ከ[ዝ] እና ከ[ዥ] በሰተቀር፣ ሌሎቹ ድምፆች በሙሉ ኢነዛሪ ናቸው። [ዕ] ግን ኢነዛሪ ብቻ ሳይሆን ፈንጅም ነው። ሰለፈንጅ ድምፆች ቀደም ሲል የተሰጠውን መግለጫ ያስታውሱ።

ፍግድ (ፍትግ-እግድ)

ፍግድ ድምፆች የሚባሉት የእግድና የፍትግ ድምፆች ያፈጣጠር ባህሪ ባንድ ላይ የሚታይባቸው ናቸው። እነሱም [ጅ፣ች] እና [ጭ] ናቸው። ካፈጣጠራቸው ባህሪ የተነሳ፣ ፍትግ-እግድ ድምፆች ሲባሉ ይችሉ ነበር። አጠራሩን ሰማሳጠር፣ ብሎም ቀላል ለማድረግ ሲባል ፍግድ ተብለዋል[8]።

እየሩ የሚታገደው ድላንቃ ላይ ሲሆን፣ እጋጁም የምላሰ የፊት ክፍል ነው። ይህ ክፍል ወደ ድላንቃ በመነሳት ከሳንባ የሚመጣውን አየር ሙሉ በሙሉ ያግደዋል። አሰተጋገዱ ልክ እግድ ድምፆች ሲፈጠሩ እንደሚታየው አይነት ነው። አየሩ ከታገደ በሁዋላ፣ አየሩን ያገደው አካል ባንድ ጊዜና በፍጥነት ሳይሆን፣ በዝግታ ወደነበረበት ቦታ ሲመለስ፣ ታግዶ ለነበረው አየር መሹለኪያ በር ቀስበቀስ ይከፍትለታል። አየሩም በሚከፈትለት ጠባብ በር እየተፋተገና እየተሹለከለከ ቀስበቀስ ይወጣል። እንደ እግድ ድምፆች በአንድ ጊዜ ቡልቅ! ብሎ ሳይሆን፣ እንደ ፍትግ ድምፆች ሹልክልክ እያለ ይወጣል።

---

[7] ጌታሁን (1990) እነዚህን ድምፆች ሹልክልክ ይላቸዋል። በእኔ ግምት አይነተኛ ባህሪያቸው በጠበቡው ቀዳዳ እየተፋተጉና ሽሽሽ.... የሚል ድምፅ እያሰሙ መፈጠራቸው ስለሆነ፣ ፍትግ የሚለው ቃል የበለጠ ይገልፃቸዋል። መሹለክለክ መፋተግን ላያስከትል ይችላል።

[8] ጌታሁን፣ <u>ዝኔ ከማሁ</u>፣ እነዚህን ድምፆች ፍትግ ይላቸዋል። ይሁን እንጅ ባህሪያቸው የፍትግነት ብቻ ሳይሆን፣ የእግድነትም ጭምር ስለሆነ፣ ፍትግ ከሚለው ይልቅ፣ ፍግድ የሚለው ይበልጥ ይገልፃቸዋል። ሰለዚህም ይህንን ሰያሜ እንጠቀማለን። "ላሽ" የሚለው ሰያሜ የጌታሁን መሆኑን እንገልፃለን።

ከዚህም የተነሳ የድምፆቹ አፈጣጠር መጀመሪያ ላይ አንደ አግድ ድምፆች ሆኖ፣ መጨረሻ ላይ፣ ማስትም አለቃቀቁ ላይ፣ አንደ ፍትግ ድምፆች ነው። [ጅ] ነዛሪ ሲሆን፣ ሌሎቹ ኢነዛሪ ናቸው። [ሞ] ደግሞ ከኢነዛሪነት በተጨማሪ ፈንጅም ነው።

ሰርናዊ

አሰካሁን ያየናቸው ድምፆች በሙሉ አየር በአፍ በኩል በተለያየ ቦታ ላይ በምላስ የተለያየ ከፍል አየታገደና አየተለቀቀ ሲወጣ የሚፈጠሩ ናቸው። ከነዚህ የሚለዩትና በዚህ ከፍል ውስጥ የሚመደቡት ድምፆች [ም፣ን] አና [ኝ] ናቸው። አነዚህ ሰርናዊ ይባላሉ። ሰዚህም ምክንያቱ ከላንባ የሚነሳው አየር በአፍ ውስጥ ላይሆን፣ በሰርን በኩል አድርጎ ሲወጣ የሚፈጠሩ በመሆናቸው ነው። ይህም የሚሆነው የትናጋ ጫፍ (ቬለም) መደበኛ ቦታዋን ለቃ፣ ወደታች በመውረድ ወደ አፍ የሚመለደውን በር ስትዘጋው ነው። ወደታች ወርዳ ይህን በር በምትዘጋበት ጊዜ፣ ወደ ሰርን የሚመለደው በር ይከፈታል። በአፍ ለመውጣት ያልቻለው አየርም በዚህ (ሰርን) በኩል አድርጎ፣ በአፍንጫችን ቀዳዳ ይወጣል። አየሩ በሰርን በኩል ላይታገድ ይውጣ አንጅ፣ አፍ ውስጥና ከናፍር ላይ የሚደረግ የአካላት ንክኪ ሰላለ፣ ንክኪው አንደሚፈጠርበት የቦታ ልዩነት የሚፈጠሩት የሰርን ድምፆችም የተለያዩ ናቸው። ለምላሌ [ም] አየር በሰርን በኩል በሚወጣበት ጊዜ፣ ከናፍርም ሰለሚጋጠሙ ሰርናዊ የከናፍር ድምፅ ይባላል። [ን]ም አየሩ በሰርን በኩል ሲያልፍና የምላስ ጫፍም ከድድ ጋር ስትነካካ የሚፈጠር ስለሆነ፣ ሰርናዊ የድድ ድምፅ ይባላል። የ[ኝ] አፈጣጠር በከፈል አንደ [ን] ነው። አንደ [ን] አየር በሰርን በኩል ይወጣል። ሆኖም [ኝ] ስትፈጠር የሚነኩት አካላት የምላስ የመሀል ከፍልና ላንቃ ስለሆኑ፣ [ኝ] ከ[ን] የተለየች ልትሆን ችላለች። ሁሉም ነዛሪዎች ናቸው።

ጎናዊ

በዚህ ውስጥ የሚገኙት ድምፆች [ል] አና [ር] ናቸው። ሁለቱም ከላንባ የሚወጣው አየር በአፋችን በኩል አድርጎ በምላስ ጎንና ጎን፣ ጉንጫችንን አየታከከ ሲወጣ የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው። አየሩ መሀል ለመሀል ላይሆን፣ በጎን በጎን ሰለሚወጣ፣ ድምፆቹ ጎናዊ ሊባሉ ችለዋል። አየሩ ዳርዳሩን በሚወጣበት ጊዜ የምላስ ጫፍ ከድድ ጋር ለለምትነካካ፣ ድምፆቹ ጎናዊ የድድ ድምፆች ይባላሉ። በሁለቱ መካከል መጠነኛ ልዩነት አለ። ይኸውም [ር] ስንል፣ የምላሳችን ጫፍ ድዳችንን በትንሹ ብቻ ነካ፣ ነካ፣ አድርጋ የምትመለስ መሆኑ ነው። ከዚህ ልዩነት የተነሳ በጎንና ጎን የሚወጣው የአየር መጠን

ይለያያል። [ል] ስንል፣ ንክኪው ጠበቅ ያለና የሚወጣውም አየር ሞቅ (በዛ) ያለ እንደሆነ ይሰማናል። ሁለቱም ነዛሪ ናቸው።

ከፍናቢ (ከፈል አናባቢ)

በዚህ ውስጥ የሚመደቡት [ው] እና [ይ] ናቸው። እነዚህ ድምፆች ከፈል አናባቢ በመባል ይታወቃሉ። ስሙን ለማሳጠር ሲባል *ከፍናቢ* ተብለዋል። ከፍናቢ የሚባሉበት ዋና ምክንያት የአናባቢነትንም ሆነ የተናባቢነትን ባህሪ ስለሚያሳዩ ነው። ወደፊት እንደምናየው፣ አናባቢዎች የሚፈጠሩት ያለምንም አየር አገዳ ከናፍርንና ምላስን የተለያየ ቅርፅ በማሰያዝ ብቻ ነው። የከፍናቢዎችም አፈጣጠር እንደዚሁ ነው። ለምሳሌ፣ [ኡ] የሚለው አናባቢ የሚፈጠረው ከንፈርን ሰብሰብ አድርጎ በማጥበብና ምላስን ወደ ሁዋላ ሸምቀቅ አድርጎ ወደ ትናጋ በማንሳት ነው። የ[ው]ም አፈጣጠር ልክ እንደዚሁ ነው። [ይ] ደግሞ ልክ [ኢ] እንደሚለው አናባቢ፣ ከንፈርን በመዘርጋትና የምላስን የፊት ከፍል ወደ የፊት ድድ አቅጣጫ በማንሳት የሚፈጠር ድምፅ ነው። በከፍናቢዎቹና በአናባቢዎቹ መካከል ያለው ልዩነት የአፈጣጠር ነው። ይኸውም የ[ኢ] እና [ኡ] አፈጣጠር ሙሉ በሙሉ የአናባቢ ሲሆን፣ የከፍናቢዎቹ ግን በተናባቢ ጀምሮ እጨራረሱ ላይ ወደ አናባቢ የሚያጋድል መሆኑ ነው። ሁለቱም ከፍናቢዎች ነዛሪ ናቸው።

ይህ እንግዲህ የከፍናቢዎችን አፈጣጠር በተመለከተ ነው። ስርጭታቸውን ስናይ ደግሞ ምድባቸው ከአናባቢዎች ጋር ሳይሆን፣ ከተናባቢዎች ጋር ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም እንደ ማንኛውም ተናባቢ፣ ከአናባቢ ጋር እንጅ ብቻቸውን በተናጠል ሊባሉ አለመቻላቸው ነው። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ አናባቢዎችን [አ፣ኡ፣ኢ፣ወዘተ] እያልን በተናጠል መጥራት እንደምንችል ሁሉ፣ ከፍናቢዎችን ግን በዚሁ አይነት መጥራት አንችልም ማለት ነው። ርግጥ፣ [አ፣ኡ፣ኢ፣ ወዘተ] እንደምንል ሁሉ፣ [ዎ፣ዉ፣ዊ፣ ወዘተ ፣] ማለት እንችል የለም ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ይህ ትክክል ነው። ነገር ግን [ዎ፣ዉ፣ዊ፣ ወዘተ] እያልን የምንጠራው እንደ [አ፣ኡ፣ኢ፣ ወዘተ] ያሉ ተራ ድምፆችን ሳይሆን፣ ቅንጅቶችን ነው። [ዎ] የ[ው] እና የአናባቢው የ[አ] ፣ [ዉ]፣ የ[ው] እና የ[ኡ] እንደዚሁም [ዊ]፣ የ[ው] እና የ[ኢ] ቅንጅቶች ናቸው። ባጭሩ አናባቢዎችን ከቅንጅት ውጭ በተናጠል ለማለት ሲቻል፣ ከፍናቢዎችን ግን ከቅንጅት ውጭ ለማለት ወይም ለመጥራት አይቻልም። ከዚህ በመነሳት የሁለቱ፣ ማለትም የአናባቢዎችና የከፍናቢዎች፣ መሰረታዊ ልዩነት የአፈጣጠር ሳይሆን፣ የስርጭት ወይም የቅንጅት ነው፣ ለማለት ይቻላል። ይኸውም ከፍናቢዎች አፈጣጠራቸው እንደ አናባቢ ሆኖ ሳለ፣ ስርጭታቸው እንደ ተናባቢ መሆኑ ነው። ይኸውም ያለአናባቢ ሊነበቡ የማይችሉ በመሆናቸው ነው።

ቀደም ሲል በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ በሰባት መካነ ፍጥረት የተመለከቱት ተናባቢ ድምፆች፣ እንደ ተቀራራቢነታቸው፣ በአራት ከፍል ብቻ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ይህም ከላይኛው ከንፈራችን ጀምሮ እስከ ማንቁርት ደረሰ

ያለውን የላይኛውን የአፋችንን ክፍል የጫፍ፣ የፊት፣ የመሀልና የሁዋላ (ሰር) ብሎ በአራት በመክፈልና በዚሁ መሰረትም ድምፆቹን እንደሚከተለው አድርጎ በመመደብ ነው።

ባህርየ ፍጥረት	ጫፍ	ፊት	መሀል	ሁዋላ
እግድ፣ ነ	ብ	ድ	ጅ	ግ ጯ
አ	ፕ	ት	ች	ክ ኵ ዕ
ፈ	ጵ	ጥ	ጭ	ቅ ቈ
ፍትግ፣ ነ		ዝ	ዥ	
አ	ፍ	ስ	ሽ	ሀ
ፈ		ፅ		
ሰርናዊ፣	ም	ን	ኝ	
ጎናዊ፣		ል ር		
ከፍናቢ፣	ው		ይ	

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ እግድና ፍግድ ድምፆች በአንድ ላይ ተጠቃለው በአግድ ሰር ተመድበዋል።ይህም ከባህርየ ፍጥረት መመሳሰል የተነሳ ነው። ፍግድ

ድምፆች የእግድነት ባህሪ ያሳያሉ፤ ከፍናቢ የሆነው [ው] የከናፍር ከሆኑት ጋር በአንድነት በጫፍ ሰር ተመድቦአል። የድላንቃና የላንቃ ድምፆች በመሀለኛው፣ እንዲሁም የትናጋና የጉሮሮ ድምፆች በሁዋለኛው የአፋችን ክፍል ሰር ተጠቃለዋል። እነዚህ አራት ክፍሎች፣ ወደፊት ከምናያቸው የምላስ የተለያዩ ክፍሎች ጋር ትይዩ ናቸው።

ከአጠቃላይ ሁኔታው፣ አብዛኞቹ የአማርኛ ተናባቢ ድምፆች በፊተኛውና በመሀለኛው የአፋችን ክፍል እንደሚፈጠሩ ለመረዳት ይቻላል። የሚፈጠሩትም በከናፍርና በምላስ ስለሆነ፣ ከዚሁ አንፃር ድምፆቹን የከናፍርና የምላስ ብለን በሁለት ብቻ ልንከፍላቸው እንችላለን፣ የምላስ የሚባሉት የፊት፣ የመሀልና የሁዋላ ድምፆች ተብለው በሶስት የተመደቡት ሲሆኑ፣ የከናፍር የሚባሉት ከአፍ ውጭ ከናፍርን በማጋጠም፣ አየር በማገድና በመልቀቅ የሚፈጠሩት ናቸው።

እነዚህ አንግዲህ ቀደም ሲል በጠቀስነው ተናጋሪ ንግግር ውስጥ ይገኛሉ የተባሉት ተናባቢ የአማርኛ ድምፆች ናቸው። በንግግሩ ውስጥ የምናገኘው ግን እነዚህን ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ቀጥለን የምናያቸውንና አናባቢ የሚባሉትን ድምፆች ጭምር ነው።

አናባቢ

የአናባቢ ድምፆች ዋና ባህሪ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ አፈጣጠራቸው አየርን የማያግድ መሆኑ ነው። ልቅ ድምፆች ናቸው። በዚህም ምክንያት እግድ ከሆኑት ከተናባቢ ድምፆች ይለያሉ። ሁለተኛም የግስተጋባት ደረጃቸው ከተናባቢዎች የበለጠ ስለሆነ በቀላሉ ይሰማሉ። በሌላ አነጋገር አናባቢዎች ጆሮ-ገብ ወይም ጨዋሂ ድምፆች ናቸው። በአማርኛ ውስጥ የሚገኙት አናባቢ ድምፆች የሚከተሉት ናቸው።

[ኧ ፣ኡ ፣እ ፣ኧ ፣አ ፣ኡ ፣ኦ]

አናባቢዎች በሙሉ አፋዊና ነዛሪ ናቸው። አፋዊ የሚያሰኛቸው፣ ሲፈጠሩ ከሳንባ የሚነሳው አየር በአፍ በኩል አድርጎ የሚወጣ መሆኑ ነው። አፈጣጠራቸውና አይነታቸው ከፍ ሲል አንዳየናቸው እንደ ተናባቢ ድምፆች ከምላስና ከከናፍር የተለያየ አንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘ ነው። ይሁን እንጅ እንቅስቃሴው አየርን የሚያግድ ሳይሆን፣ አፍን የሚያስከፍትና የሚያዘጋ፣ በዚያው መጠንም ከናፍርን የሚያስከብብና የሚያዘረጋ፣ ምላስንም ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ እንደዚሁም ወደላይ እና ወደ ታች የሚያንቀሳቅስ ነው። ስለዚህም ተናባቢዎች ሲፈጠሩ የምናየው አይነት የአካላት ንክኪ ብሎም የአየር አገዳ በአናባቢዎች አፈጣጠር ላይ የለም።

ከዚህ አኳያ የድምፆቹን አፈጣጠር በውል ለማየት መጀመሪያ ስለ ምላስ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳቱ ጠቃሚ ይሆናል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ምላስ ለድምፅ ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋፅየ ያለው አካል ነው። ምላስ የሌለው ሰው መናገር አይችልም። ለዚህም ነው፣ አንዳንድ ጊዜ ንግግርንና ምላስን፣ ከዚያም አልፎ ምላስና ቁዋንቁዋን፣ አንድ አድርገን የምናየው። አገሌ ደህና ምላስ አለው፤ የሚለው አባባልም የሚያስገነዝበን ይህንኑ የሁለቱን አንድነት ነው።

ምላስ አንዲህ ከፍተኛ ተግባር ሊኖረው የቻለው ቀልጣፋ አካል በመሆኑ ነው። ቀልጣፋ ያደረገው ደግሞ አንደልብ የሚተጣጠፍ አጥንት-የለሽ መሆኑ

ነው። ከእንቅስቃሴው አኳኋያም በሶስት ሊከፈል ይችላል። ከፍሎቹም ፊተኛ፣ መሀለኛና ሁዋለኛ ናቸው። ፊተኛ የሚባለው ከላይኛው የፊት ድድ ጋር ትይዩ የሆነውና ከድድ ጋር ንክኪ በመፍጠር ክፍ ሲል ፊተኛ ያልናቸውን ተናባቢዎች የሚፈጠረው ክፍል ነው። ሁዋለኛ የሚባለው ከትናጋ ጋር ትይዩ የሆነውና ሁዋለኛ ተናባቢ ያልናቸውን ድምፆች የሚፈጠረው ክፍል ነው። መሀለኛ የሚባለው ደግሞ በነዚህ በሁለቱ መካከል የሚገኘው ወይም የላንቃ ትይዩ የሆነው የምላስ ክፍል ሲሆን፣ እሱም መሀለኛ ያልናቸውን ተናባቢ ድምፆች የሚፈጥረው ነው። እያንዳንዱ ክፍል ራሱን ችሎ ለእሱ ተይዩ ወደሆነው ክፍል ሊንቀሳቀስ ይችላል። የሚንቀሳቀሰውም በአረፍት ላይ፣ ማለትም በማንነጋገርበት ጊዜ ከሚገኝበት ቦታና ሁኔታ ተነስቶ ወደ ፊት፣ ወደ መሀልና ወደ ሁዋላ በመነሳት ነው። እንደ ተንቀሳቃሹ የምላስ ክፍል አይነት፣ የሚፈጠረው ድምፅም እንደዚሁ የፊት፣ የመሀል ወይም የሁዋላ እናባቢ ወይም ተናባቢ ይባላል። በእንቅስቃሴው ምክንያት በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ እየር በክፈል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚታግድ ከሆነ፣ የሚፈጠሩት ድምፆች ተናባቢ ናቸው። እንቅስቃሴው እየር የማያግድ ከሆነ፣ የሚፈጠሩት ድምፆች እናባቢ ናቸው።


ከዚህ አንፃር ያለምንም አየር እገዳ የሚፈጠሩትና ከላይ የተዘረዘሩት ሰባት አናባቢ ድምፆች እንደሚከተለው ሆነው በሶስት ሊመደቡ ይችላሉ። ይህም ቀደም ሲል በአፍ ውስጥ በምላስ አማካኝነት ይፈጠራሉ ካልናቸው ተናባቢ ድምፆች አመዳደብ ጋር እንድ ነው።

ፊተኛ	ኢ	ኤ	
መሀለኛ	እ	ኧ	ኣ
ሁዋለኛ	ኡ	ኦ	

እንደዚሁም ተንቀሳቃሹ የምላስ ክፍል እንደሚገኝበት ከፍታ ወይም ዝቅታ መጠን፣ እነዚሁ አናባቢዎች ላየኛ፣ ልከኛ እና ታቸኛ ተብለው እንደገና በሶስት እንደሚከተለው ይመደባሉ።

ላየኛ	ኢ	እ	ኡ
ልከኛ	ኤ	ኧ	ኦ
ታቸኛ		ኣ	

እነዚህን ሁለት አይነት አከፋፈሎች እንደሚከተለው አድርጎ በአንድ ማዕቀፍ አጠቃሎ ማሳየት ይቻላል።



የአናባቢ ማዕቀፍ

ይህ እንግዲህ አናባቢዎች ስማንነጋገርበት፣ ማለትም በዝምታ ጊዜ ምሳስ ከሚገኝበት ቦታ ተነስቶ፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ፣ እንዲሁም ወደ ላይና ወደ ታች እያለ ከሚፈጥረው የመሳላብ እንቅስቃሴ እኩዋያ ሊታይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከናፍር ከዚሁ የምሳስ እንቅሰቃሴ ጋር በሚያደርጉት <u>ተሰተጋብሮት</u> ምክንያት፣ ሊከበቡና ሊዘረጉ ይችላሉ። በዚህም መሰረት ከላይ የተመለከቱት አናባቢዎች ከብ፣ መካከለኛና ዝርግ ተብለው በሶስት ሊከፈሉ ይችላሉ። ከብ የሚባሉት የምሳስ የሁዋላ ከፍል ወደ ትናጋ ሲወጣና ከናፍርም ስብሰብና ጥብብ ሲሉ የሚፈጠሩት ናቸው። እነዚህም የሁዋላ አናባቢዎች ያልናቸው [ኡ] እና [ኣ] ናቸው። መካከለኛ የሚባሉት፣ ምሳስ ወደ ፊትም ሆነ ወደ ሁዋላ ሳይል፣ መካከለኛ ቦታውን እንደያዘ፣ ከናፍርም ሳይጠቡና ሳይሰፉ ልከኛ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ የሚፈጠሩት ናቸው። እነዚህም መሀለኛ አናባቢዎች ያልናቸው [እ፣ኧ] እና [ኣ] ናቸው። ዝርግ የሚባሉት ደግሞ ምሳስ ወደ ላይ ማለትም፣ ወደ ድዳችን፣ ቢሉጠጥና ከናፍርም ልከኛ መሆናቸው ቀርቶ፣ ሲዘረጉ ወይም ሲሰፉ የሚፈጠሩት ናቸው። እነዚህም የፊት አናባቢዎች ያልናቸው [ኢ] እና [ኤ] ናቸው። በጥቅሉ ግን አናባቢዎችን ዝርግና ከብ (ሙጥሙጥ) ብሎ በሁለቱ ከፍሎች ብቻ መወሰን ይቻላል። ቀደም ሲል የጠቀሰናቸው ከፍናቢዎችም በነዚህ በሁለቱ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ይኸውም [ይ] ከፊት (ዝርግ) አናባቢዎች ጋር፣ [ው] ደግሞ ከሁዋላ (ከብ) አናባቢዎች ጋር በመሰለፍ ነው።

ቀደም ሲል የዘረዘርናቸው 30 ተናባቢዎችና ከላይ በማዕቀፉ ውስጥ የሚታዩት ሰባት አናባቢዎች ሲደመሩ፣ የቁዋንቁዋው ድምፆቹ ጠቅላላ ቁጥር 37 ይሆናል። እንደ ተመሳሳይነታቸው፣ ሁሉንም በአንድ ስንጠረዥ እካቶ እንደሚከተለው ማሰቀመጥ ይቻላል።

ባህርየ ፍጥረት	ጫፍ	ፊት	መሀል	ሁዋላ
እግድ፡ ነ	ብ	ድ	ጅ	ግ ጉ
ኢ	ፕ	ት	ች	ክ ኩ ዕ
ፈ	ጵ	ጥ	ጭ	ቅ ቁ
ፍትግ፡ ነ		ዝ	ዥ	
ኢ	ፍ	ስ	ሽ	ህ
ፈ		ፅ		
ሰርናዊ፡	ም	ን	ኝ	
ትናዊ፡ ላሽ፡		ል C		
ክፍናቢ፡	ው		ይ	

ላዮኛ ኢ እ ኡ

ልከኛ ኤ ኧ ኦ

ታቸኛ አ

የእግርኛ ፎኒሞች

ስትርጉምም ሆነ ስሰርዓተ ዕሀፈት መሰረት ሊሆኑ የሚገባቸው ድምፆች እነዚህ ብቻ ናቸው። ይሁን እንጅ ስርዓተ ዕሀፈታችን በነዚህ ድምፆች ላይ ብቻ ላይሆን፣ በግዕዝ

ድምፆችና ፊደሎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ለአማርኛ ምንም ፋይዳ የሌላቸው እንዳንድ ፊደሎችን ሊይዝ ችሎአል። ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ።

ፎኒም

እስካሁን ድረስ ያተኮርነው በድምፆች እፈጣጠርና በዚህም ላይ በሚመሰረተው በአይነታቸው ወይም አከፋፈላቸው ላይ ነው። የከናፍር፣ የጥርስ፣ የድድ፣ የድላንቃ፣ የላንቃ፣ ወዘተ፣ እያልን በመካነ ፍጥረታቸው፣ ነፋሪ፣ እግድ፣ ልቅ፣ ወዘተ፣ እያልን ደግሞ በባህርየ ፍጥረታቸው፣ እንደዚሁም በአየሩ መውጫ በር መሰረት የለርን እና የእፍ እያልን፣ ሰንከፋፍላቸው ቆይተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ እነዚህ ድምፆች እንዴት እንደሚቀናጁ · እንመለከታለን። ወደዚያ ከመግባችታችን በፊት ግን እንድ ነጥብ ማንሳት ይኖርብናል። ይኸውም እስካሁን ያየናቸው ድምፆች በቁዋንቁዋው ውስጥ ለሚገኙት ቃላት መሰረት መሆናቸው ነው። እንድ ቃል ከሌላ ቃል በትርጉምም ሆነ በቅርፅ የሚለየው በውስጡ የሚገኙት ድምፆች በሌላው ቃል ውስጥ ከሚገኙት ድምፆች በከፊል ወይም በሙሉ የተለዩ ሲሆኑ ነው። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት።

/ብኧርኧት/[9]	በረት
/ውኧርኧት/	ወረት

እነዚህ ጥንድ ቃላት በትርጉም ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ናቸው። ያንዱ ትርጉም ከሌላው ጋር የሚዛመድ አይደለም። ይሁን እንጅ፣ ቃላቱ በቅርፅ ብዙም የተለያዩ አይደሉም። በውስጣቸው ከሚገኙት እምስት እምስት ድምፆች መካከል በመጀመሪያዎቹ፣ ማለትም በ[ብ] እና በ[ው] ብቻ ነው፣ የሚለያዩት። እነዚህ ድምፆች ደግሞ ትይዩ በሆነ ተዋረድ (ላይና ታች) ሰርዓት የተሰለፉ ናቸው። ከነዚህ ሁለት ትይዩ ድምፆች መለያየት የተነሳም፣ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ትርጉም ሊይዙ ችለዋል። ለትርጉሞቹ መለያየት ምክንያት የሆኑት እነዚህ ሁለት ትይዩ ተዋረድ ድምፆች ናቸው፣ ማለት ነው። እንደዚህ ያሉ ትርጉም-ሰዩ የሆኑ ድምፆች በእንግሊዝኛ አጠራር ፎኒም ይባላሉ። ጌታሁን (1990) ንጥረ-ድምፀ-ልሳን ይላቸዋል። የሁን እንጅ ይህ ሰያሜ ረዥምና ለአጠራርም እስቸጋሪ ሰለሚመሰል፣ ፎኒም የሚለውን እጭር ቃል እንጠቀማለን። ሰለዚህም ማንኛውንም ትርጉም-ሰዩ የሆነን ድምፅ ፍኒም እያልን እንጠራለን።

---

[9] ይህ አይነቱ እፃፃፍ ፎኒማዊ ነው። እንደ ላቲኑ እፃፃፍ ተናባቢና እናባቢ እየተለዩ የሚታዩበት እፃፃፍ ነው። መደበኛው የአማርኛው እፃፃፍ እናባቢዎቹን ከተናባቢዎቹ ጋር እያዋህደ በአንድ ምልክት የሚያሳይ ነው። ዝርዝሩን ከባየ እና ቲም 89 (1989) ይመልከቱ።

ከዚህ አኩዋያ እስካሁን የተመለከትናቸው አናባቢም ሆኑ ተናባቢ ድምፆች ትርጉም-ለዪ ስለሆኑ፣ በሙሉ ፎኒሞች ናቸው። ትርጉም ለይነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ከላይ እንደተጠቀሱት ያሉና በአንድ ድምፅ ብቻ የሚለያዩ ጥንድ ቃላትን እየፈለጉ ትርጉማቸውን ማነፃፀር ያስፈልጋል። እዚህ ላይ በዚህ አይነት የሁሉንም ድምፆች ፎኒማዊነት ማሳየት ጊዜ-ፈጅ ስለሆነ፣ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ብቻ እናቀርባለን።

[ከአርአር]	ከራር	[ብኧልልኣ]	በላ	[እድድአር]	አድር	2
[ግአርኣር]	ግራር	[ብአልልኣ]	ባላ	[አድድአል]	አድል	

አነዚህ ጥንድ ጥንድ ቃላት የሚለያዩት ባንዳንድ ትይዩ ድምፆች ብቻ ነው። የመጀመሪያው ጥንድ መነሻ ላይ ትይዩ ሆነው በገቡት በ[ግ] እና በ[ከ]፣ የሚቀጥለው ጥንድ፣ መካከል ላይ በሚገኙት በ[ኧ] እና በ[አ]፣ አንደዚሁም የመጨረሻው ጥንድ፣ መጨረሻ ላይ በሚገኙት በ[ል] እና በ[ር] ነው። በትይዩዎቹ ድምፆቹ ልዩነት ምክንያት፣ ቃላቱ የተሰያየ ትርጉም ሊይዙ ችለዋል። ስለዚህም ለየጥንዱ ቃላት የትርጉም ልዩነት መንስዔ የሆኑት ድምፆች፣ ማለትም /ከ፣ግ፣ኧ፣አ፣ል፣እና ር/ ፎኒሞች ናቸው። ከዚህ ላይ ግን ፎኒሞቹ የሚገኙበት ቦታ ትይዩ መሆኑን አንደገና ማጤን ያስፈልጋል። የሚገኙበት ቦታ ትይዩ ካልሆነ፣ ፎኒምነታቸውን በርግጠኝነት ለመናገር ያዳግታል።

ፎኒሞች ረቂቅ ናቸው። ስለሆኑም አዕምሮአዊ አንጅ አካላዊ ገፅታ የላቸውም። አካላዊ ገፅታ የሚኖራቸው በአንደበት አካላት አየተፈጠሩ ሲወጡና በጆሮም ሲሰሙ ነው። አንደበታዊ አፈጣጠራቸው ደግሞ ቀደም ሲል አንደተመለከትነው፣ የተለያየ ነው። ስለዚህም አንድ ፎኒም የተለያየ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል። ሰምሳሌ፣ የሚከተሉትን አንመልከት።

/<u>ብ</u>ኣት/	[<u>ብ</u>ኣት]	ባት	3
/ልኣ<u>ብ</u>/	[ልኣ<u>ብ</u>]	ላብ	

በነዚህ ቃላት ውስጥ የሚገኘው [ብ] የተለያየ <u>ጋበት</u> አለው። ይኸውም <u>ላ</u>ብ ([ልኣብ]) በሚለው ቃል መድረሻ ላይ የሚገኘው፣ ልል [ብ] ሲሆን፣ <u>ባ</u>ት ([ብኣት]) በሚለው መነሻ ላይ የሚገኘው [ብ] ልል አለመሆኑ ነው። ይሁን እንጅ፣ <u>ባ</u>ት በሚለው መነሻ ላይ ያለውን [ብ] አላልተን፣ <u>ላ</u>ብ በሚለው መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ደግሞ አጥብቀን ብንጠራው፣ ቃሉ ትርጉሙን አይቀይርም። የሁለቱ ድምፆች መቀያየር የንበት አንጅ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም ማለት ነው። ይህ ከሆነ፣ ሁለቱ ድምፆች የአንድ አዕምሮአዊ ፎኒም የተለያዩ አካላዊ ገፅታዎች ወይም ክሳቾች እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ። አዕምሮአዊ የሆነው አንድ ፎኒም አካላዊ ሆኖ ከአንደበት በሚወጣበት ጊዜ፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቅርፅ ሊያሳይ ይችላል። እነዚህ የተለያዩ አካላዊ ቅርፆች <u>በፎ-ፎኒም</u>

ይባላሉ፡፡ ፎኒምንና ዘረ-ፎኒምን ለመለየት፣ ፎኒሙን በአዝባር ዘረ-ፎኒሙን በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ እንፅፋለን፣ የዘረ-ፎኒሙ መከሰቻ ቦታም ይገለፃል፡፡ በዚህ መሰረት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

/ብ/ → [ቧ] / ከእናባቢ በሁዋላ 4
→ [ብ] / በሌላ ቦታ

ይህ እቀራረብ አዕምሮአዊ የሆነችው ፎኒም /ብ/ አካላዊ፣ ማለትም እንደበታዊ፣ ሆና ስትወጣ፣ ሁለት አይነት ቅርፅ እንደሚኖራት ያሳያል፡፡ እንደኛው ልል ሆና የምትከሰትበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ልል ሳትሆን የምትጎንበት ነው[10]፡፡ ልል ሆና የምትከሰተው እናባቢ ተከትላ ስትገባ ነው፡፡ ልል ሳትሆን የምትከሰተው፣ በግንኛውም ሌላ ቦታ ስትገኝ ነው፡፡ በዚህ አይነት ግንኛውም ፎኒም በአካል ሲከሰት፣ የተለያየ ቅርፅ ይይዛል፡፡ የተለያዩት ቅርፆችም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ የረቂቁ (አዕምሮአዊው) ፎኒም ዘሮች ናቸው፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

/ን-ብ/	[ንአብ]	ንብ	5
/ም-ን/	[ምአን]	ምን	
/ምኽንግ-ለት/	[ምኽኻግለስት]	መንግስት	
/ምኽንክ-ር/	[ምኽኻክአር]	መንከር	

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የሚታየው [ን] አንድ አይነት አይደለም፡፡ በመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት ውስጥ የሚገኘው [ን] በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቃላት ውስጥ ከሚገኘው [ን] የተለየ ነው፡፡ ልዩነቱ የመካነ ፍጥረት ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቃላት ውስጥ የሚገኘው ድኅሮ [ን] ሲሆን፣ በመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት ውስጥ የሚገኘው ትናጋዊ ነው፡፡ በትናጋዊው ፋንታ ድኅሮውን [ን] ብናሰገባ፣ የቃሉ ትርጉም አይለወጥም፡፡ ይህ ከሆነ፣ ሁለቱ ድምፆች የአንድ ፎኒም የተለያዩ አካላዊ ክሳቾች፣ ማለትም ዘረ-ፎኒሞች፣ ናቸው ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከፍ ሲል እንዳደረግነው፣ ፎኒሙንና ዘረ-ፎኒሞቹን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

/ን/ → [ᵑ] / ከትናጋ ድምፅ በፊት ሲገኝ 6
→ [ን] / በሌላ ቦታ ሲገኝ

ስለፎኒሞችና ስለ ዘሮቻቸው ይህን ያህል ከተረዳን፣ ከፍ ሲል ወደተነሳንበት፣ የቅንጅት ጉዳይ እንመለስና የፎኒሞችን የአቀነጃጀት ስርዓት እንመልከት፡፡

[10] ተራ እግድ የምንለው ጥብቅ ያልሆነን እግድ ድምፅ ነው፡፡

አቀንጃጀት

ቀደም ሲል በአይነት በአይነት ያሰቀመጥናቸው ድምፆች፣ ካሁን በፊት እንደተገለፀው፣ ተናጠሳዊና ቅንጅታዊ ባህሪ አላቸው። ባለፈው ንዑስ ክፍል ለማሳየት የሞከርነው ተናጠሳዊ ባህሪያቸውን ነበር። ይኸውም እያንዳንዱ ድምፅ የትና እንዴት እንደሚፈጠር እናም እንዱ ከሌላው በምን እንደሚለይ በማሳየት ነው። በዚህ ክፍል ደግሞ የእያንዳንዱን ድምፅ ቅንጅታዊ ባህሪ ለማሳየት እንሞክራለን። ቅንጅታዊ ባህሪ ሰንል፣ እንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ወይም ድምፆች ጋር ሲሰለፍ፣ የሚይዘው ቦታና በዚያ ቦታ በመገኘቱም በራሱ ወይም በጎረቤቱ፣ ማለትም አብሮት በሚሰለፈው ድምፅ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ ማለታችን ነው። በለውጡ ምክንያት ፎኒሞች በተለያየ ቦታ፣ ማለትም አቀነጃጀት፣ የተለያየ ገፅታ ወይም መልክ ሊኖራቸው ይችላል። የአንድ ፎኒም የተለያዩ ገፅታዎችም ዘረ ፎኒም እንደሚባሉ ከፍ ሲል ገልፀናል። ፎኒሞቹ በአዝባር (//) ውስጥ ሲፃፉ፣ ዘረ-ፎኒሞች በማዕዘን ቅንፍ ([ ]) ውስጥ እንደሚፃፉም አሳይተናል። ይህም አስማቀፋዊ የሆነ ስነ-ልሳናዊ የአፃፃፍ ሰርዓት ነው።

ከአሰላለፍ የሚመጣን ባህሪ በወጉ ለማየት፣ መጀመሪያ ምን ፎኒም ከምን ሌላ ፎኒም ወይም ፎኒሞች ጋር ሊሰለፍ ይችላል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል። ከዚህ አንፃር፣ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት አናባቢና ተናባቢ ፎኒሞች እያንዳንዳቸው ከሌላ ፎኒም ጋር ሊሰለፉ፣ የሰልፉ መጀመሪያ (ከግራ ወደቀኝ) ወይም መጨረሻ የመሆን እድል አላቸው ብሉ፣ መነሳት ይቻላል። በዚህ መሰረት ተናባቢ ያልናቸውን ፎኒሞች ሰርጭት ብንመለከት፣ ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ በቃል መነሻ ላይ ሊገኙ፣ ማለትም የሰልፉ የመጀመሪያ ድምፅ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ቦታ ላይ የማይገኘው /ኝ/ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት በዚህ ፎኒም የሚጀምር የእማርኛ ቃል የለም። አሰቲ ያሰቡ።

ከአናባቢዎች መካከል ደግሞ በመነሻ ሊገኙ የሚችሉት /እ፣ ኧ እና ኡ/ ብቻ ናቸው። እነዚህም መሀለኛ አናባቢ ያልናቸው ናቸው። ሌሎቹ፣ ማለትም ዳረጎቹ፣ በቃል መነሻ ላይ አይገኙም። ለለዚህም በእነሱ የሚጀምር የእማርኛ ቃል ያለ አይመስልም። ርግጥ፣ እንደ <u>ኢ</u>የሱስ ያሉ የውጭ ስሞች አሉ። ይሁን እንጅ ተወላጅ የአማርኛ ተናጋሪ እንደነዚህ ያሉትን ስሞች <u>እ</u>የሱስ እንጅ፣ <u>ኢ</u>የሱስ እያለ አይጠራም። ዳረጎውን /ኢ/ በመሀለኛው /እ/ ይተካዋል። የቁዋንቁዋው የአናባቢዎች የአገባብ ሰርዓት እይፈቅድለትማ።

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ከ/ኝ/ እና ከዳረጎ አናባቢዎች በስተቀር ማንኛውም ፎኒም በመነሻ ሊገኝ ከቻለ፣ ከዚያ ፎኒም ቀጥሎ ሊሰለፍ የሚችለው ፎኒም ምንድን ነው? የሚል ሌላ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል። በመሰረቱ የመጀመሪያው ተሰላፊ ተናባቢ ከሆነ፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚገባው አናባቢ ብቻ ነው። የመጀመሪያው ተሰላፊ አናባቢ ከሆነ ደግሞ፣ ከሱ ቀጥሎ ሊመጣ

የሚችለው እንድ ወይም ሁለት ተናባቢ ፎኒም ብቻ ነው። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

ተአ	ምሳሌ፡			
	(ሀ)	/ንእ/	ና	1
ተአ	(ለ)	/አፍ/	አፍ	

በምሳሌ (ሀ) አካሄድ ብንቀጥል፣ ካናባቢው ቀጥለን አንድም የተለያዩ ሁለት ተናባቢዎችን ወይም አንድ ረዥም (ጥብቅ) ተናባቢን ብቻ ልናገኝ እንችላለን። ረዥም ተናባቢን ፊደሉን ደግመን በመፃፍ እናመለክታለን። ለሳቀነጃጀቱ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

አተተ	ምሳሌ፡		
1 2	(ሀ)	/አንድ/	2
	(ለ)	/አምድ/	
	(መ)	/አሰም/	

ከምሳሌ (2) እንደምንረዳው፣ ተከታትለው ከሚገቡት ሁለት ተናባቢዎች መካከል የመጀመሪያው <u>ቀጣይ</u> መሆን አለበት። ሁለተኛው ቀጣይ ወይም እግድ ሊሆን ይችላል። ይህ አገባብ ሊፋለስ አይችልም። ከተፋለሰ፣ ማለትም እግዱ ቀድሞ ቀጣዩ ተናባቢ ከተከተለ፣ በመካከላቸው [አ] የሚለው አናባቢ ይገባል። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ)	[ብአርቅ]	3
(ለ)	[ፍአቅአር]	

በቅንፍ ውስጥ ከሚታየው አፃፃፍ እንደምንረዳው፣ በምሳሌ 3(ሀ)፣ /ር/ እና /ቅ/ ሊከታተሉ እንደሚችሉ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ ግን /ቅ/ እና /ር/ ሊከታተሉ እንደማይችሉ እንመለከታለን። ይህም በመሆኑ፣ [አ] በመካከላቸው ሊገባ ችሉአል። አንድ ረዥም ተናባቢ የሚገኝባቸው ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

አተተ	ምሳሌ፡			
1 1	(ሀ)	/አጥ/	አጥ	4
	(ለ)	/አከክ/	አክ	
ተአተ	ምሳሌ፡			
	(ሀ)	/ልአት/	ላት	5
	(ለ)	/ብአት/	ባት	
	(መ)	/ሰአር/	ሳር	

አተተ ምሳሌ፡
1 2

(ሀ)	/ክኧርስ/	ከርስ	6
(ለ)	/ለኧርክ/	ለርክ	
(መ)	/ብኧልግ/	በልግ	

ተአተተ ምሳሌ፡
1 1

(ሀ)	/ለኧቅቅ/	ለቅ (ቀበቶ)	7
(ለ)	/ድኧግግ/	ደግ	
(መ)	/ሀኣቅቅ/	ሀቅቅ	

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም፣ በተናባቢ በሚጀምሩ ቅንጅቶች ውስጥ፣ ከአናባቢው ቀጥሎ፣ አንድም ሁለት የተለያዩ ተናባቢዎች አለያም አንድ ረዥም ተናባቢ ይገኛል ለንል፣ <u>በአንድምታም</u> ቢሆን በቁጥቁዋው ውስጥ ረዥም ተናባቢዎች አሉ ማለታችን ነው፡፡ ይህ ምን ያህል ውነት ነው? የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል በአየነው የፎኒም ስንጠረዥ ውስጥ አይመልከት እንጅ፣ ከ/ሀ/በስተቀር እያንዳንዱ ተናባቢ ፎኒም ረዝሞ፣ ማለትም ጠብቆ፣ ሊነበብ ይችላል፡፡ ረዝሞ የሚገኝበት ዐታ ግን በመሰረቱ አንድም በቃል መሀል፣ አለያም በቃል መድረሻ ላይ ነው፡፡ በቃል መድረሻ ላይ ያለውን ሁኔታ ከላይ በተራ ቁጥር (4) እና (7) ከተሰጡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በቃል መሀል ስለሚታየው ጥብቀት ግን የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ)	/ፅኧግኣ/	ፀጋ	8
(ለ)	/ድኧስስኤት/	ደሴት	
(መ)	/ኣብብኣት/	አባት	

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ በአናባቢዎቹ መካከል የሚታየው ተናባቢ ጥብቅ ነው፡፡ አንድ ድምፅ ረዥም ወይም ጥብቅ ነው የሚባለው፣ <u>ንበቱ</u> ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ተራውን [ጣ] ለማለት (ለመጥራት) ግማሽ ሴኮንድ ይወስድ እንደሆነ፣ ረዥሙን [ጣጣ] ለማለት ከግማሽ ሴኮንድ በላይ ይወስድብናል ማለት ነው፡፡ በዚህም የጊዜ ልዩነት ምክንያት፣ እንደ [ጣጣ] ያሉት ረዥም ድምፆች ይባላሉ፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ <u>ጥብቅ</u> ድምፅ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሁለት ቃላት በመካከላቸው በሚገኙ ትይዩ ድምፆች የርዝመት ልዩነት ምክንያት፣ የትርጉም ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ)	/ግኧንንኣ/	ገና	(ለ)	/አልልኧ/	አለ	9
	/ግኧንኣ/	ገና		/አልኧ/	አለ	

(መ) /ግአምምአ/ ጋማ (ስ) /ክአብብአ/ ካባ
/ግአምአ/ ጋማ /ከአብአ/ ካባ

በየጥንዱ ውስጥ ያሉት ቃላት ትርጉም የሚለያየው በየመካከላቸው በሚገኘው ተናባቢ ድምፅ መርዘም ወይም አለመርዝም ምክንያት ነው። ይኸውም፣ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የ[ን] ፣ በምሳሌ (ለ) የ[ል]፣ በምሳሌ (መ) የ [ም]፣ እንዲሁም በምሳሌ (ስ) የ [ብ] ድምፅ መርዘምና አለመርዝም ነው። ሁኔታው የሚያሳየው፣ ርዝመት ወይም ጥብቀት ትርጉም-ለየ. መሆኑን ነው። ሁለት ቃላት በሁለት ትይዩ ፎኒሞች መለያየት ብቻ የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው እንደሚችል ሁሉ፣ በአንድ ፎኒም ማጠርና መርዘም ምክንያትም እንደዚሁ የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። ስርዓተ ፅሀፈታችን ከላይ በምሳሌዎቹ እንዳሳየነው የየድምፁን ፊደላዊ ምልክት ደግሞ በመግፍ ርዝመትን ማሳየት ሲችል፣ ይህን ባለማድረጉ ጉዳዩ አንደ ችግር ሊቆጠር ኖሮአል[11]።

ወደተነሳንበት የቅንጅት ጉዳይ እንመለስ። በቃል መካከል ሊገኙ የሚችሉት ሁለት የተለያዩ ተናባቢዎች ወይም የአንድ ረዥም ተናባቢ ብቻ ነው። ሶስተኛ ተናባቢ ከተገኘ፣ ከሱ በፊት [አ] የሚለው አናባቢ ስርጎ ይገባና ሶስተኛውን ተናባቢ ከቀዳሚዎቹ ተናባቢዎች ይለየዋል። ይህንን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን።

ቀለም

ከፍ ሲል በተመለከትነው ሁኔታ፣ ፎኒሞች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት አካል ቀለም[12] ይባላል። ትርጉም ሊኖረው ወይም ላይኖረውም ይችላል። ቀለም የሚያሰኘው አንድ አናባቢ ብቻውን ወይም ከተናባቢ(ዎች) ጋር ሆኖ አንድ ቅንጅታዊ አካል መፍጠሩ ነው። ለምሳሌ፣ ላሙና [ለአምኡንአ] የሚለውን ቃል አንመልከት።

---


[11] ምልክቱን እየደገሙ መፃፉ ራሱን የቻለ ጣጣ አለው። አንዱ እየደገመ የሚፅፈውን ሌላው እየነጠለ ሊፅፈው ይችላል። በላቲኑ አፃፃፍ፣ የሚታየው ዋናው ችግር ይህ ነው። ርምጃው የፅሀፈት ትምህርትን ከባድ የሚያደርግ ነው። ዝርዝሩን በተመለከተ ባየ (1984)ን እና ባየ እና ቲም 89 (1989)ን ይመልከቱ።

[12] አዚህ ላይ ቀለም የምንለው በስርዓተ ፅሀፈታችን ውስጥ ቀለም ከምንለው የተለየ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ልጅ ፊደል ቆጥሮ ሲጨርስ፣ ቀለም ለየ ይባላል። በዚህ አገባብ፣ ቃሉ የየፊደሉን ልዩ ምልክት ያመለክታል። እያንዳንዱ ምልክት ደግሞ የአንድ ተናባቢንና የአንድ አናባቢን ድምፅ ቅንጅት ባንድ ላይ ስለሚወክል፣ እኛ አዚህ ላይ ቀለም ከምንለው ጋር ይመሳሰላል። ይሁን እንጅ፣ እኛ ቀለም የምንለው፣ በውስጡ ከአንድ ተናባቢ በላይ ስለሚይዝና ትርጉምም ሊኖረው ስለሚችል፣ ከስርዓተ ፅሀፈቱ ቀለም ይለያል። ሁለቱን ቀለሞች ስርዓተ ፅሀፈታዊና ስርዓተ ድምፃዊ ብለው መለየት ይቻላል። ሁለቱም ምት ስላላቸው፣ በስርዓተ ግጥም ለየስንኙ ቤት መምቻ አየሆኑ ያገለግላሉ። ለዝርዝሩ መንግስቱ (1963)ን፣ ደረጀ (1975)ን፣ ባየ እና ቲም (89) (1989)ን፣ ተሾመ (1997)ን፣ አንዲሁም ብርሀኑ (2000)ን ይምልከቱ።

ቃሉ [ሰአ -ምኡ -ንአ] የሚሉትን ሶስት ቀለሞች ይዞአል። የየቀለሙ አቀነጃጀት [ተአ-ተአ-ተአ] ፣ ማለትም ተናባቢ - አናባቢ - ተናባቢ - አናባቢ አያለ የሚሄድ ነው። አያንዳንዱ ቀለም ትርጉም የለውም። ትርጉም ያለው የቀለሞቹ ቅንጅት የሆነው ሳሙና [ሰአምኡንአ] የሚለው ቅርፅ ነው። አንደዚህ ያለው ትርጉም-አዘል ቀለም <u>ምዕላድ</u> ይባላል። ዝርዝር ባህሪውን በምዕራፍ ሁለት ስለምንመለከተው፣ ከዚህ ላይ ከስሙ ጋር ብቻ እንተዋወቅ።


ምዕላዶች በውስጣቸው ባለው የቀለም መጠን መሰረት ባለ አንድ፣ ባለ ሁለት፣ ባለ ሶስት፣ ወዘተ ቀለም ምዕላድ እየተባሉ ይለያሉ። ለምሳሌ፣ እንደ <u>ሳሙና</u> ያሉት ባለ ሶስት፣ እንደ <u>ሰባ</u> [ሰኧብአ] ያሉት ባለ ሁለት፣ እንደ <u>ና</u> [ንአ] ያሉት ደግሞ ባለ አንድ ቀለም ምዕላዶች ናቸው። ከዚህ በመነሳት እንደ <u>ና</u> [ንአ] ያሉት ተራ፣ እንደ <u>ሳሙና</u> [ሰአምኡንአ] ያሉት ደግሞ ውስብስብ ቀለሞች ይባላሉ። የህፃናት የቁዋንቁዋ <u>ልምደት</u> የሚጀምረው በተራ፣ ማለትም በባለ አንድ ቀለም ምዕላዶች ነው። የንባብ ትምህርትም እንደዚሁ።

በአንድ ቀለም ውስጥ የሚገኙ ድምፆች <u>በተናጠላዊ</u> ቅደም-ተከተል ብቻ የሚደረደሩ ላይሆኑ፣ <u>በተዋረዳዊ</u> አቀማመጥም እየተዋቀሩ አንድ አካል የሚፈጥሩ ናቸው። የመዋቅሩ ምስሶ አናባቢው ድምፅ ነው። ያለሱ መዋቅሩ ሊቆም አይችልም። አሱ ግን ብቻውን አለያም ከአንድ ቀዳሚ ወይም ተከታይ ተናባቢ ጋር ሆኖ፣ የመዋቅሩን አንድ ክፍል ወይም ርከን ሊፈጥር ይችላል። ይህ ክፍል ደግሞ እንደዚሁ ብቻውን ወይም ከአንድ ቀዳሚ ተናባቢ ድምፅ ጋር ሆኖ፣ አጠቃላዩን ቀለማዊ መዋቅር ይፈጥራል። ያወቃቀሩን ዝርዝር ስርዓት በ<u>ዕፀ-መዋቅር</u> እንደሚከተለው እናሳያለን።



ከታች ወደ ላይ ብንመለከት፣ የመዋቅሩ ምስሶ የሆነው አናባቢ (አ) ብቻውን ቆሞ የመዋቅሩን <u>ማዕከል</u> (ማ)ን መስርቶአል። ይህ ማዕከል ደግሞ ከጨራሹ (ጨ) ተናባቢ ድመፅ ጋር ሆኖ፣ የቀለሙን <u>ምት</u> መስርቶአል። ምቱም በተራው ከከፋቹ (ከ) ተናባቢ ጋር ሆኖ፣ አጠቃላዩን ቀለም አዋቅሮአል። በሌላ አነጋገር [አ] ማዕከሉን፣ ማዕከሉና ጨራሹ ተናባቢ [ም] ምቱን፣ ምቱና ከፋቹ ተናባቢ (ል) ቀለሙን መስርተዋል። ከፋቹና ጨራሹ ተናባቢዎች ለመዋቅሩ የአናባቢውን

ያህል አስፈላጊ አይደሉም። ስለዚህም ሊቀሩ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ያለነሱ የሚዋቀረው ቀለም አናባቢውን ምስሶ ብቻ ይዞ ይቆማል። ስምሳሌ፣ <u>አሳ</u> የሚለውን ምዕላድ ብንመለከት፣ በውስጡ ሁለት ቀለሞች አንዳሉት እንገነዘባለን። እነሱም [አ-] እና [-ስእ] ናቸው። የመጀመሪያው ቀለም ከአናባቢው ምስሶ ላይ ብቻ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከምስሶው እና ከጨራሹ ተናባቢ ብቻ የተዋቀረ ነው። የሁለቱን ቀለሞች አወቃቀር እንደሚከተለው በዕፀ መዋቅር አናሳያለን።



በግልፅ እንደሚታየው፣ የመጀመሪያው ቀለም ከምስሶው፣ ማለትም ከአናባቢው ብቻ የተዋቀረ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከከፋችና ከአናባቢው ምስሶ ጋር የተዋቀረ ነው። ሁለቱ ቀለሞች ርስበርስ ተዋቅረው ምዕላዱን መስርተዋል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም በባለብዙ ቀለም ምዕላድ ውስጥ የየቀለሙን ድንበር መለየት የሚቻለው እንዴት ነው? ስምሳሌ፣ ከላይ በተሰጠው ምዕላድ ውስጥ /ስ/ የተዋቀረው ከሁለተኛው ቀለም አናባቢ ጋር ነው። ከመጀመሪያው ቀለም አናባቢ ጋር አዋቅረን ቀለሞቹ /አስ-/ እና /-አ/ ናቸው፣ ለማለት አንችልም ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው ተገቢ ነው። የትኛው ተናባቢ ከየትኛው አናባቢ ጋር እንደሚዋቀር የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም በማንኛውም ቁዋንቁዋ፣ በባለ ብዙም ይሁን በባለ ተራ ቀለም ውስጥ ያለውን ያወቃቀር ስርዓት እንደሚከተለው እናቀርባለን።

(ሀ) መጀመሪያ ለቀለማዊ መዋቅር አይቀሬ የሆነው ከፍል አናባቢ ስለሆነ፣ እሱን ሰይተን እናወጣለን፣

(ለ) ያወጣነውን አናባቢ፣ በግራው በኩል ከሚገኝ አንድ ተናባቢ ድምፅ ጋር እናቀናጀዋለን፣


(መ) በሶስተኛ ደረጃ ይህንኑ አናባቢ በቀኙ በኩል ከሚገኝ አንድ ሌላ ተናባቢ ጋር እናቀናጀዋለን፤

(ሰ) ይህንን አድርገን ስንጨርስ፣ ያልተቀናጀ (ተራፊ) ተናባቢ ካለ፣ ይህን ተናባቢ ከአናባቢው ቀኝ ጎን ከሚገኘው ጨራሽ ተናባቢ ጋር እናዳብለዋለን።

በዚሁ ሰርዓት መሰረት ለአብነት *አላኦጋገርናቸውም* የሚለውን ቃል አንውሰድና ቀለማዊ አወቃቀሩን እንመልከት።

መጀመሪያ ቃሉን በፎነማዊ አፃፃፍ እንደሚከተለው እንፅፈዋለን። ከዚያ በሁዋላ አናባቢዎቹን እየመረጥን፣ አናታቸው ላይ መስመር በማቆም እንደሚከተለው አንለያቸዋልን።


(ሀ)



3

ከዚህ ቀጥለን እነዚህን አናባቢዎች በየግራ ጎናቸው በኩል ካለው ተናባቢ ጋር እንደሚከተለው እናያይዛቸዋለን።


(ለ)



4

አሁን ደግሞ እነዚህኑ አናባቢዎች በየቀኝ ጎናቸው በኩል ካለው ተናባቢ ጋር እንደሚከተለው አናገናኛቸዋለን።


(መ)



5

ይህን ካደረግን በሁዋላ የሚተርፍ ተናባቢ ቢኖር፣ በቀኝ ጎኑ በኩል ካለው ሌላ ተናባቢ ጋር እናገናኘዋለን። በዚህም መሰረት በቃሉ መጨረሻ ላይ የምትገኘው /ም/፣ ቀድሞአት ከሚገኘው ከ/ው/ ጋር ትያያዛለች። በዚህ አካሄድ የቃሉ ቀለሞች የሚከተሉትን ይመስላሉ ።

(ለ)



6

በመጨረሻ የቃሉ ቀለሞች /እ - ልእን -ንእ - ግእግ -ግእር -ንእች - ችእውም/ መሆናቸውን እንረዳለን። ቃሉ ባለ ሰባት ቀለም ስለሆነ፣ ውስብስብ ነው። የእወቃቀሩ ስርዓት የእግርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የማንኛውም ቁዋንቁዋ ነው። ስርዓቱን በትክክል ከተከተልን፣ የቁ ተናባቢ ከየቁ አናባቢ ጋር መዋቀር እንዳለበት በቀላሉ እንረዳለን። ሰባተኛው ቀለም ሁለት ጨራሽ ተናባቢዎች አሉት። ይሁን እንጅ ከነዚህ ተናባቢዎች ቀጥሎ እንድ አናባቢ ለምሳሌ፣ /እ/ ቢገባ፣ ከሁለቱ ጨራሽ ተናባቢዎች፣ የመጨረሻው፣ ማለትም /ም/፣ ከዚህ አናባቢ ጋር ይዋቀርና /ምእ/ የሚል ስምንተኛ ቀለም ይፈጥራል። ይህ ሲሆን፣ ሰባተኛው ቀለም እንድ ጨራሽ ተናባቢ ብቻ ይኖረዋል። በዚህ አካሄድ፣ የእግርኛ መደበኛ ወይም አይነተኛ የቀለም እወቃቀር፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ /ተእተ/ የሚል ስርዓት እንደሚከተል ያሳያል።

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የሚዋቀሩ ቀለሞች ዝግና ክፍት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ዝግ የሚባሉት ጨራሽ ተናባቢ ያላቸው ሲሆኑ፣ ክፍት የሚባሉት ጨራሽ የሌላቸው ናቸው። ከላይ በተራ ቁጥር (6) ከተመለከቱት ሰባት ቀለሞች ውስጥ የመጀመሪያውና ሰለተኛው ብቻ ክፍት ናቸው።

ፎኒሞች ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ቀለምን ለመፍጠር ሲዋቀሩ ርስበርስ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በራሳቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊያለከትሉ ይችላሉ። ለውጡን የሚያለከትሉት ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች ይባላሉ። የለውጡን ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ድምፀ ልሳናዊ ሂደት

ከፍ ሲል ወደ ተነሳንበት የፎኒሞች ቅንጅት እንደገና እንመለስና በአቀነጃጀቱ ምክንያት ፎኒሞቹ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በተቃናጅ ፎኒሞች ላይ ለለሚደርሰው ለውጥ እንወያይ። ከዚያ በፊት ግን ከሁለት ቃላት ጋር እንተዋወቅ። እነዚህም <u>ላዕላይ</u> እና <u>ታህታይ</u> የሚሉት ናቸው። በውይይታችን ላይ እየደጋገሙ ለለሚመጡ፣ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆኑልን ይገባል። ላዕላይ ማለት እንደበታዊ፣ ማለትም ከአንደበት የሚወጣና በጆሮ የሚሰማ ማለት ነው። ታህታይ ደግሞ አዕምሮአዊ፣ ማለትም በአዕምሮአችን ብቻ የሚለማንና የምናውቀው፣ ግን በአንደበታችን የማናወጣው፣ ማለት ነው። አዕምሮአዊ የሆነ ነገር ረቂቅ ሲሆን፣ አንበደበታዊ የሆነ ደግሞ ግዝፍ ነው፤ እንደ ምላስ ባለ ግዝፍ የአንደበት አካል ለለሚፈጠርና በጆሮም ለለሚሰማ። ፎኒሞች አዕምሮአዊ ለለዚህም ረቂቅ ናቸው። ይሁን እንጅ አካላዊ፣ ማለትም አንደበታዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው በንግግር ጊዜ ከአዕምሮ ወጥተው በአንደበት አካላት እማካኝነት ሲፈጠሩ ወይም ሲገዝፉ ነው። እያንዳንዱ ፎኒም በአዕምሮ ውስጥ ረቂቅ የሆነ ገፅታ ሲኖረው፣ በአንደበት አማካኝነት በመካነ ፍጥረት ላይ በሚፈጠርበት ጊዜ አካላዊ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ፎኒም ቢያንስ እንድ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል። ከዚህ ልዩነት በመነሳት፣

በመጨረሻ የቃሉ ቀለሞች /አ - ልአን -ንአ - ግአግ -ግአር -ንአች - ችአውም/ መሆናቸውን አንረዳለን። ቃሉ ባለ ሰባት ቀለም ለሰሆነ፣ ውስብስብ ነው። የአወቃቀሩ ስርዓት የአግርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የማንኛውም ቁዋንቁዋ ነው። ስርዓቱን በትክክል ከተከተልን፣ የቱ ተናባቢ ከየቱ አናባቢ ጋር መዋቀር አንዳለበት በቀላሉ አንረዳለን። ሰባተኛው ቀለም ሁለት ጨራሺ ተናባቢዎች አሉት። ይሁን እንጅ ከነዚህ ተናባቢዎች ቀጥሎ አንድ አናባቢ ለምሳሌ፣ /አ/ ቢገባ፣ ከሁለቱ ጨራሺ ተናባቢዎች፣ የመጨረሻው፣ ማለትም /ም/፣ ከዚህ አናባቢ ጋር ይዋቀርና /ምአ/ የሚል ስምንተኛ ቀለም ይፈጥራል። ይህ ሲሆን፣ ሰባተኛው ቀለም አንድ ጨራሺ ተናባቢ ብቻ ይኖረዋል። በዚህ አካሄድ፣ የአግርኛ መደበኛ ወይም አይነተኛ የቀለም አወቃቀር፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ /ተአተ/ የሚል ስርዓት አንደሚከተል ያሳያል።

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የሚዋቀሩ ቀለሞች ዝግና ክፍት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ዝግ የሚባሉት ጨራሽ ተናባቢ ያላቸው ሲሆኑ፣ ክፍት የሚባሉት ጨራሽ የሌላቸው ናቸው። ከላይ በተራ ቁጥር (6) ከተመለከቱት ሰባት ቀለሞች ውስጥ የመጀመሪያውና ሰስተኛው ብቻ ክፍት ናቸው።

ፎኒሞች ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ቀለምን ለመፍጠር ሲዋቀሩ ርስበርስ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በራሳቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለውጡን የሚያስከትሉት ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች ይባላሉ። የለውጡን ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ድምፀ ልሳናዊ ሂደት

ከፍ ሲል ወደ ተነሳንበት የፎኒሞች ቅንጅት እንደገና እንመለስና በአቀነጃጀቱ ምክንያት ፎኒሞቹ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በተቃናጅ ፎኒሞች ላይ ስለሚደርሰው ለውጥ እንወያይ። ከዚያ በፊት ግን ከሁለት ቃላት ጋር እንተዋወቅ። እነዚህም <u>*ሳዕላይ*</u> እና <u>*ታህታይ*</u> የሚሉት ናቸው። በውይይታችን ላይ እየደጋገሙ ስለሚመጡ፣ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆኑልን ይገባል። ሳዕላይ ማለት አንደበታዊ፣ ማለትም ከአንደበት የሚወጣና በጆሮ የሚሰማ ማለት ነው። ታህታይ ደግሞ አዕምሮአዊ፣ ማለትም በአዕምሮአችን ብቻ የሚሰማንና የምናውቀው፣ ግን በአንደበታችን የማናወጣው፣ ማለት ነው። አዕምሮአዊ የሆነ ነገር ረቂቅ ሲሆን፣ አንበደበታዊ የሆነ ደግሞ ግዝፍ ነው፤ አንደ ምሳሌ ባለ ግዝፍ የአንደበት አካል ስለሚፈጠርና በጆሮም ስለሚሰማ። ፎኒሞች አዕምሮአዊ ስለዚህም ረቂቅ ናቸው። ይሁን እንጅ አካላዊ፣ ማለትም አንደበታዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው በንግግር ጊዜ ከአዕምሮ ወጥተው በአንደበት አካላት አማካኝነት ሲፈጠሩ ወይም ሲገዝፉ ነው። አያንዳንዱ ፎኒም በአዕምሮ ውስጥ ረቂቅ የሆነ ገፅታ ሲኖረው፣ በአንደበት አማካኝነት በመካነ ፍጥረት ላይ በሚፈጠርበት ጊዜ አካላዊ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል። በዚህም ምክንያት አያንዳንዱ ፎኒም ቢያንስ አንድ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል። ከዚህ ልዩነት በመነሳት፣

አዕምሮአዊ ገፅታውን ታህታይ፣ አካላዊ ገፅታውን ላዕላይ አያልን አንጠራዋለን። ይህ በፎኒም ብቻ ላይሆን፣ ወደፊት እንደምናየው፣ በምዕላድ፣ በቃላት፣ በሀረጋትና በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይም የሚታይ አጠቃላይ የቁዋንቁዋ ባህሪ ነው[13]።

ፎኒሞች ቀለማትን ለመመሰረት ርስበርስ ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቅርፅ ታህታይ ነው። በዚህ ደረጃ ማንኛውም ፎኒም አንድ ቅርፅ ብቻ አለው። ይህ ቅርፅ ከአንደበት በሚወጣበት፣ ማለትም በንግግር ጊዜ በአንደበት አካላት ሲፈጠር፣ መልኩ በከፊል ወይም በሙሉ ሲለወጥ ይችላል። ለዚህም ከአንድ በላይ የሆኑ አንደበታዊ (ላዕላይ) ቅርፆች ይኖሩታል። እነዚህም የተለያዩ ቅርፆች ዘረ ፎኒም አንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል። የሰውኩ መንስዔ አንዱ ፎኒም ከሚቀድመው ወይም ከሚከተለው ሌላ ፎኒም ጋር የሚፈጥረው ጉርብትና አና ይህም የሚያስከትለው ንክኪ ብሎም የባህሪ መወራረስ ሂደት ነው። ሁለቱን ቅርፆች ለመለየት ላዕላዩን በቅንፍ፣ ታህታዩን በዕዝባር ውስጥ አንፅፈዋለን። የታህታዊው አፃፃፍ ፎኒማዊ ሲባል፣ የላዕላዊው ዘረ ፎኒማዊ ወይም ንበታዊ ይባላል። ይህንም ቀደም ሲል በመጠኑም ቢሆን አይተነዋል። ይሁን አንጅ፣ ሁኔታውን <u>በርቺ</u> የሚለውን ቃል አንውለድና እንደገና በምሳሌ አንረዳው። የቃሉ ስርዓተ ፅህፈታዊ ቅርፅ ያው <u>በርቺ</u> ነው። ላዕላይ ዘረ ፎኒማዊ ቅርፁ [ብኧርችኢ] ነው። ታህታይ ቅርፁ ግን /ብኧርችኢ/ ነው። ይህ በአዕምሮአችን የሚለማን ቅርፅ ነው። በሁለቱ ቅርፆች መካከል ያለው ልዩነት፣ በታህታዩ ቅርፁ ውስጥ /ት/ የነበረችው ተናባቢ የድድ ድምፅ በላዕላዩ ቅርፅ ወስጥ ወደ ድላንቃ ተለውጣ [ች] መሆንዋ ነው።


አዚህ ላይ [ች] በታህታዩ ቅርፅ ውስጥ /ት/ ለመሆንዋ ማሰረጃው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ይችላል። ድምፅዋ /ት/ ለመሆንዋ ማሰረጃው፣ ለተባዕ ታይ ዖታ የምንጠቀምበት የቃሉ ቅርፅ ነው። አሱም በርታ [ብኧርትኣ] ነው። ከ[ር] ቀጥሉ የምትታየው ድምፅ [ት] ነች። የቃሉ ታህታይ ቅርፅም /ብኧርትኣ/ ነው። ከላዕላዩ ቅርፅ ጋር አንድ አይነት ነው። በ/ብኧርትኣ/አና በ/ብኧርትኢ/ መካከል ያለው ልዩነት በመጨረሻዎቹ አናባቢዎች ላይ ብቻ ነው። ይኸውም የ/ብኧርትኢ/ የመጨረሻ አናባቢ /ኢ/ ሲሆን፣ የ/ብኧርትኣ/ የመጨረሻ አናባቢ /ኣ/ መሆኑ ነው። ከዚህ በሁዋላ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ /ብኧርትኢ/ በሚለው ታህታይ ቅርፅ ውስጥ /ት/ የነበረችው ፎኒም [ብኧርችኢ] በሚለው ላዕላይ ቅርፁ ውስጥ አንዲት ወደ [ች] ተለወጠች? ከተለወጠችስ <u>በርታ</u> በሚለው ላይ ለምን አልተለወጠችም የሚል ነው? ወደፊት ጉዳዩን በዝርዝር አሰከምናየው ድረስ

---

[13] ባህሪንቱ ግን የቁዋንቁዋ ብቻ አይደለም፣ ማንኛውም ነገር ረቂቃዊና አካላዊ ባህሪ አለው። ለምሳሌ፣ የሰው ተፈጥሮ በከፊል አካላዊ (ሲጋዊ) በከፊል ደግሞ መንፈላዊ (ረቂቅ) ነው። ነፍስና ሲጋ አያልን አንዱን ከሌላው እንለያለን። ሲጋ ተሰዋዋሯ ነው፣ ይከሳል፣ ይጠቁራል፣ ያድጋል፣ ይጫጫል፣ ይሞታል፣ ይበሰብሳል። ነፍስ ግን አትሰዋወጠም፣ አትሞትም፣ ዘላለማዊት ናት ይባላል።

/ብኧርትኢ/ በሚለው ውስጥ /ት/ ወደ [ች] የምትለወጠው /ኢ/ ከሚለው አናባቢ በፊት ገብታ ስትገኝ ብቻ ነው ብለን፣ አናልፈዋለን።

የሁለቱን ቃላት ቀለማዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



ከዕፀ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ ምዕላዱ ባለሁለት ቀለም ሊሆን፣ የመጀመሪያው ቀለም ዝግ ነው። በተናባቢ ይፈፀማል። ሁለተኛው ፈሪሽ ተናባቢ ስለሌለው ክፍት ነው። ለውጡም የሚካሄደው በሁለተኛው ቀለም ክፋች ተናባቢ በሆነችው በ/ት/ ላይ ነው። መንስዔውም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ከጎንዋ የሚገኘው /ኢ/ የሚለው አናባቢ ነው። አሁን ወደ ርዕሰ ጉዳያችን እንመለስና ሌሎች ድምፅ-ልሳናዊ ሂደቶችን እንመልከት።

ምስለት

ክፍ ሲል እንደተገለፀው፣ በአንድ ቅንጅት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ፎኒሞች በትንጅቱ ውስጥ በሚፈጥሩት ጉርብትና ምክንያት፣ የአንዱ ባህሪ ወደ ሌላው ሊጋባ ይችላል። በዚህም ተጋቦት ምክንያት አንዱ ሌላውን ሊመስል ይችላል። የመመሳሰሉን ሂደት ምስለ-ሽ፣ ውጤቱን ደግሞ <u>*ምስለት*</u> እንለዋለን። አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ይመሳሰላል የምንለው የጎረቤቱን ድምፅ ባህሪ በከፊል ወይም በሙሉ ሲወስድና አሱን ሲመስል ነው። በዚሁ መሰረት የምስለቱን ሂደት ከፊል ወይም ሙሉ ምስለ-ሽ እንለዋለን። አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳስሎአል የምንለው፣ ጎረቤቱ በሚፈጠርበት ቦታና ሁኔታ አሱም

ሲፈጠር ነው። ይህም ከጎረቤቱ ጋር በመካነ ፍጥረቱና በባህርየ ፍጥረቱ አንድ ሲሆን ነው። ከጎረቤቱ ጋር በከፊል የሚመሳሰለው፣ ከሁለቱ በአንዱ ብቻ ሲመሳሰል ነው።

ሁለቱን ባህሪ ተወራራሽ ድምፆች መሳይና እለመሳይ አንላቸዋለን። መሳዩ ባህሪ ወሳጁ ሲሆን፣ እስመሳዩ ባህሪ ሰጭው ነው። መሳዩ ድምፅ ሁለት ቅርፅ ይኖረዋል። አንዱ የጎረቤቱን ባህሪ ከመውሰዱ በፊት የነበረው ሲሆን፣ ሁለተኛው ባህሪውን ከወሰደ በሁዋላ የሚያገኘው ነው። በዚሁ መሰረት የመጀመሪያውን ታህታይ፣ ሁለተኛውን ላዕላይ ቅርፅ አንለዋለን። ለምሳሌ /ብኧርትኢ/ በሚለው ውስጥ የምትታየው /ት/ የምትለዋ ፎኒም /ኢ/ የሚለውን የፊት አናባቢ ባህሪ ስትወስድ [ች] ትሆናለች። ስለዚህም ፎኒምዋ ሁለት ቅርፅ አላት፣ /ት/ እና [ች]። ከዚህ መንደርደሪያ አንፃር የተለያዩ የምለሳት እይነቶችን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ከናፍራዊነት

ከናፍራዊነት ከምለሳት አይነቶች አንዱ ነው። የሚከሰተውም እንድ በመካነ ፍጥረቱ የከናፍር ያልሆነ ድምፅ ከናፍራዊ በሆነ ድምፅ ንክኪ ምክንያት ወደ ከናፍር ድምፅ ሲለወጥ ነው። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን።

/አንብኧለስኣ/	[አምብኧለስኣ]	አንበሳ	1
/አንብኧጥጣ/	[አምብኧጥጣ]	አንበጣ	
/ክኧንፍኧር/	[ክኧምፍኧር][14]	ክንፈር	

እነዚህ ቃላት አያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ተፅፈዋል። መጀመሪያ በአዝባር ውስጥ፣ ከዚያ በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ፣ በመጨረሻ ደግሞ በመደበኛው የአፃፃፍ ስርዓት ተመዝግበዋል። በአዝባር ውስጥ የሚታየው ቅርፃቸው ፎኒማዊ፣ ማለትም አዕምሮአዊ ሲሆን፣ በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ የሚታየው ዘረ ፎኒማዊ፣ ማለትም አንደበታዊ ወይም ንበታዊ ቅርፅ ነው። ፎኒማዊ ስንል ታህታይ፣ ዘረ ፎኒማዊ ስንል ላዕላይ ቅርፅ ማለታችንን እንርሳ። የታህታይና ላዕላይ ልዩነት ቀደም ሲል እንደተገለፀው ነው። ላዕላዩ የታህታዩ አንደበታዊ ክሳች ነው። አንዳንድ ጊዜ በታህታዩ ውስጥ የሌለ ባህሪ ሲያሳይ ይችላል። በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው ስርዓተ ፅሀፈታዊ፣ ማለትም ፊደላዊ ቅርፅ ነው። ይህ አፃፃፍ ከላዕላይም ሆነ ከታህታይ ቅርፅ ጋር ግንኙነት ላይኖረው ይችላል። መሰረቱም ስነ-ልሳናዊ ሳይሆን፣ ባህላዊ

[14] እዚህ ላይ [ም] የሚለው ድምፅ ሙሉ በሙሉ የከናፍር አይደለም። የታችኛው ከንፈር የላይኛውን የፊት ጥርስ ሲነካ የሚፈጠር ስለሆነ፣ የስንፈር (የጥርስና የከንፈር) ድምፅ ነው። በአለማቀፋዊው የስነ-ልሳን ፊደል ይህ ድምፅ የሚወከለው በ[ɐ] ነው ። የሙሉው ቃል ዘረ-ፎኒማዊ ቅርፅ በዚህ ፊደል ሲፃፍ [kämɐfär] የሚል ይሆናል።

ለውጥ፣ ማለትም ሰልጣኔ ያመጣው የፅሀፈት ጥበብና የአፃፃፍ ስርዓት ነው። ይህም እንደየሰልጣኔው አይነት ይለያያል። ለምሳሌ፣ የአረብኛው አፃፃፍ ከእንግሊዝኛው፣ የፈረንሳይኛው ከቻይንኛው፣ ወዘተ፣ ይለያል።

በዘረ ፎኒማዊው (ንበታዊ) ቅርፅና በፎኒማዊው ቅርፅ መካከል መጠነኛ ልዩነት ይታያል። ይኸውም በፎኒማዊው ቅርፅ /ን/ ሆና የምትታየው፣ በዘረ-ፎኒማዊው ቅርፅ [ም] መሆንዋ ነው። ጥያቄው ታድያ ይህ ለውጥ ከየት መጣ? የሚል ነው። ለዚህ በፎኒማዊው ቅርፅ ውስጥ የ/ን/ን እስላሰፍ እንደገና ማየት ያስፈልጋል። ይህች ፎኒም የገባችው ከ/ብ/ ቀድማ ነው። /ብ/ ደግሞ እግድ የከናፍር ድምፅ ነች። እየር በአፍ በኩል ሲያልፍ፣ ከናፍር ተጋጥመው ሲሳቀቁ የምትፈጠር እግድ ድምፅ ነች። /ን/ ስርናዊ የድድ ድምፅ ነች። እየር በስርን በኩል ሲያልፍና የምላስ ጫፍ ድድን ሲነካ ትፈጠራለች። በሁለቱ ፎኒሞች መካከል ያለው ልዩነት የመካነ ፍጥረት፣ ማለትም የመፈጠሪያ ቦታ ብቻ ነው። ሁለቱም ነፃሪ ስለሆኑ፣ በባህርየ ፍጥረታቸው አንድ ናቸው። በላዕላይ ወይም ዘረ-ፎኒማዊ ቅርፅ ውስጥ /ን/ ወደ [ም] የተለወጠችው፣ በመካነ ፍጥረት ነው። የድድ የነበረችው ድምፅ የከናፍር ሆናለችና። ወደ ከናፍር ድምፅነት የተለወጠችውም፣ ከጎንዋ በሚገኘው የከናፍር ድምፅ፣ ማለትም በ/ብ/ ምክንያት ነው። የዚህ ድምፅ ከናፍራዊነት ወደ እስዋ ተጋብቶአል። ስለዚህም /ን/ ወደ [ም] ተለወጠችና በመካነ ፍጥረትዋም /ብ/ን ልትመስል ቻለች።

ምስስሉሹ ግን ከፊል ነው። ምክንያቱም አንድ የባህርየ ፍጥረት ልዩነት በመካከላቸው አለ። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ሁለቱም ስርናዊና ነፃሪ ናቸው። ይሁኑ እንጅ፣ ከእየር እወጣጥ እንፃር፣ ሁለቱ ድምፆች አሁንም የተለያዩ ናቸው። /ብ/ አግድ ስትሆን፣ /ን/ ልቅ ነች። ስትፈጠር አየር ሳይታገድ በነፃ በሰርን በኩል እድርጎ ይወጣል። /ን/ ሙሉ በሙሉ /ብ/ን ብትመስል ኖሮ፣ ቅርፅዋ [ም] ሳይሆን [ብ] ይሆን ነበር። ስለዚህም [እምብኧለስእ] የነበረው ቃል [እብብኧለስእ] ይሆን ነበር። ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለው ቃል አይደልም። ስለዚህም አይባልም።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ታህታዊው ቅርፅ አዕምሮአዊ ስለሆነ፣ ለላዕላዊው ቅርፅ መሰረት ነው። ላዕላዩ የታህታዩ ልዋጭ ወይም ክሳች ነውና። ልዋጩና መሰረታዊው ድምፅ ያላቸውንም ዝምድና በ<u>ቅምር</u> ማሳየት ይቻላል። ቅምሩ እንድ ታህታይ ቅርፅ ወደ ላዕላይ ቅርፅ እንዲት እንደሚለወጥ የሚያሳይ ስለሆነ፣ <u>*ለዋጭ ህግ*</u> እንለዋለን። በዚሁ መሰረት ከፍ ሲል ያየነውን ለውጥ እንደሚከተለው እድርገን እናሳያለን።

/ን/ ⟶ [ም] / - /ብ/ 2

ይህ ቅምር /ን/ ከ /ብ/ በፊት ስትገባ ወደ [ም] ትለወጣለች የሚል ነው። ይበል እንጅ፣ /ን/ ወደ [ም] የምትለወጠው ከ/ብ/ በፊት ብቻ ለትገኝ አይደለም። ለምሳሌ፣ [ከኧምፍኧር] የሚለው ቃል ታህታይ ቅርፅ /ከኧንፍኧር/ ነው። በዚህ

ውስጥ ደግሞ /ን/ የምትገኘው ከ/ፍ/ በፊት ነው። ይሁን አንጅ [ከኽምፍኽር] በሚለው ውስጥ አለዋም ወደ [ም] ተለውጣለች። በቅምሩ መሰረት ይህ መሆን አልነበረበትም። ምክንያቱም /ን/ን የተከተለችው ፍኒም /ብ/ ሳትሆን፣ /ፍ/ ነችና። ሁኔታው /ን/ ከ/ፍ/ በፊት ለትገባም ወደ [ም] እንደምትለወጥ ይጠቁማል። ይህ ከሆነ፣ ሁለቱንም የመለወጫ እውዶች እንዲያሳይ፣ ከላይ የተመለከተው ቅምር እንደሚከተለው ሆኖ መሻሻል ይኖርበታል።

$$/ን/ \longrightarrow [ም] \quad / \quad \left\{ \begin{matrix} /ብ/ \\ /ፍ/ \end{matrix} \right\} \qquad 3$$

ይህ ቅምር /ን/ ከ/ብ/ ወይም ከ/ፍ/ በፊት ለትገባ፣ ወደ [ም] ትለወጣለች የሚል ነው። ለለዚህ ከላይ በ-ኮራ ቁጥር (2) ክተመለከተው ቅምር ሰፋ ያለ የምለሰሉሽ አውድን ያሳያል። ሆኖም ይህም ቢሆን ድክመት ይታይበታል። ይኸውም /ን/ ወደ [ም] የምትለወጠው ከ/ብ/ ወይም ከ/ፍ/ በፊት ለትገባ ነው አያለ፣ ድምፆቹን መዘርዘሩ ነው። አንድ ቅምር እንደዚህ አያለ ያንድን ድምፅ መለወጫ አውድ የሚዘረዝር ከሆነ፣ ቅምር መሆኑ ይቀርና ተራ አባባል ይሆናል። በሌላ አነጋገር፣ አጠቃላይ ሳይሆን ዘርዛሪ ይሆናል። አጠቃላይነት ደግሞ የቅምር ዋነኛ መለያ ባህሪ ነው። ክዚህ አንፃር ቅምሩን ለማሻሻል የ/ብ/ን እና የ/ፍ/ን የጋራ ባህሪ አውጥቶን፣ ከዚያ ባህሪ አኩዋያ የለወጡን አውድ በጥቅል ማለየት ይኖርብናል።

የ/ብ/ እና የ/ፍ/ የጋራ ባህሪ <u>ከናፍራዊነት</u> ነው። ይህም ሁለቱም ድምፆች በከናፍርዚአማካኝነት ይፈጠራሉ ማለት ነው። /ብ/ ሙሉ በሙሉ የከናፍር ድምፅ ስትሆን፣ /ፍ/ የከናፍር ድምፅነትዋ በከፊል ነው። ለዚህም ምክንያቱ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ይህች ድምፅ በታችኛው ከንፈርና በላይኛው የፊት ጥርስ ንክኪ ለለምትፈጠር ነው። ለለዚህም በከፊል የጥርስ ድምፅ ነች። አንግዲህ የጋራ ባህሪያቸው በከፊልም ቢሆን ከናፍራዊነት ከሆነ፣ በዚሁ ባህሪ መሰረት ከላይ በ-ኮራ ቁጥር (3) የ-ተመለከተውን ቅምር እንደሚከተለው አድርገን ማሻሻል ይኖርብናል።

$$\begin{bmatrix} +ለ \\ -ፊት \\ -ላይ \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + ስ \\ + ፊት \\ - ላይ \end{bmatrix} / \begin{bmatrix} - ተ \\ + ከ \end{bmatrix} \qquad 4$$

ተ = ተነባቢ ስ = ሰርን ከ = ከናፍራዊ

ይህ ቅምር ድኅዋ ([- ፊት]) የሆነ የሰርን ድምፅ፣ ከናፍራዊ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገባ፣ ወደ ከናፍራዊ የለርን ድምፅነት ይለወጣል የሚል ነው። አጠቃላይ

ባህሪን እንጅ ከዚህ ወይም ከዚያ ድምፅ በፊት አያለ ስለማይዘረዝር በተራ ቁጥር (3) ከተጠቀሰው ቅምር የበለጠ እጠቃልይነት አለው። ይህን ከተገነዘብን፣ ወደ ሌላ የምስለት አይነት እንሂድ።

ከፊል ላንቃዊነት

ይህ የምስለት አይነት በተናጠላዊ ፍጥረታቸው ላንቃዊ ያልሆኑ ድምፆች በቅንጅታዊ ባህሪያቸው ምክንያት ከፊል ላንቃዊ የሚሆኑበት ሂደት ነው። የሚከተሉት ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ናቸው።

/ክኢስ /	[ክ^{ዕ}ኢስ]	ኪስ	I
/ብኤት/	[ብ^{ዕ}ኤት]	ቤት	
/ጥኢስ/	[ጥ^{ዕ}ኢስ]	ጢስ	
/ምኧልትኢ/	[ምኧልት^{ዕ}ኢ]	መልቲ	
/ክኧይስኢ/	[ክኧይስ^{ዕ}ኢ]	ክይሲ	

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ በእዝባር ውስጥ የተመለከተው ነው። ላዕላይ ቅርፃቸው በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ነው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በታህታዩ ውስጥ /ክ፣ብ፣ጥ፣ት፣ስ/ የነበሩት ፎኒሞች በላዕላዩ ውስጥ [ክ^{ዕ}፣ብ^{ዕ} ፣ጥ^{ዕ} ፣ት^{ዕ} ፣ስ^{ዕ}] ሆነው መከሰታቸው ነው። /ክ/ እና /ብ/ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የትናጋና የከናፍር ድምፆች ናቸው። /ጥ፣ት/ እና /ስ/ ደግሞ የድድ ድምፆች ናቸው። [ክ^{ዕ}፣ብ^{ዕ} ፣ጥ^{ዕ} ፣ት^{ዕ} እና ስ^{ዕ}] እንደ ቅደም-ተከተላቸው የእነዚህ ድምፆች ከፊል ላንቃዊ አቻዎች ናቸው። ባጭሩ ላንቃዊ ያልነበሩት ድምፆች ወደ ከፊል ላንቃዊነት ተለውጠዋል ማለት ነው።

ለዚህ ለውጥ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድን ነው? ለምሳሌ ኪስንና [ክ^{ዕ}ኢስ] እና ከይሲን [ክኧይስ^{ዕ}ኢ] እያነፃፀርን እንመልከት። [ክ^{ዕ}ኢስ] ውስጥ ያለችው [ክ^{ዕ}] ከፊል ላንቃዊ ሆናለች። በመሆንዋም [^{ዕ}] በሚል ምልክት ተጠቁማለች። [ክኧይስ^{ዕ}ኢ] በሚለው ውስጥ ግን [ክ] ላይ የተጨመረ ምልክት የለም። ምልክት ያለው [ስ^{ዕ}] ላይ ነው። [ክኧይስ^{ዕ}ኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ላንቃዊ አይደለችም ማለት ነው። [ክ^{ዕ}ኢስ] ውስጥ ያለችው [ክ^{ዕ}] ላንቃዊ ስትሆን፣ [ክኧይስ^{ዕ}ኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ለምን ላንቃዊ አልሆነችም? ለዚህ የምንሰጠው መልስ ከላይ ለጠየቅነውም ጥያቄ ምላሽ ይሆናል። መልሱ ከሁለቱ ድምፆች የአገባብ ልዩነት ጋር የተያያዘ ነው። [ክኧይስ^{ዕ}ኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] የገባችው [ኧ] ከሚለው የመሀል እናባቢ ቀድማ ነው። [ክ^{ዕ}ኢስ] ውስጥ ያለችው [ክ^{ዕ}] ግን የገባችው ከ[ኢ] በፊት ነው። ይህችም አናባቢ ላየኛና ፊተኛ ነች። ይህን ቀደም ሲል ከተሰጠው የአናባቢ ስንጠረዥ መመልከት ይቻላል። [ክ] ወደ [ክ^{ዕ}]

ልትለወጥ የቻለችውም የ[ኢ]ን የላየኛነት ባህሪ በመውሰድ ነው። ስርዓቱን እንደሚከተለው እድርጎ ማሳየት የቻላል።

$$\begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ -\ \text{ላይ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ +\ \text{ላይ} \end{bmatrix} \ / \ \text{-} \begin{bmatrix} +\ \text{እ} \\ +\ \text{ላይ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

እስካሁን የተመለከትነው ሁለት ተጎራባች ድምፆች በመካነ ወይም በባህርየ ፍጥረታቸው በከፊል ሲመሳሰሉ ነው። በሁሉም ምሳሌዎች ውስጥ የሚመሳሰሉት ድምፆች አስላለፍ መሳይ-አሰመሳይ የሚል ቅደም-ተከተል የያዘ ነው። ይህም መሳዩ ድምፅ ካሰመሳዩ ድምፅ ቀድሞ ይገኛል ማለት ነው። በዚህ አይነት አሰላለፍ የሚከሰት የምሰሰሉሽ ሂደት <u>መላሽ</u> ምሰሰሉሽ ይባላል። መላሽ የሚባልበት ምክንያት ባህሪው ካሰመሳዩ ድምፅ ወደ መሳዩ ድምፅ የሚመለስ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ ከፍ ሲል በሚታየው የመጨረሻው የምሰሰሉሽ ሂደት ውስጥ፣ ከፊል ላንቃዊነት ወይም ላየኛነት የአሰመሳዩ ድምፅ፣ ማለትም የ/ኢ/፣ ባህሪ ነው። /ኢ/ ደግሞ ከመሳዩ ተናባቢ በሁዋላ፣ ማለትም ከመሳዩ ድምፅ በስተቀኝ ነው የሚገኘው። የሁለት ድምፆች አሰላለፍ ይህ ከሆነ፣ የላንቃዊነቱ ባህሪ ከላየኛው አናባቢ፣ ከ/ኢ/ ወደ ተናባቢው /ክ/ ሲጋባ የቻለው ወደ ሁዋላ፣ ማለትም ወደ ግራ ተመልሶ ነው። ስለዚህም ሂደቱ መላሽ ሊባል ችሎአል። ሁኔታው አንድ ቀዳሚ፣ ማለትም ቀድሞ ከእንደበት የሚወጣ፣ ድምፅ የተከታዩን ድምፅ ባህሪ ሲወስድ የሚያሳይ ነው። ባጭሩ መላሽ ምሰሰሉሽ ቀዳሚው መሳይ ተከታዩ አሰመሳይ የሆነበት ሂደት ነው።

መላሽ ምሰሰሉሽ እንዳለ ሁሉ፣ <u>ገሰጋሽ</u> ምሰሰሉሽ የሚባል ሂደትም አለ። ይህ አይነቱ ምሰሰሉሽም አንድን ባህሪ ከቀኝ ወደ ግራ የሚመልስ ሳይሆን፣ ባህሪውን ከግራ ወደ ቀኝ በመውሰድ፣ በዚያ ቦታ ለሚገኝ ድምፅ የሚያጋባ ሂደት ነው። በቁዋንቁዋው ውስጥ በስፋት የሚታይ ሂደት አይደለም። ይሁን እንጅ፣ ለአብነት የሚሆኑ ምሳሌዎች አይጠፉም። የሚገኙት በአዲስ አበባ ሳይሆን፣ በአብዛኛው በጎጃም አማርኛ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

/ውኧጥትኦ/	[ውኧጥጥኦ]	ወጠ	3
/ምኧጥትኦ/	[ምኧጥጥኦ]	ጠጠ	

በእዝባሮቹ ውስጥ በሚታዩት ምሳሌዎች ውስጥ /ት/ የነበረቸው ድምፅ በግዕዘኑ ቅንፍ ውስጥ [ጥ] ሆና ትታያለች። /ት/ እግድ የድድ ድምፅ ስትሆን፣ /ጥ/ እግድና ግንቁርታዊ የድድ ድምፅ ነች። ልዩነታቸው በግንቁራታዊነት ነው። ሁለቱ ድምፆች ከላይ በእዝባሩ ውስጥ በሚታዩበት ሁኔታ ተከታትለው ሲገቡ፣ እግድ የድድ ድምፅ የነበረችው /ት/ ወደ ግንቁርታዊነት ትለወጥና በግዕዙ

ውስጥ አንደሚታየው [ጥ] ትሆናለች። የማንቁርታዊነቱን ባህሪ ያገኘችው ቀድሞአት ከገባው ከ/ጥ/ ነው። ባህሪው የሚሄደው ከግራ ወደ ቀኝ ለሰሆነ፣ የምስስሎሹ አይነት ገስጋሽ ነው። ተመሳሳይ የምስለሎሽ ሂደት በአዲስ አበባ አማርኛም አለ። ሁኔታው ዝቅ ብለን ከምናየው ሌላ ድምፅ-ልሳናዊ ሂደት ጋር የተያያዘ ስለሆነ አዚህ ላይ አናየውም። ስለዚህም ወደ ሌላ የምስስሎሽ ሂደት እንሸጋገራለን።

ሙሉ ላንቃዊነት

ሁለት አይነት የላንቃዊነት ደረጃ አለ። አንደኛው አይነት መለስተኛ ወይም ከፊል ያልነው ሲሆን፣ ሂደቱን በቦታው አንደ [ሰ^{ይ}ኤት] እና [ከ^{ይ}ኢስ] ያሉ ምሳሌዎችን አየጠቀስን ለማሳየት ሞክረናል። በታህታይ ቅርፃቸው /ስ/ እና /ክ/ የነበሩት ተናባቢ ድምፆች በላዕላይ ቅርፃቸው ወደ [ሰ^{ይ}] እና [ከ^{ይ}] ሊለወጡ ችለዋል። ለለውጡ ምክንያት የሆነችው ድምፅ /ኢ/ ወይም /ኤ/ ነች። ይህች ድምፅ በተፈጥሮዋ ላየኛ ስለሆነች፣ ከአስዋ ቀድመው የሚገቡ ድምፆችን ወደ ላየኛነት የመለወጥ ባህሪ አላት። ይህም ሂደት ከፊል ላንቃዊነት አንደሚባል ተገልያአል።

ሁለተኛው አይነት ላንቃዊነት ከፍተኛ የሆነ የባህሪ ለውጥ የሚታይበት ሂደት ስለሆነ፣ ሙሉ ላንቃዊነት ይባላል። ከዚህ በታች በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ የሚታዩት ምሳሌዎች የዚህ አይነት ለውጥ የሚካሄድባቸው ናቸው።

/ግኧድኣል-ኢ/	[ግኧድኣይ]	ገዳይ	1
/ብኧርርኣዝ-ኢ/	[ብኧርርኣዥ]	በራዥ	
/ክኧስኣስ-ኢ/	[ክኧስኣሽ]	ከሳሽ	
/ዝኧምኣት-ኢ/	[ዝኧምኣች]	ዘማች	
/ውኧልኣድ-ኢ/	[ውኧልኣጅ]	ወላጅ	
/ዝኧንንኣጥ-ኢ/	[ዝኧንንኣጭ]	ዘናጭ	
/ልኧምምኣን-ኢ/	[ልኧምምኣኝ]	ለማኝ	

እንደነዚህ ያሉ ቃላት አድራጊ ሰሞች ይባላሉ። በሚቀጥለው ከፍል በስፊው አንደምናየው፣ አንድን ድርጊት የሚፈፅምን አካል ወይም ሀይል ያመለክታሉ። በአዝባር ውስጥ የሚታየውን ታህታይ ቅንጅታቸውን ስንመረምር፣ ሁሉም በ/ኢ/ አንደሚጨርሱ አንረዳለን። ይህች ድምፅ ተራ አናባቢ ፎኒም አይደለችም፣ ምዕላዳዊ ፎኒም ነች። በመሆንመዋም ከፍ ሲል ስለ ከፊል ላንቃዊነት ስንወያይ ካየናት ፎኒማዊ /-ኢ/ ትለያለች። ንክኪውም የተፈጠረው በሁለቱ ምዕላዶች፣ ማለትም በአምዶቹና በዚች ምዕላዳዊ ፎኒም መካከል ነው። ከዚች ድምፅ በፊት የሚገኙት የየአምዱ ተናባቢ ድምፆች በሙሉ የድድ ድምፆች ናቸው። ይሁኑ አንጅ፣ በየቅንፉ በሚታየው ላዕላይ ቅርፅ ውስጥ አንደሚታየው፣ የድድ የነበሩት

ድምፆች ወደ (ድ)ላንቃ ድምፅነት ተለውጠዋል። በድዳዊነትና በ(ድ)ላንቃዊነት መካከል ያለው ልዩነት ላየኛነት ነው። ይኸውም ድዳዊ የሆነ ድምፅ [- ላየኛ] ሲሆን፣ (ድ)ላንቃዊ የሆነ ድምፅ [+ ላየኛ] መሆኑ ነው። (ድ)ላንቃ የአፋችን ጣሪያ ስለሆነ፣ በዚያ ላይ የሚፈጠር ማንኛውም ድምፅ [+ ላየኛ] ነው[15]። በዚህ መሰረት ከላይ በእዝባር ውስጥ የሚታዩት ድዳዊ ድምፆች በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው ወደ (ድ)ላንቃዊነት፣ ማለትም ወደ ላየኛነት፣ ተለውጠዋል። የለውጡ ምክንያት [+ ላይ] የሆነችው አናባቢ፣ ማለትም /-አ/፣ ነች። ይህች ድምፅ የላየኛነት ባህሪዋን ለድዳዊያኑ በማጋባት እነሱም [+ ላየኛ] እንዲሆኑ አድርጋለች። /አ/ [+ ላየኛ] የሆነችበት ምክንያት እፈጣጠርዋ የምላስን የፊት ክፍል ወደ ላይ፣ ማለትም ወደ (ድ)ላንቃ የሚያስነሳና ወደላይኛው የፊት ጥርሰ የሚሰብ ስለሆነ ነው።

በመለስተኛው ላንቃዊነት [ትᵒ፣ ድᵒ፣ ጥᵒ፣ ስᵒ፣ ልᵒ፣ ንᵒ፣ ዝᵒ] የነበሩት ድምፆች፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በከፍተኛው ላንቃዊነት ወደ [ች፣ ጅ፣ ጭ፣ ሽ፣ ይ፣ ኝ፣ ወዘተ፣] ሊለወጡ ችለዋል። የመለስተኛዎቹ መካነ ፍጥረት አሁንም ድድ ሲሆን፣ የከፍተኛዎቹ መካነ ፍጥረት ወደ (ድ)ላንቃ ተለውጧል። የባህሪ ብቻ ሳይሆን፣ የመካነ ፍጥረት ለውጥም አድርገዋል።

የዚህ አይነት ለውጥ የሚታየው በአድራጊ ሰሞች ላይ ብቻ አይደለም። በተውላጠ ሰሞች፣ በቅፅሎችና በግሶች ላይም ይከሰታል። ለዚህም የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ)	አንተ	አንቺ	2
	ክሰስ	ክሰሺ	
(ለ)	ረዘመ	ረዣም	
	ቀጠነ	ቀጭን	

በመጀመሪያው ረድፍ ከተዘረዘሩት መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቃላት የመጨረሻ ተናባቢ ድምፆች /ት/ እና / ስ/ ናቸው። የሚቀጥሉት ሁለት ቃላት የመሀለኛ ድምፅ ደግሞ / ዝ/ እና /ጥ/ ናቸው። አራቱም ድምፆች ድዳዊ ናቸው። በሁለተኛው ረድፍ ውስጥ ባሉት ቃላት ውስጥ እነዚሁ ድምፆች ወደ (ድ)ላንቃዊነት ተለውጠው [ች፣ ሽ፣ ዥ፣ እና ጭ] ሆነዋል። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ድምፆቹ ከታቸኛነት ወደ ላየኛነት ተለውጠዋል። የለውጡ መንሰዔ አሁንም /አ/ ነች። የእያንዳንዳቸውን ታሀታይ ቅርፅ እንመልከት።

---

[15] (ድ)ላንቃ በሚለው ቃል መነሻ ላይ የሚታየው (ድ) በቅንፍ ውስጥ እንዲታይ የተደረገው ድምፆቹ ወደ ላንቃና ወይም ወደ ድላንቃ የሚለወጡ መሆናቸውን ለማሳየት ነው።

/አንትኧ/	/አንት-ኢ/	[እንችኢ]	3
/ክ-ሰኧስ/	/ክ-ሰኧሰ-ኢ/	[ክእሰኧሽ]	
/ርኧዝዝ-ም/	/ርኧዝዝ-ኢ-ም/	[ርኧዥዥኢም]	
/ቅኧጥጥ-ን/	/ቅኧጥጥ-ኢ-ን/	[ቅኧጭጭኢን]	

በግልፅ እንደሚታየው፣ የመሀከለኛው ረድፍ ቃላት የመጨረሻ አናባቢ ምዕላዳዊ /-ኢ/ ነች። ከእስዋ እየቀደመ የሚገኘው ተናባቢ /ት፣ለ፣ዝ፣ጥ/ ደግሞ የድድ ድምፅ ነው። በግዕዙ ውስጥ እንደሚታየው፣ እያንዳንዱ የድድ ድምፅ ወደ (ድ)ላንቃ ድምፅ ተለውጦአል። አጠቃላይ የለውጡን ሂደት እንደሚከተለው እናሳያለን።

$$\begin{bmatrix} - \text{ላይ} \\ - \text{ፊት} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{ላይ} \\ - \text{ፊት} \end{bmatrix} \; / __ \; \begin{bmatrix} + \text{ላይ} \\ - \text{ሁዋ} \end{bmatrix} \qquad 4$$

ቅምሩ እንድ የድድ ድምፅ ከላንቃ ድምፅ በፊት ሲገባ፣ ወደ (ድ)ላንቃ ድምፅ እንደሚለወጥ ያመለክታል።

ትናጋዊነት

ይህ በመሰረተ ፍጥረታቸው ትናጋዊ ያልሆኑ ድምፆች በቅንጅት ምክንያት ትናጋዊ የሚሆኑበት ሂደት ነው። ትናጋዊ ድምፆች ሁዋለኛ እና ላየኛ ናቸው። የሚከተሉት ሂደቱ የሚከሰትባቸው ቃላት ምሳሌ ናቸው።

/ምኧንግ-ሰት/	[ምኧ^{ŋ}ግእለት]	መንግስት	1
/እንቅ-ርት/	[እ^{ŋ}ቅእርት]	እንቅርት	
/አንክት/	[አ^{ŋ}ክእት]	አንክት	

በእዝባሩ ውስጥ /ን/ ሆና የምትታየው ድምፅ፣ በግዕዙ ውስጥ [^{ŋ}] ሆናለች። በመሰረተ ፍጥረትዋ /ን/ ድዳዊ የሰርን ድምፅ ነች። [^{ŋ}] ደግሞ ትናጋዊ የሰርን ድምፅ ነች። በታሀታይ ቅርፆቹ ውስጥ ድዳዊ የነበረችው፣ በላዕላይ ቅርፆቹ ውስጥ ወደ ትናጋዊነት ተለውጣለች ማለት ነው። የትናጋዊነቱ መንስዔ ከ/ን/ ቀጥሉ የተከለፈው ድምፅ ማለትም፣ /ግ/ ወይም / ቅ/ ወይም /ክ/ ነው። እነዚህ ድምፆች በመሰረተ ፍጥረታቸው ትናጋዊ ናቸው። ስለዚህም ቀድሞአቸው

የተሰለፈውን ድዳዊ /ን/ ወደ ትናጋዊነት እንዲለወጥ ምክንያት ሆነዋል። የለውጡን አካሄድ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

$$\begin{bmatrix} -\text{ላይ} \\ -\text{ሁዋ} \\ +\text{ሰ} \end{bmatrix} \rightarrow \begin{bmatrix} +\text{ላይ} \\ +\text{ሁዋ} \\ +\text{ሰ} \end{bmatrix} \quad / __ \quad \begin{bmatrix} +\text{ላይ} \\ +\text{ሁዋ} \\ -\text{ሰ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

ቅምሩ አንድ የላይና የሁዋላ ያልሆነ የሰርን ድምፅ፣ ከአንድ የላይና የሁዋላ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገባ፣ የሁዋላና የሰርን ድምፅ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ባጭሩ እንደ /ን/ ያለ የድድ ድምፅ እንደ /ግ/ ካለ የትናጋ ድምፅ ቀድሞ ሲግባ፣ አሱም እንደ ጎረቤቱ የትናጋ የሰርን ድምፅ ይሆናል፡፡

ማንቁርታዊነት

ቀደም ሲል ሰለ ድምፆች አፈጣጠር ስንወያይ፣ ማንቁርታዊ ድምፆች አየር በአፍ ውስጥና በማንቁርት ውስጥ በአንድ ጊዜ ታግዶ፣ በአንድ ጊዜ ሲለቀቅ፣ እንደሚፈጠሩ ገልፀን ነበር፡፡ በዚህ አይነት የሚፈጠሩት ድምፆች /ጵ፣ ጥ፣ ፅ፣ ጭ እና ቅ/ ናቸው፡፡ በቅንጅት ወቅት፣ ከነዚህ ድምፆች በፊት የሚገኝ ሌላ ድምፅ ከነሱ በሚመጣ ተጋቦት ምክንያት ማንቁርታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ አይነት የባህሪ ተጋቦት ሂደት ማንቁርታዊነት ይባላል፡፡ የሚከተሱት ሂደቱ የሚከሰትባቸው ቃላት ናቸው፡፡

/አስ-ፅ-ፍኧው/	[አፅ-ፅእፍኧው]	አፅፈው	1
/አት-ጥኧይይ-ቅ/[16]	[አጥ-ጥኧይይእቅ]	አጠይቅ	
/አት-ጭኧቅጭ-ቅ/	[አጭ-ጭኧቅጭእቅ]	አጨቅጭቅ	
/አት-ቅኧቅቅ-ል/	[አቅ-ቅኧቅቅእል]	እቀቅል	

/አለ-/ በሚለው ምዕላድ መጨረሻ ላይ የሚገኘው /ስ/ እና /ት/ ኢማንቁርታዊና ኢነዛሪ የድድ ድምፆች ናቸው፡፡ ከነሱ ቀጥለው የሚገኙት የየአምዱ መነሻ ድምፆች ማንቁርታዊና ኢነዛሪ ናቸው፡፡ በዚህ ጉርብትና ምክንያት፣ ማንቁርታዊ ያልነበሩት /ት/ እና /ስ/ ማንቁርታዊ ለሆኑ ችለዋል፡፡ ሂደቱ /ስ/ን ወደ [ፅ]፣ /ት/ን ወደ [ጥ] ፣ እንዲሁም [ጭ] ን ወደ [ቅ] ስውጦታል፡፡ የ/ስ/ ለውጥ የመካነ ፍጥረት ላይሆን፣ የባህርየ ፍጥረት ነው፡፡ በመካነ ፍጥረትዋ / ስ/ አሁንም ድዳዊ ነች፡፡ የ/ት/ ለውጥ ግን የሁለቱም ነው፡፡ ምክንያቱም /ት/ በመሰረታዊ ፍጥረትዋ

---

[16] የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ /አል-ት-ጥኧይይ-ቅ/፣ /አል-ት-ጭኧቅጭ-ቅ/፣ /አል-ት-ቅኧቅቅ-ል/ ነው፡፡ ከ/-ት-/ በፊት ገብታ የምትገኘው /-ል/ ቢታህታይ ቅርፅ ላይ ትገደፋለች፡፡ የ/አስ-ፅ-ፍኧው/ ባህሪ ከነዚህ የተለየ ነው፡፡ ሂደቱን ወደፊት እናየዋለን፡፡

ድዳዊ ሰትሆን፣ የተለወጠችው ድኅንቃዊ ወደሆነው ወደ [ጭ] እና ትናጋዊ ወደ ሆነው ወደ [ቅ] ነው። የለውጡን ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

$$\begin{bmatrix} + \text{ድድ} \\ - \text{ማንቅ} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{ድድ} \\ + \text{ማንቅ} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} / __ \begin{bmatrix} + \text{ማንቅ}^{17} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \quad 2$$

ቅምሩ አንድ ማቋርታዊ ያልሆነ የድድ ድምፅ ምንቋርታዊ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገኝ፣ ማንቋርታዊ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል። ይህ አጠቃላይነት ያለው ቅምር ነው። በተናጠል መልክ ቢቀመጥ፣ ለውጡ የሚከተለውን ይመስል ነበር።

/ስ/	⟶	[ፅ]	/	-	/ፅ/
/ት/	⟶	[ጥ]	/	-	/ጥ/
	↘	[ቅ]	/	-	ቅ/

3

የ/ፅ፣ጥ፣እና ቅ/ የጋራ ባህሪ ማንቋርታዊነት ነው። የ/ት እና ስ/ የጋራ ባህሪ ደግሞ ኢማንቋርታዊነት ነው። ከኢማንቋርታዊነት ወደ ማንቋርታዊነት የተደረገውን ለውጥ ለማሳየት የአያንዳንዱን ድምፅ የለውጥ ሂደት መዘርዘሩ ጥናቱን አጠቃላይነት ያሳጣዋል። ስለዚህም ከላይ በተራ ቁጥር (2) በተመለከተው ቅምር መልክ በጋራው ባህሪ ላይ ብቻ ማተኮሩ ተገቢ ነው።

ክበት

ይህ ሂደት አንድን ዝርግ የሆነ ድምፅ ወደ ኩብነት የሚለውጥ ነው። የሚከሰተውም ድምፁ ከ/አ/፣ ከ/ኡ/ እንዲሁም ከ/ው/ አጠገብ ሲገኝ ነው። ከ/ው/ አጠገብ የሚገኝ ድምፅ እንዴት ወደ ክብነት እንደሚለወጥ ከፍ ሲል <u>ጠረ</u> እና <u>ዞረ</u> በሚሉት ምሳሌዎች አማካኝነት አሳይተናል። ከዚህ ቀጥለን ተመሳሳይ ሁኔታ የሚታይባቸውን ሌሎች ቃላት እንመልከታለን።

1

/ሰኡቅ/	[ሰ°ኡቅ]	ሱቅ
/ጥኡት/	[ጥ°ኡት]	ጡት
/ዝኡፍአን/	[ዝ°ኡፍአን]	ዙፋን
/ምኦርኧድ/	[ምሙ ኧርኧድ]	ሞረድ
/ጭኦምኣ/	[ጭ°ኦምኣ]	ጮማ
/ድኦምኣ/	[ድ°ኦምኣ]	ዶማ

[17] ማንቋርታዊነት መካነ ፍጥረትን የሚመለከት ለውጥ ነው። ፈንጅነት የአፈጣጠር ባህሪን የሚመለከት ሁኔታ ነው። ለውጡ የባህሪ ስለሆነ ሂደቱ ፈንጅነት ሊባል ይችላል።

በቅንፉ ውስጥ የሚታየው የየቃሉ የመጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ፣ በእዝባሩ ውስጥ ከሚታየው የየቃሉ የመጀመሪያ ድምፅ በመጠኑ የተለየ ነው። የሚለየውም የክብነት ባህሪ በመያዙ ነው። ይህን ባህሪ ያገኘው ከእሱ ቀጥሎ ከገባው ከ/ኡ/ ወይም ከ/ኦ/ ነው። አነዚህ አናባቢዎች ክብ ስለሆኑ፣ ይህኑ ባህሪያቸውን ቀድሞአቸው ለገባው ተናባቢም ሊያጋቡ ችለዋል። አሁንም ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ባህሪው የሚጋባው ከቀኝ ወደ ግራ ነው።

የለውጡን ሁኔታ እንደሚከተለው አድርጎ መቀመር ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} + \text{ ተ} \\ - \text{ ክብ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{ ተ} \\ + \text{ ክብ} \end{bmatrix} \quad / \text{ ---} \quad \begin{bmatrix} + \text{ ተ} \\ + \text{ ክብ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

ተ = ተናባቢ

ቅምሩ ከ/ኡ/ ወይም ከ/ኡ/ በፊት የሚገኝ ተናባቢ ድምፅ ወደ ክብነት እንደሚለወጥ ያሳያል። የባህሪው ተጋቦት ከቀኝ ወደ ግራ መሆኑ ስለ መላሽ ምስለሎሽ የጠቀስነውን ያስታውሰናል።

ድምፀት

አንድ በተፈጥሮው ኢነዛሪ የሆነ ድምፅ ነዛሪ በሆነ ድምፅ ጉርብትና ምክንያት ወደ ነዛሪነት ሊለወጥ ይችላል። የዚህ አይነት ሂደት <u>ድምፀት</u> ይባላል። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን።

/አል-ት-ድኽፍርአም/	[አድድኽፍርአም]	አደፍርም	1
/አል-ት-ዝኽርአም/	[አዝዝኽርአም]	አዘራም	
/አሱ-ዝኽርርአህኡ/	[አዝዝኽርአህኡ^{ሥ}]	አዘራሁ	

በእዝባሩ ውስጥ በሚታዩት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ፣ በመነሻ ላይ የሚገኘው /አል-/ የእሱታ ምዕላድ ነው። ዝርዝሩን በሚቀጥለው ምዕራፍ እናየዋለን። ከእሱ ቀጥላ የምትገኘው /ት/ም ወደ ፊት እንደምናየው፣ የሁለተኛ መደብን የምታመለክት ምዕላድ ነች። ከእሰዋ ቀጥሎ የሚገኘው የየግሱ አምድ ሲሆን፣ የሚጀምረውም በነዛሪ ድምፅ ነው። የእሱታው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ል/፣ የሁለተኛ መድብ አመልካችዋ /ት/፣ እንዲሁም የየግሱ አምድ የመጀመሪያ ድምፅ በመካነ ፍጥረታቸው አንድ ናቸው። ሁሉም ድዳዊ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ /ት/ ብቻ ኢነዛሪ እግድ የድድ ድምፅ ነች። በመሆንዋም ከእሰዋ ቀጥሎ ያለውንና ነዛሪ የሆነውን የየግሱን አምድ የመጀመሪያ ድምፅ ባህሪ ትወርስና አሰዋም እንደ እሱ ነዛሪ ትሆናለች።

በሶስተኛው ምሳሌ ውስጥ ያለው ሁኔታም ከመጀመሪያዎቹ ጋር ተመሳሳይ ነው። ወደፊት አንደምናየው /አል-/ አስደራጊ ምዕላድ ነች። የዚች ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ስ/፣ ኢነዛሪ ፍትግ የድድ ድምፅ ነች። የግሱ የመጀመሪያ ድምፅ ደግሞ አንደ አሰዋ ፍትግ፣ ግን ነዛሪ የድድ ድምፅ ነው። የሚለያዩት በነዛሪነት ብቻ ነው። ስለዚህም ኢነዛሪዋ /ስ/ የ/ዝ/ን የነዛሪነት ባህሪ ወስዳ አሰዋም ነዛሪ ትሆናለች። የምስሰሉሹን ሂደት አንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} + \text{ ድድ} \\ - \text{ ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{ ድድ} \\ + \text{ ድምፅ} \end{bmatrix} \Big/ __ \begin{bmatrix} + \text{ ተ} \\ + \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

ሂደቱ በድምፀት ብቻ አያበቃም። የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ የሆነችው /ል/ም ትገደፋለች። የግድፈቱ ምክንያት ሶስት የድድ ድምፆች ተከታትለው መምጣታቸው ይመስላል። ይህን የምንልበት ምክንያት /ት/ በማትገኝበት ጊዜ፣ የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ም/፣ በግልፅ ስለማትገደፍ ነው። ይህም የሚታየው አንደሚከተሉት ባሉ ምሳሌዎች ውስጥ ነው።

/አል-ድኽፍር-ም/	[አልድኽፍርአም]	አልደፍርም
/አል-ዝኽርአም/	[አልዝኽርአም]	አዘራም

3

በነዚህ ቃላት ውስጥ፣ /ት/ ባለመገኘትዋ ከትትሉሹ የ/ል/ እና የ/ድ/ ወይም /ዝ/ ብቻ ነው። ስለሆነም የግድፈት ሂደት አይታይም። ምናልባትም ግድፈቱን የአሉታዊው ምዕላድ ከግሱ አምድ ጋር ካለው የቅርበት ደረጃ ጋር ማገናኘት ይቻል ይሆናል። ከዚህ አንፃር በአሉታዊው ምዕላድና በግሱ የመጀመሪያ ተናባቢ መካከል ምዕላድ ከተገኘ፣ /ል/ ትገደፋለች ለማለት ይቻላል። ለዚህ አባባላችን ማስረጃ የሚሆኑን እንደሚከተሉት ያሉት ቃላት ናቸው።

/አል - ቅኽርርኽብኽም/	/አል-ይ-ቅኽርብ-ም/
[አልቅኽርርኽብኽም]	[አይቅኽርብአም]
/አል - ስኽብብኽርን-ም/	/አል-ን-ስኽብር-ም/
[አልስኽብብኽርንአም]	[አንስኽብርአም]

4

በሁለቱም ምሳሌዎች ታህታይ ቅርፅ ውስጥ የአሉታዊው ምዕላድ /አል-/ ነው። በስተግራ በኩል በሚገኙት ምሳሌዎች ውስጥ /አል-/ የተቀጠለችው ከግሱ አምድ ላይ ነው። በስተቀኝ በኩል ባሉት ውስጥ ግን አገባብዋ በቀጥታ ከግሱ አምድ ላይ ሳያሆን፣ /ይ-/ እና /ን-/ ከሚሉት ምዕላዶች በፊት ነው፣ ስለዚህም ከአምዱ ርቃለች። ይህም በመሆኑ፣ በነዚህ ምሳሌዎች ላዕላይ ቅርፅ ውስጥ /ል/ በግሀድ

አትታይም። ተገድፋለች ማለት ነው። በቀጥታ ከግሱ አምድ ላይ በምትገኝበት ጊዜ ግን በግሀድ ትታያለች፣ አትገደፍም ማለት ነው። ሰለዚህም <u>አልቀረበም</u> ([አልቅኧርርኧብኧም]) በሚሰው ውሰጥ በግሀድ ሰትታይ፣ <u>አይቀርብም</u> ([አይቅኧርብአም]) በሚለው ውሰጥ ግን አትታይም።

አንድ መደብ አመልካች ቅጣይ ከግሰ አምድ መነሻ ላይ የሚገኘው በካልዓይ አንቀፅ፣ በአምድ መድረሻ ላይ የሚገኘው ደግሞ በቀዳማይ አንቀፅ ግሰ በሰሆነ፣ የግድፈቱን አውድ ከዚሁ የአንቀፅ ልዩነት ጋር ማያያዝ ይቻላል። ከዚህም አኳኩዋያ /ል/ የምትገደፈው በካልዓይ አንቀፅ ግሰ ውሰጥ ነው፣ ብሎ ማጠቃሰል ይችላል። ይህም ቀደም ሲል የ/ው፣ይ፣ህ፣ዕ/ን የግድፈት አኳውድ ከተሰየ የቃል ከፍል፣ ማለትም ከግሰነት፣ ጋር አንዳያያዝነው ሁሉ፣ አኳሁንም የ/ል/ን ግድፈት ከተወበነ የግሰ አአምድ አአይነት፣ ማሰትም ከካልዓይነት ጋር ማያያዛችን፣ የግድፈቱ ሂደት በሰነ-ድምፃዊ አኳውድ ላይ ሳይሆን፣ በሰነ-ምዕ ላዳዊ ቅርፅ ላይ የተመሰረተ አንደሆነ ይጠቁማል። ሰለ ቀዳማይና ካልዓይ አአንቀፅ በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው አንወያያለን።

ኢድምፀት

ቀደም ሲል ድምፆች በተፈጥሮአቸው ነዛሪና ኢነዛሪ ተብሰው በሁሰት አንደሚከፈሉ ገልፀናል። በዚህ ልዩነት ምክንያት ነዛሪ ድምፆች [+ ድምፅ] ኢነዛሪዎቹ ደግሞ [- ድምፅ] ተብሰው ይመደባሉ። አንድ ነዛሪ የሆነ ድምፅ ነዛሪ ካልሆነ ሌላ ድምፅ ጋር ሲገባ፣ የባህሪ መወራረሰ ይከሰታል። ይኸውም ከፍ ሲል አንዳየነው፣ ኢነዛሪ የነበረው ነዛሪ ሊሆን፣ ወይም በተቃራኒው ነዛሪ የነበረው ኢነዛሪ ሊሆን ይችላል። ኢነዛሪ የነበረን ድምፅ ነዛሪ የሚያደርግ ሂደት ድምፀት አንደሚባል ሁሉ፣ ነዛሪ የነበረን ድምፅ ኢነዛሪ የሚያደርገው ሂደት ኢድምፀት ይባሳል። የሚከተሉት የዚህ የሁሰተኛው ሂደት ምሳሌዎች ናቸው።

/ፍኧልልኧ<u>ግ</u>-ክ/	[ፍኧልልኧ<u>ኩ</u>ክ]	ፈለክ	1
/ድኧንኧዝዝኧ<u>ዝ</u>-ክ/	[ድኧንኧዝዝኧ<u>ሰ</u>ክ]	ደነዘዝክ	
/ኣ<u>ል</u>-ት-ውጥኣ/	[ኣ<u>ት</u>ትውጥኣ]	አትውጣ	

በአዝባሩ ውሰጥ በሚታዩት የመጀመሪያ ምሳሌዎች፣ የየአምዱ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ግ/ እና /ዝ/፣ ነዛሪ፣ ሰሰዚህም [+ ድምፅ] ናቸው። ከነዚህ ቀጥላ የምትታየው /-ክ/ ግን ኢነዛሪ እናም [- ድምፅ] ነች። በከትትሉቹ ምክንያት የ/-ክ/ ኢነዛሪያዊ ባህሪ ወደ ቀዳሚው ድምፅ ይጋባል። በዚህም ምክንያት /ግ/ እና /ዝ/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው ወደ [ኩ] እና [ሰ] ሊለወጡ ችለዋል። በመጨረሻው ምሳሌም የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ

የሆነችው /ል/ ከአሰዋ ቀጥላ በምትገኘውና ኢነዛሪ በሆነችው በ/ት/ ምክንያት፣ አሰዋም ወደ ኢነዛሪነት ተለውጣ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው [ት] ሆናለች።


ከዚህ ላይ ቀደም ሲል የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ የሆነችው /ል/ መደብ አመልካች ከሆነችው ምዕላድ ከ/ት-/ቀድማ ስትገባ ትገደፋለች ብለን ነበር። አሁን ደግሞ ይህችው ድምፅ ማለትም /ል/ ወደ ኢነዛሪነት ትለወጣለች እያልን ነው። እነዚህ የሚጣረሱ ሀሳቦች ይመሰላሉ። በአንድ በኩል ግድፈት፣ በሌላ በኩል ኢድምፀት ይካሄድበታል ማለታችን ነው። እነዚህ ሁለት የተሰያዩ ሂደቶች በአንድ ድምፅ ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ። የግድፈቱንና የኢድምፀቱን አውድ መለየት ግን ያስፈልጋል። ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ግድፈቱ የሚከሰተው በካልዓይ አንቀፅ ላይ ነው። ኢድምፀት ግን የሚከሰተው በትዕዛዝ አንቀፅ ላይ ነው።

ተመሳሳይ የኢድምፀት ሂደት በአናባቢዎች ላይም ይከሰታል። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

/ጥኧግግኧብከ-ኡ/	[ጥኧግግኧብከኡ^{ሀ}]	ጠገብኩ	2
/ውኧጥጥኣሀ-ኡ/	[ውኧጥጥኣሀኡ^{ሀ}]	ወጣሁ	

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የመጨረሻው አናባቢ ድምፅ /ኡ/ ነው። እንደማንኛውም አናባቢ ድምፅ በመሰረተ ባህሪው ነዛሪ ብሎም [+ ድምፅ] ነው። ይሁን እንጅ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው፣ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጧ [ኡ^{ሀ}] ሆኖአል። ለዚህም ምክንያቱ፣ ድምፁ ኢነዛሪ ከሆኑት ከ/ክ/ እና ከ/ሀ/ ቀጥሎ መገኘቱና የአነሱ የኢነዛሪነት ባህሪ ወደሱ መጋባቱ ነው። የተጋቦቱ አቅጣጫ ግን ከፍ ሲል ከሚታየው የተለየ ነው። ምክንያቱም የላይኛው ሂደት መላሽ ያልነው አይነት ሲሆን፣ ይኸኛው ግን ቀደም ሲል የጠቀስነው የገሰጋሽ ምስለ-ሽ ምሳሌ ነው። ባህሪው የሚጋባው ወደፊት ማለትም ወደ ቀኝ ሂዶ ነውና።

የሁሉንም ኢድምፀታዊ ሂደቶች ጠቅለል አድርጎ በአንድ ቅምር ማሳየት አስቸጋሪ ነው። አንደኛ ባህሪው ሚሄድበት የአቅጣጫ ልዩነት አለ። ሁለተኛም በቅምሩ ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉ ምሳሌዎች ያጋጥሙናል። እነዚህም አንደ *ወደደክ* ([ውኧድድኧድከ]) እና *ወሰድክ* ([ውኧሰስኧድከ]) ያሉት ቃላት ናቸው። ከፍ ሲል ባየነው አካሄድ መሰረት፣ በነዚህ ቃላት ውስጥ ከ/ክ/ በፊት የሚገኘው /ድ/ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጦ [ት] መሆን ነበረበት፣ ግን ነዛሪነቱን አንደጠበቀ ይገኛል። በቅምሩ መሰረት ድምፁ ወደ ኢነዛሪነት ቢለወጥ ኖሮ፣ የቃላቱ ቅርፅ [ውኧድድኧትከ] እና [ውኧሰስኧትከ] ይሆንና ተቀባይነትን ያጣ ነበር። በጥቅሉ ግን አንድ ነዛሪ የነበረ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ሌላ ድምፅ ቀድሞ ወይም ተከትሎ ሲገኝ፣ ወደ ኢነዛሪነት ይለወጣል የሚሉ ቅምሮችን እንደሚከተሰው አድርጎ ማሰቀመጥ ይቻላል። ተፈፃሚነቱን ሂደቱ በሚታይባቸው ቃላት ላይ ብቻ መወሰን ይቻላል።

(ሀ) 

(ለ) 

የመጀመሪያው ቅምር ነዛሪ የሆነ ተናባቢ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ ድምፅ በፊት ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል፣ ሁለተኛው ግን ነዛሪ የሆነ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ በሁዋላ ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል ያሳያል። ይህ ህግ እናባቢንም ያጠቃልላል።

ግድፈት

በተጎራባች ድምፆች መካከል የባህሪ መወራረሰ ብቻ ላይሆን፣ አንዱ በሌላው ምክንያት ከቦታው የመጥፋት ሂደትም ሊደርሰበት ይችላል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ <u>አዘነ</u>፣ <u>አየለ</u>፣ <u>አነፀ</u>፣ ወዘተ፣ ያሉት ግሶችና እንደ <u>ሀገር</u>፣ <u>ሀሞት</u>፣ ወዘተ ያሉ ሰሞች ናቸው። የግሶቹ ታህታይ ቅርፅ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ /ህኧዝዝኧንኧ/፣ /ህኧይይኧልኧ/፣ /ህኧንንኧፅኧ/ ነው። ይህ ሰመሆኑ ማሰረጃው፣ በየግሶቹ ሰማዊ አቻ ላይ /ህ/ የሚሰው የየቃሉ የመነሻ ድምፅ በግልፅ መታየቱ ነው። ለምሳሌ የ/ህኧዝዝኧንኧ/ ሰማዊ አቻ <u>ህዘን</u> ([ህኣዝኧን]) ሲሆን፣ የ/ህኧይይኧልኧ/ ደግሞ <u>ህይል</u> ([ህኣይል]) ነው። ሌላው ማሰረጃ የግሶቹ የመጀመሪያ ላዕላይ ድምፅ እናባቢ መሆኑ ነው። ይህ ከቁዋንቁዋው አጠቃላይ የግሰ ባህሪ የሚያፈነግጥ ሁኔታ ነው። ከተወሰኑት በስተቀር፣ የእግርኛ ግሶች በተናባቢ እንጅ በእናባቢ አይጀምሩም። ለምሳሌ፣ እንደ <u>ገደለ</u>፣ <u>ሰበረ</u>፣ <u>ዘመረ</u>፣ ወዘተ ያሉ ግሶች በተናባቢ የሚጀምሩና፣ ከዚያ ተናባቢ ቀጥሎም /ኧ/ የሚሰውን የመሀል እናባቢ የሚያሰከትሉ ናቸው። ሰምሳሌ፣ የ<u>ገደለ</u> ታህታይ ቅርፅ /ግኧድድኧልኧ/ ነው። በግልፅ እንደሚታየውም፣ የመጀመሪያው ድምፅ ተናባቢ ሲሆን ከእሱ ቀጥሎ የሚታየው እናባቢ ደግሞ ሌላ ላይሆን፣ /ኧ/ ነው። ይህም መሀለኛ እናባቢ ነው። የቃሉ ላዕላይ ቅርፅም የሚጀምረው እንደዚሁ በተመሳሳይ ተናባቢ ድምፅ ነው።

/ህኧዝዝኧንኧ/ በሚለው ቅርፅ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው ተናባቢ፣ ማለትም /ህ/፣ ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ ባህሪውን ለእናባቢው ድምፅ ሰጥቶ፣ እሱ ከቦታው ይጠፋል። የ/ህ/ ባህሪ ታቸኛነት ነው። የታች ድምፅ ነው፣ ማለት ነው። የታች የሚባልበት ምክንያት፣ ድምፁ ማንቁርት ውስጥ ሲፈጠር ምላሰ ወደታች ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው። ይህ ታቸኛ ድምፅ ከፍ ሲል ከተገለፀው መሀለኛ ከሆነው ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ የታቸኛነት ባህሪውን ለ/ኧ/ ሰጥቶ፣ እሱ ከዚያ ቦታ ይጠፋል።

የታቸኛነት ባህሪን የተላበሰው /ኧ/ም ከመሀለኛነት ወደ ታቸኛነት ይለወጥና [አ] ይሆናል። ዝርዝሩን በመተው አጓጠቃላይ ለውጡን ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን።

(ሀ) $\begin{bmatrix} + \text{አ} \\ - \text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{አ} \\ + \text{ታ} \end{bmatrix} \; / \; \begin{bmatrix} - \text{አ} \\ + \text{ታ} \\ + \text{ሁሞ} \end{bmatrix} \; _ \quad 1$

(ለ) $\begin{bmatrix} - \text{አ} \\ + \text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \text{Ø} \; / \; _ \; \begin{bmatrix} + \text{አ} \\ + \text{ታ} \end{bmatrix}$

አ = አናባቢ ታ = ታች

ህጎቹ ተከታታይና ተደጋጋፊ ናቸው። መጀመሪያ /ኧ/ በ/ሀ/ ምክንያት ወደ [አ] ይለወጣል። ከዚያ በሁዋላ፣ /ሀ/ በ[አ] ምክንያት ከቦታው ይጠፋል። ሂደቱ በክፈል የምስስሉሽ በክፈል ደግሞ የግድፈት ነው። ምስስሉሹ ለግድፈቱ መንስዔ ሆኖአል።

በ/ሀ/ ምክንያት በ/ኧ/ ላይ የደረሰው ለውጥ ቀደም ሲል የጠቀስነው የገስጋሽ ምስስሉሽ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። /ሀ/ የታቸኛነት ባህሪዋን በቀኝዋ በኩል ለሚገኘው ለ/ኧ/ አጋብታ ጠፍታለች። የመሀለኛ አናባቢ የነበረችው /ኧ/ም በተጋቦቱ ምክንያት ታቸኛ ልትሆን ችላለች። ሌላም የዚህ አይነት ምሳሌ ስለ <u>ትናጋዊነት</u> ስንወያይ እንመለከታለን።

/ሀ/ የምትገደፈው ከላይ እንደሚታየው በቃል መነሻ ላይ ብቻ አይደለም። በቃል መካከልና በቃል መድረሻም ጭምር ነው። በሁለቱም ቦታዎች የታቸኛነት ባህሪዋን ተከትሎአት ለሚገባው ድምፅ ሰጥታ እስዋ ከቦታዋ ትጠፋለች። የሚከተሉት ቃላት ለዚህ ምሳሌ ናቸው።

ማለ 2
ፃፈ

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

/ምኧህኧልኧ/[18] 3
/ፅኧህኧፍኧ/

[18] ቀደም ሲል እንደተገለፀው /ህ/ ጠባቂ ድምፅ አይደለችም። ብትሆን ኖሮ፣ የግሱ ቅርፅ /ምኧህህኧልኧ/ ይሆን ነበር። ይህ ደግሞ ትክክለኛ አባባል አይደለም።

ነው። በየታህታይ ቅርፃቸው ውስጥ/ህ/ ስመናሩ ማስረጃው፣ በነዚህ ግሶች ስማዊ አቻ ውስጥ /ህ/ በግሀድ መታየቱ ነው። ይኸውም ስምሳሌ፣ <u>መህላ</u> እና <u>ፀህፌ</u> ስንል ነው። ሁለተኛም በየግሶቹ ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው እናባቢም ቅርፁ ከ/ኧ/ ወደ /አ/ መለወጡ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፣ /ህ/ የታቸኛነት ባህሪውን ለ/ኧ/ ሲሰጥ፣ መህለኛ የነበረው /ኧ/ ወደ ታቸኛነት ይለወጥና [አ] ይሆናል። በነዚህ ምሳሌዎችም በግሀድ የሚታየው ይኸው ሁኔታ ነው።

ምሳሌዎቹ በቃል መካከል የሚገኝ /ህ/ ባህሪውን ሰጎረቤቱ እየሰጠ ሲጠፋ፣ የሚያመለክቱ ናቸው። በቃል መድረሻም ቢሆን እንደዚሁ ባህሪውን እየሰጠ ሲጠፋ የሚያሳዩ ምሳሌዎች አሉ። እነሱም እንደ፣

በራ 4
ፈራ

ያሉ ቃላት ናቸው። የእነዚህ ታህታይ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከትላቸው፣

/ብኧርርኧህኧ/ 5
/ፍኧርርኧህኧ/

ነው። ይህ ውነት ስመሆኑ አሁንም ማስረጃው የየግሶቹ አቻ የሆኑት ሰሞች /ህ/ን በግልፅ ማሳየታቸው ነው። ይኸውም፣

ብርሃን 6
ፍርሃት

ስንል ነው። በግሶቹ ውስጥ በጠፋበት ቦታ ላይ፣ በየአቻ ሰሞቹ ውስጥ ሊከሰት ችሉአል። ሁለተኛም እንደ <u>በራ</u> ያሉ የመጨረሻ ተናባቢያቸውን የሚጥሉ ግሶች በአርዕስታዊ፣ በቦዝ እንቀፃዊና በአጠንካሪ አቻ ቅርፆቻቸው ላይ፣ [ት]ን በምትክነት ያሳያሉ። የሚያሳዩትም በግሱ ስር ድምፅዋ በተገደፈችበት ቦታ ላይ ነው። ስምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

<u>ስር</u>	<u>ግስ</u>	<u>አርዕስት</u>	<u>ቦዝ</u>	<u>አጠናካሪ</u>	
/ብ-ር-ህ/	/ብኧርር-/	/ምኧብርኣት/	/ብኧርት-ኦ/	[ብኣርርኣትት]	7
/ፍ-ር-ህ/	/ፍኧርር-/	/ምኧፍርኣት/	/ፍኧርት-ኦ/	[ፍኣርርኣትት]	
/ስ-ር-ህ /	/ስኧርር-/	/ምኧስርኣት/	/ስኧርት-ኦ/	[ስኣርርኣትት]	
/ብ-ል-ዕ/	/ብኧልል-/	/ምኧብልኣት/	/ብኧልት-ኦ/	[ብኣልልኣትት]	

በአርዕስት፣ በቦዝ እና በአጠንካሪ አምዶች ውስጥ የሚገኘው የመጨረሻ ድምፅ [ት] አንደሆነ እንረዳለን። ይህ ድምፅ በየአቻ ግሶቹ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ መጨረሻ ላይ የሚገኘውና በላዕላይ ቅርፁ የተገደፈው የ/ህ/ ወይም የ/ዕ/ ምትክ ነው። ሁኔታው አንድ በታህታይ ቅርፅ ውስጥ የሚገኝ ድምፅ ያለምንም ምትክ ወይም ምልክት ከቦታው ሊጠፋ አንደማይችል ያመለክታል። ከዚህ ሁኔታ፣ [ት] የተገዳፊ ድምፅ ቤት ጠባቂ አንደሆነች ለመረዳት ይቻላል።

[ት] ምትክ ወይም ቤት ጠባቂ እየሆነች በየአምዱ መጨረሻ ላይ የምትገባው በግሱ ስር መጨረሻ ላይ ለሚገደፍ ተናባቢ ድምፅ ብቻ እይደለም። በጣም ውሱን በሆኑ ግሶች ውስጥ፣ የመጀመሪያ ተናባቢ በነበረና በተገደፈ ድምፅ ምትክ ልትገኝ ትችላለች። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን <u>አየ</u> እና <u>አለ</u> [ኣልልኧ] የሚሉት ግሶች ናቸው። የነዚህ ግሶች ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው እንደ ቅደም-ተከተላቸው በ/ር/ እና በ/ህ/ ነው። ይህ ውነት ለመሆኑ ሁለት ማስረጃዎች አሉ። የመጀመሪያው የየቃላቱ ታሪካዊ አመጣጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው የአቻ ስሞቻቸው ላዕላይ ቅርፅ ነው። ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ አሁንም አንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ /ር-ፅ-ይ/ እና /ህ-ል-ው/ ከሚሉ ስሮች ነው። እነዚህ ስሮች በግዕዝ <u>ርዕየ</u> እና <u>ህለወ</u> የሚል ግላዊ ቅርፅ አላቸው። በአማርኛ ደግሞ በየስሩ ከሚገኙት ድምፆች የተወሰኑትን ጥለው፣ ከላይ በሚታዩበት ቅርፃቸው <u>አየ</u> እና <u>አለ</u> [ኣልልኧ] ሆነው ይገኛሉ። የነዚህ ግሶች ለግዊ አቻዎች ግን የተገደፉትን ድምፆች በላዕላይ ቅርፃቸው ውስጥ ያላያሉ። አነዚህም <u>ራዕይ</u> እና <u>ህልውና</u> ናቸው። የየግሶቹ አርዕስታዊ ቅርፅም በመድረሻቸው ላይ ቦግሶቹ መነሻ ላይ ቡተገደፉት ተናባቢዎች ምትክ [ት]ን ያላያሉ። ይኸውም <u>አየ</u> ብለን፣ <u>ግየት</u> ስንል ነው። ርግጥ፣ በዚሁ አካሄድ <u>አለ</u> [ኣልልኧ] ብለን፣ <u>ግለት</u> [ምኣልልኧት] ግለት ነበረብን። የምንለው ግን <u>መኖር</u> ነው። ይህ ደግሞ <u>የኖረ</u> አርዕስታዊ አቻ አንጅ <u>የለ</u> አይደለም። <u>አለ</u> የራሱ የሆነ አርዕስታዊ አቻ የለውም[19]።

የመሀል ተናባቢ ድምፃቸውን የሚገድፉ ግሶች በአርዕስታዊ አቻቸው መድረሻ ላይ [ት]ን አያሳዩም። ስለዚህም <u>የግል</u> አርዕስታዊ ቅርፅ <u>መግል</u> እንጅ <u>መግልት</u> አይደለም። ባህሪውን ለቀዳሚ ጎረቤቱ ሰጥቶ የሚጠፋው ድምፅም /ህ/ ብቻ አይደለም። አንደሱ የማንቁርት ድምፅ የሆነው /ዕ/ም አንደዚሁ የታቸኛነት ባህሪውን ለጎረቤቱ አየሰጠ ይጠፋል። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

ላለ	8
በላ	

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተገደፈው ድምፅ /ዕ/ ነው። ይህ ለመሆኑ ማሰረጃው አሁንም ታሪካዊ ነው። ሁለቱም ቃላት አንደ ቅደም-ተከተላቸው <u>ሰዓለ</u> እና <u>በልዓ</u> የሚል ግዕዛዊ አቻ አላቸው። በአማርኛም ቢሆን በተለይ <u>ላለ</u> የሚለው ግስ

[19] የሁለቱን ግሶች ታህታይ አቀነጃጀትና ላዕላይ ለውጥ በተመለከተ ዝርዝሩን ከባየ (1997፣ 1999) ይመልከቱ።

በለግዒ አቻው ውስጥ /ዕ/ን በግሀድ ያላያል። ይኸውም ስዕል በምንልበት ጊዜ ነው።

/ዕ/ የተገደፈው በመጀመሪያው ግስ መሀልና በሁለተኛው ግስ መድረሻ ላይ ነው። በሁለተኛው ግስ ላይ ድምፁ የተገደፈው መድረሻ ላይ በመሆኑም የዚሁ ግስ አርዕስታዊ ቅርፅ፡ በተገደፈው ድምፅ ቦታ ላይ [ት]ን በምትክነት ያሳያል። ይኸውም በላ ብለን መብላት ስንል ነው። ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም /ዕ/ በመሀልና በመድረሻ እንደምትገደፍ ሁሉ፣ በመነሻስ ልትገደፍ ትችላለች ወይ? የሚል ነው። የዚሁ ተከታይ ሊሆን የሚችለው ሌላ ጥያቄ ደግሞ፣ /ዕ/ በግስ መነሻ ላይ የምትገደፍ ከሆነ፣ በአርዕስታዊ አቻው ላይ በ[ት] ትተካለች ወይ? የሚል ነው። በርግጥ /ዕ/ በአንዳንድ ግሶች መነሻ ላይ ትገደፋለች። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

አወቀ	9
አበደ	

የእነዚህ ግሶች መነሻ /አ/ የሚለው ታቸኛ አናባቢ ነው። ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአማርኛ ግሶች ታህታይ ቅርፅ በተናባቢ እንጅ በአናባቢ አይጀምርም። በዚሁ መሰረት የነዚህ ግሶች ታህታይ ቅርፅም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

/ዕኧውውኧቅኧ/	10
/ዕኧብብኧድኧ/	

መሆን ይኖርበታል። የሁለቱም መነሻ አግድ የማንቁርት ድምፅ የሆነው /ዕ/ ነው። ይህ ድምፅ እንደ /ህ/ የታቸኝነት ባህሪውን ከእሱ ቀጥሎ ለነባው መሀለኛ አናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ይስጥና ክፀታው ይጠፋል። የእሱን ባህሪ የወለደው /ኧ/ ከመሀለኛነት ወደ ታቸኛነት ተለውጦ [አ] ይሆናል። ይህ ቀደም ሲል ካየው ከ/ህ/ ሁኔታ ጋር አንድ ነው። ይሁን እንጅ፡ /ዕ/ም ሆነ /ህ/ በመነሻ ላይ ሲገደፉ፣ በሚገደፉበት አርዕስታዊ አቻ መድረሻ ላይ [ት]ን በምትክነት አያላዩም። ለሰዚህም የግሶቹ አርዕስታዊ አቻዎች ማወቅ እና ማበድ ናቸው። [ት]ን በመድረሻቸው ላይ ቢጨምሩ፣ ማውቀት እና ማብደት ይሆኑ ነበር። እነዚህ ደግሞ ተቀባይነት ያላቸው የአማርኛ ቃላት አይደሉም። ከዚህ የምንረዳው በአርዕስታዊ አቻቸው ላይ |ት|ን በምትክነት የሚያስገቡት እንደ አየ ያሉት የመነሻ ተናባቢ ድምፃቸውን ባህሪ ለሚቀጥለው አናባቢ ድምፅ ሳያጋቡ የሚገደፉት ብቻ መሆናቸውን ነው። ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፣ የአየ የመጀመሪያ ድምፅ /ር/ ነው። ይህ ድምፅ ከመነሻ ቦታው የጠፋው ያለምንም ዱካ ነው። ስለዚህም በግሉ መነሻ ላይ የተጎረደ ድምፅ እንዳለ ለማሳየት በአርዕ-ስቱ መድረሻ ላይ |ት|ን ያሳያል። ዝርዝሩን አሁንም ከባየ (1999) ላይ ይመልከቱ።

የግድፈት ሂደት የሚታይባቸው ሌሎች ቃላትም አሉ። አነሱም አንደ ሸጠ አና መሸ ያሉት ግሶች ናቸው። በነዚህ ቃላት ላዕላይ ቅርፅ የሚገኙት አናባቢዎች [ኧ] አና [ኤ] ናቸው። በዚህም ቀደም ሲል ካየናቸው ገዳፊ ቃላት ይለያሉ። ምክንያቱም ቀደም ሲል ባየናቸው ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ውስጥ ያየናቸው አናባቢዎች [ኧ] አና [አ] ስለነበሩ ነው። ለምሳሌ፣ በላ በሚለው ቃል ውስጥ መጀመሪያ [ኧ]ን ቀጥሎ ደግሞ [አ]ን ስናገኝ፣ ግለ በሚለው ቃል ውስጥ ደግሞ መጀመሪያ [ኣ]ን፣ ቀጥለን [ኧ]ን አናገኛለን። የአናባቢዎቹ መለያየትና የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆንም፣ በየቃሉ ውስጥ አንድ ተናባቢ ድምፅ አንደ ተገደፈ ሊጠቁም ይችላል። የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆን ግን ብቻውን የግድፈት ምልክት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ከሰረ-መሰረታቸው ባለሁለት ተናባቢ የሆኑ አንደ ተወ ያሉ ቃላት በቁዋንቁዋው ውስጥ ስለሚገኙ ነው[20]።

ከዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ታዲያ አንደ ሸጠ አና መሸ ያሉት ቃላትሰ ቢሆኑ አንድ ተናባቢ ለመገደፋቸው ማስረጃው ምንድን ነው? አነዚህስ ቢሆኑ ከሰረ-መሰረታቸው አንደ ተወ ባለሁለት ተናባቢ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? የሚል ነው። አንደ ሸጠ ያሉትን ባለሁለት ተናባቢ ናቸው አንዳንልማ፣ አንደ ተወ ካሉት ባለሁለት ተናባቢ የሚለዩበት አንድ ባህሪ አላቸው። ይኸውም በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] የምትለዋን ቤት ጠባቂ ድምፅ ማሳየታቸው ነው። ስለዚህም መሸ ብለን መምሸት አንደምንል ሁሉ፣ ተወ ብለን መተው አንጅ መተውት አንልም። ከዚህም በመነሳት አንደ መሸ ያሉት ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሁለት ሳይሆኑ፣ ባለሶስት ተናባቢ ናቸው ለማለት አንችላለን። ከተናባቢዎቻቸውም መካከል የመጨረሻውን፣ ማለትም ሶስተኛውን፣ ተናባቢ ይገድፋሉ። ተገዳፊው አሱ ባይሆን ኖሮ፣ በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] አትታይም ነበር። ይህች ድምፅ ምትከንትዋ በቃል መጨረሻ፣ አንዳንድ ጊዜም በቃል መነሻ ላይ ለሚገደፍ ድምፅ ነው ብለናልና።

ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው ሌላ ጥያቄ የተገደፈው ድምፅ ምንድን ነው? የሚል ነው። ቀደም ሲል ያየነው /ህ/ ወይም /ዕ/ ሊሆን አአይችልም። ቢሆን ኖሮ፣ ድምፁ ታቸኛ ስለሆነ፣ ይህን የታቸኛነት ባህሪውን ቀድሞት ለሚገባው አናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ሰጥቶ ሲጠፋ፣ አናባቢው ወደ [ኣ] ተለውጠ፣ የየቃላቱ ላዕላይ ቅርፅ ሻጠ አና መሻ መሆን ነበረበት። ይህ አለመሆኑ፣ ተገዳፊው ድምፅ የታቸኛነት ባህሪ ያለው አንደ /ህ/ ወይም /ዕ/ ያለ ተናባቢ

[20]ይህን ጉዳይ አለመልከቶ ባየ (1999) ሁሉም የአማርኛ ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሶስት ተናባቢ ብቻ እንደሆኑ ይገልፃል። በዚህ አመለካከት መሰረት፣ አንደ ተወ ያሉትም ባለሶስት ተናባቢ ናቸው። የመጨረሻው ተናባቢ ለመገደፉ ምልክቱ፣ በተወ አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ላይ [ት] በምትከነት ብቅ ማለትዋ ነው። ምንም ድምፅ ባልጎረዱ አንደ ሰበረ ባሉ ግሶች አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ምንም ምትክ ድምፅ አይገኝም። ስለዚህም ሰበረ ብለን ሰብር አንጅ ሰብርት አንልም። ተወ ብለን ትውት አንደምንለው ማለት ነው። ሸጠ ብለን መሸጥት ወይም ሽጥት አንልም፣ ምክንያቱም /ት/ በምትክነት የምትገባው በቃል መጨረሻ ላይ ለተጎረደ ድምፅ ነው። ሸጠ የጎረደው መካከለኛ ተናባቢውን ነው።

ድምፅ እንዳልሆነ ይጠቁመናል። የተገደፈው ደምፅ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሳችን /ይ/ ነው የሚል ነው። ይህ ውነት ከሆነ፣ የቃላቱ ታህታይ ቅርፅ፣

/ምኽስኽይኽ/ 11
/ለኽይይኽዋኽ/

መሆን አለበት።

ታህታይ ቅርፃቸው ይህን ከመሰለ፣ ላዕላይ ቅርፃቸው <u>መሸ</u> እና <u>ሸጠ</u> ሊሆን የቻለው አንዴት ነው? ቀደም ሲል አንድ በታህታይ ቅርፅ ውስጥ የሚገኝ ድምፅ ከላዕላይ ቅርፅ የሚጠፋው ባህሪውን አጠፉ ለሚገኝ ድምፅ አውርሶ ነው፣ ብለን ነበር። በዚያ መሰረት <u>መሸ</u> ውስጥ /ይ/ የተገደፈው ባህሪውን ለ/ኧ/ አና ለ/ለ/ ከሰጠ በውዋላ ነው ለማለት ይቻላል። የ/ይ/ ባህሪ ላየኛነትና ፌተኛነት ነው። ለዚህ ምክንያቱ ድምፁ የሚፈጠረው ላንቃ ላይ ስለሆነና ላንቃ ደግሞ፣ ቀደም ሲል አንደተገለፀው፣ የአፋችን መህል ጣሪያ መሆኑ ነው። በተጨማሪም [ይ] ለንል፣ የምላሳችን የፌት ከፍል ወደ ላይ፣ ማለትም ወደ ላንቃ ብቻ ሳይሆን፣ ወደፌት፣ ማለትም ወደ ላይኛው የውስጥ ድዳችን ክፍል ሰለሚላብ፣ ድምፁ የፌተኛነት ባህሪም አለው። ስለዚህም ላየኛነትንም ሆነ ፌተኛነትን አጣምሮ የያዘ ድምፅ ነው። ባንፃሩ ደግሞ /ኧ/ አና /ለ/ የላንቃ ድምፆች አይደሉም። /ኧ/ የመህል አናባቢ ሲሆን፣ /ለ/ ተናባቢ የድድ ድምፅ ነው። ድድም ከላንቃ ጋር ሲወዳደር ደረጃው ታቸኛነት ነው። ስለዚህም /ኧ/ ከ/ይ/ በፊት ሲገባ፣ የ/ይ/ን የላየኛነትና ፌተኛነት ባህሪያት ውሰዶ [ኤ] ይሆናል። እንደዚሁም /ለ/ የላየኛነቱን ባህሪ ውሰዶ [ሸ] ይሆናል። /ይ/ ሁለቱንም ባህሪያቱን ይሰጣል ማለት ነው። ላየኛነትን ለ/ለ/ ፌተኛነትን ደግሞ ለ/ኧ/።

የተገደፈው ድምፅ /ይ/ ለመሆኑ ማሰረጃው ምንድን ነው ቢባል፣ መልሳችን አንደ /ኧ/ ያለ የመህል አናባቢ ድምፅ ወደ [ኤ] ሊለወጥ የሚችለው ፌተኛ እና ላየኛ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገኝ ብቻ ነው፣ የሚል የሆናል። እነዚህን ባህሪያት የያዙ ድምፆች ደግሞ /ኢ/ እና /ይ/ ናቸው። ይሁን እንጅ በተጠቀሱት ምላሌዎች ውስጥ የተገደፈው ድምፅ /ኢ/ ላይሆን /ይ/ ነው። /ኢ/ ቢሆን ኖሮ የ ሸጠ ታህታይ ቅርፅ /ስኽኢዋኽ/ ይሆን ነበር። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችል አይደለም፤ ምክንያቱም ቁዋንቁዋው የአናባቢ ክትትሉሽን አይፈቅድም። ሁለተኛም የተገደፈው ድምፅ በርግዋ /ይ/ ለመሆኑ፣ የ<u>ሸጠ</u> ለማዊ አቻ በሆነው ቃል፣ በ<u>ሽያጭ</u> ውስጥ [ይ] በግህድ መክሰትዋ ማረጋገጫ ነው።

<u>መሸ</u> የሚለው ግስ ሁኔታም እንደ <u>ሸጠ</u> ነው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት /ይ/ የምትገባበት ቦታ ነው። <u>መሸ</u> ውስጥ /ይ/ የምትገኘው በቃሉ መህል ላይ ላይሆን፣ በመድረሻው ነው። ለዚህም ነው በአርዕስታዊ አቻው፣ ማለትም <u>በመሸሸት</u> ውስጥ [ት] በምትክነት የምትታየው።

/ይ/ ከፍናቢ ድምፅ አንደሆነች ቀደም ሲል ስለ ድምፆች አፈጣጠር ለንወያይ ገልፀናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ባህሪውን ለጎረቤቱ እያጋባ በቃል መህክል የሚጠፋው ሌላው ከፍናቢ /ው/ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ <u>ጠረ</u>

እና ዞረ ያሉ ግሶች ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ሁለት ተናባቢ ብቻ የሚታይባቸው ናቸው። ከአናባቢያቸው መካከልም የመጀመሪያው /አ/ ነው። እንደ ሰበረ እና እንደ ደመረ ያሉ ግሶችን ስንመለከት ግን በየተናባቢያቸው መካከል ላይ የሚገኘው ድምፅ /ሸ/ የሚለው አናባቢ እንደሆነ እንረዳለን። ይህ መደበኛው የግሶች ስርዓት ነው። የየግሱ አናባቢ ድምፅ ከ/ሸ/ የተለየ የሚሆነው፣ በግሱ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ ከነበሩት ተናባቢዎች መካከል እንደኛው በላዕላይ ቅርፅ በማይታይበት ጊዜ ነው። ተናባቢዎቹ ድምፆች በሙሉ በላዕላይ ቅርፅ የሚታዩ ከሆነ፣ አናባቢው ድምፅ ምን ጊዜም /ሸ/ ነው።

ከዚህ አንፃር ሲታዩ፣ እንደ ጠረ ያሉ ግሶች እንድ ተናባቢ ድምፅ ጎድሎአቸዋል ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም የመጀመሪያው አናባቢያቸው /ሸ/ መሆን ሲገባው፣ /አ/ ሆኖአልና። የማንኛውም መደበኛ ግሰ አናባቢ /ሸ/ ነው ካልን፣ የጠረ እና የዘረ ታህታይ ቅርፅም እንደሚከተለው መሆን አለበት።

/ጥሸውውሸርሸ/ 12
/ዝሸውውሸርሸ/

በግልፅ እንደሚታየው፣ በሁለቱም ግሶች ውሰጥ ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ /ው/ ነው። አናባቢውም /ሸ/ ነው። በታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ው/ የሚለው ተናባቢ ለመኖሩ ሶስት ማስረጃዎች አሉ። አንደኛው ከፍ ሲል እንደተጠቆመው የመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ ከመሀልኛነት ወደ ሁዋለኛነት፣ ማለትም ከ/ሸ/ ወደ /አ/ መለወጡ፣ ሁለተኛው ራሱ /ው/ የግሱቹ ሰማዊ እቻዎች በሆኑት፣

ጥውር [ጥእውውእር] 13
ዘዋሪ [ዝሸውአርኢ]
መዘውር [ምሸ-ዝሸውውእር]

በሚሉት ቃላት ውስጥ በግሀድ መከሰቱ ሲሆን፣ ሶስተኛው የየቃሉ መነሻ ተናባቢ ከዝርግነት ወደ ከብነት መለወጡ ናቸው። የግሶቹን የመነሻ ተናባቢ ድምፅ ለውጥ ከሚከተለው የየግሶቹ ላዕላይ ቅርፅ መመልከት ይቻላል።

ጠረ [ጥኦርሸ] 14
ዞረ [ዝኦርሸ]

በግልፅ እንደሚታየው፣ በየታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ጥ/ እና /ዝ/ የነበሩት ድምፆች በየላዕላይ እቻቸው ውስጥ ወደ [ጥ] እና [ዝ] ተለውጠዋል።

የየግሶቹ ታህታይ ቅርፅ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ከሆነ፣ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ /ው/ ባህሪውን ቀድሞት ለገባው አናባቢ ለ/ሸ/ ሰጥቶ ጠፍቶአል ማለት ነው። ታዲያ እዚህ ላይ ጥያቄው፣ /ው/ ለ/ሸ/ የሰጠው ባህሪ ምንድን

ነው? የሚል ነው። ከላይ እንደተመለከተው፣ የወረደ ታህታይ ቅርፅ /ጥኧውውኧርኧ/ ከሆነና፣ የላዕላይ ቅርፁ [ጮኦርኧ] ከሆነ፣ በታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ኧ/ የነበረው የመጀመሪያው አናባቢ ድምፅ ቅርፁን ለውጦ [እ] ሆንዋል፤ የመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ፣ ማለትም /ጥ/ ወደ [ጮ]፣ እንዲሁም /ዝ/ ወደ [ዝ] ተለውጦአል። አናባቢውም ሆነ ተነባቢዎቹ የተለወጡት ወደ ከብነት ነው። ይህ የከብነት ባህሪ በመለረቱ የ/ው/ ነው፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ድምፁ በሚፈጠርበት ጊዜ ምላስ ወደ ሁዋላ በመሳብ ወደ ትናጋ ለለሚወጣና፣ ከናፍረም ክብ ለለሚሆኑ ነው። ለለዚህም እንደ /ው/ ካለ ከብ ድምፅ ቀድሞ የሚገባ ሌላ አይነት ድምፅ ከብነትን ሊላበስ ይችላል። በዚሁ መለረት መጀመሪያ /ኧ/ ወደ /እ/ ሊለወጥ ችሎአል። ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ተናባቢው /ጥ/ ወይም /ዝ/ በ/እ/ ምክንያት ከብ ሊሆን ችሎአል።

የ/ስ/ን ወደ [ሽ]፣ እንዲሁም የ/ጥ/ን ወደ [ጭ] የመለወጥ ሂደት ቀደም ሲል በላንቃዊነት ለር ያየነው ለለሆነ፣ ቅምሩን እዚህ ላይ እንደገመውም። የ/ጥ/ን እና የ/ዝ/ን ወደ [ጮ] እና [ዝ] መለወጥም ዝቅ ብለን ለለምናየው፣ እዚህ ላይ የግድፈቱን ለርዓት ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን።

15

$$\begin{bmatrix} + \text{ ቀጣይ} \\ - \text{ ላይ} \\ + \text{ ሁዋ} \end{bmatrix} \longrightarrow \emptyset \; / \; \begin{bmatrix} + \text{ ግለ} \\ - \text{ ለም} \end{bmatrix}$$

ለርዓቱ አንድ ሁዋለኛ፣ ላየኛ፣ ወይም ታቸኛ እንዲሁም ቀጣይ የሆነ ድምፅ በግለ ውስጥ ሲገኝ፣ እንደሚገደፍ ያመለክታል። እዚህ ላይ ቅምሩን እለክሁን ካየናቸው ሌሎች ቅምሮች ለየት የሚያደርገው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ለድምፆቹ ግድፈት ምክንያት የሚሆነው የሚቀድማቸው ወይም የሚከተላቸው ድምፅ ላይሆን፣ የሚገቡበት የቃል ክፍል መሆኑ ነው። ድምፆቹ ግሳዊ በሆኑ ቃላት ላዕላይ ቅርፅ ውስጥ አይገኙም ማለት ነው።

በዝርዝር ሲታዩ ለግድፈት የሚዳረጉት ድምፆች /ህ፣ ዕ፣ ው እና ይ/ ናቸው። እነዚህም በሙሉ ተናባቢዎች ናቸው። ባህሪያቸውም የ/ይ/ እና /ው/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ ላየኛነትና ሁዋለኛነት ሲሆን፣ የ/ዕ/ እና /ህ/ ሁዋለኛነትና ታቸኛነት ነው። ግድፈቱ ግን አንባቢዎችንም ይጨምራል። ለዚህም የሚከተሉት ጥሩ ምላሌዎች ናቸው።

/ዝኧልኧ - አልኧም/	[ዝኧልኣልኧም]	ዘላለም	16
/ግኧድድኧልኧ-ኣችችኧው/	[ግኧድድኧልኣችችኧው]	ገደላቸው	
/ግኧድድኧልኧ-ኣት/	[ግኧድድኧልኣት]	ገደላት	

በነዚህ ምላሌዎች ውስጥ፣ ዘለለ (/ዝኧልኧ/) ቦሚለውና ገደለ (/ግኧድድኧልኧ/) በሚለው መድረሻ ላይ የሚገኘው /ኧ/ በቅንፉ ውስጥ በሚታየው ላዕላይ ቅርፅ

ውስጥ አይታይም፤ ተገድፎአል ማለት ነው። የተገደፈውም አለም (/አልኸም/) እና -አቸው (/-አችችኦው/) እና (/-አት/) በሚሉት ምዕላዶች መነሻ ላይ ቢሚገኘው በ/አ/ ምክንያት ነው። በየቃሉ ድንበር ላይ /ኧ/ እና /አ/ ተከታትለው ስለመጡ፤ /ኧ/ ለግድፈት ተዳርጎአል። ምክንያቱም ቁዋንቁዋው በላዕላይ ቅርፅ ውስጥ የአናባቢ ክትትሎሽን አይፈቅድም። ስለዚህም በታህታይ ቅርፅ ውስጥ ሁለት አናባቢዎች ተከታትለው ሲመጡ፤ ከሁለቱ አንዱ በላዕላይ ቅርፅ ላይ ይገደፋል። የአገዳደፉን ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

$$\begin{bmatrix} + \text{አ} \\ - \text{ታች} \end{bmatrix} \longrightarrow /_{\emptyset} - \begin{bmatrix} + \text{አ} \\ + \text{ታች} \end{bmatrix} \qquad 17$$

ቅምሩ በታህታይ ቅርፅ ውስጥ፤ እንደ /ኧ/ ያለ፤ [-ታች] የሆነ አናባቢ፤ እንደ /አ/ ካለ [+ ታች] ከሆነ አናባቢ በፊት ገብቶ ሲገኝ፤ እንደሚገደፍ ያመለክታል። የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት።

/ሰኧክርኡ-አል/	[ሰኧክርᵚአል]	ሰክሮአል	18
/ይ-ፍኧርኡ-አል/	[ይአፍኧርᵚአል]	ይፈሩአል	

በመጀመሪያው ምሳሌ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ /አ/ እና /አ/ ተከታትለው ገብተዋል። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ /ኡ/ እና /አ/ እንደዚሁ ተከታትለዋል። በላዕላይ ቅርፆቹ ውስጥ ግን /አ/ እና /ኡ/ ተገድፈው፤ ከነሱ ቀድሞ የገባው ተናባቢ፤ ማለትም /C/፤ ወደ [Cᵚ] ተለውጦአል። የለውጡ ምክንያት የተገደፉት ተናባቢዎች ናቸው። እነዚህ ተናባቢዎች ሁዋለኛ፣ ብሎም ከብ ስለሆኑ፤ ይህን ባህሪያቸውን ለ/C/ በማጋባት አሉንም እንደነሱ ከብ ያደርጉታል። ይህን ካደረጉ በሁዋላም ከቦታቸው ይጠፋሉ። በቃላቱ ውስጥ ሁለት ለውጦች ተካሂደዋል ማለት ነው። አንደኛው የተናባቢው /C/ ክበት ሲሆን፤ ሁለተኛው የአናባቢዎቹ ግድፈት ነው። ሁኔታው አሁንም ቁዋንቁዋው የአናባቢ ክትትሎሽን እንደማይፈቅድ የሚያረጋግጥ ነው።

የተገደፉት አናባቢዎች ዳረጎቹ /ኡ/ እና /አ/ ሲሆኑ፤ አስገዳፊው አናባቢ /አ/ ነው። አገባባቸውም ቀደም ሲል ስለ ምስስሎሽ ስንወያይ እንደተጠቀሰው፤ ከመሳይና ከአስመሳይ አስላለፍ የተለየ አይደለም። መሳዩ በስተግራ የሚገኘው እንደሆነ ሁሉ፤ ተገዳፊውም እንደዚሁ በስተግራ የሚገኘው አናባቢ ነው። ስርዓተ ግድፈቱን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} + \text{ከብ} \\ - \text{ታች} \end{bmatrix} \longrightarrow /_{\emptyset} - \begin{bmatrix} - \text{ከብ} \\ + \text{ታች} \end{bmatrix} \qquad 19$$

ቅምሩ በቃላት ሲገለፅ፣ በታሀታይ ቅርፅ ውስጥ፣ /ኡ/ ወይም /ኦ/ ከ/ኣ/ በፊት ሲገኝ ይገደፋል የሚል ነው።

ጥብቀት

እንድ በተፈጥሮው ጥብቅ ያልሆነ ድምፅ በአገባብ ምክንያት ጥብቅ ሊሆን ይችላል። ይህን የሚያበክትለው ሂደት ጥብቀት ይባላል። ሂደቱ በሶስት ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። እነዚህም ከትትሎሽ፣ ምሰሰሎሽ እና ሰነ-ምፅ-ላዳዊ እውዶች ናቸው። የሚከተሉት የያንዳንዳቸው ምሳሌዎች ናቸው።

(ሀ)	/ሰኤት ት-ሀኡን/	[ሰ^{ዖ}ኤትትእሀ^{ው}ኡ^{ው}ን]	ሴት ትሁን	1
(ሰ)	/ብኤት ሰኧርርኣ/	[ብ^{ዖ}ኤሰሰኧርርኣ]	ቤት ሰራ	
(መ)	/ል-ቅቅኣም-ኢ/	[ልእቅቅኣም^{ዖ}ኢ]	ልቃሚ	

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ የመጀሪያው ቃል መጨረሻና፣ የሁስተኛው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ እንድ አይነት ናቸው። ሁለት እንድ አይነት ድምፆች ተከታትለው በመምጣታቸው እንደ አንድ ጥብቅ ድምፅ ሊነበቡ ችለዋል። በሁስተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ የመጀመሪያው ቃል የመጨረሻ ድምፅ፣ (/ት/)፣ ከሁስተኛው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ፣ ከ(/ስ/)፣ ጋር በባህርየ ንባብ (ፍጥረት) በመመሳሰልዋ፣ የሁሰት /ስ/ ከትትሎሽ ሊከሰትና ይህም እንደ አንድ ጥብቅ [ሰሰ] ሊነበብ ችሉአል።

በሶስተኛው ምሳሌ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከመጀመሪያዎቹ የተለየ ነው። እንደ <u>ልቃሚ</u> ያሉ ሰሞች በሙሉ <u>*ቅድመ መድረሻ*</u> (ከመድረሻ በፊት የሚገኝ) ተናባቢያቸውን ያጠብቃሉ። ይህም ከሌሎች አይነት ሰሞች የሚለያቸው ባህሪ ነው። ስምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እናነፃፅር።

(ሀ)	/ጥኧራግኣ/	ጠራጊ	/ትኧ-ጥኧርርእግኢ/	ተጠራጊ	2
	/ጥኧርኣብኣ/	ጠራቢ	/ትኧ-ጥኧርርኣብኣ/	ተጠራቢ	
	/ሰኧብኣርኣ/	ሰባሪ	/ትኧ-ስኧብብኣርኣ/	ተሰባሪ	
(ለ)	/ጥ-ርርእግኣ/		[ጥእርርኣጊ]	ጥራጊ	3
	/ጥ-ርርኣብኣ/		[ጥእርርኣብኢ]	ጥራቢ	
	/ሰ-ብብኣርኣ/		[ሰእብብኣርኢ]	ሰባሪ	

በ(ሀ) ሰር የመጀመሪያው ረድፍ ላይ፣ በእዝባር ውስጥ የሚታዩት ቃላት አድራጊ ስሞች ይባላሉ። ድርጊት ፈፃሚ የሆነ ሰውን ያመለክታሉ። በሶስተኛው ረድፍ

በአዝባር ውስጥ የሚታዩት ደግሞ ተደራጊ ስሞች ይባላሉ። አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን፣ ግለትም የድርጊት ተጠቂ የሆነውን ነገር፣ ያመለክታሉ። በ(ለ) የመጀመሪያ ረድፍ ውስጥ የሚታዩት፣ የውጤት ስሞች ይባላሉ። አንድ ድርጊት ከተፈፀመ በሁዋላ የሚታየውን ውጤት ወይም ድራጊ ነገር ያመለክታሉ። ተደራጊዎቹና ድራጊዎቹ ቅደመ-መድረሻ ድምፃቸውን ያጠብቃሉ። በዚህም ምንም ድምፅ ከማያጠብቁት ከአድራጊ ስሞች ይለያሉ። ተደራጊና ድራጊ ስሞች የሚለያዩት /ተ/ን በማለቀደምና ባለማስቀደም ብቻ ነው። ተደራጊዎቹ ብቻ /ተ/ን ያስቀድማሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታም የዚሁ የቅድመ-መድረሻ ድምፅ መጥበቅና አለመጥበቅ በግሶች መካከልም ልዩነትን ይፈጥራል። ለአለብነት የሚከተሉትን አንመልከት።

/ጥሾርርሾግሾ/	ጠረገ	/ይ-ጥሾርግአለል/	ይጠርጋል	4
/ጥሾርርሾብሾ/	ጠረበ	/ይ-ጥሾርብአለል/	ይጠርባል	
/ስሾብብሾርሾ/	ሰበረ	/ይ-ስሾብርአለል/	ይሰብራል	

በመጀመሪያው ዕዝባር ውስጥ የተመለከቱት ግሶች የቀዳማይ አኳንቀፅ ግሶች ይባላሉ። ያለቀ ድርጊትን ያመለክታሉ። በሶስተኛው ረድፍ የሚታዩት ደግሞ የካልዓይ አኳንቀፅ ግሶች ይባላሉ። የሚያመለክቱት ያላለቀ ወይም ያልተጀመረ ድርጊትን ነው። የሁለቱን አኳይነት ግሶች ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ድምፅ ብንመለከት፣ በቀዳማዮቹ ውስጥ ድምፁ አንደጠበቀ፣ በካልዓዮቹ ውስጥ ደግሞ አንዳልጠበቀ አንረዳለን። የሁለቱ አኳንቀያች ልዩነት መበረት የዚህ ድምፅ መጥበቅ ወይም አለመጥበቅ ነው። ከዚህ አኳንፃር ሲታይ፣ ጥብቀት ስሞችንና ግሶችን በአኳይነት በአኳይነት የመለያየት ተግባር እንዳለው እንረዳለን። ቅድመ-መድረሻው ድምፅ የሚጠብቀው፣ ቀደም ሲል ግድፈትን አኳስመልክተን አንደገለፅነው፣ ስነ-ድምፅ-ልሳናዊ በሆነ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ምፅላዳዊ በሆነ አኳኅብም ጭምር ነው።

ከዚህ ላይ ጥብቀት በቃል መነሻ ካልሆነ በስተቀር፣ በሌላ በማንኛውም ቦታ ሊከሰት ይችላል። በቃል መካከል ላይ የሚከሰተው ከላይ በተራ ቁጥር (3) የሚታየውን ይመሰላል። በቃል መድረሻ የሚከሰተውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

/ስ-ብ-ረ-/	[ሰሾብሾርር-]	ሰበር-	5
/ፍ-ጥ-ን-/	[ፍሾጥሾንን-]	ፈጠን-	
/ው-ሰ-ድ-/	[ውሾሰሾድድ-]	ወሰድ-	

በግልፅ እንደሚታየው፣ በእዝባሩ ውስጥ የተመለከቱት ቃላት የመድረሻ ተናባቢ ጥብቅ ነው። ቃላቱ በቀዳማይ አንቀፅ ቅርፅ ሲገኙ ይህን ተናባቢያቸውን እያጠብቁም። ስለዚህም [ሰኣብብኣር-ኣ] እንጅ [ሰኣብኣርር-ኣ] አንልም።

ልለት

ልለት የጥብቀት ተቃራኒ ነው። አንድ እግድ ድምፅ ወደ ፍግድነት ከዚያም አልፎ ወደ ፍትግነት ሊሰወጥ ይችላል። ይህ አይነቱን ሰውጥ የሚያመጣው ሂደት ልለት ይባላል። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

/ልኣብ/	[ልኣብ]	1
/ክኣብ/	[ክኣብ]	
/ሰ-ብ/	[ሰእብ]	
/ዝ-ንኣብ/	[ዝእንኣብ]	
/ጥ-ግኣብ/	[ጥእግኣብ]	

በዕዝባሩ ውስጥ የሚታዩት ቃላት የሚጨርሱት በ/ብ/ ነው። ይህ ድምፅ ‘ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው እግድ ነው። ይሁን እንጅ፣ እነዚህን ቃላት በምናነብበት ጊዜ፣ ድምፁ የሚወጣው (የሚሰማን) እግድ ሆኖ እይደለም፤ ፍትግ ሆኖ ነው። በቃላት መካከልም እንደዚሁ ፍትግ ሆኖ የሚነበብበት ጊዜ እስ። ስምሌ የሚከተሉትን አንመልከት።

/ፅኣብኣል/	[ፅኣብኣል]	ፀበል	2
/ዝኣብኣንኣይ/	[ዝኣብኣንኣይ]	ዘበናይ	
/ውኣብኣቅ/	[ውኣብኣቅ]	ወበቅ	

በቅንፉ ውስጥ በሚታዩት ምሳሌዎች ውስጥ የሚገኘው [ብ] ልል ነው። ድምፁ እግድ ሆኖ የሚነበበው እንደሚከተሉት ባሉ ቃላት ውስጥ፣ በመነሻ ላይ ሲገኝ ነው።

/ብኣግ/	[ብኣግ]	3
/ብኣል/	[ብኣል]	
/ብኣርር/	[ብኣርር]	
/ብ-ል/	[ብእል]	

ሁኔታው ሁለት አይነት የ[ብ] ድምፅ እንዳስ ያስገነዝባል። አንደኛው እግድ፣ ሊላኛው ደግሞ ፍትግ [ብ] (β) ነው። ፍትጉ [ብ] በቃል መሀከልና በቃል

መድረሻ ላይ ሲገኝ፣ እግዱ ግን በቃል መነሻ ላይ ይገኛል። የፍትጉ [ቧ] ስርጭት ይሰፋል ማለት ነው። ይህ ከሆነ፣ ምናልባትም ፎኒሙ እግዱ ሳይሆን፣ ፍትጉ ሊሆን ይችላል[21]። ምክንያቱም የስርጭት ስፋት የፎኒምነት ምልክት ስለሆነ ነው። ከዚህ ላይ ግን አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም እግድ [ብ] ስንል፣ ጥብቅ ([ብብ]) ማለታችን አለመሆኑን ነው። ጥብቅ ([ብብ]) በቃል መካከልና በቃል መድረሻ ላይ እንደሚከሰት ቀደም ሲል ስለ ጥብቀት ስንወያይ አይተናል። ሁኔታው ሶስት የ/ብ/ ድምፅ እንዳለ ያስረዳል። እነዚህም መደበኛው /ብ/፣ ጥብቁ /ብብ/ እና ልሉ ወይም ፍትጉ [ቧ] ናቸው። ፍትጉ የመደበኛው /ብ/ ማለትም የፎኒሙ ላዕላይ ከሳች ነው። ስርዓቱን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

4

$$\begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ +\ \text{እግድ} \\ -\ \text{ድድ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ -\ \text{እግድ} \\ -\ \text{ድድ} \end{bmatrix} \Big/ \begin{bmatrix} +\ \text{አ} \end{bmatrix} __$$

ቅምሩ አንድ የድድ ያልሆነ እግድ ተናባቢ፣ ከአናባቢ ድምፅ በሁዋላ ሲገኝ፣ ወደ ፍትግነት እንደሚለወጥ ያሳያል።

በዚሁ አካሄድ አንድ አናባቢ ድምፅ ከሌላ አናባቢ ድምፅ ቀጥሎ ሲገባ፣ አናባቢነቱን ትቶ ወደ ከፍናቢነት የሚለወጥበት ጊዜ አለ። ይኸውም እንደሚከተሉት ባሉ ቃላት ውስጥ ነው።

			5
/ልኤልኣ-ኡ/	[ልኤልኣው]	ሌላው	
/ጥ-ጅጅኣ-ኡ/	[ጥእጅጅኣው]	ጥጃው	
/ጅኽብኽንኣ-ኢትኡ/	[ጅኽብኽንይትኡ]	ጀበናይቱ	
/ይኣችች-ንኘኣ-ኢትኡ/	[ይኣችችእኘኘእይትኡ]	ያችኖይቱ	

በእዝባሩ ውስጥ በሚታዩት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ፣ /ኡ/ እና /ኡ/ ተከታትለው በመግባታቸው፣ /ኡ/ ወደ ከፍናቢነት ተለውጦ [ው] ሆኖአል። ይህም በቅንፉ ውስጥ በግልፅ ይታያል። በሁለተኛዎቹ ምሳሌዎች፣ በዕዝባሩ ውስጥ /ኣ/ እና /ኢ/ እንደዚሁ ተከታትለው ገብተዋል፣ በቅንፉ ውስጥ እንደሚታየው፣ /ኢ/ ወደ [ይ] ተለውጣለች። /ኡ/ እና /ኣ/ ከሙሉ አናባቢነት ወደ ከፊል አናባቢነት፣ ማለትም ወደ ከፍናቢነት፣ ተለውጠዋል።

ቀደም ሲል ስለ ቀለም አወቃቀር ስንወያይ አንዳየነው፣ አናባቢዎች የየቀለሙ ምሰሶዎች ናቸው ብለን ነበር። ያለእነሱ ቀለም ሊዋቀር አይችልም። በዚህም ባህሪያቸው ከተናባቢዎች ይለያሉ። ከፍናቢዎችም እንደ ተናባቢዎች ምሰሶ አየሆኑ ቀለም ሊያዋቅሩ አይችሉም። ከዚህ ተግባራዊ ልዩነት የተነሳ

[21] ይህን ጉዳይ በሚመለከት ደግፍ ኤጥሮስ (1998)ን ይመልከቱ።

እናባቢዎችን <u>ቀለማይ</u>፣ ተናባቢዎችን (ከፍናቢዎችን ጭምር) <u>ኢቀለማይ</u> ብሎ መለየት ይቻላል። አንድ አናባቢ ወደ ከፍናቢነት ሲለወጥም፣ ሂደቱ ከቀለማይነት ወደ ኢቀለማይነት ነው። ከዚህ አኳያ ከላይ የሚታየውን ለውጥ አንደሚከተለው በቅምር ማስቀመጥ ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} + \text{ቀለ} \\ + \text{ላይ} \\ + \text{ሁሞ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} - \text{ቀለ} \\ + \text{ላይ} \\ + \text{ሁሞ} \end{bmatrix} \Big/ \begin{bmatrix} + \text{ቀለ} \end{bmatrix} \quad 6$$

ቀለ = ቀለማይ
ሁሞ = ሁሞላ

ይህ ቅምር እንድ፣ ሁሞለኛና ላየኛ የሆነ ድምፅ ከቀለማይ ድምፅ በሁሞላ ሲገባ፣ ወደ ኢቀለማይነት ይለወጣል የሚል ነው። በተራ አነጋገር፣ /ኡ/ ከሌላ አናባቢ በሁሞላ ሲገኝ፣ ወደ [ው]፣ /ኢ/ም እንደዚሁ ባለ አካባቢ ለትገኝ ወደ [ይ] ትለወጣለች የሚል ነው። ሌሎች የማይመሳሰሉ አናባቢዎች ተከታትለው ሲገቡ ከሁለቱ እንደኛው ይገደፋል እንጅ ወደ ከፍናቢነት አይለወጥም። ሁኔታውን ቀደም ሲል ስለ ግድፈት ሰንወያይ አይተነዋል።

ኢምሰለት

እስካሁን ያየናቸው ሂደቶች እንድ ድምፅ ቀድሞት ወይም ተከትሎት ከጣ ሌላ ድምፅ ጋር ሲመሳሰል ነው። ስለዚህም ሂደቶቹ በሙሉ ምሰለታዊ ነበሩ። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ አንድ ድምፅ ከጎኑ ካለ ሌላ ድምፅ ጋር በመሰረተ ፍጥረቱ ተመሳሳይ ከሆነ፣ ከዚያ ድምፅ የተለየ እንዲሆን የሚያደርግ ሂደትን እንመለከታለን። ለዚህ አይነቱ ሂደት የሚከተሉት ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

/አቅጥአጭጭአ/	[አግጥአጭጭአ]	አቅጣጫ/አአግጣጫ[22]	1
/ግ-ድግ-ድድአ/	[ግአርግእድድአ]	ግድግዳ/ግርግዳ	
/-እንብ-ድብ-ድ/	[እንብእርብእድ]	እንብድብድ/ እንብርብድ	
/ግ°ኧድግ°አድድአ/	[ግ°ኧርግ°አድድአ]	ጎድጉዋዳ/ጎርጉዳ	

በዕዝባሩ ውስጥ /-ቅጭ-/፣ /-ድግ-/፣ /-ድብ-/ እና /-ድግ°-/ የነበሩት ድምፆች በማዕዘኑ ውስጥ[-ግጥ-]፣ [-ርግ-]፣ [-ርብ-] እና [-ርግ°-] ሆነዋል። በመጀመሪያው

[22] እዚህ ላይ በየዕዝባሩ የተመልከተው ታህታይ ቅርፅ ሁለት፣ ሁለት ላዕላይ ቅርፅ ሊኖረው እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ምናልባትም አንዱ ቀርፅ በአንዱ አካባቢ፣ ሌላው ደግሞ በሌላ አካባቢ ሊነገር ይችላል። እንደዚህም ሆኖ፣ የቃላቱ ልዩነት መንሰዔ በታህታይ ቅርፅ ላይ የሚታየው የድምፆቹ ተመሳሳይ ባህሪ ነው።

ምሳሌ ተከታትለው የገቡት /ቅ/ እና /ጥ/፣ እግድ፣ ግንቁርታዊና ኢነዛሪ ድምፆች ናቸው። እግድነት፣ ግንቁርታዊነትና ኢነዛሪነት የጋራ ባህሪያታቸው ናቸው። /ድ/ እና /ግ/ ፣ /ድ/ እና /ብ/ እንዲሁም /ድ/ እና /ሞ/ እግድና ነዛሪ ድምፆች ናቸው። እነዚህም እግድነትንና ነዛሪነትን ይጋራሉ። ባጭሩ በየጥንዱ ቃላት መካከል ያለው የድምፅ ልዩነት የመካነ ፍጥረት ብቻ ነው። በባህርየ ፍጥረታቸው እንድ ናቸው፤ ከናፍራዊ (ከብ) ከሆነችው ከ/ሞ/ በስተቀር። እንደነዚህ ያሉ ተመሳሳይ ድምፆች ተከታትለው ሲገቡ፣ እንደኛው ከሌላኛው በእንዱ ባህሪው ይለያል። ስምሳሌ፣ በመጀመሪያው ቃል ውስጥ /ቅ/ ግንቁርታዊነትዋንና ኢነዛሪነትዋን ትታ፣ ትናጋዊነትዋን ጠብቃ ነዛሪ ሆናለች። በዚህም ግንቁርታዊና ኢነዛሪ ከሆነው ጎረቤትዋ ግለትም ከ/ጥ/ ልትለይ ችላለች። በሚቀጥሉት ውስጥም የየጥንዱ የመጀመሪያ ድምፅ እግድነቱን ትቶአል። በመተውም እግድ ከሆነው ጎረቤቱ ሊለይ ችሉአል።

እዚህ ላይ ተለዋጩ ድምፅ ቀዳሚ፣ እስለዋጩ ደግሞ ተከታይ መሆኑንና ይህም ቀደም ሲል ካየነው፣ ከመሳይና ከአስመሳይ ድምፆች እስላለፍ ጋር አንድ መሆኑን ልብ ይሉአል። በተመለከትናቸው የምስለት ሂደቶች ውስጥ አስመሳዩ ድምፅ ባብዛኛው ተከታይ፣ መሳዩ ደግሞ ቀዳሚ እየሆነ እንደሚገባ ተመልክተናል። የኢምስለቱን አካሄድ እንደሚከተለው እናሳያለን።

(ሀ)
$$\left[+\ \text{ግንቁ}\right] \longrightarrow \left[-\ \text{ግንቁ}\right] \quad / \quad \text{—} \quad \left[+\ \text{ግንቁ}\right]_{2}$$

(ለ)
$$\begin{bmatrix}+\ \text{እግድ}\\+\ \text{ድምፅ}\end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix}-\ \text{እግድ}\\+\ \text{ድምፅ}\end{bmatrix} \quad / \quad \text{—} \quad \begin{bmatrix}+\text{እግድ}\\+\text{ድምፅ}\end{bmatrix}$$

የመጀመሪያው ቅምር /ቅ/ ወደ [ግ]፣ ሁለተኛው ደግሞ /ግ/ እና /ብ/ ወደ [ር] እንደተለወጡ ያመልክል።

ሰርገት

ቀደም ሲል፣ የአግርኛን የቀለም እወቃቀር ስንመረምር፣ እንድ ቀለም በመነሻው ላይ እንድ ተናባቢ ብቻ፣ በመድረሻው ላይ፣ እንድ ረዥም ወይም ከሁለት የማይበልጡ ተራ ተናባቢዎች ሊኖሩት እንደሚችል ገልፀን ነበር። እንደ በግ ([ብኧግ])፣ ቀልድ ([ቅኧልድ]) እና ሰቅ ([ስኧቅት]) (=ቀፀቶ) ያሉ ባለ አንድ ቀለም ምዕላዶች ስዚህ ምሳሌ ናቸው። ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ በባለ ብዙ ቀለም ምዕላድ ውስጥ፣ በየቀለሞቹ ድንበር ላይ የተናባቢዎች ወይም የአናባቢዎች

ክትትሎሽ ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ፣ ቀልድ (ቅኧልድ) እና ሰቅ (ሰኧቅቅ) በሚሉት ባሰ አኣንድ ቀሰም ምዕላዶች መጨረሻ ላይ የሁለተኛ መደብ እመልካች የሆነውን /-ህ/ን ብንጨምር፣ የምናገኘው ቀልድህ /ቅኧልድ-ህ/ እና ሰቅህ /ሰኧቅቅ-ህ/ የሚል ይሆናል። ይህም ከእናባቢው ቀጥሎ ሶሰት ተናባቢዎች ተከታትለው እንደ ገቡ ያሳያል። ይህ ደግሞ ከቁዋንቁው የቀሰም አወቃቀር ሰርዓት ውጭ ነው። ምክንያቱም የእወቃቀሩ ሰርዓት ሶሰት ጨራሽ ተናባቢዎችን አይፈቅድም። ሰርዓቱን አንዲከተል ከፈለግን፣ ከሁለተኛው ተናባቢ ቀጥሎ፣ አንድ አናባቢ ድምፅ ጣልቃ ማሰገባትና የተከታተሉትን ተናባቢ ድምፆች መለያየት ያሰፈልጋል። የምናሰገባው እናባቢም፣ ማንኛውም ሳይሆን /እ/ ብቻ ነው።

ይህ አናባቢ በተጠቀሱት ቦታዎች ሲገባ፣ የምናገኘው ቀልድህ [ቅኧልድኣህ] እና ሰቅህ [ሰኧቅቅኣህ] የሚል ይሆናል። ህጉ-ወጥ የነበረው የሶሰት ተናባቢዎች ከትትሉሽ፣ በገባው አናባቢ ምክንያት ህገኛ ሲሆን ችሉአል። በዚህ አይነት የተናባቢዎችን ከትትሉሽ ሰማሰቀረት የሚገባ አናባቢ *ሰርን-ገብ* አናባቢ ሲባል፣ የማሰገባቱ ሂደት ደግሞ *ሰርገት* ይባላል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም ሰርጎ-ገብዋ አናባቢ በተናባቢዎቹ መካከል ሰትገባ፣ በፊት የነበረው የቀለም አወቃቀር ይቀየራል ወይ? የሚል ነው። ቀልድህ [ቅኧልድኣህ] የሚሰውን ቃል አንውሰድና ሁኔታውን አሰቲ አንመልከተው። ቃሉ ሁለት ቀሰሞች አሉት። የመጀመሪያው ቀለም በፊትም /ኧ/ ቢሚለው አናባቢ ምሰኑት የተፈጠረውና ቀልድ [ቅኧልድ] የሚሰው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሰርጋ በገባችው አናባቢ አማካኝነት የተፈጠረው ሁለተኛው ቀሰም ነው። አፈጣጠሩም አንደሚከተለው ነው።

(ሀ)



ቅኧልድኣህ 1

በያናባቢው አናት ላይ የሚታዩት ቁዋሚ መበመሮች አናባቢዎቹ የቀለሙ ምሰሶ ወይም ቁዋሚ መሆናቸውን ያመለክታሉ። ቀደም ሲል ስለ ቀለም አወቃቀር ባየነው ሰርዓት መሰረት፣ እናባቢዎቹ መጀመሪያ በሰተግራቸው ካለው አንድ ተናባቢ ጋር ይቀናጃሉ። ይህን ሲያደርጉ ቅንጅቱ የሚከተለውን ይመስላል።

(ለ)



ቅኧልድኣህ 2

ከዚህ በሁዋላ አያንዳንዱ አናባቢ በሰተቀኙ ካለው ተናባቢ ጋር አንደገና ይዋቀራል። ይህ ሲሆን፣ በ(ለ) የተመለከተው መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።

(መ) 3



ቅኧልድአህ

በሰርጎ-ገብዋ አናባቢ ምክንያት ሁለት ቀለሞች ሊፈጠሩ ችለዋል።

ሰርጎ-ገብዋ አናባቢ ከመግባትዋ በፊት የነበረው ቀለማዊ አወቃቀር የሚከተለውን ይመስል ነበር።

ቀ 4



ቅ ኧ ል ድ

አሁን የዚህንና ከላይ በ(መ) የተመለከተውን የቀለም አወቃቀር አናነፃፅር። በዚህ ቀለም ውስጥ የጨራሹ ከፍል የሆነችው ተናባቢ ድምፅ፣ ማለትም [ድ]፣ በ(መ) ውስጥ ሰርጋ ከገባችው እናባቢ ጋር ተዋቅራ የሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ ሆናለች። ያወቃቀር ለውጥ አድርጋለች ማለት ነው። ይህም ስለሆነ፣ የሁለቱ ቀለሞች ይዘት ከላይ እንደሚታየው [ቅኧል - ድእህ] የሚል ቅርፅ ሊይዝ ችሉአል። ሁለቱም ቀለሞች እኩል /ተኣተ/ እና /ተኣተ/ የሚል መዋቅር ሊይዙ ችለዋል። ባጭሩ /ተኣተተ/ የነበረው መዋቅር፣ የመጨረሻ ተናባቢውን ለሁለተኛው ቀለም ሰጥቶ፣ /ተኣተ/ ሆኖአል። ስለዚህም ከላይ ለተነሳው ጥያቄ መልሳችን፣ አወን የአወቃቀር ለውጥ ሊኖር ይችላል የሚል ነው። ለውጡም ሁለት ጨራሽ ተናባቢ ያለው ቀለም፣ የመጨረሻውን ጨራሽ ተናባቢ ለሚቀጥለው ቀለም ከፋች ተናባቢ እንዲሆን የሚያስገድድ ነው። ባጭሩ ብዙ ጨራሽ ተናባቢ ያለው፣ ምንም ከፋች ተናባቢ ለሌለው ቀለም አንደሚሰጥ ያሳያል።

ከተሰጡት ምሳሌዎች እንደምንረዳው፣ አናባቢዋ ሰርጋ የምትገባው፣ በቀለሙ መድረሻ እና ቅድመ-መድረሻ ተናባቢዎች መካከል ነው። ሰርገቱ ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም። በቃል መነሻ ላይ በሚገኙ ተከታታይ ተናባቢ ድምፆች መካከልም ሊካሄድ ይችላል። ለዚህ የሚከተሉት ምሳሌዎች ናቸው።

/ል-ብ-ስ/	[ልኣብሰ]	5
/ጥ-ብ-ቅ/	[ጥኣብቅ]	
/ው-ር-ስ/	[ውኣርሰ]	

በእዝባሩ ውስጥ የሚታዩት ሰር ምዕላዶች ናቸው። ወደፊት በሰነ-ቃላቱ ክፍል በሰፈው እንደምናየው፣ እንደነዚህ ያሉ ሰሮች ከተናባቢ ድምፆች ብቻ የሚቀናጁ ናቸው። በየተናባቢዎቹ መካከል በሚታየው ክፍት ቦታ (-) የተለያዩ አናባቢዎችን በማስገባት ከሰሮቹ ላይ የተለያዩ ቅርፆችን መመሰረት ይቻላል። ለምሳሌ፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ተናባቢ መካከል ላይ ብቻ [አ]ን አሰርጎ በማስገባት የተናባቢዎችን ክትትሉሽ ሰብሮ፣ ከላይ በቅንፉ ውስጥ እንደሚታዩት ያሉ ቃላትን መፍጠር ይቻላል። የአናባቢውን የአሰራረግ ሰርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

$$(ሀ)\quad \text{Ø} \longrightarrow \text{አ} \;/\; \underset{\text{ቃል}}{[\text{ተ-ተ...}]} \qquad 6$$

ሰርዓቱ በቃል መነሻ ላይ ተናባቢዎች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ፣ ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ [አ] እንደሚገባ ያመለክታል። ይህንና ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ሰርዓት እንደሚከተለው አድርጎ ማጠቃለል ይቻላል።

$$(ለ)\quad \text{Ø} \longrightarrow \text{አ} \;/\; \underset{\text{ቃል}}{[\text{ተ-ተተ-ተ(ተ)}]} \qquad 7$$

ይህ የተጠቃለለው ሰርዓት፣ በቃል መነሻ ከሚገኝ አንድ ተናባቢ ቀጥሎ እና በቃል መካከል ከሚገኙ ሁለት ተከታታይ ተናባቢዎች ቀጥሎ [አ] መግባት እንዳለበት ያሳያል። የተናባቢዎች ክትትሉሽ የሚፈቀደው በቃል መካከልና መድረሻ ላይ ሲሆን፣ የሚከታተሉት ተናባቢዎች ቁጥርም ሁለት ብቻ ነው። የተናባቢዎቹ ቁጥር ከሁለት በሚበልጥበት ጊዜ፣ ክትትሉሹን ለመሰበር [አ] እየሰረገ ይገባል።

ጉዳዩ በዚህ ብቻ አያበቃም። በቃል መድረሻ ወይም መካከል ላይ [አ] በሁለት ተናባቢዎች መካከል ልትገባ ትችላለች። ይህም የሚሆነው ከተናባቢዎቹ ሁለተኛው /ር፣ ል፣ ን፣ ም፣ ኝ/ ሲሆን ነው። እነዚህ ድምፆች ቀደም ሲል ጎናዊና ሰርናዊ ብለን የገለፅናቸው ናቸው። ከሌሎች ተናባቢዎች የሚለዩበት የጋራ ባህሪ አላቸው። እሱም <u>አሰተጋቢነት</u> ነው። ይህም ማለት ከሌሎች ተናባቢዎች የበለጠ ደምቀው ለጆሮ ይሰማሉ እንደማለት ነው። ለምሳሌ፣ ወና ቤት ውስጥ ገብተን /ል/፣ /ክ/ ብንል፣ /ል/ ከ/ክ/ የበለጠ ራሱን ሲያሰተጋባ ይሰማናል። በዚህ ባህሪያቸው አሰተጋቢ ድምፆች ከአናባቢዎች ጋር ሊመደቡ ይችላሉ፤ ምክንያቱም አናባቢዎች ከሁሉም ድምፆች የበለጠ አሰተጋቢ ናቸው። ወደዝረዝሩ እንሂድም።

/ክኧድር/ የሚለው ታህታይ ቅርፅ ውስጥ ክትትሉሹ የ/ድ/ እና የ/ር/ ሰለሆነ፣ ከ/ድ/ ቀጥሎ፣ [አ] በመግባቱ፣ ላዕላይ ቅርፁ [ክኧድኧር] የሚል ሆኖአል። /ውኧርድ/ በሚለው ውስጥ ግን ክትትሉሹ የ/ር/ እና የ/ድ/ በመሆኑ፣ በመካከላቸው [አ]ን ማስገባት አላስፈለገም። ሰለዚህ በቃል መካከል ላይ

የተናባቢዎች ከትትሎሽ የሚፈቀደው፣ ተናባቢዎቹ ከሁለት ሲበልጡ፣ ወይም ሁለተኛው ተናባቢ *ሉስታንቢ* ሲሆን ነው[23]።

እስካሁን ያየናቸው ምሳሌዎች [እ] ተናባቢዎችን እየተከተለ ሲገባ የሚያመለክቱ ናቸው። በተቃራኒው ይኸው ድምፅ ተናባቢዎችን እየቀደመ የሚገባበት ጊዜም አለ። ላዚህ ምሳሌ የሚሆኑት እንደሚከተሉት ያሉ ቃላት ናቸው።

/ር-ግም3ን/	[እርግእም3ን]	እርግማን	8
/ር-ጥብእን/	[እርጥእብእን]	እርጥባን	
/ሰ-ልእም/	[እሰልእም]	እሰላም	

በእገባሩ ውስጥ /ተተተእተ/ የነበረው፣ በቅንፉ ውስጥ [እተተእተእተ] ሆኖአል። ከላይ ተጠቃሉ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት፣ በቅንፉ ውስጥ የተቀመጠው ቃል ቅርፅ [ተእተተእተ] መሆን አለበት። ይህ ከሆነ፣ ለምሳሌ፣ <u>እርግማን</u> [እርግእም3ን] የሚለው <u>ርግማን</u> [ርእግእም3ን] መሆን ነበረበት። በእጠቃቀም ደረጃ ሁለቱም ቅርፆች ተቀባይነት ያላቸው ይመስላል። ይህ ከሆነ፣ ከአንድ ታህታይ (ፎኒማዊ) መሰረት ላይ ሁለት ላዕላይ ቅርፆች ይወጣሉ ማለት ነው። እንደኛው <u>ርግማን</u> [ርእግእም3ን] ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ <u>እርግማን</u> [እርግእም3ን] ነው። የመጀመሪያው ከላይ ተጠቃሉ በቀረበው ስርዓት መሰረት የወጣ ነው። የሁለተኛው አወጣጥ ግን አሻሚ ነው። ተጠቃሉ ከተቀመጠው ስርዓት አንፃር ስናየው፣ ቃሉ የሚከተለውን ሂደት እንዳለፈ እንረዳለን።

/ ር-ግም-ን /

↓ 9

(ሀ) [ርእግምእን]

↓

(ለ) [እርግ-ምእን]

↓

(መ) [እርግእምእን]

መጀመሪያ፣ ተጠቃሉ በተቀመጠው ህግ መሰረት፣ ስርጎ-ገብዋ እናባቢ /ር-ግም-ን/ በሚለው ውስጥ በሚገኙት ከፍት ቦታዎች ትገባለች። ይህን በታደርግ፣

[23] ተከታታዮቹ ተናባቢዎች እገድ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፡

/ውኽት/	[ውኽት]	* [ውኽእት]
/ው-ቅጥ/	[ውእቅጥ]	* [ውእቅእጥ]
/ን-ግድ/	[ንእግድ]	* [ንእግእድ]

ርግግን ([ርእግምእን]) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን። በሌላ በኩል፣ ይህችው አናባቢ ከመነሻው ተናባቢ፣ ማለትም ከ/ር/ ጋር ቦታ በመቀያየር በቃሉ መነሻ ላይ ስትገባ፣ [እርግምእን] የሚል ቅርፅ እናገኛለን። ይህ ቅርፅ ግን ከላይ ተጠቃሎ ከተቀመጠው ህግ ያፈነገጠ ነው። ምክንያቱም ከአናባቢው ቀጥሎ ሶስት ተከታታይ ተናባቢዎች ስለሚገኙበት ነው። በቃል መካከል ቁጥቁጥው የሚፈቅደው የሁለት ተናባቢዎችን ከትትሎሽ ብቻ ነው። ስለዚህም የሶስቱን ተናባቢዎች ከትትሎሽ ለማስቀረት፣ ስርጎ-ገብዋን አአናባቢ ከሁለቱ ተከታታይ ተናባቢዎች ቀጥሎ እንደገና ማስገባት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን፣ እርግግን ([እርግእምእን]) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን። አአናባቢው ሁለት ሂደቶችን እኳልፎአኳል ማለት ነው። አአንደኛው ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኙት ከፍት ቦታዎች መግባት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከመነሻው ተናባቢ ጋር ቦታ ተቀያይሮ የቃሉ የመነሻ ድምፅ መሆን ነው።

ይህ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ጋር ቦታ የመቀያየር ሂደት ግን ውሱን ነው። አናባቢው ቦታ የሚቀይረው የቃሉ የመነሻ ተናባቢ እንደ /ር፣ ን ፣ ል/ እና /ስ/ ያለ ቀጣይ ድምፅ ሲሆን ብቻ ነው። <u>ቀጣይ</u> የሚባሉት ትንፋሽ ሳይቁዋረጥ የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው። እንደ /ክ፣ ድ፣ ግ፣ ወዘተ/ ካሉ ትንፋሽ ከሚቆርጡ ድምፆች ይለያሉ።

በሌላ በኩል ግን ስርጎ-ገብዋ አናባቢ በሌሎች ተናባቢ ድምፆች በሚጀምሩ ቃላት መነሻ ላይም የምትገባ ትመስላለች። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

እደላ	[አድድኧልኣ]	10
እገዳ	[አግግአድኣ]	
እቅድ	[አቅቅአድ]	
እክት	[አክክአት]	

እንደነዚህ ያሉ ቃላት ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው /ዕ/ በሚለው ተናባቢ የግንቁርት ድምፅ ነው። ለዚህ ምልክቱ ግሱ /አ/ በሚለው አናባቢ መጀመሩ ነው። ይኸውም አደሰ /አድድኧለኧ/፣ እገዳ /አግግኧድኧ/፣ ወዘተ፣ ስንል ነው። ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአግርኛ ግስ ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው በጠቅላላው በተናባቢ ድምፅ ብቻ ነው። ከዚህ ስንነሳ፣ <u>አደሰ</u> የሚለው ታህታይ ቅርፅም /ዕኧድድኧልኧ/ የሚል መሆን አለበት። ቀደም ሲል፣ ስለ ግድፈት ሰንወያይ /ዕ፣ ው፣ ይ/ እና /ህ/ ባህሪያቸውን አጠባባቸው ስሚገኝ አናባቢ እያጋቡ እንደሚገደፉ ገልፀን ነበር። በዚሁ መሰረት /ዕ/ የታቸኛነት ባህሪዋን ከእስዋ ቀጥሎ ስሚገኘው ለ/ኧ/ አጋብታ ተገድፋለች። /ኧ/ም በዚሁ ተጋቦት ምክንያት ወደ /አ/ ተለውጣለች። ይህ እንግዲህ በግሱ ቅርፅ ላይ የሚካሄድ ለውጥ ነው።

ከላይ የሚታዩት ቃላት ግን ለሞች ናቸው። አፈጣጠራቸውም ከግስ አፈጣጠር የተለየ ነው። ለምሳሌ <u>እደላ</u> የሚለውን ብንወስድ /ዕ-ድድ-ል/ ከሚለው

ስር ላይ /ኧ/ን በሁለተኛው ክፍት ቦታ ላይ በማስገባት፣ *መጀመሪያ* /ፅ-ድድኧል-/ የሚለውን ቅርፅ ይፈጥራል። ከላይ በተራ ቁጥር (2) ባገለፅነው የስርገት ስርዓት መሰረት፣ {እ}ን ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ ያስገባና {ፅእድድኧል-} የሚለውን አምድ ይፈጥራል። ከዚህ አምድ ላይ /-እ/ የሚለው ቅጣይ ምዕላድ በአምዱ መድረሻ ላይ ሲጨምር ቃሉ ሙሉ ቅርፁን ይይዛል። ቅርፁ፣ በአናባቢው በ{እ} የሚጀምር ይመስላል። ስለሚመስልም {እ}ን እንደ <u>*ቀድሞ-ገብ*</u> አናባቢ ልንቆጥራት እንችላለን። በቀድሞ-ገብነት የምትገኘው እንደ <u>እየሱስ</u> [እይይኧስኡስ]፣ <u>እዚህ</u> [እዝዝኢህ]፣ እግዜር [እግዝኤር] ፣ <u>እስቲ</u> [እስትኢ]፣ <u>እንካ</u> [እንክእ] ፣ ወዘተ፣ ባሉ ቃላት ነው። በነዚህ መነሻ ላይ የሚታየው {እ}፣ ከተናባቢ ጋር በቃ በመቀያየር የመጣ ሳይሆን፣ መጀመሪያውኑ በመሻው ላይ የተተከለ ነው። ስለዚህ ሁለት የስርገት አይነት አለ። እንደኛው <u>*ቀደሙ-ገብ*</u> ሲሆን፣ ሁለተኛው <u>*ድህረ-ገብ*</u> ነው። ድህረ-ገቡ ከተናባቢ በሁዋላ ሲገባ፣ ቅደመ-ገቡ በቃል መነሻ ላይ ከሚገኝ ተናባቢ በፊት ይገባል።

ቅየራ

ከፍ ሲል እንደ /ር፣ ን ፣ ል/ እና /ስ/ ያሉ ቀጣይ ተናባቢዎችን ተከትሎ የሚመጣ {እ} ፣ ከተናባቢዎቹ ጋር ቦታ በመቀያየር ቀድሞ ሊገባ ይችላል ብለን ነበር። ወደ ሁዋላ ግን እናባቢው በመነሻ ላይ የሚገኘው፣ በቅይይር ሳይሆን፣ መጀመሪያውኑ በዚያው በመነሻው ቦታ ላይ በመተከሉ እንደሆነም ገልፀናል። እንደዚህ ያለውን አናባቢም ቀደሞ-ገብ ብለን፣ በቃል መሀል የሚከታተሉ ተናባቢዎችን ለመለያየት ከሚገባው መሀል-ገብ {እ} ስይተነዋል።

ከዚህ ላይ የምናየው የቅየራ ሂደት ግን ከፍ ሲል ከጠቀስነው የተለየ ነው። ልዩነቱም በተቀያያሪዎቹ ድምፆችና በቅርበታቸው መጠን ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ)	ክብሪት	/ክ-ብርኢት/	[ክእብርኢት] [ክእርብኢት]	1
	ከበሮ	/ክኧብኧርኦ/	[ክኧብኧርኦ] [ክኧርኧብኦ]	
	ማከሰኞ	/ምኣክስኧኝኧኦ/	[ምኣክስኧኝኝኦ] [ምኣስክኧኝኝኦ]	
	መጥረቢያ	/ምኧጥርኧብኢያ/	[ምኧጥርኧብ^{y}ኣ] [ምኧርጥኧብ^{y}ኣ]	

መከረልት	/ምኧክፍኧልት/	[ምኧክልኧፍት] [ምኧልክኧፍት]
ስፍራ	/ሱ-ፍርኣ/	[ስእፍርኣ] [ሰእርፍኣ]
እግዜር	/-ግዝኤር/	[እግዝኤር] [እዝግኤር]
ለበቅ	/ልኧብኧቅ/	[ልኧብኧቅ] [ብኧልኧቅ]

በዕዝባሩ ውስጥ የሚታዩት በማዕዘኑ ውስጥ የሚታዩት ጥንድ ጥንድ ቃላት ታህታይ ቅርፆች ናቸው። በማዕዘኑ ውስጥ ከሚታዩት ጥንድ ጥንድ ቃላት የመጀመሪያው መደበኛ በሚባለው የከተማው አማርኛ ውስጥ የሚነገረው ነው። ሁለተኛው በእንዳንድ የገጠር ቀበልኛዎች፣ ለምሳሌ በወሎ አካባቢ የሚሰማ ነው። የሁለቱም ላዕላይ ቅርፆች መሰረት በዕዝባር ውስጥ የሚታየው ሲሆን፣ አወጣጣቸውን ማ<u>ክሰኛ</u> በሚለው ምሳሌ እንደሚከተለው እናሳያለን።

/ም-ክሰ-ኛኝ-ኦ/ ⟶ [ምኣ<u>ክስ</u>ኧኛኝኦ]
[ምኣ<u>ስክ</u>ኧኛኝኦ] 2

<u>ማክሰኛ</u> የሚለው በታህታዩ ውስጥ የሚታየውን የተናባቢዎቹን ቅደም-ተከተል ጠብቆአል። <u>ማስክኛ</u> የሚለው የተናባቢዎቹን ቅደም-ተከተል አፋልሶአል።


የሁለቱም መሰረት የሆነው /ም-ክሰ-ኛኝ-ኦ/ የሚለው ቅርፅ ነው የምንልበት ምክንያት <u>ማክሰኛ</u> የሚለው <u>ማስክኛ</u> ከሚለው የሰፋ ስርጭት ያለው በመሆኑ ነው። በብዙ አካባቢና በብዙ ፅሁፍ ላይ የሚገኘው እሱ ነው[24]።

የቦታ ቅይይሩ በተናባቢዎቹ ድምፆች ብቻ የሚካሄድ ሰለሆነ፣ አናባቢዎቹን ማመልከቱ አስፈላጊ አይደለም። በእዝባሩ ውስጥ /-ክሰ-/ የነበሩት ተናባቢዎች፣ በቅንፉ ውስጥ፣ ማለትም በገጠሩ አማርኛ፣ [-ስክ-] የሚል ቅደም-ተከተል ይዘዋል። ከዚህም በየዕዝባሩ ውስጥ ከሚታየው ታህታይ ቅርፅ ላይ ሁለት ላዕላይ ቅርፆች እንደሚወጡ እንረዳለን። አንደኛው <u>ማስክኛ</u> የሚለውና የተናባቢዎቹን ቦታ አቀያይሮ የሚወጣው የገጠሩ ቃል ሲሆን፣ ሁለተኛው የተናባቢዎቹን ቦታ ሳይቀያይር የሚወጣው መደበኛው ቃል ነው። የሁለቱን ቅርፆች ያወጣጥ ስርዓት እንደሚከተለው አአጠቃሉ ማሳየት ይቻላል።

---

[24] የስርጨት ስፋት አንዱ መስፈርት ነው። የቃሉ ታሪካዊ አመጣጥና በተዘግጅ ቁየንቁየዎች ውስጥ የሚታይበት ቅርፅና ለአጠቃላይ ስርዓት ያለው አስተዋፅየ እኩል ሊታዩ የሚገባቸው መስፈረቶች ናቸው።

ም-ከስ-ኝ- 3
1 2



[ም-ከስ-ኝ-[[ም-ስክ-ኝ-[
1 2 2 1

የሌሎቹ ምሳሌዎች አካሄድም እንደዚሁ ነው። ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ ጊዜ ቦታ የሚቀያየሩት ድምፆች እዚህ ላይ እንደምናየው ተከታታይ ላይሆኑ ይቻላሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ <u>በለቅና</u> <u>መክለፍት</u> ያሉት ቃላት ናቸው። ታህታይ ቅርፃቸው በየእቅጣጫቸው ከላይ በየእዝባሩ የተመለከተው ነው። ሁለቱን ብቻ እንደገና እንመልከታቸው።

/ልኧብኧቅ/ ⟶ [ብኧልኧቅ] 4
/ምኧክፍኧልት/ ⟶ [ምኧክልኧፍት]

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ በእዝባሩ ውስጥ /ል/ እና /ብ/ የነበሩት በቅንፉ ውስጥ [ብ] እና [ል]፣ ሆነዋል። በሁለተኛው፣ በእዝባሩ ውስጥ /ፍ/ እና /ል/ የነበሩት፣ በቅንፉ ውስጥ [ል] እና [ፍ] ሆነዋል። ቦታ ተቀያይረዋል ማለት ነው። በየመካከላቸው /ኧ/ የሚለው አናባቢ ድምፅ ስለሚገኝ፣ ድምፆቹ <u>ተርታ-ተከታታይ</u> አይደሉም። የቅይይሮሹን ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን።


/ልኧብ.../ ⟶ [ብኧል...] 5
/...ፍኧል.../ ⟶ [...ልኧፍ...]

በተቀያያሪዎቹ ድምፆች መካከል /ኧ/ የሚለው አናባቢ ስለሚገኝ፣ ተናባቢዎቹ ቦታ የሚቀያየሩት ይህን አናባቢ ድምፅ በመዝለል ነው። በዚህ አይነትም ሆነ ከፍ ሲል ባየነው ተርታ-ተከታታይ ተናባቢዎች መካከል የሚታየውን የትይይሮሽ ስርዓት እንደሚከተለው አጠቃሉ ማስቀመጥ ይቻላል።

/(...) $ተ_1$(...) $ተ_2$ .../ ⟶ [(...) $ተ_2$ (...) $ተ_1$ ...] 6

ስርዓቱ ሁለት ተከታታይ ወይም ኢተከታታይ የሆኑና በቃል መነሻ ወይም መካከል ላይ የሚገኙ ተናባቢ ድምፆች ቦታቸውን ሲቀያየሩ እንደሚችሉ ያሳያል። ይህም ማንኛውንም ተናባቢ የሚመለከት ሳይሆን፣ ለውጡ በሚታይባቸው ቃላት ውስጥ ብቻ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው። በዚሁ

መስረት ለበቅ እና በሰቅ የሚሉትን ቅርፆች አወጣጥ እንደሚከተለው አሳሳይተን ጉዳዩን እንቋዋጨዋለን።



ታህታይ ቅርፁ በእዝባር የተመለከተው ነው። ከአሱ ላይ ሁለት ላዕላይ ቅርፆች ተመሰርተዋል። የተመሰረቱትም የመጀመሪያዎቹን ሁላት ተናባቢዎች ቦታ በመቀያየር ወይም ባስመቀያየር ነው። የሚቀያይረው [ብ$_2$ኧል$_1$ኧቅ] የሚለው የገጠሩ ቀበልኛ ቃል ነው።

ይህን በዚህ እንተወውና በዚህ ክፍል እስካሁን በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው አናጠቃለው። በመሰረቱ ስማየት የሞከርነው ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ነው። የመጀመሪያው በእማርኛ ውስጥ የሚገኙትን የንግግር ድምፆች መጠን፣ እይነትና አፈጣጠር መመርመር ሲሆን፣ ሁለተኛው የነዚህኑ ድምፆች አቀነጃጀትና ከዚህም ላይ የሚሰርፀውን የተለያየ ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት መመልከት ነው።

የመጀመሪያውን በተመለከተ፣ ቁዋንቁዋው 30 ተናባቢዎችና ሰባት አናባቢዎች እንዳሉት አይተናል። ከተናባቢዎቹ መካከል 13ቱ አግድ፣ ሰባቱ ፍትግ፣ አራቱ ፍግድ፣ ሶስቱ ስርናዊ፣ ሁለቱ ከፍናቢ እና ሁለቱ ደግሞ ጎናዊ ናቸው። ይህ አከፋፈል ከባህርየ ፍጥረታቸው አኩዋያ ነው። ከመካነ ፍጥረታቸው አንፃር ሲታዩ ደግሞ፣ ስድስቱ ከናፍራዊ፣(ስነፈራዊውን [ፍ]ን ጨምሮ)፣ ዘጠኙ ድዳዊ፣ ሰባቱ ዳላንቃዊ (ላንቃዊያኑን [ይ] እና [ኝ]ን ጨምሮ) ስድስቱ ትናጋዊ፣ ሁለቱ ደግሞ ማንቁርታዊ ናቸው።

እናባቢዎቹ ደግሞ ሰባት ሲሆኑ፣ እነሱም ምላስ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ከሚያደርገው አንቅስቃሴ አኩዋያ፣ የፊት፣ የመሀል እና የሁዋላ ተብለው፤ እንዲሁም ይሽው አካል ወደ ላይና ወደ ታች ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንፃር፣ ላየኛ፣ ልከኛና ታኮኛ ተብለው በሶስት እንደሚከፈሉ አይተናል።

ከ/ነ/ በለተቀር ተናባቢዎቹ በሙሉ ሊጠብቁ ይችላሉ። ጥብቀቱም የትርጉም ልዩነትና የሰዋሰዋዊ ባህሪ ለውጥን ሊያስከትል ይችላል። እንደ ገና [ግእንእ] እና ገና [ግእንንእ] ያሉት የትርጉም ለውጥ የሚከስትባቸው ቃላት ሲሆኑ፣ እንደ [ግእድድአይ]፣ [ጥእርርአኒ] ወዘተ፣ ያሉት የድራጊ፣ ማለትም የውጤት ስሞች፣ እና የተገብሮ ስሞች ናቸው። ተገብሮነትን ወደፊት እናየዋለን።

የተናባቢዎቹን ስርጭ ለንመለከት፣ ከ/ኝ/ በስተቀር ማንኛውም ሌላ ተናባቢ ድምፅ በቃል መነሻ፣ መሀል ወይም መድረሻ ላይ ሊገባ ይችላል። /ኝ/

ብቻ በቃል መነሻ አይገኝም። ከአናባቢዎቹ መካከልም የመሀለኞቹ ብቻ በሁሉም ቦታ ሲገኙ፣ ዳረኞቹ በቃል መነሻ ብቻ አይገኙም።

አቀነጃጀታቸውን ስንመለከት፣ ተናባቢ ድምፆች በቃል መነሻ ብቻ ተከታትለው አይመጡም። በሌላ ቦታም ቢሆን ከትትሉሹ ከሁለት ተናባቢዎች አይበልጥም። በልጠ ሲገኝ፣ ሶስተኛውን ተናባቢ ከሁለቱ ቀዳሚ ተናባቢዎች የሚለይ አናባቢ ድምፅ ሰርጎ ይገባል። ሁለተኛም ከሚከታተሉት ድምፆች የመጀመሪያው ልቅ መሆን አለበት። አናባቢ ድምፆች በላዕላይ ቅርፅ ተከታትለው አይገቡም። ከተከታተሉ አንድም ከሁለቱ አንደኛው ይገደፋል፣ ወይም ወደ ከፍናቢነት ይለወጣል። ወደ ከፍናቢነት የሚለወጡት የፊትና የሁዋላ አናባቢዎች ናቸው።

በዚህ መሰረት አጠቃላዩ የቁዋንቁዋው ቀለም አወቃቀርም /ተ-አ-ተ/ የሚል ነው። በዚህ አይነት የሚዋቀሩ ቀለሞች እየተከታተሉ ሊገቡ፣ ከሚፈጠረው ንክኪ የተነሳ የአንዱ ድምፅ ባህሪ ወደ ሌላው ድምፅ የመጋባት ሂደት ሊከሰት ይችላል። በዚህ ሁኔታ የሚታዩት የመካነ ፍጥረት ባህሪያት ከናፍራዊነት፣ ላንቃዊነትና ትናጋዊነት ናቸው። ከባህሪየ ፍጥረት አኩዋያ ደግሞ ድምፀት፣ ኢድምፀት፣ ጥብቀት፣ ልለት፣ ማንቁርታዊነት ዋና ዋናዎቹ ሂደቶች ናቸው። በተጨማሪም የድምፅ ግድፈት፣ ስርገት ወይም ቦታ ቅየራ ሊከሰት እንደሚችል አይተናል።

ድምፀ-ልላናዊ ሂደቶቹ በምዕላድ ውስጥ፣ በምዕላድ ድንበር ወይም በቃል ድንበር ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ። በዚህ ረገድ፣ ከፊል ላንቃዊነት በምዕላድ ውስጥ ሊከሰት፣ ሙሉ (ድ)ላንቃዊነትና ኢድምፀት በምዕላድ ድንበር ላይ እንደሚከሰቱ አይተናል። በዚህም ይህን ክፍል ተሰናብተን ወደሚቀጥለው እንሄዳለን።

መልመጃ


1. የምላሰን ፊተኛ መሀለኛ እና ሁዋለኛ ክፍሎች መሰረት በማድረግ የአማርኛን ድምፆች በጠቅላላ በሶስት ክፍሎች ይመድቡ።

2. <u>ከላገኘንባቸውሰ</u> የሚለውን ቃል በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉና ፎኒሞቹን በባህርየ ፍጥረታቸው መሰረት ይከፋፍሉ።

3. /ሹ/ እና /ኝ/ ፎኒም መሆናቸውን የሚያሪጋግጡ ጥንድ ጥንድ ቃላት ይፈልጉ።

4. የሚከተሉተን ድምፆች መካነ-ፍጥረት ይግለፁ።

[ም፣ ፍ፣ ጥ፣ ት፣ ሰ፣ ሽ፣ ጅ፣ ኧ፣ ቅ]

5. 

(ሀ) ከቀስቱ በፊት (በስተግራ) የሚታዩት ድምፆች ከቀስቱ በስተቀኝ ወደሚታዩት እኛ ድምፆች የሚለወጡበትን ሂደት ይግለፁ።

(ለ) ለእያንዳንዱ ድምፅ ለውጥ ምሳሌ የሚሆን ቃል በፎኒማዊ አፃፃፍ ያሳዩ።

6. ጣለ፣ ማስ፣ ሳስ፣ ወዘተ፣ የሚሉት ቃላት ስላ፣ ሰላ፣ ጠፋ፣ ወዘተ፣ ከሚሉት ቃላት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንዴት እንደሚለያዩ ያስረዱ።

7. በርታ፣ ስረታ፣ አበረታታ፣ ካላበረታታህ የሚሉትን ቃላት የቀለም አወቃቀር ስርዓት ያሳዩ።

8. <u>ቀጨማ</u> እና <u>ቄጠማ</u> እንዲሁም <u>ሚስጥር</u> እና <u>ምስጢር</u> በትርጉም እንድ ናቸው። በቅርፅ ግን መጠነኛ ልዩነት ያሳያሉ። የልዩነታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ይግለፁ።

9. /ፍ/ ፣ /አእ/ ፣ /ዝ/ ፣ /ክ/

(ሀ) እነዚህን ፎኒሞች በመጠቀም በአማርኛ የቀለም አወቃቀር ስርዓት መሰረት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀለሞችን አሳይ።

(ለ) ከቀለሞቹ መካከል ስእንዱ ውስጥ /ዝ/ ወደ [ስ] ይለወጣል። የለውጡን ሂደትና አቅጣጫ ይግለፁ።

10. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉ።

እንክብል፣ እበት፣ አጉዋት፣ ሙጫ፣ ቅቅል፣ መቸ

11. ጥበቀት የትርጉም ለውጥ እንዴት እንደሚያስከትል ጥንድ ጥንድ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

ምዕራፍ ሁለት

ስነ-ቃላት

"መጀመሪያ ቃል ነበር" ዮሀንስ፣ምዕ. ፩፣ ቁ. ፩

መግቢያ

ባለፈው ምዕራፍ ስለ አማርኛ ድምፆች አፈጣጠር፣ አይነት፣ አቀነጃጀትና ስለሚያደርጉት ስነ-ድምፀ-ልሳናዊ ለውጥ ተወያይተናል። ድምፆች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቀለሞችን ነው። ቀለሞች ትርጉም ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል። ትርጉም ያላቸው፣ ትርጉም ከሌላቸው ተለይተው ምዕላድ ይባላሉ። ምዕላዶች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቃልን ነው። ድምፆች የቀለም፣ የምዕላድ እንዲሁም የቃል መሰረት ናቸው ማለት ነው። ይህ ከሆነ፣ "መጀመሪያ ቃል ነበር" የሚለው ጥቅስ "መጀመሪያ ድምፅ ነበር፣ ድምፅም ቃል ሆነ" ማለት ነበረበት። ይህ ያልሆነበት ምክንያት አለው። ድምፆች በራሳቸው ትርጉም የላቸውም። ትርጉም ያላቸው የነሱ ቅንጅት የሆኑት ምዕላድና ቃላት ናቸው። የሰው ልጅም ሀሳቡን የሚያስተላልፈው ጎደለ ሲባል በቃላት፣ ሞላ ሲባል በአረፍተ ነገር ነው። ርግጥ፣ አንዳንድ ጊዜ ድምፅንና ቃልን አንድ አድርጎ የማየት ሁኔታ አለ። ድምፃችንን እናሰማ ስንል፣ አንናገር ማለታችን ነው። ከዚህ አንፃር ድምፅ አንደ ቃል ሊቆጠር ይችላል።

ከዚህም አልፎ ቃላት እንደ ዘር ሊታዩ ይችላሉ። ይበቅላሉ፣ ሀረግ ይለዳሉ፣ ያብባሉ፣ በመጨረሻም ያፈራሉ። ፍሬአቸውም ያው ከፍ ሲል የጠቀስነው ትርጉማቸው ነው። በተራ ቃላትነት፣ ማለትም በዘርነታቸው፣ የሚሰጡት ትርጉም አንዱ ሲሆን፣ አድገው ሀረግ ሲሰዱና አረፍተ ነገር ሲመሰርቱ የሚሰጡት ትርጉም ሌላው አይነት ነው። ሁለቱን ትርጉሞች ቃላዊና አረፍተ ነገራዊ ብለን ልንለያቸው እንችላለን። የአረፍተ ነገር ትርጉም በከፊል አረፍተ ነገሩን የሚመሰርቱት ቃላት ትርጉም ድምር ውጤት ነው። በከፊል የተባለበት ምክንያት፣ አረፍተ ነገሩን የሚመሰርቱት ቃላት[1] አገባብም ለትርጉሙ አስተዋፅዖ ስለሚኖረው ነው። ለዚህ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እንመልከት።

1

(ሀ) አንበሳ ነብር ነከሰ
(ለ) ነብር አንበሳ ነከሰ

[1] በርግጥ፣ እነዚህ ነገሮች በአረፍተ ነገር ደረጃ ሲታዩ፣ ቃላት አይደሉም፣ ሀረጎች ናቸው። እዚህ ላይ ውይይታችን ስለ ቃላት ስለሆነ፣ ለጊዜው ቃላት እያልን እንጠራቸዋለን። ለምን ሀረግ እንደሚባሉ በምዕራፍ ሶስት እንገልፃለን።

ሁለቱም አረፍተ ነገሮች የተመሰረቱት ከአንድ አይነት ቃላት ነው። ይሁን እንጅ፣ የአረፍተ ነገሮቹ ትርጉም ሰየቅል ነው። የልዩነቱ መንሰዔ <u>አንበሳ</u> እና <u>ነብር</u> የሚሉት ቃላት አገባብ የተለያየ መሆኑ ነው። በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>አንበሳ</u> የሚለው ቃል የአረፍተ ነገሩ መነሻ ሆኖ ሲገባ፣ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ የአረፍተ ነገሩ ቅድመ-መድረሻ ሆኖ ገብቶአል። በዚህም የአገባብ ልዩነት ምክንያት የትርጉም ለውጥ ሊከሰት ችሎአል። ይህም፣ አገባብ ለአረፍተ ነገራዊ ትርጉም ያለውን አስተዋፅዖ ያሳያል። በዚህ ምዕራፍ የምናየው ቃላዊውንም ሆነ አረፍተ ነገራዊውን ትርጉም አይደለም። ትኩረታችን በቃላት አይነትና ውስጣዊ የአቀነጃጀት ሰርዓት ላይ ነው።

የእህል ዘር አይነት የተለያየ እንደሆነ ሁሉ፣ የቃላት ዘር አይነትም እንደዚሁ የተለያየ ነው። ልዩነቱ የቅርፅና የተግባር ነው። በአንድ በኩል ነገሮችንና የነገሮችን ባህሪ የሚገልፁ ቃላት አሉ። በሌላ በኩል የነገሮችን ተግባርና የእተግባበር ሁኔታ የሚገልፁ ሌሎች ቃላት አሉ። በዚህም መሰረት ቃላትን በጥቅሉ የነገርና የተግባር ወይም ድርጊት ብሎ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል። የየክፍሉ ቃላት ቅርፅም በመጠኑም ቢሆን የተለያየ ነው። ልዩነቱን በዚህ መዕራፍ ዘርዘር አድርገን አናየዋለን።

አንድ ገበሬ በአንድ አካባቢ የሚገኝን የእህል ዘር በአይነት በአይነት አየለየ በተለያየ ዕቃ አንደሚያሰቀምጥና በውዋላም በተለያየ ወቅትና ማሳ ላይ ዘርቶ፣ ለተለያየ ዓላማ እንደሚያመርት ሁሉ፣ አንድ የስነ-ልሳን ባለሙያም በአንድ ቁዋንቁዋ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን እንደየቅርፅና ተግባራችው በተለያየ መደብ አየመደበ ለተለያየ ተግባር የት፣ እንዴት እና መቼ እንደሚውሉ ማህበራዊ ህግጋቱንና ስነ-ልሳናዊ ሰርዓቱን ያሰቀምጣል። በዚሁ መሰረት በአማርኛ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አንደዚሁ በወገን በወገናቸው አየመደብን እናሰቀምጣቸዋልን። የአንዱ ወገን ቃለት ተግባርም ከሌላው ወገን የተለየ አንደሆነ ለማሳየት እንሞክራለን። ወደ አመዳደቡ ከመግባታችን በፊት ግን በጥቅሉ ቃል የምንሰው ነገር ምን ማለት እንደሆነ ትንሽ ዘርዘር አድርገን ማየት ይኖርብናል። ብዙ ጊዜ ለመግለፅ የምያሰቸግረን የምናውቀው የሚመሰለን ነገር ስለሆነ፣ የዚህን ምዕራፍ ጡይይት በቃል ትርጉም እንጀምራለን።

ቃል

የቃልን ምንነት በወጉ ለመግለፅ፣ ከቃል አሰፍ ብለን በምዕላድ መጀመር አለብን። ባለፈው ምዕራፍ አንደገለፅነው፣ ምዕላድ የምንሰው አንድን ትርጉም-አዘል የሆነንና አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሲሸነሸን የማይችልን የመጨረሻ ንዑስ <u>*አሀድ*</u> ነው። <u>ሰው</u> የሚለውን አሀድ አንውሰድና ነገሩን በምሳሌ አንረዳው። ይህ አሀድ ትርጉም-አዘል ነው። ትርጉም አለው ማለት ነው። ትርጉሙ አሀዱን በምንሰማበት ጊዜ በአዕምሮአችን የሚሰማንና በአይናችንም ልናየው የምንችለው ነገር ነው። አሀዱ ወደ አነስተኛ ትርጉም-አዘል ክፍሎች

ሊከፈል አይችልም። ቢከፈል የምናገኘው ፎኒሞችን ይሆናል። ፎኒሞች ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ትርጉም የላቸውም። ስለዚህም ሰው የሚለው አሀድ ምዕላድ ነው።

ሰዎች የሚለውን አሀድ ደግሞ እንውሰድ። ይህም ትርጉም-አዘል ነው። በዚህም ሰው ከሚለው አሀድ ጋር ይመሳሰላል። ይሁን እንጅ፣ ሰዎች /ሰኣው/ እና /-ኦችች/[2] ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል። ሁለቱ ክፋዮችም ትርጉም-አዘል ናቸው። የ/-ኦችች/ ትርጉም ከአንድ በላይ የሆነ፣ ጥቂት ወይም ብዙ ማለት ነው። /-ኦችች/ም ሰው እንደሚለው አሀድ አነሰተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል አሀዶች ሊከፈል አይችልም። ስለዚህም ምዕላድ ነው። ይሁን እንጅ፣ /-ኦችች/ ሰው እንደሚለው ምዕላድ ራሱን ችሎ ሊቆም አይችልም። ስለዚህም እንደ ሰው ካለ ራሱን ችሎ ሊቆም ከሚችል ምዕላድ ጎን መጠጋት አለበት። ይህን ሊያደርግ የምናገኘው /ሰኣው-ኦችች/ የሚለውን አሀድ ይሆናል። ይህ አሀድ ከሁለቱ ምዕላዶች የተመሰረተ ስለሆነ፣ ምዕላድ አይደለም፣ ከምዕላድ በላይ ነው። አንድ ከምዕላድ በላይ የሆነ አሀድ ቃል ይባላል። ስለዚህም /ሰኣው/ እና /-ኦችች/ ምዕላድ ሲሆኑ፣ ከሁለቱ ቅንጅት የተገኘው ሰዎች የሚለው አሀድ ግን ምዕላድ ሳይሆን ቃል ነው።

ነገሩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ሆዳም የሚለውን አሀድ ደግሞ እንመልከት። ይህ አሀድ ትርጉም እሰው። አነሰተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊከፈል ይችላል። ክፍሎቹም ሆድ እና /-ኣም/ የሚሉት አሀዶች ናቸው። ሁለቱም ትርጉም አላቸው። የሆድ ትርጉም ግልፅ ነው። የ/-ኣም/ ትርጉም ግን ትንሽ ገለፃ ያስፈልገዋል። /-ኣም/ አንድን ሰም የሆ ቃል ወደ ቅፅል የመለወጥ ተግባር ያለው ቅጣይ ነው። በዚህም ተግባሩ ምክንያት ቅፅል መሰራች ምዕላድ ልንለው እንችላለን። እንደ ሆድ ያለ ሰም የሆነ አሀድ እንደ /-ኣም/ ያለ ቅጣይ ሲከተለው ቅፅል ይሆናል። ሁለቱም አሀዶች አነሰተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል አሀዶች ሊከፈሉ ስለማይችሉ ምዕላዶች ናቸው። ከሁለቱ ምዕላዶች የተመሰረተው ሆዳም የሚለው አሀድ ግን፣ የሁለቱ ምዕላዶች ቅንጅት የሆነ ቃል ነው። እንደ /-ኦችች/ ሁሉ፣ /-ኣም/ም ራሱን ችሎ የሚቆም ምዕላድ ሳይሆን፣ እንደ ሆድ ካለ ራሱ-ቻይ ምዕላድ ጎን የሚጠጋ ነው።

ከምሳሌዎቹ የምንረዳው፣ ምዕላድ ትርጉም-አዘልና አነሰተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊከፈል የማይችል ንዑስ አሀድ መሆኑን ነው። በተጨማሪም እንዳንድ ምለሳዶች ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ እንደሚችሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን ማድረግ እንደማይችሉ ተገንዝበናል። እንደ ሰው እና ሆድ ያሉት ራሳቸውን ችለው ከሚቆሙት ወገን ሲሆኑ፣ እንደ /-ኦችች/ እና /-ኣም/ ያሉት ራሳቸውን ከማይችሉት ወገን የሚመደቡ ናቸው። በዚሁ መሰረት ምዕላዶች ባጠቃላይ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና የማይቆሙ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ራሳቸውን ችለው የሚቆሙት ነፃ፣ ራሳቸውን የማይችሉት ጥገኛ

[2] ቅጣይ ምዕላዶችን በእዝባር ውስጥ በፎኒማዊ አፃፃፍ እናመለክታለን። ይህም አፃፃፍ ከስርዓተ ፅሁፉት የተለየ እንደሆነ እናስገነዝባለን።

የቃላት ክፍል

ምዕላድ ይባላሉ። ጉዳዩ እንደ ወላጅና እንደ ልጅ ግንኙነት መሆኑ ነው። ልጅ የወላጅ ጥገኛ ነው። አሰከተወሰነ ጊዜ ድረስ፣ 'የገሌ ልጅ' ይባላል እንጅ፣ 'ገሌ' እየተባለ በራሱ ሰም ላይጠራ ይችላል። ልዩነቱ ልጅ ሲያድግ ነፃ ይሆናል። ጥገኛ ምዕላድ ግን ሁሌም ጥገኛ ነው፡ አልፎ አልፎ ነፃ የነበሩ ምዕለዶችም ጥገኛ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። ይህም ደጋፊ እንደሚሹ አዛውንት ወላጆች መሆኑ ነው። ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ።

ጥገኛ ምዕላዶች ከነፃ ምዕላዶች ካልተጠጉ ትርጉም አይኖራቸውም። ለምሳሌ /-አችች/ የሚለው ምዕላድ ብቻውን ቢነገር፡ ምንም ትርጉም አይኖረውም። ብዛትን የሚያመለክተው ሊቆጠር የሚችል ነገርን ከሚገልፁ ሰሞች ቀኝ ጎን ሲጠጋና የሰሞቹ አካል ሲሆን ነው። ይህን ሲያደርግ ያ እሱ የተጠጋበት ቃል መጠናቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮችን እንደሚያመለክት ያሳያል። አንድ ምዕላድ ጥገኛ መሆኑን ለማመልከት ከጎኑ ላይ ጭረት(-) እናስቀምጣለን።

ሰለ ምዕላድ ይህን ያህል ከተገነዘብን፣ በምዕላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ደግሞ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። መጀመሪያ ነገር፣ እንደ ምዕላድ ሁሉ፣ ቃልም ትርጉም-አዘል አሀድ ነው። ሁለተኛም፣ ቃል ራሱን ችሎ መቆም ለሚችል ነፃ ነው። በዚህም ባህሪው ከነፃ ምዕላድ ጋር ሊመደብ ይችላል። ሶስተኛም፣ ቃል በውስጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዶችን ሊይዝ ይችላል። ትርጉም-አዘል ወደሆኑ አነሰተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን ይችላል ማለት ነው። በዚህ ባህሪው ደግሞ (ከነፃ) ምዕላድ ይለያል። ምክንያቱም ምዕላድ የሆነ አሀድ ትርጉም-አዘል ወደሆኑ አነሰተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን አይችልም ብለናልና። አራተኛ፣ ቃል ከቃላት ክፍሎች ውስጥ ባንዱ ሊመደብ ይችላል። ለምሳሌ፣ ሆዳም የሚለውን አሀድ ብንወስድ፣ ወደፊት በሰፊው እንደምናየው፣ ቅፅል በሚባለው የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደብ አሀድ ነው። ምዕላድ ግን በዚህ አይነት ላይመደብ ይችላል፣ በተለይ ጥገኛ ከሆነ። ምናልባት እንደ /-አም/ ያለው ምዕላድ አንድን ሰም የሆነ ቃል ወደ ቅፅል የሚለውጥ ሰለሆነ፣ ራሱም በቅፅል ክፍል ሊመደብ ይችል ይሆናል። ይህ ከሆነ፡ እንደ /-አም/ ያለ አሀድ ንዑስ ወይም ቅጣይ ቅፅል ሊባል ይችላል። እንደዚህ እያደረጉ ቅጣዮችን በክፍል፡ በክፍል መመደብ ሁል ጊዜ ቀላል አይደለም። በየትኛውም የቃላት ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የማይችሉ ምዕላዶች አሉ። ለምሳሌ፣ /-ስ/ የሚለው አሀድ ጥገኛ ምዕ ላድ ነው። እኔ-ስ፣ አንተ-ስ፣ ወዘተ፡ ሰንል በግልፅ እናየዋለን። ምድቡ ግን ወደፊት ከምናያቸው የቃላት ክፍሎች፣ ከየትኛውም ጋር አይገጥምም። ሌሎችም እንደዚህ ያሉ ምዕላዶች አሉ። ወደፊት እናያቸዋለን።

እንግዲህ ከላይ ከአንድ እስከ አራት የተዘረዘሩትን መሰፈርቶች የሚያሙዋላ ማንኛውም አሀድ ቃል ሊባል ይችላል። በዚህ መሰረት ሆድ የሚለውን አሀድ እንደገና እንመርምረው። ትርጉም-አዘል ሰለሆነ፣ ነፃ ሰለሆነና ከቃላት ክፍሎች ውስጥም ባንዱ፣ ማለትም ሰም በሚባለው ክፍል፣ ሊመደብ ሰለሚችል ቃል ነው። ይሁን እንጅ፣ ነፃ ምዕላድም ነው ሊባል ይችላል። ለዚህ ምክንያቱ አነሰተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን ሰለማይችል ነው።

ወደ እነሰተኛ ክፍሎች ብንከፋፍለው፣ የምናገኘው እሀዱ የተመለረተባቸውን ፎኒሞች ብቻ ነው። ፎኒሞች ደግሞ ትርጉም ያላቸው እሀዶችን ይመስርታሉ እንጅ፣ ራሳቸው ትርጉም እንደሌላቸው ቀደም ሲል ገልፀናል። ስለዚህም ሆድ የሚለው እሀድ የምዕላድንም ሆነ የቃልን ባህሪ በከፊል ስለሚያመዋላ ምድቡ ከቃል ወይም ከምዕላድ ሊሆን ይችላል። በሌላ አነጋገር፣ ነፃ ምዕላዶች ቃልም፣ ምዕላድም ናቸው።

ሆዳም የሚለውን እሀድ ብንወስድ ግን ሁኔታው ከዚህ የተለየ እንደሆነ እንረዳለን። ሆዳም የሚለው በውስጡ ሁለት ምዕላዶች ስላሉት፣ ማለትም ትርጉም-አዘል ወደሆኑ እሀዶች ሲከፈል ስለሚችል፣ ቃል አንጅ ምዕላድ አይሆንም። ከቃልም ባለሁለት ምዕላድ ቃል ስለሆነ፣ አንደ ሆድ ካለ ተራ ነፃ ምዕላድ የተለየ ነው። ይሁን እንጅ፣ ሆድ ከሚለው ጋርም አንድነት አለው። ይኸውም ሁለቱም ቃል መሆናቸው ሲሆን፣ ልዩነታቸው ሆድ የሚለው ብቻ ነፃ ምዕላድ መሆኑ ነው።

እንደነዚህ ያሉ ተራ ነፃ ምዕላዶች ተራ ፎኒማዊ ቃላት ሊባሉ ይችላሉ። ፎኒማዊ የሚያሰኛቸው መሰረተ ነገራቸው ፎኒሞች መሆናቸው ነው። ቢከፋፈሉም ከፍልፋዮቹ ፎኒሞች ናቸው። ለምሳሌ ሆድ የሚለውን ምዕላድ ብንከፋፍለው፣ ውጤቱ /ሀ/፣ /ኦ/ እና /ድ/ የሚሉት ሶስት ፎኒሞች ናቸው። ስለዚህም እሀዱ ፎኒማዊ ምዕላድ ወይም ፎኒማዊ ቃል ነው።

እንደ ሆዳም ያሉት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ጥንኛ ምዕላዶችን በውስጣቸው የያዙ እሀዶች ምዕላዳዊ ቃላት ሊባሉ ይችላሉ። ምዕላዳዊ የሚሰኙበት ምክንያት፣ የምዕላዶች ቅንጅት ውጤት መሆናቸው ነው። ስለዚህም የፎኒሞች ቅንጅት ከሆኑት ነፃ ፎኒማዊ ምዕላዶች ይለያሉ። በጥቅሉ ቃላትን የምዕላዶች፣ ምዕላዶችን ደግሞ የፎኒሞች ቅንጅት አድርጎ መውሰድና አንዱን ከሌላው በዚሁ መሰረት መለየት ይቻላል። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ማንኛውም ቁዋንቁዋ የነፃና የጥገኛ ምዕላዶች ከምችት ነው ሊባል ይችላል። ስለሆነም በዚህ ደረጃ የሚደረግ የአንድ ቁዋንቁዋ ጥናት በመሰረቱ ምዕላዶች እየተቀናጁ ቃላት እንዴት እንድሚመሰርቱ፣ እንዴትም በአይነት በአይነት እንደሚመደቡ፣ አንዱ አይነት ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ የሚመረምር ነው። እኛም ከዚህ ቀጥለን ለማሳየት የምንሞክረው ይህንኑ ነው። የአማርኛ ቃላትን አቀነጃጀት፣ እከፋፈልና እያንዳንዱ ከፍልም ከሌላው ጋር ያለውን ተዛምዶ ማየት።

የዋና ዋና ቃላት ክፍል

የምዕላድንና የቃልን እንድነትና ልዩነት ባለፈው ንዑስ ክፍል ለማየት ሞክረናል። ምዕላድ ከፎኒሞች የሚፈጠር ትርጉም-አዘል ንዑስ አሀድ እንደሆነ፣ ቃል ደግሞ የምዕላዶች ቅንጅት እንደሆነ ገልፀናል። አንድ ቁዋንቁዋም የአነዚህ ክምችት ነው ሊባል እንደሚችል ጠቁመናል። ይህ ክምችት ግን በዘፈቀደ በአንድ ቦታ የተከመረ ሳይሆን፣ ነፃውም ሆነ ጥገኛው ምዕላድ በየወገኑ እየተለየ

የቃላት ክፍል

አንዲታይ በየሚያሰችል ሰርዓት የተቀመጠ ነው። ብቃል ደረጃ በተናጠል ሊታይ የሚችሰውን ቃላት በፊደል ተራ አየመዘገቡ በቁዋንቁዋ ትምህርትነት ለአዲሱ ትውልድ ማቅረብ፣ አሰያም በቅርሰነት ሰመጭው ትውልድ ግቆየት ይቻላል። የአንከሳቱ ብርሃን ተሰማ መዝገበ ቃላት ሰዚህ የሚጠቀሱ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። አሳማቸው <u>ቃላትን</u> በቅደም ተከተል ከነተሰያየ ትርጉማቸው ማሰቀመጥ ነው። ውሰጣዊ የአቀነጃጀት ሰርዓታቸውን ማሳየት አይደሰም። ሊሆንም አይችልም ነበር። ምክንያቱም አሁን ያለው ጥበብ ያኔ አንዳሁኑ በአካባቢያችን አልደበረም።

በአንድ ቁዋንቁዋ ውሰጥ የሚገኙ ቃላት በአንድ ህብረተሰብ ውሰጥ እንደሚገኙ ግለሰቦች ሊቆጠሩ ይችላሉ። ቁዋንቁዋውም አንደ ማህበረሰብ ሊታይ ይችላል። በዚያ ውሰጥ፣ ቃላት አንደ ግለሰብ ተወልደው ሊያድጉ፣ አድገውም ሊያረጁና ሊሞቱ ይችላሉ። ቁዋንቁዋው ግን ይቀጥላል፤ እንደ ህብረተሰቡ። ጥሩ ምሳሌ ባይሆኑም፣ የማዕረግ ሰሞቻችን ለዚህ ሁኔታ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ዛሬ አንደነ አጋፋሪ፣ ባልደራሰ፣ ነጋድራሰ፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ሰሞች ከጥቅም ውጭ ናቸው። በአብዛኛው ንግግራችን ውሰጥ የሚሰሙ አይደሱም። ሞተዋል ማሰት ግን አይቻልም፤ በመዝገበ ቃላት ውሰጥ ይገኛሱና። ሞተዋል ሊባሱ የሚችሱት ከአንደበት አንደጠፉ ሁሱ፣ ከመዝገብም ባይገኙ ነበር።

አንደነ <u>ነጋድራሰ</u> ያሱት ቃላት በመጥፋት ላይ ያሱትን ያህል፣ አንደነ <u>ሙሰኛ</u> ያሱ አዳዲሰ ቃላትም አየተወሰዱ ወይም በትውሰት ወደ ቁዋንቁዋው አየገቡ ነው። ነባሮቹን በቅርሰነት፣ አዲሶቹን በአንግድነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሰተላሰፍ የሚቻለው በአጠቃላይ በዕሁፍ፣ በተሰይ ደግሞ በመዝገበ ቃላት አማካኝነት ነው።

ቃላትን በቅደም-ተከተል በመዝገበ ቃላት ማሰቀመጥ፣ በዚህ ደረጃ ለሚደረግ ጥናት አንዱ ክፍል ነው። ግን ውሱን ክፍል ነው። ውሱን የሚያደርገው አዘጋጁ በሚገኝበት ህብረተሰብ ማህበራዊ የቁዋንቁዋ ችሱታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ችሱታው በቁዋንቁዋው ውሰጥ ሊግኝ የሚችሰውን ቃል ሁሱ አይሸፍንም። ሊሸፍን የሚችሰው የማህበረሰቡን ግንዛቤ የሚገልፁትንና በአዘጋጁም የግል ችሱታና ትውሰታ ውሰጥ ያሱትን ቃላት ብቻ ነው። የቁዋንቁዋው የቃላት ይዞታ ግን በአንድ የማህበረሰባዊ ግንዛቤ አይወሰንም፤ አልፎ ይሄዳል። ሰምሳሌ፣ መዝገበ ቃላት አዘጋጁ <u>ግርጣት</u> የሚለውን ቃል ሰለሚያውቅ፣ በሚያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውሰጥ ተርታ አሲዞ ሊያሰፍረው ይችላል። <u>ብርናት</u> የሚለውን ቃል ግን ሊያሰፍረው አይችልም። ምክንያቱም ቃሱ ከአሱም ሆነ ከማህበረሰቡ ወቅታዊ የቁዋንቁዋ ችሱታ ውጭ ነው። ከቁዋንቁዋው ሰርዓት ውጭ ግን አይደሰም። ምክንያቱም ሰርዓቱ <u>በረታ</u> ብሱ <u>ብርታት</u>፣ <u>ገረጣ</u> ብሱ <u>ግርጣት</u> የሚል የቃላት አካሄድ ሰላለው፣ በዚሁ ሂሳብ በረታ በሚለው ግሰ አኩዋያ፣ <u>በረና</u> የሚል ግሰ አውጥቶ፣ ከአሱ ላይ ደግሞ <u>ብርናት</u> የሚል ሰም መመሰረት ይቻላል። ቁዋንቁዋው እንደነዚህ ያሱ ገና ማህበረሰባዊ ያልሆኑ <u>ፅንሰ-ቃላት</u> አሱት። የሚገኙትም በአዕምሮአችን ውሰጥ ነው። ማንኛውም የአማረኛ ቁዋንቁዋ ተናጋሪ <u>ገረጣ</u> ብሎ <u>ግርጣት</u> ማለት አንደሚችል ሁሱ፣ <u>በረና</u>

ብሎ ብርናት ማለት አያቀተውም። ትረጉሙን ግን ላያውቅ ይችላል። ምክንያቱም ቃሉ አዕምሮአዊ ብቻ ነውና። አንድ ቃል፣ ከአዕምሮአዊነት ወደ ማህበራዊነት ሲመጣ ማህበራዊ ትርጉም ያገኛል። ይህም ትርጉም አያደር ግለሰባዊ ይሆናል። አያንዳንዱ ሰው ያውቀዋል ማለት ነው።

አንደነዚህ ያሉ ፅንሰ-ቃላት ሰጥነታቸው ለመዝገበ ቃላት አዘጋጆች ሳይሆን፣ ለስነ-ቃላት ተመራማሪ ነው። ተመራማሪው የቁዋንቁዋውን ስርዓት ለለሚያውቅ፣ በዚያው መሰረት እንደነዚህ ያሉ ፅንሰ-ቃላትን አየፈለፈለ በማውጣት ለልዩ ልዩ ግንዛቤ ሰያሜ ሊያውላቸው ይችላል። በዚህም ማህበራዊ ያደርጋቸዋል። ማህበራዊ ሲሆኑ፣ መዝገበ ቃላት አዘጋጁም ሰለሚያውቃቸው፣ ተርታ አሊዞ በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ያሰፍራቸዋል። ባጨሩ፣ የስነ-ለሳኑ ባለሙያ ቃላትን ከአዕምሮአዊነት ወደ ማህበራዊነት ያመጣቸዋል፤ የመዝገበ ቃላቱ ባለሙያ ደግሞ መዝግቦ ከነማህበራዊ ትርጉማቸው ለተጠቃሚ ያቀርባቸዋል። ለትውለድም ያቆያቸዋል።

የተመራማሪው ተግባር ቃላትን ባጠቃላይ በቅደም-ተከተል ሳይሆን፣ በአይነት በአይነት መመደብና በየምድቡ ውስጥ የሚገኙትንና ሊገኙ የሚችሉትንም ፅንሰ-ቃላት ጭምር ውስጣዊ የአወቃቀር ስርዓት መመርመር ነው። በዚህም መሰረት፣ በቅደም-ተከተል የመመዝገቡን ክፍል ምዝገባ ቃላት፣ ውስጣዊ አወቃቀራቸውን የሚመለከተውን ክፍል ስርዓተ-ቃላት በማለት ሁለቱን ክፍሎች ልንለያቸው አንችላለን። ስነ-ቃላት አነዚህን ሁለት ክፍሎች የሚያጠቃልል አቢይ ዘርፍ ነው። ዘዚህ ክፍል የምናተኩረው ግን በሁለተኛው ክፍል፣ ማለትም በቃላት ክፍፍልና ውስጣዊ ስርዓት ላይ ነው።

ቃላትን በወገን በወገን መከፋፈሉ፣ የአያንዳንዱን ክፍል ባህሪ ለመገንዘብና አንዱ ክፍል ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድና በቀላሉ ለማየት ያስችላል። የቁዋንቁዋውን አጠቃላይ ባህሪ ለማወቅ፣ ቁዋንቁዋውን አንዳለ በጥቅሉ አያነላበሱ ከማየት ይልቅ፣ ክፋፍሎ አያንዳንዱን ንዑስ ክፍል በተናጠል፣ ከዚያም አንዱን ክፍል ከሌላው ጋር በጋራ ማየቱ ሰለ ቁዋንቁዋው ባህሪ የተሻለ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል። በቁዋንቁዋው ውስጥ ወደ ህምሳ ሺ የሚጠጉ ቃላት አሉ ብንል፣ አያንዳንዱን ቃል ወይም ምዕላድ አያነሱና አየጣሉ በተናጠል መመርመሩ ምን ያህል አድካሚና ጊዜ-ፈጅ እንደሚሆን ለመገንዘብ አያዳግትም። ከዚህ ይልቅ ቃላቱንም ሆነ ምዕላዱን አንደ ተቀራራቢነታቸው በክፍል በክፍል አየመደቡ፣ አያንዳንዱን ክፍል በተናጠልና በትኩረት፣ ከዚያም በጋራና በንፅፅር ማየቱ ቀና አና ፍሬያማ አሰራር ነው። በዚህ መሰረት የአማርኛን ቃላት አንዲትና በሰንት ሊመደቡ አንደሚችሉ ከዚህ ቀጥለን ለማየት አንሞክራለን። ይህንን ሰናደርግም ቃላቱ የሚመደቡባቸውን ክፍሎች ለመለየት ቀደምት የስዋለው ሊቃውንት ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ሰያሜዎች አንደ አሰፈላጊነታቸው አንጠቀምባቸዋለን።

ሊቃውንቱ የአማርኛ ቃላት በሙሉ በለምንት ዋና ዋና ክፍሎች አንደሚመደቡና የክፍሎቹም ለሞች የሚከተሉት አንደሆኑ ይገልፃሉ።

የቃላት ክፍል

ሰም	ግስ	መስተዋድድ	2
ተውላጠ ስም	ተውሳከ ግስ	መስተፃምር	
ቅፅል		ቃለ-አጋኖ	

እነዚህ አያንዳንዳቸው በንዑስ በንዑስ ክፍል ይመደባሉ። ስምሳሌ፣ ስም የሚለው ክፍል የወል፣ የተፀውያ፣ የጥቅል፣ የረቂቅ፣ የቁሳቁስ ወዘተ፣ እየተባለ እንደገና ይለያል። በቁሞንቁዋው ውስጥ የሚገኙት ቃላት ግን በነዚህ በስምንቱም ሆነ በንዑስ ክፍሎቻቸው ብቻ የሚወሰኑ አይደሉም። በነዚህ በአንዱም ሊመደቡ የማይችሉ በርካታ ምዕላዶች አሉ። ያም ሆኖ የቃላቱ በዚህ አይነት መከፋፈል፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ እያንዳንዱን ቃል በስም እየጠቀሱ ባህሪውን ከመዘርዘር ይልቅ፣ በክፍል ስሙ፣ ሰም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ እያሉ መለየቱ፣ ተናጠል ባህሪውን ከክፍሉ ባህሪ አንፃር ለማየት ስለሚረዳ ከአጠናንም ሆነ ከውጤት አኩዋያ የሚመረጥ አካሄድ ነው።

ቃላቱ እንዲት በሰምንት ብቻ ሊከፈሉ ቻሉ? አንዱ ቃል የአንዱ ወይም የሌላው ክፍል አባል ስመሆኑ ወይም ሳስመሆኑ መስኪያው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ከዚህ ላይ ሊነሱ ይችላሉ። የቃላቱ አከፋፈል የተመሰረተው በምለስልነት ላይ ነው። ምስስልነቱ አንዳንድ ጊዜ የቅርፅ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የትርጉም ነው። ስምሳሌ፣ ተከለማሪያም ፋንታዱ አንድን ቃል ስም ወይም የስም ክፍል ነው ሲሉ፣ መነሻቸው ትርጉም ነው። ይኸውም ቃሉ ለመጠሪያነት የሚያገለግል መሆኑ ነው። ስለዚህም ለመጠሪያ ተግባር የሚውሉ ቃላት በዚሁ የተግባር ተመሳሳይነታቸው ስም ተብለው፣ ለመጠሪያ ተግባር ከማይውሉት ሌሎች ቃላት ይለያሉ። ይሁን እንጅ፣ መጠሪያነትን እንደ መሰፈርት ከወሰድነው መጠሪያ ያልሆነ ቃል በቁሞንቁዋው ውስጥ የለም ለማለት ይቻላል። ግስና ቅፅል በሚባሉት ክፍሎች ውስጥ የሚመደቡትን ቃላት ወሳደን፣ በስም ክፍል ውስጥ ከመመደብ የሚያግደን ነገር የለም። ምክንያቱም በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚመደቡ ቃላትም ቢሆኑ፣ የድርጊትና የባህሪ መጠሪያ ወይም ስያሜ ናቸው ብሎ መከራከር ስለማቻል ነው። ስምሳሌ እንደ <u>ዘፈነ</u>፣ <u>ጨፈረ</u>፣ <u>ቆረጠ</u>፣ ወዘተ፣ ያሉትን ቃላት ብንወስድ፣ የሚያመለክቱት ወይም የሚሰይሙት የመዝፈንን፣ የመጨፈርንና የመቁረጥን ተግባር ነው። <u>ጨፈረ</u> ስንል፣ የምናመለክተው የጭፈራ ተግባርን ነው። እንደዚሁም እንደ <u>ረዥም</u>፣ <u>ብልህ</u>፣ <u>ጥቁር</u>፣ ወዘተ፣ ያሉትን ብናይ፣ መጠንን፣ ባህሪንና አይነትን የሚጠቁሙ ቃላት ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህም በስም ውስጥ እንደሚመደቡት ቃላት ሁሉ ለመጠሪያነት ሲያገለግሉ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ምድባቸው በሰም ውስጥ ይሆናል።

ይህ አካሄድ ግን በቁሞንቁዋው ውስጥ የሚገኘውን ቃል ሁሉ ባንድ ክፍል ውስጥ የሚያጉር ነው። ምናልባት፣ አከፋፈሉን በመጠሪያነት ላይ ላይሆን፣ በሚጠሩት ነገሮች ልዩነት ላይ ብንመሰርተው፣ የተለያዩ የመጠሪያ ክፍሎችን ልናገኝ እንችላለን። ይኸውም የነገሮች፣ የድርጊቶች፣ የሁነቶች፣ የባህሪያት፣ ወዘተ መጠሪያ እያልን በመለያየት ነው። እንደዚህም ሆኖ አከፋፈሉ የጠራ አይሆንም። ነገሮች የምንላቸው ምንድን ናቸው? ወደሚል የፍልስፍና

ጥያቄም ሊወስደን ይችላል። ለምሳሌ፣ ብልግና የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ መጠሪያነቱ ለነገር፣ ለተግባር ወይስ ለባህሪ? መልሱ አስቸጋሪ ነው። በሌላ በኩል፣ አንደ ዛፍ ያለ ቃል መጠሪያነቱ ለነገር መሆኑ ብዙም የሚያጠራጥር አይደለም። በተጨማሪም አንደ ዛፍ ያሉ ቃላት የድርጊት መጠሪያ ከሚባሉት የተለዩ ሆነው አናገኛቸዋለን። ልዩነታቸው የቅርፅ ነው። ለምሳሌ፣ አንደ ዛፍ ያሉት፣ ነገሮችን የሚያመለክቱ ቃላት፣ የብዛት ምልክት የሆነውን /-አች/ን ለማስከተል ሲችሉ፣ የድርጊት መጠሪያ የሆኑት ይህን ምልክት ሲያስከትሉ ከቶም አይችሉም። ስለዚህም ዛፍ ብሎ ዛፍ-አች ማለት ሲቻል፣ ገደል ብሎ ገደል-አች ማለት አይቻልም። /-አች/ን ማስከተል መቻልና አለመቻል በነገሮችና በድርጊቶች መጠሪያዎች መካከል ያለ አንድ ልዩነት ነው። ስለሆነም ከዚሁ በመነሳት /-አች/ን ሲያስከትሉ የሚችሉና የማይችሉ ብሎ፣ ቃላትን በቅርፃቸው ብቻ በሁለት መከፈል ይቻላል። ይህ አይነቱ አከፋፈልም መጠሪያ የሆነ ወይም ያልሆነ በሚል ትርጉማዊ መስፈርት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ ቃላቱ በሚያሳዩት የቅርፅ ልዩነት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። ሲበዙ /-አች/ን ሲያስከትሉ የሚችሉና የማይችሉ ብሎ ቃላትን በሁለት መከፈል፣ የነገሮች፣ የድርጊቶች፣ የባህሪያት፣ ወዘተ፣ መጠሪያ የሆኑና ያልሆኑ ከሚለው አከፋፈል እጅግ የተሻለ ነው። ቢያንስ ነገሮች ምንድን ናቸው? ከድርጊቶችና ከባህሪያትስ እንዴት ይለያሉ ወደሚሉ ጥያቄዎች አይወስደንም።

አንዳንድ ጊዜ ሊቃውንቱ መጠሪያ የሚለው ቃል ያዘሰውን ፅንሰ-ሀሳብ ለማጥበብና ሰም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉትን ቃላት መጠን ለመወሰን ሲሉ፣ መጠሪያነትን ለሰው፣ ለቦታና ለነገሮች ብቻ ይወስኑታል። የሰውና የቦታ መጠሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ምናልባት በቀላሉ መለየት ይቻል ይሆናል። የነገሮች መጠሪያ የሚሆኑትን ቃላት መለየት ግን አሁንም አስቸጋሪ ነው። ሞት፣ ህይወት፣ ህልም፣ ዕውቀት፣ ወዘተ፣ ነገሮች ናቸው ወይስ አይደሉም? መለኪያው ምንድን ነው? ቤት፣ ዛፍ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ ከሚሉት የነገሮች መጠሪያ በምን ይለያሉ? የማይለዩ ከሆነ፣ የሰው፣ የቦታና የነገሮች መጠሪያ ብሎ መደንገጉ ምን ያህል ያስኬዳል? የሚለዩ ከሆነ፣ እንደነዚህ ያሉ ቃላት ከፍሳቸው ከምን ይሆናል? የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ።

በትርጉም ላይ የተመሰረተ የቃላት አከፋፈልም እንደነዚህ ካሉ ጥያቄዎች ሊያመልጥ አይችልም። ጥያቄዎቹም በቀላሉ የሚመለሱ አይደሉም። ለአንዱ የሚሰጠው መልስ ሌላ ጥያቄ ይጋብዛል። ከዚህ አይነቱ አከፋፈል ይልቅ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው በቅርፅ ልዩነት ላይ የሚመሰረተው አከፋፈል ብዙ አያስቸግርም። የዚህ አይነት ቅርፅ ያላቸውና የሌላቸው እያለ ስለሚለይ፣ የበለጠ ተጨባጭና አስተማማኝ ነው። አያጨቃጭቅም። ስለዚህም ከአጠናን አንፃር ተመራጭ ነው።

በቅርፅ ላይ የተመሰረተን አከፋፈል ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ቃላትን፣ ካገባባቸው አኳኋያም መለያየት ይቻላል። ቃላት በሀረግና በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ፣ አዘውትረው የሚገኙበትን ቦታ በመመልከት፣ በዚህ ቦታ ሊገቡ የሚችሉና የማይችሉ እያሉ መከፋፈል ይቻላል። ለምሳሌ፣ አንደ ሰው

የቃላት ክፍል

ያሉ ቃላት በአረፍተ ነገር ውሰጥ ሲገቡ፣ ቦታቸው በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መካከል ላይ ነው። በሌላ በኩል አንደ ገደሰ ያሉ የድርጊት መጠሪያ የሚባሉት ቃላት በነዚህ ቦታዎች አይገቡም። እነሱ የሚገኙት በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መሀል ሳይሆን በመድረሻው ላይ ነው። ስለዚህም፣

(ሀ) ቀበሮ ፍየል በላ 3

ማለት ሲቻል፣

(ለ) በላ ቀበሮ ፍየል

ማለት ግን በተሰየ ሁኔታ፣ ሰምሳሌ በግጥም፣ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት ያለው ጤነኛ አባባል አይደለም። የቀበሮ እና የበላ አገባብ ሰየቅል ነው፣ ማሰት ነው። ሰለሆነም አንዱ ሌላውን ተክቶ ሊገባ አይችልም።

ከፍ ሲል እንደተገሰፀው፣ ይህ አይነቱ የቃላት ክፍፍል የሚመሰረተው በቃላት ቅርፅ ሳይ ሳይሆን፣ በአገባብ ላይ ነው። ከምሳሌዎቹ አንደሚታየው፣ እንደ በላ ያሉ የድርጊት መጠሪያ ቃላት በአርፍተ ነገር መድረሻ ላይ ሲገኙ፣ እንደ ሰው ያሉና የነገር መጠሪያ የሆኑት ግን በዚህ ቦታ አይገኙም። ከዚህም የሁለቱ የመጠሪያ ቃላት አገባብ የተሰያየ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ከዚህ ልዩነት በመነሳትም ቃላቱን በሁለት መከፈል ይቻላል። አንደ ቀበሮ እና ሰው ያሉትን የነገር መጠሪያዎች በአንድ በኩል፣ አንደ በላ ያሉትን የድርጊት መጠሪያዎች በሌላ በኩል።

ይህ አያነቱ በአገባብ ሳይ የሚመሰረት አከፋፈል በትርጉም ሳይ ከሚመሰረት አከፋፈል የተሻለ ነው። ምክንያቱም የቃላቱ አገባብ እንደ ቅርፃቸው ሁሉ፣ በዐይን የሚታይ ግሀድ ነገር ሰሰሆነ ነው። ይህ አይነቱ አከፋፈል ለቁጥቋቁ ትንተናም ሆነ ሰቁዋንቁዋ ትምህርት አቀራረብ ቀና ነው። ብዙ ለው በቀላሉ ሊያየውና ሊገነዘበው የሚችል ለለሆነ አያከራክርም። በትርጉም ላይ የሚመሰረት አከፋፈል ግን ለዐይን ሳይሆን፣ ለአዕምሮ ብቻ የሚታይና ለሚታዊ የሆነ ግንዛቤን ሰለሚሰጥ፣ አከራካሪና ተቀባይነቱም እንደየግለሰቡ የግንዛቤ ደረጃና ሰሜት የተለያየ ነው። አንድ ወጥ የሆነ መረጃ ሊያሰገኝ አይችልም። ይህ ሲባል ግን ሰቃሳት አከፋፈል ትርጉም ፈፅሞ አያሰፈልግም፣ ማለት አይደልም። የሚያሰፈልግበት ጊዜ በርግጥ ይኖራል፣ ግን ለክፍፍሉ አንደ ዋና ሳይሆን፣ እንደ ረዳት መሰኪያ ወይም መሰፈርት ሆኖ መወሰድ ያለበት መሆኑን ሰማስገንዘብ ነው።

እንግዲህ ቃላትን ሰመከፋፈል አይነተኛ መሰኪያዎቹ ቅርፅና አገባብ ናቸው ካልን፣ በቅርፃቸው ወይም ባገባባቸው ወይም በሁለቱም የሚመሳሰሉትንና የሚሰያዩትን ቃላት፣ በተለያየ ክፍል ማሰቀመጡ በዚህ ደረጃ ለሚደረግ ጥናት የግድ ይሆናል። ሰለሆነም በአማርኛ ውሰጥ የሚገኙትን ቃላት ከላይ የተዘረዘሩትን ሰምንት ክፍሎች መነሻ በማድረግ፣ አንደገና እንነበኛቸዋለን።

የቃላት ክፍል

ይህን የምናደርግበት ምክንያት በትርጉም መስፈርትነት በስምንት የተከፈሉት ቃላት ከቅርፅና ከአገባብ እንፃር ብቻ ሊታዩ፣ በስንት ሊመደቡ እንደሚችሉ ለማወቅ ነው።

ስም

አንድ ቃል ስም ወይም የስም ክፍል ነው የሚባለው በቅርፁ /-አች/ የሚለውን የብዛት ምዕላድ ሊይዝ የሚችል ከሆነ፣ በአገባቡም በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ ሰው የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ከሆነ ነው።

(ሀ) ሰው ቅዱስ ነው 1
(ለ) እኔ ሰው እፈራለሁ
(መ) ያ ሰው
(ሰ) ትልቅ ሰው
(ረ) ትናንት የመጣው ሰው

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ እንደ ልጅ፣ ውሻ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ቃላት ሰው የሚለውን ቃል እየተኩ ሊገቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ሰው ቅዱስ ነው፣ አንዳልን ሁሉ፣

ልጅ ቅዱስ ነው 2

ለማለት እንችላለን። እንደነዚህ አይነት ቃላትም በዚሁ የአገባብ ተመሳሳይነት ምክንያት ስም ተብለው በአንድ ላይ ሊመደቡ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ረዥም፣ አጭር፣ ቀጭን፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት ሰው የሚለውን ቃል ተክተው በዚሁ ቦታ ሊገቡ ስለማይችሉ፣ እሱ በተመደበበት ክፍል ስም ተብለው ሊመደቡ አይችሉም። በቅርፃቸውም ቢሆን እንደ ልጅ፣ ውሻ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ ያሉት ቃላት /-አች/ የሚለውን ምዕላድ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ሰው ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ሰለዚህም እንድ ላይ ሊመደቡ ይችላሉ።

እንደነዚህ ያሉት ያገባብና የቅርፅ ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው። እንዳንድ ቃላት ግን በቅርፃቸው ሳይሆን፣ ባገባባቸው ብቻ ስም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ይመሰላሉ። ለምሳሌ እኔ፣ እንተ፣ እሱ፣ ወዘተ፣ የሚሉትን ቃላት ብንመለከት፣ ሰው እንደሚለው ቃል /-አች/ የሚለውን ምዕላድ እያስከትሉም። በዚህም ምክንያት እኔ-አች ወይም አንተ-አች ማለት እይቻልም። ሰው ከሚሉ ቃል ጋር የቅርፅ ተመሳሳይነት የላቸውም ማለት ነው። ነገር ግን ባገባባቸው ሰው የሚለው ቃል በገባበት ቦታ በከፊልም ቢሆን

ሊገቡ እንደሚችሉ በቀደምት ሊቃውንት ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) አሱ ቅዱስ ነው 3
(ለ) እኔ አሱን አፈራዋለሁ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ <u>አሱ</u> የሚለው ቃል የገባው በተራ ቁጥር 3(ሀ) እና (ለ) በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ <u>ሰው</u> የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ላይ ቃሉን (ሰውን) ተክቶ የገባ ይመስላል፡፡ በዘህም ምክንያት እንደነዘህ አይነት ቃላት ምድባቸው ስም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ክሌሎች በዘህ ክፍል ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ጋር ባላቸው የቅርፅ ልዩነት ምክንያት በቀደምት የሰዋሰው ሊቃውንት ዘንድ ስም ላይሆን፣ ተውላጠ ስም በሚል ልዩ ክፍል ውስጥ ለብቻቸው ሲመደቡ ችለዋል፡፡ ተውላጠ ስም ማለትም የስም ልዋጭ ወይም ምትክ ተብሎ ተገልፆአል፡፡ <u>ግዛዌው</u> ቃላቱ ክስም ጋር ያላቸውን የአገባብ ተመሳሳይነት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ተመሳሳይነቱ ግን ምሳሌዎቹ አንዲሁ ላይ ላዩን ሲታዩ፣ የሚከሰት ነገር ነው፡፡ ጠለቅ ብለን ስናየው፣ ተውላጠ ስም የሚባሉት በስም ቦታ ስምን ተክተው አይገቡም፡፡ በምሳሌ 3(ሀ) <u>አሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም የገባው ከዚህ በታች በምሳሌ (4) የሚታየውን <u>ልጅ</u> የሚለውን ስም ተክቶ አይደለም፡፡ ይልቁንስ የገባው በራሱ ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ደግሞ ልጅ ከሚለው ስም ቀድሞ ነው፡፡ ስለዚህም ምሳሌ 3(ሀ) በጥልቀት ሊታይ፣ <u>አሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም አግባብ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

<u>አሱ</u> ልጅ ቅዱስ ነው 4

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>አሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም ቦታ ልጅ ከሚለው ስም በፊት ነው፡፡ ልጅ የሚለው ስም ሲገደፍ፣ ተውላጠ ስሙ በስሙ ቦታ የገባ ይመስለናል፡፡ ከዚህም ምስለት የተነሳ፣ ቃሉ ተውላጠ ስም (የስም ልዋጭ) ለመባል በቅቶአል፡፡ በቅርፅም ቢሆን ተውላጠ ስሞች ክስሞች የተለዩ ናቸው፡፡ ስምሳሌ ስሞች ብዛትን ለማመልከት /-ኦች/ የሚለውን ምዕላድ ያስከትላሉ፡፡ ተውላጠ ስሞች ግን /-ኦች/ን አያስከትሉም፡፡ ስስዚህም <u>ልጅ</u> ብለን <u>ልጅ-ኦች</u> ማለት ስንችል፣ <u>አሱ</u> ብለን <u>አሱ-ኦች</u> ማለት አንችልም፡፡ ሁኔታው ተውላጠ ስም የሚባሉት በአገባብም ሆነ በቅርፅ ክስም የተሰዩ መሆናቸውን በግልፅ ያመለክታል፡፡ ስስዚህም ክስም ተለይተው ለብቻቸው መታየት አለባቸው፡፡ የሚታዩት ግን በተውላጠ ስምነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ስምን <u>ተክተው</u> በስም ቦታ ስለማይገቡ ነው፡፡ ምሳሌ (4) የሚያሳየን ይህንን ሁኔታ ነው፡፡ ዝርዝሩን ወደሁዋላ እንመለስበታለን፡፡ በዚህ ክተሰማማን ወደሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እንሂድና ሌሎች ቃላትን እንመልከት፡፡

ግስ

ማንኛውም በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ ሊገባ የሚችልና እንደ /-ሁ/፣ /-ህ/፣ /-ሽ/፣ ወዘተ፣ ያሉ መደብ አመልካች ምዕላዶችን ሊያስከትል የሚችል ቃል ሁሉ ግስ ተብሎ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊመደብ ይችላል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) እኔ ዳቦ በላ-ሁ 1
(ለ) አንተ ወተት ጠጣ-ህ
(መ) አንቺ ዶሮ ገዛ-ሽ

በነዚህ ሶስት አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ የመድረሻዎቹ ቃላት በላ-ሁ፣ ጠጣ-ህ እና ገዛ-ሽ የሚሉት ናቸው። እነዚህ ቃላት ስግስ የሰጠነውን የአገባብ መስፈርት ስለሚያሙዋሉ፣ ግስ ተብለው በዚሁ ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ። በተጨማሪም በሚቀጥለው ክፍል በዝርዝር የምናያቸውን እንደ /-ሁ/፣ /-ህ/ እና /-ሽ/ ያሉትን መደብ አመልካች ምዕላዶችን ስላስከተሉ፣ በቅርፅ ረገድ የተስጠውን መስፈርት ያሙዋላሉ። /-አችች/ የሚለውን የብዛት ምዕላድ ከሚያስከትሉትና ስም በሚሰው ክፍል ውስጥ ከሚመደቡት ቃላትም በቅርፅ ብቻ ላይሆን፣ በአገባብም እንደሚለዩ መረዳት ይቻላል። በስም ክፍል ውስጥ የሚመደቡት በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ አይገኙም። እንደ በላ ያሉ በግስ ክፍል ውስጥ የሚመደቡትም፣ በስም ውስጥ እንደሚመደቡት በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ አይገኙም።

እነዚህ ሁለት ክፍሎች በቁዋንቁዋው ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን አብዛኛውንና ለሀሳብ መግለጫነትም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መደበኛ መድበለ ቃላት ይሸፍናሉ። በማንኛውም ቁዋንቁዋ ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ቃል የድርጊትና የነገር ስም ነው። አብዛኛው አረፍተ ነገርም የነገሮችና የድርጊቶች መግለጫ የሆኑት የስሞችና የግሶች ቅንጅት ነው። ሌሎች ቃላት የነዚህ የሁለቱ ክፍሎች አጃቢዎች ናቸው። ከነዚህም ከፊሎቹ ቅፅል የሚባሉትና ከዚህ ቀጥለን የምናያቸው ናቸው።

ቅፅል

በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ ጎበዝ የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ቃል ቅፅል ተብሎ በዚህ ክፍል ሊመደብ ይችላል።

(ሀ) ጎበዝ ተማሪ 1
(ለ) በጣም ጎበዝ

የቃላት ክፍል

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ <u>ነበዝ</u> የሚለውን ቃል እንደ ብልህ፣ አስተዋይ፣ ረዥም፣ ሰነፍ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት ሊተኩት ይችላሉ። እንደ <u>ገደለና</u> እንደ <u>ሰው</u> ያሉት ግን ሊተኩት አይችሉም። ምክንያቱም፣

(ሀ) *<u>ገደለ</u> ተማሪ 2
(ለ) *በጣም <u>ሰው</u>

ማለት ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለምና። ከፍ ሲል እንደ ተመለከትነው፣ እንደ <u>ገደለና</u> <u>ሰው</u> ያሉት ቃላት ምድባቸው፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በሰምና ሰግስ ከፍሉች ውስጥ ነው። ስለዚህም በቅፅል ውስጥ እንደገና ሊመደቡ አይችሉም። እንድ ቃል ሊመደብ የሚችለው በመሰረቱ በእንድ ከፍል ውስጥ ብቻ ነው። ርግጥ፣ አንዳንድ አጉራ-ዘለል አይጠፉም፤ እንደ ሰው።

ከላይ በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ እንደሚታየው፣ <u>ነበዝ</u> የሚለውን ቃል እንደ <u>ሰውና</u> እንደ <u>ገደለ</u> ያሉ ቃላት ሊተኩት አይቻሉ እንጅ፣ ሌሉች ቃላት ሊተኩት የሚችሉ ይመስላል። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) <u>ይህ</u> ተማሪ 3
(ለ) በጣም <u>ቸኮለ</u>

በነዚህ ምሳሌዎች መሰረት፣ እንደ <u>ይህና</u> እንደ <u>ቸኮለ</u> ያሉ ቃላት በተራ ቁጥር (1) ውስጥ በሚገኙት ምሳሌዎች የሚገኘውን ቅፅል፣ ማለትም <u>ነበዝን</u>፣ ተክተው ሰለገቡ፣ ምድባቸው ቅፅል ውስጥ ነው፣ ሊባል ይችል ይሆናል። ይባል እንጅ፣ እንደ <u>ይህ</u> እና እንደ <u>ቸኮለ</u> ያሉ ቃላት ቅፅል አይደሉም። ምክንያቱም በ3(ሀ) ውስጥ <u>ይህ</u> የሚለው ቃል የገባው <u>ነበዝ</u> የሚለውን ቅፅል ተክቶ አይደለም። ቃሉ የገባው በቅፅሉ ቦታ ላይሆን፣ አሁንም በራሱ ቦታ ነው። ቅፅሉን ተክቶ የገባ የሚመስለው ቅፅሉ ሲገደፍ ብቻ ነው። ሁለቱም በየቦታቸው ሲገኙ፣ 3(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል።

ይህ ነበዝ ተማሪ 4

<u>ይህ</u> የሚለው ቃል፣ <u>ነበዝ</u> የሚለውን ቅፅል ቀድሞ በራሱ ቦታ እንደገባ ግልፅ ነው። <u>ነበዝ</u> የሚለው ቅፅል ከቦታው ሲገደፍ፣ <u>ይህ</u> በሚለው የተተካ ይመስላል። ዋናው ነገር ሁለቱ ቃላት የተለያየ ቦታ ያላቸው መሆኑ ነው።

በነዚህ ቃላትና ቅፅል ባልናቸው መካከል ሌሉች የእገባብ ልዩነቶችም አሉ። ለምሳሌ በ3(ለ) ውስጥ እንደሚታየው፣ <u>ቸኮለ</u> የሚለው ቃል <u>በጣም</u> የሚለውን ቃል ተክትሉ ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ <u>ነበዝ</u> እንደሚለው ቅፅል፣ <u>ተማሪ</u> የሚለውንና ምድቡም ሰም ውስጥ የሆነውን ቃል ቀድሞ ሊገባ አይችልም። ስለዚህም፣

የቃላት ክፍል

(ሀ) ጎበዝ ተማሪ 5

ማለት እንደሚቻል ሁሉ፣

(ለ) *ቸኮለ ተማሪ

ማለት አይቻልም። ይህ የሚለው ቃልም ቢሆን፣ ጎበዝ እንደሚለው ቅፅል በጣም የሚለውን ቃል ተከትሎ ሊገባ አይችልም። ስለዚህም፣

(ሀ) በጣም ጎበዝ 6

ማለት ሲቻል፣

(ለ) *በጣም ይህ

ማለት አይቻልም። ይህም የሚያሳየው፣ አንድ ቃል ቅፅል ለመባል ቀደም ሲል ስለ ቅፅል የተሰጡትን ሁለት መስፈርቶች ማሙዋላት ያለበት መሆኑን ነው። ከሁለቱ አንዱን ብቻ ማሙዋላቱ ቅፅል ሊያስኘው አይችልም። ነገሩን ለማቃለል መለፈርቶቹን በአንድ ላይ አካቶ፣ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል። በሚከተለው ምሳሌ ውስጥ ጎበዝ የሚለውን ቃል የሚተካ ማንኛውም ቃል ቅፅል ሊባል ይቻላል።

በጣም ጎበዝ ተማሪ 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ይህ የሚለውም ሆነ ቸኮለ የሚለው ቃል ጎበዝ የሚለውን ቃል ፊፅሞ ሊተካ አይችልም። ቃሉ ሊተካ የሚችለው፣ እንደ ሰነፍ፣ ብልህ፣ ንቁ፣ ወዘተ፣ ባለ ቅፅል ብቻ ነው። እንደዚህ ያለ ቃል ደግሞ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ምድቡ ቅፅል በሚለው ክፍል ውስጥ ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም፣ በምሳሌ 5(ለ) እንደሚታየው፣ ቸኮለ ተማሪ ማለት አይቻል እንጅ፣ የቸኮለ ተማሪ ማለት በሚገባ ይቻላል። ይህ ከሆነ፣ የቸኮለ የሚለው ቃል ቅፅል አይሆንም ወይ?

ርግጥ ነው፣ የቸኮለ የሚለው ቃል ጎበዝ የሚለውን ቅፅል ሊተካ ይችላል። ስለዚህም ምሳሌ (7) እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል።

በጣም የቸኮለ ተማሪ 8

የቸኮለ የሚለው ግን ቸኮለ ከሚለው ይለያል። ምክንያቱም ቸኮለ የሚለው ሊጣ ግስ ሲሆን፣ የቸኮለ የሚለው ግን ከግስ በላይ ነው። የ የምትለዋ ምዕላድና ቸኮለ የሚለው ግስ ቅንጅት ነው። ከቅንጅትም አረፍተ ነገራዊ ቅንጅት ነው። ስለዚህም በቃል ደረጃ የሚታይና በቃላት ክፍል የሚመደብ አሀድ አይደለም። ምድቡ ከአረፍተ ነገር ጋር ነው። ውስጣዊ ሰርዓቱን ወደፊት እናየዋለን። በቃል ደረጃ ልናየው የምንችለው፣ ቸኮለ የሚለውን ሊጣ ግስ ብቻ ነው። እሱ ደግሞ በተራ ቁጥር 5(ለ) በግልፅ እንደሚታየው፣ ጎበዝ የሚለውን ቅፅል አይተካም።

የቃላት ክፍል

እስካሁን ያየነው የቅፅል አከፋፈል በአገባብ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። እንደ ሰምና ግስ ያሉት ቃላት አከፋፈል ግን ቅርፅንም መሰረት ያደረገ ነበር። ይህም ቅፅል ቅርፃዊ መለያ የሰውም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊያሳስብ ይችላል። ርግጥ ነው፤ እንደ <u>ረዥም</u> ያሉ የቅፅል ክፍል ቃላት ከሰሞችና ከግሶች የሚለያቸው ቅርፅ አላቸው። ይህም ብዛትን ወይም ሰብሰብን ከየሚያሳዩበት ሰርዓት ጋር የተያያዘ ነው። የሚከትሉትን እንመልከት።

<u>ነጠላ</u>	<u>ብዙ</u>	9
ረዥም	ረዣ-ኣ-ዣም	
አጭር	አጭ-ኣ-ጭር	
ጥቁር	ጥቋ-ኣ-ቁር	

በግልፅ እንደሚታየው፤ የነጠላ ቁጥሩ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ድምፅ በብዙ ቁጥሩ ውስጥ ተደግሞአል። ሁለተኛም /ኣ/ የሚል አናባቢ ድምፅ በሁለቱ ተደጋጋሚ ድምፆች መካከል ገብቶአል። ይህ ሰርዓት ቅፅሎችን ከሰሞችና ከግሶች በመጠኑ ይለያቸዋል። በመጠኑ የምንልበት ምክንያት ሰሞችና ግሶችም የዚሁ አይነት ባህሪ፤ ሰየት ባለ መልክ፤ ሰለሚያሳዩ ነው። ሰሞች ሰብሰብን ለማመልከት ራሳቸውን የሚደግሙበት ሰርዓት አላቸው። ለምሳሌ፤ <u>ቅጠል</u> ብለን <u>ቅጠል-ኣ-ቅጠል</u> (ቅጠሳቅጠል) እንላለን። ሁኔታው <u>ረዥም</u> ብለን <u>ረዥ-ኣ-ዣም</u> እንደምንለው ነው። ይሁን እንጅ፤ ሰሞች ሙሉ ቅርፃቸውን ሲደግሙ፤ ቅፅሎች ግን ቅድመ-መድረሻ ድምፃቸውን ብቻ ይደግማሉ። በሙ ሙሉ አካሉን ሲደግም፤ ቅፅሉ እንዱን ድምፁን ብቻ ይደግማል። ልዩነቱ የደረጃ ነው። ቢሆንም አንዱን ከሌላው ለመለየት ያስችላል። ወደሚቀጥለው እንሂድ።

ተውሳክ ግስ

ከዚህ በታች በተሰጠው አረፍተ ነገር ውስጥ <u>ትናንት</u> የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ቃል ተውሳክ ግስ ሊባል ይችላል። የቃሉ ትርጉም የግስ ጭማሪ ማለት ነው። ከግስ ጋር እየገባ ግሱ ለሰሚገልፀው ድርጊት ተጨማሪ ሀሳብ ይሰጣል።

እሱቴር <u>ትናንት</u> ምሳ አልበላችም 1

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፤ <u>ትናንት</u> የሚለውን ቃል እንደ <u>ሰው</u>፤ እንደ <u>ቸኮሰ</u> ወይም <u>ጎበዝ</u> ያሉ ቃላት ሊቲኩት አይችሉም። ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ከፍላቸው ስም፤ ግስና ቅፅል ነው ብለናል። ተውሳክ ግስ የሚባሉት ከነዚህ አይነት ቃላት በአገባባቸውም ሆነ በቅርፃቸው የተሰዩ መሆን አለባቸው።

በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ ትናንት የሚለው ቃል እንደ ቶሉ፣ ዛሬ፣ ገና፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት ሊተኩት ይችላሉ። ለምሳሌ፣

(ሀ) አስቴር ቶሉ ምሳ አልበላችም 2
(ለ) አስቴር ገና ምሳ አልበላችም
(መ) አስቴር ዛሬ ምሳ አልበላችም

ማለት ይቻላል። በነዚህ እረፍተ ነገሮች ውስጥ ቶሉ፣ ገና እና ዛሬ የገቡት በተራ ቁጥር (1) በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ ትናንት የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ነው። ስለዚህም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ክፍል ተውላክ ግሰ ነው ለማለት ይቻላል።

ክፍሉ እንደ ሰሞችና እንደ ግሶች በርካታ ቃላት የሉትም። ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ምናልባት ልናነኝ የምንችለው የሚከተሉትን ነው።

ግምኛ 3
ጅልኛ
ምንኛ
ክፉኛ
እንደገና

እነዚህ የተውላክ ግሰ ክፍል ለመሆናቸው ማረጋገጫው፣ ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (1) በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ትናንት የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ሊገቡ መቻላቸው ነው። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ትናንት ታሞ ነበር 4
(ለ) ካሳ ክፉኛ ታሞ ነበር
(መ) ካሳ እንደገና ታሞ ነበር

ከዚህ ላይ እንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም በምሳሌ 2(ሀ) እና በምሳሌ (4) ውስጥ በተውላክ ግሰነት የገቡት ቃላት በምሳሌ (1) የሚታየውን ትናንት የሚለውን ቃል ተክተው ነው ወይ? የሚል ነው። ለምሳሌ፣

ካሳ ትናንት ክፉኛ ታሞ ነበር 5

ሰንል፣ ትናንት እና ክፉኛ ተከታትለው በየራሳቸው ቦታ እንደገቡ ግልፅ ነው። ይህ ከሆነ፣ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ክፍል ቃላት ናቸው፣ ለማለት እይቻልም ወይ? ርግጥ ነው፣ ቃላቱ ተከታትለው በየግል ቦታቸው ገብተዋል። ይህ ግን በተለያየ ክፍል ውስጥ እንዲመደቡ አያደርጋቸውም። ቃላት በክፍላቸው አንድ ሆነው፣ በግብራቸው ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ትናንት የሚለው ጊዜን የሚያመለክት

ቃል ሲሆን፣ ክፉኛ የሚለው ሁኔታን የሚያመልክት ነው። ሁለቱም ታሞ ነበር የሚለውን ግሰ የሚገልፁ ተውሳክ ግሶች ናቸው። አንዱ የህመሙን ጊዜ፣ ሌላው የህመሙን መጠን ይገልፃል። ሁኔታው፣ የተለያየ ተውሳክ ግሳዊ ተግባርን የሚገልፁ የተለያዩ ተውሳክ ግሶች ተከታትለው ሊመጡ እንደሚችሉ ያሳያል።

በሌሎቹም ክፍሎች ቢሆን ተመሳሳይ ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ቅፅሎችን ብንወሰድ፣ እንደሚከተሉት ያሉ ምሳሌዎችን እናገኛለን።

ካሳ ጥሩ ነጭ ላም አለችው 6

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ጥሩና ነጭ ተከታትለው ገብተዋል፣ ግን ክፍላቸው አንድ ነው። ተከታትለው የገቡት የተለያየ ቅፅላዊ ባህሪን ወይም አይነትን ለመግለፅ ነው። ጥሩ የሚለው ባህሪን ሲገልፅ፣ ነጭ የሚለው ቀለምን ይገልፃል። በዚህም መሰረት ሁለቱ ቃላት የባህሪና የአይነት ቅፅል ሊባሉ ይችላሉ።

ተውሳክ ግሰ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ቃላት በቁዋንቁዋው ውስጥ በብዛት የሉም። ይህ ግን ተውሳክ ግሳዊ የሆነ ተግባር የለም ማለት አይደለም። ብዙ ተውሳክ ግሳዊ ተግባራት አሉ። ለምሳሌ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ ሁኔታ፣ ወዘተ፣ መግለፅ ተውሳክ ግሳዊ ተግባር ነው። ይህ ተግባር የሚገለፀው ግን በአብዛኛው በተውሳክ ግሰ ሳይሆን፣ በሰማዊ ሀረጎች፣ በመሰተዋድዳዊ ሀረጎች ወይም በጥገኛ አረፍተ ነገሮች ነው። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) የካሳ ልጅ [በፍጥነት ወደ ጎንደር ሄደ] 7
(ለ) አሰቴር [የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ አለቀሰች]

በ7(ሀ) ውስጥ በፍጥነት የሚለው ክፍል፣ የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር የሄደበትን ሁኔታ ያመለክታል። በ7(ለ) ውስጥ፣ የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ የሚለው ክፍል አሰቴር ያለቀሰችበትን ጊዜ ይገልፃል። በፍጥነት የሚለውም ሆነ የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ የሚለው ክፍል ተውሳክ ግሰ አይደለም። ከቅርፅ አንፃር ሲታዩ፣ የመጀመሪያው ከመሰተዋድድና ከሰም የተቀናጀ መሰታውድዳዊ ሀረግ ነው። መሰተዋድዱ በ ሲሆን፣ ሰሙ ደግሞ ፍጥነት የሚለው ነው። ሁለተኛው ከሰማዊ ሀረግና ከግሳዊ ሀረግ የተመሰረተ ጥገኛ አረፍተ ነገር ነው። ሰማዊ ሀረጉ የካሳ ልጅ የሚለው ክፍል ሲሆን፣ ግሳዊ ሀረጉ ወደ ጎንደር ሲሄድ የሚለው ነው። መሰተዋድዳዊ ሀረጉም ሆነ ጥገኛው አረፍተ ነገር ቅንጅታዊ መዋቅር እንጅ ተራ ተውሳክ ግሳዊ ቃላት አይደሉም። ተራ ተውሳክ ግሳዊ ቃላት የሚባሉት እንደ ክፉኛ ያሉ ተናጠል ቃላት ብቻ ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ የቦታ ተውሳክ ግሰ ይባሉ የነበሩትን ብንመለከት፣ ክፍላቸው ከቃላት ሳይሆን፣ ከመሰተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ሆኖ እናገኘዋለን። የሚከተሉት የነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

(ሀ) ካሳ <u>ወደታች</u> ወረደ 8
(ለ) አስቴር <u>እዚህ</u> ነበረች

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>ወደ ታች</u>ና <u>እዚህ</u> የሚሉት ክፍሎች፣ በተግባራቸው ተውሳክ ግስ ናቸው። የሚያመለክቱት ካሳ የወረደበትንና አስቴር የነበረችብትን ቦታ ነውና። በቅርፃቸው ግን መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው። <u>ወደታች</u> የሚለው፣ <u>ወደ</u> ከሚለው መስተዋድድና <u>ታች</u> ከሚለው ስም የተመሰረተ ሀረግ ነው። <u>እዚህ</u> የሚለውም <u>ከ</u> የሚለው መስተዋድድና <u>ይህ</u> የሚለው ጠቁዋሚ ምዕላድ ቅንጅት ነው። ከዚህ ቦታ እንደ ማለት ነው። ስለዚህም መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ምናልባት ወደ ተራ ቃልነት የተለወጠ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፤ ማለቱ ይቀል ይሆናል።

ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው፣ በአማርኛ የተውሳክ ግስ ተግባር የሚገለፀው በአብዛኛው በክፍላቸው ሳይሆን፣ በተግባራቸው ብቻ ተውሳክ ግሳዊ በሆኑ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና ጥገኛ አረፍተ ነገሮች መሆኑን ነው። ይህም ሊሆን የቻለው፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ተውሳክ ግስ የሚባለው ክፍል ሁሉንም ተውሳክ ግሳዊ ተግባራት የሚገልፅበት ተውሳክ ግሳዊ ሊባሉ የሚችሉ ቃላት ስለሌለው ነው። ክፍሉ እንደ ስም ወይም እንደ ግስ ሰፊ የቃላት ክምችት ስለሌለው፣ እንደ ክፉኛ ባሉ መደበኛ ተውሳክ ግሶች ሊገለፅ የማይችለውን ተውሳክ ግሳዊ ተግባር፣ በሀረጎችና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች ይገልፃል። ይህን በዚሁ አንተወውና ወደሚቀጥለው ክፍል እንሂድ።

እስካሁን ያየነው ሁኔታ የአማርኛ ቃላት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችሳሉ ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ነው። ክፍሎቹም የሚከተሉት ናቸው።

ስም ግስ 9
ቅፅል ተውሳክ ግስ

እነዚህ በሙሉ የይበት፣ ማለትም የትርጉም፣ ቃላት ናቸው። ዋና ዋና የተባሉበት ምክንያትም ስዚሁ ነው።

በአራቱ ክፍሎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን ቃላት አገባባዊና ቅርፃዊ ባህሪያት ገልፀናል። በዚህ መሰረት፣ በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ቃል በአገባቡ ወይም በቅርፁ ወይም በሁለቱም ከነዚህ ዋና ዋና ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው ሊመደብ የሚችል ነው። በነዚህ ውስጥ ሊመደቡ የማይችሉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቃላት ግን አሉ። እነዚህም ከዚህ ቀጥሰን የምንመለከታቸው ናቸው።

የንዑስ ቃላት ክፍል

ባለፈው ክፍል ያየነው የዋና ዋና ቃላትን ክፍሎች ነው። ዋና ዋና ቃላት የሚባሉት በቃል ደረጃ ትርጉም፣ በመዋቅር ደረጃ ሰዋሰዋዊ ተግባር ያላቸው ናቸው። ክትርጉም አኳያ፣ ነገሮችንና ባህሪያቸውን እንዲሁም ድርጊቶችንና አደራረጋቸውን ይጠቁማሉ። ነገሮችን የሚጠቁሙት ሰሞች ሲሆኑ፣ ባህሪያቸውን የሚጠቁሙት ቅፅሎች ናቸው። ድርጊቶችን የሚጠቁሙት ግሶች፣ አደራረግን የሚጠቁሙትም ተውሳክ ግሶች የሚባሉት ናቸው። በዚሁ መሰረት አራቱን የቃላት ክፍሎች የገላጭና የተገላጭ ወገን ብለን በሁለት ልንመድባቸው እንችላለን። ሰምና ግሰ የተገላጭ ሲሆኑ፣ ቅፅልና ተውሳክ ግሰ የገላጭ ወገን ናቸው። ህይወትም እንደዚሁ የገላጭና የተገላጭ ጥምረት ነው፣ በወጉ ካየነው።

ከነዚህ ውጭ፣ ትርጉም ሳይሆን መዋቅራዊ ተግባራት ብቻ ያላቸው ቃላት አሉ። እነዚህም በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ተውላጠ ሰም፣ መስተዋድድ፣ መስተፃምር፣ ቃሰ አጋኖ እንዲሁም በዘመናዊ ስነ-ልሳን መስተዓምር በመባል የሚታወቁት ናቸው። ሁሉንም በጥቅል ንዑስ ቃላት ብለናቸዋል። ንዑስ የሚሰኙባቸው የጋራ ባህሪያት አሉዋቸው። እነዚህም የሚከትሉት ናቸው።

(ሀ) የራሳቸው የሆነ ቃላዊ ትርጉም የላቸውም፤
(ለ) ለአዳዲስ ቃላት ምስረታ ዘር ወይም እናት ቃል አየሆኑ ሊረቡ አይችሉም፤
(መ) የራሳቸው የሆነ የቁጥር፣ የፆታ፣ የጊዜ፣ ወዘተ፣ ቅጣይ ምዕላድ የላቸውም፤
(ሰ) ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ አይጨምርም። ሰለዚህም ትረጉም ያላቸው ቃላት መጠን ሲጨምር የእነሱ አይጨምረም፣ አይቀንስምም፤
(ረ) በ<u>መጠን-ወርዳቸው</u> ንዑስ ናቸው

ወደፊት በሰፊው እንደምናየው፣ ዋና ዋና ክፍሎች የሚባሉት አዳዲስ ቃላትን ሰመፍጠር ግብዓት ወይም ዘር በመሆን ያገለግላሉ። በዚህም ምክንያት የየክፍሉ የቃላት መጠን በየጊዜው ይጭምራል። ከዚህ አፃርም የንዑስ ቃላት መጠን የመጨመርም ሆነ የመቀነስ አዝማሚያ አያሳይም። በወርደ-መጠናቸውም ድሀር ናቸው። ከትርጉም፣ ክቅርፅና ከመዋቅር አኳያ እንደነዚህ ያሉትንና ከአራቱ ዋና ዋና ክፍሎች ውጭ የሆኑትን ቃላት በሙሉ ንዑስ ቃላት ብሰን ከዋና ዋና ቃላት ክፍሎች እንሰያቸዋለን። ይሁን እንጅ፣ እንደመዋቅራዊ ባህሪያቸው በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ልንመድባቸው እንችላለን። እነዚህም መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው። ዝርዝራቸውን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

መለስተዋድድ

ማንኛውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ቃል መስተዋድድ ሊባል ይችላል፡፡

(ሀ) ከሰም በፊት እየገባ ተውሳክ ግሳዊ ተግባራትን፣ ለምሳሌ ጊዜን፣ ቦታን፣ ምክንያትን፣ አሳማን፣ ወዘተ፣ የሚገልፅ፣
(ለ) ምንም አይነት ቅጣይ ምዕላድን የማያስከትል፣ እና
(መ) ለአዳዲስ ቃላት ምስረታ መስረት ሊሆን የማይችል፡፡

በነዚህ መስፈርቶች መሰረት መለተዋድድ ሊባሉ የሚችሉት እንደ፣ ስለ፣ ወደ፣ ከ፣ ለ፣ ወዘተ፣ ያሉ በመጠነ-ወርዳቸው ንዑስ የሆኑ ምዕላዶች ናቸው፡፡ የራሳቸው የሆነ ትርጉም የላቸውም፡፡ ተግባር ግን አላቸው፡፡ ይህም ከስም ጋር እየተዋቀሩ መስተዋድዳዊ ሀረግ በመፍጠር ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፣ የተለያዩ ተውሳክ ግሳዊ ተግባራትን መግለፅ ነው፡፡ ይህንን ከሚከተሉት ምሳሌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

(ሀ) [ሰለ ትምህርት] ብዙ ሰው ይቆረቆራል (1)
(ለ) [እንደ ርግብ] የዋህ ሁኑ
(መ) [ወደ ጎንደር] እሄዳለሁ
(ሰ) [በሶስት ሰዓት] ይመጣል
(ረ) [ለሰርግ] የተጠመቀ ጠላ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተሰመረባቸው ንዑስ ቃላት እንደ ቅደም-ተከተላቸው (ከላይ ወደ ታች) ትምህርት፣ ርግብ፣ ጎንደር፣ ሶስት ሰዓት፣ እና ሰርግ ከሚሉት ስሞች በፊት በመግባትና በመቀናጀት፣ ከሰሞቹ ጋር መለተዋድዳዊ ሀረግ ፈጥረዋል፡፡ ሀረጎቹም በቅንፍ ውስጥ የሚታዩት፣ ሰለ ትምህርት፣ እንደ ርግብ፣ ወደ ጎንደር፣ በሶሰት ሰዓት እና ለሰርግ የሚሉት ናቸው፡፡ ተግባራቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ ምክንያትን፣ ንፅፅርን፣ አቅጣጫን፣ ጊዜን እና ዓላማን መግለፅ ነው፡፡ እነዚህም ተውሳክ ግሳዊ ተግባራት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ብንወስድ፣ ሰብዙ ሰው መቆርቆር ምክንያት የሆነው ጉዳይ፣ ትምህርት እንደሆነ የሚገልፅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለሰ ትምህርት የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ተግባር፣ ምክንያትን መግለፅ ስለሆነ፣ ከዚሁ ተግባሩ እንፃር የምክንያት ተውሳክ ግሰ ልንሰው እንችላለን፡፡

ከሁለተኛው መስፈርት አኳያ ብናያቸው፣ እንደ ሰለ እና እንደ ወዘተ፣ ያሉ መለተዋድዳዊ ቃላት እንደ ሌሎቹ ቃላት፣ ለምሳሌ፣ ግስ እንደሚባሉት፣ ልዩ ልዩ ምዕላዶችን እያለከትሉም፡፡ ለምሳሌ፣ ሰበረ የሚለው ግሰ ሰበር-ኩ፣ ሰበር-ክ፣ ሰበር-ን፣ ወዘተ፣ እያለ መደብ ወይም ቁጥር እመልካች ምዕላዶችን

የቃላት ክፍል

በማስከተል ቅርፁን በከፊል መስዋወጥ ይችላል። እንደ <u>ስለ</u> እና <u>አንደ</u> ያሉ ቃላት ግን ቅርፃቸውን በዚህ አይነት አይስዋውጡም። ስለዚህም ስለ-ሁ፣ ስለ-ህ፣ ስሉ-ን ወዘተ፣ ማለት አይቻልም። እንደነዚህ አይነት ቃላት ቅርፃቸውን በዚህ አይነት ቢለዋውጡ ኖሮ፣ ምድባቸው እንደ <u>ስበረ</u> ካሉ ቃላት ጋር በግስ ውስጥ ይሆን ነበር። ይህም ቢሆን፣ ከቅርፅ አኩዋያ ብቻ ነው። አገባባቸው ከግሶች የተለየ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የግሶች አገባብ በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ ነው። እንደ <u>ስለ</u> እና እንደ <u>አንደ</u> ያሉ ቃላት ደግሞ በዚህ ቦታ ፈፅሞ አይገኙም፣ ምክንያቱም፣

(ሀ) ካሳ ወደ ጎንደር ኼደ 2

ማለት ሲቻል፣

(ለ) *ካሳ ወደ ጎንደር <u>ስለ</u>

ማለት፣ ውል ያለው አባባል ባለመሆኑ ነው።

በመጨረሻም፣ አንደ <u>ሰበረ</u> ያሉ ቃላት ለሌሎች ቃላት ምስረታ መሰረት ለመሆን ሲችሉ፣ እንደ <u>ስለ</u> ያሉት ግን መሰረት ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህም <u>ሰበረ</u> በሚለው ግስ አኩዋያ እንደ ሰባሪ፣ ሰባሪ፣ ሰበራ፣ መሰበር፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ቃላትን መመስረት ሲቻል፣ አንደ <u>ለስ</u> ባሉት አኩዋያ ግን ምንም አይነት ቃላት መመስረት አይቻልም። ስለዚህም <u>ስበረ</u> ብለን <u>ሰባሪ</u> ማለት እንደምንችል ሁሉ፣ <u>ስለ</u> ብለን <u>ሰላይ</u> ማለት አንችልም።

እንግዲህ፣ ቀደም ሲል ከ(ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩትን መሰፈርቶች የሚያሙዋሉ እንደ <u>ስለ</u> ያሉ ድሁር ቃላት ከሌሎች ተለይተው መስተዋድድ በሚባለው ንዑስ ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ። መስተዋድድ ማለትም የሚያዋድድ፣ የሚያፋቅር አንደ ማለት ነው። አንዴት አንደሚያዋድድ በሌላ ክፍል አናያለን። አሁን ወደ ሌላ ጉዳይ እንሂድ።

መስተፃምር በመባል የሚታወቅ አንድ ራሱን የቻለ የቃል (የንግግር) ክፍል አንደ ነበር፣ ወደ መጀመሪያው እካባቢ በተሰጠው ዝርዝር ውስጥ ተመልክቶአል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቃላት ግን በቅርፃቸው መስተዋድድ ውስጥ ከሚመደቡት ጋር አንድ ናቸው። ባገባባቸውም ቢሆን ከመስተዋድዶች ብዙ የተለዩ አይደሉም። መስተፃምር የሚለው ለያሜ ራሱ የሚያጣምር፣ የሚያያይዝ አንደ ማለት ስለሆነ፣ የሚያዋድድ ከሚለው ከመስተዋድድ ግላዌ ጋር ተመሳሳይ ነው። ስማንኛውም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) አስቴር [ስለ ገንዘብ] ደንታ የላትም 3
(ለ) ካሳ አስቴር [ስለ ታመመች] በጣም አዘነ

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ስለ</u> የሚለው ቃል የገባው <u>ገንዘብ</u> ከሚለው ስም ቀድሞ ሊሆን፣ በሁስተኛው ምሳሌ ደግሞ <u>ታመመች</u> ከሚለው ግስ በፊት ነው።

ከስም ጋር መግባቱ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ መስተዋድድ ያስኘዋል። ስለ ተንዘብ የሚለውን የአረፍተ ነገሩን ከፍልም መስተዋድዳዊ ሀረግ ያደርገዋል። ይሁን እንጅ፣ ይኸው ቃል በሊቃውንቱ ዘንድ የሚታወቀው መስተፃምር በመባል ነው። መስተፃምር የሚያሰኘው ምክንያት ደግሞ በሁስተኛው ምሳሌ እንደማታየው ከግስ በፊት መግባቱ ብቻ ነው። ከፍ ሲል ስለ መስተዋድድ የተሰጡትን ሌሎች መስፈርቶች ሁሉ ስለሚያሙዋላ ቃሉ መስተዋድድ በሚለው ክፍል ውስጥ ሊገባ ይችል ነበር። አሁንም በዚሁ ክፍል ሊመደብ ስለሚችል መስተፃምር የሚል ከመስተዋድድ የተለየ ከፍል አያስፈልግም ብለን ልናልፈው እንችላለን። አገባቡን በተመለከተ ግን ትንሽ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው።

ከላይ እንደገለፅነው፣ መስተዋድድ የሚባሉት ከስም ጋር የሚገቡት ሲሆኑ፣ መስተፃምር የሚባሉት ከግስ ጋር የሚገቡት ናቸው። ከግስ ጋር የሚገቡትን እንደገና በሚከተሉት ምሳሌዎች አማካኝነት እንያቸው።

(ሀ) ካሳ [ስለ ታመመ] አስቴር አዘነች 4
(ለ) ካሳ [እንደ መጣ] አስቴር ሄደች
(መ) ካሳ [ከሰከረ] አስቴር ትናደዳለች
(ሰ) ካሳ [ሲዜድ] (<ስ-ይ-ዜድ) አስቴር ትደሰታለች

ከምሳሌዎቹ አንደምንመለከተው፣ ስለ፣ እንደ፣ ከ- እና ሰ- እንደ ቅደም ተከተላቸው ታመመ፣ መጣ፣ ሰከረ እና -ይዜድ ከሚሉት ግሶች በፊት ገብተዋል። ተግባራቸውም ግሶቹ የሚገኙበት አረፍተ ነገር፣ ራሱን የቻለ ሳይሆን፣ በልሳ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ነው። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ብንመልከት፣

(ሀ) አስቴር አዘነች 5
(ለ) ካሳ ታመመ

ከሚሉ ሁለት አረፍተ ነገሮች የተዋቀረ እንደሆነ እንረዳለን። አወቃቀሩም ካሳ ታመመ የሚለው፣ አስቴር አዘነች በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ እንደሚከተለው ሆኖ በመግባት ነው።

[አስቴር [ካሳ ታመመ] አዘነች] 6

ካሳ ታመመ የሚለው አረፍተ ነገር አስቴር አዘነች በሚለው ውስጥ ጥገኛ ሆኖ ስመግባቱ ምልክት ያስፈልገዋል። የጥገኝነት መታወቅያ ያስፈልገዋል ማለት ነው። መቸም ጥገኛ ምን ጊዜም ይኸው ነው! ሰውነቱ ብቻ አይበቃውም።

ለዚህ የጥገኝነት ምልክት የሚሆኑት ደግሞ እንደ ስስ ያሉ የትርጉም ሳይሆን፣ የግብር ቃላት ብቻ ናቸው። ጥገኝነትን የማመልከት ተግባር ስላላቸው በጥንት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር በመባል ይታወቃሉ።

ምልክትነታቸው ግን ጥገኛ ስሆነው አረፍተ ነገር ግስ ሳይሆን፣ በጠቅላላ ለጥገኛው አረፍተ ነገር ነው። ጥገኛ የሆነው ሙሉው አረፍተ ነገሩ እንጅ፣ ግሱ ብቻ አይደለምና። በመሆኑም ጥገኛ አረፍተ ነገር እንጅ ጥገኛ ግስ አንልም። በዚህም ምክንያት እንደ <u>ስለ</u> ያሉ ቃላት መዋቅራዊ ግንኙነት በመሰረቱ ጥገኛ ከሆነው፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው። ከአረፍተ ነገሩ ግሱ ጋር አይደለም። ርግጥ፣ በግሀድ የሚታዩት የግሱ አካል ሆነው ነው። ይህ ግን ላይ ላዩን ስናይ ነው። መሰረታዊ ቦታቸውን በሌላ ክፍል እናየዋልን። የአንድ ሰው የጥገኝነት ምልክት በደረቱ ላይ ሊታይ ይችላል። ጥገኛው ግን ሙሉ አካሉ እንጅ ደረቱ ብቻ አይደለም።

ሁኔታው መስተዋድድ የሚባሉት ቃላት በአገባብ ልዩነት መሰረት በሁለት ንዑስ ክፍሎች ሊመደቡ እንደሚችሉ ያሳያል። ይኸውም በእንድ በኩል፣ ከስም ጋር ገብተው መስተዋድዳዊ ሀረግ የሚመሰርቱትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአርፍተ ነገር ጋር ገብተው ጥገኝነትን የሚያሳዩትን በመለየት ነው። ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩትን ብቻ ለይተን <u>ሞይ</u> በሚል ስያሜ እንጠራቸዋለን። ከአረፍተ ነገሩ ጋር ያላቸውን የአወቃቀር ስርዓት በክፍል ሶስት በሰፊው እናየዋለን። እስከዚያው ግን፣ ከስም ጋር የሚዋቀሩት ተራ መስተዋድድ፣ ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት ሞይ መስተዋድድ ይባሳሉ ብለን፣ እንስማማ። ስለ ሞይ መዋቅር ወደፊት በክፍል ሶስት እንወያያልን።

ሌሎች ንዑስ ቃላት ሊባሉ የሚችሉት በቀደምት ሊታውንት ዘንድ ቃለ-አጋኖ በመባል የሚታወቁት ናቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትም እንደ ጎሽ! ዘራፍ! እልል፣ ኡ! ኡ!፣ ዋ! ወዘተ፣ የመሳሰሉት ጨዋሂ ቃላት ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት ድንጋጤን፣ ግራሜን (መገረምን)፣ ቁጣን፣ ወዘተ፣ አጉልቶና ከበድ አድርጎ ለመግለፅ ሊፈልግ የሚገቡ የሰሜት ቃላት ናቸው። የራሳቸው ትርጉም የላቸውም። የሌሎች ቃላትን ትርጉም የማጋነን ተግባር ግን አላቸው። ስለዚህም እንደ መስተዋድዶችና መስተፃምሮች የግብር ቃላት ናቸው። ቅርፃቸውን ስንመለከት፣ መስተዋድድ ካልናቸው ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው እንረዳለን። ይኸውም እንደ መስተዋድዶች ሁሉ ቃለ-አጋኖ የሚባሉትም ምንም አይነት ምዕላድ አያስከትሉም ወይም አያስቀድሙም። ስለዚህም ቅርፃቸውን አይለዋውጡም። ለአዳዲስ ቃላት ምስረታም መሰረት አይሆኑም። በነዚህ ቅርፃዊ ባህሪያታቸው ከመስተዋድዶች ጋር ስለሚመሳሰሉ በመስተዋድድ ክፍል ውስጥ ሊካተቱ ይችሉ ነበር።

አገባባቸውን ስናይ ግን ቃለ-አጋኖዎች ከመስተዋድዶች ጋር ሊመደቡ የማይችሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን። ቀደም ሲል፣ መስተዋድዶች ከስም ወይም ከአረፍተ ነገር ጋር እየገቡ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራትን እንደሚያሳዩ ገልፀናል። ቃለ-አጋኖዎች ከስምም ሆነ ከሌላ ቃል ጋር፣ ከዚያም አልፎ ከማንኛውም ቃል ጋር አይገቡም። ስለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እናስተውል።

(ሀ) <u>ጎሽ</u>! ካሳ መጣ
(ለ) <u>ዋ</u>! አንተ ልጅ ነግሬሀለሁ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>ጎሽ!</u> ሆነ <u>ዋ!</u> በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ከሚገኙት ቃላት ከአንደኛቸውም ጋር አይዋቀሩም። ለምሳሌ፣ <u>ጎሽ!</u> የሚለውን ብንወስድ፣ <u>ካሳ</u> ከሚለው ስምም ሆነ <u>መጣ</u> ከሚለው ግስ ጋር መዋቅራዊ ዝምድና የለውም። ዝምድና ያለው <u>ካሳ መጣ</u> ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ነው። በዚህም ባህሪው ተራ መስተዋድድ ካልናቸው ቃላት ጋር አይመሳሰልም። ምክንያቱም ተራ መስተዋድድ ያልናቸው ቅንጅታቸው ከአረፍተ ነገር ጋር ሳይሆን፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ ከሚገኙ ስሞችና ሀረጎች ጋር ነውና። ሞይ ካልናቸው ጋርም ሊሰለፉ አይችሉም፣ ምክንያቱም ተግባራቸው አንድን አረፍተ ነገር የሌላ አረፍተ ነገር ጥገኛ ማድረግ አይደለም። ተግባራቸው አረፍተ ነገሩ ያዘለውን ሀሳብ ማነልበት ወይም ማኮሰስ ነው።

ቃለ-አጋኖዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የተወሰነ ቦታ የላቸውም። በአረፍተ-ነገር መነሻ፣ መካከል፣ ወይም መድረሻ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ይህ ሊሆን፣ ከላይ የተሰጡት ምሳሌዎች እንደሚከተለው ሊሆኑ ይችላሉ።

(ሀ) ካሳ መጣ <u>ጎሽ!</u> 8
(ለ) እንተ ልጅ <u>ዋ!</u> ነግሬሀለሁ
(መ) እንተ ልጅ ነግሬሀለሁ <u>ዋ!</u>

በዚህ አይነት አንደ ልቡ አገባበን እየቀያየረ የሚገባ መስተዋድድ ወይም ሞይ የለም። ሌሎቹም እንደ ስም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ያሉት ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ከተወሰነ ቃል ጋር ተቀናጅተው በተወሰነ ቦታ የሚገኙ ናቸው። ይህም በመሆኑ በዚህ ቦታ የሚገኙ ወይም የማይገኙ እየተባሉ፣ ከሌሎች ቃላት ተለይተው ሊታወቁ ይችላሉ። በዚህ አይነት ቃለ-አጋኖ የሚባሉትን መለየት ያስቸግራል፤ የትም ዘማች ናቸው።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ቃለ-አጋኖ የሚባሉት ቃላት ቅንጅት ከሌሎች ቃላት ጋር ሳይሆን፣ በአጠቃላይ ከየአረፍተ ነገሩ ጋር ነው። ከአረፍተ ነገር ጋር ግብተው፣ በአረፍተ ነገሩ የተገለፀው ሀሳብ በተናጋሪው ላይ የሚፈጥረውን የደስታ፣ የድንጋጤ፣ የግራሚ፣ ወዘተ፣ ስሜት የጎላ፣ አንዳንድ ጊዜም የኮሰለ መሆኑን ይገልፃሉ። ይህ ሁኔታ ምን ያመለክታል? ሁኔታው ቃለ-አጋኖዎች እንደ ስም፣ ግስ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት በሚመደቡበት ሁኔታ ሊመደቡ የማይችሉ መሆናቸውን ያሳያል። ስርጭታቸው ከቃላት ጋር ቢሆን ኖሮ፣ ከዚህ አይነት ቃል ጋር በዚህ ቦታ የሚገቡ ወይም የማይገቡ እየተባሉ ከዚያ ቃል አቡዋያ ተለይተው ሊመደቡ ይችሉ ነበር። ቅንጅታቸው ከቃል ጋር ሳይሆን፣ ከአረፍተ ነገር ጋር ከሆነ ግን፣ ሊታዩ የሚችሉት በቃል ደረጃ ሳይሆን፣ በዚያው በአረፍተ ነገር ደረጃ ነው። አስተዋፅዋቸው ለአረፍተ ነገሩ መዋቅር ወይም ሀሳብ ሳይሆን፣ የአረፍተ ነገሩ ሀሳብ ለሚፈጥረው ስሜት ነው። አረፍተ ነገሩ ያዘለው ሀሳብ የሚፈጥረው ስሜት መግለጫ ናቸው፤ ለማለት ይቻላል። እንደሚገለፁት

ሰሜት ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት ድምፀታቸው ከፍና ዝቅ ይላል። ርግጥ ቃለ አጋኖ የሚለው ሰያሜ መጋነንን ብቻ እንደሚገለፅ ተደርጎ ተወስዶአል።

ይህ ሰሜት ገላጭነታቸው ሰዋሰዋዊ፣ ማለትም መዋቅራዊ፣ ተግባራት ካላቸው አንደ ሰምና ግሰ ካሉ ቃላት ይለያቸዋል። ሰሞች በአረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትነት ወይም የተሳቢነት፣ ግሶች ደግሞ በግላዊ ሀረግ ውስጥ የአንቀፅነት ተግባር አላቸው። ወደፊት እንደምናየው፣ ባለቤትነት፣ ተሳቢነትና አንቀፅነት ሰዋሰዋዊ ተግባራት ናቸው። ሌሎቹም ቀደም ሲል በየክፍሉ ያየናቸው ቃላት እንደዚሁ ያሉ የተለያዩ ተግባራት አሉዋቸው። ቃለ-አጋኖዎች ግን ሰዋሰዋዊ ተግባር የላቸውም። የእነሱ ተግባር ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሰን ሀሳብ ማጎልበት፣ ወይም ማኮሰስ ነው። ይህን ሲያደርጉም ሰልፋቸው በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ከሚገኝ ከአንድ ወይም ከሌላ ቃል ጋር ሳይሆን፣ የሀሳቡ መግለጫ ከሆነው ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው። ያም ሆኖ የተወሰነ ቦታ የላቸውም። እንደፈለጉ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ለመንሸራሸር ይችላሉ። ይህም ሁኔታ ቃለ-አጋኖ የሚባል ክፍል በቃላት ክፍል ደረጃ መፍጠር አሰፈላጊ አለመሆኑን ያጠናክራል።

የቃለ-አጋኖዎች ባህሪ መታየት ያለበት በአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ የአረፍተ ነገር ጥንቅር በሆነው በንግግር (ዲስኩር) ደረጃ ነው። እንደዚያም ሆኖ ጥናቱ በመዋቅራዊ ባህሪ ላይ ሳይሆን፣ መዋቅሩ በሚፈጥረው ሰሜት ላይ ነው። ይህም ጥናቱን በከፊል ትርጉማዊ ያደርገዋል። ትርጉም ደግሞ አዕምሮአዊ ሰለሆነ፣ ለመዋቅራዊ ሰርዓት ብዙም አይገዛም። በጥቅሉ ቃለ-አጋኖ የመዋቅር ክፍል ቃላት ሰላልሆኑ፣ በሰዋሰው ጥናት ውስጥ ሊታዩ አይገባም። ከታዩም በትርጉምና በአጠቃቀም ደረጃ ነው። አጠቃቀም ደግሞ መዋቅራዊ ብቻ ሳይሆን፣ ማህበራዊና ባህላዊ ስለሆነ፣ በመዋቅር ህግጋት ውስጥ ወግ ባለው መልክ ሊካተት አይችልም። ርግጥ ነው፣ አንዳንድ የቁዋንቁዋ ሰዎች መዋቅርና የመዋቅር አጠቃቀም ተለያይቶ መታየት የለበትም ይላሉ። ወደ ዝርዘሩ እንሂድ።

መስተዓምር

መስተዓምር የሚባሉት ቃላት አንድ ነገር፣ ድርጊት፣ እና ባህሪ ከሌላ ነገር፣ ድርጊት፣ እና ባህሪ ተለይቶ የታወቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚያመለክቱ ንዑስ ቃላት ናቸው። መስተዓምር ማለትም የሚያሳውቅ፣ የሚለይ እንደ ማለት ነው[3]። ሰያሜውን የሚያሳውቀውም በሶስት መንገድ ነው። አንደኛው ነገሩን ከሌሎች ነገሮች ለይቶ፣ ከሚገኝበት ቦታ ወይም ጊዜ አንፃር በመጠቆም ነው። ሁለተኛው ነገሩ የማን አንደሆነ በማገናዘብ ሲሆን፣ ሶስተኛው ነገሩ በመጠን

[3] መስተዓምር የሚለውን ሰያሜ ለመጀመሪ ጊዜ ያስተዋወቁት ባለቅኔው አለማየሁ ሞገስ ናቸው።

ሲተመን ምን ያህል እንደሆነ በመግለፅ ነው። እያንዳንዳቸውን ከዚህ ቀጥሰን እንመለከታለን። በዚሁ መሰረት መሰተዓምሮቹን ጠቁዋሚ፣ አገናዛቢና መጣኝ ብለን ከጥንቱ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንመለከታቸዋልን።


ጠቁዋሚ መሰተዓምር

ጠቁዋሚ መሰተዓምር የሚባሉት ቃላት ከስማዊ ሀረጎች ጋር እየገቡ፣ በሀረጉ ውስጥ የሚገኙት ሰሞች የሚገልፁትን ነገር ከሌሎች ነገሮች ለይተው በመጠቆም የሚያመልክቱ ናቸው። እንደ ሌሎች ንዑሳን ቃላት የራሳቸው የሆነ ትርጉም የላቸውም። በመዋቅር ውስጥ ግን ሰሞች የሚገልፁዋቸውን ነገሮች ከጊዜና ከቦታ አኩዋያ፣ ከሌሎች ነገሮች እየለዩ ይጠቁማሉ። የዚህ ተግባር ያላቸው ቃላት ሁለት አይነት ናቸው። ተራ ጠቁዋሚና ለዩ ጠቁዋሚ ልንላቸው እንችላለን። ተራ ጥቁዋሚ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው[4]።

(ሀ)	ይህ	ይህች	እነዚህ	1
	ያ	ያች	እነዚያ	
	እሱ	እሰዋ	እነሱ	
(ለ)	እኔ	-----	እኛ < እኑ-እኔ (?)	
	እንተ	እንች	እናንተ < እኑ-እንተ	

በ(ሀ) ክፍል ውስጥ የሚታዩት፣ በአንድ በተወሰነ ቦታ ወይም ወቅት ላይ የሚገኝን ነገር ወይም ነገሮች ከሌሎች ለይተን በመጠቆም ለማሳየት ስንፈልግ፣ የምንጠቀምባቸው ጠቁዋሚ መሰተዓምሮች ናቸው። እነዚህም እንደገና የቅርብና የሩቅ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። የቅርብ የሚባሉት ለጠቁዋሚው ሰው ቅርብ የሆኑ ነገሮችን የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ የሩቅ የሚባሉት ደግሞ ከእሱ ርቀው የሚገኙ ነገሮችን የሚጠቁሙ ናቸው። የቅርብ ጠቁዋሚዎች እንደገና በሁለት ይከፈላሉ። ከፍሉቹም ለጠቁዋሚው ለራሱ ቅርብ የሆኑ ነገሮችን የሚጠቁሙና ጥቆማውን ለሚያየው ወይም ለሚያዳምጠው ሰው ቅርብ የሆኑ ነገሮችን የሚያመለክቱ ናቸው። ሁኔታውን እንደሚከተለው በመዋቅር እናሳያለን።

[4] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ባየ (1988)ን ይመልከቱ



ጠቋሚው ለምሳሌ፣ <u>እኔ</u> ብሎ እራሱን ይጠቁምና፣ ከአጠገቡ የሚገኘውን ነገር ይህ፣ ይህች፣ ወዘተ፣ በማለት *ያመለክታል*። ተጠቋሚውን ሰው <u>አንተ</u> ብሎ ይጠራና፣ ከእሱ አጠገቡ ያለውን ነገር እሱ፣ አሰዋ፣ ወዘተ፣ በማለት *ያመለክታል*። ከሁለቱም ርቆ የሚገኝን ነገር ያ፣ ያች፣ ወዘተ፣ ብሎ *ያመለክታል*።

በ(ለ) ክፍል ውስጥ የሚገኙት ጠቋሚዎች ማንኛውንም ነገር ሳይሆን፣ በተለይ ሰውን የሚመለከቱ ናቸው። ስለዚህም *ሰዋዊ* ጠቋሚ ልንላቸው እንችላለን። ተናጋሪን፣ ተነጋሪንና ታዛቢን *ያመለክታሉ*። ተናጋሪው <u>እኔ</u> እያለ ራሱን፣ <u>አንተ</u> እያለ ተነጋሪውን እንዲሁም <u>እሱ</u> እያለ ታዛቢውን ይጠቁማል። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) <u>እኔ ካሳ</u> ማንንም አልፈራም 3
(ለ) አንተ <u>ልጅ</u> ፖሊስ እንዳያስርህ
(መ) <u>እሱ ሰው</u> ጤና የለውም?

እሱ የሚለው ጠቋሚ ለሰው ብቻ የተወሰነ እይደልም፤ ማንኛውንም ነገር ሊጠቁም ይቻላል። ለምሳሌ፣ <u>እሱ ሰው</u> እንዳልን ሁሉ፣ <u>እሱ መፅሀፍ</u> ማለት እንችላለን።

እንደ እኔ፣ አንተና እሱ ያሉት ጠቋሚዎች ከሚጠቁሙት ሰም በፊት እንደገቡ እንጅ ሰሙን እየወከሉ በእሱ ፋንታ እንዳልገቡ እናስተውል። የተጠቁሚዎቹ ምንነት ከእውዱ በሚታወቅበት ጊዜ፣ ተጠቁሚዎቹን ነገሮች የሚገልፁት ሰሞች በግሀድ ላይከሰቱ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ለምሳሌ፣ 3(ሀ) እንደሚከተለው ሆኖ ሊከሰት ይችላል።

እኔ ማንንም አልፈራም 4

ይህ ሲሆን፣ ካሳ የሚለው ስም እኔ በሚለው ጠቁዋሚ ምዕላድ የተተካ ሲመስለን ይችላል። በዚህም ምክንያት ጠቁዋሚዎቹ ተውላጠ ስም እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፅናል። ይህ ሁኔታ የሚከሰተው፣ የቃላቱን አገባብ ጠለቅ አድርገን ሳናይ ሰንቀር ነው። ጠለቅ አድርገን ካየነው፣ የጠቁዋሚዎቹና፣ የተጠቁዋሚዎቹ ስሞች አገባብ ለየቅል መሆኑን ከላይ በተራ ቁጥር (3) ከሚታየው ምሳሌ በግልፅ መረዳት ይቻላል።

መለተዓምሮች እንደሚጠቁሙት ነገር ቅርበትና ርቀት፣ ቁጥርና ፆታ ቅርፃቸውን ይሰዋውጣሉ። ለቁጥር /እንንኧ-/ የሚለውን ምዕላድ ሲያለቅድሙ፣ ለፆታ ደግሞ /-ኢ/ን ወይም /-አ/ን ያለከትላሉ። /-ኢ/ እንስታይ ተጠቁዋሚን፣ /-አ/ እንለታይ ታዛቢን ታመለክታለች። /እንንኧ-/ የሚለው ምዕላድ /-ኦችች/ የሚለው፣ የሰሞች የቁጥር ምዕላድ እቻ ነው። ተግባሩም እንደ /-ኦችች/ ብዙነትን ሳይሆን፣ ጥቂትነትን ማመልከት ነው። በመሰረቱ መለተዓምሮች የሚጠቁሙት መጠነ-ጥቂትና ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ነው። መጠነ-ብዙ የሆነ ነገር ይህ ሁሉ ወይም ያ ሁሉ በግ፣ ለው፣ ወዘተ፣ እየተባለ በጥቅሉ ይጠቆማል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መለተዓምሮቹ የሚያለከትሉዋቸው ቅጣዮች የሚያመለክቱት የተጠቁዋሚውን ነገር ቁጥርና ፆታ ነው። ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን።

በምሳሌ 3(መ) እንደሚታየው፣ መለተዓምሮቹ የገቡበት ቦታ እንደ ትልቅ ያሉ የቅፅል ወገን የሆኑ ቃላት የሚገቡበት ነው፣ ለማለት ይቻል ይሆናል። ለምሳሌ፣ እሱ በሚለው መለተዓምር ፋንታ፣ ከፉ የሚለውን ቅፅል በመተካት ከፉ ሰው ማለት ይቻላል። ከዚህ ያገባብ ተመሳሳይነት የተነሰ መለተዓምሮቹ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ እመልካች ቅፅል በመባል ይታወቃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር (1) እንደሚታየው፣ መለተዓምሮቹ ከመዋቅር ውጭ ብቻቸውን መቆም ይችላሉ። በዚህ ምክንያት እመልካች ተውላጠ ስም ይባላሉ። እመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም የሚያሰኛቸው፣ አብሮአቸው የሚዋቀረው ስም በቦታው በግሀድ መታየት ወይም አለመታየት ነው። ለምሳሌ፣ የሚከተለውን እንመልከት።

(ሀ) [ያቺ ልጅ] ሂደች 5
(ለ) [ያቺ —] ሂደች

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ያቺ የሚለው፣ ልጅ ከሚለው ስም በፊት ስለገባ፣ በሊቃውንቱ እመለካከት እመልካች ቅፅል ነው። በምሳሌ (ለ)፣ ልጅ የሚለው ስም በቦታው ባለመገኘቱ፣ ያቺ የሚለው ጠቁዋሚ፣ ልጅ በሚለው ቦታ የገባ ይመስላል። እንደዚህ ሲመስል፣ ቃሉ እመልካች ተውላጠ ስም ነው። በሁለቱም ምሳሌዎች ያቺ የሚለው ቃል የገባው፣ ልጅ ከሚለው ስም ቀድሞ በራሱ ቦታ እንጅ፣ ልጅ በሚለው ስም ቦታ ስሙን ተክቶ አይደለም። ስለዚህም ተውላጠ ስም ሊሆን አይችልም፤ ሊባልም አይገባም። ስሙን ተክቶ አልገባምና። ስሙን

ግን ሊጠቁም ይችላል። ይህንም የሚያደርገውም በራሱ ቦታ እንደ ጠቁዋሚ ሆኖ ነው።

አመልካች ቅፅል መባሉም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም አገባቡ እንደ ቅፅል በቅፅል ቦታ አይደለም። ላይ ላዩን ሲያዩት ብቻ በቅፅል ቦታ የገባ ይመስላል። ይህም የመመሳሰል ሁኔታ የሚከሰተው ቅፅሉ በቦታው ላይገኝ ሲቀር ነው። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

(ሀ) <u>ያች ጎበዝ</u> ልጅ 6
(ለ) <u>ያች</u> —— ልጅ

ከምሳሌ (ሀ) በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው፣ <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል ቦታ <u>ያች</u> ከሚለው መስተዓምር ቀጥሎ ነው። የሁለቱ ቦታ የቀለያየ ነው፣ ግለት ነው። በምሳሌ (ለ)፣ <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል በቦታው የለም። ለለዚህም <u>ያች</u> የሚለው ቃል በቅፅሉ ቦታ የገባ ይመስላል። ይምሰል እንጅ፣ ቃሉ (ያች) አሁንም የሚገኘው በራሱ ቦታ ነው። የቅፅሉ ቦታ በግልፅ እንደሚታየው፣ በሰረዝ የተመለከተው ነው። በቅፅል ቦታ ለላልገባና ሊገባም ለለማይችል፣ አመልካች ቅፅል ሊባል አይገባውም። ሊባል የሚገባው መስተዓምር ነው፣ አገባቡም ቅፅልን እየቀደመ በሀረግ መነሻ ነው። ይህ መደበኛ የመስተዓምር አገባብ ነው። ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን። አሁን በጠቀስናቸው የአገባብ ልዩነቶች ምክንያት አመልካች ቅፅልም ሆነ አመልካች ተውላጠ ስም የሚባል ክፍል ሊኖር አንደማይገባ ብቻ እንረዳ።

ይህ እንግዲህ ተራ ጠቁዋሚ መስተዓምሮችን በሚመለከት ነው። ሁለተኛው የጠቁዋሚ መስተዓምር አይነት ለዪ የሆኑ ጠቁዋሚ መስተዓምሮች የሚገኙበት ክፍል ነው። ለዪ መስተዓምሮች የሚባሉት ከጥቁም ወይም <u>ዕምር</u> ነገሮች መካከል አንዱን ወይም የተወሰኑትን ብቻ ከሌሎቹ ለይቶ የማመልከት ተግባር ያላቸው መስተዓምሮች ናቸው። እነዚህም በመሰረቱ ከላይ በተራ ቁጥር (1) የተዘረዘሩት መስተዓምሮች ናቸው። ይሁን እንጅ፣ ይህን የለዪነት ተግባር ሊፈፅሙ የተለየ ምዕላድ ያላያሉ። ምዕላዱ /-ኝኝ/ ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ)	ይኸኛው	ይህችኛዋ	እነዚህኞቹ	7
	ያኛው	ያችኛዋ	እነዚያኞቹ	
	እሱኛው	እሰዋኛዋ	እነሱኞቹ	
	አንተኛው	አንችኛዋ	እናንተኞቹ	
(ለ)	ላይኛው	ላይኛዋ	ላይኞቹ	
	ታችኛው	ታችኛዋ	ታችኞቹ	

የቃላት ክፍል

በ(ሀ) ክፍል የሚታዩት እንድን ጥቁም ነገር ከሌሉች ጥቁም ነገሮች በተሰይ ነጥለው የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ በ(ሰ) ክፍል የሚታዩት በበታ አቀማመጣቸው ሳይና ታች ከሆኑ ጥቁም ነገሮች መካከል አንዱን ወይም ሌላውን ብቻ፣ ከሚገኝበት ቦታ አንፃር ለይቶ ለማሳየት የሚገቡ መሰተዓምሮች ናቸው። በሁሉም ውስጥ ይህን ተግባር የሚገልፀው ምዕላድ /-ኝኝአ/ ነው። ነጣይ ምዕላድ ልንለው እንችላለን። እንደ <u>ይዝኛው</u> ያሉ ቃላት ነጣይ ጠቁዋሚ ሊባሉ ይችላሉ። ከምዕላዱ ቱጥሉ በተከታታይ የሚታዩት የቁጥርና የቦታ ምዕላዶች ናቸው። የሚያመለክቱትም የተጠቁዋሚውን ነገር ቦታና ቁጥር ነው። ዝርዝሩን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን።

አገናዛቢ መሰተዓምር

በዚህ ሰር የሚካተቱት እንድ ሰም የሚገልፀውን ነገር ከባሰነገሩ (ባለንብረቱ) አኩዋያ ለይተው የሚጠቁሙ ቃላት ናቸው። እነዚህም በመሰረቱ በጠቁዋሚነት የፊረጅናቸው ተውላጠ ሰሞችና የተፀውያ፣ ማለትም የመጥሪያ ሰሞች ናቸው። አገባባቸውም እንደግንኛውም ጠቁዋሚ፣ ነገሩን የሚገልፀውን ሰም እየቀደሙ ነው። ይሁን እንጅ በስሙና በእነሱ መካከል ያለውን ግንኙነት የገንዘብና የባለገንዘብ መሆኑን ለማመልከት /የ-/ የምትል ምዕላድ ያሰቀድማሉ። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) የእኔ መፅሀፍ 1
(ሰ) የእንተ መፅሀፍ
(መ) የካሳ (የእሱ) መፅሀፍ

ከምሳሌዎቹ እንደምንመለከተው፣ <u>የእኔ</u>፣ <u>የእንተ</u> እና <u>የካሳ</u> (የእሱ) የሚሉት ቃላት <u>መፅሀፍ</u> የሚለውን ሰም ቀድመው በመግባት ስሙን ከባለገንዘብ (ከባለ መፅሀፉ) አኩዋያ ፅውቅ አድርገውታል። በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ <u>መፅሀፍ</u> የሚለው ገንዘብ ሲሆን፣ <u>እኔ</u> የሚለው ደግሞ ባለገንዘብ፣ ማለትም የመፅሀፍ ባለንብረት፣ ነው። /የ-/ ይህን የሁሰቱን ሰሞች የገንዘብና የባለገንዘብ መዋቅራዊ ግንኙነት ሰግመልከት የገባች ምዕላድ ነች። አገባብዋም ባለገንዘቡን ከሚያመለክተው፣ <u>እኔ</u> ከሚለው መሰተዓምር ጋር ነው። እለዋ ከሌለች <u>እኔ</u> በሚለውና <u>መፅሀፍ</u> በሚለው ሰም መካከል ያለው ግንኙነት የገንዘብና የባለገንዘብ መሆኑ አይታወቅም።

ከዚህ ሳይ እንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም የመሰተዓምሮቹንና ገንዘቡን የሚያመለክተውን ሰም ግንኙነት የሚመለከት ነው። ሰምሳሌ፣ ከላይ ከምሳሌ (መ) እንደሚታየው፣ የካሳ ወይም <u>የእሱ መፅሀፉ</u> ሰንል፣ የመፅሀፉ ባለቤት (ባለንብረት)፣ በርግጥ <u>እሱ</u> የሚለው ጠቁዋሚ ቃል ነው ወይ፣ የሚል ነው። መልሳቸን፣ በርግጥስ አይደለም ነው። ለዚህም ምክንያቱ፣ እሱ የሚለው ቃል ከፍ ሲል እንደተገለፀው መሰተዓምር መሆኑ ነው። በመሰረቱ የእሱ መፅሀፍ ስንል፣ <u>የእሱ</u>

ሰው መፅሀፍ ግለታችን ነው። ባለገንዘቡ የእሱ ሰው የሚለው ሀረግ ነው። በዚህ ውስጥ እሱ የሚለው፣ ሰው ለሚለው ስም ጠቁዋሚ መስተዓምር አንጅ መፅሀፍ ለሚለው ስም አይደለም። ባለገንዘቡ ተጠቁዋሚ ስም ሰው ነው። ባለገንዘብ መሆኑን የምታመለክተው ምዕላድ ደግሞ /የ-/ ነች። ይህ ለመሆኑ ምልክቱ ጠቁዋሚ ሰሌለበት ጊዜ፣ /የ-/ ከሰሙ በፊት መገኘትዋ ነው። ይህም የሰው መፅሀፍ ሰንል ነው። ባለገንዘቡን የሚያመለክተው ስም በሚገደፍበት ጊዜ፣ /የ-/ የመስተዓምሩ ክፍል መሰላ ትታያለች። ይህም የእሱ ሰንል ነው። ሰሙ ሰለተገደፈ የእሱ የሚለው ምትክ ሆኖ የገባ ሊመስል ይችላል። ሰለሚመስልም እገናዛቢ ተውላጠ ስም ይባል እንደነበር ቀደም ሲል ተገልያለል።

መጣኝ መስተዓምር

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚመደቡት በቀደምት ሊቃውንት የአህዝ ቅፅል በመባል የሚታወቁት ቃላት ናቸው። ተግባራቸው ከተለያዩ ሀረጎች ጋር እየገቡ፣ ሀርጥ የሚጠቁመውን ነገር አህዛዊ መጠን መጠቆም ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) አንድ ልጅ 1
(ለ) አንዳንድ ልጆች
(መ) ብዙ ልጆች
(ሰ) ጥቂት ልጆች

በምሳሌዎቹ ውስጥ አንድ፣ አንዳንድ፣ ብዙና ጥቂት የሚሉት ቃላት ሰው ወይም ሰዎች የሚለው ስም የሚጠቁመው መጠን ሰንት እንደሆነ ይገልፃሉ። መጣኝ የተባሉትም በዚህ ተግባራቸው ምክንያትም ነው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት፣ በቅፅል ክፍል ውስጥ ከተመደቡ፣ እንደ ጎበዝ ካሉት ቃላት ጋር በምን ይለያሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በርግጥም የሁሉም ባይሆን፣ የአንዳንዶቹ አገባብ ቅፅል ካልናቸው ቃላት አገባብ ጋር ተመሳሳይ ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ አይነተኛ የቅፅሎች አገባብ ሰምን ቀድሞ በጣም የሚለውን ቃል ተከትሎ መምጣት ነው። ይህም በሚከተለው ምሳሌ እንደሚታየው ነው።

(ሀ) በጣም ጎበዝ ልጅ 2
(ለ) በጣም ብዙ ልጆች
(መ) በጣም ጥቂት ልጆች
(ረ) *በጣም አንድ ልጅ
(ሰ) *በጣም አንዳንድ ልጆች

በምሳሌዎቹ ውስጥ ብዙ፣ ጥቂት፣ አንድና አንዳንድ የሚሉት ቃላት የገቡት በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ጎበዝ የሚለው ቅፅል በገባበት ቦታ ነው። ይሁን እንጅ፣

ምሳሌ(ለ) እና (መ) ተቀባይነት ሲኖራቸው፣ ምሳሌ (ረ) እና ምሳሌ (ሰ) ግን ተቀባይነት የላቸውም። ይህም የሚያሳየው ብዙና ጥቂት የሚሉት ቃላት ከቅፅል ጋር የአገባብ አንድነት የላቸው መሆኑንና፣ አንድ እና አንዳንድ የሚሉት ግን ከቅፅሎች ጋር የአገባብ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ነው። ለለዚህም ብዙና ጥቂት ብቻ ቅፅል ሊባሉ ይችላሉ፣ ለግለት አንችላለን። ሆኖም ግን ብዙና ጥቂት እንደ አንድና አንዳንድ የነገሮችን አህዛዊ መጠን ገላጭ በመሆናቸው፣ የነገሮችን አካላዊ መጠን፣ ለምሳሌ ውፍረትን፣ ወይም ባህሪን፣ ለምሳሌ ደግነትን፣ እንዲሁም አይነትን፣ ለምሳሌ ጥቁረትን፣ ከሚገልፁት እንደ ወፍራም፣ ደግ፣ እና ጥቁር ከመሳሰሉ ቅፅሎች የተለዩ ናቸው። ይህ ከትርጉም አኳር ነው። ሁለተኛም እንደ ብዙና ጥቂት ያሉ ምፅላዶች ከሌሎች ቅፅሎች የሚለዩበት ሌላ እገባባዊ ባህሪ አላቸው። ይኸውም እንደ ሌሎቹ ቅፅሎች ከሰም ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከግስም ሆነ ከሌሎች ቅፅሎች ጋር ሊገቡ መቻላቸው ነው። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ጥቂት አጠቆርኩው 3
(ለ) ብዙ ወፍራም አይደለም

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ጥቂት የሚለው ቃል የገባው ከግስ ጋር ሲሆን፣ በሁለተኛው ደግሞ ብዙ የሚለው የገባው ከቅፅል ጋር ነው። ሁለቱም የሚገልፁት የጥቁረትንና የውፍረትን መጠን ነው። ለለዚህም የነገሮችን መጠን ከሚጠቁሙት ከአህዞች ጋር መመደባቸው ተገቢ ነው።

ከፍ ሲል የተመልከትነው ከስማዊ ፅረጎች ጋር ብቻ የሚገቡትን መጣኝ መሰተዓምሮች ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ከግሳዊና ከቅፅላዊ ሀረጋት ጋር የሚገቡም ስላሉ፣ እነሱን በሚከተሉት ምሳሌዎች አግካኝነት እንመለከታለን።

(ሀ) በጣም ትሁት 4
(ለ) በጣም ሰከረ

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ በጣም የሚለው ቃል ትሁት ከሚለው ቅፅል በፊት ገብቶአል። ተግባሩም ቅፅሉ የሚገልፀውን ባህሪ መጠን መግለፅ ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ቃል ሰከረ ከሚለው ግሰ ጋር ገብቶ ግሱ የሚገልፀውን የመስከር ሁኔታ ወይም የስካር ደረጃ ያመለክታል። ከዚህም በመነሳት በጣም የሚለው ቃል እንደ ብዙና ጥቂት ካሉት መጣኝ መስተዓምሮች ጋር ሊመደብ ይችላል። አገባቡ ግን ከግሶችና ከቅፅሎች ጋር ብቻ የተወሰነ ነው። ለለዚህም በጣም ትሁት ማለት ሲቻል፣ በጣም ሰው ማለት አይቻልም።

በአንፃሩ ደግሞ እንደ አንድ ያሉ አህዛዊ መጣኞች ከሰም ጋር እንጅ ከግስም ሆነ ከቅፅል ጋር አይገቡም ለለዚህም፣

(ሀ) *እንድ ትሁት 5
(ለ) *እንድ ሰከረ

ግለት አይቻልም። ሁኔታው የመጣኝ መስተዓምሮች አገባብ እንደየቃላት ክፍሉ እንደሚለያይ ያመለክታል። እለያየቱን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስማዊ ግሳዊ ቅፅላዊ 6

{እንድ, አንዳንድ, ብዙ, ጥቂት} ሰው {ብዙ, ጥቂት, በጣም} ወፈረ {ብዙ, ጥቂት, በጣም} ወፍራም

በግልፅ እንደሚታየው ከግሶችና ከቅፅሎች ጋር የሚገቡት መጣኝ ምዕላዶች እንድ እይነት ናቸው። ስለዚህም ምዕላዶቹን ስማዊና ግሳዊ ብሎ በሁለት ብቻ በመክፈል የመስተዓምሮቹን አገባብ እንደሚከተለው እጠቃሎ ማሳየት ይቻላል።

ስማዊ	ግሳዊ	7
አንድ	ብዙ[5]	
አንዳንድ	ጥቂት	
ብዙ	በጣም	
ጥቂት		

ቀደም ሲል አራቱ የቃላት ክፍሎች ገላጭና ተገላጭ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉና ተገላጮቹም የስምና የግስ ክፍል ቃላት እንደሆኑ ገልፀን ነበር። ያ እከፋፈል ከመስተዓምር አገባብ አኳያም ትክክለኛ መሆኑን ከዚህ ላይ መረዳት ይቻላል።

በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። መጀመሪያ የምዕላድንና የቃልን ምንነት፣ እንዲሁም እንድነትና ልዩነት ለማየት ሞክርን። ምዕላድ ትርጉም-አዘል የፎኒም ቅንጅት እንደሆነ፣ ወደ ንዑስ ትርጉም-አዘል ቅንጅቶች ሊከፈል እንደማይችልና በአቁዋሙም ነፃ ወይም ጥገኛ ሊሆን እንደሚችል ገልፀናል። ቃል የምዕላዶች ቅንጅት እንደሆነና ቁዋንቁዋም የቃላትና የምዕላድ ክምችት እንደሆነ ጠቁመናል። ከዚያም የእግርኛን ቃላት የይዘትና የግብር ብለን በሁለት ከፈልናቸው። የይዘት ቃላት

[5] ከዚህ ላይ አማርኛና ሌሎቹም የሀገራችን ቁዋንቁዋዎች ብዙ እና ጥቂት የሚሉትን የመጠን ቃላት ለሚቆጠሩም ሆነ ለማይቆጠሩ ነገሮች እንደሚጠቀሙ መረዳት አለፈላጊ ነው። እንደ እንግሊዝኛ ባሉ ቁዋንቁዋዎች many and much, few and little እየተላሉ የሚቆጠሩት ከማይቆጠሩት ይለያሉ። በከላይ በግላዊው ከፍል የሚታዩት ብዙ እና ጥቂት የሚሉት few and little የሚሉት እቻ ናቸው።

የሚባሉት ትርጉም ያላቸው ሊሆኑ፣ የግብር የሚባሉት ትርጉም ሳይሆን፣ መዋቅራዊ ተግባር ያላቸው ናቸው።


የይዘት ቃላት የሚባሉትን በቅርፅና በአገባብ ባህሪያቸው መሰረት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መደብናቸው። እነሱም ስም፣ ቅፅል፣ ግሰና ተውላከ ግስ ናቸው። ከነዚህ መካከል ተውላከ ግስ የሚባለው ክፍል በርካታ ቃላት እንደሌሉትና ተውላከ ግሳዊ ተግባራትን ለመግለፅ ሀረጎችንና ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን እንደሚጠቀም አየን። ከነዚህ ከአራቱ ክፍሎች ውጭ የሚገኙትን ቃላት በሙሉ ንዑስ ቃላት ብለን ከሞናዎቹ ክፍሎች ለየናቸው። በዚህ ክፍል የሚካተቱት ቀደም ሲል የግብር ቃላት ብለን ከይዘት ቃላት የለየናቸው ናቸው።

እነዚህንም በመዋቅራዊ ባህሪያቸው መሰረት መስተዋድድና መስተዓምር ብለን በሁለት ከፈልናቸው። መስተዋድድ የሚባለው ክፍል መስተዓምር ይባሉ የነበሩትን ሊያጠቃልል እንደሚችል አየን። መስተዋድድ የሚባሉት ከሰማዊ ሀረጎች ጋር የሚዋቀሩት ሲሆኑ፣ መስተዓምር የሚባሉት ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት ናቸው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ቃለ አጋኖ ይባሉ የነበሩት በቃል ሳይሆን በሀረግና በአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ በአጠቃቀም ደረጃ መታየት ያለባቸው እንደሆኑ አሳየን። ተግባራቸው ሰዋሰዋዊ ተግባርን ሳይሆን ቅፀበታዊ ስሜትን አያጎሉ ወይም አያኮሰሱ መግለፅ እንደሆነም ገልፀናል። ስሜት ደግሞ ለአዕምሮአዊ ትርጉም አንጅ ለመዋቅራዊ ሰርዓት ስለማይገዛ፣ በመዋቅር ደረጃ መታየት እንደሌለበት ገለፅን።

መስተዓምር የሚባለው ክፍል በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ምድብ ተውላጠ ስም፣ አመልካች ቅፅልና አመልካች ተውላጠ ስም ይባሉ የነበሩትን ያጠቃልላል። መስተዓምር የሚባሉት ከአገባብ ባህሪያቸው አኩዋያ ጠቁዋሚ፣ አጎናፃቢና መጣኝ ተብለው በሶስት ሊከፈሉ እንደሚችሉ አየን። ጠቁዋሚዎቹ ተራ ጠቁዋሚና ለዩ ጠቁዋሚ ተብለው እንደገና ሊልዩ እንደሚችሉም ተረድተናል። በዚህም የአማርኛ ቃላት በአራት የይዘትና በሁለት የግብር ክፍሎች ብቻ እንደሚከፈሉ አይተናል።

በአጠቃላይ በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኙትን ቃላት የሰዋሰውና የአጠቃቀም ብሎ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል። የሰዋስው የሚባሉት እስካሁን ያየናቸው ናቸው። የአጠቃቀም የሚባሉት በማንኛውም የቃል ክፍል ሊመደቡ የማይችሉት ናቸው። እነዚህ የሚገኙት በንግግር (ዲስኩር) እና በድርሰት ውስጥ ነው። የሰዋስው የሚባሉት በተራ ወይም በውስብስብ አረፍተ ነገር ደረጃ የሚገኙትና ከተለየ አውድ ጋር ቁርኝት የሌላቸው ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን የትርጉምና የግብር ብሎ በሁለት መለየት ይቻላል። የትረጉም የሚባሉት በአራቱ ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉት ናቸው። የግብር የሚባሉት በመስተዋድድና በመስተዓምር ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው። የትረጉም (ይዘት) የሚባሉት አራቱ ክፍሎች የገላጭና የተገላጭ ወገን ተብለው በሁለት ብቻ ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ አይተናል። በዚህ መሰረት አጠቃላዩን የቁዋንቁዋውን ቃላት እንደሚከተለው እናሳያለን።

የቃላት ክፍል



ከዘህ ላይ አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህም የግብር ቃላት ሲባል፣ ሁሉም የዚህ ክፍል ቃላት ይዘት የላቸውም ማለት አለመሆኑን ነው። እንደ ስሞችና ግሶች በቀጥታ የሚገልፁት ነገር ወይም ድርጊት የላቸውም ለማለት እንጅ፣ በጥቅሉ ትረጉም-አልባ ናቸው ለማለት አይደለም። በአረፍተ ነገር ውስጥ የይዘት ቃላትን ሲያገናኙ የሚሰጡት የተለያየ ትረጉም አለ። ይህን ወደፊት እንመለከተዋለን። ስለዚህ የሚከተለውን መልመጃ በውይይታችን መሰረት እንዲሞክሩት እየጋበዝን፣ ወደሚቀጥለው ክፍል እንሄዳለን።

መልመጃ

1. በቃላትና በምዕላድ መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ።

2. ፎኒማዊ ቃላት ከስነ-ምዕላዳዊ ቃላት እንዴት እንደሚለዩ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

የቃላት ክፍል

3. /-ህ/ እና /-ሽ/ የሚሉትን መደብ አመልካች ቅጣዮች የሚያሰከትል ቃል ሁሉ ግሰ ነው ለማለት የማይቻለው ለምንድን ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

4. /-አችች/ የሚለውን የቁጥር ምዕላድ የሚያሰከትል ቃል ሁሉ ሰም ነው ለማለት አይቻልም። ለምን?

5. <u>ሞት</u> ብለን <u>ሞቶች</u> አንልም፣ <u>ገደለ</u> ብለንም <u>ገደሎች</u> አንልም። ይህ ውነት ከሆነ፣ <u>ሞት</u>ና <u>ገደለ</u> የአንድ ክፍል ቃላት ናቸው ለማለት ይቻላል? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

6. <u>በጣም</u> ከሚለው ምዕላድ ቀጥሎ የሚገባ ቃል ሁሉ ቅፅል ነው ለማለት የማንችለው ለምንድን ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

7. <u>ገጠመኝ</u>፣ <u>አራዳ</u> ፣ <u>አይነ-ደረቅ</u> እና <u>እባከሽ</u> የሚሉትን ቃላት ክፍል ይግለፁ።

8. የሚከተሉትን ምሳሌዎች ይመልከቱ።
   (ሀ) <u>አንኩዋን</u> መጣህ
   (ለ) <u>አንኩዋን</u> አንተ ግንም ይሰራዋል
   (መ) <u>አንኩዋን</u> ሰገንፎ ለሌላም አልጉዋጉዋ

   <u>አንኩዋን</u> የሚለው ቃል ክፍል ምንድን ነው?

9. በሰነ-ቃላት፣ በምዝገባ-ቃላትና በክፈለ-ቃላት መካከል የሚታየውን አንደነትና ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ።

10. በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚገባ ቃል ሁሉ ግሰ ነው የሚለውን ድንጋጌ ከሚከተሉት ምሳሌዎች አንፃር ይገምግሙ።

    (ሀ) ካሳ መጣ እንዴ?
    (ለ) ካሳ መጥቶአል እኮ!
    (መ) ካሳ መጣ።

ርባታ

ባለፈው ንዑስ ክፍል እንዳየነው የአማርኛ ቃላት በአራት ዋና ዋና እና በሁለት ንዑስ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ይህ አከፋፈል በቃላቱ ቅርፅና አጣብቂ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ የቃላቱን ይዘት ግንዛቤ ውስጥ ብናስገባ፣ ምናልባት በሁለት ብቻ መከፈል ይቻል እንደነበር ገልፀናል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል ይዘት ያላቸው፣ በሌላ በኩል ይዘት የሌላቸው ቃላት በማለት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ ክፍል ውስጥ ስምናያቸው ጉዳዮች ቀና መንገድ ይከፍትልናል፡፡ ወደ ከፍፍሉ ከመሄዳችን በፊት ግን ይዘት ሰንል ምን ማለታችን እንደሆነ ለመነሻ የሚሆን ሀሳብ እንሰጥ፡፡

ይዘት የአንድ ቃል ትርጉም ወይም ፍች ነው፡፡ አንድን ቃል በተናጠል፣ ወይም ከሌሎች ቃላት ጋር በህብረት፣ በመዋቅር ውስጥ ሳገኘነው ጊዜ፣ በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥረው ሰሜት ወይም ምስል የቃሉ ይዘት ወይም ፍች ነው፣ ስማለት እንችላለን፡፡ ስምሳሌ፣ <u>አንበሳ</u> የሚለውን ቃል ሰንሰማ፣ በአዕምሮአችን ውስጥ አንድ የአራዊት ወገን የሆነ አሰፈሪ ፍጡር ይታየናል፡፡ ያ አዕምሮአዊ ምስል የቃሉ ፍቺ ወይም ይዘት ነው፡፡ አንደ አንበሳ ያሉ ሰሜት ወይም ምስል በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥሩ ቃላት፣ በምንስማቸው ጊዜ ሰሜት ወይም ምስል ከማይፈጥሩ ሌሎች ቃላት ተለይተው ሊጠኑ ይችላሉ፡፡ ስምሳሌ፣ <u>እንደ</u> የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ ቃሉን ሰንሰማ፣ <u>አንበሳ</u> እንደሚለው ቃል በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥረው አንዳችም ምስል ወይም ሰሜት የለም፡፡ በአጠቃላይ ግን ቃሉ እንደ <u>አንበሳ</u> ካሉ ባለይዘት ቃላት ጋር እየገባ በመዋቅር ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለሚያጋጥመን፣ ከዚያ ገጠመኝ የሚመነጭ፣ ግን ደግሞ ይህ ነው ስማለት የሚያስቸግር፣ ደብዘዝ የሆነ ሰሜት ሊሰጠን ይችላል፡፡ ይህ ሰሜት ግን ከቃሉ ከራሱ የመነጨ ሳይሆን፣ ይዘት ካላቸው ሌሎች ቃላት ጋር ገብቶ ከፈጠረው መዋቅራዊ ዝምድና የሚመጣ ነው፡፡ ለምሳሌ፣

እንደ አንበሳ 1

ብንል፣ <u>እንደ</u> የሚለው ቃል የንፅፅር ተግባርን የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ካሳ <u>እንደ</u> አንበሳ ደፋር ነው 2

ብንል፣ የካሳንና የአንበሳን የድፍረት ተመሳሳይነት መግለፃችን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን <u>እንደ</u> የሚለው ቃል በራሱ በአዕምሮአችን ውስጥ የሚያሳየን ምስል ወይም የሚፈጥርልን ሰሜት የለም፡፡ ስለዚህም የዚህ አይነት ቃላት ሰሜት ከማሰጡ ወይም ምስል ከሚፈጥሩ እንደ <u>አንበሳ</u> ካሉ ሌሎች ቃላት ይለያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከፍ ሲል እንደጠቀስነው፣ በቁዋንቁዋው ውስጥ ያሉትን ቃላት

ይዘት ያላቸውና የሌላቸው ብሎ በሁለት መከፈል እንደሚቻል ባለፈው ክፍል አይትናል። በዚያ ክፍል እንዳየነው፣ የቃላት ክፍሎች በዚህ ረገድ እንደሚከተለው ሆነው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።

3

(ሀ) ስሞች
ግሶች
ቅፅሎች
ተውላከ ግሶች

(ለ) መስተዋድዶች
መስተዓምሮች

በ(ሀ) ውስጥ ቦሚታዩት ክፍሎች የሚመደቡ ቃላት ሰንሰማቸው በአዕምሮአችን ውስጥ ስሜት ወይም ምስል ሲፈጥሩ የሚችሉ ናቸው። በ(ለ) ውስጥ የሚታዩት ደግሞ ይህን ማድረግ የማይችሉ ይዘት-የለሽ ቃላት ናቸው። ይዘት-የለሽ ይሁኑ እንጅ፣ ግብር-የለሽ አይደሉም። ከፍ ሲል እንዳሳየነው፣ እንደ ንፅፅር ያለ ሰዋሰዋዊ ተግባር አላቸው።

በሁለቱ ክፍሎች መካከል የባህሪ ልዩነት አለ። ይኸውም ይዘት ያላቸው ቃላት ቅርፃቸውን በከፈል መለዋወጥ ሊችሉ፣ ከተወሰኑ ተውላጠ ስሞች በስተቀር፣ ሌሎች ይዘት የሌላቸው ቃላት ይህን ማድረግ አይችሉም። ለምሳሌ እንደ <u>እንበሳ</u> ያለ የይዘት ቃል፣

4

እንበሳ - ው
እንበሳ - ው -ን
እንበሳ - የ
እንበሳ - እች
ወዘተ -

እያለ፣ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር ቅርፁን በከፈል ይለዋውጣል። እንደ <u>እንደ</u> ያለ ይዘት-የለሽ ቃል ግን ይህን ማድረግ አይችልም። ሰለዚህም ቅርፁ ሁል ጊዜ አንድ አይነት ነው።

ይዘት ያላቸው ቃላት ለአዳዲስ ቃላት ምስረታ መሰረት ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ <u>እንበሳ</u> ከሚለው ቃል ላይ <u>እንበሳነት</u> የሚል ሌላ ቃል መመስረት ሲቻል፣ <u>እንደ</u> ከሚለው ላይ ግን በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ ቃል መመስረት አይቻልም። በዚህም መሰረት እንደ <u>እንበሳ</u> ያሉትን <u>ረቢ</u>፣ እንደ <u>እንደ</u> ያሉትን መሀን ቃላት ብሎ አንዱን ወገን ከሌላው መለየት ይቻላል።

ይህን ልዩነት መነሻ በማድረግ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ረቢ ቃላትን ብቻ እንመረምራለን። እነዚህም ከላይ በክፍል (ሀ) ውስጥ የተመደቡት ሲሆኑ፣ የምንመረምረው ደግሞ የአረባብ ስርዓታቸውን ነው። ስርዓታቸውን የምናየውም ከሰዋሰዋዊ ተግባራት አኩዋያ ነው። ሰዋሰዋዊ ተግባራት የሚባሉት በሁለት ይከፈላሉ። እከፋፈሉ በነገሮችና በድርጊቶች ባህሪ ላይ የተመሰረተ ነው። ነገሮች በመደብ ሊከፈሉ፣ በአህዝ ሊቆጠሩ፣ በፆታና በሙያ ሊለዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

ርባታ

አንድ ሰው ለአንድ ሌላ ሰው ስለ አንበሳ የሚያወራበትን አውድ ብናስብ፣ ተናጋሪው እኔ አያስ ስለሚያወራ አንደኛ (መደብ) ሰው ይባላል። ተናጋሪ ሰው እንደግስት ነው። ወሬውን የሚሰማው ሁስተኛ (መደብ) ሰው ሲባል፣ የወሬው ርዕስ የሆነው አንበሳ ደግሞ ሶስተኛ (መደብ) ይባላል። የንግግሩ ርዕስ የሆነው አንበሳ በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ በላይ፣ ሰዶታውም ሓንሳታይ ወይም ተባዕ ታይ ሊሆን ይችላል። አንዲሁም በተግባሩ ነካሽ ወይም ተነካሽ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ስሞች ብሰን በስም ክፍል ውስጥ የምንመድባቸው ቃላት አይነተኛ ባህሪያት ናቸው። ስለዚህም ስማዊ ባህሪያት ልንላቸው እንችላለን። ይሁን እንጅ፣ የእነሱ ገላጭ ወይም ጠቁዋሚ በሆኑ ቃላት ላይም ሊከሰቱ ይችላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ድርጊቶችን የሚያመለክቱ ብለን በግስ ክፍል ውስጥ የምንመድባቸው ቃላት አሉ። እነዚህም አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ወይም የሚፈፀምበትን ጊዜ፣ የድርጊቱን ፈፃሚ አካል መደብ፣ ቁጥርና ፆታ፣ የድርጊቱን አይነት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ስምላሌ አንበሳ የመገደልን ድርጊት ብናስብ፣ የጎደዩ ሰው መደብ፣ ቁጥር፣ ፆታ አንዲሁም ግድያው የተፈፀመበት ጊዜ ይጠቀሳል። ጊዜው፣ ያለፈ ወይም ገና ያላለፈ ሊሆን ይችላል። በባህሪውም ተፈፅሞ ያለቀ ወይም በመፈፀም ላይ የሚኖ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ባህሪያት በምዕላድ መልክ በግስ ላይ ስለሚከሰቱ፣ ግሳዊ ባህሪያት ተብለው ከስማዊ ባህሪያት ይለያሉ።

አንግዲህ የይዘት ቃላት ቅርፃቸውን በክፈል ይለዋውጣሉ ስንል፣ ከዚህ በላይ ስለብነት ያህል የጠቀስናቸውን ግሳዊና ስማዊ ባህሪያትን ስማሳየት የሚያደርጉትን የቅርፅ ለውጥ አያስብን ነው። ዝርዝር ሁኔታውን ከዚህ ቀጥለን በስሞች በመጀመር እናሳያለን።

ስም

በስም ክፍል ውስጥ የሚመደቡ የአማርኛ ቃላት ቁጥርን፣ ፆታን፣ ሞያንና ዕምርነትን ስማሳየት ልዩ ልዩ ቅጣዮችን በማስከተል ቅርፃቸውን በክፈል ይለዋውጣሉ። ዝርዝሩን በቁጥር በመጀመር ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ቁጥር

ቁጥር በአንድ ስም የሚጠቀሰን ነገር ምን ያህልነት ወይም ስንትነት የሚገልፅ ሰዋሰዋዊ ባህሪ ነው። አንድ ስም የሚገልፀው ነገር አህዛዊ መጠን አንድ፣ ሁለት፣ ጥቂት፣ ብዙ ወይም ከመጠን፣ ማለትም ከቁጥር በላይ ሊሆን ይችላል። ቁጥሩ አንድ ብቻ የሆነን ነገር የሚጠቁም ስም የነጠላ ቁጥር ስም ይባላል። መጠኑ ብዙ የሆነን ነገር የሚጠቁም ስም፣ የብዙ ቁጥር ስም ይባላል። በዚህ አይነት ቁጥርን ስጥቅሱ ነጠላና ብዙ ብለን በሁለት ብቻ እንከፍለዋለን።

ስሞችንም እንደዚሁ እንደሚያመልክቱት የቁጥር አይነት ነጠላ ወይም ብዙ ብለን እንለያያቸዋለን።

ነጠላ ስሞች ነጠላነትን የሚያመለክቱበት ምንም የተለየ ምልክት የላቸውም። ልጅ፣ በግ፣ ሰው፣ ወፅተ፣ የነጠላ ስሞች ምሳሌ ናቸው። ይሁኑ እንጅ፣ ነጠላነታቸውን የሚያመለክት ምዕላድ የላቸውም። አንዳንድ ስሞች ግን *ንጥልነትን* ወይም ልዩነትን የሚያመለክቱበት ምዕላድ አላቸው። ምዕላዱም /እይይኦ-/ ነው። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

1

ነጠላ	ንጥል
ባል	ባል-እየ-
ሚስት	ሚስት-እየ-
ወንድም	ወንድም-እየ-
እህት	እህት-እየ-
እናት	እናት-እየ-
አባት	አባት-እየ-

በነጠላ ስር የሚታዩት ተራ ነጠላ ነገርን ብቻ የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ በንጥል ስር ያሉት ግን ተራ ነጠላነትን ሳይሆን፣ የተለየ ነጠላነትን ወይም ንጥልነትን የሚያመለክቱ ናቸው። አንድ ነገርን ብቻ ሳይሆን፣ አንድ የተለየና የታወቀ ነገርን ይጠቁማሉ። እንደነዚህ ያሉ ስሞች አንድ ከሌሎች ተለይቶና ተነጥሎ የሚታወቅ ነገርን ስለሚጠቁሙ ንጥል ስሞች ይባላሉ።

ንጥልነት የማንኛውም ስም ባህሪ አይደለም። *ሰበ-ነክ* የሆኑና በተለይ ደግሞ ቤተዘመድን የሚያመለክቱ ስሞች ልዩ ባህሪ ነው። ከዚህ ውጭ የሆኑ ስሞች ይህ ባህሪ የላቸውም። ስለዚህም ወንድም-እየ፣ እህት-እየ (እትየ) ማለት እንደሚቻል ሁሉ፣ በግ-እየ፣ ፍየል-እየ ማለት አይቻልም[1]።

ሌላው የንጥል ስሞች ባህሪ ከመስተዓምር ምዕላዶች ጋር መቆራኘታቸው ነው። ያለመስተዓምር ብቻቸውን ሊቆሙ አይችሉም። ለዚህ ምክንያቱ በባህሪያቸው ከሌሎች ነገሮች ተለይተው፣ ማለትም ተነጥለው፣ የሚታወቁ ነገሮችን ስለሚያመለክቱ ነው። ስለዚህም ለንጥልነቱ /እይይኦ-/ን ለዕምርነቱ (ለዕውቅነቱ) ደግሞ መስተዓምርን ያስከትላል። ይህ ሲሆን፣ ከላይ የተዘረዘሩት ንጥል ስሞች የመስተዓምሩን ምዕላድ /-ው/ ወይም /-ዋ/ን ያስከትላሉ። ዝርዝሩን ወደፊት ስለ ዕምርነት ስንወያይ እናየዋለን። ለጊዜው ከላይ የጠቀስናቸውን ስሞች ብቻ እንመለከታለን።

2

ነጠላ	ንጥል	ዕምር	
ባል	ባል-እየ-	ባል-እየ-ው	ባልዮው
ሚስት	ሚስት-እየ-	ሚስት-እየ-ዋ	ሚስትዮዋ
እህት	እህት-እየ-	እህት-እየ-ዋ	እህትዮዋ

ርባታ

ነጠላ ወይም ንጥል ነገርን ሳይሆን[1] በርካታ ነገሮችን የሚያመለክቱ ስሞች የብዙ ቁጥር ስሞች ይባላሉ። መለያቸው ቀደም ሲል ስንጠቅሰው የነበረው /-ኦች/ የሚለው ምዕላድ ነው። ይህን ከሚከተለው መዘርዝር መመልከት ይቻላል።

ነጠላ	ብዙ	3
በግ	በጎ-ኦች	በጎች
ዛፍ	ዛፍ-ኦች	ዛፎች
ላም	ላም-ኦች	ላሞች
ወፍ	ወፍ-ኦች	ወፎች
ቤት	ቤት-ኦች	ቤቶች

ከግዕዝ የተወረሱ ስሞች አንዳንድ ጊዜ በግዕዙ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአማርኛው ስርዓት መሰረት የብዙ ቁጥርን ያሳያሉ። የሚከተሉት የእነዚህ አይነት ስሞች ምሳሌ ናቸው።

ስም	ግዕዝ	አማርኛ	4
ካህን	ካህን-ኣት	ካህን-ኦች	
ሊቅ	ሊቅ-ኣውንት	ሊቅ-ኦች	
መኩንን	መኳንን-ት	መኳንን-ኦች	
መፅሀፍ	መፃህፍ-ት	መፃህፍት-ኦች/	

አንዳንድ ጊዜ የብዙ ቁጥር የሆኑ የግዕዝ ስሞች ወደ አማርኛ ሲገቡ፣ እንደ ነጠላ ቁጥር የአማርኛ ስሞች ይቆጠሩና /-ኦች/ የሚለውን ምዕላድ ያስከትላሉ። በዚህም ምክንያት እንደ ካህናት ያሉ ስሞች ምዕላዱን ሲያስከትሉ፣ ካህናት-ኦች ይሆናሉ። እንዱ ስም የሁለቱንም ቁጥጉጥሮች የቁጥር ስርዓት በአንድ ጊዜ ይጠቀማል። ይህም ብዙ ጊዜ የግዕዝ ሊቃውንትን ያስቀጣል። ለዚህ ምክንያቱ ስሞቹ የብዙ ብዙ እንዲሆኑ መደረጋቸው ነው። አማርኛ ተናጋሪ እንደ ካህናት ያሉ ስሞች የብዙ ቁጥር መሆናቸውን ስለማያውቅ የአማርኛውን የብዙ ቁጥር ምዕላድ ይጨምርባቸዋል።

እስካሁን ያየነው አንዱን አይነት የብዛት መግለጫ ስርዓት ነው። ሌላው አይነት አንድን የነጠላ ቁጥር ስም በመድገም ብዛትን የሚያሳይ ነው። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ነጠላ	ብዙ	5
ቅጠል	ቅጠል -ኣ - ቅጠል	ቅጠላቅጠል
ጥሬ	ጥሬ - ኣ - ጥሬ	ጥራጥሬ
ቁስ	ቁስ - ኣ - ቁስ	ቁሳቁስ
ቅል	ቅል - ኣ - ቅል	ቅላቅል

[1] በዚህ ላይ ባየ (1988፣ 1994)ን ይመልከቱ

ሰርዓቱ ነጠላውን ሰም የሚደግም ብቻ ሳይሆን፣ ነጠላውንና የአሱ ድጋሚ የሆነውን ቃል በማያያዝ አንድ ጥምር ሰም የሚፈጥር ነው። ሁለቱን ነጠላ ሰሞች የሚያጣምረው ምዕላድ/-ኢ-/ ነው። በዚህ ምክንያት ሰርዓቱን <u>ጥመራ</u> ልንለው እንችላለን። አንደ /-ኦች/ ያለ ምዕላድን በነጠላው ሰም ላይ የሚቀጥል አይደለም፤ ነጠላውን ሰም ራሱን የሚደግምና ከድጋሚው አሀድ ጋር የሚያጣምር ሰርዓት ነው።

ርግጥ፣ በዚህ አይነት የሚረቡ ሰሞች የሚያመለክቱት ያንድን ነገር ብዛት ብቻ ሳይሆን፣ ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን ስብስብ ነው። ለምሳሌ፣ ቅጠላቅጠል የሚለውን ጥምር ብንወስድ፣ የሚያመለክተው አንድ አይነት የሆኑ ብዙ ቅጠሎችን ሳይሆን፣ የተለያዩ ቅጠሎች የሚገኙበትን ከምችት ነው። እንደ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ቆሰጣ፣ ወዘተ፣ ያሉት በጥቅል ቅጠላቅጠል ይባላሉ። ከምችቱ የአንድ አይነት ቅጠል ብቻ ከሆነ፣ በሱሙ ላይ ምንም አይነት የብዛት ምልክት ሳይኖር፣ በነጠላ ቅርፁ ብቻ ሰላጣ፣ ጎመን፣ ወዘተ፣ እየተባለ ይጠራል። መጠኑ በጥቅል ሳይሆን ለአሀዝ የሚታወቅ ከሆነ ቅጠሎች ሊባል ይችላል።

አሰካሁን የተመለከትነው ሰሞች ብዛትን ወይም ስብስብነትን ለማመልከት የሚከተሉትን ሰርዓትና በቅርፃቸው ላይ የሚያሳዩትን ለውጥ ነው። ከዚህ ላይ ግን አንድ መነሳት ያለበት ጉዳይ አለ። ይኸውም አሰካሁን ያየነው ሰርዓት በርግጥ ብዛትን የሚያሳይ መሆኑን የሚመለከት ነው። ርግጥ፣ ቀደምት ሊቃውንት ሰርዓቱ የብዛት መሆኑን ይናገራሉ። ጉዳዩ ግን አጠራጣሪ ነው። አስቲ የሚከተሉትን አንመልከት።

(ሀ) ካላ ብዙ በግ-ኦች አሉት 6
(ለ) ካላ ብዙ በግ አለው

በምሳሌ(ሀ) ውስጥ፣ በግ የሚለው ሰም /-ኦች/ የሚለውን ምዕላድ አስከትሉአል። ከፍ ሲል ባየነው ሰርዓት መሰረት፣ ሰሙ የብዙ ቁጥር መሆን አለበት። ብዛትን ያመለክታል ማለት ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ይኸው ሰም /-ኦች/ የሚለውን ምዕላድ አሳሰከተለም። ባለማስከተሉ ግን የሚያመለክተው አንድ ነጠላ በግን ብቻ አይደለም፤ ከአንድ በላይ የሆኑ በጎችን ነው። ብዙ በጎችን የማመልከቱ ምክንያት ብዙ የሚለውን ቃል ማስቀደሙ ነው፣ ይባል ይሆናል። ይህ አንዳይሆን ግን፣ ይኸው ብዙ የሚለው ቃል በምሳሌ (ሀ) ውስጥም ከዚሁ ሰም፣ ማለትም ከበግ በፊት ገብቶ ይገኛል። ብዙ በሚለው ቃል መኖር ወይም አለመኖር ምክንያት ሁለቱ ምሳሌዎች አይለያዩም። የሚለያዩት በ/-ኦች/ መኖርና አለመኖር ብቻ ነው። ይኸውም በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ /-ኦች/ ሲገኝ፣ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ አለመገኘቱ ነው። ይህን ልዩነት እንደ መነሻ እናድርግና አስቲ በሁለቱ ምሳሌዎች መካከል የትርጉም ልዩነት እንዳለ እንመርምር።

ርባታ

በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱት በጎች መጠን አንድ ነው? ወይስ የተለያየ? ለምሳሌ፣ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ብዙ በጎች</u> የሚለው አሰር በጎችን ያመለክታል ብንል፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ <u>ብዙ በግ</u> የሚለው የሚያመለክተው አሰር በጎችን ነው ወይ? በእኔ አመለካከት ብዙ በጎችና ብዙ በግ የሚያመለክቱት የበግ መጠን የተሰያየ ነው። <u>ብዙ በጎች</u> የሚለው የሚገልፀው መጠን፣ <u>ብዙ በግ</u> የሚለው ከሚገልፀው መጠን ያነሰ ነው። ርግጥ፣ በሁለቱም ምሳሌዎች የሚገለፀው ነጠላነት ሳይሆን ብዙነት ነው። የብዙነቱ ደረጃ ግን የተለያየ ነው። ሁኔታው ለሞችን የነጠላና የብዙ ቁጥር ብሎ በሁለት ከፍል ብቻ መመደቡ ትክክል እንዳልሆነ ያመለክታል።

ብዙ በጎች የሚለው ብዙ በግ ከሚለው ያነሰ መጠንን የሚያሳይ ከሆነ፣ ያ አነሰተኛ መጠን ምን ሊባል ነው? ነጠላ እንዳይባል፣ ከአንድ በላይ የሆነ ነገርን ያመለክታል። ብዙ እንዳይባል፣ እሱ ከሚያሳየው መጠን የበዛ አለ። በእጭሩ ከአንድ በላይና ከብዙ በታች የሆነ መጠን አለ። እኔ እንደሚመስለኝ ይህ መጠን <u>ጥቂት</u> ነው። /-ኦች/ የሚለው ምዕላድም የሚያመለክተው ይህንኑ መጠን ነው። /-ኦች/ የጥቂትነት ምዕላድ ከሆነ፣ ብዙነት እንዴት ይገለፃል ብሎ መጠየቅ ይቻላል። ብዛትን የሚያመልክት ምዕላድ በቁዋንቁዋው ውስጥ የለም። በዚህም ምክንያት ከጥቂት ያለፈ መጠን የሚገለፀው እንደ /-ኦች/ ባለ ምዕላድ ሳይሆን፣ በሀረግ ነው። ብዙ በግ፣ መዓት በግ፣ ከመጠን ያለፈ በግ፣ ወዘተ፣ እየተባለ በተሰያዩ የመጠን ቃላትና ሀረጎት ይገለፃል። እንደነዚህ ባሉ ሀረጎች ውስጥ /-ኦች/ የሚለው ምዕላድ አይገባም። ምክንያቱም እሱ የሚያመለክተው ብዙነትን ሳይሆን ጥቂትነትን ነውና[2]።

ይህ አመለካከት ትክክል ከሆነ፣ በአማርኛ ቁጥር በሁለት ሳይሆን፣ በሶስት ይከፈላል ማለት ነው። እነዚህም ነጠላ፣ ጥቂትና ብዙ ናቸው። ለነጠላነት ምንም ምዕላድ የለም። ለጥቂትነት ግን አለ። እሱም /-ኦች/ ነው። ብዙነት የሚገለፀው በምዕላድ ሳይሆን በሀረግ ነው። ጉዳዩን በይበልጥ ለመረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች ደግሞ እንመልከት።

(ሀ) ይህ ሁሉ በግ የማን ነው? 7
(ለ) እነዚህ ሁሉ በጎች የማን ናቸው

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ በግ የሚለው ሰም በቅርፁ ነጠላ ነው። የሚያመልክተው የበግ መጠን ግን ከፍተኛ ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ በጎች የሚለው ሰም በቅርፁ ብዙ ነው። ምክንያቱም የብዙ ቁጥር ምልክት ነው የሚባለውን /-ኦች/ ሰላበከተለ ነው። ይሁን እንጅ፣ የሚያመለክተው የበግ

---

[2] በከተማው አማርኛ፣ <u>መዓት በጎች አሉት</u>፣ ማለት የተስመደ መሆኑ ለበዙዎቻችን ግልፅ ነው። በገጠሩ ግን መዓት በግ እንጅ፣ <u>መዓት በጎች</u> እንደማይባል ራሴ ምስክር ነኝ። /-ኦች/ን ከየበሙ ጋር የመጠቀሙ ልምድ የውጭ ቁዋንቁዋ ተጋቦት እንደሆነ ግልፅ ነው። ጉዳዩን ይበልጥ ለመረዳት ከአማርኛ ሌላ ምንም ቁዋንቁዋ የማይናገሩ የገጠር አዛውንቶችን ንግግር ወስዶ የ/-ኦች/ን አገባብ መመርመር ያስፈልጋል።

መጠን በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ የሚሰጥው በግ የሚለው ስም ከሚያሳየው መጠን ያነሰ ነው። የመጀመሪያው ምሳሌ የሚያመለክተው እጅግ ብዙ የሆነን ቁጥር ነው። ሁለተኛው ምሳሌ የሚያመለክተው ግን ቁጥራቸው ብዙ ያልሆነ በጎችን ነው። የብዛታቸውን ልክ ይህን ያክላል ብሎ በእህዝ መናገር ይቻላል። በመጀመሪያው ምሳሌ የተጠቀሰውን የበግ መጠን ግን በእህዝ ስግስተመተ ያስቸግራል። የሚያስቸግረውም መጠኑ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ነው። ይህን መጠን ግመልክት የሚቻለው በስሙ ላይ /-ኦች/ን በመጨመር ሳይሆን፣ እንደ ሁሉ ባለ ጥቅል አመልካች የመጠን ቃል ብቻ ነው። የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት።

(ሀ) ካላ ሁለት በጎች አሉት 8
(ለ) ?ካላ ሁለት በግ አለው

በእኔ ግምት የመጀመሪያው ምሳሌ ተቀባይነት አያጠራጥርም፣ የሁለተኛው ግን ያጠራጥራል። የአገር ቤት ሰዎች የሚቀበሉት አይነት አባባል አይደለም። ይህ ልዩነት ከምን የመጣ ነው? ሁለት የሚለው ቃል የሚያመለክተው መጠን ጥቂት ነው። አባባቡ ግን ብዛትን ሊያመልክት ከሚችል ስም ጋር ነው። የስሙ ቅርፅ ብዛትን ሊያመለክት የሚችል ሲሆን፣ አህዙ ግን ጥቂትነትን የሚያመለክት ቃል ነው። ስለዚህም የአረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አጠራጣሪ ሊሆን ችሉአል። አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችለው፣ ሁለት በሚለው ፋንታ ከፍተኛ መጠንን በሚያመለክት አህዝ ስንጠቀም ነው። ይህን ስናደርግ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን አይነት ይሆናል።

ካላ ሽ በግ አለው 9

ይህ ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ነው። ባንነሩ ግን፣

?ካላ ሽ በጎች አሉት 10

ብንል፣ ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ይሆናል፣ ቢያንስ በጠሩ አካባቢ። ለዚህም ምክይንያቱ ሽ የሚለው ከፍተኛ መጠንን የሚያመለክት አህዝ ጥቂትነትን የሚያመለክተውን /-ኦች/ን ካስከተለ ስም ጋር መግባቱ ነው። አረፍተ ነገሩ በአንድ በኩል ብዙነትን፣ በሌላ በኩል ጥቂትነትን የሚያመለክቱ ቃላትን ስለያዘ፣ ተቀባይነቱ ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ ችሉአል። ርግጥ፣ እንደ እንግሊዝኛ ካሉ የውጭ ቋንቋዎች ትምህርት የተነሳ በማንኛውም ስም ላይ /-ኦች/ን እየቀጠሉ መናገር በተለይ በከተማው አካባቢ ከምን ጊዜውም የበለጠ እየተስመደ መጥቶአል። ስለዚህም የከተማው አማርኛ ለስርዓቱ ጥሩ መረጃ ሊሆን አይችልም። ስርዓቱን ለወጉ ለመረዳት፣ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው፣ ከአማርኛ ሌላ የግይናገሩ የገጠር አዘውንቶችን ንግግር ማዳመጥ ያስፈልጋል። የከተማው አማርኛ፣ ስርዓተ-ቃሉ ብቻ ሳይሆን፣ ትላቴውም ቢሆን የውጭ ቋንቋዎ እየመሰለ መጥቶአል።

ርባታ

ቁጥር ነጠላ፣ ጥቂትና ብዙ ወይም ጥቅል ተብሉ በሶስት የመከፈሉ ነገር የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የሌሎች የሴም ቁዋንቁዋችም ባህሪ ነው። ለምሳሌ ስልጢ በሚባለው የቤተ-ጉራጌ ቁዋንቁዋ የሚከተሉትን እናገኛለን።

ጫፍ	'ቅጠል'	11
ቻፍ-ቻ	'ጥቂት ቅጠሎች'[3]	

የመጀመሪያው ምሳሌ ነጠላነትን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ጥቂትነትን ያመለክታል። ብዙነት ወይም ጥቅልነት የሚገለፀው በምዕላድ ሳይሆን፣ እንደ አማርኛው በሀረግ ነው። ሁኔታው ምናልባትም በሌሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች የሚታይ ላይሆን አይቀርም።

እንግዲህ እስካሁን አንዳየነው፣ የአማርኛ ስሞች የነጠላ፣ የጥቂትና የብዙ ወይም የጥቅል ተብለው በሶስት ይከፈላሉ ለማለት ይቻላል። ይህ ሲባል ግን ማንኛውም ስም በነዚህ ሶስት ከፍሎች ውስጥ ይካተታል ማለት አይደለም። ርግጥ፣ ማንኛውም ስም በነጠላነቱ በነጠላ ክፍል ውስጥ ሊመደብ ይችላል። ከዚህ ውስጥ በጥቂትነት ሊመደቡ የሚችሉት አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን የሚያመለክቱ ስሞች ብቻ ናቸው። አንድ፣ ሁለት፣ ተብለው ሊቆጠሩ የማይችሉ ነገሮችን የሚያመለክቱ ስሞች ዝቅተኛ መጠንን ለማሳየት እንደ ጥቂት፣ ትንሽ፣ ወዘተ፣ ካሉ መጣኝ ምዕላዶች ጋር ይዋቀራሉ። ከፍተኛ መጠንን ለማሳየት ደግሞ እንደ ብዙ፣ መዓት፣ ጅንድ፣ (ከፍተኛ መጠን) ወዘተ፣ ካሉ ሌሎች መጣኝ ምዕላዶች ጋር ይቀናጃሉ። የሚከተሉትን እንመልከት።

<u>ነጠላ</u>	<u>ጥቂት</u>	<u>ብዙ</u>	12
ለኩዋር	ጥቂት ለኩዋር	መዓት ለኩዋር	
ወተት	ትንሽ ወተት	ብዙ ወተት	
ላም	ላም-አች	መዓት ላም	

ከቅርፅ አንፃር፣ ባጠቃላይ ስሞችን የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ብሉ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል። የሚቆጠሩትን አንደገና የጥቂትና የብዙ ብሉ አሁንም በሁለት መመደብ ይቻላል። የጥቂት ስሞች ብቻ /-አች/ን ያስከትላሉ። ሌሎቹ በሙሉ ከተለያዩ መጣኝ ምዕላዶች ጋር በመቀናጀት የተለያየ መጠንን ሊያመለክቱ ይችላሉ ብሉ ማጠቃለል ይቻላል።

ይህ ግን ስምችን በተመለከተ ነው። የመስተዓምሮች የቁጥር ለርዓት ከዚህ የተለየ ነው። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

---

[3] ስለዚህ ጉዳይ ሀሳብ የለገሱኝ ባልደረባየ ዶ/ር ኧርነስት ጉት ናቸው። በክስታኔም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ ሌላው ባልደረባየ በድሉ ዋቅጅራ አሜውቶኛል።

ርባታ

13

ነጠላ	ብዙ	
ይህ	እነ-ይህ	> እነዚህ
ያ	እነ-ያ	> እነዚያ
እንተ	እነ-አንተ	> እናንተ
እሱ	እነ-እሱ	> እነሱ
ማን	እነ-ማን	> እነማን

በግልፅ እንደሚታየው፣ የብዙ ቁጥር ምዕላዱ /እንንኧ-/ የሚለው ቅጣይ ነው። እገባቡም በየቃሉ መነሻ ላይ ነው። ተግባሩ ግን በርግጥ ብዙነትን ማመልከት አይደለም፤ አውንም ጥቂትነትን ነው። ለዚህም ምክንያቱ እንደ እነዚህ ያሉ መስተዓምሮች የሚዋቀሩት /-እችች/ የሚለውን ምዕላድ ከሚያስከትሉ ስሞች ጋር መሆኑ ነው። ይህ ምዕላድ ደግሞ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የጥቂትነት ምልክት ነው። ስለሆነም ይህን ምዕላድ የያዘ ስም ሊዋቀር የሚችለው ጥቂትነትን ከሚገልፁ መስተዓምሮች ጋር ብቻ ነው። ስሙና መስተዓምሩ በቁጥር ስምሙ መሆን አለባቸውና። ከዚህ አንፃር የሚከትሉትን እንመልከት።

14

(ሀ) እነዚህ ሰጎች
(ለ) እነዚህ ሁሉ በጎች
(መ) ይህ ሁሉ በግ
(ሰ) *እነዚህ ሁሉ በግ

በ14(ሀ) እና በ14(ለ) ውስጥ በጎች የሚለው ስም የጥቂትነት ምልክት የሆነውን /-አችች/ን ለለያዘ እነዚህ ከሚለው መስተዓምር ጋር ተዋቅሮአል። በ14(መ) ውስጥ ደግሞ በግ የሚለው የነጠላ ቁጥር ስም የሚያመለክተው አንድን ነጠላ በግ አይደለም፤ ብዙ በግን ነው። ከዚህ ስም ጋር የተዋቀረው መስተዓምርም እንደዚሁ ነጠላ ነው። ይሁን እንጅ የሚያመለክተው ብዙ በግን ነው። 14(ሰ) ተቀባይነት ያለው አባባል አይደልም። ለዚህ ምክንያቱ በግ የሚለው ስም ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሲሆን፣ እነዚያ የሚለው መስተዓምር ጥቂት ቁጥርን የሚያመለክት በመሆኑ ነው። በሁለቱ መካከል የቁጥር ስምሙነት የለም። ሁኔታው በርግጥም /-እችች/ በስሞች፣ /እንንኧ-/ በመስተዓምሮች የጥቂትነት ምዕላዶች እንደሆኑ ያሳያል።

ለዚህ አመለካከት ተጨማሪ ድጋፍ የሚሆነን /እንንኧ-/ የሚለው ምዕላድ ትረጉም ነው። ይህ ምዕላድ እንደ ካሳ ካሉ የተፀውዖ ስሞች ጋር ሲገባ "ካሳ እና..... የሚል ትርጉም አለው። ይህም ካሳ እና ከእሱ ጋር ያሉ ጥቂት ሰዎች ማለት ነው። በዚሁ እይነት እነዚህ የሚለውን መስተዓምር ብናጤነው፣ ትርጉሙ "ይህ እና ...' ማለት እንደሆነ እንረዳለን። ይህ እና ከእሱ ጋር ያሉ ነገሮች ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት /እንንኧ-/ን አጉዎዳኝ ምዕላድ ልንለው እንችላለን። የሚጉዋደኑ ነገሮች ደግሞ ጥቂት እንጅ ብዙ ሊሆኑ አይችሉም። ብዙ ከሆኑ፣ ግንኙነታቸው የጉድኝት

ሳይሆን የስብስብ ይሆናል። ስለዚህም "እነ... " መሆናቸው ይቀርና "ይህ ሁሉ ... " ይሆናል።

ፆታ

ፆታ ሊላው ስሞችን በወገን በወገን የምንለያይበት ሰዋስዋዊ ባህሪ ነው። ስዋስዋዊ ብቻ ሳይሆን፣ ተፈጥሮአዊም ሊሆን ይችላል። በተፈጥሮአዊነቱ ስሞችን የወንድና የሴት ወገን ብለን፣ በሁለት እንድንከፍል ይረዳናል። በተፈጥሮአቸው የወንድ ምልክት ያላቸው፣ የወንዴ ፆታ፣ በተፈጥሮአቸው የሴት ምልክት ያላቸው፣ የሱቴ ፆታ ወገን ተብለው ይለያሉ። ከሰዋስው አኩዋያም ስሞች ተባዕታይና አንስታይ ተብለው አንደዚሁ በሁለት ይከፈላሉ። ተባዕታይነትና አንስታይነት ከተፈጥሮ ፆታ፣ ግለትም ከወንዴነት ወይም ከሴቴነት ጋር ሊያያዝ ወይም ላይያያዝ ይችላል።

የተባዕታይ ፆታ ስሞች ፆታቸውን የሚያመለክት ምዕላድ የላቸውም። የአንስታይ ፆታ ስሞች ግን ምዕላድ አላቸው። ምልክቴ እንድም በስሞቹ በራሳቸው ላይ፣ አለያም በሚገኙበት አረፍተ ነገር ግስ ላይ ይታያል። በግስ ላይ አንዲት እንደሚከሰት ወደ ሁዋላ እናየዋለን። በስሞች ላይ ስለሚታይበት ሁኔታ የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንመልከት።

ተባዕታይ	አንስታይ	1
አይጥ	አይጥ-ኢት-ኡ	
ጥጃ	ጥጃ-ኢት-ኡ	
በግ	በግ-ኢት-ኡ	
ልጅ	ልጅ-ኢት-ኡ	
ቤት	ቤት-ኢት-ኡ	

በግልፅ እንደሚታየው አንስታዮቹ ስሞች /-ኢት-/ የሚል ምዕላድ አስከትለዋል። ይህ የአንስታይነት ምልክት ነው። ከእሱ ቀጥሎ የሚገኘው /-ኡ/ የዕምርነት ምልክት ነው። ዕምርነትና ፆታ ቁርኝት አላቸው። የፆታ ምዕላድ በሚገኝበት ሁሉ የዕምርነት ምዕላዱም አብሮ ይገኛል። ይገኝ እንጅ፣ ከዚህ ላይ አትኩሮታችን ፆታ ላይ ስለሆነ፣ እሱን ስጊዜው አናየውም።

በመጠናቸው ትንሽ የሆኑ ነገሮችም በአማርኛ እንደ አንስት ስለሚቆጠሩ፣ እነሱን የሚገልፁ ስሞች የአንስታይ ፆታ ምዕላድን ያስከትላሉ። አንስታይነት ትንሽነትን ያመለክታል ማለት ነው። ተባዕታይነትም በአንፃሩ ትልቅነትን ሊያመልክት ይችላል። ስለዚህም በተፈጥሮ ፆታው ወንዴ የሆነ እንስሳ በመጠኑ ትንሽ ከሆነ፣ በአንስታይ ፆታ ሊጠራ ይችላል። እንዲሁም በተፈጥሮ ፆታው እንስት (ሴቴ) የሆነ እንስሳ በመጠኑ ትልቅ ወይም በባህሪው ወንዳወንድ ከሆነ፣ በተባዕታይ ፆታ ሊጠራ ይችላል። ስለዚህም ወንዱን <u>አንቺ</u> ብለን በአንስታይ፣ ሴትዋን ደግሞ <u>አንተ</u> ብለን በተባዕታይ ፆታ የምንጠራበት ጊዜ አለ። ጉዳዩ ፆታ

ከወንዲነትና ከሴቲነት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከመጠንና ከባህሪ ጋርም ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል የሚጠቁም ነው። ቁዋንቁዋውም ይህን በምዕላድ ወይም በመዋቅር ያሳያል። ከዚህም ሰዋሰዋዊ ባህሪያትን ብቻ ማሳየት ሳይሆን፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችንም ማንፀባረቁን ልብ ልንል ይገባል። ስነንሩግ ቁዋንቁዋ ተናጋሪውን ይመስላል ይባል የሰ?

እንደ ሰሞች ሁሉ ቅፅሎችም አንስታይ ፆታን የሚያመለክቱበት ስርዓት አላቸው። ይህም የሚታየው በተለይ እንደ ተፀውዖ ሰም ሆነው ለመጥሪያነት በሚውሉበት ጊዜ ነው።

	መጥሪያ	2
ቅፅል	ተባዕታይ	እንስታይ
ሞኝ	ሞኝ-አ	ሞኝ-ኢት
ብልጥ	ብልጥ-አ	ብልጥ-ኢት
ቂል	ቂል-አ	ቂል-ኢት

መዘርዝሩ /-አ/ ተባዕታይነትን፣ /-ኢት/ እንስታይነትን እንደሚያመለክቱ በግልፅ ያሳያል። ከፍ ሲል እንደ ተመለከትነው፣ ሰሞች ለእንስታይነት እንጅ ለተባዕ ታይነት የተለየ ምልክት የላቸውም። መጥሪያ ቅፅሎች ግን ለሁለቱም ፆታዎች የተለያየ ምዕላድ አላቸው። እንስታይነትን ልክ እንደ ሰሞች /-ኢት/ በሚሰው ምዕላድ ሲያመለክቱ፣ ተባዕታይነትን ከሰሞች በተለየ ሁኔታ /-አ/ የሚል ምዕላድ በማስከተል ያመለክታሉ።

በመጥሪያነት ሳይሆን፣ በገላጭነት በሚገቡበት ጊዜ፣ ቅፅሎች ከዚህ በላይ ከተመለከትነው የተለየ የፆታ መግለጫ ስርዓት አላቸው። እሱን ወደ ሁዋላ እንመለከተዋለን። ከዚህ ላይ ባለፈው ክፍል በጠቁዋማ መሰተዓምርነት የፈረጅናቸው መደበኛና አመልካች ተውላጠ ሰሞች ፆታን እንዲት እንደሚያሳዩ እንመለከታለን።

		3
ተባዕታይ	እንስታይ	
አንተ	እን-ት-ኢ	አንቺ
እሱ	እሰ-ኡ-አ	እሰዋ
ይህ	ይህ-ት-ኢ	ይህች
ያ	ያ-ት-ኢ	ያች

ከመዘርዝሩ እንደምንመለከተው፣ ቃላቱ እንስታይነትን በ/-ኢ/ እና በ/-አ/ ያመለክታሉ። ሁለት የተለያዩ የእንስታይ ፆታ ምልክቶች እሱ ማሰት ነው። አገባባቸውም /-ኢ/ ከሁለተኛ መደብ፣ /-አ/ ከሶስተኛ መደብ ጋር ነው። አሰዋ /እሰ-ኡ-አ/ በሚለው ውስጥ፣ ከፆታ ምዕላዱ በፊት የሚገኘው /-ኡ-/ ሶስተኛ መደብ አመልካች ቅጣይ ምዕላድ ነው። አገባቡ ግን በመሰተዓምርነት ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መሰተዓምርና ፆታ ቁርኝት ስላላቸው፣ እንዱ በሚገኝበት ቃል ሁሉ፣ ሌላውም እሱን ተከትሎ ይገኛል። ቅጣዮቹ ያረፉበት

ርባታ

መሰረታዊ ቃል <u>እስ-</u> ሲሆን፣ እሱም ራስ የሚለው ስም ጉራጅ ነው። ይህ ለመሆኑ ማስረጃው <u>አፀፋ</u> ተውላጠ ስም በሚባሉት ውስጥ ሙሉ ቃሉ በግልፅ መታየቱ ነው። እፀፋ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

<u>ነጠላ</u>	ብዙ
ራስ-ኤ	ራስ-አች-ን
ራስ-ህ	ራስ-አች-ሁ
ራስ-ሽ	
ራስ-ኡ	ራስ-አች-ኧው
ራስ-ኡ-አ	

ከዚህ ላይ መደቡ ቃል <u>ራስ</u> የሚለው ስም መሆኑ አያጠራጥርም። ከእሱ ቀጥለው የሚገኙት የመደብ፣ የፆታ ወይም የቁጥር ምዕላዶች ናቸው።

<u>እንተ</u> በሚለው ተውላጠ ስም መድረሻ ላይ የምትታየው /-ት/ ሁለተኛ መደብ አመልካች ምዕላድ ነች። ከእሰዋ ቀጥላ የገባችው /-ኢ/ የእንስታይ ፆታ ምዕላድ ነች። በስነ-ድምፁ ክፍል እንዳየነው፣ በ/-ኢ/ ምክንያት /ት/ ወደ [ች] ትለወጣለች። <u>ይህች</u> በሚለው ጠቁዋሚ ቃል ውስጥ የሚታየው ሁኔታም እንደዚሁ ነው። ታህታይ ቅርፁ /ይህ-ት-ኢ/ ነው። /-ት/ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ስትሆን፣ /-ኢ/ አንስታይ ፆታ አመልካች ነች። ሁለቱ ሲከታተሉ /ት/ ወደ [ች] ትለወጣለች። <u>ራስሽ</u> በሚለው አፀፋ ተውላጠ ስም ውስጥ፣ የሁለተኛ መደብ የአፀፋ ምዕላድ የሆነው /-ህ/ እና የዚሁ መደብ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችው /-ኢ/ ስለተከታተሉ፣ /-ህ/ ወደ [ሽ] ተለውጣለች። ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው፣ እነዚህ በምዕላድ ድንበር ላይ የሚታዩ የሙሉ (ድ)ላነቃቂነት ምሳሌዎች ናቸው።

እንግዲህ እስካሁን እንደ ተመለከትነው፣ አንስታይ ፆታን የሚያመለክተው ምዕላድ በስሞችና በቅፅሎች ላይ /-ኢት/፣ በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስሞችና ጠቁዋሚ ቃላት ላይ /-ኢ/፣ በሶስተኛ መደብ ላይ /-አ/ የሚል ቅርፅ አለው። እነዚህ የተለያዩ ቅርፆች ዘረ-ምዕላድ ይባላሉ። የአንድ ምዕላድ ዘሮች እንደማለት ነው። ከነዚህ ዘረ-ምዕላዶች አንዱን በራሱ ወይም አብሮት በሚዋቀር ግስ አማካኝነት የሚያላይ ስም፣ ቅፅል ወይም መሰተዓምር የአንስታይ ፆታ ስም፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ሲባል፣ ይህንን የማያደርግ ደግሞ የተባዕታይ ፆታ ስም፣ ወዘተ፣ ይባላል። ማንኛውም ስም ከነዚህ ከሁለቱ በአንዱ ወይም በሌላው ውስጥ መመደብ አለበት።

ይህን ሁኔታ ካለመገንዘብ፣ ቀደምት ሊቃውንት እንደ <u>ፈረስ</u> ላሉ ስሞች የወል ፆታ የሚባል ከአንስታይና ከተባዕታይ የተለየ ክፍል መድበው ነበር። መግለጫውም ወንዱ ወይም ሴቱ መሆኑን የማያመለክት ስም የሚመደብበት የፆታ አይነት የሚል ነው። በስሞች ቅርፅ ላይ ላይሆን፣ ስሞቹ በሚያመለክቱት ነገር የተፈጥሮ ፆታ ላይ የተመሰረተ ግላዜ ነው። በዚህም መሰረት እንደ ፈረስ በተፈጥሮአቸው ወንዱ ወይም ሴቱ የሆኑ እንስሳትን ሊያመለክቱ የሚችሉ

ስሞች፣ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደሚመደቡ ሲታውቁ ይገልፃሉ። አስካሁን በዚህ ክፍል ባየነው የያታ ባህሪ መሰረት ግን ግንኛውም የአንስታይ ያታን ምዕላድ ያላስከተለ ስም፣ ምድቡ በተባዕታይ ያታ ውስጥ ነው። በዚህ መሰረት እንደ ፈረስ ያሉ ስሞችም ምድባቸው በዚሁ ያታ ስለሚሆን፣ የወል ያታ የሚል ክፍል መመደብ አስፈላጊ አይደለም።

የሲቃውንቱ ጥናት በአብዛኛው የተመሰረተው በስሞች ቅርፅ ላይ ላይሆን፣ በትርጉም ላይ በመሆኑና፣ ትርጉምም ስሚታዊና ተለዋዋጭ ስለሆነ፣ በቅርፃቸው በአንድ ወይም በሁለት ክፍሎች ሊካተቱ ስሚችሉ ቃላት እንደ ትርጉማቸው ልዩነት፣ የተለያዩ ክፍሎች እንዲፈጠሩ አስገድደዋል። በዚህም ምክንያት ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ከቅርፅ አኳያ በሁለት ሲመደቡ ስሚችሉ ስሞች፣ ሶስት የያታ ክፍሎች ሊፈጥሩ ችለዋል። ጉዳዩ ግን በዚህ ብቻ አያበቃም። እነዚህ ሶስት ክፍሎች ህይወት ያላቸውን ነገሮች ለሚያመለክቱ ስሞች ብቻ የተመደቡ ናቸው። ህይወት የሌላቸው ነገሮችን የሚያመለክቱ እንደ ድንጊያ፣ ዛፍ፣ ቤት፣ መዘተ፣ ያሉ ስሞች በነዚህ ክፍሎች ሲካተቱ አይችሉም። ስለዚህም ለእነዚህ አይነት ስሞች የተለየ ክፍል መፍጠር አስፈልጎአል። ለዚህም ግዑዝ ያታ የሚባል አራተኛ የያታ ክፍል ተመድቦአል።

በእኔ አመለካከት እንደ <u>ድንጊያ</u> ያሉ ስሞች ህይወት የሌላቸው ነገሮችን ቢያመለክቱም፣ በቅርፃቸው ብቻ በተባዕታይ ያታ ውስጥ ሲመደቡ ይችላሉ። ከቅርፃቸው አንፃር ሲመረመሩ፣ የግዑዝ ያታ ምልክት የላቸውም፣ ሊኖራቸውም አይችልም። ምክንያቱም የወል ያታ ምዕላድ በቁዋንቁዋው ውስጥ እንደሌለ ሁሉ፣ የግዑዝ ያታ ምዕላድ የሚባልም የለም። በቁዋንቁዋው ውስጥ ያሚገኙት የያታ ክፍሎች ቀደም ሲል የተጠቀሱት ተባዕታይ እና አንስታይ ብቻ ናቸው። ከነዚህም በተለየ ምዕላድ የሚገለፀው አንስታይ ያታ ብቻ ነው። የዚህን ያታ ምዕላድ ያስከተለ ማንኛውም ስም አንስታይ፣ ያላስከተለው ደግሞ ተባዕታይ ነው።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከነዚህ ከሁለቱ ውጭ የሚሆን ስም የለም። ስለዚህም የወልና የግዑዝ ያታ ብሎ ተጨማሪ ክፍል መፍጠሩ አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፣ አጨቃጫቂም ነው። ህይወት የሌላቸው ነገሮች ሲባል፣ ምን ማለት ነው? ወደሚል ዋያቄም ይወስዳል። ለምሳሌ፣ ግዑዝ የሚባለው ህይወት የሌለው ነው፣ ተብሎአል። በዚህ መሰረት አንድ ህይወት የነበረው ነገር፣ ህይወቱን ሲያጣ ግዑዝ ሊሆን ነው። በዚህን ጊዜ ያታው ከምን ክፍል ሲመደብ ነው? ለምሳሌ፣ <u>ክሰች</u> የሚለው የተፅውዖ ስም ያታ አንስታይ ነው። ለዚህም ምክንያቱ [-ች] < /ት-ኢ/ የሚለውን የአንስታይ ያታ ምዕላድ ማስከተሉ ነው። በዚህ ስም የምትጠራዋ ሴት የተፈጥሮ ያታ ሴቴ ነው። ይህች ሴት ህይወትዋን ብታጣ፣ ያታዋ ግዑዝ ነው፣ ሲባል ነው? በእኔ አመለካከት ሲትዮዋ ህይወትዋን ብታጣም፣ የእስዋ መጠሪያ የሆነው <u>ካሰች</u> የሚለው ስም፣ አሁንም ክፍሉ አንስታይ ነው። ምናልባት ሴትዮዋ ህይወትዋን ካጣች፣ በድን ወይም ግዑዝ ስለምትሆን፣ የዚያ ግዑዝ አካል የያታ ክፍል ግዑዝ ነው፣ ይባል ይሆናል። በእኔ በኩል ግን ለዚያ

ርባታ

ግዑዝ አካል የሚሰጠው ስም ሬሳ ነው። ሬሳ የሚለው ስምም በቅርፁ ተባዕታይ ነው። ሁኔታው ግዑዝ ፆታ የሚባል ከፍል የሰም የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። ይህን በይበልጥ የግሰን ርባታ በምናይበት ጊዜ እናስተውሰዋለን። ለጊዜው ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ብቻ እንመልከትና ነገሩን እንቁዋጨው።

(ሀ) ፈረሰ ገራም ነ-ው 4
(ለ) አንበሳ ደፋር ነ-ው
(መ) ጠጣ ብልጥ ነ-ች
(ሰ) ድመት ፈጣን ነ-ች

በምሳሌ (ሀ) እና (ሰ) ውስጥ የተጠቀሱት ስሞች ተባዕታይ ናቸው። ይህ ውነት መሆኑን ከግሱ ቅርፅ መገንዘብ ይቻላል። ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ አንድም በስሞች ላይ፣ አለያም ሰሞቹ በሚገኙበት አረፍተ ነገር ግስ ላይ መታየት አለበት። በነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ውስጥ [-ች] < /ት-አ/ የሚለው የአንስታይ ፆታ ምዕላድ በስሞቹ ላይም ሆነ በግሶቹ ላይ አይታይም። ስለዚህም ስሞቹ ተባዕታይ ናቸው። በአንፃሩ ግን በምሳሌ (መ) እና (ሰ) ውስጥ [-ች] < /ት-አ/ የምትሰዋ ምዕላድ በግሱ ላይ በግልፅ ትታያለች። ይህም ስሞቹ አንስታይ መሆናቸውን ያመለክታል። ሁኔታው አንስታይ ፆታ ምዕላዳዊ ወይም መዋቅራዊ ሊሆን አንደሚችል ያስገነዝባል። ምዕላዳዊ የሚሆነው እንደ ቆንጂት፣ ማሚት፣ ውቢት፣ ወዘተ፣ ባሉ ስሞች ውስጥ አንደሚታየው፣ /-ኢት/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት ሲከሰት ነው። መዋቅራዊ የሚሆነው ደግሞ በስሙ በራሱ ላይ ሳይሆን፣ ስሙ በሚገባበት አረፍተ ነገር ውስጥ፣ በግሱ ላይ [-ች] < /ት-አ/ በሚል ምዕላድ ሲገለፅ ነው። በጥቅሉ፣ ማንኛውም ስም በቃል ደረጃ እንደ /-ኢት/ ያሰ ምዕላድ እስከላስከተለ ድረስ፣ ተፈጥሮአዊ ፆታው ምንም ይሀን ምን፣ ከፍሉ ተባዕታይ ነው።

ሙያ

ሙያ ስሞች በመዋቅር ውስጥ ሲገቡ የሚፈፅሙትን ተግባር የሚመለከት ስዋሰዋዊ ባህሪ ነው። አንድ ስም በአረፍተ ነገር ውስጥ የባስቤትነት፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የተሳቢነት፣ እንዲሁም በስማዊ ሀረግ ውስጥ የዘርፍነት ተግባር አለው። ባስቤትነት በአረፍተ ነገር ውስጥ ግሱ የሚገልፀውን ተግባር ከመፈፀም ጋር ሲገናዘብ ይችላል። ተሳቢነት ደግሞ ግሱ የሚገልፀውን ድርጊት ተቀባይ ከመሆን ጋር ይዛመዳል። ዘርፍነት ግን ከድርጊት ፈፃሚነትም ሆነ ከተቀባይነት ጋር ሳይሆን፣ አንድ ስም የሚጠቁመውን ነገር በባለገንዘብነት (በገንዛቢነት) ከመያዝ ጋር የሚገናኝ ሀሳብ ሊሆን ይችላል።

ስሞች እነዚህን ተግባራት ሲፈፅሙ በመዋቅር ውስጥ በተለያየና በተወሰነ ቦታ በመገኘትና ወይም የተለየ ምዕላድ ማግሳየት ሊሆን ይችላል። መዋቅራዊ

ባህሪውን፣ ወደፊት በቦታው እናየዋለን። አሁን ግን እነዚህን ተግባራት ሲፈፅሙ የሚያሳዩዋቸውን የተለያዩ የቅርፅ ለውጦች ብቻ እንገልፃለን።

ስሞች ከላይ ከተጠቀሱት ሙያዎች መካከል ለሁለቱ ብቻ ቅርፃቸውን በከፊል ይለውጣሉ። ሙያዎቹም ተሳቢና ዘርፍ ናቸው። ለዚህ የሚከተለውን እንመልከት።

ስም	ባለቤት	ተሳቢ	ዘርፍ	1
ቤት	ቤት	ቤት-ን	ቤት-የ	ቤቴ
በግ	በግ	በግ-ን	በግ-የ	በጌ
ልጅ	ልጅ	ልጅ-ን	ልጅ-የ	ልጄ
ላም	ላም	ላም-ን	ላም-የ	ላሜ

በግልፅ እንደሚታየው፣ ስሞቹ ለተሳቢነት /-ን/ን፣ ለዘርፍነት ደግሞ /-የ/ን ያስከትላሉ። ለባለቤትነት ምንም ምልክት የላቸውም። ምልክት አለማሳየታቸው ራሱ ምልክታቸው ነው፤ ለማለት ይቻላል። ስለዚህም በአረፍተ ነገር ውስጥ በባለቤት ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ምልክት የሌለው ስም ሙያው ባለቤት ነው፤ ሊባል ይችላል።

ክላይ እንደተገለፀው ስሞች በባለቤትነትና በተሳቢነት በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ፣ የተለያየ ቦታ አላቸው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አስቴር-ን መታት
(ለ) አስቴር ካሳ-ን መታችው
(መ) *አስቴር ካሳ መታችው

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ካሳ የሚለው ስም ባለቤት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለባለቤትነት የተለየ ምዕላዳዊ ምልክት የለም። ስለዚህም ስሙ የሚታየው ሌላውን ነው። ይሁን እንጅ በአገባቡ የአረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ቃል ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ስም መታችው ከሚለው ግስ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ ቦታ የተሳቢ ስለሆነ፣ ስሙ የተሳቢ ምልክት የሆነውን /-ን/ን አስክትሎአል። ሶስተኛው ምሳሌ ተቀባይነት ያለው አርፍተ ነገር አይደለም። ምክንያቱም ካሳ የሚለው ስም በተሳቢ ቦታ ያለተሳቢ ምልክት መግባቱ ነው።

ዘርፍ ሙያ የሚገኘው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ስሞችን በያዘ ስማዊ ሀረግ ውስጥ ነው። የሚገልፀውም በሀረጉ ውስጥ የሚገኙትን ስሞች ዝምድና ነው። ዝምድናው የገንዘብና የባለገንዘብ ነው። ይህም የሚገለፀው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው ባለገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም በፊት /የ-/ የሚል ምዕላድ በማስቀመጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም መድረሻ ላይ የተለያዩ ምዕላዶችን በመቀጠል ነው። ሁለቱንም መንገዶች እንደሚከተለው በየተራ እናሳያለን።

ርባታ

(ሀ) የ-ካሳ ቤት
(ለ) የ-አስቴር ቤት
(መ) የ-ልጆቹ ቤት 3

እነዚህ የስማዊ ሀረግ ምሳሌዎች ናቸው። በያንዳንዳቸው ውስጥ ሁለት፣ ሁለት ስሞች አሉ። ከሁለቱ ስሞች የመጀመሪያው፣ በሁለተኛው ስም የሚጠቆመው ነገር ባለገንዘብ ወይም ባለቤት ነው። ይህንንም የባለንብረትነት ሙያውን ለማሳየት /የ-/ን አስቀድሞአል። ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው ሀረግ ውስጥ ካሳ ባለገንዘብ፣ ቤት ደግሞ ገንዘብ ወይም ንብረት ነው። ስለሆነም ባለገንዘቡ ካሳ /የ-/ን አስቀድሞ ገብቶአል። ይህች ምዕላድ ገንዘብንና ባለገንዘብን ስለምታያይዝ አገናዛቢ ትባላለች።

ሁለተኛው መንገድ ከላይ የሚታየው ተቃራኒ ነው። ይኸውም ባለገንዘቡን የሚያመለክተው ምዕላድ ከባለገንዘቡ ላይ ሳይሆን፣ ገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም መድረሻ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነው። የምዕላዱም ቅርፅ ከላይ እንደሚታየው እንደ /የ-/ አንድ አይነት ሳይሆን፣ እንደ ባለገንዘቡ መደብ፣ ቁጥርና ፆታ የተለያየ ነው። እንዴት እንደሚለያይ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

መደብ		ስም	ዘርፍ	4
1ኛ		ቤት	ቤት-የ	
2ኛ	ተ		ቤት-ህ	
	አ		ቤት-ሽ </-ህ-ኢ/[4]	
3ኛ	ተ		ቤት-ሉ	
	አ		ቤት-ዋ </-ሉ-አ/	
	ብ		ቤት-አችን /-አችች-ን/	
			ቤት-አችሁ </-አችች-ህ-ሉ/	
			ቤት-አቸው </-አችች-ኧ-ሉ/	

በዚህ አይነት ማንኛውም ስም የተለያዩ ቅጣዮችን በማስከተል ቅርፁን እየለዋወጠ ዘርፍ ሙያን ያሳያል። ምዕላዶቹ ባለገንዘብን ስለሚያመለክቱ፣ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አገናዛቢ አፀፋ በመባል ይታወቃሉ። አፀፋነታቸው ባለገንዘቡን ለሚያመለክተው ስም ነው። ይሁን እንጅ ምዕላዶቹ የሚያገናዝቡት ባለገንዘብና

[4] ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ /-ህ/ ሁለተኛ መደብ አመልካች ለሆን፣ /-ኢ/ አንለታይ ፆታን አመልካች ነች። [-ሽ] የሁለቱ ውህደት የፈጠራት ውሁድ ቅርፅ ነች። /ኢ-/ አንስታይ ፆታ አመልካችና ከመደብ አመልካቹ ከ/ህ-/ የተለየች ስመሆንዋ ምልከቱ፣ በግሱ ትዕዛዛዊ ቅርፁ ውስጥ ብቻዋን መገኘትዋ ነው። ይህም ስምላሌ፣ ኦር ብለን ኦር-ኢ ስንል ነው። እንደዚሁም /-ሉ-/ ሶስተኛ መደብ አመልካች ሲሆን፣ /-ኢ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ነች። የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ዘረ-ምዕላዶች አንዳሉት ቀደም ሲል ገልፀናል። በብዙ ቁጥር ስር የሚታዩትም መደብንና ቁጥርን ያዋሀዱ ውሁድ ምዕላዶች ናቸው። ዝርዝሩን ከባየ (2004) ላይ ይመልከቱ።

ገንዘብን ብቻ ሳይሆን፣ ባለድርጊትንና ድርጊትንም ሊሆን ይችላል። ባለድርጊት ስንል፣ ድርጊት ፈፃሚን የሚያመለክት ስም ማለታችን ነው። ስለ ሁኔታው የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

መደብ		ስም	ዘርፍ	5
1ኛ		መሂድ	መሂድ-የ [5]	
2ኛ	ተ		መሂድ-ሀ	
	አ		መሂድ-ሺ	</-ሀ-አ/
3ኛ	ተ		መሂድ-ኡ	
	አ		መሂድ-ዋ	</ኡ-አ/
	ላ		መሂድ-አችን	</-አች-ን/
			መሂድ-አችሁ	</-አች-ሀ-ኡ/
			መሂድ-አቸው	< /-አች-ኧ-ኡ/

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የዘርፉ ምዕላዶች የሚያመለክቱት ባለገንዘብን ሳይሆን፣ ባለድርጊትን ነው። መሂድ የሚለው ቃል የድርጊት ስም ስለሆነ፣ ምዕላዶቹ የሚያመለክቱት የድርጊቱን ፈፃሚ፣ ማለትም አድራጊውን፣ ነው። ይህን ሙያውን አንድም፣ ከላይ እንደሚታየው፣ በተለያዩ ምዕላዶች፣ አለያም ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፣ /የ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም እንደሚከተለው ያሳያል።

		6
የ-እኔ	መሂድ	
የ-አንተ	መሂድ	
የ-አንቺ	መሂድ	
የ-አሱ	መሂድ	
የ-አስዋ	መሂድ	
የ-እኛ	መሂድ	
የ-አናንተ	መሂድ	
የ-አነሱ	መሂድ	

አድራጊው ወይም ባለገንዘቡ ስም /የ-/ን አስቀድሞ ከገባ፣ ድርጊቱን ወይም ገንዘቡን የሚያመለክተው ስም፣ አድራጊውን ወይም ባለገንዘቡን የሚጠቁም ምንም አይነት ቅጣይ አያስከትልም። ስለዚህም፣

				7
(ሀ)	*የእኔ	ቤት-የ	*የእኔ	መሂድ-የ
(ለ)	*የአንተ	ቤት-ሀ	*የአንተ	መሂድ-ሀ

ወዘተ፣

[5] የእነዚህን ምዕላዶች ባህሪ በተመለከተ ሀይሉ (1967)ን እንዲሁም ባየ (1990)ን ይመልከቱ።

ርባታ

ማለት ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም። ባንዛሩ ግን፣

(ሀ) እኔ ቤት-የ እኔ መሄድ-የ 8
(ለ) አንተ ቤት-ሀ አንተ መሄድ-ሀ
ወዘተ፣

ማለት ይቻላል። ባሮሩ፣ ዘርፍ ሙ-ያ በቅጣይ የአፀፋ ምዕላዶች ወይም /የ/ በሚለው ምዕላድ ይገለፃል። /የ/ የሚገባው ከባለገንዘቡ ወይም ከባለድርጊቱ፣ ወዘተ፣ ሰም በፊት ሲሆን፣ አፀፋው የሚገባው ከተገናዛቢው ሰም መድረሻ ላይ ነው።

ዕምርነት

ዕምርነት ሰንል ዕውቅ መሆን ማለታችን ነው። አንድ ሰም የሚገልፀው ነገር የታመረ (የታወቀ) ከሆነ፣ ሰሙ ላይ የዕምርነት ምልክት ይኖራል። ያልታመረ (ያልታወቀ) ነገርን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገልፅ ከሆነ፣ ኢዕምር ሰም ይባላል። ዕምር ያልሆነ ሰም ምንም ቅጣይ ምልክት የለውም። ዕምር የሆነ ሰም ግን ምልክት አለው። ምልክቱም /-ኡ/ ነው። ቀደም ሲል ከየታ ጋር ያለውን ቁርኝት አለመልክተን በመጠኑ አይተነዋል። የሚከተለውን ሰንጠረዥ እንመልከት።

ሰም	ኢዕምር	ዕምር	1
ቤት	ቤት	ቤት-ኡ	
በግ	በግ	በግ-ኡ	
ድመት	ድመት	ድመት-ኡ	
ዛፍ	ዛፍ	ዛፍ-ኡ	
አይጥ	አይጥ	አይጥ-ኡ	

እነዚህ ሰሞች በሙሉ ተባዕታይ ናቸው። አንስታይ ሲሆኑ የዚሁ መግለጫ የሆነችውን /-ኢት/ን ከዕምሩ ምዕላድ በፊት ማሰገባት፣ ወይም ሌላዋን ዘረ ምዕላድ፣ ማለትም /-አ/ን፣ ከዕምሩ ምዕላድ በሁዋላ ማለከተል አለባቸው። ይህ ሲሆን፣ ቤት የሚለው ሰም /ቤት-ኢት-ኡ/ ወይም /ቤት-ኡ-አ/ ይሆናል። /ቤት-ኡ-አ/ በሚለው ውሰጥ የዕምሩ ምዕላድ /-ኡ/ እና የየታው ምዕላድ /-አ/ እየተዋሀዱ /-ዋ/ የሚል ቅርፅ ይፈጥራሉ። ከዚህም የተነሳ፣ ይህ ውሁድ ቅርፅ እንደ ተራ ምዕላድ እየተቆጠረ የአንስታይ ፆታ ሰሞች የዕምርነት ምልክት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ግን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ዕምርነትን ከቁጥር ጋር አገናዝበን ብንመለከተው፣ የየታዋ ምዕላድ ከዕምርዋ ምዕላድ የተለየች እንደሆነች ለመረዳት ሰለምንችል ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

ርባታ

ንጥል ተባዕታይ፡	/ሰኸው - አይይኽ - ኡ/	ሰውየው 2
ንጥል አንስታይ፡	/ሰኸው - እይይኽ - ኡ - ኣ/	ሰውየዋ
ብዙ፡	/ሰኸው - - - አችች - ኡ -/	ሰዎቹ
		*ሰውየዎቹ
		*ሰውየዎችኡኣ

በንጥሉ የተባዕታይ ስም፣ የንጥልነቱ ምዕላድ /-አይይኽ-/ እና የዕምርነቱ /-ኡ/ ተከታትለው እንደገቡ እናያለን፡፡ በንጥሉ የአንስታይ ስም ግን የንጥልነቱ /-አይይኽ-/፣ የዕምርነቱ /-ኡ/ እና የአንስታይነቱ /-ኣ/ በዚሁ ቅደም ተከተል ተከታትለው ገብተዋል፡፡ /-ኣ/ የምትለዋ ምዕላድ እንደ <u>ሰውየው</u> ባሉ ስሞች መድረሻ ላይ ስትገኝ፣ አንስታይነትን ሳይሆን፣ ንዑስነትን ታመለክታለች፡፡ ስለዚህም <u>ሰውየዋ</u> ስንል፣ በአዕምሮአችን የሚፈጠረው ምስል አጭር፣ ቀጭንና ምናልባትም ብልጣ-ብልጥ ሽማግሌ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህንኑ ሁኔታ /-ኢት/ በምትለዋ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ አማካኝንት መግለፅ ይቻላል፡፡ ስለዚህም ሰውየዋ (/ሰኸው-አይይኽ-ኡ-ኣ/) የሚለው ሰውየይቱ (/ሰኸው-አይይኽ-ኢት-ኡ/) ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ቃል ውስጥ /-ኢት/ የምትለዋ ምዕላድ ከነጣዩ ምዕላድ ከ/-አይይኽ-/ ቀጥላ ገብታለች፡፡ በዚህም በቃል መድረሻ ከምትገኘው ከ/-ኣ/ በአገባብ ብቻ ትለያለች፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ /-ኢት/ እና /-ኣ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ የተለያዩ ቅርፆች ወይም ዘረ-ምዕላዶች ናቸው፡፡

በብዙ ቁጥር ላይ ደግሞ የንጥልነቱም ሆነ የአንስታይነቱ ምዕላድ አይታይም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ፣ በአንድ በኩል፣ አንድ ስም በአንድ ጊዜ ንጥልና ብዙ ሊሆን አለመቻሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በአማርኛ የብዙ ቁጥር የሆነ ስም የአንስታይነትን ምዕላድ የማያሳይ መሆኑ ነው፡፡ ባጭሩ፣ አንድ ስም የብዙ ቁጥር ከሆነ፣ የንጥልነትንም ሆነ የአንስታይነትን ምዕላድ አያሳይም፡፡ አሳይቶ ቢገኝ፣ አባባሉ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ዋናው ቁም ነገር፣ በአማርኛ ዕምርነትና ፆታ፣ እንዲሁም አንስታይነትና ንዑስነት ቁርኝት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ነው፡፡

ቅፅል

ቅፅሎች እንደ ስሞች ሁሉ ለቁጥር፣ ለፆታ፣ ለሙያና ለዕምርነት ቅርፃቸውን ይለዋወጣሉ፡፡ ሙያን፣ ዕምርነትንና ፆታን የሚያሳዩት ከፍ ሲል እንዳየናቸው አንደ ስሞች ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ እንደገና አንደግመውም፡፡ ቁጥርን በሚመለከት ግን ከስሞች ለየት የሚያደርጋቸው ትንሽ ሁኔታ ስላለ፣ በእሱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡

ቅፅሎች ብዛትን (ጥቂትነትን) የሚያሳዩት በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው፣ እንደ ስሞች /-አችች/ የሚለውን ምዕላድ በማስከተል ሲሆን፣ ሁለተኛው ከመጀመሪያው (ከግራ ወደ ቀኝ) ቀጥሎ የሚገኘውን ተናባቢ ድምፅ በመድገምና ከእሱ ቀጥሎ /-ኣ-/ የሚል አያያዥ ምዕላድ በማስገባት ነው፡፡

ርባታ

ይህን ሁለተኛውን ተናባቢ ድምፅ ይደጋግማል የሚለውን አመለካከት ግን በደንብ ማጤን ያስፈልጋል። ቅፅሎቹ ሁለተኛውን ተናባቢ ድምፅ ይደጋገማሉ ስንል፣ ምን ማለታችን ነው? በርግጥስ ድምፁ ነወይ የሚደጋገመው? የሚደጋገመው ቃሉ ራሱ ነው፣ ብንልስ? ለምሳሌ፣ ቅጠል የሚለው ቃል ራሱን ደግሞ ቅጠል - ቅጠል ይሆንና በተደጋጋሚዎቹ ቃላት መካከል /-እ-/ የሚለውን አያያዥ አናባቢ በማስገባት ቅጠል-እ-ቅጠል "ቅጠላቅጠል" የሚለውን የስብስብ ስም አገኘን እንበል። በዚሁ መስረት ጥቁዋቁር የሚለውን ቅፅል እንየው። ጥቁር የሚለው ቃል ራሱን ደግሞ ጥቁር-ጥቁር ከሆነ በሁዋላ /-እ-/ የሚለውን አያያዥ ምዕላድ በሁለቱ ቃላት መካከል በማስገባት መጀመሪያ ጥቁር-እ-ጥቁር "ጥቁራጥቁር" ሆነ ለማለት እንችላለን። በመሰረቱ ይህን ቃል የሚለማ እማርኛ ተናጋሪም የቃሉን ተርጉም ያጣዋል ለማለት አንችልም። እባባሉም ቢሆን፣ እንገዳ የሚሆነበት አይመስለንም። ለዚህ ምክንያቱ የዚህ አይነት ለርዓት የሚከተሉ እንደ ስው-እ-ለው፣ ልጅ-እ-ልጅ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን ለስሚያውቅ ነው። ይህ ከሆነ፣ አንደ ጥቁር-እ-ጥቁር ያሉ ቅፅሎች ከስሞቹ የሚለዩት የመጀመሪያውን ቃል የመጨረሻ ተናባቢና የሁለተኛውን ቃል የመጀመሪያ ተናባቢ በመግደፋቸው ብቻ ነው።

እነዚህን የሚገደፉ ድምፆች ባለፈው ምዕራፍ ከተመለከትነው ከቀለም መዋቅር ጋር እያገናዘብን እናስባቸው። ማንኛውም ቀለም ከእንድ አናባቢና ከእንድ ወይም ከሁለት ተናባቢ ድምፆች እንደሚዋቀር አይተናል። ተናባቢዎቹ የየቀለሙ በር ከፋችና ዘጊ (ጨራሽ) አንደሆኑና አንዳንድ ጊዜም በግህድ እንደማይታዩ ገልፀን ነበር። ከዚህ አንፃር በየቅፅሉ፣ በየስሙ፣ ወደፊት እንደምናየውም፣ በየግሱ ውስጥ ይደገማል የምንለውን ሁለተኛ ተናባቢ ድምፅ፣ የየቃሉ ሳይሆን፣ የየቀለሙ ከፋች እና ጨራሽ ተናባቢ ድምፅ ነው፣ ለማለት እንችላለን። ጥቁር-እ-ጥቁር የሚለውን ቅፅል እንመርምረው።

1	2
/ጥ ቅ እ ር/	/ጥ ቅ እ ር/

የመጀመሪያው ቀለም ጨራሽ ተናባቢ ድምፅ /ር/ ነው። የሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ ደግሞ /ጥ/ ነው። የሚጎረዱትም እነዚህ ሁለት ድምፆች ናቸው። ሲጎረዱ የምናገኘው /ጥ ቅ እ/ - /ቅ እ ር/ የሚሉትን ጉርድ እህዶች ነው። ሁለቱን ጉራጆች አያይዞ አንድ ሙሉ ቃል ለመፍጠር /እ/ በመካከላቸው ይገባል። ከዚህ ሁኔታ የሚጎረዱት እንደ /ር/ እና /ጥ/ ያሉ ከፋችና ጨራሽ ተናባቢዎች ናቸው፤ በሎ መደምደም ይቻላል።

ርግጥ፣ ይህን ድምፅን የመጉረድና ቃልን የማሳጠር ሂደት የማይፈቀዱ እንደሚከተሉት ያሉ ቃላት አሉ። እነሱን ለብቻ ማየት ይቻላል።

ርባታ

1

ነጠላ	ብዙ
ሰነፍ	ሰነፍ-አች
ብልህ	ብልህ-አች
ብልጥ	ብልጥ-አች
የዋህ	የዋህ-አች
ጎበዝ	ጎበዝ-አች

አንደነዚህ ያሉት ሰነፍ - ሰነፍ፣ ብልህ - ብልህ አያሉ የሚደግሙ ብቻ ናቸው። ለምሳሌ፡

2

ሰነፍ - ሰነፉ ስራ አይሰራም

ማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ ከላይ ባየነው መሰረት አነዚህንም ቢሆን፣ በ/አ/ አማካኝነት አያጣመሩ ሰነፍ -አ- ሰነፍ "ሰነፋሰነፍ" ማለት ይቻላል።

ወደ ቁጥር ተግባር እንመለስ። /-አች/ የሚለውን ምዕላድ ያሚያስከትሉ ቅፅሎች የአንድን ሰው ወይም አንስሳ ባህሪ፣ ማለትም ሰንፍናውን፣ ጉብዝናውን፣ ብልጠቱን፣ ወዘተ፣ መግለፅ ነው። ለለሆነም፣ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ የባህሪ ቅፅል በመባል ይታወቃሉ። ይሁን እንጅ፣ /-አች/ የሚያመለክተው የባህሪውን መጠን ሳይሆን፣ የባህሪውን ባለቤቶች ቁጥር ነው። ባህሪ በአይነት አንጅ በአህዝ ሊቆጠር የሚችል ነገር አይደለምና። በአህዝ ሊቆጠር የሚችለው የባህሪው ባለቤት የሆነው ነገር ነው። ስለዚህም ሰነፎች ስንል፣ ሰነፍ የሆኑ ሰዎች ማለታችን ነው። /-አች/ የሚለው ምዕላድ ሰው የሚለውን ስም አንጅ፣ ሰነፍ የሚለውን ቅፅል አያመለክትም።

ከፍ ሲል በተገለፀው ሁኔታ ሙሉ አካላቸውን የሚደጋግሙትና ድምፅ የሚጎርዱት አንደሚከተሉት ያሉት ናቸው።

3

ነጠላ	ብዙ
ረዥም	ረዥ-ኡ-ዥም
ነጭ	ነጭ-ኡ-ጭ
ቀይ	ቀይ-ኡ-ይ

አነዚህ የአንድን ነገር የቀለም አይነት ስለሚያመሰክቱ፣ የአይነት ቅፅል ተብለው ከላይ ካየናቸው የባህሪ ቅፅሎች ሊለዩ ይችላሉ። ቅፅሎቹ የሚጠቁሙት የሰዎችን የቀለም አይነት ሲሆን፣ /-አች/ የሚለውን ምዕላድ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ስለዚህም ነጭ-አች፣ ጥቁር-አች፣ ወዘተ፣ በማለት የሰዎቹን ብዛት መግለፅ ይቻላል። እንደነዚህ አይነት ቅፅሎች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ በቂ ቅፅል ይባላሉ። በቂ የሚባሉበት ምክንያት ያለምንም ስም ብቻቸውን ሊቆሙ መቻላቸው ነው። ለምሳሌ፣ *ጥቁር ህዝቦች* በማለት ፋንታ፣ *ጥቁሮች* ብሎ ህዝቦች የሚለውን ስም መግደፍ ይቻላል። ህዝቦች የሚለው ስም /-አች/ የሚለውን

ርባታ

የቁጥር ምዕላድ ለቅፅሉ እየሰጠ ከቦታው ሊሰወር ይችላል። የሰሙን ባህሪ የያዘው ቅፅልም ስሙ ለሚፈፅመው ተግባር ብቁ እንደሆነ ተቆጥሮ፣ በቂ ቅፅል ሊባል ችሎአል።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ተናባቢ ድምፃቸውን እየደጋገሙ የአንድን ነገር አካላዊ መጠን የሚገልፁ ቅፅሎችም አሉ። እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ነጠላ	ብዙ	4
ትልቅ	ትል-ኣ-ልቅ	
ትንሽ	ትን-ኣ-ንሽ	
ረዥም	ረዥ-ኣ-ዥም	
ወፍራም	ወፍ-ኣ-ፍራም	
ቀጭን	ቀጭ-ኣ-ጭን	

እንደነዚህ ያሉት ቅፅሎች፣ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው መጠንን ብቻ ሳይሆን፣ ወገንነትንም ሊያመለክቱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ <u>ትል-ኣ-ልቅ</u> የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ የሚያመለክተው ከእንድ ስብስብ ውስጥ፣ የትልቅ ወገን የሆኑትን ነገሮች ነው። ትልቅ፣ ትልቅ የሆኑ ነገሮችን ብዛት ለማመልከት ሲፈለግ፣ ትል-ኣ-ልቅ በሚለው ላይ /-አችች/ን መጨመር ያስፈልጋል። ይህንን ስናደርግ ትላልቆች የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን። ስለ ትርጉሙ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ትላልቁን ዛፍ ቁረጠው 5
(ለ) *ትላልቁን ዛፎች ቁረጣቸው

ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም። ለዚህም ምክንያቱ ትላልቅ የሚለው ቅፅልና ዛፎች የሚለው ስም በቁጥር ስምሙ አለመሆናቸው ነው። ዛፎች የሚለው ስም የብዙ ቁጥር (ጥቂት) ስለሆነ፣ እሱን የሚገልፀው ቅፅልም እንደዚሁ የብዙ ቁጥር መሆን አለበት። ትላልቅ የሚለው የብዙ ቁጥር ቢሆን ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያገኝ ነበር። የአረፍተ ነገሩ መዘባት ቅፅሉ ብዛትን ሳይሆን፣ ወገንን ብቻ እንደሚያመለክት ያሰገነዝባል። ብዛትን እንዲገልፅ ከፈልግን፣ በቅፅሉ ላይ /-አችች/ን መጨመር ይኖርብናል። ይህን ስናደርግ፣ የሚከተለውን እናገኛለን፣

ትላልቆቹን ዛፎች ቁረጣቸው 6

ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው የትልቅ ወገን የሆኑ ጥቂት ዛፎችን ነው።

እንደ ትላልቅ ያሉ ቅፅሎች /-አችች/ የሚለውን ምዕላድ ሳያስከትሉ ብዛትን የሚገልፁበት ሁኔታም አለ። ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ትልቅ ልጅ አለው 7
(ለ) ካሳ ትላልቅ ልጆች አሉት
(መ) ?ካሳ ትልቅ ልጆች አሉት

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ልጅ የሚለው ስም ነጠላ በመሆኑ፣ ትልቅ የሚለው ቅፅልም እንደዚሁ ነጠላ ሲሆን ችለእል። በሁለተኛው ምሳሌም ልጆች የሚለው ስም የብዙ ቁጥር በመሆኑ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ የብዙ ቁጥር ነው፤ ለማለት ይቻላል። ብዙነቱን የሚያመለክተው ግን /-ኦች/ን በማስከተል ሳይሆን፣ ራሱን በመደጋገም ነው። ከዚህም የምንረዳው ድግግሞሽ አንዳንድ ጊዜ ወገንን፣ ሌላ ጊዜ ብዛትን የሚያመለክት መሆኑን ነው። ወገንን የሚያመለክተው ከቅፅሉ ጋር የሚዋቀረው ስም በምሳሌ 6(ሀ) እንደሚታየው የነጠላ ቁጥር ስም ሲሆን ነው። ብዛትን የሚያመለክተው ደግሞ ስሙ የብዙ ቁጥር ሲሆን ነው። ባጭሩ ድግግሞሽ ከነጠላ ስም ጋር ወገንን፣ ከብዙ ቁጥር ስም ጋር ብዛትን ያመለክታል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። የምሳሌ (መ) መዛባት የሚያሳየው ይህንኑ የስሞችንና የቅፅሎችን የቁጥር ለምሙነት ነው። ወደሚቀጥለው እንሂድ።

ግሰ

ግሶች ለመደብ፣ ለያታ፣ ለቁጥር፣ ለአንቀፅ፣ ለስልት እንዲሁም ለጊዜ የተለያዩ ቅጣይ ምዕላዶችን፣ በማለቀደም ወይም በማለከተል፣ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በማጥበቅ ወይም ባለማጥበቅ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ረዳት ግሶች ጋር በመጣመር ቅርፃቸውን ሊለዋውጡ ይችላሉ። ዝርዝሩን በዚህ ንዑስ ክፍል እንመለከታለን። ከዚያ በፊት ግን አንድ ነገር ማንሳት አለብን። ይኸውም ግሶች የ(ሀ) አና የ(ለ) ክፍል ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ነው። የ(ሀ) ክፍል የሚባሉት ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በቀዳማይ አንቀፅ ብቻ የሚያጠብቁ ሲሆኑ፣ የ(ለ) ክፍል የሚባሉት ይህንኑ ተናባቢ ድምፅ በማንኛውም አንቀፅ የሚያጠብቁ ናቸው። ለምሳሌ ለረቀ ብለን ይለር-ቃል ስንል፣ [ር] በመጀመሪያው ላይ ሲጠብቅ፣ በሁለተኛው ላይ አይጠብቅም። ፈለገ ብለን ይፈል-ጋል ስንል ግን [ል] በሁለቱም ላይ ይጠብቃል። ከዚህም የተነሳ እንደ ሰረቀ ያሉትን የ(ሀ)፣ እንደ ፈለገ ያሉትን ደግሞ የ(ለ) ክፍል ግሶች ብለን እንለያቸዋለን[6]። የተናባቢው መጥበቅ ወይም አለመጥበቅ የየግሱን የአንቀፅ አይነት ይወስናል። ይህን ወደ ሁዋላ እናየዋለን።

---

[6] ሶስተኛ የግስ ክፍል አንዳለ አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ። ይህም የባረከ አይነት ግሶችን የሚያዝ ነው። መሰረቱም የተናባቢ ጥብቀት ላይሆን፣ የአናባቢ አይነት ነው። ይኸውም የሌሎች ግሶች የመጀመሪያ አናባቢ /ኧ/ ሲሆን፣ የዚህ ክፍል ግሶች የመጀመሪያ አናባቢ /አ/ መሆኑና አንደ (ለ) ክፍል ግሶች፣ በካልዓይ አንቅፅ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን ማጥበቃቸው ነው። ይሁን አንጅ፣ ጥብቀቱ በሌሎቹ ቅርፆች የሚታይ ሳይሆን፣ በዚሁ አንቀፅ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። የሚከትሉትን አንመልከት።

/ፍ<u>ልል</u>ኧ-/	/ብ<u>ለር</u>ኧክ-/
/ይ-ፍ<u>ልል</u>-ግ/	/-ይ-ብ<u>ለር</u>-ክ/
/ፍ<u>ልል</u>-ግ/	/ብ<u>ለር</u>ክ/
/ም<u>ኧ</u>-ፍ<u>ልል</u>ኧግ/	/ም<u>ኧ</u>ብ<u>ለር</u>ኧክ/

ርባታ

መደብ

ሰሰ ሰሞች ሰንወያይ እንዳወሳነው፣ መደብ ሰዎች በሚነጋገሩበት ወቅት ከሚኖራቸው ሚና ጋር የተገናዘበ ሰማዊ ባህሪ ነው። በንግግር ወቅት፣ የተነጋጋሪዎች ሚና፣ ተናጋሪነት፣ ተነጋሪነት ወይም አድማጭነትና አንዳንድ ጊዜም ታዛቢነት ነው። ታዛቢ ባሰበት እንነጋገር የሚባሰውም ሰዚሁ ነው። ተናጋሪ የንግግሩ ምንጭ ሰሰሆነ፣ እንደኛ መደብ ይባላል። የሚናገረውም <u>እኔ</u> እያሰ ነው። ተነጋሪው ነገሩ የሚነገረው ሰው ነው። ሰሰዚህም ሁሰተኛ መደብ ይባላል። "እንተ ሰማ!" እየተባሰ ይነገረዋል። ከነዚህ ከሁሰቱ ውጭ የሆነ በው ካለ፣ ያ ሰው ሶሰተኛ መደብ ይባላል። <u>እሱ</u> ወይም <u>ይኽ</u> ፣ ወዘተ፣ እየተባሰ ይጠቆማል። እነዚህ ሶሰት መደቦች በሁሰት አይነት ቅርፅ ይከሰታሉ። እንደኛው በነፃ ምዕላድ መልክ ሲሆን፣ ሌላኛው በጥገኛ ምዕላድ ቅርፅ ነው። በመጀመሪያው ቅርፃቸው ሲከሰቱ፣ መደበኛ ተውላጠ ሰም ይባላሉ። እንደ ሰሞች ሁሉ ለቁጥርና ለያታ የተሰያዩ ምዕላዶችን ሊያሰክትሉ ወይም ሊያሰቀድሙ ይችላሉ። ዝርዝሩ እንደሚከተሰው ነው።

መደብ	ነጠላ	ብዙ	አክብሮት
1ኛ	አን-ኤ	እነ-አን-ኤ [እኛ]	
2ኛ ተ	አን-ተ	እነ-አንተ	አንት-ኡ
አ	አን-ት-ኢ [ሳንቺ]		
3ኛ ተ	እርሰ-ኡ	እነ-እርሰ-ኡ	እርሰ-እ [እርሶ]
እ	እርሰ--ኡ-ሳ [እርሰዋ]		

1 የተውላጠ ሰም ሰንጠረዥ

ባለፈው ንውሰ ክፍል ሰለ ሰሞችና ቅፅሎች የርባታ ሰርዓት ሰንወያይ እንደገሰፅነው፣ /-ኢ/ እና /-ኢ/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የሁሰተኛና የሶሰተኛ መደብ የአንሰታይ ያታ ምዕላዶች ናቸው። /-ኢ/ የአነደኛ መደብ፣ /-ተ/ የሁሰተኛ መደብ ፣ /-ኡ/ የሶሰተኛ መደብ ምዕላድ ናቸው። /እንንኧ-/ እጉዋዳኝ የጥቂት ቁጥር ምዕላድ ነው። የእክብሮት ምዕላዶቹም ለሁሰተኛ መደብ /-ኡ/፣ ለሶተኛ

/ፍኧልልኢግኢ/ /ብኢርእክኢ/

በግልፅ እንደሚታየው፣ /ል/ በሁሉም ቅርፆች ሊጠብቅ፣ /ር/ ግን በሁለቱ ብቻ ነው የጠበቀው። ይህ ሁኔታ እንደ <u>ባረከ</u> ያሉ ግሶች የ(ሀ) ከፍል ግሶች አካል ናቸው፣ የሚያሰኝ ነው።

መደብ /-አ/ ናቸው፡፡ /-ኤ/ የአንደኛ መደብ ምዕላድ ለመሆኑ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቤት-ኤ 2
ቤት-ህ
ቤት-ኡ

ሶስቱ መደቦች የተለያየ ቅጣይ ምዕላድ እንዳላቸው ግልፅ ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ <u>እንትን</u> እና <u>እንትና</u> የሚባሉ ተውላጠ ሰሞችም አሉ፡፡ የመጀመሪያው አንድን ነገር በለሙ ለመጥራት ሳንፈልግ በንቀር፣ ወይም ሰሙ ሲረሳን በምትክነት የምንጠቀምበት ተውላጠ ሰም ነው፡፡ ለነገር እንጅ፣ ለሰው አይሆንም፡፡ ለሰው ሰም ምትክ የሚሆነው <u>እንትና</u> የሚለው ነው፡፡ አንድን ሰው <u>እንትና</u>! ወይም በቁልምጫ <u>እንትናዬ</u>! ብሎ ለመጥራት ያገለግላል፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያውን ብቻ ተውላጠ-ነገር ልንለው እንችላለን፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

ከእንትናችን ውስጥ እንትን ገብቶበት 3
እንትን አምጭልኝ እንትን አልበት
አንችም ነይልኝ እንትን ትይልኝ

ባገር ቤት እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ አባባል ነው፡፡ አንድ ጭሰኛ ገበሬ ባቄላው ውስጥ ወጥመድ አጥምዶ ያድራል፡፡ ጥዋት ሲሄድ ሚድያቄዋ ይዛ ያገኘዋል፡፡ ባለቤቱን ጠርቶ ቢላዋ ይዛ እንድትመጣና እንድትረዳው ይፈልጋል፡፡ በግልፅ እንዳይነግራት ባለመሬቱ፣ ግለትም ጌታው፣ በአንግድነት መጥቶ ቤቱ ውስጥ ሰለሚገኝ፣ ጉዳዩን ሲሰማበት ሆነ፡፡ ከሰማ ደግሞ ይወሰድባቸዋል፤ ወጥመዱ የተጠመደበት መሬት የእሱ ነውና፡፡ ስለዚህም ገበሬው ባለቤቱን ይጠራትና፣ ከእንትናችን ውስጥ ...፣ አላት ይባላል፡፡ ሞኝ ጌታ ካልሆነ በስተቀር፣ ይችን እንኩዋ መረዳት አያቅተውም! ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው መደቦች ከላይ እንደሚታዩት ባሉ መደበኛ ተውላጠ ሰሞች ብቻ ሳይሆን፣ በጥገኛ ምዕላድነትም ይከሰታሉ፡፡ በዚህ መልክ የሚከሰቱት አፀፋ ተውላጠ ሰም ይባላሉ፡፡ አፀፋ የሚያሰኛቸው የመደበኛዎቹ እጣፊ ወይም አምሳል መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህም የሚከሰቱት በሰሞችና በግሶች ላይ ነው፡፡ በግሶች ላይ የሚከሰቱት በሁለት መልክ ነው፡፡ በቀዳማይ አንቀፅና ቦዝ አንቀፅ በሚባሉት አምዱን ተከትለው፣ በካልዓይ አንቀፅ ደግሞ አምዱን ቀድመው ይገባሉ፡፡ ሰለ አንቀፅ ወደ ሁዋላ እንወያያለን፡፡ አሁን ሁኔታውን <u>ሰበረ</u>

ርባታ

በሚሰው ግሰ አምድና <u>ሰብራት</u> በሚለው ሰም አማካኝነት ከሚከተለው ሰንጠረዥ አንመልከት፡፡

መደብ	ካልዓይ	ቀዳማይ		ሰም	
1ኛ	እ-ሰብር	ሰበር-ኩ[7]		ሰብራት-የ	
2ኛ ተ	ት-ሰብር	ሰበር-ህ		ሰብራት-ህ	
እ	ት-ሰብር-ኢ	ሰበር-ሽ	< /ሰበር-ህ-ኢ/	ሰብራት-ሽ	< /ሰብራት-ህ-ኢ/
3ኛ ተ	ይ-ሰብር	ሰበር-ኧ		ሰብራት-ኡ	
እ	ት-ሰብር	ሰበር-ኧች	</ሰበር-ኧት-አ/	ሰብራት-ዋ	< /ሰብራት- ኡ-አ/
ብ	አ-ን-ሰብር	ሰበር-ን		ሰብራት-አች[8]-ን	
	ት-ሰብር-ኡ	ሰበር-ኣችሁ		ሰብራት-አች-ሁ	</ሰብራት-ኣች-ህ-ኡ/
	ይ-ሰብር-ኡ	ሰበር-ኡ		ሰብራት-ኣች-ው	/ሰብራት-አች-ኧ-ኡ/

4 የመደብ፣ የቁጥርና የዖታ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ በካልዓይ አንቀፅ /እ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የአንደኛ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች ናቸው፡፡ /-ኢ/ የአንስታይ ዖታ ምዕላድ ሰትሆን፣ አገባብዋም አምዱን ተከትላ ነው፡፡ /-ን/ የአንደኛ መደብ፣ /-ኡ/ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላዶች ናቸው፡፡ መደብ፣ ቁጥርና ዖታ በተሰያዩ ምዕላዶች አንደተገለፁ መረዳት ይቻላል፡፡ በቀዳማይ አንቀፅ ደግሞ እነዚሁ የመደብ ምዕላዶች /-ኩ/፣ /-ህ/ እና /-ኧ/ በሚሰ ቅርፆች በአምዱ መድረሻ ላይ ይታያሉ፡፡ የዖታና የቁጥር ምዕላዶቹ በተናጠል ላይሆን ከመደብ አመልካቾቹ ጋር አየተዋህዱ ገብተዋል፡፡ በሰሙ ላይ ደግሞ የመደብ ምዕላዶቹ /-የ/፣ /-ህ/ እና /-ኡ/ ሆነው ይታያሉ፡፡

በግሶቹ ላይ የሚታዩት የመደብ፣ የቁጥርና የዖታ ምዕላዶች በአንድነት የባለቤት አፀፋ ይባላሉ፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት የሆነን ሰም የሚያመለክቱ ወይም የሚተኩ ምዕላዶች ናቸው፡፡ አነሱ በግሱ ላይ ሰለሚታዩ፣ ሰሙ በግሀድ ላይከሰት ይችላል፡፡

አንድ ሰም የአረፍተ ነገር ባለቤት መሆኑ የሚታወቀው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚገኝበት ቦታ ሲሆን፣ ሁለተኛው በግሱ ላይ በሚታየው የአፀፋ ምዕላድ አማካኝነት ነው፡፡ በሰሙ ላይ የሚታዩት አፀፋዎች የሚያመለክቱት፣ ሰሙ የሚጠቁመው ነገር የማን መሆኑን ሰለሆነ፣ በዚሁ መሰረት አገናዛቢ አፀፋ እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡

---

[7] በቀዳማይ አንቀፅ የአንደኛ መደብ ምዕላድ ቅርፅ /-ሁ/፣ የሁለተኛ መደብ ደግሞ /-ህ/ ሆኖ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው አምዱ በአናባቢ የሚጨርስ ሲሆን ነው፡፡

[8] /-አች-/ ለአገናዘቢ ሰሞች ላይ የሚገኘው የብዙ ቁጥር ምዕላድ ነው፡፡ በግሶች ላይ የሚገኝበት ምክንያት፣ የቀዳማይ አንቀፅ ግሶች ከሰም የመጡ ስለሆነና፣ የሰሙ የብዙ ቁጥር ምዕላድም አብሮ በመምጣቱ ነው፣ የሚል ነው፡፡ ዝርዝሩን ከሀድሰን (1981) ይመልከቱ፡፡

ርባታ

ከላይ እንደሚታየው፣ መደቦች ነጠላ ወይም ብዙ ተብለው በቁጥር፣ እንዲሁም ተባዕታይ ወይም አንስታይ ተብለው በፆታ ይለያሉ። ይህን ቀደም ሲል በለሞች ርባታ ላይም አይተነዋል። አሁንም በግሶች ላይ እያየነው ነው። ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ የአነስታይ ፆታ ምዕላድዋ /-ኢ/ ስትሆን፣ የሶስተኛ መደብ የአንስታይ ምዕላድ ደግሞ /-ት/ ነች። አሰዋም የምትገኘው በካልዓይ አንቀፅ አምድ መነሻ ላይ እና በቀዳማይ አንቀፅ አመድ መድረሻ ላይ ነው። በዚህ አምድ ከፆታ ምዕላድዋ ከ/-ኢ/ ቀድማ ትገኛለች። ሁለት የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች አሉ ማለት ነው። አንደኛው /ይ-/ን እና /-ኧ-/ን ይዞአል። የመጀመሪያው በካልዓይ፣ ሁለተኛው በቀዳማይ አንቀፅ ይገኛል። ሁለተኛው /-ት-/ን ብቻ ይዞአል። አሰዋም በሁለቱም አንቀፆች ትገባለች። ይህም አንደሚከተለው ነው።

ካልዓይ	ቀዳማይ	
/ይ-ሰኧብር-/	/ሰኧብብኧር-ኧ/	5
/ት-ሰኧብር-/	/ሰኧብብኧር-ኧ[9]-ት-ኢ/	ሰበረች

በቀዳማይ አንቀፅ፣ የግሱን አምድ ተከትላ ለትመጣ፣ /-ት-/ በ/-ኢ/ ምክንያት ወደ ላንቃዊነት ትለወጥና [ች] ትሆናለች።

እነዚህ ባለፈው ክፍል ለለ ስሞች ርባታ ለንወያይ ያየናቸው የፆታ ምዕላዶች ናቸው። በዚያ ላይ፣ ማንኛውም ሰም ተባዕታይ ወይም አንስታይ እንደሆነ ገልፀን፣ የወልና የግዑዝ ፆታ የሚባሉ ክፍሎች እንደሌሉ ጠቁመን ነበር። በዚህ በግሱ ርባታ ውስጥ የምናየው ሁኔታም ይህን የሚያረጋግጥ ነው። በግሱ ውስጥ የምትገኘው የአንስታይ ፆታ ምዕላድ /-ኢ/ ብቻ ነች[10]። የወልና የግዑዝ የሚባሉ የፆታ ክፍሎች ቢኖሩ ኖሮ፣ እንደ አንስታይ ፆታዋ ምዕላድ በተለያየ ቅርፅ በግሱ ርባታ ላይም መታየት ነበረባቸው።

መደብ አመልካች ምዕላዶች ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የሚታዩት ብቻ አይደሉም። እነዚህ ባለቤት ወይም ባለገንዘብ የሆነን ሰም መደብ የሚያመለክቱ ናቸው። ከነዚህ ሌላ ተሳቢ የሆነን ሰም መደብ የሚያመለክቱ ምዕላዶችም አሉ። እነዚህ ግን በሁሉም ግሶች ላይ ሳይሆን፣ ሳቢ በሚባሉት ላይ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ሳቢ ግሶች የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር የሚቀናጁ ናቸው። አቀነጃጀቱን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን። የአፀፋዎቹን አይነት ግን አሁንም ሰበረ በሚለው ሳቢ ግስ አማካኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን።

---

[9] ይህ አናባቢ /-ኧ-/ በስነ-ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ምክንያት የገባ አናባቢ ድምፅ ነው።

[10] ይህን የምንለው የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችውን /-ኣ/ ሳንዘነጋ ነው።

ርባታ

መደብ		ነጠላ		ብዙ	
1ኛ		ሰበር-እ-ኝ		ሰበር-እ-ን	
2ኛ	ተ	ሰበር-እ-ህ		ሰበር-እ-ኣችሁ	</ሰበር-እ-ኣችች-ህ-ኡ/
	አ	ሰበር-እ-ሽ	</ሰበር-እ-ህ-ኢ/		
3ኛ	ተ	ሰበር-እ-ው		ሰበር-እ-ኣችሁ	</ሰበር-እ-ኣችች-ኡ/
	አ	ሰበር-እ-ኣት			

6. የተሳቢ ምዕላድ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚታየው ምዕላድ /-እ/ ሲሆን፣ እሱም ከፍ ሲል ያየነው የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው። ከእሱ ቀጥሎ የሚገኙት የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው። ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና ከሶስተኛ መደብ በስተቀር፣ የሌሎቹ አፀፋዎች ቅርፅ ከባለቤት አፀፋ ምዕላዶች ጋር አንድ አይነት ነው። ለምሳሌ፣ የአንደኛ መደብ የባለቤት አፀፋ የብዙ ቁጥር /-ን/ ሲሆን፣ የተሳቢውም እንደዚሁ /-ን/ ነው።

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን አንድ ጉዳይ አለ። ይኸውም የምዕላዶቹን ቅደም-ተከተላዊ አገባብ የሚመለከት ነው። ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው ሁል ጊዜም የባለቤት አፀፋ ሲሆን፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚመጣው የተሳቢው አፀፋ ነው። የባለቤቱም ሆነ የተሳቢው አፀፋ የመደብና የቁጥር ወይም የፆታ ምዕላድ ውሁድ ነው። ምዕላዶቹ ከመዋሀዳቸው በፊት የሚገኙበት ቅደም-ተከተላዊ ለርዓትም መደብ አመልካቹ ቀድሞ፣ ቁጥር ወይም ፆታ አመልካቹ አሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው። ለምሳሌ፣ /-ሽ/ የሚለው የሁለተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ፣ የመደብ አመልካቹ /-ህ/ እና የአነስታይ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ ውሁድ እንደሆነ፣ ከፍ ሲል ተገልፆአል። የእነዚህ ምዕላዶች ቅደም-ተከተላዊ አቀማመጥም /-ህ-ኢ/ ሲሆን፣ ወደ [-ሽ] የሚለወጡት በለነ-ድምፅ-ልሳናዊ ሂደት ነው። ሂደቱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው ሊሆን ይችላል። ግን ወቅታዊነትም አለው። ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ በየግሱ የትዕዛዝ አንቀፅ አምድ መድረሻ ላይ ብቻዋን ትገኛለች። ይህም ስበሪ (/ስ - ብእር-ኢ/) ስንል ነው።

እሰካሁን ያየናቸው ስማዊ የተሳቢ አፀፋዎች ሊባሱ ይችላሉ። የሚያመለክቱት ተሳቢ የሆነ ስማዊ ሀረግን ነው። ከነዚህ ሌላ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች የሚባሉ አሉ። አነዚህ የሚያመለክቱት የተለያየ ተውሳክ ግስዊ ተግባር ያላቸውን መስተዋድዳዊ ሀረጎች ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [በአዲሱ ብዕር] ደብዳቤ ፃፍ-እ-በት 7
(ለ) ካሳ [ገነትን] ገንዘብ ወስድ-እ-ባት </ብ-እት/

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው /እ/፣ የባለቤቱ አፀፋ ነው። ከእሱ ቀጥሎ የሚገኘው /-በት/ የሚለው የመስተዋድድ ሀረግ አፀፋ

ነው። ይህም ከ/ብ/ እና ከ/-ት/ የተጣመረ ድርብ ምዕላድ ነው። አፀፋነቱም [በአዲሱ ብዕር] ሰሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ሀረጉ [በ] የሚለው መሰተዋድድና [አዲሱ ብዕር] የሚለው ሰማዊ ሀረግ ቅንጅት ነው። የስማዊ ሀረጉ አፀፋ /-ት/ ነች። አሰዋም ከመሰተዋድዱ ከ[በ] ጋር ተቀናጅታ /-በት/ ሆናለች። በሁለተኛው ምሳሌ፣ [ገነትን] የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መሰተዋድዱ [ን][11] ሲሆን፣ ከአሱ ጋር የተዋቀረው ደግሞ ገነት የሚለው ሰም ነው። በግሱ ላይ ይህን ሀረግ የሚያመለክተው አፀፋ /-ባት/ ነው። አሱም የ[በ] እና ገነት የሚሰው ሰም አፀፋ የሆነችው የ/-አት/ ቅንጅት ነው። ይህች ምዕላድ ከፍ ሲል ባየነው የግሰ ዝርዝር ርባታ ውሰጥም በተሳቢ አፀፋነት ትታያለች።

መሰተዋድዳዊ አፀፋዎች በግሶች ለሚገለፁ ተግባራት ተሳጅ ወይም ተጠቃሚ መሆንን ሊያመለክቱ ይችላሉ። ተሳጅነት [በ] በሚለው፣ ተጠቃሚነት ደግሞ [ለ] በሚለው መሰተዋድድ አማካኝነት ይገለፃል። ሰለሁኔታው የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ እናቱ መጡ-በት 8
(ለ) ካሳ እናቱ መጡ-ለት

በመጀመሪያው ምሳሌ /-በት/ የሚለው መሰተዋድዳዊ አፀፋ በእናቱ መምጣት ካሳ ተሳጅ መሆኑን ይገልፃል። መመጣታቸው እሱን ችግር ላይ የሚጥል ሲሆን ይችላል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ የተገለፀው የዚህ ተቃራኒ ነው። ካሳ በእናቱ መምጣት ተጠቃሚ ነው። ይህን ለማመልከት /-ለት/ የሚለው አፀፋ በግሱ ላይ ይታያል። በዚሁ መሰረት [በ]ን እና [ለ]ን የተሳጅና የተጠቃሚ መሰተዋድድ አፀፋ ልንላቸው እንችላለን።

ከፍ ሲል እንደጠቆምነው፣ የተሳቢ አፀፋዎች የሚገኙት በሳቢ ግሶች ላይ ነው። የመሰተዋድድ አፀፋዎች ግን ነው ከሚለው የመሆን ግሰ በስተቀር በሌላ በማንኛውም ግስ ላይ ይገኛሉ። ይሁን አንጅ ከሳቢ ግሰ ላይ በሚገኙበት ጊዜ፣ የተሳቢው አፀፋ በቦታው ሊገኝ አይችልም። ግሱ የተሳቢ አፀፋን በሚያሳይበት ጊዜ ደግሞ የመሰተዋድድ አፀፋው በቦታው አይታይም። ሰለዚህም፣

*ካሳ መፅሀፉን ለእኔ ሸፈን-ኝ-ው-ልኝ 9

ማለት አያቻልም። ለዚህም ምክንያቱ ግሱ /-ው/ የሚለውን የተሳቢ አፀፋና /-ልኝ/ የሚለውን የመሰተዋድድ አፀፋ በማሳየቱ ነው። ማሳየት የሚችለው ከሁለቱ አንዱን ብቻ ነው። ይህም ግሱ ከባለቤቱ አፀፋ ሲላ፣ አንድ ተጨማሪ

[11] /-ን/ እንደ ተሳቢ አመልካች ብቻ ላትሆን፣ አንደ መሰተዋድድም ታገለግላለች። ለምሳሌ፣ ወደ አገሩ ሄደ፣ በማለት ፋንታ አገሩን ሄደ፣ እንላለን። አገሩን ከሚለው ላይ የምትታየው /-ን/ ወደ በሚለው መሰተዋድድ ፋንታ የገባች ነች። መኪናውን አፈር ጫነበት፣ ሰንልም በመኪናው አፈር ጫነበት፣ ማለታችን ስለሆነ፣ መኪናውን በሚለው ስም ላይ የምትታየው /-ን/ በመኪናው በሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ መነሻ ላይ የምትገኘው የ/በ/ ምትክ ነች። በዚህ አይነት /ን/ የተለያዩ መሰተዋድዶችን ስለምትተካ፣ ተውላጠ-መሰተዋድድ ልትባል ትችላለች።

ርባታ

አፀፋ ብቻ የመያዝ ችሎታ አንዳለው ያሳያል። የባለቤቱ አፀፋ ምን ጊዜም አይቀሬ ነው። የተሳቢ አፀፋዎች ግን ሊቀሩ ይችላሉ። በጥቅሉ የአማርኛ ግስ ቅርፅ የሚከተለው ይመሳሳል ብሎ መቋቋጨት ይቻላል።

(ሀ) አምድ-የባለቤት-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ 10
ምሳሌ፣ ሰበር-ኧ-ሽ < /ሀ-ኢ/
ሰበር-ኧ-ብኝ

(ለ) የባለቤት አፀፋ-አምድ-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ
ምሳሌ፣ ይ-ሰብር-ሽ- </ሀ-ኢ/
ይ-ሰብር-ብኝ-

የመጀመሪያው የቀዳማይ፣ ሁለተኛው የካልዓይ አንቀፅን የግሰ ስርዓት ይከተላል። ሀሁለቱም አንቀፆች መደብና ዖታ ወይም መደብና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች አንድም ተለያይተው አለያም ተዋህደው ሊከሰቱ ይችላሉ። ተዋህደው የሚከሰቱት አምዱን ተከትለው ሲመጡ ነው። ይህም በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፅ ነው። ስለ አንቀፅ ከዚህ ቀጥለን እንወያያለን።

አንቀፅ

አንቀፅ በአንድ ግስ የሚገለፅ ድርጊት ወይም <u>ሁኔታ</u> መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ በመጨረሻም ተፈፅሞ ያለቀ ወይም ያላለቀ መሆኑን የሚያሳይ ሰዋስዋዊ ባህሪ ነው። የተፈፀመ ድርጊትን የሚገልፅ ግሰ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ፣ ያላለቀ ድርጊትን የሚገልፅ የካልዓይ አንቀፅ ግሰ ይባላል። የሁለቱ አንቀፆች ቅርፅም የተለያየ ነው። ልዩነቱን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት።

<u>ቀዳማይ</u>		<u>ካልዓይ</u>		
/ሰኧብብኧር-/	ሰበር-	/-ሰኧብር-/	-ሰብር-	1
/ግኧድድኧል-/	ገደል-	/-ግኧድል-/	-ገድል-	
/ፍኧልልኧግ-/	ፈለግ-	/-ፍኧልልግ-/	-ፈልግ-	
/ዝኧምምኧር-/	ዘመር-	/-ዝኧምምር-/	-ዘምር-	

አነዚህ የመደብ፣ የቁጥር ወይም የዖታ ምዕላድ የቀራቸው አይነተኛ የአንቀፅ አምዶች ናቸው። ቅርፃቸውም እንደሚከተለው ነው።

ቀዳማይ : / ተ$_1$ኧተ$_2$ተ$_2$ኧተ$_3$-/ 2
ካልዓይ : /-ተ$_1$ኧተ$_2$(ተ$_2$)ኧተ$_3$ -/

የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ያጠብቃል። ከመነሻው ተናባቢ በሁዋላና ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /ኧ/ የሚለውን አናባቢ ያስገባል። የካልዓይ አንቀፅ አምድ ደግሞ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ ብቻ ይህንኑ አናባቢ

ያስገባል። ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ሊያጠብቅ ወይም ላያጠብቅ ይችላል። ተናባቢው ($ተ_2$) በቅንፍ ውለጥ የተቀመጠውም ይህንኑ ሀኔታ ለማሳየት ነው። እነዚህ ሁለት አንቀፆች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከእነሱ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተለያዩ የድርጊትና የሁነት አይነቶችን የሚገልፁ አንቀፆች መፍጥር ይቻላል። ከነዚህ መካከል አራቱን ብቻ እንመለከታለን። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

(ሀ) አቃጅ አንቀፅ 3
(ለ) ወጣኝ አንቀፅ
(መ) ቀጣይ አንቀፅ
(ሰ) ጨራሽ አንቀፅ

አቃጅ አንቀፅ

አቃጅ አንቀፅ የሚባለው አንድ ድርጊት ይፈፀም ዘንድ መታቀዱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ልዩ ምለክቱ /ል-/ የሚል ምዕላድ ነው። የሚመለረተው በካልዓይ አንቀፅ ላይ ነው። የሚከተለው የዚህ አንቀፅ ምሳሌ ነው።

ካሳ አንጨት <u>ል-ይ-ፈልጥ</u> ነው = <u>ሊፈልጥ</u> 4

ምሳሌው፣ ካሳ አንጨት ለመፍለጥ ማቀዱን ያመለክታል። ይህን የምታመለክተው ምዕላድ የባለቤት አፀፋ የሆነችውን /-ይ/ ቀድማ በመነሻ ላይ ገብታለች።

ወጣኝ አንቀፅ

የታቀደ ነገር ሳይጀመር አይቀርም፣ ይዋል ይደር አንጅ። ሲጀመር፣ የድርጊቱ ግላጭ ከሆነው አምድ ቀጥሎ <u>ጀመር</u> የሚል ምዕላድ ይገባል። ይህም <u>ጀመረ</u> ከሚለው ግስ ጋር ተዛምዶ ይኑረው አንጅ፣ የተለየ ተግባር ያለው አህድ ነው። ተግባሩ ለወጣኙ አንቀፅ ረዳት መሆን ነው። ዋናው አምድ የተመለረተው ከአይነተኛው የካልዓይ አንቀፅ አምድ ላይ ነው። የሚከተለውን ምሳሌ እንመለከት።

ከሳ አንጨት <u>ይ-ፈልጥ ጀመር</u> 5

ምሳሌው ድርጊቱ መጀመሩን ብቻ ያመለክታል። ከዚያ በሁዋላ ስላለው ሁኔታ የሚነግረን ነገር የለም። የተጀመረው ድርጊት ሊቀጥል ወይም ሊቋዋረጥ ይችላል። የሚቀጥል ከሆነ የተለየ መግለጫ ይኖረዋል። ይህን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ርባታ

ቀጣይ አንቀፅ

ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ቀጣይ አንቀፅ አንድ የተጀመረ ድርጊት ሳይቋዋረጥ መቀጠሉን ያመለክታል። ልዩ ምልክቱ /እይይኡ-/ የሚል ምዕላድ ነው። መስረቱ ደግሞ የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ነው። የሚከተለው የዚህ መሳሌ ነው።

ካሳ እንጨት <u>እየ-ፈለጠ</u> ነው 6

አንቀፁ <u>እየፈለጠ</u> የሚለው ነው። እሱን ተከትሎ የገባው <u>ነው</u> የሚለው ረዳት ግስ ነው። ተግባሩን በሚቀጠለው ንዑስ ክፍል እናየዋለን።

ድርጊቱ ተቋዋርጦ ወዲያውኑ ወይም ቆይቶ፣ እንደገና ሊጀምርና ሳይቋዋረጥ ለተወሰነ ጊዜ ሊቀጥል፣ እንደገናም ሊቋዋረጥና ደግሞ ሊቀጥል ይችላል። አንደዚህ ያለ ድርጊት ደጋጋሚ ይባላል። የሚደጋግመውም አንድም በድርጊቱ ፈፃሚ ለው ባህሪ ምክንያት ወይም በድርጊቱ ልዩ ባህሪ ሊሆን የችላል። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የመጠጥ ሱስኞች በየምሹቱ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት የሚያደርጉት የመመላለስ ድርጊት የዚህ አይነት ነው። ድርጊቱ ደጋጋሚ መሆኑን ለመግለፅ የግሱ አምድ ራሱን ይደጋግማል። ይህም እንደሚከተለው ነው።

ካሳ እዚህ ቤት ሁል ጊዜ <u>ይ-መላለስ-ኣል</u> 7

ድርጊቱ የአንድ ጊዜ ብቻ ሊሆን፣ አንቀፁ <u>ይመለስ-ኣል</u> የሚል የሆናል።

አንዳንዱ ድርጊት በባህሪው ሳያቋዋርጥ ለተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ሙቀጫ ከከፍተኛ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚያደርገው የመንከባለል እንቅስቃሴ የዚህ አይነት ነው። ደልዳላ ቦታ ወይም ደጋፊ እስኪያገኝ ድረስ ይቀጥላል። ዳገት የመውጣት ተግባርም እንደዚሁ ጊዜ ፈጅ ነው። "<u>ወጣ ወጣና</u> እንደ ሽንብቆ፣ <u>ተንከባለለ</u> እንደ ሙቀጫ" እንደሚባለው አይነት ነው። ሁለቱም አምዶች ደጋጋሚ ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቀጣይ ድርጊቶችን እንደ <u>ዳብ</u> አለ፣ ከሚሉት ቅፅበተቀዊ ድርጊቶች ጋር በንፅፅር ማየቱ፣ ድርጊቶች አንድ ወጥ እንዳልሆኑ ለመረዳት ያስችላል። አንቀፅ የምንለውም በመስረቱ ይህን የድርጊቶችንና የሁነቶችን ውስጣዊ ሁኔታ የሚመለከተውን የግስ ባህሪ ነው።

ጨራሽ አንቀፅ

ወጣኝ አንቀፅ ድርጊት መጀመሩን እንደሚያመለክት ሁሉ፣ ጨራሽ አንቀፅም አንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ማለቁን ያመለክታል። አትኩሮቱ ከፍፃሜው ላይ ነው። ይህን የሚገልፀው አንቀፅ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ቦዝ አንቀፅ የሚባለው ነው። ቦዝ የሚባልበት ምክንያት ካልዓይ ወይም ቀዳማይ አንቀፅ ካልተከተለው በስተቀር በራሱ ብቻ ጊዜን ለመግለፅ ባለመቻሉ ነው። ይህን ከሚከተለው መሳሌ መረዳት የቻላል።

ርባታ

ካሳ እንጨት ፈልጥ-ኦ ... 8

ይህን የሚስማ ሰው፣ በርግጥ ፈለጣው ማሰቁን ይረዳል፤ ግን ከዚያስ? የሚል ጥያቄ መጠየቁ እይቀርም። ጥያቄው እንዳይነሳ፣ <u>ሄደ</u> ወይም <u>ይሄዳል</u> የሚል የቀዳማይ ወይም የካልዓይ አንቀፅ ግስ እንዲከተለው ማድረግ ያስፈልጋል።

የጨራሽ አንቀፅ መስረት ካልዓይ አንቀፅ ነው። በዚህም ከቀዳማይ አንቀፅ ላይ ከሚመስረተው፣ ከቀጣይ እንቀፅ ይለያል። በተጨማሪም አምዱን ተከትሎ የሚገባው የባለቤት አፀፋ እገናዘቢ ነው። ሰለዚህም ፈለጥ-<u>እ</u> ብሎ፣ ፈልጥ-<u>ኦ</u> ይላል።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው አንቀፆች የተለያዩ የድርጊት ባህሪያትን ያመለክታሉ። ድርጊት መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ መቁዋጨቱንና ከዚያም መፈፀሙን ያመለክታሉ እንጅ መቸነቱን እያመለከቱም። ይህ የሚገለፀው <u>ጊዜ</u> በሚባለው ሌላ ሰዋስዋዊ የግስ ባህሪ ነው። እሱን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ጊዜ

ከፍ ሲል ድርጊቶች በጥቅሉ የተፈፀሙ ወይም ያልተፈፀሙ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ገልፀናል። ግን እያንዳንዱ ድርጊት የሚታቀድ፣ የሚወጠን፣ የሚቀጥል፣ እናም የሚቁዋጭ ሊሆን እንደሚችልና ይህም ሁኔታ የሚገለፀው በተለያየ የግስ አምድና በተለያዩ ቅጣዮች እንደሆነ ተጠቅሶአል። የተፈፀሙትም ሆኑ ያልተፈፀሙት ድርጊቶች በጊዜ ይወሰናሉ። ለምሳሌ፣ እንድ ድርጊት የተፈፀመው የዛሬ አመት ወይም ከዚያ በፊት፣ ወይም ደግሞ የዚያን ያህል ሳይርቅ ከእንድ ደቂቃ በፊት ሊሆን ይችላል። ገና ያልተፈፀመ ድርጊትም ፍፃሜ የሚያገኘው ከቅርብ ወይም ከረዥም ጊዜ በሁዋላ ሊሆን ይችላል። በፊትና በሁዋላ የምንለው ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ተነስተን ነው። ያ ጊዜ <u>አሁን</u>፣ ከአሁን <u>በፊት</u> ወይም <u>በሁዋላ</u> ሊሆን ይችላል። ከዚያ ጊዜ በፊት የተፈፀመ ድርጊት የሀላፊ ጊዜ ሲባል፣ ከዚያ ጊዜ በሁዋላ የተፈፀመ፣ የትንቢት ጊዜ ድርጊት ይባላል። እነዚህ ሁለት የጊዜ አይነቶች የሚገለፁት ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የተለያዩ የአንቀፅ እይነቶች መስረትነትና በተለያዩ ረዳት ግሶች እንዲሁም የጊዜ ተውሳክ ግሶች ነው። እንቀያቹ ድርጊቶቹን ሲገልፁ፣ ረዳት ግሶቹና ተውሳክ ግሶቹ ጊዜውን ያመለክታሉ። ሁኔታውን እያንዳንዱን የጊዜ አይነት እየጠቀስን እንደሚከተለው እናሳያለን[12]።

[12] በዚህ ጉዳይ ላይ ለፋ ያለ ትንታኔ ለማግኘት ጎልደንበርግ (1964)ን ይመልከቱ።

ርባታ

የሀላፊ ጊዜ

ባለፈ ጊዜ የተፈፀመ ድርጊትን ይገልፃል። የዋሀ፣ የቅርብ፣ አንዲሁም የሩቅ ሀላፊ ተብሎ በሶስት ንዑስ ክፍሎች ይከፈላል። የመጀመሪያው በቀዳማይ አንቀፅ፣ ሌሎቹ በካልዓይ አንቀፅና በረዳት ግሶች አማካኝነት ይገለፃሉ።

የዋሀ ሀላፊ

አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ብቻ ያመለክታል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንመልከት።

(ሀ) ካሳ አንበሳ ገደለ 1
(ለ) አለቴር ስኒ ሰበረች

የምሳሌዎቹ ግሶች ቅርፅ የቀዳማይ አንቀፅ ነው። ግሶቹም የሚያመለክቱትም የድርጊቶቹን መፈፀም ብቻ ነው። ድርጊቶቹ የተፈፀሙበትን ጊዜ ለይተው አይጠቅሱም። ጊዜውን ለመወሰን አንደ ትናንት፣ ዛሬ፣ ወዘተ፣ ያሉ የጊዜ ተውላከ ግሶችን መጠቀም ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የሚከተለውን ሊመስሉ ይችላሉ።

(ሀ) አኔ ትናንት አንበሳ ገደልኩ 2
(ለ) አስቴር ዛሬ ስኒ ሰበረች
(መ) አሁን ስኒ ሰበረች

በዚህም ምክንያት በምሳሌ (1) አንደተጠቀሱት ያሉ አረፍተ ነገሮች አንቀፅ አንጅ በግሀድ የሚታይ የጊዜ ምዕላድ የላቸውም። <u>ገደልኩ</u> የሚለው አንቀፅ የሚገልፀው ድርጊትም በማንኛውም የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል። የዋህ የተባለበትም ምክንያት፣ ጊዜውን በውል ለማሳየት ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል። አንቀፁ ባጠቃላይ ድርጊቱ ያለፈ መሆኑን አንጅ፣ መቸ አንደተፈፀመ ጊዜውን የሚያመለክት ረዳት ግስ የለውም።

የቅርብ ሀላፊ

አንድ ድርጊት መ·ሉ በሙ·ሉ የተፈፀመ መሆኑንና፣ ከተፈፀመም ብዙ ጊዜ ያልቆየ፣ ሰለዚህም ያልተረሳ መሆኑን ያመለክታል። ድርጊቱ የሚገለፀው በፈራሽ አንቀፅ አምድና /-አል/ በሚል ረዳት ግስ አማካኝነት ነው። የሚከተለውን ምሳሌ አንመልከት።

ካሳ አንበሳ ገድል-አ-አል (= ገድሎአል) 3

ርባታ

የግሱ አምድ /ማኧድል-/ የሚል ሲሆን፣ መሰረታዊ ቅርፁም የካልዓይ አንቀፅ ነው። ከአምዱ ቀጥሎ የሚታየው /-አ/ የባለቤት አፀፋ ነው[13]። ከእሱ ቀጥሎ የሚታየው /-አል/ የሚለው ረዳት ግሰ ነው። ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን ብቻ ያመለክታል።

እኔ አንበሳ <u>ገድል-ኤ</u> -ኣለሁ (= ገድያለሁ) 4

በግሱ አምድ ላይ የሚታየው የባለቤት አፀፋ በቀዳማይ አንቀፅ ከሚታየው ተመሳሳይ አፀፋ የተለየ ነው። የቀዳማይ አንቀፅ የአንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ የባለቤት አፀፋ /-ኩ/ ሲሆን፣ በጨራሽ አንቀፅ አምድ ላይ ግን፣ ይኸው አፀፋ የሚከሰተው /-ኤ/ ሆኖ ነው። የአፀፋው አይነትና የአምዱ ቅርፅ የአንቀፁን አይነት ይወስናሉ። አንቀፁም ከላይ እንደተገለፀው፣ ጨራሽ ነው። /-አል/ የሚለው ረዳት ግሰ ከዚህ ጨራሽ አንቀፅ ጋር ሲገባ፣ ድርጊቱ ከተፈፀመ በሁዋላ ብዙ የጊዜ እንዳላለፈ ብቻ ያመለክታል። የግሱን ውስጣዊ አወቃቀር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

5

<u>አምድ</u>	<u>አንቀፅ</u>	<u>አፀፋ</u>	<u>ጊዜ</u>	<u>አፀፋ</u>
ካልዓይ	ጨራሽ	ዘርፍ	ቅርብ	ባለቤት
ሰኧብር-		-ኤ	-አል	-ሁ

የረዳት ግሱ አፀፋና የአንቀፁ አፀፋ የተለያዩ መሆናቸውን ልብ እንበል። የአንቀፁ አፀፋ የድርጊቱን ፍፃሜ ብቻ ያመለክታል። የረዳት ግሱ አፀፋ የባለቤቱን መደብ፣ ቁጠር ወይም ፆታ ይጠቁማል። በመጨረሻም የአንቀፁ አፀፋዎች ቀደም ሲል በስሞች ርባታ ላይ ካየናቸው የዘርፍ ሙያ አፀፋዎች ጋር እንድ ናቸው፤ ከ/-አ/ በስተቀር። ይህ አፀፋ በስሞች ላይ /-ኤ/ ሆኖ እንደሚከሰት አይተናል። ከዚህ ላይ ቅርፁን መለወጡ፣ ከአንቀፁ ጋር ያለውን ቁርኝት ያመለክታል።

የሩቅ ሀላፊ

ከላይ እንዳየነው የቅርብ ሀላፊ ጨራሽ አንቀፅ፣ ይህም አንድ ተፈፅሞ ያለቀ ድርጊትን ያመለክታል። በዚህና በዚያ መካከል ያለው ልዩነት ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ርቀትና ቅርበት ብቻ ነው። ይህም ስለድረጊቱ ከምንናገርበት ጊዜ አኳያ ሲሰላ ነው። በዚህ ላይ ጊዜው ሩቅ ስለሆነ፣ ከአንቀፁ ጋር የሚዋቀረው ረዳት ግሰ <u>ነበር</u> የሚለው ነው። የዋናው ግሰ አምድ አንቀፅ አሁንም ጨራሽ ነው። የረዳቱ ግሰ አንቀፅም ቀዳማይ ነው። የሁለቱ አንቀፆች ቅንጅት ጊዜውን ሩት ያደርገዋል። በዚህም /-አል/ ከሚለው ረዳት ግሰ ጋር ከሚዋቀረው የቅርብ ሀላፊ ጨራሽ አንቀፅ ሲለይ ችሎአል። ልዩነቱ ግን የጊዜ ብቻ ነው፤ የድርጊት

[13] /-አ/ ሶስተኛው አይነት የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፅፋ ነው። አንደኛው በቀዳማይ አንቀፅ የሚገኘው /-ኧ/ ሲሆን፣ ሁለተኛው በካልዓይ አንቀፅ መነሻ ላይ የሚገኘው /ይ-/ ነው። /-አ/ ደግሞ በካልዓይ አንቀፅ አምድ መድረሻ ላይ የሚገኝ ነው። ሁሉም የሶስተኛ መደብ ዘረ-ምዕላዶች ናቸው።

ርባታ

አይደለም። በድርጊት ደረጃ ሁለቱም ጨራሾች ናቸው። የግሱን ያቀነጃጀት ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

<u>አምድ</u>	<u>እንቀፅ</u>	<u>አፀፋ</u>	<u>ረዳት</u>	<u>አፀፋ</u> 6
ካልዓይ	ጨራሽ	ዘርፍ	ነበር	---
ሰኽብር-		-ኦ		

በዚህ መሰረት፣ ከላይ በተራ ቁጥር (3) /-አል/ በሚለው ረዳት ግሰ አማካኝነት የተጠቀሰው የቅርብ ሀላፊ አረፍተ ነገር፣ በሩቅ ሀላፊ ጊዜ ሲነገር የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ አንበሳ <u>ገድሎ ነበር</u> 7

<u>ገድሎ</u> የሚለው ግስ መሰረት የካልዓይ አንቀፅ ይሁን እንጅ፣ ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ ሀላፊ፣ ከሀላፊም የሩቅ ሀላፊ ነው። ከዚህም አንቀፅና ጊዜ የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ጊዜው ሀላፊ ሆኖ፣ ድርጊቱ ያላለቀ፣ ስለዚህም አንቀፁ ካልዓይ፣ ሲሆን ይችላል። ከዚህ በላይ የተገለፁትን ሶስት የጊዜ አይነቶች እጠቃሎ በሀለፊ ጊዜ ስር ማስቀመጥ ይቻላል።

የኢሀላፊ ጊዜ

አንድ ገና ያልተፈፀመ ድርጊት የሚፈፀምበትን የሚሳይ የጊዜ አይነት ነው። የሚገለፀው ከካልዓይ አንቀፅ አምድ ላይ /-አል/ የሚለውን ረዳት ግስ በመቀጥል ነው። የሚከተለውን እንመልከት።

ካሳ አንበሳ ይ-ገድል-አል (ይገድላል) 8

/ይ-/ ቀደም ሲል ያየነው የሶስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው። /-ግኧድል-/ የሚለውን የካልዓይ እንቀፅ አምድ ነው። ድርጊቱ ገና ያልተፈፀመ መሆኑን ያመለክታል። /-አል/ የሚለው ረዳት ግሱ ሲሆን፣ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ጊዜ ያመለክታል። ይህም ከአሁን ጀምሮ ወደፊት የሚመጣውን የቅረብም ሆነ የሩቅ ጊዜ ሁሉ ያጠቃልላል። በጣም የቅርብ ሲሆን፣ <u>ከአሁን</u> ጋር አንድ ይሆናል። ሲርቅም እንደዚሁ ልዩ ልዩ የመጭ ጊዜ ተውሳክ ግሶችን መጠቀምን ያስከትላል። ይህም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ) ካሳ <u>አሁኑኑ</u> ይ-መጥ-አል 9
(ለ) ካሳ <u>አሁን</u> ይ-መጥ-አል
(መ) ካሳ <u>ትንሽ ቆይቶ</u> ይ-መጥ-አል
(ሰ) ካሳ <u>ከርሞ</u> ይ-መጥ-አል

ሁሉም ያልተፈፀመ ድርጊትን ያመለክታል። ልዩነታቸው ድርጊቶቹ ወደፊት የሚፈፀሙበት ጊዜ፣ ንግግር ከምናደርግበት ጊዜ መራቅና መቅረብ ነው። ይህም የሚገለፀው በግሱ ቅርፅ ወይም በረዳት ግሱ ሳይሆን፣ በተውሳክ ግሶቹ ነው። ከዚህ የምንረዳው በግሳዊ ቅርፁ ከትንቢት ጊዜ የተለየ፣ የአሁን የሚባል የጊዜ አይነት አለመኖሩን ነው።

አስካሁን ያየነው በካልዓይ፣ በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፆች የሚገለፁ ድርጊቶችንና /-አል/ እና <u>ነበር</u> በሚሉ ረዳት ግሶች አማካኝነት የሚገለፁ የጊዜ አይነቶችን ነው። አንቀፆቹ ያልተፈፀመ፣ የተፈፀመ እና የተጨረሰ ድርጊትን ሲያመለክቱ፣ ጊዜያቱ ድርጊቱ የተፈፀመበት ወይም ያልተፈፀመበት ወይም የተጨረሰበት ወቅት፣ ስለድርጊቱ ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ወይም በሁዋላ መሆኑን ይገልፃሉ። ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ያለውን <u>ሩቅ ጊዜ፣ ነበር</u> በሚለው፣ ለምንነጋገርበት ጊዜ ቅርብ፣ ወይም ከእሱ ጋር አንድ የሆነውን ጊዜ፣ /-አል/ በሚለው ረዳት ግስ አንገልፃለን።

የአንድ ድርጊት አፈፃፀም ግን ከዚህ ላይ አንደገለፅነው በሶስት ብቻ ሊወሰን የሚችል አይደለም። በመፈፀም ላይ ያለና ያላለቀ ሊሆን ይችላል። ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ አንደዚሁ ቀጣይ ሊሆን ይችላል። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጊዜው ብቻ ተለይቶ የማያቁዋርጥ ጊዜ ይባላል። ይሁን እንጅ፣ ቀጣዩ ጊዜው ብቻውን ሊሆን አይችልም፣ ቀጣዩ ድርጊቱ ነው፣ ሊባል ይችላል። ጊዜ ያለድርጊት ብቻውን አይታሰብም ማለት ይቻላል።

አንድ ድርጊት ላይቁዋረጥ በመፈፀም ላይ የሚገኘው አሁን ወይም ከአሁን በፊት ሊሆን ይችላል። በዚሁ መሰረት የማያቁዋርጥ የአሁን ወይም የሀላፊ ጊዜ ድርጊት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የድርጊቱን ቀጣይነት ለማመልከት፣ /እይይኧ-/ የሚል ምዕላድ በአምዱ መነሻ ላይ ይገኛል። የሚከተለውን አንመልከት።

ካሳ እየ-አነበበ... 10

ይህ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ነው። ይሁን እንጅ፣ ጊዜ የለውም። <u>እየ-አነበበ</u> የሚለው የቀጣይ አንቀፅ ግስ ነው። የሚያመለክተውም፣ ከፍ ሲል አንደተገለፀው፣ አንቀፅን ብቻ ነው። ጊዜን አያሳይም። ይህን ለማሳየት ረዳት ግስ ያስፈልገዋል። የድርጊቱ ቀጣይነት ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ በፊት ከሆነ፣ <u>ነበር</u> የሚል ረዳት ግስ ጋር ይገባል። ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ጋር አንድ ከሆነ፣ <u>ነው</u> ከሚለው ጋር ይገባል። የድርጊቱ ቀጣይነት ወደፊት የሚታይ ከሆነ፣ ከጊዜ ተውሳክ ግሰ ጋር ይገባል። ይህን ሲያደርግ፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር ግስ የሚከተሉትን ይመስላል።

(ሀ) ካሳ መፅሀፍ እየ-አነበበ ነው (የአሁን) 11
(ለ) ካሳ መፅሀፍ እየ-አነበበ ነበር (የሀላፊ)
(መ) ካሳ [ነገ መፅሀፍ እየ-አነበበ] ይጠብቅሀል... (የትንቢት)

ምሳሌ (መ) ቀጣይ አንቀፅንና የትንቢት ጊዜን ያመለክታል።

ርባታ

ነበር የሚሰው ረዳት ግሰ ከካልዓይ አንቀፅ ግስ ጋር ሲገባ፣ ያልተፈፀመና ተደጋጋሚ የሆነ ተግባርን ሊያመለክት ይችላል። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ካሳ በግ ይ-ጠብቅ-ኣል 12

(ለ) አስቴር በወጣትነትዋ እንጨት ት-ሰብር ነበር

ሁለቱም ያልተፈፀመ ድርጊትን ያመለክታሉ። የመጀመሪያው ድርጊት ጊዜ፣ አሁንና ወደፊትን ያጠቃልላል። ወደ ሁዋላም ሊሄድ ይችላል። ሁለተኛውም እንደዚሁ የአስቴርን የልጅነት ዘመን የሚሸፍን ረዥም ጊዜ ሊሆን ይችላል። ረዥም ጊዜ የሚፈጅ ድርጊት ደግሞ ከዕለት ያልፍና የዘወትር ወይም የሰርክ ተግባር ይሆናል። ይሁን እንጅ፣ ከጊዜ አንፃር ሀሳፊ ወይም ኢ.ሀሳፊ ነው። ሀሳፊው የቅርብና የሩቅ፣ ኢ.ሀሳፊው የአሁንና የወደፊት የሚሉ ከፋዮች አሰት። ከአንቀፅ አኩዋያ ድርጊቱ፣ የታቀደ፣ የተጀመረ፣ የቀጠለና የተጨረሰ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ ያለተ እና ያላለቀ ተብለው፣ አንደ ጊዜው በሁለት ብቻ ሊከፈሉ ይችላሉ። ዋናው ጉዳይ ጊዜና አንቀፅ የተለያዩ፣ ግን ደግሞ የተዛመዱ የግስ ባህሪያት መሆናቸውን መረዳት ነው።

ሰልት

ሰልት ከአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ ከቁዋንቁዋ ተግባር ጋር የተቆራኘ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። አንድ አረፍተ ነገር የሚነገረው፣ አንድ የተወሰነ ሀሳብን ለመግለፅ፣ በተገለፀ ሀሳብ ላይ አሰተያየት ለመስጠት፣ ጥያቄ ለመጠየቅ፣ ተቃውሞ ለማሰማት፣ ትዕዛዝ ለማሰተላለፍ፣ አጥፊን ለመግሰፅ፣ ለመርገም፣ ደግ አድራጊን ለመመረቅ፣ ለማመስገን፣ ለማቆላመጥ፣ ወዘተ፣ ነው። እነዚህንና የመሳሰሉትን ለመግለፅ የመንጠቀምበት የመዋቅር አይነት የተለያየ ነው። ይህን የተለያየ ተግባር ምንገልፅበት ሰርዓት ሰልት ይባላል።

ማንኛውም ቁዋንቁዋ የተለያዩ ተግባራትን የሚገልፁ የተለያዩ መዋቅሮች ክምችት ነው። በየቀኑ የምንለውንና የምንሰማውን ሁሉ ብናሰበው፣ ከዚህ ከምቸት የሚወጣና ከእሱም የማይዘል መሆኑን እንገነዘባለን። ለንነጋገርም የምንፈፅመው በመሰረቱ እነዚህን ልዩ ልዩ ተግባራትን ነው። መፈፀሚውም ልዩ ልዩ ቁዋንቁዋ ነው። መርገሚያው ከመመረቂያው፣ ትዕዛዝ መለመኛው ከማለቻው የተለየ ነው። በተለምዶ ቁዋንቁዋ የሀሳብ መግለጫ መሳሪያ ነው፣ እንላለን እንጅ፣ መሳሪያነቱ ከዚህ ያለፈ ነው።

በዚሁ መሰረት ማንኛውም አረፍተ ነገር ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ አሉታዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ወዘተ፣ እየተባለ እንደ ግብሩ አይነት፣ አንዱ ከሌላው ይሰያል። ልዩነቱ በአብዛኛው የሚታየው በግሱ ላይ ነው። ልዩነቱ የአምድ ወይም የቅጣይ ሊሆን ይችላል። ዝርዝሩን እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አናሳያለን።

ርባታ

መደብ	ሁተታዋ	መጠይቃዊ	እሉታዊ	ትዕዛዛዊ/ይሁንታዊ	
1ኛ	እ-ሰብር-	ል-አ-ሰበር[14]	ኣል-ሰበር-		————
2ኛ ተ	ት-ሰብር-	ት-ሰብር	ኣት-ሰበር-	<ኣል-ት-ሰበር	ሰበር
እ	ት-ሰብር-ኢ-	ት-ሰብር-ኢ	ኣት-ሰበር-ኢ-	<ኣል-ት-ሰበር-ኢ	ሰበር-ኢ
3ኛ ተ	ይ-ሰብር-	ይ-ሰበር	ኣይ-ሰበር-	<ኣል-ይ-ሰበር	ይ-ሰበር
እ	ት-ሰብር-	ት-ሰበር	ኣት-ሰበር-	<ኣል-ት-ሰበር	ት-ሰበር
	ት-ሰብር-ኡ-	ት-ሰብር-ኡ	ኣት-ሰበር-ኡ-	<ኣል-ት-ሰበር-ኡ	ሰበር-ኡ
	ይ-ሰብር-ኡ-	ይ-ሰበር-ኡ	ኣይ-ሰበር-ኡ-	<ኣል-ይ-ሰበር-ኡ	ይ-ሰበር-ኡ

1 የስልት ስንጠረዥ

የሀተታዊው ግስ ታህታይ ቅርፅ /-ሰኽብር-/ ነው። ይህም ቀደም ሲል ያየነው የካልዓይ አንቀፅ አምድ ነው። የትዕዛዛዊ ስልት ታህታይ ቅርፅም /ሰብኽር-/ ሲሆን፣ በሁለቱ አንቀፆች መካከል ያለው ልዩነት አናባቢው /ኽ/ የገባበት ቦታ ነው። በሁተታዊው ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ ሲገባ፣ በመጠይቃዊ፣ በትዕዛዛዊና በእሉታዊ ስልት ከሁለተኛው ተናባቢ ቀጥሎ ይገባል።

በትዕዛዛዊ ስልት፣ ፆታንና ቁጥርን የሚያመለክቱት ምዕላዶች እምዱን ተከትለው ሲገቡ፣ በመጠይቃዊ ስልት መደብ አመልካች የሆኑት ምዕላዶች ብቻ እምዱን አየቀደሙ ይገባሉ። መደብ አመልካቾቹ /እ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ ባለቤትን ያመለክታሉ። ፆታ

[14] ቀደም ሲል ስለ አንቀፅ ስንወያይ እንዳየነው፣ /ል-/ የአቃጅ አንቀፅ ምዕላድ ነው። ይህ አንቀፅ የሚገኘው በ*ዕቃኛ* አረፍተ ነገር ነው።

[[አስቴር ል-ትሄድ] ነው]

ስንል ድርጊቱ መታቀዱን ያመለክታል። ስለዚህም ከአቃጅነት በተጨማሪ የሞይነት ተግባር አለው። አንደ አቃጅ አንቀፅ፣ መጠይቃዊ ስልትም የሚገለፀው በተራ ሳይሆን፣ በፅቅፍ አረፍተ ነገር ነው። ለምሳሌ፣

ሂድ!

ስንል፣

[እኔ [አንተ ሂድ] ብያለሁ]

ግስታችን ነው። በዚህ ውስጥ [አንተ ሂድ] የሚለው ትዕዛዝ አንቀፅ ነው። አገባቡ በፅቅፍነት ነው። /ል-አ-ሰብኽር-/ የሚለውም አንደዚሁ ነው። ጉዳዩን ስተመለከተ ሀይሉ (1980)ን ይመልከቱ።

ርባታ

አመልከችዋ /-ኢ/ ስተሆን፣ ቁጥር አመልካቾቹ ደግሞ /-ን/ እና /-ኡ/ ናቸው። የመጀመሪያው አንደኛ መደብን፣ ሁለተኛው ሌሎቹን መደቦች ያመለክታል። ከዚህ ላይ ቀደም ሲል ስለያታ ስንወያይ፣ አንሰታይ ያታ ብቻ በምዕላድ እንደሚገለፅና ከዚህ የተለየ የወል ወይም የግውዝ ያታ የሚባል እንደሌለ ገልፀን ነበር። ከላይ የሚታየው ስንጠረዥም ይህንኑ ያረጋግጣል።

አሉታዊ ስልት የሚገለፀው /አል-/ በሚል ምዕላድ ነው። አገባቡ መደብ አመልካቹን ምዕላድ እየቀደመ ነው። በዚህ ምዕላድ መድረሻ ላይ የሚገኘው /ል-/ በአንደኛና በሶስተኛ መደብ ላይ ሲገደፍ፣ በሁለተኛ መደብ ላይ፣ ከመደብ አመልካቹ ምዕላድ ጋር ተመሳስሎ /ት/ ይሆናል። ዝርዝሩን በስኑ-ድምፁ ውስጥ ስላየነው ከዚህ ላይ አንደግመውም።

አስካሁን ያየነው እንደ <u>ስበረ</u> ያሉትን ግሶች የርባታ ስርዓት ነው። የእነዚህ አይነት ግሶች ስርዓት አንድ ወጥ ነው። ስለዚህም ከአንዱ ግስ የርባታ ሂደት የሌሎቹንም ግሶች ሂደት መተንበይ ይቻላል። ለዚህ ነው፣ ስርዓቱን በአንድ ግስ አማካኝነት ስግሳየት የሞከርነው። ሁሉንም ግሶች በተራ እየወሰድን ስርዓታቸውን እንይ ብንል፣ ጊዜም፣ ቦታም አይበቃንም! አስፈላጊም አይደለም። የአንዱ ግስ የርባታ ስርዓት የሌሎቹም ነውና። የቁዋንቁዋ ስርዓታዊነት እንዱ መገለጫ ይህ ነው።


የርባታው ስርዓት የተወሰኑ ግሶችን ባህሪ የማይሸፍን ከሆነ፣ የእነሱን በተሰየ ሁኔታ ማሳየት ያስፈልጋል። አንደነዚህ ያሉ ግሶች በየቁዋንቁዋው አሉ። ድርጊትን ሳይሆን በአንድ ቦታ መገኘትን፣ ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር መስወጥን እንዲሁም አንድ ነገር መሆንን ያመለክታሉ። እነዚህን የሚያመለክቱ ግሶች በቀደምት ሲቃውንት ዘንድ በሁለት ብቻ ተከፍለው፣ የመኖርና የመሆን ግስ በመባል ይታወቃሉ። ግሶቹም /ኦ-/ እና /አል-/ ናቸው። እነዚህ ግሶች በረዳት ግስነት የተለያየ ጊዜን የመግለፅ ተግባር አንዳላቸው ቀደም ሲል ስስ አንቀፅና ጊዜ ስንወያይ ተመልክተናል።

ረዳት ግሶች በቅርፃቸውም ሆነ በትርጉማቸው ጎደሎ ናቸው። ይህ በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቁዋንቁዋ ነው ስማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ከዋና ግሶች የርባታ ስርዓት ያፈነግጣሉ። እንዴት አንደሚያፈነግጡ በሚቀጥለው ስንጠረዥ አንመለከታለን።

ግስ	መደብ	መደብ ያታ	መደብ ቁጥር
ነ	1	ነ-ኝ	ነ-ን
	2-ተ	ነ-ህ	ነ-ኣች-ሀ-ኡ >ናችሁ
	ኣ	ነ-ሀ-ኢ > ነሽ	
	3-ተ	ነ-ኡ > ነው	ነ-ኣች-ኧ-ኡ > ናቸው
	ኣ	ነ-ት-ኢ >ነች	
አል-	1	አል-ኧሁ	አል-ኧን
	2-ተ	አል-ኧህ	አል-ኣች-ሀ-ኡ > አላችሁ
	ኣ	አል-ኧህ-ኢ >አለሽ	
	3-ተ	አል-ኧ	አል-ኡ > አሉ
	ኣ	አል-ኧት-ኢ >አለች	

2 የመደብ፣ የቁጥርና ያታ ስንጠረዥ

ርባታ



ግስ		የሩት	የቅርብ	የሞሀ	የእሁን	ትንቢት
ነ-ለሆን-	1	ሆን-የ ነበር ሆኘ ነበር	ሆን-የ-አለ-ሁ ሆኖለሁ	ነበር-ሁ	ነ-ኝ	አ-ሆን-አለ-ሁ እሆናሉ
	2ተ	ሆን-ኧሀ ነበር ሆነህ ነበር	ሆን-ኧሀ-ላለ ሆነሀለ	ነበር-ሀ	ነ-ህ	ት-ሆን-አለ-ህ ትሆናለህ
	አ	ሆን-ኧሀ-ኢ ነበር ሆንሽ ነበር	ሆን-ኧሀ-ኢ-ላለ ሆንሻለ	ነበር-ሀ-ኢ- ነበርሽ	ነ-ሀ-ኢ ነሽ	ት-ሆን-ኢ-አለ-ሀ-ኢ ትሆኛለሽ
	3ተ	ሆን-ኦ በር ሆኗ ነበር	ሆን-ኦ-ኣለ ሆናለ	ነበር-ኧ ነበር	ነ-ኡ ነው	ይ-ሆን-ኣለ ይሆናል
	አ	ሆን-ኣ በር ሆና ነበር	ሆን-ኣ-ኣለ-ት-ኢ ሆናለች	ነበር-ኧት-ኢ ነበረች	ነ-ኧት-ኢ ነች	ት-ሆን-ኣለ-ት-ኢ ትሆናለች
	ብ	ሆን-ን ነበር ሆነን ነበር	ሆን-ን-ኣለ ሆንናለ	ነበር-ን ነበርን	ነ-ን ነን	ዕ-ን-ሆን-ኣለ-ን ዕንሆናለን
		ሆን-ኣች-ሁ-ኡ ነበር ሆናችሁ ነበር	ሆን-ኣች-ሁ-ኡ-ላለ ሆናችሁለለ	ነበር-ኣች-ሁ-ኡ ነበራችሁ	ነ-ኣች-ሁ-ኡ ናችሁ	ት-ሆን-ኣለ-ኣች-ሁ-ኡ ትሆናላችሁ
		ሆን-ኧ-ኡ ነበር ሆነው ነበር	ሆን-ኧ-ኡ-ላለ ሆነዋለ	ነበር-ኡ ነበሩ	ነ-ኣች-ኧ-ኡ ናቸው	ይ-ሆን-ላለ-ኡ ይሆናሉ
አለ/ ናር	1	ናር-የ-ነበር ናሬ ነበር	ናር-የ-አለ-ሁ ናሬአለሁ	ነበር-ሁ	አለ-ሁ	አ-ናር-አለ-ሁ አናራለሁ
	2ተ	ናር-ኧሀ-ነበር ናረሀ ነበር	ናር-ኧሀ-ላለ ናረሀለ	ነበር-ሀ	አለ-ሀ	ት-ናር-አለ-ሀ ትናራለህ
	አ	ናር-ኧሽ-ነበር ናረሽ ነበር	ናር-ኧሽ-ላለ ናረሻለ	ነበር-ሽ	አለ-ሽ	ት-ናር-ኢ-አለ-ሽ ትናራለሽ
	3ተ	ናር-ኦ-ነበር ናር ነበር	ናር-ኦ-ላለ ናርኣለ	ነበር-ኧ	አለ-ኧ	ይ-ናር-ኣለ ይናራል
	አ	ናር-ኣ-ነበር ናራ ነበር	ናር-ኣ-ላለች ናራለች	ነበር-ኧች	አለ-ኧች	ት-ናር-አለ-ኧች ትናራለች
	ብ	ናር-ኧን-ነበር ናረን ነበር	ናር-ኧን-ላለ ናረናለ	ነበር-ን	አለ-ን	አን-ናር-አለ-ን አንናራለን
		ናር-ኣችሁ-ነበር ናራችሁ ነበር	ናር-ኣችሁ-ላለ ናራችሁለለ	ነበር-ኣችሁ	አለ-ኣችሁ	ት-ናር-አለ-ኣችሁ ትናራላችሁ
		ናር-ኧው-ነበር ናረው ነበር	ናር-ኧው-ላለ ናረዋለ	ነበር-ኡ	አለ-ኡ	ይ-ናር-አለ-ኡ ይናራሉ

ርባታ

ሰልት



ግሰ	መደብ	ሁተታዊ	መጠይቃዊ	አሉታዊ	ትዕዛዛዊ/ይሁንታዊ
ኑ/ሆን	1	ኑ-ኝ	ል-ሁን	አል-ሆን	ል-ሁን ልሁን
	2-ተ	ኑ-ህ	ት-ሆን	አል-ት-ሆን አትሆን	ሁን
	አ	ኑ-ህ-ኢ ነሽ	ት-ሆን-ኢ ትሁኝ	አል-ት-ሆን-ኢ አትሆኝ	ሁን-ኢ ሁኝ
	3-ተ	ኑ-ው	ይ-ሁን	አል-ይ-ሆን አይሆን	ይ-ሁን ይሁን
	አ	ኑ-ት-ኢ ኗ	ት-ሁን	አል-ት-ሆን አትሆን	ት-ሁን ትሁኚ
	ብ	ኑ-ን	አ-ን-ሁን	አል-ን-ሆን አንሆን	አ-ን-ሁን አንሁን
		ኑ-አች-ህ-አ ናችሁ	ት-ሆን-አ	አል-ት-ሆን-አ አትሆኑ	ሁን-አ ሁኑ
		ኑ-አች-ኧ-አ ናቸው	ይ-ሁን-አ	አል-ይ-ሆን-አ አይሆኑ	ይ-ሁን-አ ይሁኑ
አል- /ኖር	1	አል-ኧሁ አለሁ	ል-ኑር	አል-ኑር	ል-ኑር
	2-ተ	አል-ኧህ አለህ	ት-ኖር	አል-ት-ኖር አትኖር	ኑር
	አ	አል-ኧህ-ኢ አለሽ	ት-ኖር-ኢ	አል-ት-ኖር-ኢ አትኖሪ	ኑር-ኢ ኑሪ
	3-ተ	አል-ኧ አለ	ይ-ኑር	አል-ይ-ኑር አይኖር	ይ-ኑር
	አ	አል-ኧት-ኢ አለች	ት-ኑር	አል-ት-ኖር አትኖር	ት-ኑር
	ብ	አል-ኧን አለን	አ-ን-ኑር እንኑር	አል-ን-ኖር አንኖር	አ-ን-ኑር እንኑር
		አል-አችች-ህ-አ አላችሁ	ት-ኖር-አ ትኖሩ	አል-ት-ኖር-አ አትኖሩ	ኑር-አ ኑሩ
		አል-ኧ-አ አሉ	ይ-ኑር-አ ይኑሩ	አል-ይ-ኖር-አ አይኖሩ	ይ-ኑር-አ ይኑሩ

ከመዘርዝሩ እንደሚታየው፣ /ንኡ-/ የሚለው ምዕላድ ጊዜያትንና ስልቶችን የሚያሳየው ሆን (/ሀኦን-/) በሚለው የመሆን ግስ አማካኝነት ነው። /አል-/ የሚለውም እነዚህኑ ባህሪያት የሚገልፀው ኖር (/ንኦር-/) በሚለው የመኖር ግስ አማካኝነት ነው። ለዚህም ምክንያቱ /ንኡ-/ እና /አል-/ ረዳት ግሶች በመሆናቸውና በትርፅም ሆነ በትርጉም ከመደበኛ፣ ግለትም ከቸና ግሶች በመለየታቸው ነው። ለምሳሌ፣ /ንኡ-/ ምንም አይነት ትርጉም የለውም። ስለዚህም ባዶ ምዕላድ ነው። ባዶ ቅል እንደማለት ነው፤ ይዘት የለውምና። በትርፁም እንደ <u>ሰበረ</u> አይነት ግሶች ሶስት ተናባቢ እግር የለውም። ጎደሎ ነው። ስለዚህም የርባታ ስርዓቱ ከመደበኛ ግስ የተለየ ነው።

ቅጣይ የሚያሳየው ለመደብ፣ ለቁጥር ወይም ለፆታ ብቻ ነው። መደብን የሚያመለክተው ግን በተሳቢ አፀፋ ነው። ይህም እንደ <u>ሰበረ</u> ካሉ ግሶች ስርዓት የተለየ ነው። ምክንያቱም እንደ <u>ሰበረ</u> ያሉ ግሶች የባለቤትን መደብ የሚያመለክቱት በባለቤት አፀፋ ስለሆነ ነው። የተሳቢ አፀፋ መታየት ያለበት ከሳቢ ግስ ጋር ለሚዋቀር ተሳቢ ስማዊ ህረግ ነው። /ንኡ-/ ሳቢ ግስ እይደለም። የድርጊትም አይደለም፤ የመሆን ነው።

/አል-/ የሚለው ግስም እንደ /ንኡ-/ ጎደሉ ነው። ግን ይዘት አለው። እንደ ጊዜና ስልት ያሉትን ተግባራት የሚገልፀው በአብዛኛው ኖር (/ንኦር-/) በሚለው ግስ አማካኝነት ነው። ይሁን እንጅ፣ አፀፋዎቹ /ንኡ-/ በሚለው ግስ እንደሚታዩት፣ የተባቢ አይደሉም፣ የባለቤት ናቸው። /ንኡ-/ም ሆነ /አል-/ በራሳቸው ቅርፅ የሚከሰቱት በሀትታዊ የአሁን ጊዜ ብቻ ነው።

/ንኡ-/ እና /አል-/ ከ<u>ሰበረ</u> አይነት ግሶች በቅርፃቸውም ሆነ በተግባራቸው የተለዩ ናቸው። እንደ ሰበረ ያሉት ድርጊትን ሲያመለክቱ፣ እነዚህ ጉረትን ወይም ሁነትን ያመለክታሉ። ሁለተኛም እንደ <u>ሰበረ</u> ያሉ ግሶች ባለ ሶስት ተናባቢ ሲሆኑ፣ እነዚህ ባለ እንድ ተናባቢ ናቸው። /ንኡ-/ የሚለው ግስ ተናባቢ ድምፅ /ን/ ብቻ ነው። /አል-/ የሚለውም እንደዚሁ /ል/ ብቻ ነው። ለዚህም ምክንያት ከሶስቱ ተናባቢዎቹ መካከል ሁለቱን ስለጎረደ ነው። ተናባቢዎቹ /ሀ-ል-ው-/ እንደሆኑ ባለፈው ክፍል ተገልያለል። ተናባቢያቸውን የሚጥሉ ግሶች በጥቅሉ ጎራጅ ግሶች ይባላሉ።[15]

የእንደዚህ አይነት ጎራጅ ግሶች ባህሪ ጎራጅ ያልሆኑ እንደ <u>ሰበረ</u> ያሉ ግሶች የሚከተሉትን የርባታ ስርዓት ለመከተል አለመቻል ነው። ብዚህም ምክንያት ህጉ-ወጥ በመባል ይታወቃሉ። የ/ንኡ-/ እና የ/አል-/ አሉታዊ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ /አይድኡል-/ እና የለ- /ይኡልልኡ-/ የሚል እምድ ነው። እምዱ ላይ የተለያየ የመደብ፣ የፆታ ወይም የቁጥር ምዕላድ ይጨምራሉ። ይህ ሲሆን ለምሳሌ፣ የእንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አሉታዊ ቅርፅ እይደለሁም (/አይድኡልልኡህኡም/) እና የለሁም (/ይኡልልኡህኡም/) የሚል ይሆናል።

[15] የጎራጅ ግሶችን ባህሪ በተመለከተ ባየ(1997፣ 1999፣ 2004፣) ይመልከቱ።

ርባታ

ሊላው የነዚህ ግሶች ባህሪ ከአንባቢዎው ጋር የተያያዘ ነው። በአንድ በኩል እንደ ግንኙውም ግስ ራሳቸውን ችለው ግላዊ ሀረገ ሊመስርቱ ይችላሉ። ይህን ወደፊት በሰፊው እናየዋለን። ለጊዜው ግን የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ንበዝ ነው] 1
(ለ) [ቤት ውስጥ አለ]

እዚህ ላይ ግሶቹ በዋና ግስነት ገብተዋል።

በሊላ በኩል፣ እነዚሁ ግሶች ለሊሎች ግሶች ረዳት በመሆን ጊዜን ሊያመለክቱ ቀደም ሲል አይተናል። ለምሳሌ፣ ሰብር-አል እና እየሰበረ ነው ስንል፣ አል እና ነው፣ ሰብር እና እየሰበረ የሚሉት የተጣይና የጨራሽ እንቀፅ ግሶች ረዳት ሆነው በመግባት ጊዜን ያመለክታሉ። በዚህ ደረጃ ምድባቸው ከንብር ቃላት ጋር ነው። ግብራቸውም ጊዜን ማሳየት ነው።

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከትነውን እናጠቃለው። የተመለከትነው የስሞችን፣ የቅፅሎችንና የግሶችን የርባታ ስርዓት ነው። ሊላው ሊታይ የሚገባው ስርዓት የተውላክ ግሶች ነበር። ይሁን እንጅ፣ ከዚህ በፊት እንዳየነው፣ ከፍሉ የግብር እንጅ የቃል ክፍል አይደለም። ተውላክ ግላዊ ተግባራት የሚገለፁት በአብዛኛው በመበተዋድድ ሀረጎች ነው። አንዳንድ ተውላክ ግስ ሲባሉ የሚችሉ ቃላት ቢኖሩም፣ የርባታ ስርዓት የላቸውም። ለምሳሌ ከፉኛ የሚለው ቃል ከፉ ከሚለው ቅፅል ላይ የተመሰረተ የሁኔታ ተውላክ ግስ ነው። ይሁን እንጅ፣ እንደ ቅፅሎች ቅጣዮችን እየጨመረ ወይም ከተናባቢዎቹ መካከል አንዱን ወይም ሊላውን እየደገመ ቅርፁን ሲለውጥ አይተኸም።

ከላይ እንደተገለፀው፣ በዚህ ክፍል ያተኮርነው በሰሞች፣ በግሶችና በቅፅሎች የርባታ ስርዓት ላይ ነው። ስሞች ስቁጥር፣ ለፆታ፣ ለሙያና ለዕምርነት የተለያዩ ቅጣዮችን እንደሚያሰከትሉ አይተናል። ቁጥርን በሚመለከት፣ /-አች/ የብዙነት ላይሆን፣ የጥቂትነት ምዕላድ እንደሆነ አይተናል። በመሰተዓምሮች ላይ እነ (/እንገአ-/) ሆኖ በአጉዋዳኝነት ይከሰታል። ብዛት የሚገለፀው በምዕላድ ሰይሆን በሀረግ ነው። ይኸውም እንደ መዓት፣ ጅንድ እና ሁሉ ያሉ የመጠን ቃላትን ከንጠላ ስሞች ጋር በመጠቀም ነው። ይህም ስምሳሌ፣ መዓት በግ፣ በግለት ነው። እንዳንድ ከግዕዝ የተወረሱ ስሞች ቁጥርን በግዕዙም ሆነ በአማርኛው ስርዓት ያሳያሉ። ያታ ተባዕታይና እንስታይ ብቻ እንደሆነና እንስታቱ ብቻ /ኢ-(ት)/ /-ኢ/ በሚል ምዕላድ እንደሚገለፅ ተገንዝበናል። የዕምርነት ምዕላዱም /ኡ-/ ሲሆን፣ /-ኢ/ ከሚለው የእንስታይ ያታ ምዕላድ ጋር ሲዋሀድ /-ዋ/ እየሆነ እንደሚከሰት አይተናል።

ግሶች መደብ፣ ቁጥር እና ያታ አመልካች የሆኑ ምዕላዶችን እንደሚያሳዩ አይተናል። መደብ አመልካቾቹ የግሱን አምድ ቀድመው ወይም ተከትለው ሊገቡ ይችላሉ። ይህም በግሱ የአንቀፅ አይነት ላይ የተመሰረተ ነው። አንቀፁ ቀዳማይ ሲሆን፣ ትጣዮቹ አምዱን ይከተላሉ፣ አንቀፁ ካለዓይ ሲሆን ይቀድማሉ። በቀዳማይ አንቀፅ የመደብና የቁጥር ወይም የመደብና የያታ ምዕላዶች ተዋህደው ይገኛሉ። በካለዓይ አንቀፅ እነዚሁ ምዕላዶች ተለያይተው

ርባታ

ይታያሉ። መደብ አመልካቾቹ /ኡ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ ሲሆኑ፣ ቁጥር አመልካቾቹ ደግሞ /-ን-/ /-ኡ-/ ናቸው።

ሁለት አይነተኛና አራት መሰስተኛ አንቀፆችን አይተናል። እነሱም አቃጅ፣ ወጣኝ፣ ቀጣይና ጨራሽ ናቸው። ቀጣዩ ከቀዳማይ አንቀፅ፣ ሌሎቹ ከካልዓይ አንቀፅ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ቀጣዩ ብቻ አገናዛቢ የባለቤት አፀፋ ያስከትላል።

ግሶች ጊዜንና ስልትን ለመግለፅ በየአንቀፁ ላይ ቅጣዮችንና ወይም ረዳት ግሶችን ያስከትላሉ። አንቀፆቹ የድርጊቱን አይነት ያሳያሉ። ረዳት ግሶቹ /አል-/፣ /ንኡ-/ እና <u>ነበር</u> የሚሉት ናቸው። እነዚህ ድርጊቱ የተፈፀመበትን ጊዜ ያሳያሉ። ይሁን እንጅ፣ እንደ ዋና ግስ ሆነው ይረባሉ። ሲረቡ፣ እንደ <u>ሰበረ</u> ያሉ ግሶች ከሚከተሉት የርባታ ሰርዓት በመጠኑ ያፈነግጣሉ። ይህ የሚታየው በተለይ /ንኡ-/ በሚለው ረዳት ግስ ነው። ይህ ግስ የሚያስከትለው ቅጣይ አፀፋ የተሳቢ ነው። ሁለተኛም የመደበኛ ግሶች አሉታዊ ምዕላድ /አል-/ ሲሆን፣ የረዳት ግሶቹ፣ <u>የአለ</u> እና <u>የነው</u> ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ <u>የለም</u> እና <u>አይደለም</u> ነው። በዚህም ይህን ክፍል እንሰናበታለን።

መልመጃ

1. መደብ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ከሚኖረው ሚና ጋር የተያያዘ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ።
2. የመደብ ምዕላዶች ቅርፅ ከአንቀፅ አይነት ጋር እንዴት እንደሚያያዝ በምሳሌ ይግለፁ።
3. የያታ ምዕላዶች ቅርፅ እንደየቃል ከፍሉ ይለያያል። ምዕላዶቹን እየጠቀሱ ከየቃል ከፍሉ ምሳሌ ይስጡ።
4. ሁለቱን ዋና ዋና የአንቀፅ አይነቶች ሰም ይጥቀሱና ለአያንዳንዳቸው ሁለት ምሳሌ ይስጡ።
5. የቀጣይና የጨራሽ አንቀፅን ባህሪ ይግለፁ።
6. /-አችች/ የሚለው ምዕላድ የብዙ ቁጥር መግለጫ አይደለም፣ የተባለበትን ምክንያት ከነማሰረጃው የግለፁ።
7. ቀጫጭን የሚለው ቃል ቀጭን ከሚለው ላይ እንዴት እንደተመሰረተ ዘርዝረው ያስረዱ።
8. የቀዳማይ አንቀፅ እምድ ሊያስከትል የሚችለውን የምዕላድ አይነትና መጠን ይግለፁ።
9. የመደብና የያታ ምዕላዶች በአንድ ቅርፅ የሚከሰቱት በምን አምድ ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።
10. በጊዜና በአንቀፅ መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።
11. <u>ሰበረ</u> እና <u>ሰብሮአል</u> በአንቀፅና በጊዜ እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ ያስረዱ።
12. የእማርኛ ግሶች የ"ሀ" እና የ"ለ" ተብለው የሚከፈሉበትን ምክንያት ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

ምሰረታ

ባለፈው ንዑስ ክፍል የሶስቱን ዋና ዋና የቃላት ክፍሎች የርባታ ሰርዓት ተመልክተናል። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራትን ለማመልከት የተለያዩ ቅጣዮችን ሰማሰቀደም፣ ሰማሰክተል፣ አንዲሁም ራሳቸውን በክፈል ወይም በሙሉ በመድገም ቅርፃቸውን በክፈል ሲለዋውጡ አይተናል። በዚህም የርባታ ሰርዓት የአንዱ ክፍል ቃላት ከሌላው ክፍል ቃላት በቅርፃቸው አንዴት እንደሚለዩም ለማሳየት ሞክረናል።

ሰርዓቱ ሰየክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ለተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራት ቅርፃቸውን አንዴት እንደሚለዋውጡ እንጅ፣ አንዴት አንደማመሰረቱ የማያሳይ አይደለም። ያለውን የሚቀያይር እንጅ፣ አዳዲሰ ቃላትን የሚፈጥር ሰርዓት አይደለም። ቅርፅ መቀያየር የቃላት አንደኛው ባህሪ ነው። ሌላው ባህሪ ለአዳዲሰ ቃላት ምሰረታ መሰረት መሆን ነው። ይህን ሲያደርጉ የሚከተሉት ራሱን የቻለ ሰርዓት አለ። ሰዚህ ክፍል የምናየው ይህን ሰርዓት ነው።

ካሁን ሰፊት እንዳደረግነው ሁሉ፣ አሁንም አያንዳንዱን የቃላት ክፍል ሰየተራ አየወሰድን ለአዳዲሰ ቃላት ምሰረታ እንዴት መሰረት ሲሆን እንደሚችልና የነባር ቃላትንም ውስጣዊ አቀነጃጀት ለማየት አንዴት አንደሚረዳ እንመረምራለን - ከመሰተዋድድና ከመሰተንምር በለተቀር። አነዚህን የማናይበት ምክንያት በውስጣቸው የሚገኙት ቃላት ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ክፍል ቃላት መሰረት ሲሆኑ የማይችሉ በመሆናቸው ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል እንደተገለፀው፣ የነዚህ ክፍሎች ቃላት ይዘት ወይም ፍሬ የላቸውም። ሰለዚህም ሲረቡና ሲራቡ አይችሉም፣ መሆን ናቸው። ይዘት ባሳቸው ክፍሎች ውስጥ የሚገኘው የቃላት መጠን ሲጨምር፣ የአነሱ አይጨምርም። ባሰፉት አሰርት አመታት አያሌ ሰሞች፣ ግሶችና ቅፅሎች ተፈጥረዋል። ለምሳሌ ሰደርግ ዘመን አንደ ሰኬት፣ ፍንዳታ፣ ቆይታ፣ ጭምብል፣ ወዘተ፣ ያሉ ሰሞች ተፈጥረዋል። አሁን ደግሞ አንደ ወነነ፣ አመከነ፣ ተገበረ፣ ያሉ ግሶችና አንደ ሙሰና፣ ተሞክሮ፣ ወዘተ፣ ያሉ ሰሞች፣ አንዲሁም አንደ ጨለምተኛና ዘገምተኛ ያሉ ቅፅሎች ብቅ ብቅ ብለዋል። ቀደም ሲልም ሆነ አሁን፣ አንድም መሰተዋድድ ወይም መሰተንምር የሆነ ቃል አልተፈጠረም፣ በውሰትም ከሌላ ቋንቋዋ አልገባም። ለዚህም ምክንያቱ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው መሰተዋድዶችና መሰተንምሮች የግብር እንጅ የይዘት ቃላት አለመሆናቸው ነው። ግብራቸውም ውሰን ሰለሆነ መጠናቸውም አንደዚሁ ውሱን ነው።


ባለፈው ክፍል እንደተጠቀሰው፣ አንደመሰተዋድድ ያለ ቃል ሁሉ በራሱ ይህ ነው የሚባል ትርጉም የለውም። ከስሙ አንደምንረዳው፣ የመሰተዋድድ ተግባር ይዘት ያሳቸው ቃላት እየተዋቀሩ ሀረግ ሲመሰርቱ የሚፈጥሩትን መዋቅራዊ ዝምድና ማሳየት ነው። ለምሳሌ፣

የሚለውን መዋቅር ብንመለከት፣ እንደ የሚለው መስተዋድድ የንጋት ኮከብ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ ስማዊ ሀረጉ ከሌላ ካልተጠቀሰ ነገር ጋር የሚነፃፀር መሆኑን የሚገልፅ ቃል ሆኖ እናገኘዋለን። ለስማዊ ሀረጉ የሚያበረክተው የትርጉም አስተዋፅዖ የለውም። የሀረጉ ትርጉም የተመሰረተው ንጋት እና ኮከብ በሚሉት የይዘት ቃላት ላይ ብቻ ነው። እንደ የሚለው መስተዋድድ ንፅፅርን የማሳየት ተግባር ብቻ ያለው የግብር ቃል ነው። ስለዚህም ለአዳዲስ ቃላት መሰረት ወይም ዘር ሊሆን አይችልም። በዚህም ምክንያት በዚህ ክፍል የምናተኩረው እንደ ኮከብ እና ንጋት ባሉ የይዘት ቃላት ላይ ነው።

ትኩረታችን በሁለት ወገን ነው። በአንድ በኩል የምናውቃቸውን፣ ማለትም የነባር ቃላትን፣ ውስጣዊ አቀነጃጀት ማየት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የእቀነጃጀቱ ስርዓት የማናውቃቸውን አዳዲስ ቃላት እንዴት እንደሚፈጥር መረዳት ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ገና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ፅንሰ-ቃላት በእያንዳንዱ ቁዋንቁዋ ተናጋሪ ልሳነ ተፈጥሮ ውስጥ እንዳሉ ገልፀን ነበር። እንደነዚህ ያሉ ቃላትን ለእብነት ያህል በዚህ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ለማየት እንሞክራለን። በስሞች እንጀምራለን።

ውልድ ስሞች


ሁለት አይነት ስሞች አሉ። እንደኛው እንደ ቤት፣ ሰው፣ ሴት፣ በግ፣ ልጅ፣ መዝሙር ያሉ ስሞችን የያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደ ስውነት፣ ሴትነት፣ ልጅነት፣ መዝሙር ያሉ ስሞችን የሚያካትት ነው። የመጀመሪያው አይነት ስሞች ክርኒሞች የተመሰረቱ ነፃ ምዕላዶች ናቸው። ስለዚህም ስነ-ድምፅ ልሳናዊ ምዕላዶች ይባላሉ። ለምሳሌ ቤት የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ /ብ/፣ /ኤ/ እና /ት/ ከሚሉት ሁለት ተናባቢና ከአንድ አናባቢ ድምፅ የተፈጠረ ባለአንድ ቀለም ምዕላድ ሆኖ እናገኘዋለን። አፈጣጠሩ ባለፈው ክፍል ባየነው የቁዋንቁዋው የቀለም አወቃቀር ስርዓት መሰረት ሲሆን፣ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው።



2

ሁሉቱ ተናባቢ ድምፆች አናባቢውን ማዕከል አድርገው መዋቅሩን እንደፈጠሩ በግለፅ ይታያል። በስነ-ድምፅ ደረጃ መዋቅሩ ቀለማዊ ሲሆን፣ በስነ-ምዕላድ ደረጃ ምዕላዳዊ ነው፤ ትርጉም ሰላለው።

ይህ ምዕላድ ከሌላ ጥገኛ ከሆነ ምዕላድ ጋር በመዋቀር ቃል ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ፣ /-ኧኘኧ/ የሚል ምዕላድ እንዲከተለው ብናደርግ፣ *ቤተኛ* የሚል ቃል ይሰጠናል። የሁለቱ አወቃቀርም እንደሚከተለው ነው።



ሁለቱ ምዕላዶች ተዋቅረው *ቤተኛ* የሚል ቃል መሰርተዋል። ይህ ቃል የሁለት ምዕላዶች ውጤት ስለሆነ፣ ስነ-ምዕላዳዊ ቃል ተብሉ፣ ከፍ ሲል ካየነው ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ምዕላድ ይለያል። በዚህም መሰረት ከፎኒሞች የሚዋቀሩትና፣ እንደ <u>ቤት</u> ያሉት ነባር፤ ከምዕላዶች የሚዋቀሩት እንደ <u>ቤተኛ</u> ያሉት ደግሞ ውልድ ሰሞች ይባላሉ። በዚህ ከፍል የምናየው ምዕላድ ከምዕላድ ወይም ከቃል ጋር እየተቀናጀ ቃላት የሚፈጥርበትን ስርዓት ነው። ወደ ዝርዝር የምስረታው ሂደት እንግባ።

ውልድ ሰሞች ከስም፣ ከቅፅል እና ከግስ ሊወለዱ ይችላሉ። ከነዚህ ከፍሎች እንዴት እንደሚወለዱ ከስም ከሚወለዱት በመጀመር ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን። ሰሞች ሰሌሎች ሰሞች ወላጅ ሲሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ከፍ ሲል ነባር ሰሞች ያልናቸው ናቸው። ከነሱ የሚወለዱ ሰሞች የረቂቅ ሰሞች ናቸው። በአይን የማይታይ ባህሪን ያመለክታሉ። ሁለት አይነት የረቂቅ ሰሞች አሉ። የመጀመሪያው አይነት ከነባር ሰሞች ላይ /-ንነኧት/[1] የሚል ምዕላድ ሲጨመር የሚወለዱ ሰሞችን የያዘ ነው። ዝርዝር ሁኔታውን በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን።

[1] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ። ለአቀራረብ እንዲቀል፣ በዚህ ከፍል የሚሰጡት ምሳሌዎች በሙሉ፣ ሁኔታ ካላስገደደ በስተቀር፣ በመደበኛው ስርዓተ ዕሀፈት ይፃፋሉ። ቅጣይ ምዕላዶቹ ብቻ በፎኒማዊ አፃፃፍ በእዝባር ውስጥ ይፃፋሉ።

ነባር ስም	ውልድ ስም		4
ሰው	ሰው-ነት	ሰውነት	
ልጅ	ልጅ-ነት	ልጅነት	
ሴት	ሴት-ነት	ሴትነት	

የዚህ አይነት ስሞች ከስም ብቻ ላይሆን፣ ከቅፅልም ሊወለዱ ይችላሉ። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው።

ቅፅል	ስም		5
ደግ	ደግ-ነት	ደግነት	
ጥሩ	ጥሩ-ነት	ጥሩነት	
ብልህ	ብልህ-ነት	ብልህነት	
ቸር	ቸር-ነት	ቸርነት	

የነዚህን ሁለት አይነት የረቂቅ ስሞች የአፈጣጠር ስርዓት እንደሚከተለው አጠቃሉ ማስቀመጥ ይቻላል።

ስርዓት 1፣

[{ስም፣ ቅፅል }] + [–ነት] ⟶ [ስም]
የረቂቅ

ስርዓቱ፣ ከስም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንንኧት/ የሚል ምዕላድ ሲጨምር፣ የረቂቅ ስም እንደሚፈጠር ያሳያል። ይህ አይነት ስም የሚመሰረተው በ/–ንንኧት/ አማካኝነት ስለሆነ፣ ይህን ቅጣይ የረቂቅ ስም መስራች ምዕላድ እንለዋለን። ምዕላዱ በስሙ ወይም በቅፅሉ መድረሻ ላይ ተቀጥሎ ስለሚገባም ተከታይ ምዕላድ ይባላል። ይህን የአመሰራረት ስርዓት በመከተል ከማንኛውም ቅፅል ወይም ስም ላይ የረቂቅ ስም መመስረት ይቻላል። ለምሳሌ፣ ውብ ከሚለው ቅፅል ላይ /-ንንኧት/ን ብንጨምር፣ ውብነት የሚል ስም እናገኛለን። ይህም ውበት ከሚለው በቅርፁ የተለየ ነው። ከውበት ጋር ተዛምዶ ላለው አዲስ ፅንሰ-ሀሳብ ስያሜ ሊሆን ይችላል። የውብነትዋ ደረጃ አሰከምን ድረስ ነው ብንል? የውበትዋ ደረጃ አሰከምን ድረስ ነው? ከሚለው ጋር አንድ አይመስልም።

ሁለተኛው የረቂቅ ስሞች አይነት ከውልድ ስሞች፣ ከነባ ወይም ዕሰር ቅፅላዊ አምዶች ላይ / ኧት/ የሚል ምዕላድ በመጨመር የሚፈጠሩ ስሞችን ያጠቃልላል። ወደ ዝርዝር ሁኔታው ከመግባታችን በፊት፣ ምናልባት አምድ የሚለውን ቃል ከዚህ ላይ መግለፁ ተገቢ ይሆናል። ቃሉን ቀደም ሲል በተደጋጋሚ የጠቀስነው ቢሆንም፣ ምንም አይነት ግላዊ አልሰጠነውም።

ማንኛውም ዕስር ምዕላድን ሊያስቀጥል የሚችል ነፃ ወይም ዕስር አህድ *ሕምድ* ይባላል። የሚከተለውን አንመልከት።

ስም	ስም		
ክብር	ክብረ-ኧት	ክብረት	6
ሹም	ሹም-ኧት	ሹመት	
ቅፅል	ስም		
ብስል	ብስል-ኧት	ብስለት	
ቅርብ	ቅርብ-ኧት	ቅርበት	
ብልጥ	ብልጥ-ኧት	ብልጠት	
ዕውቅ	ዕውቅ-ኧት	ዕውቀት	

ከዚህ በላይ የሚታዩት ውልድ ስሞች ከነፃ ስማዊና ቅፅላዊ አምዶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከዚህ በታች የሚታዩት ደግሞ ከዕስር አምዶች ላይ ይህንኑ ምዕላድ በማስከተል የተመሰረቱ ውልድ ስሞች ናቸው።

ቅፅል	ስም		
ድርስ-	ድርስ-ኧት	ድርስት	7
ቅብጥ-	ቅብጥ-ኧት	ቅብጠት	
ክስር-	ክስር-ኧት	ክስረት	
ፍጥር-	ፍጥር-ኧት	ፍጥረት	
ውፍር-	ውፍር-ኧት	ውፍረት	
ውርድ-	ውርድ-ኧት	ውርደት	
ግድፍ-	ግድፍ-ኧት	ግድፈት	

የእነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ዕስር አምዶች ከፍል በርግጥ ቅፅል መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ከፍላቸው ምናልባትም ስም ሊሆን ይችላል። ይህን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነበት ምክንያት ስምና ቅፅል ተመሳሳይ የሆነ የአምድ አመሰራረት ስርዓት ሊከተሉ ስለሚችሉ ነው። ስምሳሌ፣ *ቅርፅ* የሚለውን ስምና *ብልጥ* የሚለውን ቅፅል ብናነፃፅር፣ የአምድ አመሰራረታቸው ስርዓት እንድ ሆኖ እናገኛለን። ሁለቱም አምዶች የተመሰረቱት ከሶስት ተናባቢና /እ/ ከሚለው አናባቢ ነው። በሁለቱም አምዶች ውስጥ አናባቢው ድምፅ የሚገኝበት ቦታ ከመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ ቀጥሎ ነው። ይህም አንደሚከተለው ማለት ነው።

/ተ-ተ-ተ/ ⟶ [ተእተተ]

ተ= ተናባቢ

ይህን ስርዓት ተከትሎ አንደ *ብልጥና ቅርፅ* ያሉ ነፃ አምዶችን ባንድ በኩል፣ አንደ *ውፍር-* አና *ግድፍ-* ያሉ ዕስር አምዶችን በሌላ በኩል መመሰረት ስለሚቻል፣ ክፍ ሊል አንደተገለፀው፣ የዕስር አምዶችን የቃል ከፍል በውል

ለመለየት አስቸጋሪ ነው። መለየት የማያስቸግረው እንደ ውፍረትና ግድፈት ያሉትን ውልድ ቃላት ክፍል ነው።

ከላይ የሚታየው የተናባቢና የአናባቢ አቀነጃጀት እንደ ልብስ፣ ፍርድ፣ ምርት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን አፈጣጠር የሚያካትት ስለሆነ፣ የሰምና የቅፅል የጋራ ሰርዓት ነው፣ ለማለት ይቻላል። በዚህ አመለካከት መሰረት ከላይ በተራ ቁጥር (1) ያስቀመጥነውን ሰርዓተ እንደሚከተለው አድርገን ማሻሻል ይኖርብናል።

ሰርዓት 2፣

[{ሰም፣ ቅፅል}+[{–ነት፣–ኧት}] ⟶ [ሰም] የረቂቅ

ሰርዓቱ ከሰም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንንኧት/ ወይም /–ኧት/ የሚለውን ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር አዳዲስ የረቂቅ ስሞችን መፍጠር ይቻላል፣ የሚል ነው። ለምሳሌ፣ ይህን ህግ በመከተል እንደ ንድፈት፣ ንቅፈት፣ ንፍቀት፣ ፅንፈት፣ ንጥፈት፣ ግልፀት፣ ብግነት፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ስሞችን በመፍጠር ለአዳዲስ ሰንፀ-ሀሳብ መግለጫ ማዋል ይቻላል። ሰርዓቱ እንደ ቅብጠት ያለ ቃላትን ውስጣዊ አተነጃጀት ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን፣ አንደ ንፍቀት ያሉና ገና በጥቅም ላይ ያልዋሉ ፅንስ-ቃላትንም አፈጣጠር ያሳያል።

የረቂቅ ስሞች ረቂቅ ባህሪን ስለሚያመለክቱ የብዛት ምልክት የላቸውም። በዚህም አካላዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚያመለክቱት ተቆጣሪ ስሞች ይለያሉ። ለምሳሌ፣ ልጅ ብሎ፣ ልጅ-አች ማለት ሲቻል፣ ብልጠት ብሎ ብልጠት-አች ማለት ግን አይቻልም። ብልጠት ሊቆጠር የሚችል የቁሳዊ ነገር ስም አይደለምና።

ከረቂቅ ስሞች ቡተጨማሪ ሌሎች ስሞችንም ከነባር ስሞችና ቅፅሎች ላይ መመስረት ይቻላል። ስሞቹ የሚመሰረቱት ከአንዳንድ የወል ስሞችና የባህሪ ቅፅሎች ላይ /-አ/ የሚል ምዕላድ አንደሚከተለው በመጨመር ነው።

ስም	ውልድ	8
ውሻ	ውሽ-አ	ውሾ
ሌባ	ሌብ-አ	ሌቦ
ንፍጥ	ንፍጥ-አ	ንፍጦ
ቅፅል	ሰም	
ቂል	ቂል-አ	ቂሎ
ሞኝ	ምኝ-አ	ሞኞ
ብልጥ	ብልጥ-አ	ብልጦ

የአፈጣጠራቸው ሰርዓት የሚከተለውን ይመሰላል።

ስርዓት 3፣ [[[{ስም፣ ቅፅል}] + [-አ]] ⟶ [ስም] መጥሪያ

ስርዓቱ ከቅፅል ወይም ከስም ላይ /-አ/ ሲጨመር፣ የመጥሪያ ስም እንደሚፈጠር ያመለክታል።

እንደነዚህ አይነቶቹ የባህሪ ስሞች ናቸው። አንድ ሰው ሌባ ከሆነ፣ ይህን ባህሪውን ስመግለፅ በመደበኛ ስሙ ሳይሆን፣ በባህሪው ሌባ! ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ካሳ፣ አበበ፣ አስቴር፣ ወዘተ፣ ብለን እንድን ሰው በተፀውዖ ስሙ እንደምንጠራው ሁሉ፣ እንደ ባህሪው አይነት ሌባ፣ ውሸ፣ ወዘተ፣ እያልን በባህሪው ልንጠራው እንችላለን።

እንደ ሌባ ያሉ ስሞችን ከሌሎች ስሞች ለየት የሚያደርጋቸው ስዋስዋዊ ሳይሆን፣ ርባታዊ ባህሪያቸው ነው። ይህም እንደ ሌሎች ስሞች የቁጥር ምዕላድ የሆነውን /-አች/ን ስማስከተል አለመቻላቸው ነው። እንደነዚህ አይነት ስሞች ብዛትን (ጥቂትነትን) የሚያሳዩት /እንንኦ-/ የሚለውን እጉዋዳኝ ምዕላድ በማስቀደም ነው። ስለዚህም፣ እነ-ሌባ እንጅ፣ ሌቦች ብሎ መጥራት አይቻልም። ሌቦች ብሎ መሳደብ ግን ይቻላል። /እንንኦ-/ የሚለው ምዕላድም ከተፀውዖ፣ ማለትም ከመደበኛ የመጥሪያ ስሞችና ከዚህ በፊት ባየነው ክፍል እንደተገለፀው፣ ከጠቁዋሚ መስተዓምሮችና ተውላጠ ስሞች ጋር የሚሄድ ምዕላድ ነው። ስምሳሌ፣ <u>ካሳ</u> ብሎ፣ <u>እነ-ካሳ</u> እንጅ፣ <u>ካሳ-አች</u> አይባልም። እንደዚሁም <u>ይህ</u> ብሎ <u>እነ-ይህ</u> (እነዚህ) እንጅ <u>ይህ-አች</u> አይባልም። እንደ ሌባ ያሉ ስሞችም ልክ እንደ <u>ካሳ</u> አይነት ስሞች፣ /እንንኦ-/ የሚለውን ምዕላድ መውሰዳቸው፣ ከፍላቸው ከፍ ሊል እንደተጠቀሰው፣ ከተፀውዖ ስሞች ጋር ነው፣ ስማለት ያስችላል።

በስዋስዋዊ ባህሪያቸው፣ የመጥሪያ ስሞች ከወል ስሞች የተለዩ አይደሉም። እንደ ማንኛውም የወል ስም በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ወይም ተሳቢ ሆነው ሊገቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ መጣ 9
(ለ) ሌባ መጣ

ማለት እንደሚቻል ሁሉ፣

(መ) ካሳን አየሁት
(ለ) ሌባን አየሁት

ማለት ይቻላል።

እስካሁን የተመለከትነው፣ ስሞች ከቅፅል ወይም ከሌሎች ስሞች እንዴት እንደሚመሰረቱና ቅርፃዊ ባህሪያቸውም ምን እንደሚመስል ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስሞች ከግሳዊ ስሮች ወይም አምዶች ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ እናያለን። ወደ ዝርዝሩ ከመሄዳችን በፊት ግን <u>ስር</u> ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ይኖርብናል። በአማርኛ፣ የማናቸውም ግስ እንደዚሁም

የተወሰኑ ቅፅሎችና ስሞች መሰረት፣ ተናባቢ ድምፆች ናቸው። የተናባቢዎቹ ቁጥር ከአንድ እስከ ስድስት እንደሚደርስ ሊታውንት ይናገራሉ።

እያንዳንዱ ተናባቢ ድምፅ እግር ይባላል። ተናባቢዎቹ አንድ ላይ ሆነው የሚፈጥሩት ቅንጅት ስር ይባላል። ይህ ስር እንደ ተናባቢዎቹ ቁጥር ባለ ሁለት፣ ባለሶስት፣ ወዘተ፣ እግር እየተባለ ይለያል። ስሩ ብቻውን አጠቃላይ የሆነ ቅርፅና ትርጉም አለው። ስለዚህም ምዕላድ ነው። ለምሳሌ /ብ - ል- ጥ-/ የሚለውን ስር ብንወስድ፣ ከመብለጥ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሆነ ትርጉም እንዳለው እንረዳለን። ቅርፁም እንደዚሁ ከተናባቢዎች ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ አሻሚ ነው። ምክንያቱም ከዚሁ ስር ላይ ቅፅልን፣ ግስን ወይም ስምን መፍጠር ስለሚቻል ነው። አሻሚነቱን ለማጎድ፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን ማስገባት ያስፈልጋል። ይህን ስናደርግ፣ የሚፈጠረው ቅርፅ <u>አምድ</u> ይባላል። አምዱ የግስ፣ የቅፅል ወይም የስም ሊሆን ይችላል። በአቁዋሙም ነፃ ወይም ዕስር ሊሆን ይችላል። ከዚህ አምድ ላይ፣ ልዩ ልዩ ቅጣዮችን በመጨመር የተለያዩ ቃላትን መመስረት ይቻላል። የተመሰረቱትን ቃላት ክፍልም ማወቅ ይቻላል። የስሩን ክፍል ማወቅ ግን አይቻልም። የሁሉም እናት ስለሆነ ሁሉ-ገብ ነው። ይህ የአግርኛ ብቻ ሳይሆን የሴም ቁዋንቁዋዎች አጠቃላይ ባህሪ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው፣ ውልድ ስሞች ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከስሩ የሚፈጠሩት፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ አናባቢዎችን በመጨመር ሲሆን፣ ከአምዱ ላይ የሚፈጠሩት ቅጣዮችን፣ ማለትም መስራች ምዕላዶችን፣ በማስከተል፣ በማስቀደም ወይም የየስሩን ተናባቢ በመድገም ነው። ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ከግስ ስር የሚመሰረቱት የሚከተሉትን ይመስላሉ።

<u>ስር</u>	<u>ስም</u>	
/ል- ብ- ስ/	[ልእብስ]	ልብስ
/ጥ- ቅ- ም/	[ጥእቅእም]	ጥቅም
/ም- ር- ት/	[ምእርት]	ምርት
/ው- ር- ስ/	[ውእርስ]	ውርስ

እነዚህ እይነት ስሞች በግሱ ስር ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች፣ ባንዱ ወይም በሁሉቱም ላይ /እ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ በመጨመር የሚፈጠሩ ናቸው። ሁኔታው /እ/ የሚለውን ድምፅ፣ ስም መስራች ምዕላድ ነው፣ ሊያስኝ የሚችል ይመስላል። በርግጥ ይህን ማለት ግን አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ይህ ድምፅ በስሩ ውስጥ የሚታዩትን ሶስቱን ተናባቢ ድምፆች ከተራ ድምፅነት ወደ ቀለምነት የመለወጥ ስነ-ድምፅ ልሳናዊ የሆነ ተግባር ስላለው ነው። ይህን ተግባር በሚፈፅምበት ጊዜ የሚፈጠረው ቅርፅ እንዳጋጣሚ ስም ሲሆን ችሎአል። ሌላም ሊሆን ይችል ነበር፣ ለምሳሌ ቅፅል። ይህን ወደ ሁዋላ በቦታው

እናየዋለን፡፡ ከዚህ ላይ ግን ከግስ ስር ሳይ [እ]ን በመጨመር የሚፈጠር ስም፣ እፈጣጠሩ ስነ- ምዕላዳዊ ነው ከማለት ይልቅ፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፡ ማለቱ የሚበጅ ላይሆን እይቀርም፡፡ ምክንያቱም ከቁዋንቁዋው የቀለም አወቃቀር ስርዓት አንፃር ስናይ፣ ለቀለሙ መፈጠር የእናባቢው /እ/ መግባት የግድ ነው፡፡ እናባቢው /እ/ ባይሆን ኖሮ፣ ስርዓቱ ስነ-ምዕላዳዊ ይሆን ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ንጉስ [ንእግሉስ] የሚለውን ስም ብንመለከት፣ /ን-ግ-ስ/ ከሚል ስር ላይ /እ/ን እና /ሉ/ን በተናባቢዎቹ መካከል በማስገባት የተፈጠረ ቃል መሆኑን እንረዳለን፡፡ /እ/ የገባው በቀለማዊ ስርዓት መስረት ነው፡፡ በስነ-ድምፁ ክፍል እንዳየነው፣ በቃል መነሻ ላይ ቁዋንቁዋው የተናባቢ ክትትሎሽን አይፈቅድም፡፡ ተናባቢዎች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ፡ ከትትሎሹን ለመስበር [እ] በመካከላቸው ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚገባው /እ/ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፡፡ የተናባቢ ክትትሎሽ በሚፈቀድበት አውድ ላይ የሚገባ /እ/ ወይም ሌላ አናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት [ንእግሉስ] በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው [እ] ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሲሆን፣ /-ሉ-/ የሚለው እናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር /-ሉ-/ ቅፅል መስራች ምዕላድ ነው፡፡ ምክንያቱም አገባቡ የተናባቢ ክትትሎሽን ለማፍረስ ላይሆን፣ በተናባቢ ብቻ ከተመሰረተው ስር ውስጥ ገብቶ ቃል ለመፍጠር ስለሆነ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ቁዋንቁዋው በቃል መሀል እና መጨረሻ ላይ የሁለት ተናባቢ ክትትሎሽን ይፈቅዳል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም እንደ <u>ውርሰ</u> ያሉ ለሞችን ከግሱ ስር ከመመስረት ይልቅ፣ ለምን ከራሱ ከግሱ መመስረት ለይቻልም? የሚል ነው፡፡ ይህም <u>ውርሰ</u> የሚለውን ስም ለምን <u>ወረሰ</u> ከሚለው ግስ ላይ በቀጥታ መመስረት አይቻልም? እንደ ማለት ነው፡፡ ርግጥ፣ ይህን ማለት ይቻላል፡፡ ግን ሂደቱ ብዙና ውስብስብ ነው፡፡ እስቲ እንመልከተው፡፡

<u>ወረሰ</u> የሚለው ግስ ድምፃዊ ቅንጅት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

/ው - ኧ - ርር - ኧ - ሰ -ኧ/ 11

በዚህ ቅንጅት ውስጥ ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች አሉ፡፡ <u>ውርሰ</u> በሚለው ስም ውስጥ ግን ከላይ እንዳየነው፣ እንድ የ/እ/ ድምፅ ብቻ ይታያል፡፡ እንግዲህ <u>ውርሰ</u> የሚለው፡ <u>ወረሰ</u> ከሚለው ግስ ላይ ተመስረተ ብንል፣ አንደኛ፣ <u>ወረሰ</u> ውስጥ ያሉት ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች ወደ አንድ የ/እ/ ድምፅ ተለውጠዋል፡ ወይም ከናባቱው ጠፍተዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ለውጥ መግለፁ ራሱ አንድ ስራ ነው፡፡ አስቸጋሪም ነው፡፡ ምክንያቱም ለለውጡ ጥሩ መንስዔ መስጠት የሚቻል አይመስልም፡፡ ሁለተኛ፣ <u>ወረሰ</u> የሚለው ግስ ስም የሚሆነው /ኧ/ የሚለው ድምፅ ወደ /እ/ ሲለወጥ ነው ካልን፣ /እ/ ስም መስራች ምዕላድ እንጅ፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ተናባቢዎቹን ድምፆች ወደ ቀለም የሚለውጥ ድምፅ አይደለም፡ ማለት ነው፡፡ በሌሎች ቃላት ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን /እ/ ቀለም መስራች መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ብልሀ /ብእልሀ/ በሚለው ቅፅል ውስጥ /እ/

አለ። ይህ /እ/ ግን ቅፅል መለራች አይደለም። ምክንያቱም ቅፅሉ የሚመስረትበት "በለሽ" የሚል ግስ በቁዋንቁዋው ውስጥ የለም። ይህም አናባቢው /እ/ የገባው በቀለም መሰራችነት መሆኑን ያሳያል። ይህ ከሆነ፣ /ውእርስ/ በሚለው ሰም ውስጥ ያለው /እ/ም እንደዚሁ ቀለም መሰራች ነው፣ ለማለት ይቻላል። ይህን ካልን ደግሞ፣ ቃሉ ወረሰ ከሚለው ግስ /ኧ/ን በ/እ/ ለውጦ የመጣ ነው፣ የሚለው አመለካከት ትክክል አይሆንም። አቁዋራጩና ትከክለኛ የሚመሰለው መንገድ፣ /ውእርስ/ የሚለው ሰም /ው - ር - ስ/ ከሚለው ሰር ላይ በቀጥታ ተመስረተ የሚለው ነው። በዚህ ከተስማማን፣ እንደ ውርስ ያሉ ሰሞች የሚፈጠሩበትን አጠቃላይ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሰርዓት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

ሰርዓት 4፡

/ተ - ተ - ተ/ ⟶ [ተአተተ]

ከምሳሌው እንደሚታየው፣ ከዚህ ሰርዓት እንደ ውርስ ያሉ ነፃ እምዶችን መፍጠር ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ሰርዓት እንደ [ቅእልም-] ያሉ ዕሰር አምዶችንም መፍጠር ይችላል። ከነሱም ላይ እንደ /-አሽ/ እና እንደ /-ንንአ/ ያሉ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር፣ የሚከተሉትን አይነት ሰሞች መፍጠር ይቻላል።

ሰር	ሰም	12
ቅልም-	ቅልም-አሽ	ቅልሞሽ
ሰርቅ-	ሰርቅ-አሽ	ሰርቆሽ
ግርድ-	ግርድ-አሽ	ግርዶሽ
ጥብቅ	ጥብቅ-ንንአ	ጥብቅና
ድርቅ	ድርቅ-ንንአ	ድርቅና
ግብር-	ግብር-ንንአ	ግብርና
ትህት-	ትህት-ንንአ	ትህትና

/-አሽ/ የሚለው ምዕላድ የሚጨመረው፣ እንደነዚህ ባሉ አሰር አምዶች ላይ ብቻ አይደለም። በነፃ አምዶች ላይም ሊቀጠል ይችላል። ለምሳሌ ቅብብል ብሎ ቅብብል-አሽ፣ ድብብቅ ብሎ ድብብቅ-አሽ፣ ድግግም ብሎ ድግግም-አሽ፣ ወዘተ፣ ማለት ይቻላል። እንደነዚህ አይነት ሰሞች አንዳንድ ጊዜ የአንድን ነገር ተደጋጋሚ ሂደት ሲያመለክቱ፣ ሌላ ጊዜ ውጤቱን ይጠቁማሉ። ለምሳሌ፣

(ሀ) ልጆቹ ቅብብሎሽ ይጫወታሉ 13

ብንል፣ ቅብብሎሽ የሚለው ስም የሚያመለክተው የአንድን ነገር የመቀባበል ረዥም ሂደት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣

(ለ) ካላ ጥሎሽ ጥሎ (ስጥቶ) ሚስት አገባ

ብንል፣ <u>ጥሎሽ</u> የሚለው ቃል የሚገልፀው፣ ስሙሽራ የሚሰጠውን ስጦታ ነው። ይሁን እንጅ፣ በዚህ ትርጉሙም ቢሆን፣ ስሙሽራ ስጦታ ሲሰጥ ጣል ጣል የማድረግን ተደጋጋሚ ድርጊት ሊያሳይ ይችላል።

/-ንን/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት የሚፈጠሩት፣ አንደ <u>ግብርና</u> ያሉት፣ አንድ ሰው የሚሰራበትን ወይም የሚኖርበትን ሁኔታ ወይም ሙያ ስለሚያመለክቱ፣ የሙያ ወይም የሁኔታ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ።

ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ አንደተዘረዘሩት ያሉ ናቸው።

<u>አምድ</u>	<u>ሰም</u>	14
ስብር-	ስብር-ኣት	ስብራት
ሽልም-	ሽልም-ኣት	ሽልማት
ስቅል-	ስቅል-ኣት	ስቅላት
ንቅሰ-	ንቅስ-ኣት	ንቅሳት
ዕርም-	ዕርም-ኣት	ዕርማት

ከሰንጠረዡ አንደሚታየው፣ ስሞቹ የተፈጠሩት ከዕሰር ምዕላዶቹ ላይ /-ኣት/ የሚለውን መሰራች ምዕላድ በመቀጠል ነው። በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ስሞች አንድ ነገር ከተደረገ በሁዋላ የሚገኘውን ውጤት ያመለክታሉ። ለምሳሌ፣ <u>ዕርማት</u> የሚለው ስም የሚያመለክተው አንድ ነገር ከታረመ በሁዋላ፣ የሚገኘውን ውጤት ነው። የማረሙን ሂደት የሚያመለክተው ቃል <u>ዕረማ</u> ሲሆን፣ የዚህ ሂደት ውጤት ደግሞ <u>ዕርማት</u> ይባላል[2]።

ከላይ በተራ ቁጥር (4) በተመለከተው ስርዓት መሰረት ([ተኣተ(ተ)-]) በሚወጡ ሌሎች ዕሰር አምዶች ላይ /-ኣት/ ወይም /-ኣትኣ/ የሚል ሌላ ምዕላድ በመጨመር አንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል።

[2] ይሁን አንጅ፣ አርማት የሚለው ራሱ አንደ ሂደት ስም ስለሚያገለግል <u>ዐረማ</u> የሚለውን ቃል አግዶታል። <u>ዐረማ</u> በሂደት ስምነት የሚታወቀው <u>ዐረም</u> ከማረም ጋር በተያያዘ ቅርፁ ነው። ርግጥ፣ ሁለቱም የማይፈለግ ነገርን ከሚፈለገው አየለዩ የማስወገድን ተግባር ያለመለክታሉ።

አምድ	ስም	15
ፍጅ	ፍጅ-አትአ	ፍጀታ
ችል-	ችል-አትአ	ችሎታ
ስም	ስም-አትአ	ሰሞታ
ብስ-	ብስ-አት	ብሶት
ቅንጥ-	ቅንጥ-አት	ቅንጠት
ስርቅ-	ስርቅ-አት	ስርቆት

እንደነዚህ ያሉ ስሞችም የሚያመለክቱት ውጤትን ይመስላል። ስምሳሌ፣ እንድ ሰው የሚፈጀው ነገር ፍጀታው ሲሆን፣ የሚችለው ነገርም እንደዚሁ ችሎታው ነው። ሁኔታው የተለያየ ቅርፅ ያላቸው የውጤት ስሞች እንዳሉ ያሳያል።

እስካሁን ያየናቸውን የውልድ ሰሞች የአመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው እድርጎ ማጠቃለል ይቻላል።

ሰርዓት 5፣

[ተአተ-(ተ)-(አ)ተ] + [{-ኧት፣-አሽ፣-ኣት፣-አ፣-አት፣-አትኣ፣-አንንኣ}] ⟶ [ስም]
አምድ ቅጣያ ውጤት

በእምዱ ውስጥ፣ በቅንፍ የተመለከቱት ተናባቢና እናባቢ ድምፆች ሲኖሩም፣ ላይኖሩም ይችላሉ። የተናባቢዎቹ መኖር ወይም አለመኖር፣ የሁለተኛውን (የተከታዩን) አናባቢ ድምፅ መኖር ወይም አለመኖር ይወሰናል። እነሱ ሲገኙ፣ እሱም ይገኛል።

ከዚህ በላይ ተጠቃሎ የተቀመጠው አንዱ አይነት የስሞች አመሰራረት ስርዓት ሲሆን፣ ሌላው አይነት የሚከተሉት ስሞች የሚፈጠሩበት ነው።

	ስር	አምድ	ስም	16	
(ሀ)	/ድ - ክ - ም/	/ድ - ክአም/	[ድአክአም]		ድካም
	/ጥ - ግ - ብ/	/ጥ - ግአብ/	[ጥአግአብ][3]		ጥጋብ
	/ድ - ግ - ፍ/	/ድ - ግአፍ/	[ድአግአፍ]		ድጋፍ
	/ዝ - ን - ብ/	/ዝ - ንአብ/	[ዝአንአብ]		ዝናብ
	ስር	አምድ	ስም		
(ለ)	/ቅ - ድድ-ስ/	/ቅ - ድድአስ-/	[ቅአድድአስ-ኤ]		ቅዳሴ
	/ግ - ስስ -ፅ/	/ግ - ስስአፅ-/	[ግአስስአፅ-ኤ]		ግሳፄ
	/ው - ድድ-ስ/	/ው - ድድአስ-/	[ውአድድአስ-ኤ]		ውዳሴ
	/ት - ክክ -ዝ/	/ት- ክክአዝ-/	[ትአክክአዜ-ኤ]		ትካዜ

[3] እተራረቡ ድምፀ ልሳናዊ ሂደትን አያመለክትም።

በ(ሀ) ውስጥ የተዘረዘሩት ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /አ/ን በማስገባት የሚፈጠሩ ስሞች ናቸው። ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /አ/ የተናባቢ ከትትሎሽ አንዳይፈጠር የገባ አናባቢ ነው። ተግባሩ ለነ-ድምፀ ልሳናዊ ስለሆነ፣ ስለሞቹ ምስረታ አስተዋፅየ የሚያደርገው /እ/ ብቻ ነው።

በ(ለ) ስር የሚታዩት፣ በ(ሀ) ስር አንዳሉት፣ /አ/ የሚለውን አናባቢ ከመድረሻው ተናባቢ በፊት በማስገባት፣ አምድ የሚፈጠሩና በየአምዱ መድረሻ ላይም /-ኤ/ የሚለውን ምዕላድ በመቀጠል የሚፈጠሩ ናቸው። ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /እ/ የተናባቢ ከትትሎሽ አንዳይኖር የገባ አናባቢ ነው።

የስሞቹን የአመሰራረት ስርዓት አንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

ስርዓት 6፣

[[ተእተ(-ተ)እተ-]	+	[(-ኤ)]]	⟶	[ተእተ-(ተ)እተ-(ኤ)]
አምድ		ቅጣይ		የውጤት ስም

በዚህ ስርዓት መስረት የሚፈጠሩ ለሞች የሚያመለክቱት የአንድን ተግባር ውጤት ነው። ለምሳሌ <u>ውዳሴ</u> የሚለው ለም የሚገልፀው፣ ተግባርን ወይም ሂደትን ሳይሆን፣ የሂደትን ውጤት ነው። የሂደቱ ስም <u>ውደሳ</u> ሲሆን፣ የተግባሩ ስም <u>ማወደስ</u> ወይም በግዕዝ መልኩ <u>መወድስ</u> ነው።

ከላይ ከቀረቡት የተለየ የአመሰራረት ስርዓት ያላቸው የውጤት ስሞችም አሉ። አነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

<u>አምድ</u>	<u>ስም</u>	17
ውጥ-	ውጥ-ኤት	ውጤት
ስል-	ስል-ኤት	ስሌት
ስም-	ስም-ኤት	ስሜት
ምር-	ምር-ኤት	ምሬት
ስክ-	ስክ-ኤት	ስኬት
ቅል-	ቅል-ኤት	ቅሌት

አምዶቹ ዕስር ናቸው። የንግግር ክፍላቸውን በትክክል መናገር ያስችግራል። ይሁን እንጅ፣ ከእነሱ ላይ /-ኤት/ የሚለውን ቅጣይ በመጨመር ስሞቹን መመስረት ይቻላል። የእመሰራረት ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 7፣

[[ተእተተ-]	+	[-ኤት]]	⟶	[ተእተተ-ኤት]
አምድ		ቅጣይ		የውጤት ስም

ከሌሎች ዕስር አምዶች ላይ ተከታይ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

18

<u>አምድ</u>	<u>ስም</u>	
ድርግ-	ድርግ-ኢት	ድርጊት
ቅንጅ-	ቅንጅ-ኢት	ቅንጅት
ግፍ-	ግፍ-ኢት	ግፈት
ዕልቅ-	ዕልቅ-ኢት	ዕልቂት
ድርጅ-	ድርጅ-ኢት	ድርጅት
ስርጭ-	ስርጭ-ኢት	ስርጭት
ትንብ-	ትንብ-ኢት	ትንቢት

እነዚህ የውጤት ስሞች ይመስላሉ፡፡ ምናልባትም፣ እንደ <u>ስርጭት</u> ያሉት የሂደት ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሂደት ስሞች አንድ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊትን እንደሚገልፁ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ መዋቅራዊ ባህሪያቸው [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድዳዊ አውድ ውስጥ ለመግባት መቻል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን አንመልከት፡፡

19

(ሀ) መድሀኒቱ በስርጭት ላይ ነው
(ለ) ወታደሮቹ በውጊያ ላይ ናቸው
(መ) *ወታደሮቹ በትንቢት ላይ ናቸው

<u>ስርጭትና ዕልቂት</u> [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድድ ውስጥ ገብተው ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ሲመሰርቱ ችለዋል፡፡ ትንቢት የሚለው ስም ግን በዚሁ ቦታ ገብቶ የፈጠረው አረፍተ ነገር ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህም በመነሳት <u>ስርጭት</u> የሂደት፣ <u>ዕልቂት</u> የውጤት ስም ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ የሁለቱ ስሞች ስነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ አገባባዊ ባህሪያቸው ለየቅል መሆኑን ከምሳሌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ ጊዜ የሂደትና የውጤት ስሞችን በአገባባቸውም ቢሆን ለመለየት ያስቸግራል፡፡ ይህን ዝቅ ብለን እንመለከታለን፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ስሞች አመሰራረት ግን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 8፣

[[ተእተ-(እ)ተ-ተ)] - + [-ኢት]] ⟶ [ተእተ-(እ)ተ-(ተ)-ኢት]
እምድ ቅጣይ የውጤት ስም

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ደግሞ እንመልከት፡፡

አምድ	ስም		20
ግፍ-	ግፍ-ኢይኣ	ግፊያ	
ግብዝ-	[ግአብዝ--ኢይኣ]	[ግአብዃኦኣ]	ግብጥ
ዝርፍ-	ዝርፍ-ኢይኣ	ዝርፊያ	
ሽም-	ሽም-ኢይኣ	ሽሚያ	
ቅድም-	ቅድም-ኢይኣ	ቅድሚያ	
ግጥም-	ግጥም-ኢይኣ	ግጥሚያ	
ፍልም-	ፍልም--ኢይኣ	ፍልሚያ	
ድርስ-	[ድአርሰ-ኢይኣ	[ድእርሸኣ]	ድርሻ

እነዚህ የተመሰረቱበት አምድ ከላይ በተራ ቁጥር(8) የሚታየው አይነት ሲሆን፣ መሰራቹ ምዕላድ /-ኢይኣ/ ነው፡፡ ስርዓቱም የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 9፣

[(ተእተ-ተ) - + [--ኢይኣ]] ⟶ [ተእተ-ተ)-ኢይኣ]
አምድ ቅጣይ የሂደት ስም


በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች በአብዛኛው ሂደትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ውጤትንም ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ግብጥ የሚለውን ስም ብንወስድ፡ በአንድ ምክንያት የተዘጋጀ ድግስን፣ ማለትም ውጤትን፣ ወይም ድግሱን የመብላትን ሂደት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ትርጉሙ አሻሚ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድርሻ የሚለውን ቃል ብንመለከት፡ አንድ ሰው አንድ ነገር ከሌሎች ጋር ተካፍሎ ሲጨርስ፡ የሚደርሰውን መጠን ስለሚያመለክት የውጤት ስም ነው፡፡

ሌሎች የማያሻሙ የውጤት ስሞችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

አምድ	ስም	21
ሽፍት-	ሽፍት-ኣ	ሽፍታ
ቁምጥ-	ቁምጥ-ኣ	ቁምጣ
ጭፍን-	ጭፍን-ኣ	ጭፍና
ጭፍር-	ጭፍር-ኣ	ጭፍራ
ብስን-	ብስን-ኣ	ብስና

የእነዚህ የአመሰራረት ስርዓት የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 10፣




ስርዓቱ በየዕስር አምዱ ላይ /-አ/ የሚለውን መሰራች ምዕላድ መቀጠል አንደለብን ያሳያል።

አሁን ደግሞ ወደ ሌሎች የውጤት ስሞች አመሰራረት አንሂድና የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት።

ስር	ስም	22
/ሰ - ር - ግ/	[ሰኧርግ]	ሰርግ
/ም - ል - ስ/	[ምኧልስ]	መልስ
/ሽ - ፍ - ጥ/	[ሸኧፍጥ]	ሽፍጥ
/ብ - ል - ግ/	[ብኧልግ]	በልግ
/ስ - ል - ፍ /	[ስኧልፍ]	ሰልፍ
/ጥ - ር - ብ/	[ጥኧርብ]	ጠርብ

የነዚህና የመሳሰሉት ስርዓት የሚከተለው ነው።

ስርዓት 11፣



ስርዓቱ ከየስሩ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ /ኧ/ የሚለውን አናባቢ በማሰገባት የውጤት ስሞችን መፍጠር አንደሚቻል ያመለክታል። በዚህ ሰርዓት ከሚመሰረቱትም ብዙዎቹ ነፃ አምዶች ናቸው። በነሱ እና በጥቂት ሌሎች አምዶች ላይ /-ኧኝኝአ/ የሚል ምዕላድ በመጨመር እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መፍጠር ይቻላል።

ሰም	ስም	23
ግንብ	ግንብ-ኧኝኝአ	ግንበኛ
ሰልፍ	ሰልፍ-ኧኝኝአ	ሰልፈኛ
ፈረስ	ፈረሰ-ኧኝኝአ	ፈረሰኛ
ጥበብ	ጥበበ-ኧኝኝአ	ጥበበኛ
ሰፈር	ሰፈረ-ኧኝኝአ	ሰፈረኛ

እንደ <u>ለልፍ</u> ያሉት የውጤት ስሞች ሲሆኑ፣ ከእነሱ ላይ የሚመሰረቱት እንደ <u>ለልፈኛ</u> ያሉት የውጤቱን ባለቤት ወይም ተላታፊ የሚያመለክቱ ስሞች ናቸው። በዚህም ምክንያት የሙያተኛ ስሞች ሲባሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ግንበኛ በግንብ ስራ ላይ የተሰማራ ሙያተኛ ነው። ይሁን እንጅ፣ እንደ <u>ሰፈረኛ</u> (ሰፈርተኛ) ያሉት በተለያየ ለፈር የሚኖርን ሰው ለለሚያመለክቱ፣ የአካባቢ ነዋሪዎች ስሞች ሲባሉ ይችላሉ። ለርዓታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ለርዓት 12፣

[[ስም] + [-ኛንኝኣኛ]] ⟶ [ስም]
ቅጣይ የሙያ ስም

ከፍ ሲል ካየናቸው በተጨማሪ፣ ያለምንም ቅጣይ ምዕላድ በየስሩ ውስጥ በሚታዩት ክፍት ቦታዎች ላይ /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በመጨመር ብቻ የሚፈጠሩ ሌሎች የውጤት ስሞች አሉ። እነሱም የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ለር	ለም		24
/ቅ - ል - ም/	[ቅኧልኧም]	ቀለም	
/ቅ - ር - ጥ/	[ቅኧርኧጥ]	ቀረጥ	
/ቅ - ልል -ብ/	[ቅኧልልኧብ]	ቀለብ	
/ም -ድ - ብ/	[ምኧድኧብ]	መደብ	
/ን - ግ - ር/	[ንኧግኧር]	ነገር	
/ዝ - ፍ - ን/	[ዝኧፍኧን]	ዘፈን	
/ግ - ድ - ብ/	[ግኧድኧብ]	ገደብ	
/ስ - ብ - ብ/	[ለኧብኧብ]	ስበብ	

የነዚህም ለርዓት እንደሚከተለው ነው።

ለርዓት 13፣

[ተ-ተ(ተ)-ተ] ⟶ [ተኧተ-(ተ) ኧተ]
ስር የውጤት ስም

እንደ /-ኧ-/ ያሉ በየስሩ ውስጥ እየገቡ ቃል የሚመስርቱ አናባቢዎች <u>ሰረ-ገብ</u> መስራች ምዕላድ ሲባሉ ይችላሉ። ይሁን እንጅ፣ /-ኧ-/ን በማስገባት የሚፈጠሩ ዕስር አምዶችም አሉ። ከእነሱ ላይ ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር የሚፈጠሩት ግን ነፃ ናቸው። የሚከተሉት የእነሱ ምሳሌ ናቸው።

ስር	አምድ	ስም	25
/ስ - ብ - ር/	/ስኧበኧር-/	/ስኧበኧር-ኣ/	ሰበራ
/ፍ - ት - ን/	/ፈኧተኧን-/	/ፈኧተኧን-ኣ/	ፈተና
/ዝ - ር - ፍ/	/ዘኧረኧፍ-/	/ዘኧረኧፍ-ኣ/	ዘረፋ
/ድ - ግ - ፍ/	/ደኧገኧፍ-/	/ደኧገኧፍ-ኣ/	ደገፋ
/ቅ - ዝ - ፍ/	/ቀኧዘኧፍ-/	/ቀኧዘኧፍ-ኣ/	ቀዘፋ
/ም - ክ - ት/	/መኧከኧት-/	/መኧከኧት-ኣ/	መከታ

ቅጣዩ ምዕላድ /-ኣ/ ሲሆን፣ በእሱ አማካኝነት የሚፈጠሩት የሂደት ወይም የውጤት ስሞች ናቸው። ለምሳሌ፣ እንደ ስበራ እና ቀዘፋ ያሉት የአንድን ድርጊት ሂደት ሲያመለክቱ፣ እንደ ደገፋ እና ፈተና ያሉት ውጤትን ሲያመለክቱ የሚችሉ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሂደት ስሞች በ----ላይ በሚል መስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ መግባት ስለሚችሉ፣ ከሌሎች አይነት ስሞች በቀላሉ ይለያሉ። ስለዚህም፣

ካሳ (በ) አንጨት ስበራ ላይ እንዳለ ተጠራ 26

ማለት ይቻላል። የቃላቱን ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ስርዓት 14፣

[[ተኧተኧተ-] [+ -ኣ]] ⟶ [ተኧተኧተ-ኣ]
አምድ ቅጣይ የሂደት ስም


ከዕስር አምድ ላይ የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞችን ደግሞ እንመልከት፣

ስር	አምድ	ስም	27
/ስ-ብ-ክ/	/ስኧብኣክ-/	/ስኧብኣክ-ኢ/	ሰባኪ
/ጥ-ር-ግ/	/ጥኣርኣግ-/	/ጥኣርኣግ-ኢ/	ጠራቂ
/ወ-ል-ድ/	/ውኧልኣድ-/	/ውኧልኣድ-ኣ/	ወላጅ
/ት-ር-ት/	/ትኧርርኣት-/	/ትኧርርኣት-ኢ/	ተራች
/ፍ-ር-ድ/	/ፍኧርኣድ-/	/ፍኧርኣድ-ኢ/	ፈራጅ

እንደነዚህ ያሉት አድራጊ ስሞች ይባላሉ። አንድን ተግባር የሚፈፅምን አካል ወይም ሀይል ያመለክታሉ። የሚመስረቱትም ከዕስሩ አምድ ላይ /-ኢ/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው። አምዱ በየስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ እና /-ኣ-/ን እንደ ቅደም-ተከተላቸው በማስገባት ይፈጠራል። በስነ-ድምፁ ከፍል እንዳየነው፣ /-ኢ/ የላየኛ እናበቢ ስለሆነች፣ ቀድሞአት የሚገባውን ተናባቢ ወደ (ድ)ላንቃዊነት እንደምትለውጠው መገንዘብ ያስፈልጋል።

የሰሞቹን አፈጣጠር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ሰርዓት 15፣




ከዚህ ሰርዓት ጋር ተቀራራቢ በሆነ መንገድ የሚከተሉትን አይነት ሰሞች መፍጠር ይቻላል።

ስር	አምድ	ስም	28
/ጥ-ርር-ግ/	[ጥኧርርኣግ-]	[ጥኧርርኣግ-ኢ]	ጥራጊ
/ው-ድድ-ቅ/	[ውኧድድኣቅ-]	[ውኧድድኣቅ-ኢ]	ውዳቂ
/ል-ቅቅ-ም/	[ልኧቅቅኣም-]	[ልኧቅቅኣም-ኢ]	ልቃሚ
/ፍ-ልል-ጥ/	[ፍኧልልኣጥ-]	[ፍኧልልኣጥ-ኢ]	ፍላጭ

እንደነዚህ ያሉት ሰሞች፣ አንድ ድርጊት ሲፈፀም ተርፎ ወይም ወድቆ የሚቀርን ነገር የሚያመለክቱ ናቸው። ስለዚህም የቅሪት ስሞች ሊባሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ጥራጊ የሚለው ስም ምርት ከተነሳ በሁዋላ እውድማ ተጠርጎ የሚገኝን ቀሪ ወይም ትርፍ እህል የሚገልፅ ቃል ነው። በእንዳንድ አካባቢ <u>ግርድ</u> ይባላል። "ምርትና ግርዱ ይለያል" የሚባለው ለዚህ ነው።

የዚህ አይነት ሰሞች በትርጉማቸው ተደራጊ ናቸው። ይህን ለማመልከት ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን ያጠብቃሉ። ለምሳሌ ጠራጊን (/ጥኧርኣግ-ኢ/) እና ጥራጊን ([ጥኧርርኣግኢ]) ብናነፃፅር፣ ጥራጊ ውስጥ የሚገኘው /ር/ ጥብቅ መሆኑን እንረዳለን። ሌሎች ተደራጊ ሰሞች ተደራጊነትን የሚያሳዩት /ተ-/ የሚል ምዕላድ በአድረጊው ስም መነሻ ላይ በማስገባት ነው። ይህም <u>ጠራጊ</u> ብሰን፣ <u>ተ-ጠራጊ</u> እንደምንለው ነው። ሁለቱን ተደራጊ ሰሞች ለመለየት፣ እንደ ጥራጊ ያሉትን <u>የድራጊ</u> ስሞች ልንላቸው እንችላለን። ያፈጣጠር ሰርዓታቸው እንደሚከተለው ነው።

ሰርዓት 16፣



እስካሁን የየናቸው ስሞች እንድም ከግሱ ስር ወይም ከአምዱ መድረሻና መካከል ላይ የተለያዩ መስራች ምዕላዶችን በመቀጠል የሚፈጠሩ ሲሆኑ፣ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ የሚፈጠሩት ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞች ናቸው።፡

ስር	አምድ	ስም	29
/ስ-ድ-ብ/	/-ስድኧብ/	/ምኧ-ስድኧብ/	መስደብ
/ስ-ብ-ር/	/-ስብኧር/	/ምኧ-ስብኧር/	መስበር
/ፍ-ልል-ግ/	/-ፍኧልልኧግ/	/ምኧ-ፍኧልልኧግ/	መፈለግ
/ጥ-ር-ግ/	/-ጥርኧግ/	/ምኧ-ጥርኧግ/	መጥረግ
/ፍ-ል-ጥ/	/-ፍልኧጥ/	/ምኧ-ፍልኧጥ/	መፍስጥ

እንደነዚህ ያሉት ስሞች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አርዕስት በመባል ይታወቃሉ። ተግባራቸው ድርጊትን ማመልከት ስለሆነ የድርጊት ስሞች ልንላቸው እንችላለን። የሚፈጠሩት /ምኧ-/ የሚለውን ቅጥያ በየአምዱ መነሻ ላይ እንደሚከተለው በመቀጠል ነው።

ስርዓት 17፣

[[ምኧ-] ተ-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ]] ⟶ [ምኧ-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ]
ቅጣይ አምድ የድርጊት ስም

ከስርዓቱ እንደሚታየው፣ ከአምዱ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ ያለው አናባቢ /-ኧ-/ ሊገኝ ወይም ሳይገኝ ይችላል። ይህን የሚወስነው የአምዱ ከፍል ነው። ቀደም ሲልም ሆነ፣ ባለፈው ንዑስ ከፍል እንደተጠቀሰው፣ የእግርኛ ግሶች የ(ሀ) እና የ(ለ) ተብለው በሁለት ከፍል ይመደባሉ። የ(ሀ) ከፍል የሚባሉት ቅድመ-መድረሻ እግራቸውን ሳያጠብቁ የሚመስረቱና የሚረቡ ናቸው። በዚህ መሰረት ከላይ በሚታየው የምስረታ ሂደት፣ እንድ አምድ የ(ለ) ከፍል ከሆነ፣ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ቀጥሎ /-ኧ-/ን ያስገባል። <u>በመስበርና</u> <u>በመፈለግ</u> መካከል የሚታየው የአመሰራረት ልዩነት ከዚህ የመነጨ ነው። <u>ሰበረ</u> የ(ሀ) ከፍል ግስ ሲሆን፣ <u>ፈለገ</u> የ(ለ) ከፍል ግስ ነው፣ ስለዚህም ቅድመ-መድረሻ እግሩን ያጠብቃል። ከመነሻ እግሩ ቀጥሎም /-ኧ-/ን ያስገባል።

ከነዚህ አርዕስታዊ ስሞች ላይ /-ኢይኣ/ የሚል ምዕላድ በመቀጠል ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል። ዝርዝሩን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት።

	<u>አርእስት</u>	<u>ስም</u>	30
መጥረግ	/ምኧጥርኧግ/	/ምኧጥርኧግ-ኢይኣ/	መጥረጊያ
መስበር	/ምኧስብኧር/	/ምኧስብኧር-ኢይኣ/	መስበሪያ

መግለጥ	/ምኽግልኽጥ/	/ምኽግልኽጥ-ኢይኣ/ [ምኽግልኽዮኣ]	መግለጫ
መፍለጥ	/ምኽፍልኽጥ/	/ምኽፍልኽጥ-ኢይኣ/ [ምኽፍልኽዮኣ]	መፍለጫ

የዚህ አይነት ስሞች አንድ ነገር የሚፈፀምበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ መሳሪያ፣ ዘዴ፣ ወዘተ፡ ስለሚያመለክቱ፣ በጥቅሉ የማድረጊያ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ። መስረታቸውም ከፍ ሲል የተመለከትናቸው የድርጊት ስሞች ናቸው። የአፈጣጠራቸው ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 18፣

[[መ-ተ-ኽተ] +[-ኢይኣ]] ⟶ [መ-ተ-ኽተ-ኢይኣ]
አምድ ቅጣይ የማድረጊያ ስም

እስካሁን ያየናቸው ውልድ ስሞች ከግስ ስሮች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን በመጨመር ወይም ከአምዶች ላይ የተለያዩ መለራች ቅጣዮችን በማስቀደም ወይም በማለከተል የሚፈጠሩ ናቸው። ከዚህ ቀጥሎን ከነዚህ ለየት ያለ የአፈጣጠር ስርዓት ያላቸውን ስሞች እንመረምራለን።

ስር	አምድ	ስም	31
/ስ-ብ-ር/	/-ሰሰኽብኣብኽር/	/ኣ-ሰሰኽብኣብኽር/	አሰባበር
/ን-ግ-ር/	/-ንንኽግኣግኽር/	/እ-ንንኽግኣግኽር/	አነጋገር
/ል-ብ-ስ/	/-ልልኽብኣብኽስ/	/ኣ-ልልኽብኣብኽስ/	አለባበስ
/ል-ቅ-ስ/	/-ልልኽቅኣቅኽስ/	/ኣ-ልልኽቅኣቅኽስ/	አለቃቀስ
/ው-ል-ድ/	/-ውውኽልኣልኽድ/	/ኣ-ውውኽልኣልኽድ/	አወላለድ

የነዚህ ስሞች አፈጣጠር፣ በየአምዱ ላይ ቀዳሚ ቅጣይ የሚጨምር ብቻ ሳይሆን፣ የየአምዱን የመነሻ እግር የሚያጠብት፣ ቅድመ-መድረሻውን የሚደጋግምና በተደጋጋሚዎቹ እግሮች መካከል /-ኣ/ የሚሰውን አናባቢ ድምፅ የሚያስገባ ነው። መጀመሪያ የአምዱን አፈጣጠር እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 19፡

/1 - 2 - 3/ ⟶ /-11ኽ2ኣ2ኽ3/

ከቀስቱ በፊት የሚታዩት ቁጥሮች የስሩን ሶስት ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ። ከነዚህ ውስጥ በአንድ ቁጥር የተወከለው፣ ማለትም መነሻው፣ ተናባቢ ይጠብቃል። በሁለት ቁጥር የተወከለው፣ ቅድመ-መድረሻ ድምፅ ደግሞ ራሱን ይደግማል። ከዚያም በተደጋጋሚዎቹ ድምፆች መካከል /-አ-/ን፣ በሌሎቹ ከፍት ቦታዎች /-እ-/ን በማስገባት አምዱን ይመሰርታል። በተመሰረተው አምድ መነሻ ላይ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ ያስገባል።[4] ዝርዝር ሰርዓቱ የሚከተሰውን ይመስላል።

ስርዓት 20፣

[[አ-]+ [11እ2አ2እ3]] ⟶ [አ-11እ2አ2እ3]
ቅጣይ አምድ የአደራረግ ስም

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች የሚያመሰክቱት የአንድን ተግባር አፈፃፀም ማለትም <u>አደራረግን</u> ነው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሳቢ ዘር በመባል ይታወቃሉ። ሳቢ ዘር የሚባሉበት ምክንያት ተናባቢ ድምፃቸውን በመሳሳብ፣ ማለትም በመደጋገም፣ ሰፋ ሰፋ ያለ አምድ ስለሚመሰርቱ ነው።

አስካሁን ከስምና ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ወይም የተለያዩ አናባቢዎችን በግሱ ስር ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ስሞችን አንዴት መመስረት እንደሚቻል አያየን መጥተናል። በየስርዓቱ የሚፈጠሩ ስሞችን ከትርጉማቸውና ከቅርፃቸው አኩዋያ ለመከፋፈል ሞክረናል። በዚሁ መሰረት ከግሰ ስር የሚመሰረቱትን የአድራጊ፣ የድርጊት፣ የድራጊ፣ የማድረጊያ፣ የአደራረግ፣ የውጤት፣ የሂደት፣ ወዘት፣ ስም በማለት የአንዱን

---

[4] ባየ (1987) ላይም ይህን ስም የሚመስርተው ቅጣይ /እስ-/ አንደሆነ ተገልያ ነበር። ከዚያ ወዲህ ጉዳዩን አንደገና በመመርመር ቅጣዩ ምናልባት /እስ-/ ሳይሆን፣ /አ-/ ብቻ ሊሆን አንደሚችል ለመገንዘብ ተችሎአል። ቅጣዩ /እስ-/ የማይሆንበት ምክንያት ስነ-ድምፃዊ ነው። /እስ-/ ውስጥ የምትገኘው /ስ/ ከስሩ የመነሻ እግር ጋር ሙሉ በሙሉ ትመሳሰልና ድምፁን ጠባቂ ታስመስለዋለች። ከላይ በስርዓት (19) የሚታየውም ይኸው ነው። ችግሩም /ስ/ ከማንኛውም ድምፅ ጋር መመሳሰልዋ ነው። አንድ ተናባቢ ድምፅ ሊመሳሰል የሚችለው ከማንኛውም ሌላ ተናባቢ ጋር ሳይሆን፣ በቦታ ወይም በአፈጣጠር ባህሪ ከሚቀርበው ሌላ ድምፅ ጋር ነው። ሁለተኛም /እስ-/ የሚለው ምዕላድ እስደራጊነትን እንጅ እደራረግን የማያመለክት መሆኑ ነው። ከዚህ ስንነሳ ምናልባት እደራረግ የሚገለፀው /-11እ2አ2እ3/ በሚል ዕስር አምድ ነው፣ ለማለት ይቻል ይሆናል። አምዱ ዕስር ስለሆነ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም ወደ ሙሉ ግስነት ይለወጣል። /አ-/ በሌሎች ዕስር አምዶች መነሻ ላይ አየገባ ሙሉ ግሶችን የሚመሰርትበት ብዙ ሁኔታ አለ። ለምሳሌ /-ገኘ/ ከሚለው ዕስር አምድ መነሻ ላይ በመግባት /አ-ገኘ/ የሚለውን ግስ ይመሰርታል። ስለዝርዝር ሁኔታው ባየ (1999)ን በተጨማሪ ይመልከቱ።

አይነት ከሌላው መለየት እንደሚቻል አሳይተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የውልድ ቅፅሎችን አመሰራረት እንመረምራለን።

ውልድ ቅፅሎች

እንደ ሰሞች ሁሉ ቅፅሎችም ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ነባር የሚባሉት እንደ ብልህ፣ ትሁት፣ ደግ፣ የዋህ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው። እነዚህ ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ የተመሰረቱ አይደሉም። ስለዚህም ነባር ወይም ዘር ይባላሉ። እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ቁጥር በጣም እነስተኛ ነው። አብዛኞቹ ቅፅሎች ውልድ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል። የሚወለዱትም ከሰሞችና ከግስ ስሮች ወይም አምዶች ላይ ነው። ያወላለዳቸውን ሁኔታ ከሰም ከሚወለዱት በመጀመር ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን።

ሰም	ቅፅል		
ሀይል	ሀይል-ኛኘአ	ሀይለኛ	1
ቂም	ቂም-ኛኘአ	ቂመኛ	
ወረት	ወረት-ኛኘአ	ወረተኛ	
ጉልበት	ጉልበት-ኛኘአ	ጉልበተኛ	
ጀብድ	ጅብድ-ኛኘአ	ጀብደኛ	

የእነዚህን አይነት ቅፅሎች የአመሰራረት ሂደት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 1፣

[[ሰም] + [-ኛኘአ]] ⟶ [ሰም-ኛኘአ]
ቅጣይ ቅፅል

ስርዓቱ አንድ ስም /-ኛኘአ/ የሚል ምዕላድ ሲከተለው ቅፅል ይሆናል የሚል ነው። እንደ *ወረተኛ* ያሉ ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪ ስለሚያመለክቱ፣ የባህሪ ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

ካሳ ወረተኛ ሰው ነው 2

ብንል፣ <u>ወረተኛ</u> መሆን የካሳ ባህሪ ነው፣ ማለታችን ነው።

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ ከሰሞች ላይ /-አም/ ወይም /-አምኦ/ን በመጨመር እንደሚከተለው ይፈጠራሉ።

ስም	ቅፅል		
ተራራ	ተራራ-አምምኣ	ተራራማ	3
ድንጋይ	ድንጋይ-አምምኣ	ድንጋያማ	
ኣሸዋ	ኣሸዋ-አምምኣ	አሸዋማ	
ሆድ	ሆድ-አም	ሆዳም	
ወተት	ወተት-አም	ወተታአም	
ሀብት	ሀብት-አም	ሀብታም	
ጥርስ	ጥርስ-አም	ጥርሳም	
ጥፍር	ጥፍር-አም	ጥፍራም	

ያአነዚህ አይነት ቅፅሎች የአንድን ነገር በአንድ ቦታ በብዛት መገኘትን ስለሚያመለክቱ፣ የብዛት ወይም የክምችት ቅፅል ሊባሉ ይችላሉ። አመሰራረታቸውም እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 2፣

[[ስም]+[-አም/-አምምኣ]] ⟶ [ቅፅል]
ቅጣይ የብዛት

የ/-አም/ አና የ/-አምምኣ/ አነባብ ስሞቹ በሚጠቁሙት ክምችት ላይ የተመሰረተ ያመስሳል። ነገሩ የሰውነት ክፍል፣ ወይም ከሰውነት ክፍል ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ /-አም/ን የሚያስገባ ይመስላል[5]። /-አምምኣ/ የሚለው ምዕላድ በአብዛኛው ለሰው የማይበጅ ክምችትን የሚያመለክቱ ቅፅሎችን የሚመስርት ይመስሳል። አንደ አሾህ፣ ደንጋይ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞች ወደ ቅፅልነት የሚለወጡት በዚህ ምዕላድ አማካኝነት ነው። ይሁን እንጅ፣ አንደ አይናማ፣ ወርቃማ፣ ወዘተ፣ የጥሩ ነገር መግለጫዎች ናቸው።


ሌሎች ቅፅሎች /-አውኢ/ በሚል ምዕላድ አማካኝነት ከስሞች ላይ ያመሰረታሉ። የሚከተሉት የአነዚህ ምሌሌዎች ናቸው።

ስም	ቅፅል		
ወገን	ወገን-አውኢ	ወገናዊ	4
ሀገር	ሀገር-አውኢ	ሀገራዊ	
ክልል	ክልል-አውኢ	ክልላዊ	
ዘመን	ዘመን-አውኢ	ዘመናዊ	

የአነዚህ አይንት ቅፅሎች ስርዓት አንደሚከተለው ነው።

[5] ይህ ግን ሁልጊዜ ላይሰራ ይችላል። ለምሳሌ፣ ሀብት የሚለው ስም ከሰውነት ክፍል ጋር ግንኙነት የለውም። የሚወስደው ግን /-አም/ የሚለውን ምዕላድ ነው።

ስርዓት 3፣



በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ቅፅሎች ወገንን ወይም ክፍልን ያመለክታሉ። ስለዚህም በቀደምት ሲቃውንት ዘንድ የወገን ቅፅል በመባል ይታወቃሉ። በአገባባቸው ከስሞች ጋር ስለሚመላለሱ በስም ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

(ሀ) ስዎቹ ጀግኖች ናቸው 5

ስንል፣ ስዎቹ የሚለው የእረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ለም ነው። በእሱ ምትክ ኢትዮጵያዊያን የሚለውን ቃል ብናስገባ፣ አረፍተ ነገሩ፣

(ለ) ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ናቸው

የሚል ይሆናል። ኢትዮጵያዊያን የሚለው ቃል ለዎቹ በሚለው ለም ቦታ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል። በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያዊያን ያሉ ቃላት እንደ ማንኛውም ለም ቅፅልን እያስቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ። ይህ ሲሆን፣ እንደ፣

ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን 6

ያሉ ለማዊ ሀረጎችን እናገኛለን። እነዚህ ሁኔታዎች እንደ ኢትዮጵያዊ ያሉ ቃላት ለሞች መሆናቸውን ይጠቁማሉ። ባለፈው ክፍል ለለ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ፣ አንድ ቃል በርግጥ ቅፅል ለመባል እንደ፣

*ያ በጣም---------- ተማሪ 7

ባለ ሀረግ ውስጥ በሚታየው ክፍት ቦታ ላይ መገኘት መቻል አለበት፣ ብለን ነበር። በዚህ መስፈርት መስረት፣ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያለ ቃል በዚህ ቦታ ሊገባ ስለማይችል፣ ቅፅል ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፣

(ሀ) *ያ በጣም ኢትዮጵያዊ ተማሪ 8

ማለት፣ ተቀባይነት ያለው አባባል አለመሆኑ ነው። በአንፃሩ ግን፣

(ለ) ያ በጣም መንፈሳዊ ተማሪ

ማለት ይቻላል። ይሁን እንጅ፣ ያለጥርጥር ቅፅል ናቸው፣ ሊባሉ የሚችሉ፣ እንደ መንፈሳዊ፣ ዘመናዊ፣ ፍትህዊ፣ ወቅታዊ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላትም በዚሁ በተራ ቁጥር (3) በትጠቅስው ስርዓት መስረት የሚፈጠሩ በመሆናቸው፣ ስርዓቱ ቅፅልን ብቻ ሳይሆን ሰምንም እንደሚመሰርት መረዳት ይቻላል። ባጭሩ፣ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ቃላት የወገን ስሞች ሲሆኑ፣ እንደ <u>መንፈሳዊ</u> ያሉት የወገን ቅፅሎች ናቸው፣ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ልዩነታቸውም የቅርፅ ሳይሆን፣ የአገባብ እንደሆነ ከተሰጡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል። እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ስሞች፣ በወገን ሰምነታቸው ሌሎች ስሞችን አየገለፁ ሊገቡ ይችላሉ። በዚህ አገባባቸው ገላጭ ከሆኑት ከቅፅሎች ጋር ሊመደቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው 9

ከዚህ በላይ ኢትዮጵያዊያን የሚለው ሰም ተማሪዎች የሚለውን ይገልፃል። ይሁን እንጅ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (7) እንደሚታየው፣ <u>በጣም</u> ከሚለው መጣኝ ምዕላድ ጋር ሊገባ አይችልም። ስለዚህም በተግባሩ ቅፅላዊ፣ በክፍሉ ስማዊ የሆነ ቃል ነው፣

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ከሰሞች የሚመሰረቱትን ቅፅሎች ነው። ከዚህ ቀጥሎን ደግሞ ሰማዊ ከሚመሰሉ ዕርር አምዶች ላይ የሚመሰረቱትን እንመለከታለን።

	<u>አምድ</u>	<u>ቅፅል</u>	10
ጥ-ም-ም-	/ጥኧምኣም-/	/ጥኧምኣም-ኣ/	ጠማማ
ም-ል-ጥ-	/ምኧልኣጥ-/	/ምኧልኣጥ-ኣ/	መሳጣ
ቅ-ር-ፍ-ፍ-	/ቅኧርፍኣፍፍ-/	/ቅኧርፍኣፍፍ-ኣ/	ቀርፋፋ
ቅ-ሸ-ሸ-	/ቅኧሸኣሸ-/	/ቅኧሸኣሸ-ኣ/	ቆሻሻ
ግ-ጥ-ብ-	/ግኧጥኣብ-/	/ግኧጥኣብ-ኣ/	ገጣባ
ሰ-ብ-ር-	/ሰኧብኣር-/	/ሰኧብኣር-ኣ/	ሰባራ
ት-ል-ክ-ሸ-	/ትኧልክኣሸሸ- /	/ትኧልክኣሸሸ-ኣ/	ተልካሻ

የእነዚህ አይነት ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪያዊ ወይም አካላዊ አይነት ስለሚጠቁሙ፣ የአይነት ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ። አመሰራረታቸውን እንደሚከተለው አድርጎ ማሳየት ይቻላል።

ስርዓት 4፣

[[ተኧተ(ተ)ኣ-ተ(ተ)-] + [-ኣ] ⟶ [ተኧተ(ተ)ኳተ(ት)-ኣ]]
የአይነት ቅፅል

ከዚህ ላይ /ተኧተ(ተ)እተ(ተ)-/ የሚለው ዕሰር እምድ፣ /ተ-ተ(ተ)-ተ(ተ)/ በሚለው ሰር ውስጥ /ኧ/ን እና /እ/ን እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በክፍቶቹ ቦታዎች በማሰገባት የተፈጠረ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እምዱ በራሱ ትርጉም ሆነ የቃል ክፍል የለውም። ሙሉ ቃል ሆኖ ትርጉምና የቃል ክፍል የሚያገኘው /-እ/ የሚለውን መስራች ምዕላድ ሲያስከትል ነው። ከዚህም ምዕላድ ገና ትርጉም ያላገ ፣ ባዶ ቅርፅ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል።

እስካሁን የተመለከትነው ከስሞችና ከስም-መሰል ዕሰር አምዶች ላይ ቅጣዮችን በመጨመር የሚፈጠሩትን ቅፅሎች ነው። ከዚህ ቀጥለን ከግሰ ስር ወይም አምድ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉትን እንመለከታለን።

ስር	ቅፅል	11
/ሰ-ን-ፍ/	/ሰኧንኧፍ/	ሰነፍ
/ድ-ን-ዝ/	/ድኧንኧዝ/	ደነዝ
/ድ-ር-ቅ/	/ድኧርኧቅ/	ደረቅ
/ው-ድ-ል/	/ውኧድኧል/	ወደል
/ጥ-ብ-ድ-ል/	/ጥኧብድኧል/	ጠብደል

የእንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች የአመሰራረት ሰርዓት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 5፣

[[ተ-ተ(ተ)-ተ-]	⟶	[ተኧተ(ተ)ኧተ] የባህሪ ቅፅል

ስርዓቱ እንደሚያሳየው፣ ቅፅሎቹ የሚመሰረቱት በየስሮች ውስጥ በሚታዩት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በማሰገባት ነው። እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ባህሪን ወይም መጠንን ስለሚያመለክቱ፣ ቀደም ሲል ካየናቸው፣ እንደ <u>ወረተኛ</u> ካሉ ሌሎች የባህሪ ቅፅሎች ጋር ሊጠቃለሉ ይችሉ ነበር። የአመሰራረታቸው ስርዓትና የሚመሰረቱበት ክፍል የተለየ በመሆኑ ብቻ ለብቻቸው እንዲታዩ ተደርጎአል። እንደ ዘፈን፣ ወረት፣ ከፈን፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ሰሞችን በዚህ ስርዓት እንደሚፈጠሩ በስም ምሰረታ ላይ አይተናል። ከዚህም ሁለቱ የቃላት ክፍሎች ተመሳሳይ የምስረታ ስርዓት እንደሚከተሉ መረዳት ይቻላል።

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ ብዛስ ስሮች ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ /ኧ/ እና /እ/ የሚሉትን አናባቢዎች በማሰገባት በሚከተለው ሁኔታ ይመሰረታሉ።

ስር	ቅፅል		12
/ር-ዝዝ-ም/	/ርኧዝዝኢም/	[ርኧዥዥኢም]	ረዥም
/ቅ-ጥጥ-ን/	/ቅኧጥጥኢን/	[ቅኧጭጭኢን]	ቀጭን
/ሀ-ጥጥ-ር/	/ሀኧጥጥኢር/	[ኣዮዮኢር]	አጭር
/ጥ-ይይ-ም/	/ጥኧይይኢም/		ጠይም
/ፍ-ር - -/	/ፍኧርኢ-/		ፈሪ

እነዚህም ቀደም ሲል እንዳየናቸው የመጠንና የአይነት ቅፅሎች ናቸው። እንደ ረዥም ያሉት መጠንን ሊያሳዩ፣ እንደ ቀይ ያሉት ቀለማዊ አይነትን ያመለክታሉ። በጥቅሉ የአይነት ቅፅል ልንላቸው እንችላለን። ለምሳሌ፡ "ሰውየው ምን አይነት ነው?" ብንባል፤ "ሰውየው አጭር፣ ረዥም፣ ቀይ፣ ወዘተ፡ ነው" ብለን፡ መመለስ እንችላለን። ርግጥ፡ "ሰውየው ክፉ ነው" ማለትም ይቻላል። ክፉ የሚለው ቅፅል ግን የሚያመለክተው የሰውየውን አይነት ሳይሆን፣ ግብሩን ነው። ክፉ የሚያስኘው ክፉ ምግባር ነውና። ስለዚህም የግብር ቅፅል ልንላቸው እንችላለን።

እንደነዚህ ባሉ ቅፅሎች ውስጥ ቅደመ-መድረሻው ተናባቢ ወደ ላንቃዊነት ይለወጣል። የለውጡ ምክንያት /-ኢ-/ የምትለዋ አናባቢ ድምፅ ነች። በስሩ ውስጥ /ዝዝ/ የነበረው ድምፅ በ(ድ)ላንቃዊነቱ ምክንያት ወደ [ዥዥ]፣ እንደዚሁም /ጥጥ/ የነበረው ወደ [ጭጭ] ሊለወጥ ችሎአል። በመጨረሻዎቹ ሁለት ሰሮች ውስጥ የመጨረሻው ተናባቢ ዕግር ተጎርዶአል። እንደዚሁም /ሀ-ጥጥ-ር/ በሚለው ሰር መነሻ ላይ የሚገኘው /ሀ/ ሰለ ተጎረደ፣ ቅፅሉ በ/ኧ/ ሊጀምር ችሎአል። እነዚህ በስነ-ድምፁ ክፍል ላየነው የግድፈት ሰርዓት መሰረት የመጡ ለውጦች ናቸው።

የቅፅሎቹን የአፈጣጠር ስርዓት ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን።

ሰርዓት 6፣


[ተ-ተ(ተ)-ተ] ⟶ [ተ-ኧ-ተ(ተ)-ኢ-ተ]
ቅፅል

የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት።

ሰር	እምድ	ቅፅል	13
/ክ-ብ-ር/	ክ-ብኡር	[ክእብኡር]	ክቡር
/ን-ፅ-ህ/	ን-ፅኡህ	[ንእፅኡህ]	ንፁህ
/ጥ-ቁ-ር/	ጥ-ቁኡር	[ጥእቅኡር]	ጥቁር
/ክ-ፍ - -/	ክ-ፍኡ	[ክእፍኡ]	ክፉ
/ብ-ር-ት- -/	ብ-ርትኡ	[በእርተኡ]	ብርቱ

እንደነዚህ ያሉት፣ አንድ ነገርን ብቻ አያመለክቱም። ባህሪን፣ አይነትን፣ ግብርን፣ ወዘተ፣ ሊያሳዩ ይችላሉ። የመጨረሻዎቹ ሁለት ስሮች፣ የመጨረሻ ተናባቢያቸውን ጎርደዋል። የቅፅሎቹ ስርዓተ-ፍጥረት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 7፣




ስርዓቱ ከመጨረሻው እግር በፊት ባለው ክፍት ቦታ ላይ /-ኡ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ በማስገባት፣ ቅፅሎችን መፍጠር እንደሚቻል ያመለክታል። ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /አ/ ስነ-ምዕላዳዊ ላይሆን፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተናባቢ ክትትሉሽን ለመለበር የገባ ለርጎ-ገብ አናባቢ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በየስሮቹ መካከል በሚገኙት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ን እና /-አ-/ን በማስገባትና የቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በማጥበቅ የሚመሰረቱ ሌሎች ቅፅሎች አሉ። እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ስር	ቅፅል	14
/ክ-ብብ-ድ/	/ክኧብብአድ/	ክባድ
/ቅ-ልል-ል/	/ቅኧልልኣል/	ቀላል
/ድ-ቅቅ-ቅ/	/ድኧቅቅኣቅ/	ደቃቅ
/ድ-ምም-ቅ/	/ድኧምምአቅ/	ደማቅ
/ው-ልል-ድ/	/ውኧልልአድ/	ወላድ
/ድ-ፍፍ-ር/	/ድኧፍፍአር/	ደፋር

እንደነዚህ ያሉት ይዘትን ወይም ሁኔታን ስለሚያመለክቱ የይዘት ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ። አፈጣጠራቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 8፣



እስካሁን ያየናቸው ልዩ ልዩ ስርዓቶች በቁዋንቁዋው ውስጥ በጥቅም ላይ የሚገኙትን ስሞችና ቅፅሎች ውስጣዊ አቀነጃጀት እንድንመረምር ብቻ ላይሆን፣ በጥቅም ላይ ያልዋሉ አዳዲስ ቃላትንም እንድንፈጥርና ለተለያዩ አዳዲስ ፅንሰ-

ሀሳብ ወይም ክስተት ሰያሜ በማድረግ አንድንጠቀምባቸው የሚያስችሉ ናቸው። ስርዓቶቹ የተወሰኑ ቢሆኑም ሊፈጥሩት የሚችሉት የቃላት መጠን ወሰን የለውም። ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት አንደ <u>ዘላል</u>፣ <u>ደባቅ</u>፣ <u>ቀዳድ</u>፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ቅፅሎችን መፍጠርና ለአዳዲስ ቅፅላዊ ፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ፣ በየቦታው አየዞረ የሀሰት ወሬ የሚነዛን ሰው <u>ቀዳድ</u> ልንለው አንችላለን። ወሬ የሚቀድ ማለት ነው። ወደሚቀጥለው ክፍል እንሂድ።

ውልድ ግሶች

ባለፉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች ውስጥ ስሞች ከቅፅሎችና ከግስ ስሮች፣ ቅፅሎችም ከስሞችና ከስሮች አንዴት አንደሚመሰረቱ አይተናል። በጥቅሉ ሲታይ፣ የቃላቱ የአመሰራረት ስርዓቶች አንድን የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለውጡ ናቸው። ስምን ወደ ቅፅል፣ ቅፅልን ወደ ስም፣ አንዲሁም ግስን ወደ ስም ወይም ወደ ቅፅል የሚለውጡ ስለሆኑ፣ ክፍል ለዋጭ ስርዓቶች ልንላቸው እንችላለን። በዚህም ምክንያት ክፉል ከማይለውጡት የርባታ ስርዓቶች ይለያሉ።

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ግሶች አንዴት አንደሚመሰረቱ እንመለከታለን። የግሶች የአመሰራረት ስርዓት ከስሞችና ከቅፅሎች የአመሰራረት ስርዓት የተለየ ነው። ስሞችና ቅፅሎች ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ሲመሰረቱ፣ ግሶች ግን ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ ሳይሆን፣ በአብዛኛው ከስር ላይ በአናባቢዎች አማካኝነት ከሚመሰረቱ አህጾች ላይ ነው። አህጾቹ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አፅማድ በመባል ይታወቃሉ። አፅማድ ቀደም ሲል አምድ አያልን ስንጠራው የነበረው ቃል የብዙ ቁጥር ነው። በሊቃውንቱ አመለካከት፣ ከየስሩ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉት የአፅማድ አይነቶች ሰባት ናቸው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

አደራጊ	ተደራጊ	1
አስደራጊ		
አዳራጊ	ተዳራጊ	
አደራራጊ	ተደራራጊ	

በእኔ እምነት የአፅማዱ አይነት በነዚህ ብቻ የሚወሰን አይመስለኝም፥ ያልተጠቀሱ አፅማድ ያሉ ይመስለኛል። ከነዚህም አንዱ የአንድን ድርጊት መደጋገም ወይም መዘውተር የሚያመለክተው ዕሰር አምድ ነው። ደጋጋሚ ወይም ደራራጊ አምድ ልንለው አንችላለን። ሌላው ድርጊትን የሚያመለክት ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ መዳረግን የሚያሳይ ነው። ዳራጊ አምድ ሊባል ይችላል። በዚህ መሰረት የአፅማዱ ዝርዝር የሚከተለው መሆን አለበት።

ደራጊ አድራጊ አሰደራጊ	ተደራጊ
ዳራጊ አዳራጊ (ሀ) አዳራጊ (ለ)	ተዳራጊ
ደራራጊ አደራራጊ (ሀ) አደራራጊ (ለ)	ተደራራጊ

ከዝርዝሩ አንደሚታየው 12 የአዕማድ አይነቶች አሉ። ከዚህ ቀጥሰን የአያንዳንዳቸውን ዝርዝር የአመሰራረት ሁኔታ እንመልከታለን።

ደራጊ አዕማድ

ደራጊ አዕማድ የሚባሉት ያለምንም መሰራች ቅጣይ ምዕላድ በቀጥታ በየግሱ ስር ውስጥ /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በማስገባት የሚፈጠሩ ናቸው። የሚገባው አናባቢ ቁጥር አንደ አዕማዱ አይነትና አንደ ተናባቢው ቁጥር ይለያያል። ለባለ ሶስት አግር ቀዳማይ አንቀፅ የሚያሰፈልገው አናባቢ ሁለት ሲሆን፣ ለባለ አራት እግር የሚያለፈልገው ሶስት ነው። ዝርዝር ሁኔታውን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስር	ቀዳማይ አዕማድ	
/ሰ-ብ-ር/	/ለኧብብኧር-/	ሰበር-
/ል-ም-ን/	/ልኧምምኧን-/	ለመን-
/ፍ-ል-ግ/	/ፍኧልልኧግ-/	ፈለግ-
/ድ-ም-ር/	/ድኧምምኧር-/	ደመር-
/ጅ-ም-ር/	/ጅኧምምኧር-/	ጀመር-
/ድ-ግ-ስ/	/ድኧግግኧስ-/	ደገስ-

አንደነዚህ ያሉ ዕስር የቀዳማይ አንቀፅ አዕማድ ናቸው። ነፃ የሚሆኑት መደብ አመልካች ቅጣዮችን ሲያስከትሉ ነው። ለምሳሌ ስበር- የሚለው አምድ አንደኛ መደብ አመልካች የሆነውን /-ክኡ/ን ሲያሰከትል፣ ስበር-ኩ ይሆናል። ይህም ዕስር ሳይሆን፣ ነፃ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ ነው። ከፍ ሲል አንደተጠቀሰው፣ የአነዚህ አይነት ግሶች ያለቀ ድርጊትን ስለሚገልፁ፣ ደራጊ አዕማድ ብለናቸዋል። ድርጊቱ ያለቀ መሆኑን የሚገልፁት በሰሩ መካከል በሚገባው አናባቢና በቅድመ-

መድረሻው ተናባቢ ድምፅ ጥብቀት ነው። ስርዓተ-ፍጥረታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 1፣

ስር		ደራጊ አምድ
[1 - 22 - 3]	⟶	[1Ⅹ22Ⅹ3-]
/ድ - ግ - ስ-/		[ድⅩግⅩስ-]

በመጀመሪያው ቅንፍ ውስጥ የሚታዩት ቁጥሮች የሰሩን ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ። ስሩ ከሶስት የተለያዩ ተናባቢዎች እንደተመሰረተ ያመለክታሉ። አምዱ ከመነሻውና ከቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ /-Ⅹ-/ የሚለውን አናባቢ በመጨመርና ቅድመ-መድረሻውን ተናባቢ በማጥበቅ ይመሰረታል። ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ጥብቅ መሆኑን ለማመልከት ቁጥሩን ደግመን እንፅፈዋለን።

ደራጊ ግሶች ድርጊትን ሰለሚያመለክቱ በጥቅሉ ገቢር ግሶች ሊባሉ ይችላሉ። እንደ መዋቅራዊ ባህሪያቸውም <u>*ሳቢ*</u> ወይም <u>*ኢሳቢ*</u> ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ሳቢ የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ጋር የሚዋቀሩት ሲሆኑ፣ ኢሳቢ የሚባሉት ይህን ማድረግ የማይችሉት ናቸው። ዝርዝር ልዩነታቸውን በክፍል ሶስት እንመለከተዋለን፤ ለአብነት ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) አስቴር [ልብስ ተኮሰች] 2
(ለ) አስቴር [---- ሳቀች]

በመጀመሪያው ምሳሌ <u>ተኮሰች</u> የሚለው ግስ <u>ልብስ</u> ከሚለው መሙሊያ ስም ጋር ተዋቅሮአል። ስሙ የግሱ ተሳቢ፣ ማለትም ተጎጅ ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ግን <u>ሳቀች</u> የሚለው ግስ ያለምንም ተሳቢ ብቻውን ይታያል። ሁለቱም ግሶች ገቢር ይሁኑ እንጅ፣ የመጀመሪያው ብቻ ሳቢ ነው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ተሻጋሪ ግስ በመባል ይታወቃል። ድርጊቱን ወደ ተሳቢው ስም የማሻገር ባህሪ አለው።

አድራጊ አዕማድ

እድራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ስው እንድን ድርጊት እሱ ራሱ በሌላ ነገር ላይ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ናቸው። አመሰራረታቸው ከደራጊ አዕማድ ላይ /እ-/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ደራጊ	አድራጊ	3
ቀመስ-	አ-ቀመስ-[6]	
በል-	አ-በል-	
ሰበሰ-	አ-ሰበሰ-	
ወረድ-	አ-ወረድ-	
ወጥ-	አ-ወጥ-	

ስርዓቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስርዓት 2[7]

ደራጊ		አድራጊ
[1ኧ22ኧ3-]	⟶	[አ-1ኧ22ኧ3-]
/ቅኧምምኧስ-/		[አቅኧምምኧስ-]

አስደራጊ አዕማድ

አስደራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ሰው አንድን ድርጊት በራሱ ሳይሆን፣ በሌላ ሰው አማካኝነት ማስፈፀሙን ያመለክታሉ፡፡ የሚመሰረቱት ከደራጊ ወይም ከአድራጊ አዕማድ ላይ /አስ-/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው[7]፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ደራጊ	አስደራጊ	4
ዘረፍ-	አስ-ዘረፍ-	[አዝዝኧርርኧፍ-] አዘረፍ-
ገረፍ-	አስ-ገረፍ-	
ፈተል-	አስ-ፈተል-	
ገዝ-	አስ-ገዝ-	
ቆረጥ-	አስ-ቆረጥ-	
ተከል-	አስ-ተከል-	
ጀመር-	አስ-ጀመር-	
ወጥ-	አስ-ወጥ-	
ሰክ-	አስ-ሰክ-	
ቀየር-	አስ-ቀየር-	

ስርዓቱን አንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

---

[6] በዚህ ክፍል የምናያቸው ቃላት ቅጣይ ብቻ የሚፈልጉ በመሆናቸው ቅርፃቸውን በስርዓተ ፅህፈት እናመለክታለን፡፡

[7] ስለዚህ ጉዳይ ላይ ስተስየ አመልካከት በዛ (1998)ን ይመልከቱ፡፡

ስርዓት 3፡

ቅጣይ	ደራጊ	አስደራጊ
[አስ-] +	[1ኧ22ኧ3-] /ግኧርርኧፍ-/	[አስ-1ኧ22ኧ3-] [አስግኧርርኧፍ-]

ደራጊ፣ እድራጊና አስደራጊ አዕማድ በመዋቅራዊ ባህሪያቸው ይለያያሉ። እንዴት እንደሚለያዩ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) ቡና ፈላ 5
(ለ) አስቴር ቡና አፈላች
(መ) አስቴር ገንቦን ቡና አስፈቀቻት
(ሰ) ካሳ አስቴርን ለፖሊስ አስያዛት

የመጀመሪያው የደራጊ፣ ሁለተኛው የአድራጊ፣ ሶስተኛው የአስደራጊ አዕማድ የሚገኙባቸው ምሳሌዎች ናቸው። በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ግሱ ከአንድ ስማዊ ፀረግ ጋር፣ በሁለተኛው ምሳሌ፣ ከሁለት ስማዊ ፀረጎች ጋር፣ እንዲሁም በሶስተኛው ምሳሌ፣ ከሶስት ስማዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅሮአል። ምሳሌ (ሰ) <u>አስቴር ለፖሊስ ተያዘች</u>፣ የሚል ትርጉም አለው። ተያዘች የሚለው ግስ ተደራጊ ነው። ወደፊት እንደምናየው የተደራጊ ምዕላድዋ /ተ-/ ነች። እዚህ ላይ በግሀድ አትታይም። ያዡ ፖሊስ ሲሆን፣ አስያዡ ደግሞ ካሳ የሚለው የእረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። በተደራጊው ግስ ላይ /አስ-/ የሚለውን የአስደራጊ ምዕላድ ስንጨምር፣ የግሱ ቅርፅ /አስ-ተ-ያዝ-/ የሚል ይሆናል። ይሁን እንጅ፣ በአማርኛ የአስደራጊና የተደራጊ ምዕላዶች ተከታትለው ሲመጡ፣ የተደራጊው ምዕላድ ስለሚገደፍ፣ በታህታይ ቅርፅ ላይ /አስ-ተ-ያዝ-አት/ የነበረው ግስ በላዕላይ ገፅታ <u>አስያዛት</u> ይሆናል። አስቴር የዚህ ግስ ተሳቢ ነች። ስለዚህ <u>አስያዛት</u> የሚለው ግስ በቁሙ አሻሚ ነው። የአድራጊ ወይም የተደራጊ አስደራጊ ሊሆን ይችላል። የየትኛው አምድ አስደራጊ እንደሆነ ግወቅ የሚቻለው አውዱ-ነገሩንና መዋቅራዊ አገባቡን በማየት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አስቴርን ሀገር <u>አስጎበኛት</u> 6
(ለ) ካሳ አስቴርን በስልክ ለፈተና <u>አስመዘገባት</u>
(መ) ካሰ አስቴርን ስራ <u>አስያዛት</u>

የመጀመሪያው <u>ጎበኘች</u> ከሚለው ሳቢ ግስ ላይ የተመሰረተ አስደራጊ ነው። ሁለተኛው <u>ተመዘገበች</u> ከሚለው ተደራጊ ግስ ላይ የተመሰረተ ነው። ምሳሌ (መ)

ያስተርጥር አስደራጊ ነው። መሰረቱ <u>አስቴር ለራ ያዘች</u> የሚል ደራጊ አረፍተ ነገር ነው።

ከዚህም የምንረዳው ደራጊ፣ አድራጊ፣ አስደራጊና ተደራጊ አዕማድ በቱተር የተለያዩ ስማዊ ሀረጎች ጋር የሚዋቀሩ መሆናቸውን ነው። በዚሁ መሰረት አያንዳንዱን ባለ አንድ፣ ባለ ሁለት እና ባለ ሶስት ስማዊ ሀረግ አምድ እያለን አንደ ባህሪው ልንለየው እንችላለን።

ተደራጊ አዕማድ

ተደራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ድርጊት በአንድ ነገር ላይ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ የሚመሰረቱት ከደራጊ አዕማድ መነሻ ላይ /ተ-/ የሚል የተደራጊነት ምዕላድ በማስገባት ነው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ደራጊ	ተደራጊ
ገደል-	ተ-ገደል-
በል-	ተ-በል-
ጠጥ-	ተ-ጠጥ-
ጀመር-	ተ-ጀመር-
ፈረም-	ተ-ፈረም-
ወቀስ-	ተወቀስ-

7

ለርዓቱን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

ለርዓት 4፣

ቅጣይ	ደራጊ	ተደራጊ
[ትኧ- +	[1ኧ22ኧ3-]	[ትኧ-1ኧ22ኧ3-]
	/ግኧድድኧA-/	[ትኧግኧድድኧA-]

የእነዚህ አይነት ግሶች መዋቅራዊ ባህሪ ከአንድ ተደራጊ ከሆነ ስማዊ ሀረግ ባለቤት ጋር ተዋቅሮ እንደሚከተሉት ያሉ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ነው።

(ሀ) ቡና ተፈላ
(ለ) አንበሳው ተገደለ

8

እንደ ተፈላ ያሉ ተደራጊ ግሶች አንዳንድ ጊዜ የተገላበጠ ግሶች ይባላሉ። እንደ አፈላ ካሉ ገቢር ግሶች በቅርፃቸውም ሆነ በአገባባቸው ይለያሉ። ገቢር ግሶች /ተ-/ን አያስቀድሙም፣ አገባባቸውም እድራጊ ከሆነ ባለቤት ጋር ነው። ዝርዝሩን በሚቀጠለው ክፍል እናየዋለን።

ዳራጊ አዕማድ

ዳራጊ የሚባሉት ለሌሎች አዕማድ ምስረታ መሰረት የሚሆኑ ዕለር አዕማድ ናቸው። እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ስር	አምድ	9
/ሰ-ብ-ር-/	/-ስስአብብኧር-/	-ሳበር-
/ፍ-ል-ግ-/	/-ፍፍአልልኧግ-/	-ፋለግ-
/ግ-ድ-ል-/	/-ግግአድድኧል-/	-ጋደል-
/ፍ-ል-ም-/	/-ፍፍአልልኧም-/	-ፋለም-

ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 5፣

ስር	ዳራጊ
[1-22-3-] ⟶	[-11አ22ኧ3-]
/ሰ-ብ-ር-/	[-ስስአብብኧር-]

ስርዓቱ በየስሮቹ መካከል ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ፣ እንደ ቅደም- ተከተላቸው፣ /-አ-/ን እና /-ኧ-/ን ማስገባትና የየስሩን የመጀመሪያ እግር መድገም (ማጥበቅ) እንዳለብን ያሳያል። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩት አዕማድ ትርጉም ሆነ የቃል ክፍል ግልፅ የሚሆነው በመነሻቸው ላይ አዳራጊ ምዕላድ ሲገባ ነው።

አዳራጊ አዕማድ-(ሀ)

አዳራጊ አዕማድ የሚባሉት በሁለት ክፍል ይመደባሉ። የመጀመሪያው ክፍል አንድ ሰው አንድ ሌላ ሰው እንድን ሰራ በሚሰራበት ጊዜ በስራው ላይ በመሳተፍ ግንዝን የሚያመለክቱ አዕማድን ያጠቃልላል። አዕማዱ የሚመሰረቱት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ዕለር ዳራጊ አዕማድ ላይ /አ-/ የሚሰውን የአዳራጊ ምዕላድ በማስቀደም ነው። የሚከተሉት የነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ሳራጊ	አሳራጊ	10
/- ስስአብብኧር-/	/አ-ስስአብብኧር-/	አሳበር-
/- ፍፍአልልኧን-/	/አ-ፍፍአልልኧን-/	አፋለን-
/- ድድአርርኧስ-/	/አ-ድድአርርኧስ-/	አዳረስ-
/- ልልአትትኧስ-/	/አ-ልልአትትኧስ-/	አላተስ-
/- ግግአድድኧል-/	/አ-ግግአድድኧል-/	አጋደል-

ሰርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያሰን።

ለርዓት 6፣

ቅጣይ ሳራጊ	አሳራጊ
[[አ-] + [-11አ22ኧ3-]] ⟶	[አ-11አ22ኧ3-]
/-ፍፍአልልኧተ-/	[አ-ፍፍአልልኧተ-]

አሳራጊ አዕማድ፣ እንደ አድራጊ አዕማድ፣ ከሰስት ለማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅረው አረፍተ ነገር ይመሰረታሉ። የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) አሰቴር እንጨት ሰበረች 11
(ሰ) ካሳ አስቴርን እንጨት አሳበራት

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ሰበረች</u> የሚለው ደራጊ ግስ፣ <u>አስቴር</u> እና <u>እንጨት</u> ከሚሉት ሁለት ሰማዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅሮአል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ <u>አሳበራት</u> የሚለው አሳራጊ ግስ፣ ካሳ፣ አስቴር እና እንጨት ከሚሉት ሶስት ሰማዊ ሀረጎች ጋር አረፍተ ነገሩን መሰርተአል። ከተግባር አኩዋያ ሲታዩ፣ እንጨት የሚለው ተሰባሪ፣ አስቴር ሰባሪ፣ ካሳ ደግሞ የዚህ ድርጊት ተባባሪ ወይም አሳባሪ አሰያም አጫፋሪ ነው።

ሁለተኛው የአሳራጊ አዕማድ ክፍል በተሳራጊ አዕማድ ላይ የተመሰረተ ሰለሆነ፣ መጀመሪያ ተሳራጊ የሚባሉትን አዕማድ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ተሳራጊ አዕማድ

ተሳራጊ የሚባሉት አንድ ሰው ከአንድ ሌላ ሰው፣ ወይም አንድ ወገን ከሌላ ወገን ጋር አንድ ነገር መዳረጉን የሚያመለክቱ አዕማድ ናቸው። የሚመሰረቱትም ከሳራጊ አዕማድ ላይ /ተ-/ የሚል የተሳራጊ ምዕላድ ከአምዱ መነሻ ላይ በመተጠል ነው። የዚህ ክፍል አዕማድ ቅርፅ ከፍ ሲል ካየነው የ(ሀ) ክፍል አዕማድ የተለየ ነው። ይህን ከሚከተሉት መሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

ሳራጊ		ተሳራጊ	12
/-ግአድድኧል-/	-ጋደል-	/ተ-ግአድድኧል-/	ተጋደል-
/-ቅአልልኧድ-/	-ቃለድ-	/ተ-ቅአልልኧድ-/	ተቃለድ-
/-ክአፍፍኧል-/	-ካፈል-	/ተ-ክአፍፍኧል-/	ተካፈል-
/-ቅአርርኧን-/	-ቃረን-	/ተ-ቅአርርኧን-/	ተቃረን-
/-ፍአልልኧም-/	-ፋለም-	/ተ-ፍአልልኧም-/	ተፋለም-
/-ውአግግኧዕ-/	-ዋግ-	/ተ-ውአግግኧዕ-/	ተዋጋ

በግልፅ እንደሚታየው፣ የሳራጊው አምድ ሁለተኛ አግር ጥብቅ ነው። በዚህም የመጀመሪያ አግራቸውን ጭምር ከሚያጠብቁት የ(ሀ) ክፍል አዕማድ ይለያል። ብአገባብም ቢሆን የዚህ ክፍል አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ከ(ሀ) ክፍል የተለየ ነው። ተሳራጊ አዕማድ ከአንድ ሰማዊ ሀረግና ከ-ጋር ከሚል አጫፋሪ መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ከሚስቱ ጋር ተቃለደ 13
(ለ) ካሳ ከአለቃው ጋር ተጣላ

የአዕማዱ ያመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 7፣

ቅጣይ	ሳራጊ		ተሳራጊ
[[ትኧ-]+	[-1አ22ኧ3-]]	⟶	[ትኧ-1አ22ኧ3-]
	/ቅአልልኧድ-/		[ትኧቅአልልኧድ-]

ይህ የተሳራጊ አዕማድ ስርዓት ሲሆን፣ አሳራጊ አዕማድ የሚባሉት የሚመሰረቱት ከዚሁ ከተሳራጊ አምድ ላይ /ኣ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም ነው።

አሳራጊ አዕማድ (ለ)

አሳራጊ አዕማድ የሚባሉት ሁለት ሰዎች ወይም ወገኖች አንድ ነገር አንዲሳረጉ ማድረግን ወይም ምክንያት መሆንን ያመለክታሉ። የሚከተሉት የአነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ተሳራጊ	አሳራጊ		14
/ትኧ-ግአድድኧል-/	/ኣ-ትኧ-ግአድድኧል-/	[አግግአድድኧል]	አጋደል-
/ቅኧ-ፍአልልኧም-/	/ኣ-ትኧ-ፍአልልኧም-/	[አፍፍአልልኧም]	አፋለም-
/ትኧ-ጥአልል-/	/ኣ-ትኧ-ጥአልል-/	[አጥጥአልል-]	አጣል-

የአዳራጊውን አምድ የምትመሰርተው /ኣ-/ እና የተዳራጊውን አምድ የምትመሰርተው /ትኧ-/ ተከታትለው ሲገቡ፣ /ትኧ-/ ላይ የሚገኘው /ኧ/ ይገደፋል። ምክንያቱም ቁጥቁጥው በቃል መካከል ላይ የሁለት ተናባቢ ክትትሉሽን ለለሚፈቅድ ነው። በአናባቢው ግድፈት ምክንያት /ት/ እና የየአምዱ የመጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ ይነካካሉ። በዚህም ምክንያት /ት/ ሙሉ በሙሉ ከየአምዱ የመጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ ጋር ትመሳሰላለች። ሁለት ስነ-ድምፃ ልሳናዊ ሂደቶች ይካሄዳሉ ማለት ነው። አንደኛው የአናባቢው ግድፈት ሲሆን፣ ሁለተኛው የተናባቢው ምለለት ናቸው። ስነ-ምዕላዳዊ ስርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 8፣

ቅጣያ ተዳራጊ		አደራጊ
[[ኣ-]+[ትኧ-1ኣ22ኧ3-]]	⟶	[ኣ-ት-1ኣ22ኧ3-]
/ትኧ-ፍኣልኧም-/		[ኣፍፍኣልኧም-/

ከስርዓት (6) እና ከስርዓት (8) እንደምንረዳው፣ ሁለት አይነት አዳራጊነት አለ። አንደኛው ከግቢር ዳራጊ አምድ ላይ /ኣ-/ የሚለውን አድራጊ ምዕላድ በመጨመር የሚመሰረት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከተዳራጊ አምድ ላይ ይህንኑ /ኣ-/ በመጨመር የሚመሰረት ነው። የመጀመሪያውን አጫፋሪ አዳራጊ ልንለው እንችላለን። ተግባሩ አንድ ድርጊት ሲፈፀም አብሮ መሳተፍን ወይም መተባበርን ማሳየት ነው። በዚህም ምክንያት ሁለት ሰዎች ርስበርስ አንድ ነገር እንዲዳረጉ ከሚያደርገው የተዳራጊ አዳራጊ አምድ ይለያል።

ደራራጊ አፅማድ

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አፅማድ አንድ ተደጋግሞ የሚፈፀምን ተግባር ያመለክታሉ። የሚከተሉትን እንመለከት።

ሰር	አምድ		15
/ሰ-ብ-ር-/	/ሰኧብኣብብኧር-/	ሰባበር-	
/ቅ-ል-ድ-/	/ቅኧልኣልልኧድ-/	ቀላለድ-	
/ሰ-ድ-ብ-/	/ሰኧድኣድድኧብ-/	ሰዳደብ-	

አመሰራረታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 9፣

ስር		ደራራጊ
[1-2-3-]	⟶	[1ኧ2አ22ኧ3-]
/ሰ-ብ-ር-/		[ሰኧብአብብኧር-]

ስርዓቱ የየስሩ ሁለተኛ ተናባቢ እንደሚደገምና ከተደጋሚው ስር ቀጥሎ /አ/ የሚል እናባቢ እንደሚገባ ያስገነዝባል። በዚህ እይነት የሚፈጠሩ አዕማድ አንድ ተግባር እየተደጋገመ የሚፈፀም መሆኑን ያመለክታሉ። የስሩ ተናባቢ መደጋገም የሚያመለክተው ይህንኑ ድግግሞሽ ነው። አዕማዱ እንደ አድራጊ አዕማድ ከሁለት ለግዥ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው እንደሚከተሉት ያሉ አርፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ።

(ሀ) ካሳ እንጨት ይሰባብራል 16
(ለ) አስቴር እንጨት ትለታትጣለች

አደራራጊ አዕማድ (ሀ)

እንደ አላራጊ አዕማድ አደራራጊ አዕማድም በሁለት ይከፈላሉ። የመጀመሪያው አንድ ለው አንድን ተግባር እየደጋገመ በሚፈፅምበት ጊዜ ደጋግሞ ተባባሪ መሆንን የሚያመለክቱ አዕማድ የሚገኙበት ክፍል ነው። እነዚህ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ ከደራራጊ አምድ በፊት በመቀጠል ይመሰረታሉ። የሚከተሉትን እንመልከት።

ደራራጊ	አደራራጊ		17
ገላደል-	/አ-ገገኧድአድድኧል-/	[አገገኧድአድድኧል-]	አገላደል-
ሰባበር-	/አ-ሰሰኧብአብብኧር-/	[አሰሰኧብአብብኧር-]	አሰባበር-
ፈላለጥ-	/አ-ፍፍኧልአልልኧጥ-/	[አፍፍኧልአልልኧጥ-]	አፈላለጥ-
ፈላለግ-	/አ-ፍፍኧልአልኧግ-/	[አፍፍኧልአልኧግ-]	አፈላለግ-

አመሰራረታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 10፣

ቅጣይ	ደራራጊ		አደራራጊ
[[አ-] +	[-11ኧ2አአ22ኧ3-]]	⟶	[አ-11ኧ2አ22ኧ3-]
	/-ሰሰኧብአብብኧር-/		[አሰሰኧብአብብኧር-]

የእነዚህ አይነት አዕማድ አረፍተ ነገር የሚመሰርቱት ከሶስት ስማዊ ሀረግ ጋር እንደሚከተለው በመዋቀር ነው።

(ሀ) ካሳ አስቴርን እንጨት አስባበራት 18
(ለ) አስቴር ገነትን ቤት አፈላስገቻት

ተደራራጊ አዕማድ

እነዚህ ከደራራጊ አዕማድ ላይ /ተ-/ የሚለውን የተደራጊነት ምዕላድ በመቀጠል የሚመሰረቱ ናቸው። ተግባራቸው፡ ስዎች ርስበርሳቸው እንድ ነገር የሚደራረጉ መሆናቸውን ማመልከት ነው። ድርጊቱ ተደጋጋሚ መሆኑን ለማመልከት፡ የየአምዱ ሁለተኛ (ከግራ ወደቀኝ) ተናባቢ ይደገማል። እንዱ የሌላው ድርጊት ተጠቂ መሆኑን ስማመልከት /ተ-/ በየአምዱ መነሻ ላይ ትገባለች። የሚከተሉትን እንመልከት።

ደራራጊ	ተደራራጊ	19
ገዳደል-	ተ-ገዳደል-	
ፈራረም-	ተ-ፈራረም-	
ሰዳደብ-	ተ-ሰዳደብ-	
ፈላለግ-	ተ-ፈላለግ-	

ሰርዓታቸውን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ሰርዓት 11፣

ቅጣይ	ደራራጊ		ተደራራጊ
[[ትኧ-] +	[1ኧ2አ22ኧ3-]]	⟶	[ትኧ-1ኧ2አ22ኧ3-]
	/ስኧድአድድኧብ-/		[ትኧሰድአድድኧብ-]


የተደራራጊ አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ እንድ አፀፋዊ ተውላጥ ካለው የብዙ ቁጥር ስማዊ ሀረግ ጋር አረፍተ ነገር መመሰረት ነው። የሚከተሉትን አናስተውል።

(ሀ) ልጆቹ ርስበርሳቸው ተሰዳደቡ 20
(ለ) ልጆቹ ርስበርሳቸው ተደባደቡ

ርስበርስ የሚለው አፀፋ መዋቅራዊ ዝምድና ከግሱ ጋር ሳይሆን፡ ከባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ማለትም ልጆቹ ከሚለው ስም ጋር ነው።

አደራራጊ አዕማድ (ለ)

ቀደም ሲል አዳራጊ አዕማድ የሚባሉት ከተዳራጊ አዕማድ ላይ /አ-/ን እየቀጠሉ ሲመስረቱ አይተናል። አደራራጊ አዕማድም ይህንኑ ምዕላድ ከተደራራጊ አዕማድ ላይ በመቀጠል የሚፈጠሩ ሲሆኑ፣ ተግባራቸውም ካሁለት የበለጡ ሰዎች ወይም ወገኖች ርስበርስ አንድ ነገር እንዲደራረጉ ማድረግን ወይም ምክንያት መሆንን ማመልከት ነው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።



ቀደም ሲል እንዳየነው በተደራራጊው ምዕላድ መድረሻ ላይ የምትገኘው /ኧ-/ ትገደፋለች። በዚህ ምክንያት /ት-/ ከእየአምዱ የመነሻ እግር ጋር ትነካካለች። ይህም /ት/ ሙሉ በሙሉ የአምዱን የመነሻ እግር እንድትመስል ያደርጋታል። ስርዓተ-ፍጥረታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 12፣

ቅጣይ	ተደራራጊ	አደራራጊ
[[አ-] +	[ትኧ-1ኧ2አ22ኧ3-]] /ትኧግኧድኣድድኧል-/	⟶ [አ-ትኧ-1ኧ2አ22ኧ3-] [አግግኧድኣድድኧል-]

የአደራራጊ አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ከሶስት ስማዊ(ፅኔነቹ የግዕ ሳአንጀ ሂከዮሰከት ያሉ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ነው።

ሰጠቀዓለ ና\-ለ\ ጷሶ ጷምዕለ ያ-ኣጵተበ ተ-ሰበየምዓ ጷምዕለ ያ-ኣዮ-ለ ሌሰ ሚጷቀ ጷምዕለ ያ-ኣ-ኣጷ(ሀ)ጵ ጷ[ኣሳ-ልጆቸን ርሳባርሳ-ሰደባጷዓቸው ።ሌዓተ-ጷጵ ተ-ኣሰመሰ ሚጷወ ቸሳሰ ኣሰከበነ ሞጵገሀሩ ቁጆቹን ርሳባርስ-ኣሳሳግቸው።ምዓ ሌጠቀመሳበ ጷሶ ሮናገመ ተዓናበሚ ሚጷወ የሞኣጷም ተ-ኣጷጷጷዮለ ጋበሪ ጷሮለ ሰጋበሰጋ ቸዓየወ **እስካሁን የተመለከትናቸውተሰሎቲካልቅ የአዕማድ ሳሳሳሳሳሳ ድርጌትን የሰሄጌቱ ናቸው።። የድርጊት አዕማድ ልንላቸው አንችላለን። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ባህሪን የሚያመለክቱ አዕማዶን ቅርዓት እንመለከታለን።**

\-ለለ\ጷጷለጷለጷ-ኣ-ተ-ለ\ ← \-ለለ\ጷጷለጷለጷ-ኣ-ተ \ ← \-ለለ\ጷጷለጷለጷ-\ ያ-ኣ-ኣጷ

የባህሪ አዕማድ

\-ለለ\ጷጷለጷለጷ-ተ-ለ\

ባህሪያዊ አዕማድ በቅርፃቸው ተዳራጊ አዕማድን ይመስላሉ። በትርጉማቸው ግን አንድ ሰው[አንድን ነገር ሆን ብሎ፣ አሰቦ ወይም ልምድ ሆኖበት የሚፈፅመው መሆኑን ያመልክታሉ። ኣምሰሬራታቸው ቋሚሚ ሲል ባየናቸው በዳራጊ አዕማድ መስረት ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

\-በ\ጷጷለጷለበ\ጷጷ-ተ-ለ\

ዳራጊ	ባህሪያው	23
/-ለአድ-ኣብ-/	/ትኣ-ለአድ-ኣብ-/	
[-በ\ጷ/ጷንጷጷጷኣበ#]	/ትኣ-ንአግግኣር-/	
\-ሚኣ\ጷጷለጷለጷኣ-ተ\ ← /-ንአክክኣበ-/	/ትኣ-ንአክክኣበ-/ ← \-ሚኣ\ጷጷለጷለጷኣ-ተ\	

ሰርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያለን።

\-ሚኣ\ጷጷለጷለጷኣ-ተ-ለ\

ሰርዓት 13፣

[-ሚኣ\ጷጷለጷለጷኣተለ]

\-ኣ\ ወ\ኖ-ኮ-ቅጣጷሶ ኮኣጷራሚ አጷሳሚ-ሚ ወ\ኮ-ጵ-ኣጷ ካበራይቁ\ሳጷኖለ ሌሰ ሚጷቀ ።ቸለሰሰ\ኖ-ቱ ጋቂ[ጵ-ኣሞ-ቶ +ኮ[-ሳ\ጷ2ጷ3ጷ1ቶ\ሳ\ለሰ \-ኮ\ ኮ[ቅኖ\ሳ\ጷ2ጷ3ጷ]። ።ቸለ-ኮጷ\ኖ-ቱ ።ሌቲ-ጋጋጷ ሌሰ\ሚ-ኮ ጷ\ለ\ሞ-ኮ\ሰ\ሰ-ኮ\ኮ\ሰ\ሰ-ኮ\ኮ\ሰ\ሰ-ኮ\

ማጀቢያ ግስም ለብቻው ቆሞ ትርጉም ሊሰጥ ስለማይችል ከሌላ ግስ ጋር ተጨምሮ ነው የሚገለገለው። ለምሳሌ፦ ሰላም ከተመለሰ አረፍቶ ነገር ከሚለው ውስጥ አደነገጠ ማጀቢያ ግስ ነው።

ካሳ አሰቴርን ሰደባት 25

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ሰደባት የሚለው ግስ አምድ፣ ተሳደበ ከሚለው አምድ ተቅቤበት የተለየ ነው። ትርጉሙም ሲሆን ሳቤ አውጥቶ ሰደበ ተሩ ድርጊትን ለማጠናከር ያስፈለገ ሲሆን ያከለው ደጋሚ ድርጊት አይመለከትም። ተሰደበ ያለው ግስ ግን ድርጊቱ ግለትም የመሳደቡ ተግባር ባጋጣሚ ሳይሆን ደጋሚ ተግባሩ የተፈፀመ መሆኑን ያመለክታል። ይህን ለማረጋገጥ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ካሳ ሰው ይሳደባል < [ይ-ት-ሳድ-ኧብ-አል] 26

ከዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ይሳደባል የሚለው ግስ አንድ ጊዜ ብቻ በአጋጣሚ የሚፈፀምን የመሳደብ ተግባር ሳይሆን፣ ሁልጊዜም ሆን ተብሎ የሚፈፀምን ድርጊት ያመለክታል። ካሳ ተራ ሰዳቢ ብቻ ሳይሆን፣ አመለኛ ሰዳቢ ነው። እንዲህ ያለ የአመል ተግባርን የሚገልፅ ግስ፣ ተራ ተግባርን ከሚገልፅ ተራ ግስ በቅርፁ ይለያል። ስለዚህም ለተራ ሰዳቢ ሰደበ የሚለውን፣ ለአመለኛ ሰዳቢ ተሳደበ የሚለውን እምድ እንጠቀማለን።

አመለኛ ሰዳቢ ተሳዳቢ ይባላል። የሚሳደበውም ማንንም ሊሆን ይችላል። ማንንም ሳይሆን፣ የተወሰነ ሰውን ሰይቶ በተወሰነ ጊዜና በተወሰነ ምክንያት የሚሳደብ ከሆነ፣ ግሱ ሰደበ ይሆናል። ሰውየውም ሰዳቢ እንጂ፣ ተሳዳቢ አይባልም። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ካሳ አሰቴርን ሰደባት 27
(ለ) ካሳ አሰቴርን ተሳደበ(-አት)

ሁለተኛው አረፍተ ነገር ተቀባይነት የለውም። ለዚህም ምክንያቱ ተሳደበ የሚለው የባህሪ ግስ አሰቴር ከሚለው ውስጥ (ዕምር) ሰም ጋር መዋቀሩ ነው። በዚህ ሰም ፋንታ፣ እንደ ሽግግሌ፣ ልጅ፣ ቤተ፣ ወዘተ፣ ያለ ኢውሱን (ያልታመረ) ሰም ጋር ቢዋቀር ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት ይኖረው ነበር። ምክንያቱም፣

ካሳ ሽግግሌ ተሳደበ 28

ማለት ይቻላልና። ምክንያቱም የምትመሰርተው /ታ-/ ቀደም ሲል ያየናቸውን ተጨማሪ አፈጣጠር ከሚያሟላው ከሦስተኛ መደብ ተባዕታይ /ተ-/ ስለሆነ ነው። ስለዚህም ምክንያቱ ያበሳሬ አፅንዖት አፍራጊነትን፣ እንጅ፣ ተደራጊነትን ስለማያመለክት ነው። ሁለተኛው የባህሪ አሳማጅን የምትመሰርተው /ታ-/ የምትቀጠለው እንዲ /-ሰደብ-/ ካለ ዕዐር አምድ ላይ ሲሆን፣ ተጨረገ አሳማጅን የምትመሰርተው /ተ-/ ግን የምትጎንው /ሰደብ-/ ከሚል አምድ ላይ ነው። የሁለቱ አፅማደ ውስጣዊ አወቃቀር ለየቅል ነው።

አንደኛው -ሳደብ- የሚል ሲሆን፣ ሌላኛው ሰደብ- የሚል መሆኑ ነው። ሰሰተኛም ከላይ በተራ ቁጥር (28) ከተሰጠው ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው፣ የባህሪ አዕማድ ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር መዋቀር ሲችሉ፣ ተደራጊ አዕማድ ግን ይህን ማድረግ ፈፅሞ አይችሉም። ምክንያቱም፣

*ካሳ ሽግግሌ ተሰደበ 29

ማለት፣ ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም። በነዚህ የቅርፅና የአነባበብ ልዩነቶች ምክንያት፣ ሁለቱን /ተ-/ዎች የተደራጊ እና የባህሪ ምዕላድ ብለን፣ ልንለያቸው እንችላለን።

አፀፋዊ አዕማድ

በዚህ ስር የሚካተቱ አዕማድ ድርጊትን ሳይሆን፣ ሁኔታን ያመለክታሉ። አንድ ሰው የሚገኝበትን ሁኔታ ወይም ይዞታ ስለሚገልፁ፣ የሁኔታ አዕማድ ሊባሉ ይችላሉ። አፈጣጠራቸው ከፅሰር ወይም ከነባ አዕማድ ላይ /ተ-/ የሚል ምዕላድ እንደሚከተለው በመቀጠል ነው።

ሁኔታዊ	አፀፋዊ		30
/ትኧግኧር-/	/ትኧ-ተኧግኧር-/	ቸገረ	ተ-ቸገር-
/-ድኧስስኧት-/	/ትኧ-ድኧስስኧት-/	-ደሰተ	ተ-ደሰት-
/-ርኧክክኧብ-/	/ትኧ-ርኧክክኧብ-/	-ረከሰ	ተ-ረከብ-
/ሠኧንንኧቅ-/	/ትኧ-ሠኧንንኧቅ-/	ጨነቀ	ተ-ጨነቅ-
/-ክኧፍፍ-/	/ትኧ-ክኧፍፍ-/	ከፋ	ተ-ከፍ-
/-ቀኧይይኧም-/	/ትኧ-ቀኧይይኧም-/	-ቀየመ	ተ-ቀየም-

ስርዓታቸውን አንደሚከተለው አድርጎ ማሳየት ይቻላል።

ስርዓት 14፣

ቅጣይ	አምድ		አፀፋዊ
[ትኧ-] +	[ኘኧ22ኧ3-]]	⟶	[ትኧ-1ኧ22ኧ3-]
	/-ድኧስስኧት-/		[ትኧድድኧስኧት]

አዕማዱን የምትመሰርተው /ተ-/፣ ቀደም ሲል ካየናት፣ ተደራጊነትን ከምታመለክተው /ተ-/ የተለየች ነች። ተደራጊነትን የምታመለክተው /ተ-/ የምትገኘው ከድርጊቶ ወይም ከገቢር አዕማድ ጋር ነው፣ በተለይም ላቢ ከሆኑ ገቢር አዕማድ ላይ ተደራጊ አዕማድን የምትመሰርት ምዕላድ ነች። አፀፋዊ አዕማድን የምትመሰርተው /ተ-/ የምትቀጠለው፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ድርጊትን ሳይሆን፣ ሁኔታን ከሚያመለክቱ አዕማድ ላይ ነው። በዚህ አይነት የሚመሰረቱ አዕማድ፣ አረፍቱ ነባር የሚመሰርቱት ከሆኑ ስማዊ ሀረግ ጋር

በመዋቀር ነው። ባለቤቱ፣ በአምዱ በተገለፀው ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ አንድ፣ ድርጊትን የሚፈፅም አይደለም። ድርጊት የሰምና፣

አዕማዱ አፀፋዊ የሚባሉበት ምክንያት፣ ሁኔታው ከውጭ ወደ ሁዋኑ ሰው የሚመጣ ሰለሆነ ነው። ለምሳሌ ፣

ካሳ ተቀየመ 31

ሰንል፣ ለካሳ ቅያሚ ምክንያት የሆነው ነገር ወይም ሁኔታ ከካሳ ውጭ ነው። በመሆኑም ካሳ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ተግኝቶአል፣ ወይም ሁኔታው በሌላ ሰው አማካኝነት ወደሱ እንዲያነጣጥር ተደርጎአል። በጥቅሉ ካሳ ከአሱ ውጭ በተፈጠረና ወደሱ ባነጣጠረ ሁኔታ ውስጥ ስለሚኖ፣ አዕማዱ አፀፋዊ ሊባሉ ችለዋል።

የአደራረግ አዕማድ

በዚህ ስር የሚካተቱት አዕማድ አንድ ድርጊት እንዴት እንደተፈፀመ ያሚያመለክቱ ናቸው። ድርጊቱ በሀይል ወይም በለሆሳስ (በቀስታ)፣ በጥንቃቄ ወይም በዘፈቀደ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል። በዚህም ምክንያት የአደራረግ አዕማድ ብለናቸዋል። በአፈጣጠር ባህሪያቸውም ሆነ በተግባራቸው ተደም ሲል፣ ሳቢ ዘር ካልናቸው ውልድ ስሞች ጋር ይተሳሰራሉ። እንደ ባህሪያቸው ልዩነት ሰውስት ንዑስ ክፍሎች እንመድባቸዋለን።


አጠንካሪ አዕማድ

አንድ ድርጊት በሀይል ወይም በድንገት መፈፀሙን የሚያመለክቱ የአደራረግ አዕማድ አጠንካሪ ይባላሉ። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ስር	አጠንካሪ [8]		
/ሰ-በ-ር-/	/ሰ-በብ-ር-/	[ሰእበብእርር-]	ሰብር-
/ከ-ፍ-ት-/	/ክፉፍ-ት-/	[ክእፍፍእት-]	ከፍት-
/ም-ል-ስ-/	/ም-ልል-ስስ-/	[ምእልልእስስ-]	ምለስ-
/ወ-ር-ድ-/	/ወ-ርር-ድድ-/	[ወእርርእድድ-]	ወርድ-
/ዝ-ግ - -/	/ዝ-ግግ-ት-/	[ዝእግግእት-]	ዝግት-
/ብ-ል - -/	/ብ-ልል-ት-/	[ብእልልእት-]	ብልት-
/ፃ-ፍ - -/	/ፃ-ፍፍ-ት-/	[ፃእፍፍእት-]	ፃፍት-
/ወ-ጥ - -/	/ወ-ጥጥ-ት-[9]/	[ወእጥጥእት]	ወጥት-

[8] ይህንዘህን እይነት አዕማድ አመሰራረት በተመለከተ፣ ስነ-ምዕላዳዊ ላይሆን መዋቅራዊ ሆኖ መንገድ ለተደረገ ጥናት ታደሰ (1980)ን ይመልከቱ።

ስርዓቱን አንደሚከተለው አናሳይዳ።



ክስርዓቱ አንደሚታየው፣ አጠንካሪ አዕማዱ የሚፈጠሩት የሃሳሩን መድረሻና ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ በማጥበቅ ነው። ስሩን በማስፋፋት ብቻ የሚፈጠሩ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል። በተሰፋፋው ስር ውስጥ የሚታየው /እ/ የተናባቢ ክትትሉሽን ለማገድ የሚገባው አናባቢ ነው። ስለዚህም ተጨባጩ ድምፁ አሳናዩ አንድ፣ ስነ-ምዕላዳዊ አይደለም።

እንደነዚህ ያሉ አዕማድ ቅርፅ ከዚህ በፊት ካየናቸው ደራጊ አዕማድ የተለየ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህ ውስጥ የሚታየው አናባቢ /እ/ ነው። እነዚህ የየስሩን መድረሻና ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ሲደጋግሙ፣ ደራጊ አዕማድ የስሩን ቅድመ-መድረሻ ብቻ ይደጋግማሉ። ስነዚህ ልዩነቶች ምክንያት እንደ [ስእብብእርርአ] ያሉ አዕማድን በሙሉ ልብ ግሳዊ ናቸው፣ ለማለት ያስቸግራል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚመጣው ከግስት ይልቅ፣ የአደራረግ አዕማድ ያልናቸው። እንደ ግስ የሚቆጠሩት አስ ወይም አደረገ ከሚሉ ግሳዊ አዕማድ ጋር ሲጣመሩ ብቻ ነው። ስለዚህ፣ ሰብር- የነበረው፣ ሰብር-አስ ወይም ሰብር-አደረገ የሚል የአደራረግ ጥምር ግስ ይሆናል። ጥምሩ፣ ግስነትን አስ ወይም አደረገ ከሚለው ግስ ሲያገኘው፣ እደጋይዳን ሰብር- ከሚለው አምድ ያገኛል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ብርጭቆው ሰብር-አስ-ው
(ለ) ካሳ ብርጭቆውን ሰብር-አደረገው

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ ብርጭቆው ራሱ በድንገት ወይም በፀይል መሰበሩን ይመለክታል። ድንገትነቱን የሚገልፀው ሰብር- የሚለው ክፍል ነው። ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ ካሳ ድርጊቱን በሀይል ወይም በድንገት እንደፈፀመው

---

[9] የመጨረሻዎቹ አራት ስሮች ሶስተኛ አግራቸውን ጎርደዋል። ይሁን እንጅ፣ አጠንካሪነትን ለማሳየት፣ በቀንጋደው እገር ቤታ ለይ /ት/ የምትለዋን ምትክ ድምፅ ያስገባሉ። ይህ በአጠቃላይ የጎሬፎ ስርአት ባህሪ ነው። ለዝርዝሩ ባየ (1999)ን ይመለከቱ።

ያሚለከታል። ስለ ጥምረትና ያአወማመር ባህረ በሚቀጥለው ንዑስ ክፍል ስለምንወያይበት፣ወደ ዘሰቴቶው የአዶቱራንት አዕማድ ከፍሎች እንገኛለን። ሚሳያየለ ፣ቸየንጋበ ሚጓመ ልጓህበ ፣መሰቅጠጥጓየለ ለለ ንብ ።ሰቲብለመሚ ስለነሳሳሽ አዕማድ ያጋጓ ።መፀጓቱነ ቸጓለ ሙመጓ-ጋከሆየበ ሚጓመ ቲለቀበ መጓለበ ።።መችን ቸ-ጓበሞተ መችበሆያመነ ቴበለ ሰሞ ብሎመተ ዝሀ ሙዋቋሆሞቋ ሙሃዕሰርጓየለ ለቅሃለ ንዑስ ክፍል ያቋሚሳቲ የማንጉ ሙበለ ሰሞ ብሎመተ ዝሀ ሙዋቋሆሞቋ ሙሃዕሰርጓየለ ለቅሃለ ንዑስ ክፍል ያቋሚሳቲ የማንጉ መ

የአደራረግ አዕማድ በተግባራቸው ግስም ተውሳክ ግስም ናቸው፣ ለግስት ይቻላል፣ በግስነታቸው ድርጊትን፣ በተውሳክ ግስነታቸው አደራረግን ያመለክታሉ። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ በሀይል ወይም በድንገት፣ እንዲሁም በቀስታ ወይም በግብር-ይውጣ አይነት የተፈፀሙ ድርጊቶችን ያመለክታሉ፣ እንኽህ በሁኔታ ተውሳክ ግሰ ሊገለፁ የሚገባቸው ተግባራት ናቸው። ባለፈው ከፍል እንደገለፅነው ቁዋንቁዋው ብዙ ተውሳክ ግሳዊ ቃላት የሉትም። ስለዚህም ተውሳክ ግሳዊ የሆኑ ተግባራትን የሚገልፀው በመሰተዋድዳዊ ሀረጎች፣ በተገኛ አረፍተ ነገሮችና እንዲሁም ከዚህ ላይ እንደምንረዳው በአደራረግ አዕማድ አምካኝነት ነው። በዚህም የውልድ ግሶችን ጉዳይ እንሰናበታለን።

ውልድ ተውሳክ ግሶች

ስለ ቃላት ክፍል ጽንወያይ እንደተገለፀው፣ ተውሳክ ግሰ የሚባለው ክፍል በርካታ ቃላት የሉትም። ስለዚህም ምክንያት ተውሳክ ግሳዊ ተግባራት የሚገለፁት በመሰተዋድዳዊ ሀረጎች፣ በተገኛ አረፍተ ነገሮችና፣ ከፍ ሲል እንዳየነውም፣ በአደራረግ አዕማድ ነው። ይሁን እንጅ፣ ለአብነት የሚሆኑ ተውሳክ ግሳዊ ቃላት ስላሉ የእነሱን ስነ-ምዕላዳዊ ባህሪ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። እንደ ሌሎቹ ከፍሎች፣ እነዚህንም ነባርና ውልድ ብለን ልንለያቸው እንችላለን። ነባር የሚባሉት እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ግና
ቶሎ
መች 1

እነዚህ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ጊዜ የሚያመለክቱ ነባር የጊዜ ተውሳክ ግሶች ናቸው። ውልድ ተውሳክ ግሰ ሊባሉ የሚችሉት እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ቅፅል	ተውሳክ ግሰ
ክፉ	ክፉ-ኝኝአ
ጅል	ጅል-ኝኝአ
ግም	ግም-ኝኝአ
ምን	ምን-ኝኝአ

2

እነዚህ ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ውልድ ተውሳክ ግሶች ሲሆኑ፣ ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 1፣

ቅጣይ	ተውሳክ ግሰ
[[ቅፅል] + [-ኝኝአ]] /ከ-ፍ-አ/	[ቅፅል-ኝኝአ] |ክአፍአ-ኝኝአ]

እነዚህ የሁኔታ ተውላከ ግሶች ናቸው። አንድ ድርጊት እንዴት እንደተፈፀመ ያመለክታሉ። መዋቅራዊ ባህሪያቸው ከግስ ጋር መግባት ነው። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ልጁ ክፉኛ ወደቀ[10] 3
(ለ) ምንኛ ጠግቦአል ጃል!

ከነዚህ በተጨማሪ ምናልባት ተውሳከ ግስ ልንላቸው የምንችለው እንደሚከተሉት ያሉትን ነው።

የሁዋሊት 4
የምብርከክ
የጎድን
የጎሪጥ

እንደነዚህ ያሉት ከስሞች ላይ /የ-/ን በማስቀደም የሚፈጠሩ ናቸው። ቅርፃቸው የአገናዛቢ ስማዊ ሀረግን ቅርፅ ይመስላል። ተግባራቸው ግን ባለገንዘብን ሳይሆን፣ አደራረግን ማመልከት ነው። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ልጁ [[የሁዋሊት] ሄደ] 5
(ለ) ሰካራሙ ሰውየ [[የጎድን] ይሄዳል]
(መ) ልጁ [[የጎሪጥ] አየኝ]

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የሁዋሊት፣ የጎድን እና የጎሪጥ የሚሉት ተውላከ ግሶች በግሶቹ የተጠቀሰው ተግባር እንዴት እንደተፈፀመ ያመለክታሉ። አንዳንድ ጊዜ

[10] ክፉኛ ከሚለው በስተቀር፣ ሌሎቹ ተውላከ ግሶች ለአዲስ አበባው ሰው እንግዳ ሳይሆኑ አይቀሩም። ይህን አንጅ፣ በገጠር፣ በተለይም በጎንደርና በወሎ፣ እጅግ የተለመዱ ናቸው። በአዲስ አበባ ፣

ክፉኛ ታሞአል

ከግስት ይልቅ፣ በህይል ወይም በጠና ታሞአል፣

ምንኛ ጠግቦአል

ይሆንኑ ሁኔታ በመስተዋድዳዊ ሀረግ መግለፅ ይቻላል። ለምሳሌ <u>የሁዋሊት</u> በሚለው ፋንታ <u>ወደ ሁዋላ</u> የሚለውን መስተዋድዳዊ ሀረግ በመተካት፣

ልጁ [[ወደ ሁዋላ] ሄደ] 6

ማለት ይቻላል።

በዘሀና በ5(ሀ) በተጠቀሰው ምሳሌ መካከል የትርጉም ልዩነት ያለ አይመስልም። ይህ ከሆነ፣ በየተውሳከ ግሱ ውስጥ የምትገኘው /የ-/ በየመስተዋድዳዊ ሀረጉ ውስጥ የሚገኘው መስተዋድድ አቻ ነች፣ ለማለት ይቻላል። ይህ ለመሆኑ ከሚከተሉት ምሳሌዎችም መረዳት ይቻላል።

(ሀ) የጎጃም መንገደኛ 7
(ለ) ወደ ጎጃም የሚሄድ መንገደኛ

(ሀ) የጎጃም አረቄ 8
(ለ) ከጎጃም የመጣ አረቄ

(ሀ) የጋን ጠላ 9
(ለ) በጋን የተጠመቀ ጠላ

በግልፅ እንደሚታየው በ(ሀ) ውስጥ /የ-/ የነበረው በ(ለ) ውስጥ ወደ ፣ ከ እና በ ሆኖአል። ይህም እንደ የሁዋሊት ባሉት ተውሳከ ግሶች መነሻ ላይ የምትታየው /የ-/ የመስተዋድድ ምትክ ወይም አቻ ነች የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር መረጃ ነው። ጉዳዩ ተጨማሪ ጥናት ይፈልጋል። ስጊዜው ግን እንደ <u>የሁዋሊትና የጎድን</u> ያሉት ከሰም የሚመሰረቱ ተውሰከ ግሶች ናቸው፣ ለማለት የሚቻል ይመስላል። ያም ሆኖ፣ እንደ <u>ጎረጥ</u> እና <u>ሁዋሊት</u> የመሳሰሉ ቃላት ከፍል ሰም መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል። እንደነዘህ ያሉ ቃላት ሰም ካልሆኑ፣ የ- የሚለው ምዕላድ የመስተዋድድ አቻ ነው ለማለትና እንደ <u>የሁዋሊት</u> ያሉ አህዶችም መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው በሎ ለመደምደም ያስቸግራል።

ከግስትም፣ <u>እንዲት ጠግበአል</u> ግስት የተሰመደ ነው። በሀይል እና እንዲት የሚሉት ግን ተራ ተውሳከ ግስ ሳይሆኑ፣ ወደፊት በዝርዝር እንደምናየው፣ ሀረጎችና ጥምሮች ናቸው።

እስካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልለዋለን፡፡ በመሰረቱ ሰማየት የሞከርነው በአራቱ የቃላት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን ቃላት የአመሰራረት ስርዓት ነው፡፡ ስርዓቱ ያንዱ ክፍል ቃላት ከሌላው ክፍል ቃላት ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ ያሳያል፡፡ እያንዳንዱ ስርዓት የሚፈጥረው የቃላት መጠንም ወሰን የለውም፡፡ ርግጥ፣ ውይይታችን በአብዛኛው ያተኮረው በምንጠቀምባቸው ቃላት ውስጣዊ እቀነጃጀት ላይ ነው፡፡ ያቀነጃጀቱ ስርዓት ጥቅም ላይ ያልዋሉ እጅግ ብዙ ቃላትንም ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህን ስርዓት በወጉ ከተረዳን፣ ለአዳዲስ ፅንሰ-ሀሳብ፣ ቁሳቁስ፣ ድርጊት፣ ወዘተ፣ መግለጫ የሚሆን ቃል ፍልጋ ወደ ሌላ ቁዋንቁዋ መሄድ እያስፈልገንም፡፡ በስርዓቱ መሰረት ከራሱ ክቁዋንቁዋው ማውጣት ይቻላል፡፡ ይህ ለእማርኛ ብቻ ላይሆን፣ ማንኛውም የሀገራችን ቁዋንቁዋ የሚገጥመውን የላይንስና የስነ ጥበብ ፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ የሚሆኑ ቃላት ለመፈልፈል የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡

ቃላትን የምናወጣው በዚህ ንዑስ ክፍል እንዳየነው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው የቁዋንቁዋውን የድምፅ አሰካክ ስርዓት በመከተል ፎኒሞችን ከፎኒሞች ጋር በማቀናጀት ነው፡፡ ለምሳሌ፣

[ተእተተ] 10

በሚል የድምፅ አሰካክ ስርዓት እንደ፣

[ፍእርድ]	ፍርድ	11
[ጥእብስ]	ጥብስ	
[ልእብስ]	ልብስ	
[ውእርስ]	ውርስ	

ያሉ ነባር ቃላትን አፈጣጠር አይተናል፡፡ በዚሁ መሰረት እንደ፣

[ውእርት]	ውርት	12
[ቅእርት]	ቅርት	
[ስእርት]	ስርት	
[ዝእልት]	ዝልት	

ያሉ አዳዲስ ቃላትንም መፍጠር ይቻላል። እንደዚህ እያደረጉ በመፍጠር ለአዳዲስ ፅንሰ-ሀሳብና ክስተት ወይም ድርጊት ለያሚ ማግኘት ይቻላል።

ሁለተኛው መንገድ ምዕላድን ከምዕላድ ጋር ማገናኘት ነው። በዚህ መንገድ የሚፈጠሩ ቃላት ስነ-ምዕላዳዊ ናቸው። መስረታቸው ምዕላድ ነውና። በዚህም አካሄድ በርካታ ውልድ ስሞችን፣ ቅፅሎችንና ግሶችን እይተናል። ስሞቹ ከቅፅሎች፣ ከነባር ስሞችና፣ ከስሮች፣ ቅፅሎች ከስሞችና ከስሮች፣ ውልድ ግሶች ደግሞ ከስሮችና ከተለያዩ አዕማድ ላይ አንደሚመሰረቱ አይተናል። እነዚህ ዘረ-ብዙ ወይም ረቢ ያልናቸው የቃላት ክፍሎች ናቸው። ተውላከ ግስ የሚባለው ክፍል አንደነዚህኞቹ በርካታ ቃላት አንደሌለው፣ ስለዚህም ተውላከ ግሳዊ ተግባራት በሀረጎች፣ በጥገኛ አረፍተ ነገሮችና በአደራረግ ግሶች እንደሚገለፅ አይተናል።

በዚህ መንገድ አዳዲስ ቃላት አንዴት መመስረት እንደሚቻልም ገልፀናል። ለአብነት እንደገና የሚከተለውን እንመልከት።

ስር	አምድ	ቃል	13
/ም-ር-ት/	/ምኧርርኧት-/	/ምኧርርኧት-ኧ/	መረተ
	/አ-ምኧርርኧት-/	/አ-ምኧርርኧት-ኧ/	አመረተ
	/አ-ምርኣት-/	/አ-ምርኣት-ኢ/	አምራች

እነዚህ የምናውቃቸው ቃላት ናቸው። በዚሁ መሰረት የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት።

ስር	አምድ	ቃል	14
/ው-ር-ት/	/ውኧርርኧት-/	/ውኧርርኧት-ኧ/	ወረተ
	/አ-ውኧርርኧት-/	/አ-ውኧርርኧት-ኧ/	አወረተ
	/አ-ውርኣት-/	/አ-ውርኣት-ኢ/	አውራች
		/ውኧርኧት/	ወረት

ከነዚህ መካከል ወረት የሚለው ብቻ በጥቅም ላይ ይገኛል። ሌሎቹ በጥቅም ላይ ገና አልዋሉም። ስርዓቱን ተከትለን የፈጠርናቸው አዳዲስ ቃላት ናቸው። አውራች የሚለው ኢንቬስተር የሚለውን የውጭ ቃል ሲተካ የሚችል ጥሩ ስያሜ ነው። በዚሁ አካሄድ እስፈላጊውን ቃል እየፈጠሩ መጠቀም ስለሚቻል፣ ቃላት ፍለጋ ወደ ሌላ ቋዋንቋዋ መሄድ አያስፈልግም። የሰው እንጅ የቋዋንቋዋ ድህ የሰውም። አያንዳንዱ ቋዋንቋዋ የማያልቅ ማዕድን ነው። በዚህም ከዚህ ከፍል ጋር እንሰያያስን።

መልመጃ

1. የሚከተሉትን ስሞች ወደ ቅፅል ይለውጡ።
   ጥፋት፣ ጥጋብ፣ ወረት፣ ስበብ

2. ጥፋት ብሎ ጥፋተኛ ማለት ይቻላል። ክፋት ብሎ ክፋተኛ ማለት አይቻልም። ለምን?

3. /-አም/ በሚለው ምዕላድ የሚፈጠሩ ሶስት ቅፅሎችን ይጥቀሱ።

4. ከነዚህ ቅፅሎች ላይ ምን አይነት ስሞች እንደሚፈጠሩ ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ።

5. ስሞችን ወደ ቅፅል የሚለውጡ ምዕላዶች የቃል ክፍል ምን ይመስልዎታል? ለምን?

6. / ው - ር - ድ/ ከሚለው ስር ላይ

   (ሀ) አንድ የቀዳማይ፣ የካልዓይ፣ የቀጣይና የጨራሽ አምድ
   (ለ) አንድ ስም
   (መ) ሁለት የተላያዩ ቅፅሎችን ይመስርቱ።

7. /ስ-ብ-ር/ ከሚለው ስር ላይ፣

   የተለያዩ ስስር አምዶችን ይመሰርቱና በነሱ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ቅፅል፣ ስምና እና የቀዳማይ እንቀፅ ግስ ይመስርቱ።

8. <u>መጥረጊያ</u> የሚለውን ስም የአመሰራረት ስርዓት ያሳዩ።

9. በቀጥታ ከስም አምድ ላይ የተመሰረተ ግስ እንዲሁም ከግስ አምድ ላይ የተመሰረተ ስም ይስጡ።

10. ደከመ፣ ደካማ እና ድካም የሚሉትን ቃላት ከፍል ይግለፁ፣ አመሰራረታቸውንም ያሳዩ።

11. /ግ-ን-ፍ/ ከሚለው ስር ላይ አንድ ስም፣ ቅፅልና አንድ የቀዳማይ እንቀፅ ግስ ይመስርቱ። ለመሰረቱአቸው ቃላት ትርጉም ለመስጠት ይሞክሩ።

12. የርባታ ምዕላዶች ከመሰራች ምዕላዶች እንዴት እንደሚለዩ ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ።

ጥመራ

ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ቃላት ከምዕላድና ከቃላት ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ ለማሳየ፡ ኑ ሞክረናል። ከነባር ቃላት ላይ የተለያዩ መሰራች ምዕላዶችን በመቀጠል አዳዲስ ቃላትን መፍጠር እንደሚቻል ተመልክተናል። ስርዓቱን ቅጠላ ልንለው እንችላለን። ይህም እንዱና ምናልባትም ዋነኛው የቃላት ምስረታ ስርዓት ነው ልንል እንችላለን። ሌላው ስርዓት <u>ጥመራ</u> ነው። ይህ ስርዓት ከነባር ቃላት ላይ ዕስር ምዕላዶችን የሚቀጥል ብቻ ሳይሆን፣ ነባር ወይም ውልድ ቃላትን፡ ከነባር ወይም ከውልድ ቃላት ጋር በማጣመር፣ ማለትም በማቀናጀት፣ ጥምር ቃላትን የሚፈጥር ነው። የአጠማመሩን ዝርዝር ሂደት በዚህ ንዑስ ክፍል እንመለከታለን። ካሁን በፊት እንዳደረግነው ሁሉ፣ አሁንም ከስም በመጀመር የእያንዳንዱን የቃላት ክፍል የጥመራ ስርዓት በየተራ እንመረምራለን።

ጥምር ስሞች

በጥመራ ስርዓት የሚፈጠሩ ስሞች ጥምር ስሞች ይባላሉ። አፈጣጠራቸውም ከስሞችና ከግሶች ነው። ከስሞች የሚፈጠሩት እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

<u>ስም</u>	<u>ስም</u>	<u>ጥምር ስም</u>	1
ቤት	ክርስቲያን	ቤት-ኧ-ክርስቲያን	ቤተ ክርስቲያን
ሴቅ	መንበር	ሴቅ-ኧ-መንበር	ሲቀ መንበር
በትር	መንግስት	በትር-ኧ-መንግስት	በትረ መንግስት
ሰብል	ወንጌል	ሰብል-ኧ-ወንጌል	ሰብለ ወንጌል

ከመዘርዝሩ እንደሚታየው ሁለት ነባር ስሞች እየተጣመሩ አንድ ጥምር ስም ለመሆን ችለዋል። በየጥምሩ የመጀመሪያ ቃል መድረሻ ላይ /-ኧ-/ የሚል ቅጣይ አለ። ይህ ቅጣይ ሁለቱ ስሞች ተጣምረው አንድ አካል መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ስለዚህም አጣማሪ ምዕላድ ልንለው እንችላለን። በእሱ አማካኝነት የሚጣመሩትን ስሞች ተጣማሪ እንላቸዋለን። አጣማሪው ምዕላድ ከሌለ፣ ስሞቹ ጥምር መሆናቸው ይቀርና ዝምድና የሌላቸው ሁለት ተከታታይ ስሞች ብቻ ይሆናሉ። ጥምር ሲሆኑ የሚከተሉትን ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 1፣

$$[\underset{\text{ስም}}{\text{ስም}}] + [\underset{\text{አጣማሪ}}{\text{ኧ}}] + [\underset{\text{ስም}}{\text{ስም}}] \longrightarrow [\underset{\text{ጥምር}}{\text{ስም-ኧ-ስም}}]$$

ከላይ በሚታየው ሁኔታ ቃላት ከቃላት ጋር እየተቀናጁ ጥምር ቃል ይፈጥራሉ።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም የሚፈጠረው ቅንጅት ጥምር ቃል ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው። በዚህ ክፍል ለምንወያይበት ጉዳይ መሰረት የሚጥል ጥያቄ ሰለሆነ፣ ከወዲሁ ግልፅ የሆነ መልስ ያስፈልገዋል።

በስርዓት አንደ በሚታየው ሁኔታ ቃላት ሲቀነጹ የሚፈጠረው ቅንጅት ጥምር ቃል ነው የሚ ንለው፣ ቅንጅቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ከሆነ ነው።

(ሀ) የቅንጅቱ ፡ ትርጉም ከሚቀናጁት ቃላት ተናጠላዊ ትርጉም የተለየ ከሆነ፣
(ለ) ቅንጅቱ ለሌለቸ ቃላት ምስረታ መሰረት ሊሆን ከቻለ፣
(መ) እንደ ማ ነንኛውም ተራ (ቅንጅት ያልሆነ) ቃል ለልዩ ልዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራት ልዩ ልዩ ቅጥዮችን በመጨመር ሊረባ የሚችል ፤ ከሆነ፣
(ሰ) እንደ ማን ኛውም ተራ ቃል በከፍል ሁለት ከጠቀሰናቸው ሰድሰት የቃላት ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ሊመደብ ከቻለ፣ እና
(ረ) በሚቀናጁት ቃላቱ መካከል ከአጣማሪ ሌላ ምንም አይነት ምዕላድ የማያስገባ ፤ ከሆነ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሙሉ ወይም በከፈል የሚያሙዋላ ማንኛውም ቅንጅት እንደ አንድ ጥምር ቃል ሊቆጠር ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱት ጥምሮች እነዚህን መስፈርቶች እንዴት እንደሚያሙዋሉ፣ እንዱን ጥምር እንደ ምሳሌ እንውሰድና እንመልከት።

<u>ሊቀ መንበር</u> የሚለውን እንውሰድ። ጥምሩ የ<u>ሊቅ</u> እና የ<u>መንበር</u> ቅንጅት ነው። የጥምሩ ትርጉም ግን የተጣማሪዎቹ ተናጠል ትርጉም፣ ማለትም የ<u>ሊቅ</u> እና የ<u>መንበር</u> ትርጉም፣ ቅንጅት አይደለም። የጥምሩ ትርጉም የጉባዔ መሪ ወይም አለቃ ማለት ነው። መሪነትም ሆነ አልቅና ከሊቅነት ጋር ግንኙነት ላይኖረው ይችላል። ሊቀ መንበር የሆነ ሁሉ ሊቅ ነው፣ ማለት አይቻልም። ቢሆን ጥሩ ነበር፤ ብዙ ጊዜ ግን አይሆንም። ሁኔታው የጥምሩ ትርጉምና የተጣማሪዎቹ ቃላት ተናጠል ትርጉም የተለያየ እንደሆነ ያመለክታል።

<u>ሊቀ መንበር</u> ከሚለው ጥምር ላይ ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር ሌላ ቃል መፍጠር ይቻላል። ለምሳሌ /-ንንኦት/ የሚለውን የረቂቅ ሰም መሰራች ምዕላድ በጥምሩ መድረሻ ላይ በመጨመር፣ <u>ሊቀ መንበርነት</u> የሚል ሌላ ቃል መፍጠር ይቻላል። በተጨማሪም ጥምሩ እንደማንኛውም ተራ (ጥምር ያልሆነ) ሰም፣ /-ኦች/ የሚለውን የቁጥር ምዕላድ፣ ወይም /-ኡ/ የሚለውን የዕምርነት ምዕላድ ሊያስከትል ይችላል። ይህን ሲያደርግ፣ <u>ሊቀ መንበር-ኦች</u> እና <u>ሊቀ መንበር-ኡ</u> የሚል ቅርፅ ይኖረዋል። ምዕላዶቹ የሚቀጠሉት <u>መንበር</u> ከሚለው ተጣማሪ ላይ ነው። <u>ሊቅ</u> ከሚለው ላይ ቢቀጠሉ፣ ቅርፁ <u>ሊቅ-ኦች መንበር</u> ወይም <u>ሊቅ-ኡ</u>

መንበር የሚል ይሆናል፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ለቁጥርና ለምርነት የሚረባው ሙሉ ጥምሩ እንጅ፣ የጥምሩ አንድ አካል የሆነው ምዕላድ በቻ ባለመሆኑ ነው፡፡ አነዚህ ሁኔታዎች ሊቀ መንበር የሚለው ቅንጅት አጭ ቃል እንጅ የሁለት ለሞች ከትትል አንዳልሆነ ያመለክታሉ፡፡ አንድ ፆል ባይሆን ኖሮ፣ መለተዓምሩ /-ኡ/ ሊቅ በሚለው ላይ ሲቀጠል፣ ተቀባይነት ያለው አባባል እናገኝ ነበር፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ሊቅ-ኡ ልጅ 2

ይህ ተቀባይነት ያለው አባባል ነው፡፡ መለተዓምሩ /-ኡ/ የሚገኘው ሊቅ ከሚለው ቃል ጋር ነው፡፡ ልጅ ከሚለው ጋር እንደሚከተለው ሆኖ ቢገኝ፣ መዋቅሩ አንድም ተቀባይነት አይኖረውም፡ አለያም ትርጉሙን ይለውጣል፡፡

*ሊቅ ልጅ-ኡ 3

ሊቅ ልጅ-ኡ የሚለው ትርጉም፣ ሊቅ የሆነው የሰውየው ልጅ አንደ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ትርጉም ለውጥ ምክንያት የሆነው /-ኡ/ የሚለው ምዕላድ አገናዛቢ (ባለገንዘብን አመልካች) በመሆኑ ነው፡፡ ከመለተዓምሩ /-ኡ/ በአገባብ ይለያል፡፡ አንዴት አንደሚለይ በከፍል ሶስት አንመለከታለን፡፡

ጥምሩ፣ ማለትም ሊቅ መንበር፣ የሰም ወገን ነው፡፡ ይህን የምንልበት ምክንያት አንደ ማንኛውም ስም ባለቤትም ሆነ ተሳቢ ሆኖ በአረፍተ ነገር ውስጥ ለለሚገኝ ነው፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

(ሀ) ሊቀ መንበሩ መጣ 4
(ለ) አለቁር ሊቀ መንበሩን ጠራችው

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ ሊቀ መንበሩ የሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል፡፡ አገባቡም በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ቃል የግሱ ተሳቢ ሆኖ ገብቶአል፡፡ ቦታውም ከግሱ በፊት ነው፡፡ አነዚህ መዋቅራዊ ባህሪያት ስሞችን ከሌሎች የቃላት ከፍሎች ለለሚለዩ፣ ጥምሩንም የስም ወገን ያደርጉታል፡፡ በተጨማሪም /-አችች/ የሚለውን የቁጥር ምዕላድ ማለከተሉ የለም ወገን ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

በመጨረሻም ሊቀ መንበር የሚለው ጥምር ለመሆኑ ማረጋገጫው በሊቅ እና በመንበር መካከል ሌላ ቃል ማስገባት አለመቻሉ ነው፡፡ ለዚህ የሚከተለውን አንመልከት፣

*ሊቀ ጥሩ መንበር 5

ይህ ተቀላጽሏት ያለው አባባል አይደለም። ለዚህ ምክንያቱ በሁለቱ ተጣጋሪዎች መካከል ጥሩ የሚለው ቃል ገብቶ ቀንጮቹ ነው። ይህም ሁለቱ ቃላት እንድ አከል ስለሆኑ፣ ባሀድ አቅል በመካከላቸው ሊያስገቡ እንዳልቻሉ ያመለክታል። ጥሩ የሚለው ቅፅል መሉ ጥምሩን እንጅ የጥምሩ ገማሽ አካል የሆነውን መንበርን ብቻ ሊገልፅ አይችልም። ሙሉ ጥምሩን በሚገልፅበት ጊዜ እንገበ እንደሚከተለው ነው።

[ጥሩ [ሊቀ መንበር]] 6

ጥሩ የሚለው ቅፅል ሊቀ መንበር ከሚለው ጥምር ስም ጋር ተዋቅር ጥሩ ሊቀ መንበር የሚል ሰፊ መዋቅር መስርቶአል። የመዋቅሩ መሪ ሙሉ ጥምሩ ነው። ቅፅሉ የተምሩ ገላጭ ነው።

እንግዲህ ሊቀ መንበር የሚለው ቅንጅት ከላይ ከ(ሀ) እስከ (ረ) ድረስ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ስላሙዋላ፣ እንደ ሁለት ተከታታይ ቃላት ሳይሆን፣ እንደ አንድ ጥምር ቃል ሊቆጠር ይችላል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ይኸውም ሊቀ መንበር የሚለው ቅንጅት ጥምር ቃል ባይሆን ኖሮ፣ ምን ለሆን ይችል ነበር? የሚል ነው። አንድ ቅንጅት ጥምር ቃል ካልሆነ፣ አንድም ዕሰር አምድ፣ አለያም ሀረግ ሊሆን ይችላል። ዕሰር አምድ ምን ማለት እንደሆነ፣ ካሁን በፊት ተገልያለል፣ ሙሉ ቃል ለመሆን ምዕላድ የሚፈልግ አሀድ ነው ብለናል። ልምላሌ፣ ገደል የሚለውን ቅርፅ ብንመለከት፣ ሙሉ ግስ አይደለም። ሙሉ የሚሆነው፣ እንደ /-ኧ/ ያለ የርባታ ምዕላድ ሲቀጠልበት ነው። ይህም ባሚሆንበት ጊዜ፣ ቅርፁ ገደል-ኧ የሚል ሙሉና ነፃ ቃል ይሆናል። በግስነት በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘውም በዚህ በሙሉ መልኩ ነው። ሀረግ የሚለውን ቃል ወደፊት በሰፊው እንገልፀዋለን። ለጊዜው ግን ደረጃው ከቃል በላይ የሆነ ቅንጅት ነው፣ ብለን እናልፈዋለን። ከዚህ አንፃር ሊቀ መንበር የሚለውን ስናይ፣ ቅርፁ ከሀረግ በታች እና ከዕሰር ምዕላድ በላይ እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ ደረጃ የሚገኝ ማንኛውም ቅርፅ ቃል ነው። ደረጃው ግን ተራ ወይም ጥምር ሊሆን ይችላል።

ጥምር ቃላት ከሙሉ ቃል ወይም አምድ ላይ ሊመሰረቱ ይችላሉ። ተጣጋሪዎቹ በጥምሩ ውስጥ የተለያየ ቦታና ተግባር አላቸው። ተግባራቸውም መሪነት ወይም ገላጭነት ነው። ከተጣጋሪዎቹ አንዱ የጥምሩ መሪ ሲሆን፣ ሌላው የእሱ ገላጭ ነው። መሪ የሚባለው፣ ሙሉ ጥምሩ በሚገባበት ቦታ ሁሉ፣ ዩትርጉም ለውጥ ሳያስከትል ብቻውን ሊገባ የሚችለውንና ከጥምሩ ጋርም በቃል ክፍሉ አንድ የሆነው ተጣጣሪ ነው። ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ጥምር እንውሰድና ሁኔታውን በምሳሌ እንረዳው።

(ሀ) ቤተ ክርስቲያኑ ተዘረፈ 7
(ለ) ቤቱ ተዘረፈ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ቤተ ክርስቲያኑ</u> የሚለውን ጥምር <u>ቤቱ</u> የሚለው የጥምሩ የመጀመሪያ ቃል፣ ማለትም ተጣማሪ፣ ተክቶታል። ይህም ሲሆን የአረፍተ ነገሩ መሰረታዊ ትርጉም አልተለወጠም። በሁለቱም አረፍተ ነገሮች የተዘረፈው <u>ቤት</u> ነው። ነገር ግን ጥምሩን <u>ቤቱ</u> የሚለው ተጣማሪ ሳይሆን፣ <u>ክርስቲያኑ</u> የሚለው ተጣማሪ ቢተካው ናሮ፣ ውጤቱ እንደሚከተለው ይሆን ነበር።

ክርስቲያኑ ተዘረፈ 8

ይህ አረፍተ ነገር የተሰተካከለ ነው። ይሁን እንጅ፣ በመሰረታዊ ትርጉሙ በተራ ቁጥር 7(ሀ) ከሚታየው ምሳሌ ትርጉም የተለየ ነው። ምክንያቱም በተራ ቁጥር 7(ሀ) ውስጥ የተዘረፈው <u>ቤተ ክርስቲያኑ</u> እንጅ <u>ክርስቲያኑ</u> አይደለም። በምሳሌ ተራ ቁጥር (8) ግን የተዘረፈው ቤቱ ሳይሆን፣ ክርስቲያኑ ነው። ክርስቲያን የሚለው ቃል ሙሉ ጥምሩን ተክቶ ሲገባ፣ በአረፍተ ነገሩ ትርጉም ላይ ለውጥ አስከትሎአል ማለት ነው። ይህን የሚያደርግ ተጣማሪ፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ የጥምር መሪ ሲሆን አይችልም። መሪ ሲሆን የሚችለው፣ ያለምንም መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ጥምሩን እየተካ ሲገባ የሚችለው ተጣማሪ ብቻ ነው። በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ይህን ሲያደርግ የሚችለው <u>ቤት</u> የሚለው ተጣማሪ ስለሆነ፣ እሱ የጥምሩ መሪ ነው። የዚህ የቃል ክፍልም ስም ስለሆነ፣ ከጥምሩ የቃል ክፍል ጋር እንድ ነው።

<u>ክርስቲያን</u> የሚለው ተጣማሪ ቃል በጥምሩ ውስጥ ያለው ተግባር ምንድን ነው? የሚል ጥያቄም ማንሳት ይቻላል። የእሱ ተግባር መሪውን ተጣማሪ መግለፅ ነው። በዚህ መሰረት በምሳሌው ውስጥ <u>ክርስቲያን</u> የሚለው ተጣማሪ ቤቱ የእስላም፣ የተማሪ፣ የመጠጥ፣ ወዘተ፣ ሳይሆን፣ የክርስቲያን ብቻ መሆኑን በመግለፅ ተግባሩን መወሰን ነው። ከዚህ አንፃር ሲታዩ፣ ተጣማሪዎቹ ገላጭ እና ተገላጭ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል። መሪው ተገላጩ ሲሆን፣ እኛቢው ወይም ተክታዩ ገላጩ ነው። ባጭሩ የተጣማሪዎች ዝምድና የመሪና የተመሪ፣ ብሎም የተገላጭና የገላጭ ነው።

ይህ ዝምድና መሪውና አኛቢው (ገላጩ) በጥምሩ ውስጥ በሚገኙበት ቦታ ይወሰናል። ስምሳሌ፡ በጠቀስነው ጥምር ውስጥ የመሪው ቦታ ከአኛቢው በስተግራ (በፊት) እንደሆነ እንመለከታለን። በተጠቀሱት ሌሎች ጥምሮች የሚታየው ቅደም-ተከተልም እንደዚሁ ነው። በዚህም ምክንያት እንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ያሉ ጥምሮች በሙሉ ግራ መሪ ጥምሮች ሲባሉ ይችላሉ። ግራ መሪ ስመሆናቸው ተጨማሪ ምልክት አለ። ይኸውም /-ኧ/ የሚለው አጣማሪ ምዕላድ ነው። ይህ ምላድ የተቀጠለው በመሪው ተጣማሪ፣ ማለትም በ<u>ቤት</u>፣ ላይ ነው። ያንድን ጥምር መሪ ለማወቅ ይህ ምዕላድ የሚገኝበትን ተጣማሪ ማየቱ ጠቃሚ ሲሆን ይችላል። <u>ቤተ ክርስቲያን</u> በሚለው ጥምር ውስጥ /-ኧ/ የሚገኘው <u>ቤት</u> ቦሚለው ተጣማሪ ላይ ስለሆነ፣ ይህ ቃል የጥምሩ መሪ ነው።

ግራ መሪ ጥምሮች እንዳሉ ሁሉ፣ ቀኝ መሪ ጥምሮችም አሉ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ስም	ስም	ጥምር	9
ዳቦ	ቤት	ዳቦ ቤት	
አየር	መንገድ	አየር መንገድ	
ብረት	ድስት	ብረት ድስት	

እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች መሪ በቀኝ በኩል ያለው ተጣማሪ ነው። ለምሳሌ፣ ዳቦ ቤት የሚለውን ጥምር ብንወስድ፣ መሪው ቤት የሚለው ተጣማሪ ነው። ዳቦ የዚህ መሪ አጃቢ ብሉም ገላጭ ነው። የቤቱ ተግባር ምን እንደሆነ ይገልፃል። ያጠማመሩን ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፣

ስርዓት 2፣

[ለም] + [ስም] ⟶ [ለም]
ጥምር

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ፣ እንደ ዳቦ ቤት ያሉ ቅንጅቶች ጥምር ቃል መሆናቸውን ቀደም ሲል በጠቀስናቸው መስፈርቶች ማረጋገጥ ይቻላል። ለምሳሌ፣

ዳቦ ቤት ገዛሁ 10

ብንል፣ ዳቦ ቤት የሚለውን ጥምር ያለ ምንም መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ሊተካው የሚችለው ቤት የሚለው ተጣማሪ ነው። ይኸውም፣

ቤት ገዛሁ 11

በማለት ነው። ቤት በሚለው ፋንታ ዳቦ የሚለው ተጣማሪ ቢገባ፣ የአረፍተ ነገሩ መሰረታዊ ትርጉም ይለወጣል። ከዚህም ዳቦ የሚለው ተጣማሪ የጥምሩ መሪ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል።

እንደ ዳቦ ቤት ያሉትን ጥምር ቃላት መሪ ለማወቅ የሚቻለው ከተጣማሪዎቹ አነባብ አንጅ፣ ቀደም ሲል አንዳየነው፣ ከቅርፅ አኩዋያ አይደለም። ከቅርፅ ማወቅ የሚቻለው በአጣማሪ አማካኝነት የሚጣመሩ ቃላትን መሪ ብቻ ነው። ሁኔታው ጥምር ቃላትን አጣማሪ ያላቸውና የሌሳቸው ብለን በሁለት አንድንከፍሳቸው የሚያደርግ ነው። አጣማሪ ያላቸውን ጥምሮች መሪ፣ በቅርፅና በአነባብ መለየት ሲቻል፣ አጣማሪ የሌሳቸውን ጥምሮች መሪ በአነባብ ብቻ ማወቅ ይቻላል።

ከፍ ሲል እንደ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ጥምሮች ግራ መሪ ሲሆኑ፣ እንደ ዳቦ ቤት ያሉት ቀኝ መሪ እንደሆኑ ገልፀናል። ይህ ደግሞ በቁዋንቁዋው ውስጥ ሁለት አይነት ጥምሮች እንዳሉ ያሳያል። ይህ ሊሆን ይችላል ወይ? በአንድ የቃላት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቃላት ሲቀናጁ የሚፈጠሩት ጥምሮች ግራ ወይም ቀኝ መሪ እንጅ፣ እንዴት ከፊሉቹ ግራ፣ ከፊሉቹ ደግሞ ቀኝ መሪ ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ጥያቄው ተገቢ ነው። በመሰረቱ

በግንኛውም ቁዋንቁዋ ቢሆን፣ በአንድ ከፍል የሚገኙ ቃላት ሲቁናኝ የሚፈጥሩት ጥምር ቃላት ወይ ግራ፣ ወይ ደግሞ ቀኝ መሪ ይሆናሉ እንጅ፣ ከፈሉቹ አንዱን አይነት፣ ሌሉቹ ሌላውን አይነት ጥምር ሊሆኑ አይችሉም። የመሪው አይነትና የአገባብ ቦታም እንደዚሁ አንድ ወጥ መሆን አለበት።

ጥምሮች ሁለት አይነት የሚሆኑት ቁዋንቁዋው ሁለት አይነት የጥመራ ሰርዓቶችን የሚከተል ሲሆን ነው። ይህም ሊሆን የሚችልው፣ ቁዋንቁዋው ከሌላ ቁዋንቁዋ ጋር ግንኙነት ሲኖረውና፣ በዚያ ቁዋንቁዋ ተጋቦት ምክንያት የዚያን ቁዋንቁዋ ሰርዓት ከራሱ ሰርዓት ጋር ሳን ሰንን ሊጠቀም ነው። ቁዋንቁዋው ሁለቱንም ሰርዓቶች የሚጠቀም ከሆነ፣ ጥምሮቹም እንደሚፈጠሩበት ቁዋንቁዋ ሰርዓት የተለያየ የመሪና የገላጭ አቀማመጥ ሊይዙ ይችላሉ።

ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ የአማርኛ የጥመራ ሰርዓትም በከፊል ከሌላ ቁዋንቁዋ የመጣ ነው ለማለት ይቻላል። ይህ ትክክል ነው። የግራ መሪ ጥምሮች ሰርዓት የአማርኛ ሳይሆን፣ የግዕዝ ነው። በዚህ ቁዋንቁዋ ጥምር ቃላት በሙሉ ግራ መሪ ናቸው። እንደ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ግራ መሪ ቃላት መሰረትም ሆነ የጥመራ ሰርዓት የዚሁ ቁዋንቁዋ ነው። የአማርኛውን ሰርዓት ተከትሏው የሚፈጠሩት እንደ ዳቦ ቤት ያሉ ቀኝ መሪ ጥምሮች ብቻ ናቸው። የርባታ ምዕላዶችም ሆኑ የምስረታ ምዕላዶች የሚቀጠሉት በዚሁ መሪ ላይ ነው፣ ስምላሌ፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ እንደ /-አች/ ያሉ የርባታ ምዕላዶችና እንደ /-ንጋኦት/ ያሉ የምስረታ ምዕላዶች የሚገቡት መሪውን ተጣግሪ፣ ግለትም ቤት የሚለውን ስም፣ ተክትሏው ነው። ስለዚህም፣

(ሀ) ዳቦ ቤት-አች ዳቦ ቤቶች 12
(ለ) ዳቦ ቤት-ንጋኦት ዳቦ ቤትነት

እንላለን።

በዚሁ በአማርኛው ሰርዓት መሰረትም፣ በግዕዙ ሰርዓት በሚፈጠሩ ግራ መሪ ጥምሮች ላይ የርባታም ሆነ የምስረታ ምዕላዶች የሚቀጠሉት ከቀኙ ተጣግረ ላይ ነው። ስለዚህም፣

(ሀ) ቤተ መንግስት-አች 13
(ለ) ሊቀ መንበር-አች

ግለት፣ የተለመደ ነው። ይሁን እንጅ፣ እንደነዚህ ባሉ ጥምሮች፣ ምዕላዶቹ የተቀጠሉት ከመሪው ላይ ላይሆን ከአሻቢው፣ ግለትም ከገላጩ ስም ላይ ነው። እንደ ግዕዙ ሰርዓት ቢሆን ኖር፣ ምዕላዶቹ ከመሪው ስም ላይ መቀጠል ነበረባቸው። ይህ ሲሆን፣ ቃሉ በግዕዝ መልኩ አብያተ መንግስት ይሆናል። የአማርኛውን /-አች/ ከመሪው ላይ ብንቀጥልበት፣

*ቤት-አች መንግስት 14

የሚልና ተቀባይነት የሌለው ጥምር ይሆናል። ተቀባይነትን የሚያጣበት ምክንያት የርባታው ምዕላድ /-አች/ በቀኝ በኩል ከሚገኘው ተጣግሪ ቃል እንጅ፣ በግራ በኩል ከሚገኘው ላይ መቀጠል ስለማይችል ነው። በቀኝ በኩል

የሚገኘው ቃል የቀደሙ መሪ በዚያንም ባይሆንም፣ ምዕላፉ የሚቀጠለው ከእሱ ጋር ነው፤ ለምዕላፉ ግራሌያ ቋሳኝ ቢታወ እንጅ በበታወ ላይ የሚገኝ ተጣማሪ ተግባር አይደለም።

በዚህ ሞዴሬት ምዕላዶችን ካቀኝ ተጣማሪ ላይ የሚያሳይ፣ እንደ ቤተ ጫንጎስቶች ያሉ ቃላት ከገዕዙ ስርዓት ደሬነገጡ ስለሚመስሉ፣ አንዳንድ የገዕዝ ምሁራንን ሳያስቆጡ አይቀሩም። ምክንያቱም የርሳታው ምዕላድ የሚያመለክተው ቤት የሚለውን መሪ ቃል ብዛት ሳይሆን፣ መንግስተ የሚለውን አጻቢ ቃል ብዛት ነው። ከአማርኛ ስርዓት አንፃር ሲታይ፣ የምዕላዱ አግብብ ትክክል ነው። የምዕላዱ አግብብ በበታ እንጅ በበታው ላይ ቢሚገኝ ቃል ተግባር ላይ የሚወሰን አይደለም[1]።

እስካሁን ለግሳየት የሞከርነው ተራ ስሞችን ቢግትናጀት ጥምር ቃላትን አንዲት መፍጠር እንደግቻል ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ጥምር ስሞች ከውልድ ስሞችና ከግስ አምዶች ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ እንመለከታለን።

ስም መዝ	ገላጭ አምድ	ጥምር ስም መዝ
አለም	አደር- አተኖ	አለም አተኖ
አየር	ወለድ-	አየር ወለድ
ሞፈር	ዘሙት-	ሞፈር ዘሙት

የእንዚህ አይነት ጥምርች ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 3፣

[ስም] + [ገለ-] ⟶ [ስም]
ተሞላ ተሞር

---

[1] በዚህ ረገድ በጅሀራት ዘንድ ዘወትር የሚወቀሳው ገባሪ ሀይል የሚለው ጥምር ነው። በገዕዙ አካሄድ፣ የጥምሩ መሪ ገብር ሲሆን፣ አጻቢው ሀይል የሚለው ተጣማሪ ነው። የጥምሩ የገዕዝ ትርጉም የሀይል ገብር ወይም ስራ ማለት ነው፣ ይህ ደግሞ በነ ቅርነም አይጀስም፣ በአማርኛ ግን የሰራ ሀይል (ታስክ ፎርስ) የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ ስለሚገልፅ በጀርግ ዘመን ስራ ላይ የዋለ ጥምር ነው። የዋምሩ መሪ ሀይል የሚለው ተጣማሪ ስለሆነ፣ አጠማመሩ የአማርኛውን ስርዓት የተከተለ ነው። ይሁን እንጅ፣ አጣማሪው ምዕላድ የሚገኘው እንደ ገዕዙ ስርዓት ከመጀመሪያው ተጣማሪ፣ ማለትም ከገብር ጋር ነው። ሁኔታው የገዕዙ የአጠማመር ስርዓት ወደ አማርኛው ዘልቆ እየገባ ሰሆኑን ይሳያል። ሲገባም አንደ አማርኛው ስርዓት ሁኔን ተጣማሪ መሪ እያደረገ ነው። ፀሎሩ እንደ ገባሪ ሀይል ያሉ ጥምርች ስርዓት እንደ ገዕዝ ሆኖ፣ የመሪ ሉተማመጣቸው እንደ አማርኛ ነው። ደሁሉ ቁዋንቁዋዎች ስርዓት የሚንፀባረቅባቸው በይነ-ልሳናዊ ምሳሌዎች ናቸው።

ግሳዊው ተጣማሪ የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ነው። ሙሉ ቃል የሚሆነው የርባታ ምዕላድ ሲከተሰው ነው። ሰምሳሌ፣ <u>አደር-</u> የሚሰውን አምድ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ሲከተለው፣ <u>አደረ</u> የሚል ሙሉ ግስ ይሆናል።

እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች አጣማሪ የላቸውም። ሁሰተኛም የጥምሩ መሪ በቀላሉ የሚታወቅ አይመስልም። ቀደም ሲል መሪ የሚሆነው ሙሉ ጥምሩን ሊተካ የሚችለው ተጣማሪ ነው፣ ብለን ነበር። በዚያ መሰረት የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ወዝ አደር ነው 16
(ለ) ?ካሳ አደር ነው
(መ) ?ካሳ ወዝ ነው

ከምሳሌ (ለ) እና (መ) መረዳት የሚቻለው፣ <u>አደር</u> የሚሰውም ሆነ <u>ወዝ</u> የሚሰው ተጣማሪ <u>ወዝ አደር</u> የሚሰውን ጥምር ሊተካው አለመቻሉን ነው። <u>አደር</u> የሚሰው ተጣማሪ ጥምሩን ሊተካው ያልቻለበት ምክንያት ምናልባት ዕሰር አምድ በመሆኑ ይሆናል። ይሁን እንጅ የጥምሩን መሰረታዊ ትርጉም አይለውጠውም። <u>ወዝ</u> የሚሰው ተጣማሪ ግን የጥምሩን መሰረታዊ ትርጉም ይሰውጠዋል። ካሳ <u>ወዝ አደር</u> አንጅ ራሱ <u>ወዝ</u> አይደለምና።

ከተግባር አንፃር ሰናያቸው፣ <u>አደር</u> የሚለው ተጣማሪ ተግባርን ወይም ድርጊትን ያመለክታል። <u>ወዝ</u> የሚሰው ደግሞ ማድረጊያን ይጠቁማል። የጥምሩ ትርጉምም በወዙ የሚያድር ወይም የሚኖር ማለት ነው። ይህ ከሆነ፣ <u>አደር</u> የሚለው ተጣማሪ የጥምሩ መሪ፣ <u>ወዝ</u> የሚለው ደግሞ አጃቢ ሲሆን ይችላል። በሀረግ ደረጃ ሲታይ፣ <u>በወዙ አዳሪ</u> የሚል ሰማዊ ሀረግ ወይም <u>በወዙ አደረ</u> የሚል ግሳዊ ሀረግ ይሆናል። አዳሪ እና አደረ የየሀረጎቹ መሪ ቃል ናቸው። በወዙ የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ተግባሩ መሪውን ሰም ወይም ግሰ መግለፅ ነው። ከዚህ አንፃር፣ <u>ወዝ አደር</u> የሚሰው ጥምር <u>በወዙ አደር</u> እንደ ማለት ሰሰየነ፣ <u>አደር</u> የሚለው የጥምሩ መሪ ይሆናል። አቀማመጡም ከፍ ሲል እንዳየናቸው አንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉ ጥምሮች መሪ በሚገኝበት በቀኝ በኩል ነው።

መሪንና ገላጭን መሰየት የሚያሰቸግረው የተጣማሪዎች የጥምረት ደረጃ ከፍተኛ ሲሆን ነው። የጥምረቱ ደረጃ ተጣማሪዎችን ከጥምርነት ወደ አንድ ቃልነት ሊለውጣቸው ይችላል። አንድ ቃል ከሆኑ ደግሞ መሪና ተመሪ የሚሰው ልዩነት ይጠፋል። የመሪና የተመሪ ልዩነት በቀላሉ የሚታወቀው የጥምረት ደረጃቸው ልል በሆኑ ጥምሮች ውሰጥ ነው። ሰዚህ እንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉ ጥምሮች ምሳሌ ሲሆኑ ይችላሉ። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ የነዚህ አይነት ጥምሮች መሪ በሰተቀኝ በኩል የሚገኘው ተጣማሪ ነው። ጥምሩን ያለምንም መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ሊተካ የሚችለው እሱ ነውና። የግራው ተጣማሪ የእሱ አጃቢ ነው። ከሁኔታው የምንረዳው የተለያየ የጥምረት ደረጃ እንዳለ ነው። ደረጃው ከፍተኛ ሲሆን፣ ተጣማሪዎቹ ከጥምረት አልፈው እንድ አካል አንድ አምሳል

ስለሚሆኑ፣ የመሪና የተመሪ ጥያቄ አይኖርም። ከኖረ፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ መልሱ አስቸጋሪ ይሆናል። ስዚህ አይነቱ ሁኔታ በአማርኛ ምሳሌ ሲሆኑ የሚችሉት እንደ ደኛዝማች፣ ግራዝማች፣ ምስለኔ፣ ወዘተ፣ ያሉት የማዕረግ ስሞችና እንደ በሶ ብላ፣(ዝቃቅቤ)፣ ባርማሽላ፣ ወዘተ፣ ያሉ የእዝርዕት ስሞች ናቸው። የማዕረግ ስሞቹ ቅርፅ በገጠሩ አካባቢ ወደ ደጃዝማይ፣ ግራማይ፣ ቀኛማይ፣ ወዘተ፣ እየተለወጠ መጥቶአል። ከጥምርነት ወደ አንድ ቃልነት ተሸጋግረዋል። <u>ቤተ ክርስቲያን</u> የሚለውም ቢሆን ቅርፁን ለውጦ ቤተክሲያን የሚባልበት አካባቢ አለ። በዚያ አካባቢ ጥምሩ አንድ ቃል ሆናአል። ስስሆነም የመሪና የተመሪ ወይም ገላጭ ጥያቄ አይነሳም።

በስርዓት ስስት የተመለከትነው ከስሞችና ከግሳዊ አዕማድ የሚመሰረቱ ስሞችን ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከግሳዊ አዕማድ ላይ የሚመሰረቱትን ጥምር ስሞች እንመለከታለን።

17

<u>ግሳዊ አምድ</u>	<u>ግሳዊ አምድ</u>	<u>ጥምር</u>
ስርት-ኦ	አደር-	ስርቶ አደር
ወልድ-ኦ	ገደል-	ወልዶ ገደል
ወር-ኦ	በላ	ወሮ በላ
ገምጥ-ኦ	ወጭ-	ገምጦ ወጭ
ወድ-ኦ	ገብ-	ወዶ ገብ (ገባ)

አንደነዚህ ያሉ ጥምሮች የሚመሰረቱት ከሁለት ግሳዊ አዕማድ ነው። የመጀመሪያው (ግራ) ተጣማሪ አምድ በቀደምት ሊቃውንት ቦዝ አንቀፅ በመባል የሚታወቀውና ባለፈው ክፍል ጨራሽ አንቀፅ ያልነው ነው። መሰረቱ ካልዓይ አንቀፅ ነው። በርባታው ስርዓት እንዳየነው፣ ይህ አንቀፅ /1ኧ23-/ የሚል ቅርፅ አለው። ስምሳሌ፣ <u>ስብር-</u> (/ ስኧብር-/) የሚለውን አምድ ብንመለከት፣ /1ኧ23-/ የሚለውን ስርዓት ተከትሎ የተመሰረተ አንቀፅ እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ አምድ ላይ /-ኦ/ የሚለውን ምዕላድ ስንጨምር፣ ስብሮ (/ ስኧብር-ኦ/ = 1ኧ23-ኦ) የሚለውን ቦዝ አንቀፅ እናገኛለን። አንቀፁ ብቻውን የአረፍተ ነገር መጨረሻ ሊሆን ስለማይችል፣ ቦዝ የሚል ስያሜ ሊስጠው ችሎአል። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

ካሳ ስራ ስርቶ... 18

ይህ ያለቀ ድርጊትን አንጅ ሙሉ አረፍተ ነገርን አይገልፅም። ስለዚህም፣ <u>ካሳ ስራ ሰርቶ</u> ምን ሆነ? የሚል ጥያቄ የግድ ያስከትላል። የጎደለ ነገር አለ ማለት ነው።

ብንል፣ ግንኙነቱ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ አይነሳም። እረፍት ንጉሥ ቅቤቀጥላአልፍ፣ ቦትቀየጠውም ሙጣ በሚለው ግስ ነው። ስለ ጀርመን የሁለተኛው ተጭማሪ ዝምድ ቅርፅ ቀዳማይ ነው፣ የዚህ አንቀፅ ቅርፅ በርሳቷው ክፍል እንዳየነው ግሥ+አ22አ8-ነ የሚል ነው፣ ሳደሰ (ሳ+አድድአል-ነ) የሚለው የዚህ ምሳሌ ነው። በዝ አንቀፁና ቀዳማይ አንቀፁ ሊጣመሩ፣ ከነጋይ የተዘረዘሩትን አይነት ጥምር ስሞች እናገኛለን። የአጠማመሩን ስርዓት አንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ስርዓት 4፣

[ግሰ-] + [ግሰ-] ⟶ [ስም]
ዮዝ ተሳጣይ

በእነዚህ አይነት ጥምሮች ውስጥ መሪው ቀዳማዩ አንቀፅ፣ ግሰትም ቀኝ ተጣማሪ ሲሆን፣ ቦዙ አንቀፅ የመሪው ገላጭ ነው። ለምሳሌ፣ በስርዓቱ መሰረት ሰከር አደር ብንል፣ የምንናገረው ስለ አዳር፣ ግሰትም ስለ ኑር፣ ነው። አዳሩ የምን አይነት እንደሆነ የሚገልፅልን ሰከር የሚለው ግራ ተጣማሪ ነው። በሌላ አነጋገር፣ የተጣማሪዎቹ ትርጉም የጥምሩን መሪ አመለየት ይረዳል። ከአገባብ አንፃር ብናየው፣ ጥምሩ ሰከር አደረ የሚል ሀረጋዊ አቻ እንዳለው አንረዳለን። ከዚህም አደረ የሚለው ግስ መሪ፣ ሰከር የሚለው ቦዝ ገላጭ መሆኑን እንገነዘባለን።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም የጥምሮቹ መሰረት የሆኑት አዕማድ ግሳዊ ከሆኑ፣ ጥምሮቹ እንዴት ስማዊ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ነው። በመሰረቱ፣ አንድ ጥምር ስማዊ ሲሆን የሚችለው፣ ከተጣማሪዎቹ አንዱ ስም ሲሆንና ጥምሩንም ሲመራ ነው። ተጣማሪዎቹ ግሳዊ ከሆኑ፣ ጥምሩ ግስ አንጅ ስም ሲሆን አይችልም ስማለት ይቻላል። ጥያቄው ቅል ተክሉ ቅል አንጅ፣ ዱባ ግንኙነት እንዴት ይቻላል? የሚል አይነት ነው። ውጉትም መሰረቱ ግሳዊ አዕማድ ከሆነ፣ መድረሻውም ግሳዊ ቃል መሆን አለበት። አለበለዚያ ቃልዘሩበቀል ይሆናል። ይሁን እንጅ፣ ከላይ የሚታዩት ጥምሮች በሙሉ ስሞች ናቸው። ለስምነት መለያ የተጠቀምንባቸውን መለፈርቶች በሙሉ ያሟላሉ። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) [ሰርቶ አደሮች] የደሞዝ ጭማሪ ጠየቁ
(ለ) ካሳ [ሰርቶ አደሮቹን] አሳረራቸው
(መ) [ታታሪ [ሰርቶ አደሮች]] ይሸማሉ

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ጥምሩ ባለቤት ሆኖ በአረፍት ነገሩ መነሻ ላይ ይገኛል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ ተሳቢ ሆኖ ከግሱ በፊት ገብቶአል። የተሳቢ ምልክት የሆነውን /-ን/ የሚለውን ምዕላድም አስከትሎአል። በሶስተኛው ውስጥ ደግሞ <u>ታታሪ</u> ከሚለው ቅፅል በሁዋላ (በስተቀኝ) ይገኛል። እነዚህ አገባባዊ የሆኑ የስሞች ባህሪያት ናቸው። የጥምሩን ቅርፅ ስንመለከት ደግሞ /-እች/ የሚለውን የስሞችን የቁጥር ምዕላድ እንዳስከተለ እንረዳለን። ያለክተለውም በቀኙ ተጣማሪ ነው። እነዚህ አይነተኛ የስም ባህሪያት ናቸው። ስለዚህም ጥምሩ ስም ነው።

ምናልባት ቅፅላዊ የሆነ አገባብ ስላለው፣ ጥምሩ ቅፅል ነው፣ ሊባል ይችል ይሆናል። ለዚህ የሚከተለውን እንመልከት።

21
(ሀ) ካሳ [[ጎበዝ] [ልጅ]] አለው
(ለ) ካሳ [[ወዝ አደር] [ልጅ]] አለው

በምሳሌ (ሀ) <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል <u>ልጅ</u> ከሚለው ስም በፊት ገብቶ ይገኛል። በምሳሌ (ለ) ይኸው ቅፅል <u>ወዝ አደር</u> በሚለው ጥምር ተተክቶ ይታያል። ይሁን እንጅ፣ <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ዋነኛ የቅፅል መለያ ነው ያልነውን መስፈርት እያሙዋላም። ይህንም ከሚከተሉት ምሳሌዎች ንፅፅር መረዳት ይቻላል።

22
(ሀ) በጣም <u>ጎበዝ</u>
(ለ) * በጣም <u>ወዝ አደር</u>

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል <u>በጣም</u> ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ገብቶ ቅፅላዊ ሀረግ ለመመስረት ችሎአል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ከዚሁ መስተዓምር ጋር ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ ሀረጉ ተቀባይነት የለውም። ይህም <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ቅፅል አለመሆኑን ያረጋግጣል። ቅፅል ቢሆን ኖሮ፣ እንደ ማንኛውም ቅፅል <u>በጣም</u> ከሚለው መስተዓምር ጋር ሲዋተር ተቀባይነት ያለው ቅፅላዊ ሀረግ መፍጠር ነበረበት። ሁኔታው በስርዓት (4) መስረት የሚፈጠሩ ጥምሮች፣ መስረታቸው ግስ ቢሆንም፣ ክፍላቸው ስም እንጅ ግስ ወይም ቅፅል እንዳልሆነ ያረጋግጣል። ይህ ከሆነ፣ የየጥምሩ ቀኝ ተጣማሪ፣ ማለትም መሪው፣ ስማዊ ባህሪ አለው ማለት ነው። ይህም ባህሪ ከተጣማሪው ቅርፅ ላይ ላይሆን፣ ከትርጉሙ የሚሰርፅ ነው። ቅርፁ፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የቀዳማይ እንቀፅ ነው። ይህ ከሆነ፣ አንድ ቃል በቅርፅ ግላዊ ሆኖ በትርጉም ስማዊ ሊሆን ይችላል፣ ማለት ነው። ለዚህ ሁኔታ ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆኑን እንደ <u>ደረሰኝ</u> እና፣ ምናልባትም፣ እንደ <u>ገጠመኝ</u> ያሉ ቃላት ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት በቅርፃቸው ግሶች ሲሆኑ፣ በትርጉማቸው ግን ስሞች ናቸው። ይህን ከሚከተሉት መረዳት ይቻላል።

—

(ሀ) ካሳ <u>ደረሰኝ</u> ተቀብሎአል 23
(ለ) አስቴር ብዙ <u>ገጠመኝ</u> አላት

ከምሳሌዎቹ መረዳት የሚቻለው፣ ቃላቱ በአገባባቸውም ሆነ በትርጉማቸው ስማዊ መሆናቸውን ነው። አንደ <u>ሰርቶ አደር</u> ያሉ ጥምሮች ስማዊነትም ከዚሁ አንፃር ሊታይ ይችላል። በቅርፃቸው ግሳዊ፣ በአገባባቸውና በትርጉማቸው ስማዊ ናቸው።

አንደ <u>ሰርቶ አደር</u> ባሉ ጥምሮች ውስጥ ከመጀመሪያው ተጣማሪ ላይ ተቀጥሎ የሚገኘው /-አ/ አጣማሪ ምዕላድ ነው፣ ለማለት ይቻላል። አገባቡ ግን እንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ባሉ ጥምሮች ውስጥ ከሚገኘው አጣማሪ፣ ማለትም ከ/-ኛ/፣ የተለየ ነው። የዚህ አጣማሪ አገባብ ከመሪው ጋር ሲሆን፣ የ/-አ/ ግን ከገላጩ ጋር ነው። ይህ አገባብ ቀደም ሲል እንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ያሉ ጥምሮችን አስመልክተን፣ ስለ መሪ ባህሪ ከለጠነው አስተያየት ጋር ይጋጫል። ምክንያቱም ያኔ የአንድ ጥምር መሪ፣ አጣማሪው ምዕላድ የሚገኝበት፣ ማለትም የሚያርፍበት ተጣማሪ ነው፣ ብለን ነበር። እሱን ከተከተልን፣ እንደ <u>ሰርቶ አደር</u> ያሉ ጥምሮች መሪ <u>ሰርቶ</u> የሚለው ተጣማሪ መሆን አለበት። ምክንያቱም አጣማሪው ምዕላድ /-አ/ የሚገኘው ከእሱ ጋር ነውና። ይህ ግን ትክክል አይደለም። <u>ሰርቶ</u> ገላጭ እንጅ መሪ እንዳልሆነ ቀደም ሲል አይተናል። ሁኔታው አንድን መሪ በአጣማሪው አገባብ ብቻ፣ ሁል ጊዜ በትክክል መለየት እንደማይቻል ያመለክታል።

ምናልባት፣ ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ይኸውም /-አ/ አጣማሪ ሳይሆን፣ መደብ አመልካች ምዕላድ ሊሆን አይችልም ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው ተገቢ ነው። ምክንያቱም ቦዝ በሚባሉት አምዶች ላይ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ አመልካች የሆነው ምዕላድ በርግጥም /-አ/ ነው። ስለሆነም፣ አጣማሪ ካልነው /-አ/ ጋር በቅርፁ እንድ ነው። በተግባሩ ግን የተለየ ነው። በጥምሮቹ ውስጥ የሚገኘው /-አ/ መደብ አመልካቹ ሳይሆን፣ ከሳይ እንደተጠቀሰው፣ አጣማሪው /-አ/ ነው። መደብ አመልካቹ ቢሆን ኖሮ፣ እንደየመደቡቹ የተለያየ ቅርፅ ይይዝ ነበር። ለምሳሌ፣ ለአንደኛ መደብ ሰርቼ /ሰኧርት-ይኤ/፣ ለሁለተኛ መደብ ሰርቱህ /ሰኧርት-ኧህ/፣ ወዘተ፣ የሚል ይሆን ነበር። ይህ ከሆነ ደግሞ ቅርፁ የጥምር ሳይሆን፣ የህረግ ይሆናል። ስምሳሌ፣ ስራ ሰርቼ፣ ስራ ስርተህ፣ ወዘተ፣ የሚል አካሄድ ያለው ግሳዊ ህረግ ይሆናል። ጥምር ከሆነ ግን እንደዚህ ያለ ልዩነት አያሳይም። ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑን እንደሚከተሉት ያሉ ጥምር ስሞች ናቸው።

<u>ግስ</u>	<u>ስም</u>	<u>ጥምር</u>	24
ሰርቶ	አዳሪ	ሰርቶ አዳሪ	
ወዶ	ዘማች	ወዶ ዘማች	
ፈጥኖ	ደራሽ	ፈጥኖ ደራሽ	

የአንዚህ ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 5፣



እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች ያለጥርጥር ሰማዊ ናቸው። ምክንያቱም መሪያቸው ስም፣ ከስምም እድራጊ ወይም ሁዋኝ ስም ነው። ስምሳሌ፣ <u>ወዶ ዘማች</u> የሚለው ጥምር መሪ <u>ዘማች</u> የሚለው ቀኝ ተጣማሪ ስም ነው። ይህ ከሆነ <u>ወዶ</u> ከሚለው ገላጭ ተጣማሪ ላይ የሚታየው /-አ/ መደብ አመልካች ሲሆን አይችልም። ምክንያቱም መደብ አመልካች ቅጣዮች ከግሶች ጋር እንጅ ከጥምር ስሞች ጋር ስለማይገኙ ነው። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ወድጂ ዘመትኩ 25
(ለ) *ወድጂ ዘማች

የመጀመሪያው ምሳሌ ግሳዊ ሀረግ ነው። በመሆኑም መደብ አመልካች ቅጣዮችን ሲያላይ ችሎአል። መደብ አመልካቾቹ <u>ወድጂ</u> ላይ የሚታየው /-የ/ እና <u>ዘመትኩ</u> ላይ የሚታየው /-ኩ/ ናቸው። በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ መደብ አመልካቹ /-የ/ ከገላጩ ላይ በመገኘቱ ጥምሩ ተቀባይነትን ሲያጣ ችሎአል። ባንፃሩ ግን እንደ <u>ወዶ ዘማች</u> አይነት ያሉ ጥምሮች ከማንኛውም መደብ ጋር እንደሚከተለው እየሆኑ ሲገቡ ይችላሉ።

(ሀ) አስቴር <u>ወዶ ዘማች</u> ነች 26
(ለ) እኔ <u>ወዶ ዘማች</u> ነኝ
(መ) ልጆቹ <u>ወዶ ዘማች</u> ናቸው

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ወዶ ዘማች</u> የሚለው ከአንስታይ ዖታ ስም ጋር፣ በሁለተኛው ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ጋር፣ እንዲሁም በሰስተኛው ምሳሌ፣ ከሰስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ጋር ገብቶአል። እንደ መደቡ፣ ዖታውና ቁጥሩ <u>ወዶ</u> የሚለው ተጣማሪ ቅርፁን አስወጠም። ይህም /-አ/ የሚለው ምዕላድ አጣማሪ እንጅ መደብ አመልካች እንዳልሆነ ያለ ጥርጥር ያመልክታል።

እስካሁን እንዳየነው ከግዕዝ እንደመጡት፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን ካሉት ጥምሮች በስተቀር፣ የአማርኛ ጥምር ስሞች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል። አይነታቸውም በሶስት የተከፈለ ነው። እንደኛው ልል የሚባሉትን እንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉትን ጥምሮች የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ሁለተኛው አይነት

ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን እና አንደ ሰርቶ አደር ያሉትን ጥብቅ ጥምሮች ሲይዝ፡ ሶስተኛው እንደ ግራማይ ያሉትን ውሁድ ሰሞች ያካትታል።

ጥምር ቅፅሎች

እንደ ሰሞች ሁሉ፡ ቅፅሎችም በጥመራ ሊፈጠሩ ይችላሉ። የሚፈጠሩትም ከቅፅልና ከሰም ነው። ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ሰም	ቅፅል	ጥምር ቅፅል		
እግር	ቀላል	እግር-አ ቀላል	እግረ ቀላል	1
ሽል	ሙቅ	ሽል -አ ሙቅ	ሽለ ሙቅ	
እዴን	መልካም	እዴነ-አ መልካም	እዴነ መልካም	
ጉዋዝ	ብዙ	ጉዋዝ-አ ብዙ	ጉዋዘ ብዙ	
ሆድ	ሰፊ	ሆድ-አ ሰፊ	ሆደ ሰፊ	

ከመዘርዝሩ እንደሚታየው፡ ቅፅሎቹ የተመሰረቱት /-አ/ በሚለው አጣማሪ ምዕላድ አማካኝነት ነው። ይህን ምዕላድ ጥምር ሰሞችንም ሲያጣምር ባለፈው ንዑስ ክፍል አይተነዋል። አሁን ደግሞ ለምን ከቅፅል እያጣመረ፣ ጥምር ቅፅል ሊመሰርት ይታያል። የሁለቱም ክፍሎች አጣማሪ ነው፡ ለማለት ይቻላል። እነባቡ፣ ቀደም ሲል በጥምር ሰሞች ላይ እንዳየነው፣ ከመሪው ጋር ሳይሆን፣ ከገላጩ ጋር ነው። ጥምሩም ቀኝ መሪ ነው። ለምሳሌ፡ እገረ ቀላል የሚለውን ጥምር ብንመለከት፣ መሪው ቀላል የሚለው ቅፅል ሲሆን፣ ገላጩ እግር የሚለው ሰም ነው። አገላለፁም ቅሰቱ የራሰ፣ ወይም የለውነት ሳይሆን፣ የእግር ብቻ መሆኑን በማሳየት ነው። የጥምሩ ትርጉም ፈጣን ማለት ነው። ፈጣን ቅፅል ሰለሆነ፡ የእሱ ትርጉም እቻ የሆነው ጥምርም እንደዚሁ ቅፅል ነው። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

2
(ሀ) ካሳ በጣም ፈጣን ልጅ ነው
(ለ) ካሳ በጣም እገረ ቀላል ልጅ ነው

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ ፈጣን የሚለው ቅፅል በገባበት ቦታ፣ በሁሰተኛው ምሳሌ እገረ ቀላል የሚለው ጥምር ቅፅል ሊገባ ችሎአል። ይህ እይነተኛ የቅፅል አገባባዊ ባህሪ ነው። የአጠማመሩን ሰርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

ሰርዓት 1፣

[ሰም] + [-አ] + [ቅፅል] ⟶ [ቅፅል]$_{\text{ጥምር}}$

በዚሁ አካሂድ ሌሉች ጥምር ቅፅሎችን እየፈጠሩ ለተለያየ ፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ማዋል ይቻላል። ለምሳሌ፡ ልበ ጥፉ፣ እይነ ክፉ፣ ህሳበ ቀና፣ ራሰ ቀላል፣ እግረ

ከባድ፣ አፈ ሰፊ፣ ወዘተ፣ ማለት ይቻላል። ሊሂድ የማይሰልጠውን (የማይፈጥነውን) እግረ ከባድ ልንለው እንችላለን። ይህም የእግረ ቀላል ተቃራኒ መሆኑ ነው።

የአንዳንድ ጥምሮች ትርጉም የተጣማሪዎቹ ትርጉም ድምር ውጤት ነው። ለምሳሌ፣ አይነ መልካም የሚለው ጥምር ትርጉም መልካም አይን ያለው ማለት ነው። ራሰ ቀላል የሚለው ግን፣ ቀላል ራስ ሳይሆን፣ ትንሽ ዕውቀት ያለው ማለት ሊሆን ይችላል። አፈ ሰፊ የሚለውም ለፍላፊ እንጅ፣ አፉ የሰፋ ማለት አይደለም። በዚህ አይነት ከተጣማሪዎቹ ጥሬ ትርጉም የተለየ ትርጉም ያላቸው ቃላት ወደ ውሁድነት የተጠጉ ጥብቅ ጥምሮች ናቸው። ትርጉማቸው ከተመሰረቱበት ቃላት ተናጠል ትርጉም የተለየ ነውና።

የብዙዎቹ ጥምሮች መሪ ከጥምሩ የቃል ከፍልም ሆነ ከአገባቡ ሊለይ ይችላል። ለምሳሌ፣ እግረ ቀላል የሚለውን ብንመለከት፣ መሪው ቀላል የሚለው ቅፅል ሲሆን፣ አገባቡም ገላጩን ተከትሎ ነው። ስለሆነም ጥምሩ ቀኝ መሪ ነው። በአንዳንድ ጥምሮች ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ግን እንደዚህ ግልፅ አይደለም። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት።

ስም	ቅፅል	ጥምር	
ገድ	ቢስ	ገድ-አ ቢስ	3
ልብ	ቢስ	ልብ-አ ቢስ	
ሆድ	ባሻ	ሆድ-አ ባሻ	

የእነዚህ ጥምሮች መሪ ሁለተኛው ተጣማሪ ነው ለማለት ይቻል ይሆናል። ይህ ግን ከተጣማሪው ቅርፅ ወይም አገባብ ሳይሆን፣ ከጥምሩ ትርጉም ስንነሳ የምንገነዘበው ነው። በርግጥ አጣማሪው ምዕላድ /-አ/ የሚገኘው ከመጀመሪው ተጣማሪ ጋር ነው። ይህ ተጣማሪ ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ሙሉ ጥምሩን ያለመሰረታዊ የትርጉም ለውጥ እየተካ ሊገባ አይችልም። ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ገደ ቢስ ሰው ነው 4

ቢሚለው ውስጥ፣ ገደ ቢስ የሚለውን፣ ገድ የሚለው ተጣማሪ ሊተካው አይችልም። ምክንያቱም፣

(ለ) ካሳ ገድ ሰው ነው

ብንል፣ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም ይለወጣል። እንደዚሁም፣

(መ) *ካሳ ቢስ ሰው ነው

ብንል፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያጣል። ይህ ከሆነ፣ ግንኛቸውም ተጣማሪዎች የጥምሩ መሪ አይደሉም፣ ለማለት ነው። አጣማሪ ምዕላድ ያስከተለ ተጣማሪ ሁሉ መሪ ሳይሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል።

ከጥምሩ ትርጉም አኩዋያ ስንመልከት ግን፣ <u>ቢስ</u> የሚለውን ተጣማሪ የጥምሩ መሪ ልናደርገው እንችላለን። ምክንያቱም የጥምሩ ትርጉም <u>ገድ</u> (ዕድል) የሌለው የሚል ነው። ልበ-ቢስ ስንልም፣ ልብ የሌለው ማለታችን ነው። ትርጉሙ ከእጠት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ ይህን ሀሳብ የሚገልፀውን ተጣማሪ የጥምሩ መሪ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ይህ ተጣማሪም፣ እስካሁን እንዳየናቸው ሌሎች ጥምሮች መሪ፣ የጥምሩ የቀኝ አካል ነው።

ከቃሉ ቅርፅ መሪነቱን ለማወቅ የማይቻልበት ምክንያት ቃሉ የርባታም ቋነ የምለረታ ምዕላድ የማያስከትልና ብቻውንም ለመቆም የማይችል በመሆኑ ነው። ስለዚህም የቃላት ከፍሉን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ትርጉሙ አሉታዊ ስለሆነ፣ ከዚሁ በመነሳት፣ <u>ቢስ</u> የአሉታ ምዕላድ ነው፣ ለማለት እንችላለን። አሉታዊነት ደግሞ ከቃል ክፍል ጋር ሳይሆን፣ ከሀረግና ከአረፍተ ነገር ተግባር ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው። ወደፊት እናየዋለን።

ቀደም ሲል እንዳየናቸው ጥምሮች ሁሉ፣ በእነዚህም ውስጥ አጣማሪው /-ኧ/ የሚገኘው ከገላጩ ተጣማሪ ጋር ነው። ይህም ቀደም ሲል፣ ይህን አጣማሪ ምዕላድ ያስከተለ ተጣማሪ ሁሉ፣ መሪ እንዳልሆነ ያስገነዘብነውን ያጠናክራል። ምናልባትም፣ /-ኧ/ የሚገኝበት ተጣማሪ መሪ የሚሆነው አንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ባሉ ግዕዛዊ ጥምሮች ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ባጭሩ በአማርኛው ስርዓት /-ኧ/ የሚያርፍበት ተጣማሪ ገላጭ ሲሆን፣ በግዕዙ ግን ይህ ምዕላድ የሚገኝበት ተጣማሪ፣ መሪ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ጥምር ግሶች

እንደ ስሞችና ቅፅሎች ሁሉ ግሶችም በጥመራ ይፈጠራሉ። ይሁን እንጅ አፈጣጠራቸው ውሱን ነው። ይህም በሁለት በኩል ነው። በአንድ በኩል፣ ከተጣማሪዎቹ አንዱ ቀደም ሲል በአዕማዱ ክፍል እንዳየናቸው እንደ <u>ስብር-</u> [ስአብብእርር-] ያሉ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ አዕማድ በመሆናቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእነዚህ ጋር የሚጣመሩት ግሶች <u>አስ</u> እና <u>አደረገ</u> የሚሉት ብቻ መሆናቸው ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

<u>አምድ</u>	<u>ግስ</u>	<u>ጥምር ግስ</u>	1
ውጥት-	አስ	ውጥት አስ	
ፍርጥ-	አስ	ፍርጥ አስ	
ብድግ-	አስ	ብድግ አስ	
ስብር-	አስ	ስብር አስ	
እልም-	አስ	እልም አስ	
ብልጭ-	አስ	ብልጭ አስ	

ስርዓተ-ፍጥረታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 1፣

[1-22-33-] + አል- [1እ22እ33 አል-]
አምድ አምድ አጠንካሪ

እምዱ ሙሉ ቃል ስላልሆነ የጥምሩ ከፍል በውል የሚታወቅ አይመስልም። ከግስ ጋር ተጣምሮ ግስ እንደሚመሰርት ሁሉ፣ ከቅጣይ ምዕላድ ጋርም ስምን ሊመስርት ይችላል። እንደ ብልጭ-ታ፣ ስርቅ-ታ፣ እሽ-ታ፣ ወዘተ፣ በዚህ አይነት የሚመስረቱ ስሞች ናቸው።

የጥምሩ መሪ አለ የሚለው ግስ ነው። እንደ ብልጭ [ብእልልእጭጭ-] ያሉ ቃላት አንደ ግስ ወይም እንደ ስም ወይም ቅፅል ራሳቸውን ችለው አይገኙም። የርባታ ስርዓትም የላቸውም። ስምሳሌ፡ ብልጭ የሚለውን ብንወስድ፣ እንደ መደበኛ ግስ፣ ስምሳሌ፡ እንደ ሰበረ፣ መደብን፣ ቁጥርን ወይም ፆታን አያሳይም። ስለዚህም ይለበር፣ ሰብሮ፣ ስበር፣ ወዘተ፣ እንደምንል ሁሉ፣ ይብለጭ፣ በልጮ፣ ወዘተ፣ ማለት አይቻልም። በዚህም ምክንያት እንደ ብልጭ ያሉትን አይረቢ ቃላት አንደ ሰበረ ካሉት ረቢ ቃላት መለየት ያስፈልጋል። እንደ ሰበረ ያሉትን ለርባታ የደረሱ በመሆናቸው አቢይ ቃላት ልንላቸው እንችላለን። እንደ ብልጭ- ያሉትን ደግሞ ለርባታ ያልደረሱ በመሆናቸው ንዑስ ቃላት ልንላቸው እንችላለን። ንዑስም በመሆናቸው ራሳቸውን ችለው አይቆሙም።

ንዑስ ቃላት ራሳቸውን ችለው ስለማይቆሙና ስለማይረቡም፣ ራሳቸውን ችለው ከሚቆሙና ከሚረቡ አቢይ ቃላት ጋር እየተጣመሩ አቢይ ውልድ ቃላትን ሊመሰርቱ ይችላሉ። በዚህ መሰረት ፀጥ የሚለው ንዑስ ቃል አለ ከሚለው አቢይ ግስ ጋር በመጣመሩ ፀጥ አለ፣ የሚል ጥምር ግስ ሊፈጠር ችሎአል። ይህ ግስ አንደ ማንኛውም አቢይ ግስ ፀጥ ይላል፣ ፀጥ ይበል፣ ፀጥ ብሎ፣ ፀጥ በል፣ ወዘተ፣ እያለ ይረባል። የርባታ ምዕላዶቹ የሚታዩት ግን በመሪው ላይ ነው። ስምሳሌ፣ ፀጥ ይበል በሚለው ጥምር፣ የሶስተኛ መደብ ምዕላዱ /ይ-/ የሚገኘው በግሱ፣ ማለትም በመሪው፣ ላይ ነው። ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በጥምር ቅፅሎችና ስሞች ላይም ታይቶአል። አሁንም በግሶች ላይ መታየቱ፣ ቅጣይ ምዕላዶችን መያዝ አጠቃላይ የመሪ ባህሪ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል።

አለ በሚለው ግስ አማካኝነት የሚፈጠሩ ግሶች ምድብ ከኢሳቢዎች ጋር ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ኢሳቢ ግሶች ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አይፈልጉም። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ፀጥ አለ 2
(ለ) *ካሳ አንበሳ ፀጥ አለ

ሁለተኛው ምሳሌ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህም ምክንያቱ ግሱ ከስም ጋር መግባቱ ነው። ከስም ጋር ሊዝቡ የሚችሉት አደረገ ከሚለው ግስ ጋር የሚፈጠሩ ጥምር ግሶች ናቸው። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

አምድ	ግሰ	ጥምር ግሰ
ፀጥ	አደረገ	ፀጥ አደረገ
ቀና	አደረገ	ቀና አደረገ
ሳብ	እደረገ	ሳብ አደረገ
ብቅ	አደረገ	ብቅ አደረገ

3

የየጥምሩ መሪ <u>እደረገ</u> የሚሰው ተጣማሪ ነው። የሚገኘውም በስተቀኝ በኩል ሰለሆነ፣ ጥምሮቹ ቀኝ መሪ ናቸው። ከዚህ አቀማመጥ አንፃር ሲታዩ፣ እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች፣ ከፍ ሲል ካየናቸው እንደ <u>ፀጥ አለ</u> ካሉት የተሰየ አይደሉም። እነዚህ ከነዚያ የሚሰዩት በሰዋሰዋዊ ባህሪያቸው ብቻ ነው። ይኸውም ተሳቢ ሰማዊ ሀረግ የግድ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው። ይህን ከሚከተሉት ምሰሌዎች መረዳት ይቻሳል።

(ሀ) ካሳ [አስቴርን] ቀና እደረጋት 4
(ለ) አስቴር [ልጁን] ሳብ አደረገችው

በሁለቱም ምሳሌዎች፣ ጥምሮቹ ግሶች በቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት ተሳቢ ሰሞች ጋር ገብተዋል። ይህም እይነተኛ የሳቢ ግሶች ባህሪ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል። ሳቢ ያደረጋቸው <u>አደረገ</u> የሚሰው መሪ ተጣማሪ ራሱ ሳቢ በመሆኑ ነው። መሪው ሳቢ ከሆነ፣ ጥምሩም ሳቢ ይሆናል ማስት ነው። ይህን ከፍ ሲል <u>አለ</u> ከሚሰው ኢሳቢ ግስ ጋር ከሚጣመሩት ግሶች ባህሪም እይተናል። ይህ ግስ ኢሳቢ በመሆኑ፣ በእሱ መሪነት የሚፈጠሩ ጥምሮችም በሙሉ ኢሳቢ ሰመሆን ችለዋል። ይህም የጥምሮቹ ባህሪ በመሪዎቹ ባህሪ እንደሚወሰን ያስገነዝበናል።

እንደ <u>ሰብር</u> ያሉ አጠንካሪ አዕማድ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በመድገም ደጋጋሚ ድርጊትን ያመለክታሉ። ይህም ሲሆን እንደሚከተሉት ያሉ አዕማድን እናገኛለን።

አምድ	ደጋጋሚ	ጥምር 5
[ሰእብብእር]	[ሰእብብእር- ሰእብብእር]	[[ሰእብብእር-ሰእብብእር] አለ/አደረገ]
[ክእፍፍእት]	[ክእፍፍእት- ክእፍፍእት]	[[ክእፍፍእት- ክእፍፍእት] አለ/አደረገ]
[ውእድድእት]	[ውእድድእት- ውእድድእት]	[[ውእድድእት-ውእድድእት]አለ/አደረገ]

ሰርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያለን፣

ሰርዓት 2፣

/1-2-3-/ ⟶ [1እ22እ3-1እ22እ3- + አለ/አደረገ]
ደጋግ

ደጋጋሚው አምድ የየስሩን ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ በማጥበቅና አምዱን ሙሉ በሙሉ በመድገም ይመስረታል። ከዚያም <u>አለ/አደረገ</u> ከሚለው ግስ ጋር ይቀናጅና ጥምር ይሆናል።

አጠንካሪ አዕማድ የሚባሉት የየስሩን የመጨረሻ ሁለት ሁለት አግሮች ይደጋግሙና የመጨረሻውን ብቻ ያጠብቃሉ። ሁለቱን ተናባቢዎች የተፈለገውን ያህል በመድገም ስብርብርብርብርብር..... እያሉ መቀጠል ይቻላል። የድግግሞሹ መጠን ለመግለፅ የተፈለገውን ሀሳብ የጥንካሬ ደረጃ ሊያመለክት ይችላል። ስለዚህም ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድ አደረገው 6
(ለ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድድ አደረገው
(መ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድድድድድድድድ አደረገው

ብንል፣ የአቀዳደዱ የጥንካሬ፣ ምናልባትም ፍጥነትና የሰውየው የልህ መጠን የተለያየ መሆኑን እንረዳለን። የሚከተሉትን አዕማድ ደግሞ እንመለከት።

<u>ስር</u>	<u>ድርብ ስር</u>	<u>አጠንካሪ</u> 7
/ስ-ብ-ር-/	/ስ-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ርር.../	[ሰእብእርብእርብእርር...]
/ግ-ል-ብ-ጥ-/	/ግ-ል-ብ-ጥ-ብ-ጥ-ብ-ጥጥ..../	[ግእልብእጥብእጥብእጥጥ....]
/ው-ል-ቅ-/	/ው-ል-ቅ-ል-ቅ-ል-ቀ-ል-ቅቅ.../	[ውእልእቅልእቅልእቅልእቅቅ...]

ስርዓቱ እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 3፣

<u>ስር</u>	<u>አምድ</u>	<u>አጠንካሪ</u>
/1-2-3-/	/1-2-3-2-3-2-33.../	[1እ2እ3ልእ2እ32እ33...]
/ስ-ብ-ር/	/ስ-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ርር./	ስእብእርብእርብእርር...]

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ እንደነዚህ ያሉ አዕማድ የሚፈጠሩት የግሱን መድረሻና ቅድመ መድረሻ ተናባቢዎች በመደጋገም ስለሆነ፣ ድግግሞሹ ከፊል ነው። በነዚህና ከፍ ሲል በተመለከትናቸው ደጋጋሚ አምዶች መካከል ያለው ልዩነትም በድርጊቱ የድግግሞሽ መጠን ላይ ነው። ከፍ ሲል ያየናቸው፣ ድርጊቱ እየተቁዋረጠና አንደገና እየተጀመረ መቀጠሉን ያመለክታሉ። በነዚህኞቹ የሚገለፀውን የድግግሞሽ መጠን በቁጥር ለመግለፅና በእህዝ ለመወሰን ያስቸግራል። ተናጋሪው ስለ ድርጊቱ ያለው ስሜት እስኪበርድ ድረስ የሚቀጥል ስለሆነ፣ መጠኑን መወሰን የሚቻል አይመስልም። ስምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድ አደረገው 8
(ለ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድ ቅድድ አደረገው

ብንል፣ ከመጀመሪያው ይልቅ በሁለተኛው አረፍተ ነገር የተገለፀውን ተግባር የድግግሞሽ መጠን መወሰን የሚቻል ይመስላል። ሂደቱ ቀጣይ ሳይሆን፣ እየተበጠሰና እየተቀጠለ የተፈፀመ ስለሆነ፣ ይህን ያህል ጊዜ ተፈፀመ ለማለት ይቻላል።

እንደ ሰብር ሰብር ያሉ አዕማድ አለ ወይም አደረገ ከሚለው ግስ ጋር ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ጥምር ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ሰብር ሰብር የሚለው ደጋጋሚ ቅርፅ ራሱ እንደ አንድ ጥምር ስለሚቆጠርና አለ ወይም አደረገ ከሚለው ግስ ጋር ሲቀናጅ የጥምረቱ ደረጃ ከፍ ስለሚል ነው። አጠማመሩን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስርዓት 4፣

(ሀ) [ሰብር] (አምድ) ⟶ [ሰብር ሰብር] (ሙሉ ደጋጋሚ)

(ለ) [ሰብር ሰብር] (ደጋጋሚ አምድ) + [አለ] (ግስ) ⟶ [ሰብር ሰብር አለ] (ውስብስብ ደጋጋሚ ጥምር)

እንደ [ሰብር ሰብር አለ] ያሉ ግሶች የአንድን ድርጊት ተደጋጋሚነት ያመለክታሉ። ከዚህ የተለየ ድርጊትን የሚያመለክቱ ጥምሮችም አሉ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ያዝ ለቀቅ 9
ከፍ ዝቅ
ሳብ ረገብ
ብቅ ጥልቅ
ወጣ ገባ
ፈራ ተባ

እንደነዚህ ያሉ ጥምር አዕማድ ናቸው። ተጣማሪዎቹ ተቃራኒ ድርጊትን ወይም ይዘትን ያመለክታሉ። የተጣማሪዎቹ የቃል ከፍል ስለማይታወቅ፣ የጥምሩ ከፍልም ሆነ መሪው በትክክል አይታወቅም። ርግጥ፣ አስካሁን ያየናቸው ተጣማሪዎች በአብዛኛው ቀኝ መሪ ስለሆኑ፣ የነዚህም መሪ በስተቀኝ በኩል ያለው ተጣማሪ ነው፣ ለማለት ይቻላል። እነዚህን ጥምር አዕማድ ከፍ ሲል

በተመለከትነው ሁኔታ <u>አለ</u> ወይም <u>አደረገ</u> ከሚለው ግስ ጋር አያጣመሩ ውስብስብ ጥምር ግሶችን አንደሚከተለው መመሰረት ይቻላል፡፡

ስርዓት 5፣

(ሀ) [[[ተኽተኣ] + [ተኽተኣ]] +አለ] ⟶ [አምድ-አምድ አለ]
አምድ 1 አምድ 1/2 ውስብስብ ጥምር

(ለ) [[[ተእተተ] + [ተእተተ / ተእተተ]] +አለ] ⟶ [አምድ-አምድ አለ]
አምድ 1 አምድ 1/2 ውስብስብ ጥምር

(መ) [[[ተእተተ] + [ተኽተኽተተ]] +አደረገ] ⟶ [አምድ-አምድ አደረገ]
አምድ 1 አምድ 1/2 ውስብስብ ጥምር

የተጣማሪዎቹ አዕማድ ውስጣዊ አቀነጃጀት አንድ ወጥ አይደለም፡፡ በ(ሀ) ውስጥ አንደ <u>ፈራ ተባ</u>፣ በ(ለ) ውስጥ እንደ <u>ብቅ ጥልቅ</u> አንዲሁም በ(መ) ውስጥ እንደ <u>ሳብ ረገብ</u> ያሉት ይገኛሉ፡፡ ሁሉም ተቃራኒ ወይም ደጋጋሚ ድርጊትን ወይም ይዘትን ያመለክታሉ፡፡ ጥምሮቹም አንደዚሁ አንድ ድርጊት በሙሉ ልብና በቁርጠኝነት ወይም በወላዋይነት መፈፀሙን ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ ፈራ ተባ አያለ ወደ ቤት ገባ 10

ስንል፣ ካሳ በልበ - ሙሉነት ሳይሆን በወላዋይነት ቤት ውስጥ አንደገባ አንገነዘባለን፡፡ በሙሉ ልብ የሚፈፀም ድርጊትን ለማመልከት ጥምሩ በደጋጋሚ አዕማድ ሳይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ አካሂድ፣

(ሀ) ካሳ ወደ ቤት <u>ገባ ገባ</u> አለ 11
(ለ) ካሳ ወደ ደጅ <u>ወጣ ወጣ</u> አለ

ማለት ይቻላል፡፡

አስካሁን ሁለት አይነት ጥምር ግሶችን አይተናል፡፡ አነሱም ከተራና ከጥምር አዕማድ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ተግባራቸው የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ማመልከት ነው፡፡ አፈፃፀሙ፣ ደጋጋሚ፣ አጠንካሪ፣ አለሳላሽ (ወላዋይ) ወይም ቁርጠኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ድርጊትን ብቻ ሳይሆን፣ አፈፃፀምንም ጨምረው ስለሚገልፁ በከፍላቸው ግሳዊ፣ በተግባራቸው ተውሳከ ግሳዊ ናቸው፡፡ ስለዚህም ተውሳከ ግሳዊ ጥምር ግሶች ሊባሉ ይችላሉ[2]፡፡

[2] ይህን ጉዳይ በተመለከተ መንግሉቱ አንበርብር (1998)ን፣ ባየ (1999)ን ይመልከቱ፡፡

ጥምር ተውሳከ ግሶች

ተውሳከ ግስ የሚባለው ከፍል በርካታ ተራ ቃላት እንደሌሉት ቀደም ባለው ክፍል ደጋግመን ገልፀናል። ተራ ቃላት ከሌሉት ጥምር ቃላት ይኖሩታል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። ይሁን እንጅ በድግግሞሽ የሚፈጠሩ ጥቂት ተውሳከ ግላዊ ቃላት ስላሉ፣ እነሱን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። የሚከተሉት ለዚህ አብነት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

ጥቂት ጥቂት 1
ትንሽ ትንሽ

ትንሽና ጥቂት የሚሉት ቃላት በመለረቱ ቅፅሎች ናቸው። በቅፅልነታቸው እንደ ማንኛውም ቅፅል በገላጭነት ከስም በፊት እንደሚከተለው እየሆኑ ይገባሉ።

(ሀ) በጣም ጥቂት እህል 2
(ለ) በጣም ትንሽ ልጅ

እነዚሁ ቃላት ከፍ ሲል ባስቀመጥነው ድግግሞሽ መልክ ሲመጡ ደግሞ፣ እንደ ተውሳከ ግሰ ይገባሉ። ለዚህ የሚከተሉትን ምላሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ትንሽ ትንሽ [እንጀራ ይበላል] 3
(ለ) ጥቂት ጥቂት [ውሀ ይጠጣል]

በነዚህ ምላሌዎች ውስጥ፣ <u>ትንሽ ትንሽ</u> እና <u>ጥቂት ጥቂት</u> በየግሶቹ የተገለፀውን ተግባር አነስተኛነት ስለሚያመለክቱ፣ የመጠን ተውሳከ ግሰ ሊባሉ ይችላሉ። የሚያመለክቱት የተበላውን ወይም የተጠጣውን ነገር መጠን ሳይሆን፣ የአበላሉን ወይም የአጠጣጡን ደካማነት ነው። ገላጭነታቸውም ለዚሁ ተግባር መሆኑን ከሚከተለው ምላሌ ይበልጥ መረዳት ይቻላል።

ትንሽ ትንሽ [ለህፃራችን እንሙት] 4

በዚህ ምላሌ <u>ትንሽ ትንሽ</u> የሚለው ደጋጋሚ ቃል የሚገልፀው ሌላ ነገርን ሳይሆን፣ ለህገር የመሞትን፣ ግለትም መለዋዕት የመክፈልን ተግባር ነው። ገላጭነታቸው በቅንፍ ውስጥ ለተመለከተው ግላዊ ሀረግ ነው።

እንደ ቅፅሎች ሁሉ <u>ቶሎ</u> የሚለው ተራ ተውሳከ ግስም በድግግሞሽ መልክ ሲገባ፣ የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ወይም መጠን ሊያመለክት ይችላል። የሚከተሉትን እናነፃፅር።

(ሀ) ካሳ ቶሎ መጣ 5
(ለ) ካሳ ቶሎ ቶሎ ዘመዶቹን ይጠይቃል

በመጀመሪያው ምሳሌ ቶሎ የሚለው ተውሳከ ግስ፣ መጣ በሚለው ግስ የተገለፀው ድርጊት የሚወስደው ጊዜ አነስተኛ መሆኑን ሲያመለክት፣ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ ቶሎ ቶሎ የሚለው ደጋጋሚ ጥምር፣ ካሳ ዘመዶቹን ለመጠየቅ የሚያደርገውን ምልልስ ያሳያል። የመጀመሪያው የጊዜ ተውሳከ ግስ ሲሆን፣ ሁለተኛው የመጠን ተውሳከ ግስ ነው። ድርጊቱ ምን ያህል ተደጋጋሚ እንደሆነ ይገልፃልና። ሁኔታው ቀደም ሲል ካየናቸው ደጋጋሚ እዕማድ ጋር ተመሳሳይ ነው።

የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ለማመልከት መሰተዋድዳዊ ሀረጎችን እንደምንጠቀም፣ ስለ ቃላት ከፍሉች ስንወያይ ገልፀን ነበር። ይሁን እንጅ፣ ይህንኑ ሁኔታ ተውሳከ ግስ ሊባሉ በሚችሉ ጥምር መሰል ቃላትም መግለፅ ይቻላል። ቃላቱም እንደ፣

ቀስበቀስ 6
ጥቂት በጥቂት
ትንሽ በትንሽ

ያሉ ሲሆኑ፣ አነባባቸውም እንደሚከተለው ነው።

ሰዎቹ ቀስበቀስ ከቤት ወጡ 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ቀስበቀስ የሚለው እህድ የሰዎቹን የአወጣጥ ሁኔታ ስለሚያመለክት፣ የሁኔታ ተውሳከ ግስ ነው። ውስጣዊ ቅርፁን ስንመለከት የቀስ እና ቀስ ጥምር ይመስላል። በጥምሩ መካከል የሚገኘው /-በ-/ ሁለቱን ንዑስ ቃላት የሚያጣምር ምዕላድ ይመስላል። አጣማሪ መሰተዋድድ ልንለው እንችላለን።

ከዚህ ሁኔታ ቀስበቀስ የሚለው ጥምር በቀስታ የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ተውሳከ ግሳዊ እቻ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ለዚህ አባባላችን ማስረጃ የሚሆኑ ተጨማሪ አቻ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ፣

(ሀ) በመኪና ተጉዋዘ 8
(ለ) ወደ ጎንደር ተጉዋዘ

በሚሉት ግሳዊ ሀረጎች ውስጥ፣ በመኪና እና ወደ ጎንደር የሚሉት መሰተዋድዳዊ ሀረጎች ተጉዋዘ የሚለውን ግስ ይገልፃሉ። የነዚህ መሰተዋድዳዊ ሀረጎች ስማዊ

አቻዎች ደግሞ <u>የመኪና</u> እና <u>የጎንደር</u> የሚሉት ሲሆኑ፣ እገባባቸውም ስምን በመግለፅ፣

(ሀ) የመኪና ጉዞ 9
(ለ) የጎንደር ጉዞ

የሚል ይሆናል። ከዚህ እካሄድ በግሳዊ ሀረግ ውሰጥ የሚገቡ መሰተዋድዳዊ ሀረጎች በስማዊ ሀረግ ውሰጥ ስማዊ አቻ አንዳላቸው መረዳት ይቻላል። በመሰተዋድዳዊ ሀረጉ ውሰጥ /ሀ/ የነበረው መሰተዋድድም በስማዊ ሀረጉ ውሰጥ /የ/ እየሆነ አንደሚገባ ቀደም ባለው ክፍልም ገልፀናል።

በተመሳሳይ ሁኔታ <u>ቀሰበቀሰ</u> የሚለው <u>በቀሰታ በቀሰታ</u> የሚለው ድርብ መሰተዋድዳዊ ሀረግ ጥምር ተውሳክ ግሳዊ እቻ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ስማዊ አቻው <u>የቀሰታ የቀሰታ</u> ነው። የሶስቱን ክፍሎች የእቻነት ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን፣

መሰተዋድዳዊ ሀረግ : በቀሰታ በቀሰታ
ስማዊ ሀረግ : የቀሰታ የቀሰታ
ተውሳክ ግሳዊ ጥምር : ቀሰበቀሰ

በሌላ በኩል /በ-/ መሰተዋድድ ለለሆነ፣ <u>ቀሰበቀሰ</u> የሚለው ጥምር ቃል ሳይሆን፣ መሰተዋድዳዊ ሀረግ ነው ለማለት ይቻል ይሆናል። ይህ አመለካከት ግን ትንሽ ችግር አለበት። ምክንያቱም መሰተዋድዳዊ ሀረግ የሚመሰረተው፣ ወደፊት በስፊው እንደምናየው፣ ከመሰተዋድድና ከስማዊ ሀረግ ሰለሆነ ነው። ከዚህ አንፃር ቀሰ የሚለው ቃል ሰም ነው ለማለት እንቸገራለን። ቃሉ ቀደም ሲል እንደጠቀሰናቸው አንደ ዝም፣ ፀጥ፣ ብቅ፣ መዘተ፣ ያለ ንዑስ ቃል ነው። ስለሆነም የቃል ክፍሉ በውል አይታወቅም። ይሁን እንጅ፣ እንደ ሌሎች ንዑስ ቃላት <u>አለ</u> ከሚለው ግሰ ጋር እየተቀናጀ ጥምር ግሰን ይፈጥራል። ቅንጅቱ ጥምር ለመሆኑም ተጨማሪ ማሰረጃ አለ። ይኸውም እንደማንኛውም ጥምር ቃል ባዕድ ምዕላድ በመካከሉ ለማለገባት አለመቻሉ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እናነፃፅር፣

(ሀ) በጣም ቀሰበቀሰ 10
(ለ) *ቀሰ በጣም በቀሰ

የመጀመሪያው ምሳሌ ተቀባይነት ሲኖረው፣ ሁለተኛው የለውም። በሁለቱ መካከል ያለው የቅርፅ ልዩነት <u>በጣም</u> የሚለው መጣኝ መሰተዓምር በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ መገኘቱ ነው። አንድ ቅንጅት ጥምር ቃል ከሆነ፣ በዚህ ንዑስ ክፍል መጀመሪያ ላይ እንደተገለፀው፣ በመካከሉ ምንም ነገር

ማስገባት አይችልም። የሁለተኛው ምሳሌ ተቀባይነት ማጣት ከመስተዓምሩ ጣልቃ ገብነት የተነሳ ነው፡ ለማለት ይቻላል።

እንደ <u>ትንሽ በትንሽ</u> ያሉ ቃላት አመሰራረትም አንደዚሁ ተውሳክ ግሳዊ ነው። ቀደም ሲል አንደገለፅነው እንደ <u>ትንሽ</u> እና <u>ጥቂት</u> ያሉ ቃላት አገባብ ተውሳክ ግሳዊ ነው። ራሳቸውን ሲደጋግሙም ሆነ በአጣማሪ አማካኝነት ጥምር ቃል ሲሆኑ የሚገልፁት ተውሳክ ግሳዊ ባህሪን ነው። ለዚህ የሚከተሉትን አንመልከት።

(ሀ) ትንሽ ትንሽ ይበላል 11
(ለ) ትንሽ በትንሽ ሰራውን ጨረሰ

በተግባር ሁለቱም የሚያመለክቱት የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ነው። በቅርፅ ግን የመጀመሪያው በድግግሞሽ ሁለተኛው በጥመራ የተፈጠሩ ስለሆኑ ይለያያሉ። ሁለቱም ተውሳክ ግሳዊ ናቸው።

አሰካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል ያየናቸውን ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡ ጉዳዮቹ ጥምር ሰሞችን፣ ግሶችን፣ ቅፅሎችንና ተውሳክ ግሶችን የሚመለከቱ ናቸው። ጥምር ሰሞች ከሰም እና ከሰም፣ እንዲሁም ከሰምና ከግስ ሲፈጠሩ ይችላሉ። አፈጣጠራቸው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው የግዕዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው የአማርኛ ነው። በግዕዙ መንገድ የሚፈጠሩት ግራ መሪ ሲሆኑ፣ በአማርኛው መንገድ የሚፈጠሩት ቀኝ መሪ ናቸው። ጥምሮቹም ልል፣ ጥብቅ እና ውሁድ ተብለው በሶስት ደረጃ ሊሰዩ ይችላሉ። ልል የሚባሉት አጣማሪ ምዕላድ የላቸውም። ጥብቅ የሚባሉት /ኧ/ ወይም /-አ/ የሚል አጣማሪ ምዕላድ አላቸው። በ/ኧ/ የሚጣመሩት ሰማዊ መሰረት ያላቸው ሲሆኑ፣ በ/አ/ የሚጣመሩት ግሳዊ መሰረት ያላቸው ናቸው። ውሁድ የሚባሉት ከጥምርነት ወደ አንድ ቃልነት የተሸጋገሩ ናቸው። ስለዚህም አጣማሪ የላቸውም።

ጥምር ግሶች ከዕስር አዕማድና <u>አለ</u> ወይም <u>አደረገ</u> ከሚሉት ግሶች ይመሰረታሉ። በ<u>አለ</u> አማካኝነት የሚፈጠሩት ኢሳቢ ሲሆኑ፣ በ<u>አደረገ</u> አማካኝነት የሚፈጠሩት ሳቢ ናቸው። ጥምሮቹ ተራ ወይም ድርብ ሲሆኑ ይችላሉ። ድርብ ጥምሮች ተቃራኒ ወይም ደጋጋሚ ድርጊቶችን ያመለክታሉ። ጥምር ግሶች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው።

ጥምር ቅፅሎች ከሰምና ከቅፅል ይመሰረታሉ። እንደ ጥምር ሰሞች ሁሉ፣ ጥምር ቅፅሎችም ቀኝ መሪ ናቸው። አንዳንድ ቅፅሎች በድግግሞሽ ይፈጠራሉ። ተደጋጋሚዎቹ ቃላት /-አ-/ በሚል ምዕላድ ይያያዛሉ። ይህም ከአንዳንድ ጥምር ሰሞች የአጠማመር ሰርዓት ጋር ይመሳሰላል።

ተውሳክ ግሶች በድግግሞሽና በጥመራ ይመሰረታሉ። አጣማሪው <u>በ</u> ወይም <u>ለ</u> ሲሆን ተጣማሪዎቹ የመጠን ቅፅል የሚባሉትና ባለፈው ክፍል በመጣኝ መስተዓምር ስር የመደብናቸው ናቸው። የጥምሩን መሪ መሰየት ያስቸግራል። ይሁን አንጅ ከሌሎች ጥምሮች አካሄድ በመነሳት ተውሳክ ግሶችም ቀኝ መሪ

ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። በዚሁ ይህን ንዑስ ክፍል እንሰናበታለን።

መልመጃ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ጥምርነት ያረጋግጡ፣ ትርጉማቸውን ይስጡ፣ ክፍላቸውንም ይናገሩ።

(ሀ) እሳተ ክላ
(ለ) በገ ፈጅ
(መ) ሀገረ ስብ
(ሰ) ሰበር ሰካ

2. የትኛው የቃል ክፍል ከየትኛው የቃል ክፍል ጋር ሊጣመር እንደሚችል በስንጠረዡ ውስጥ ምሳሌ እየሰጡ ያሳዩ። የመጀመሪያው ምሳሌ ተሰጥቶአል።

	ስም	ግስ	ቅፅል	ተውሳክ ግስ
ስም	ግብረ ሀይል	--------	መልከ ጥፉ	-------
ግስ				
ቅፅል				
ተውሳክ ግስ				

3. <u>ገጠመኛችን</u> የሚለውን ቃል በፅፀ-መዋቅር ተንትነው ያሳዩ። <u>ዘመናችን</u> ከሚለው ጋርም ያነፃፅሩና የአወቃቀር ልዩነታቸውን ይግለፁ።

4. <u>ቀስበቀስ</u> የሚለው ጥምር ተውሳክ ግስ እንደሆነ ተገልፆአል። በዚሁ መሰረት <u>እጅለጅ</u> የሚለውም ጥምር ተውሳክ ግስ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት ይጥቀሱ።

5. አጣማሪ ምዕላድ ያረፈበት ተጣማሪ ሁሉ የጥምር መሪ ነው። ይህን አባባል የሚደግፉ ምሳሌ በአንድ በኩል፣ የሚቃረን ምሳሌ በሌላ በኩል ይስጡ።

6. <u>ባለቤት</u> የሚለውን ቃል ውስጣዊ ስርዓት ያመልክቱ።

ምዕራፍ ሶስት

ስነ-መዋቅር

መግቢያ


ባለፈው ምዕራፍ ሰለ እማርኛ ቃላት አከፋፈልና በየክፍሉ ሰለሚገኙት ቃላት የርባታና የምስረታ ሰርዓት ተወያይተናል። ትኩረታችን በቃላቱ ውስጣዊ ስርዓት ላይ ነበር። ሰርዓቱ በየክፍሉ ውሰጥ የሚገኙት ቃላት ከምንና እንዴት እንደሚመሰረቱ የሚያሳይ ነበር። ለምሳሌ፣ እንደ <u>ደግነት</u> ያሉ ቃሰተ <u>ደግ</u> ከሚለው ቅፅላዊ ነፃ ምዕላድና /-ንንኧት/ ከሚሰው ዕስር መሰራች ምዕላድ ላይ የተፈጠሩ የስም ክፍል ቃላት እንደሆኑ ተመልክተናል። የአቀነጃጀታቸው ስርዓትም ከነፃው ቅፅላዊ ምዕላድ ቀኝ ጉን ላይ /-ንንኧት/ የሚሰውን ዕስር ምዕላድ መቀጠል ነው።

በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ሰሞች ለመደብ፣ ሰቁጥር፣ ለያታ፣ ሰሙያ፣ ወዘተ፣ ይረባሉ። ይህን ሲያደርጉም ቅርፃቸውን በከፊል እንደሚለዋውጡ አይተናል። ሁኔታውን ይበልጥ ሰመረዳት <u>ደግነት</u> የሚሰውን ስም ርባታ ከዚህ ቀጥሰን እናሳያሰን።

መደብ		1
1ኛ		ደግነት-ኤ
2ኛ	ተ	ደግነት-ህ
	አ	ደግነት-ህ-ኢ > ሽ
3ኛ	ተ	ደግነት-ኡ
	አ	ደግነት-ኡ-ኣ
	ብ	ደግነት-አች-ን
		ደግነት-አች-ህ-ኡ
		ደግነት-እች-ኧ-ኡ

የርባታውን ስርዓት ሰናይ እንደ /-ኤ/፣ /-ህ/፣ ወዘተ፣ ያሉ ቅጣይ የርባታ ምዕላዶች ቀደም ሲል <u>ደግ</u> ከሚሰው ቅፅል ሳይ /-ንንኧት/ በሚሰው መሰራች ምዕላድ አማካኝነት ከተመሰረተው፣ <u>ደግነት</u> ከሚሰው ሰም ቀኝ ጉን ላይ እንደሚቀጠሉ

እንረዳለን። ስለዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩትና የሚረቡትን ቃላት ውስጣዊ ሰርዓት በጥቅሉ እንደሚከተለው እናሳያለን።



እንግዲህ ባለፈው ክፍል የተመለከትነው እንደዚህ ያሉ ቃላትን ያወቃቀር ሰርዓት ሲሆን፥ በዚህ ክፍል ደግሞ ቃላት ብቻቸውን እየቆሙ፣ ወይም ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋ ሰፋ ያሉ መዋቅሮችን እንዴት እንደሚመሰርቱ እንመለከታለን። ከላይ በሚታየው ሁኔታ፣ ምዕላድ ከምላድ ጋር ሲቀናጅ ቃል እንደሚፈጥር ሁሉ፣ ቃልም ከሀረግ ጋር ሲቀናጅ ከቃል ከፍ ያለ መዋቅርን ይፈጥራል። ምዕላድ ከምዕላድ ጋር እየተቀናጁ ቃል የሚፈጥሩበት ሰርዓት ሰነ-ቃላት እንደሚባል ሁሉ፥ ቃላት ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋፊ መዋቅርን የሚፈጥሩበት ሰርዓትም ሰነ-መዋቅር ይባላል። ባለፈው ክፍል በሰነ-ቃላቱ ላይ እንዳተኮርን ሁሉ፥ በዚህ ክፍል በሰነ-መዋቅሩ ላይ እናተኩራለን።

ባለፈው ክፍል እንዳደረግነው፣ በዚህ ክፍልም እያንዳንዱን የቃላት ክፍል በየተራ እየወሰድን በውስጡ የሚገኙ ቃላት ከክፍላቸው ወይም ከሌላ ክፍል ሀረጎች ጋር እንዴት እንደሚቀናጁ፣ ማለትም እንደሚዋቀሩ ለማየት እንሞክራለን።

ሀረግ

ሀረግ የምንለው እንድን ከቃል የሰፋ፥ ከአረፍተ ነገር ያነሰን መዋቅር ነው። ከዚህ ላይ እንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸውም በመዋቅርና በሀረግ መካከል ያለውን ልዩነት የሚመለከት ነው። መዋቅር አጠቃላይ ቃል ነው ፣ ማንኛውንም ቅንጅት ያካትታል። ለምሳሌ፥ በሰነ-ድምፅ ደረጃ የቀለምን፣ በሰነ-ቃላት ደረጃ የቃላትን፣ እንደዚሁም በሰነ-መዋቅር ደረጃ የሀረግንና የአረፍተ ነገርን ውስጣዊ ቅንጅት

ይመለከታል። ሀረግ ግን ውሱን ነው። ውሱንነቱም በሁለት ወገን ነው። በአንድ ወገን በአደነቱ ወይም በከፍሉ ሲሆን፣ በሌላ ወገን በይዘቱ፣ ማለትም በመጠኑ ነው። በከፍሉ ሲታይ፣ አንድ ሀረግ ስማዊ፣ ግሳዊና ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ ሲሆን ይችላል። ስለዚህም ስማዊ ሀረግ፣ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ወዘተ፣ እያልን አንዱን የሀረግ አይነት ከሌላው እንለያለን።

የሀረጉ አይነት የሚወሰነው በቁዋንቁዋው ውስጥ በሚገኙት የቃላት ከፍሎች መጠን ነው። አንድ ቁዋንቁዋ አምስት የቃላት ክፍሎች አሉት ብንል፣ የሀረጉ አይነትም እንደዚሁ አምስት ይሆናል። ባስፈው ከፍል የአማርኛ ቃላት በስድስት እንደሚከፈሉ አይተናል። ስለዚህም ቁዋንቁዋው ስድስት የሀረግ አይነቶች ይኖሩታል። እያንዳንዱ የቃላት ክፍል በውስጡ ከሚገኘው ቃል ላይ ሀረግ የመመስረት ዕድል አለውና። ባስፈው ንዑስ ከፍል፣ ቃላት በቅለው ሀረግ ሲሰሩ ያችላሉ ብለን ነበር። ለምሳሌ፣ አንድ ስም የሆነ ቃል፣ አድጎ ሀረግ ሲሰደ፣ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። ይህ እንግዲህ ከአይነት አንፃር ሲታይ ነው።

ከመጠን አኩዋያ ሲታይ ደግሞ፣ አንድ ሀረግ ንዑስ ወይም አቢይ ሊሆን ይችላል። ይህ የሚወሰነው በሀረጉ ውስጣዊ ይዘት ነው። ትንሽ ነገሮችን የያዘ ንዑስ ሊባል፣ በርካታ ነገሮችን የያዘ አቢይ ሀረግ ይባላል። ይህን ወደ ዝርዝሩ እንገባ እናየዋለን። ከዚህ ላይ ለመግለፅ የምንፈልገው ንዑስም ይሁን አቢይ ሀረግ በቃል ላይ የተመሰረተ የመዋቅር አይነት መሆኑን ነው።

ስማዊ ሀረግ

ስማዊ ሀረግ የምንለው ከአንድ ስምና ከሌሎች ሀረጎች የሚፈጠርን መዋቅር ነው። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

የሳር ቤት 1

ይህ የስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። የተዋቀረውም ቤት ከሚለው ስምና <u>የሳር</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ስሙ ከሀረጉ ጋር ተቀናጅቶ አንድ ከቃል በፉ ያለ አሀድ ፈጥሮአል። ይህም አሀድ የሳር ቤት የሚለው መዋቅር ሲሆን፣ በአይነቱ ስማዊ፣ በመጠኑ ደግሞ ሀረጋዊ ነው። ከቃል ይበፋል ማለት ነው።

ከዚህ ላይ አሁንም ሁለት ነገሮችን ከወዲሁ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያው ማንኛውም ሀረግ ከመሪ ቃልና ከሀረግ የሚፈጠር መሆኑ ነው። ቃሉ ለሚፈጠረው ወይም ለሚመሠረተው ሀረግ ዘር ሲሆን፣ ሀረጉ ደግሞ አሳዳጊው ነው። የሚያሳድገውም ልዩ ልዩ መግለጫ ስለዘሩ በመስጠት ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ከስሙና ከሀረጉ የሚፈጠረው መዋቅር አንድ አሀድ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? ከሚል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው። ጥያቄው መሰረታዊ ነው። ወደፊት በየደረጃው አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው፣ እያልን የምንለየውንና የምንተነትነውን መዋቅር ሁሉ የሚመለከት ስለሆነ፣ ከወዲሁ ውል ያለው ምላሽ ማግኘት አለበት።

በመሰረቱ፣ እንድ ዘር ቃልና እንድ ሀረግ ሲቀናጁ፣ የሚፈጠረው ቅንጅት እንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው የምንለው፣ ቅንጅቱ የሚከተሉትን መሰረርቶች በከፊል ወይም በሙሉ የሚያሙዋላ ከሆነ ነው።

(ሀ) ቅንጅቱ በአረፍተ ነገር ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዳሰ፣ ማለትም ከተዋቃሪዎቹ መካከል እንዱም ሳይቀር፣ ሲንቀሳቀሰ ከቻለ፣

(ሰ) ቅንጅቱ በሙሉ በአንድ ተውላጥ (ትክ) ሊተካ ከቻለ፣

(መ) በአረፍተ ነገር ውስጥ፣ ቅንጅቱ ያለምንም ቀሪ ሲገደፍ ከቻለ፣

(ለ) በውስጡ ሌላ ቃል የማያሰገባ ከሆነና

(ረ) ቅንጅቱ እንደ እና ባሉ አያያዥ ቃላት አማካኝነት ከሌላ አቻ ቅንጅት ጋር ሲዋቀር የሚችል ከሆነ።

ከነዚህ መሰረርቶች አኩዋያ አሰቲ ከላይ በተራ ቁጥር (1) የተሰጠውን ምሳሌ እንድ አሀዳዊ መዋቅር (ቅንጅት) መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንመርምር።

የመጀመሪያው መስፈርት አንድ ቅንጅት አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው የሚባለው በአንድ ላይ ሊንቀሳቀሰ ከቻለ ነው የሚል ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ የሳር ቤት ነበረው] 2
(ለ) የሳር ቤት [ካሳ —— ነበረው]
(መ) * የሳር [ካሳ —— ቤት ነበረው]
(ሰ) * ቤት [ካሳ —— የሳር ነበረው]

ቅንፉ የሚያመለክተው የአረፍተ ነገሩን መጀመሪያና መጨረሻ ነው። በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ካሳ ከሚለው በም ቀጥሎ ገብቶአል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ግን ይኸው ቅንጅት የገባው ካሳ ከሚለው ለም በፊት፣ ማለትም ከአረፍተ ነገሩ ውጭ ነው። ይህም በመሆኑ፣ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት የነበረበት ቦታ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ ክፍት ሆኖ ይታያል። ይህም የሚያመለክተው፣ ቅንጅቱ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ከነበረበት መሰረታዊ ቦታ ተነስቶ ወደ አረፍተ ነገሩ ውጭ መሄዱን ነው። ነጠብጣቦቹም የሚያመለክቱት መሰረታዊ ቦታው መለቀቁን ነው። መዋቅሩ የተንቀሳቀሰው እንደ አንድ አሀድ ነው። በመሆኑም አረፍተ ነገሩ ትቀባይነት ሊኖረው ችሎአል። ምሳሌ (መ) እና ምሳሌ (ሰ) የተዛቡ አረፍተ ነገሮች ናቸው። የተዛቡበት ምክንያት የሳር ቤት በሚለው ቅንጅት ውስጥ የሚገኙት ክፍሎች በአንድ አሀድነት ሳይሆን፣ በተናጠል በመንቀሳቀሳቸው ነው። ይኸውም በምሳሌ (መ) የሳር የሚለው ብቻውን፣ በምሳሌ (ሰ) ቤት የሚለው እንደዚሁ ብቻውን ተንቀሳቅሰአል። ይህም የተናጠል እንቅሰቃሴ ለአረፍተ ነገሮቹ መዛባት

ምክንያት ሆኖአል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ እንደሚታየው፣ የሳር ቤት የሚለው አንዳለ ሊንቀሳቀስ መቻሉ፣ እንደ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ሊያስቆጥረው ይችላል።

ሁለተኛውን መሰፈርት እንመልከት። ይህም አንድ ቅንጅት እንዳለ በአንድ ተውላጥ ሊተካ ከቻለ፣ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል የሚል ነው። ከዚህ አንፃር አሁንም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] አለው 3
(ለ) [እሱም] ቀበሌ 13 ውስጥ ይገኛል
(መ) * [የሳር እሱም] ቀበሌ 13 ውስጥ ይገኛል

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ያለው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ [እሱም] በሚለው ተውላጥ ተተክቶአል። ተውላጡ የተካው ቅንጅቱን በሙሉ ነው። ስለዚህም ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ነው። በምሳሌ (መ) ውስጥ ግን፣ ተውላጡ የተካው [የሳር ቤት] የሚለውን ቅንጅት በሙሉ ሳይሆን፣ የቅንጅቱ አንድ አካል የሆነውን [ቤት] የሚለውን ስም ብቻ ነው። በመሆኑም አረፍተ ነገሩ ሊዛባና ተቀባይነትን ሊያጣ ችሉአል። ይህም የሚያሳየው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት በሙሉ አንድ፣ በከፊል ብቻ በተውላጥ ሊተካ አለመቻሉን ነው። ይህም ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል። ወደ ሶስተኛው መስፈርት እንሂድ።

መስፈርቱ አንድ ቅንጅት አንዳለ ሊገደፍ ከቻለ፣ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር እንደሚችል ይገልፃል። ከዚህም አንፃር የሚከተሉትን ምሳሌዎች ደግሞ እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] ነበረው 4
(ለ) አስቴርም [—] ነበራት

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የሚታየው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት በምሳሌ (ለ) ውስጥ በቦታው የለም፣ ተገድፎአል ማለት ነው። የተገደፈውም በሙሉ እንጅ በከፊል አይደለም። በሙሉ ሊገደፍ መቻሉ፣ ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል።

አራተኛውን መስፈርት ደግሞ እንመልከት። ይህም አንድ ቅንጅት አንድ አሀዳዊ መዋቅር ከሆነ፣ በመካከሉ ሌላ ቃል ጣልቃ ሊያስገባ እንደማይችል ይገልፃል። ስለዚህ የሚከተሉትን በአሰረጅነት እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] አለው 5
(ለ) ? ካሳ [የሳር ትንሽ ቤት] አለው

ምሳሌ (ሀ) ተቀባይነቱ የማያጠራጥር አረፍተ ነገር ነው። ምሳሌ (ለ) ግን ተቀባይነቱ አጠያያቂ ነው። በሁለቱ ምሳሌዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ በ(ለ) ውስጥ፣ ትንሽ

የሚለው ቃል [የሳር ቤት] በሚለው ቅንጅት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። የዚህ ቃል ጣልቃ መግባት አረፍተ ነገሩን ሊያዛባውና ተቀባይነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ችሎአል። ቃሉ በቅንጅቱ መካከል ሳይሆን፣ በመነሻው ላይ ቢገባ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት ይኖረዋል። ይህም እንደሚከተለው ሊሆን ነው።

ካሳ [ትንሽ [የሳር ቤት]] አለው 6

የምሳሌ 5(ለ) ተቀባይነት አጠያያቂ መሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ የምሳሌ (6) ትክክል መሆን የሚያመለክተው፣ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት፣ በውስጡ ሌላ ቃል ሊያስገባ አለመቻሉን ነው። ይህም ቅንጅቱ አንድ አህጻዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል።

የመጨረሻው መስፈርት አንድ ቅንጅት አህጻዊ መዋቅር ከሆነ፣ እንደ <u>እና ወይም</u> ባሉ አያያዥ ምዕላዶች ሊቀናጅ የሚችለው ከእኅ መዋቅር ጋር ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። በዚህ መስረት <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ቅንጅት ሊያያዝ የሚችለው እንደ <u>የቆርቆሮ ቤት</u> ካለ እኅ ቅንጅት ጋር ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ) [የሳር ቤት] እና [የቆርቆሮ ዳስ] 7
(ለ) ?[የሳር ቤት] እና [ዳስ]

የምሳሌ 7(ለ) ተቀባይነት አጠራጣሪ ነው። ምክንያቱም <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ቅንጅት የተያያዘው <u>ዳስ</u> ከሚል ተራ ስም ጋር በመሆኑ ነው። <u>ዳስ</u> የሚለው ተራ ስም ሊያያዝ የሚችለው አንደኑ ተራ ከሆነ ስም ጋር እንጅ፣ እንደ <u>የሳር ቤት</u> ካለ ስፊ ቅንጅት ጋር አይደለም። አንደ <u>ቤት</u> ካለ ተራ ስም ጋር ሊያያዝ፣ የሚከተለውን ይመስላል።

ቤት እና ዳስ 8

ይህ ተቀባይነት ያለው መዋቅር ነው። ሁኔታው "ያላቻ ጋብቻ... " ጥሩ አይሆንም የሚለውን ተረትና ምሳሌ ሊያስታውሰን ይችላል።፣

እንግዲህ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት ከፍ ሲል ከ(ሀ) እስከ (ረ) ድረስ የተዘረዘሩትን የመዋቅር መስፈርቶች ስለሚያሙዋላ እንደ አንድ አህጻዊ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ማንኛውም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ቅንጅት ሁሉ፣ እንደዚሁ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ወደፊት መዋቅር እያልን የምን ጠቅሳቸው ቅንጅቶች ሁሉ፣ ከነዚሁ መስፈርቶች አኩዋያ የሚታዩ መሆናቸውን ከወዲሁ እንገልፃለን። አሁን ከፍ ሲል ወደጀመርነው የመዋቅር ጉዳይ እንመለስ።

ከላይ ስመጠቆም እንደሞከርነው፣ በማንኛውም መዋቅር ውስጥ የሚገኝ ከፍል <u>ተዋቃሪ</u> ይባላል። ማንኛውም መዋቅርም የተዋቃሪዎች ቅንጅት ነው። አንድ ተዋቃሪ በመዋቅር ውስጥ የሚገኝበት የተለየ ቦታና ተግባር አለው። ተግባሩ የመዋቅሩ መሪ ወይም ተመሪ መሆን ነው። ለምሳሌ በ5(ሀ) ውስጥ [የሳር ቤት] የሚለው መዋቅር ተዋቃሪዎች <u>ቤት</u> የሚለው ስምና <u>የሳር</u> የሚለው ሀረግ ናቸው። አቀማመጣቸው <u>የሳር</u> የሚለው ቀድሞ፣ <u>ቤት</u> የሚለው እሱን ተከትሎ ስመምጣት ነው። በዚህ አቀማመጥ፣

<u>ቤት</u> የሚለው ተዋቃሪ ተግባር አጠቃላይ መዋቅሩን መምራት ነው። የመዋቅሩ ምሰሶ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ያለሱ መዋቅሩ ብቻውን አይቆምም። ስለዚህም የመዋቅሩ <u>አይቀሬ</u> አካል ወይም ተዋቃሪ ነው። <u>የሳር</u> የሚለው ተዋቃሪ ተግባር መሪውን፣ ማለትም <u>ቤት</u> የሚለውን ስም ማጀብ ነው። እጅቦም [የሳር ቤት] የሚለውን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታል። ያለመሪው ብቻውን ይህን ሊያደርግ አይችልም። መሪው ሰም ግን ያላጃቢው ብቻውን እንደ ምሰሶ ሊቆምና ሀረግ ሊሆን ይችላል። ስፊ መዋቅር ግን ሊሆን አይችልም፣ አጃቢ የለውምና። በዚሁ መሰረት ወደፊት እንደ ምሰሶ ብቻቸውን እየቆሙ የምናገኛቸውን አሀዶች ሀረግ እያልን እንጠራቸዋለን። ስራዊቱ አንደከዳው የጦር መሪ ሊቆጠሩ ይችላሉ።፣

መሪው ከአጃቢ ጋር ሲዋቀር፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አጃቢውን በስተግራ አስከትሎ እሱ በስተቀኝ ቀድሞ በመገኘት ነው። መሪው ከአጃቢው ቀድሞ በስተቀኝ ስለሚገኝ ሀረጉ ቀኝ መሪ ሀረግ ይባላል። ይህም ባለፈው ክፍል ስለ ጥምር ቃላት ስንወያይ እንዳየነው የተጣማሪዎች አሰላለፍ መሆኑ ነው። በአጃቢው መነሻ ሳይ የምትገኘው "የ" ባለፈው ክፍል ያየነውን ዘርፍ ሙያን እመልካች ምፅላድ ነች። እስዋ የምትገኝበት ስም ሙያው ባለቤት ወይም ተሳቢ ሳይሆን ዘርፍ ነው[1]። ይህን ወደፊት በክፋት እናየዋለን። ለጊዜው ግን ተግባርዋ አጃቢው ስም፥ ማለትም <u>ሳር</u>፥ የመሪው አካል ሆኖ ሀረጉን መመሰረቱን ማመልከት ነው፣ ብለን፣ ከፍ ሲል ወደ አነሳነው የመሪና የተመሪ (አጃቢ) ተግባር እንመለስ።

አንድ መሪ የሀረግን አይነት ብቻ ሳይሆን፣ ክፍሉንም ይወስናል። መሪው ስም ከሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። መሪው ግሽ ከሆነ፣ መዋቅሩም እንደዚሁ ግሳዊ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ መሪ <u>ቤት</u> የሚለው ስም ስለሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ነው።

የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

ትልቅ ቤት 9

ይህ መዋቅር <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅልና <u>ቤት</u> የሚለው ስም ቅንጅት ነው። የመዋቅሩ መሪ አሁንም <u>ቤት</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ አጃቢው <u>ትልቅ</u> የሚለው <u>ቅፅል</u> ነው። መሪው ስም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፣ የአንድ መዋቅር መሪ ስም እስከሆነ ድረስ፣ አጃቢው ምንም ይሁን ምን፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ እንጅ ሌላ ሊሆን እሰመቻሉን ነው ።

በምሳሌ (1) እና (7) ውስጥ መሪው የተዋቀረው ከአንድ አጃቢ ጋር ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ ግን አንድ መሪ ከአንድ በላይ አጃቢ አይኖረውም ወደሚል

[1] የ "የ"ን የተለያየ ተግባር ቡተመለከተ አሁንም ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ።

ድምዳሜ አይወሰድም፣ ብዙ አቫቢ ሊኖረው ይችላል፤ እንደ ትልቅ መሬ። ስለዚህት የሚከተለውን እንመልከት።

ትልቅ የሳር ቤት 10

ይህ አንድ መዋቅር ነው። መሪው አሁንም ቤት የሚሰው ሰም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው ሁለት አቫቢዎች አሉት። እነሱም የሳር የሚለው ስማዊ ሀረግና ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ናቸው። በምሳሌ (1) ውስጥ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ራሱን የቻለ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ ከፍ ሲል አይተናል። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ደግሞ ያው ሀረግ ትልቅ ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ይህን በማድረጉ የተለየ ሀረግ አልፈጠረም። አሁንም የፈጠረው ስማዊ ሀረግ ነው። ርግጥ፣ የአሁኑ ሀረግ ከፊተኛው ሰፋ ይላል። ስለዚህም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የይዘት ነው። በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ ከእሱ ይሰፋል ያልነውና በተራ ቁጥር (10) የሚታየው መዋቅር ምን ሊባል ነው? ሀረግ ወይስ ከሀረግ በላይ የሆነ መዋቅር?


ቀደም ሲል፣ አንድ ሀረግ በመጠኑ ንዑስ ወይም አቢይ ሊሆን እንደሚችልና ይህንንም የሚወስነው በውስጡ የሚገኘው የተዋቃሪ ብዛትና ተግባር እንደሆነ ገልፀን ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ አቫቢ ብቻ ስላለው፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘውና ሁለት አቫቢ ካለው መዋቅር በይዘቱ ያነሰ ነው። ስለዚህም ይህን መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ከእሱ የሚበልጠውንና በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘውን መዋቅር ደረጃ ለመወሰን፣ ተጨማሪ ምሳሌዎች ያስፈልጉናል። እስቲ የሚከተለውን እንመልከት።

የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት 11

ይህ መዋቅር በተራ ቁጥር (1)ም ሆነ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘው መዋቅር የሰፋ ነው። የሰፋበት ምክንያት መሪው ሶስት አቫቢዎች ስላሉት ነው። በዚህም ምክንያት መዋቅሩን አቢይ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ይህን ስንል ግን፣ መዋቅሩ ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ አይችልም ማለታችን አይደለም። ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ ይችላል፤ ደረጃው ግን አሁንም ከአቢይ ሀረግ አያልፍም። እንዴት እንደሚሰፋ ከማየታችን በፊት በተራ ቁጥር (1፥ 10፥ እና 11) ውስጥ የሚታየውን የአቫቢዎችና የመሪ ቅንጅት ከሁለቱ የአቢይና የንዑስ ሀረግ ደረጃዎች አንፃር እንደገና እናጢነው።

በተራ ቁጥር (1) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ነው ካልን፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ከዚህ ንዑስ ሀረግና ትልቅ ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፤ ለማለት ይቻላል። ይህም ማለት፣ ምሳሌ (10) ቤት ከሚለው መሪና የሳር እና ትልቅ ከሚሉት አቫቢዎች በአንድ ጊዜና በአንድ ደረጃ

የተዋቀረ ሳይሆን፣ መጀመሪያ ቤት የሚለው መሪና የሳር የሚለው አጃቢ ተዋቅረው በተራ ቁጥር (1) የሚታየውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ ከፈጠሩ በሁዋላ፣ በሁለተኛ ደረጃ ወይም ርከን ላይ ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ከዚሁ ንዑስ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን ስፋ ያለ መዋቅር ፈጥሮአል ማለት ነው። ከዚህ በሁዋላ ደግሞ ይኸው በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚታየው ሀረግ፣ የትናንቱ ከሚለው ጊዜን አመልካች ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (11) የሚታየውን በጣም ሰፊ የሆነ አቢይ ሀረግ ፈጥሮአል። በሌላ አነጋገር፣ አቢይ ሀረጉ በውስጡ ሁለት ሀረጎችን ይዞአል። እነሱም የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ሀረግና የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው አቢይ ሀረግ ናቸው። የንዑሱ ሀረግ መሪ ቤት የሚለው ስም አንደሆነ ሁሉ፣ የአቢይ ሀረጉ መሪ የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ሀረግ ነው። ይህን የሁለቱን ሀረጎች የደረጃ ልዩነት እንደሚከተለው አድርጎ ስዕዐ መዋቅር ማሳየት ይቻላል።



ከዕዐ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ በመጀመሪያው ርከን ላይ የሳር እና ቤት ተዋቅረው [የሳር ቤት] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) ፈጥረዋል። [የሳር ቤት] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሆነበት ምክንያትም መሪው አንድ አጃቢ ብቻ ስላለው ነው። በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ይህ ሀረግ ትልቅ ከሚለው አጃቢዎች ጋር ተዋቅሮ፣ [ትልቅ የሳር ቤት] የሚለውን ሰፊ ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ፈጥሮአል። ይህ አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። አቢይ የሚያሰኘው ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ የበለጠ ሰፊ ይዘት ያለው መሆኑ

---

[2] የሀረጎችን ውስጣዊ አቀነጃጀት ከዚህ ላይ እንደሚታየው፣ በቅንፍ ወይም በዕዐ-መዋቅር ማመልከት ይቻላል። ዕዐ-መዋቅር የአቀነጃጀቱን ስርዓት በቀላሉ ስማየት ስለሚያስችል፣ ብዙ ጊዜ እሱን እንጠቀማለን፤ ምንም እንኩዋ ቦታ-ፈጅ ቢሆንም።

ነው። ንዑሱ ሰማዊ ሀረግ የዚህ አቢይ ሀረግ አካልና መሪም ነው። ሀረጉ የትናንቱ ከሚለው የጊዜ ሰማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ሰርክን (3) ሳይ እንደሚታየው ከሁሉም የሰፋ ሀረግ ሊሆን ችሎአል።

ከዕዐመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ጠቅላላ ሀረጉ ሶስት ርከኖች አሉት። እነሱም በቁጥሮቹ የተመለከቱት የንዑሱ ሀረግ (ስሀ1) የአቢዩ ሀረግ (ስሀ2) እና ስሀ(3) አንጉዋዎች ናቸው። በነዚህ ርከኖች ላይ የሚገኙት አጃቢዎችም የተለያዩ ናቸው። ልዩነታቸውም መሪውን ከሚገልፁበት ተግባር አኩዋያ ነው። በንዑስ ሀረጉ ርከን ውስጥ የሚገኘው የሳር የሚለው አጃቢ፣ የሀረጉ መሪ የሆነው፣ ቤት የሚለው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደ ተሰራ ያመለክታል። የሳር ቤት ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው።

በሁለተኛው ርከን ላይ የሚገኘው ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ የሳሩ ቤት መጠን ምን ያህል እንደሆነ ይገልፃል። የመጀመሪያው አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ነገር ሲገልፅ፣ ሁለተኛው አጃቢ የቤቱን መጠን፣ ማለትም ትልቅነቱን፣ ይገልፃል። በሶስተኛው ርከን ላይ የሚገኘው የትናንቱ የሚለው ተጨማሪ አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ወይም የተገኘበትን ጊዜ ያመለክታል። ሶስቱም አጃቢዎች መሪውን ሰም ከተለያየ አንፃር ይገልፁታል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ሁሉም ገላጭ አጃቢዎች ናቸው።

መሪውን ከተለያየ አንፃር የሚገልፁ እንደመሆናቸው መጠን፣ አገባባቸውም እንደዚሁ በተለያየ ርከን ላይ ነው። መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደተሰራ የሚገልፀው አጃቢ በመጀመሪያው ርከን፣ በንዑስ ሀረጉ ውስጥ፣ በቀጥታ ከመሪው ሰም በሰተግራ በኩል ተጠግቶ ሲገባ፣ መሪው የሚጠቁመውን ነገር መጠን የሚገልፀው ቅፅል በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ጊዜውን የሚያመለክተው የትናንቱ የሚለው አጃቢም በሶስተኛው ርከን ሰይ የሳር ቤት የሚለውን ንዑስ ሀረግ አየቀደመ ገብተዋል። በዚህ ደረጃ የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው አቢይ ሀረግ መሪ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው ሀረግ ነው። የዚህ ሀረግ መሪም የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ዘረግ ነው። የአቢይ ሀረጉ መሪ ንዑስ ሀረግ ሲሆን፣ የንዑስ ሀረጉ መሪ ግን ሀረግ ሳይሆን ተራ ቃል ነው። ቃሉ ሌሎች ነገሮችን በየርከኑ እየጨመረ በማደግ መጀመሪያ ንዑስ፣ ከዚያ በየደረጃው አየሰፋ አቢይ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ ሳይ ባለፈው ንዑሰ ክፍል ቃሳት ዘረግ ይመዛሉ ያልነውን ያስታውሱ።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ሀረጉ በተራ ቁጥር (11) ከሚታየው የበለጠ ሊሰፋ ይችላል። የሚለፋውም የተለያዩ አጃቢዎችን በመጨመር ነው። ተጨማሪዎቹ አጃቢዎች የሚገቡት በተለያየ ርከን ላይ ነው። በመጀመሪያው ሳይ የሚገባ ተጨማሪ አጃቢ የለም። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ሊገባ የሚችለው አጃቢ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት አጃቢ ብቻ ነው። እንደዚህ ያለ አጃቢ ደግሞ ከአንድ በላይ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ምንም እንኩዋ አንዳንድ ነገሮች ከብዙ ነገር ሊሰሩ የሚችሉ ቢሆኑም፣ የሚጠቀሱት ከተሰሩባቸው ነገሮች በአንዱ ብቻ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ፣ የሳር ቤት ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው። ይሁን እንጅ፣ ቤቱ ከሳር ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ነገሮች ጭምር የተሰራ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም፣ ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው የቤቱ ጣሪያና ግድግዳ ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት ጣሪያው ወይም ግድግዳው የተሰራበትን ነገር ስመጥቀስ፣ ጠቅላላ ቤቱን እንገልፃለን። የሳር ወይም የቆርቆሮ በማለት ከዳኑን፣ የእንጨት፣ የሸክላ፣ ወዘተ፣ በማለት ግድግዳውን እንጠቁማለን። ስለዚህም አንድን ቤት ስንገልፅ አትኩሮታችን ከነዚህ ከሁለቱ አያልፍም። በንዑስ ሀረግ ደረጃ ሲገባ የሚችለው አጃቢ አንድ ብቻ የሚሆነውም ከነዚህ

ከሁለቱ በአንዱ ብቻ ሰለሚጠቀስ ነው። ሌሎች ነጋሮችንም የምንገልፀው እንደዚሁ በአንዱ ባህሪያቸው ወይም አካላቸው ላይ በማተኮር ነው።

ሁለተኛው፣ በሰስተኛው፣ ወበተ ርከን ላይ ግን ከላይ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ገላጭ አቻቢዎች ሊገቡ ይችላሉ። ተግባራቸውም ንዑስ ሀረጉ የሚጠቁመው ነገር የሚገኝበትን ሁኔታ ወይም የተሰራበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ዓላማ፣ መሳሪያ፣ ወበተ፣ መግለፅ ነው። የሚከተለውን ተጨማሪ ምሳሌ እንመልከት።

የመርካቶው ትልቅ የሳር ቤት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>የመርካቶው</u> የሚለው ገላጭ አቻቢ፣ <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅል ቀድሞ ገብቶአል። ተግባሩም <u>የሳር ቤት</u> የሚለውን ንዑስ ሀረግ ከቦታ አንፃር መግለፅ ነው። <u>የትናንቱ</u> የሚለው የጊዜ ሀረግ በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሊገባና ሀረጉን የበለጠ ሊያሰፋው ይችላል። እገባቡም ከዚህ ቀጥሎን እንደምናየው በሀረጉ መነሻ ላይ ነው።

(ሀ) <u>የትናንቱ</u> የመርካቶው ትልቅ የሳር ቤት 14
(ለ) ?የመርካቶው <u>የትናንቱ</u> ትልቅ የሳር ቤት
(መ) * የመርካቶው ትልቅ <u>የትናንቱ</u> የሳር ቤት

የእነዚህ ምሳሌዎች የተቀባይነት ደረጃ ከ(ሀ) ወደ (ለ) ከዚያም ወደ (መ) እሽቆልቁሎአል። ስለዚህም ምክንያት የሆነው <u>የትናንቱ</u> የሚለው ገላጭ ሀረግ በ(ሀ) ውስጥ የሚገኝበትን ቦታ ትቶ፣ መጀመሪያ በ(ለ) ውስጥ <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅል በፊት፣ እንደገናም በ(መ) ውስጥ <u>የሳር</u> ከሚለው ስም በፊት መግባቱ ነው። ከዚህ የምንረዳው በእቢይ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ ገላጮች ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ሰርዓት የሚከተሉ መሆናቸውን ነው። ይኸውም የጊዜው ገላጭ ከቦታው፣ የቦታው ገላጭ ደግሞ ከቅፅሉ እየቀደመና ከፍ እያለ የሚገባ መሆኑ ነው። ይህ ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ሰልፍ ሲፋለስ አረፍተ ነገሩ ይዛባል።

በዚሁ አይነት ሌሎች ገላጭ አቻቢዎችን እየጨመሩ ሀረጉን ማስፋትና በዚያም ውስጥ ቅደም-ተከተላዊ እገባባቸውን ማየት ይቻላል። ለተጨማሪ ማስረጃ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) <u>የበርሜሉ</u> ደረቅ የማር ጠጅ 15
(ለ) ? ደረቅ <u>የበርሜሉ</u> የማር ጠጅ
(መ) * ደረቅ የማር <u>የበርሜሉ</u> ጠጅ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>የበርሜሉ</u> የሚለው ስማዊ ገላጭ በመነሻ ላይ ይገኛል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ደግሞ በቅፅሉና <u>የማር</u> በሚለው ገላጭ መካከል ይገኛል። ስለዚህም ምክንያት የሀረጉ ተቀባይነት እጠያያቂ ሆኖአል። በምሳሌ (መ) ውስጥ ደግሞ ጠጅ ከሚለው መሪ ስም ቀድሞ በመግባቱ አረፍተ ነገሩ ተዛብቶአል።

በነዚህና በተራ ቁጥር (12) ውስጥ በአቢዩ ሀረግ ርከን ላይ የሚገኙ ስማዊ ገላጮች ቦታቸውን እየለቀቁ ወደ ንዑሱ ሀረግ በተጠጉ ቁጥር፣ የሀረጎቹ ተቀባይነት እየቀነሰ እንደሚሄድ አይተናል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ዘንዑስ ሀረግ ርከን ላይ መገኘት ያለበት ገላጭ ቦታውን ለቆ ወደ እቢይ ሀረጉ ርከን ሲጠጋ፣ የአረፍተ ነገር መዛባትን ሊያስከትል ይችላል። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።


(ሀ) የተገዘካሩ ደረቅ የማር ጠጅ 16
(ለ) ? የተገዘካሩ የማር ደረቅ ጠጅ
(መ) * የማር የተገዘካሩ ደረቅ ጠጅ

የማር የሚለው ስማዊ ገላጭ መለረታዊ ቦታው በምሳሌ (ሀ) ውስጥ እንደሚታየው፣ ጠጅ ከሚለው መሪ ስም በፊት ነው። በዚህ ቦታ ተገኝቶ መሪውን ስም በማጀብ ንዑሱን ሀረግ ይመሰርታል። ይህን ቦታውን በመልቀቅ ከመሪው እየራቀ በሄደ ቁጥር፣ የሀረጉ የተቀባይነት ደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚህም ሁኔታ በመሪውና የማር በሚለው ገላጭ ስም መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዳለ መረዳት ይቻላል።

እስካሁን ካየናቸው ምሳሌዎች እንደምንረዳው፣ በአቢይ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ አጃቢዎች ሁለት አይነት ናቸው። እነሱም ስሞችና ቅፅሎች ናቸው። በሞቹን በጥቅሉ ተውሳከ ስሞች ልንላቸው እንችላለን። ትርጉሙ የስም ጭማሪዎች ማለት ነው። ጭማሪነታቸው ከነሱ ቀጥሎ ለሚገኘው ሀረግ ነው። ተውሳከ ስሞች የሚባሉበት ምክንያት ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ ላይ እየተጨመሩ ሀረጉን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከምክንያት፣ ወዘተ፣ አኳያ ስለሚገልፁትና ስለሚያሰፉት ነው።

በንዑሱ ሀረግ ውስጥ የሚገኘውን አጃቢ ስማዊ ልንለው እንችላለን። መሪው ስም የሚጠቁመው ነገር የተነሪበትን ወይም የተገኘበትን፣ ማለትም ምንጩን፣ ስለሚጠቁም ነው። ለምሳሌ የማር ጠጅ በንል፣ የማር የሚለው ሀረግ ጠጁ የተጠመቀበትን (የተጣለበትን) ነገር ይገልፃል። የነጃም የማር ጠጅ ስንል ደግሞ የነጃም የሚለው የማሩ ጠጅ የመጣበትን ወይም የተጠመቀበትን ቦታ ይገልፃል። ስለዚህም የነጃም የሚለው ተውሳከ ስማዊ ገላጭ ሲሆን፣ የማር የሚለው ስማዊ ገላጭ ነው። ስማዊ ገላፊዎችን መመሙሊያ በማለት፣ ከተውሳከ ስማዊ ገላፊች ልንለያቸው እንችላለን። ከዚህ አኩዋያ በአቢይ ሀረግ ስር የሚገኙ ተዋቀሪዎችን በጥቅሉ ገላጭ፣ በንዑስ ሀረግ ስር የሚገኙትን ደግሞ መመሙሊያ ብሎ መለየት ይቻላል። ርከናቸውንም በዕፀ-መዋቀር እንደሚከተለው ማሳየት የቻላል።

17



ከመመሙሊያውና ከመሪው የተዋቀረውን ንዑስ ሀረግ (ስሀ1) ወደ አቢይ ሀረግነት የሚያሳድገው ልዩ ልዩ ገላጭ ተዋቃሪ ነው። ስለሆነም በየርከኑ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ገላጭ አጎላማሽ (አሳዳጊ) ይባላል። ስለ መሪው የተሰያየ ተጨማሪ መረጃ


አየሰጠ የሚያጅብና የሚያሰፋ እናም የሚያጎላምስ መዋቅር ነው። ርክኑም በሶስት ብቻ ሳይወሰን ይችላል። የከከብ ምልክትዋ (*) የምታመለክተውም ይህን ሁኔታ ነው።

በተራ ቁጥር (12) ከሚታየው ዕፀ-መዋቅር ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ተዋቃሪዎቹ በሙሉ ተራ ቃላት ይመስላሉ። ይህ ግን ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም መሪው ስም ብቻ ነው፣ ተራ ቃል ሊሆን የሚችለውና የየሀረጉ ዘር በመሆንም እይነቱን የሚወስነው። መሪው ቃል ስም ከሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ይሆናል። መሪው ቃል ቅፅል ከሆነም፣ ሀረጉም እንደዚሁ ቅፅላዊ ይሆናል፣ ወዘተ። የሀረጉ አይነት በመሪው ቃል ክፍል እንደሚወሰን ሁሉ፣ ሀረጋዊ ሰፋቱ፣ ይዘቱ ብሎም ርክኑ በተዋቃሪዎቹ ሀረጎች ይወሰናል። ስለዚህም ከመሪው ጋር የሚዋቀሩት ክፍሎች በሙሉ ሀረጎች ናቸው። ባጭሩ አንድ ሀረግ አይነቱን ከመሪው፣ ሀረጋዊ ደረጃውን ከተዋቃሪ መሙሊያዎችና አጎላማሽ ሀረጎች ያገኛል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

እስካሁን የተመለከትነው አንድ ስም ከአንድ መሙሊያና ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጎላማሾች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ ንዑስና አቢይ ስማዊ ሀረግን ሊመሰርት ነው። ከሰሙ ጋር የሚዋቀሩት ሀረጎች በነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። ከአቢይ ሀረጉ ጋር እየተዋቀሩ ይህንኑ ሀረግ ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ ሊያሳድጉ የሚችሉ ሌሎች መዋቅሮች አሉ። እነዚህም ባለፈው ከፍል ያየናቸውና መስተዓምር ያልናቸው ክፍሎች ናቸው። አገባባቸው በየሀረጉ መነሻና አንዳንድ ጊዜም በመድረሻው ላይ ነው። ዝረዘሩን ቆየት ብለን እናየዋለን። ለጊዘየው የሚከተሉትን ለእብነት እንመልከት።

(ሀ)	<u>ያ</u> ንበዝ የሰዋሰው መምህር	18
(ለ)	<u>አንድ</u> የጎሻም የቅኔ መምህር	
(መ)	<u>የእኛ</u> የእንግሊዝኛ መፅሀፍ	
(ሰ)	የአንግሊዝኛ-ው መፅሀፍ	

የመስተዓምሮች ተግባር አቢይ ስማዊ ሀረጎች የሚገልፁዋቸውን ነገሮች መወሰን ነው። እወሰኑም ነገሮቹ ከሚገኙበት ቦታ፣ ከመጠናቸውና ከገንዘቢያቸው (ባለቤታቸው) እና ካዚህ በፊት የተጠቀሱና ስለዚህም የታወቁ ከመሆናቸው ወይም ካለመሆናቸው አኩዋያ ነው። በዚሁ መስረት ጠቁዋሚ፣ መጣኝ፣ አገናዛቢ እና ዕምር (የታወቁ) መስተዓምሮች እንደሚባሉ ባለፈው ከፍል ተገልያለል። ከነዚህ መካከል የዕምርነቱ ምዕላድ በመሪው ቃል ወይም በአጎላማሽ መድረሻ ላይ ይገኛል። የሀረጎቹ ወርዳዊ (ቅደም-ተከተላዊ) አቀማመጥ በምላሌ (ሀ) እንደሚታየው ሲሆን፣ ተዋረዳዊ አቀማመጣቸው ደግሞ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው።



ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ መስተዓምሩ ያ የተዋቀረው ከስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ጋር ነው። ተግባሩም ይህ ስማዊ ሀረግ፣ ማለትም ጎበዝ የሰዋሰው መምህር የሚለው ከፍል፣ የሚጠቁመውን ነገር የትነት መወሰን ነው። እንደዚያ እያደረገ ሀረጉን ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ (ስሀ3) ያሳድገዋል።

ሶስቱ የመስተዓምር አይነቶች ተከታትለው ሊመጡና ስማዊ ሀረጉን (ስሀ2)ን ሊወስኑ ይችላሉ። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

(ሀ) እነዚያ የእኔ ሁሉት [የሰዋሰው መፃህፍት] 20
(ለ) ? የእኔ እነዚያ ሁሉት [የሰዋሰው መፃህፍት]
(መ) ? ሁሉት የእኔ እነዚያ [የሰዋሰው መፃህፍት]


መስተዓምሮቹ የሚወስኑት በቅንፉ ውስጥ የሚታየውን አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። መስረታዊ ቅደም-ተከተላዊ ብሎም ተዋረዳዊ አገባባቸውም በምሳሌ (ሀ) እንደሚታየው፣ ጠቁዋሚው ቀድሞ፣ አገናዛቢው እሱን ተከትሎ፣ መጣኙ ደግሞ ሶስተኛ ሆኖ በመስለፍ ነው። ይህ አገባብ ቢፋለስ፣ ውጤቱ በምሳሌ (ለ) እና (መ) እንደሚታየው ያለ መዛባት ይከሰታል። ይህን ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

---

[3] መስተዓምሮችም የራሳቸውን ሀረግ ይመሰርታሉ። እንዴት እንደሚመሰርቱ ቆይተን እንመለከታለን።

[ጠቋዋሚ - አገናዛቢ- መጣኝ - ሰሀ 21

አንድ ንዑስ ስማዊ ሀረግ በተለያዩ አነላማሾች ሊገለፅ እንደሚችል ሁሉ፣ አንድ አቢይ ስማዊ ሀረግም በተለያዩ መስተዓምሮች ሊወሰን እንደሚችል ከምሳሌ 20(ሀ) መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር፣ ከአንድ መሙሊያ ሀረግ ጋር ብቻ የሚዋቀረው ቃላዊ የሆነው መሪ ስም ብቻ ነው። ይህን በየርከኑ ሊገኝ የሚችለውን የተዋቃሪ መጠን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው አጠቃሉ ማሳየት ይቻላል።



22

እንግዲህ አሰካሁን በዝርዝር ያየነውን ጠቅለል ብናደርገው፣ አንድ ስማዊ ሀረግ የአራት ነገሮች ቅንጅት ነው፣ ስማለት እንችላለን። እነሱም ከዚህ ዕፀ-መዋቅር እንደሚታየው፣ መሪ፣ መሙሊያ፣ አነላማሽና መስተዓምር ናቸው። አወቃቀራቸው ወርዳዊና ተዋረዳዊ ነው። መሪው ቃልና መመሊያው ሀረግ በአንድ ወርድ ወይም ርከን ላይ ይገኛሉ። አነላማሹና ንዑሱ ስማዊ ሀረግ (ሰሀ1) እንደዚሁ በሁለተኛው ርከን በቅደም-ተከተል ይገኛሉ። በመጨረሻም መስተዓምሩና አቢዩ ስማዊ ሀረግ (ሰሀ2) በሶስተኛው ርከን ላይ እንደዚሁ በቅደም-ተከተል ተሰልፈዋል። ይህ አይነተኛ የመዋቅር ባህሪ ነው። ባህሪነቱ ግን የቁዋንቁዋ ብቻ ሳይሆን፣ የየቁዋንቁዋው ተናጋሪ ማህበረ-ሰብም ሥምር ነው። ያልተዋቀረ የማህበረሰብ አባል የትም የለም። መዋቅሩ የዕድር፣ የፓለቲካ፣ የማህበር፣ ወዘተ፣ ሊሆን ይችላል። በዚህም ውስጥ መሪና ተመሪ አለ። እነዚህ ደግሞ በአንድ የስልጣን ርከን ላይ አይቀመጡም። ፕሮቶኮሉ አይፈቅድም። ወደ ጉዳያችን እንመለስ።

ከላይ በዕፀ መዋቅሩ ውስጥ የሚታየው መዋቅራዊ ተዛምዶ መመሊያ ያላቸውን፣ እንደ ጠጅ ያሉ ሰሞችን ሀረግ መሰረት ያደረገ ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰሞች ባለመመሊያ ሰሞች ሊባሉ ይችላሉ። ይህ ደግሞ መመሊያ የሌላቸው ሰሞች

---


[4] ይህ የኮከብ ምልክት የአነላማሾችና የመስተዓምሮች ቁጥር ከአንድ በላይ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል።

[5] ከፍተኛ አቢይ ሀረጎችን በአህዝ አናመለክትም። ተራ አቢይ ሀረጎችን በሁለት ቁጥር፣ ንዑስ ሀረጎችን በአንድ ቁጥር እናመለክታለን። በገሀድ የሚታይ ገላጭ ወይም መሙሊያ የሌለው፣ ማንኛውም አቢይ ሀረግ በዕፀ-መዋቅር ላይ በቁጥር ላይመለክት ይችላል።

አሉ እንዴ? የሚል ጥያቄን ያሳስባል። ርግጥ ነው፣ የዚህ አይነት ስሞች አሉ። ስለዚህም ስሞችን መመዯቢያ ያላቸውና የሌላቸው ብሎ በሁለት መመደብ ይቻላል። ሁኔታው ግን በስሞች ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ ሌሎች የቃላት ክፍሎችንም ያጣቅሳል። ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን። አሁን መመዯቢያ ወደሌላቸው ሀረጎች እንሂድና ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት።

(ሀ) ያች የምስራቅ ኮከብ 23
(ለ) ያች የንጋት ጨረቃ
(መ) የገና ጀንበር
(ሰ) የጥቅምት ውርጭ

የእነዚህ ሀረጎች መሪ ስሞች <u>ኮከብ</u>፣ <u>ጨረቃ</u>፣ <u>ጀንበር</u> እና <u>ውርጭ</u> የሚሉት ስሞች ናቸው። ከእነዚህ ጋር የተዋቀሩት ጊዜንና ቦታን የሚያመለክቱ ተውሳክ ስማዊ ገላጮችና መስተዓምሮች ናቸው። ተግባራቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ አንድን ንዑስ ሀረግ ማጎላመስና መወሰን ነው። የየምሳሌዎቹ ንዑስ ሀረግ የተመሰረተው በመሪው ስም ብቻ ነው። ስለዚህ ምክንያቱ መሪው ስም የሚጠቁመው ነገር የተስራበትን ነገር የሚገልፅ ሀረግ አለመኖሩና ሊኖርም አለመቻሉ ነው። <u>ቤት</u> ከምን እንደሚሰራ የሚታወቀውን ያህል፣ ኮከብ ከምን አንደሚፈጠር ቢያንስ ለተራው የቁዋንቁዋ ተጠቃሚ ፅውቅ አይደለም። ስለዚህም እንደ <u>ኮከብ</u> ያሉ ስሞች ገላጭ እንጅ መመዯቢያ ሀረግ የላቸውም። ስዚህ መስረት የምሳሌ 23(ሀ) መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።



<u>ኮከብ</u> የሚለው መሪ ስም መመዯቢያ ስለሌለው፣ ንዑሱን ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) የመስረተው ብቻውን ነው። አቢዩን ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ግን <u>የምስራቅ</u> ከሚለው ገላጭ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ መስርቶአል። ይህ ደግሞ በተራው <u>ያች</u> ከሚለው ጠቁዋሚ መስተዓምራዊ ሀረግ ጋር በመቀናጀት ዋናውን ሀረግ ሊመስርት ችሉአል።

እንደ ከከብና ጠጅ ባሉ ስሞች መካከል ያለው መዋቅራዊ ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ይኸውም እንደ ጠጅ ያሉት፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ መሙሊያ ሲኖራቸው፣ እንደ ከከብ ያሉት የሌላቸው መሆኑ ነው። ከዚያ ውጭ ሁሉም ከገላጮችና ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ አቢይ ሀረጋቸውን ስለሚመሰርቱ በመካከላቸው ልዩነት የለም።

እስካሁን ያየነው የነባር ሰሞችን ሀረግ አወቃቀር ነው። ከዚህ ቀጥለን የውልድ ስሞችን ባህሪ እንመለከታለን። በክፍል ሁለት እንዳየነው፣ ውልድ ስሞች የሚባሉት ከነባር ሰሞች፣ ቅፅሎችና ከስሮች ላይ በመስራች ምዕላድ አማካኝነት የሚፈጠሩ ናቸው። የነዚህ አይነት ስሞች የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ከሚወለዱበት ቃል ያወቃቀር ባህሪ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምንጩ ቃል መሙሊያ የሚይዝ ከሆነ፣ ውልዱ ቃልም እንደዚሁ መሙሊያ ይይዛል። ስምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመለከት።

(ሀ) ካሳ ዜማ ደረሰ
(ለ) ያ የዜማ ደራሲ
(መ) ያ የዜማ ድርሰት 25

የነዚህ ሀረጎች መሪዎች የተሰመረባቸው ቃላት ናቸው። ሁሉም ውልድ ሲሆኑ፣ አወላለዳቸው /ድ-ር-ስ/ የሚለውን ስር መስረት ያደረገ ነው። ይህ ስር ደግሞ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል። የእሱ ውልድ የሆኑት ደረሰ፣ ደራሲ እና ድርሰትም እንደዚሁ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። በግሱና በስሞቹ መካከል ያለው ልዩነት፣ ግሱ መሙሊያዎቹን የግድ ሲፈልግ፣ ስሞቹ ግን የግድ የማይፈልጉ መሆናቸው ነው። በሌላ አነጋገር፣ ስሞቹ ያለመሙሊያቸው ሀረጉን እንደሚከተለው ሊመሰርቱ ይችላሉ።

(ሀ) ያ [ ] ደራሲ
(ለ) ያ [ ] ድርሰት
(መ) ? ካሳ [ ] ደረሰ 26

ቅንፎቹ ዜማ የሚለውን መሙሊያ ቦታ ያመለክታሉ። መሙሊያው በምሳሌ (ሀ) እና (ለ) ቢገደፍም፣ የምሳሌዎቹ ተቀባይነት አልቀነሰም። የምሳሌ (መ) ተቀባይነት ግን ጥያቄ ውስጥ ገብቶአል። ስለዚህ ምክንያቱ የመሙሊያው መገደፍ ነው። ይህም እንደ ደረሰ ያሉ ግሶች ያለመሙሊያቸው ሊቆሙ እንደማይችሉ ያሳያል። ዋናው ቁም ነገር፣ ከእንድ ዘር የሚፈጠሩ ቃላት የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ሊወራረሱ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ነው።

ስለ ስማዊ ሀረግ እስካሁን በዝርዝር ያየነውን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል። ማንኛውም ስማዊ ሀረግ ከመሪ ስም፣ ከመሙሊያ፣ ከተስያዩ ገላጮች እና ከመስተዓምሮች ይመሰረታል። መሪው ስም ከመሙሊያው ጋር ተቀናጅቶ ንዑሱን ሀረግ ይመሰርታል። ይህ ሀረግ ደግሞ ከቅፅላዊና ከተውሳከ ስማዊ ሀረጎች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ አቢዩን ስማዊ ሀረግ ይመስርታል። ይህም አቢይ ሀረግ ከመስተዓምሮች ጋር በመቀናጀት ዋናውን ስማዊ ሀረግ ይፈጥራል። መሪው ስም

ሊዋቀር የሚችለው ከአንድ መሙሊያ ሀረግ ጋር ብቻ ነው። ይህም መሙሊያ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት ነው። ከአቪዩ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩት መስተዓምሮች ሶስት አይነት ናቸው። እነሱም ጠቁዋሚ፣ አገናዛቢና መጠኛ ይባላሉ። ጠቁዋሚው የትኑቱን፣ አገናዛቢው የማንኑቱን፣ መጠኑ ደግሞ መጠኑን ይወስናል። የንዑሱ ሀረግ መሪ ስም ተራ ቃል ነው። ሀረግ ሊሆን የሚችለው በየርከኑ ከመሙሊያና ከገላጭ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀር ነው። ከየተዋቃሪው ሀረግ ሀረጋዊነትን፣ ከመሪው ስም ስማዊነትን ያገኛል። ስሞች መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። መሙሊያ የማይዙት ንዑስ ሀረጋቸውን በመሪው ስም አማካኝነት ብቻ ይመሰርታሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መሪ ስሞች ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ውልድ የሆኑት የተወሰዱበትን ቃል መዋቅራዊ ባህሪ ይወስዳሉ። ቃሉ መሙሊያ የሚወስድ ከሆነ፣ እነሱም መሙሊያ ይወስዳሉ። በዚህም ይህን ንዑስ ክፍል ለጊዜው እንቁዋጫለን። ለጊዜው የምንልበት ምክንያት ወደፊት በሌላ ክፍል ስለምንመለስበት ነው።

ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ንዑስ ክፍል ስሞች ከስማዊ መሙሊያ ሀረግ፣ ከተውሳከ ሰማዊና ቅፅላዊ አነላማሽ ሀረጎች እንዲሁም ከሶስት አይነት መስተዓምሮች ጋር በየደረጃው እየተዋቀሩ ንዑስና አቪይ ስማዊ ሀረጎችን ሊመሰርቱ ተመልክተናል። በዚህ ንዑስ ክፍል፣ ግሶች ልክ እንደ ስሞች ከመሙሊያዎች፣ ከአነላማሾችና ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ንዑስና አቪይ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ እናያለን።

ይህን ለማድረግ ቀና ይሆን ዘንድ፣ ግሶችን በአይነት በአይነታቸው እንከፋፍላቸዋለን። ከትርጉም አንፃር ሊታዩ፣ ግሶች የሁኑትና የድርጊት ተብለው በሁለት ብቻ ሊከፈሉ ይችላሉ። የድርጊት የሚባሉት አንድ ሰው የሚፈፅመውን ተግባር የሚገልፁ ናቸው። መጀመሪያ የሚከተሉትን የድርጊት ግሶች እንይ።

ጠጣ	መጣ	ሄደ	1
ጠረገ	ሰበረ	ቀደደ	

የድርጊት ግሶች ባለቤት አድራጊ፣ ማለትም የድርጊቱ ፈፃሚ ነው። ለምሳሌ፣

ካሳ ብርጭቆ ሰበረ 2

ስንል፣ ካሳ የሚለው ስም የድርጊቱ ፈፃሚ ባለቤት መሆኑን መግለፃችን ነው። ድርጊቱ የተፈፀመው በብርጭቆ ላይ ነው። በለዚህም ብርጭቆ ተደራጊ ወይም ድርጊት ተቀባይ ስም ነው።

የሁኑት ግሶች የሚባሉት፣ እንድ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ሳይሆን፣ እሱ ራሱ የሚሆነውን ነገር ወይም የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም፣ የሚያሳየውን ባህሪ የሚገልፁ ናቸው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

ሆነ	ወፈረ	አዘነ	3
ከሳ	ቀጠነ	ፈዘዘ	

የእነዚህ እይነት ግሶች ባለቤት ሁዋኝ ስም ነው። እድራጊ እይደለም። ስምሳሌ፣

ካሳ አስተማሪ ሆነ 4

ሰንል፣ የምንገልፀው የካሳን አስተማሪ የመሆን ነገር ነው። በዚህም ካሳ አስተማሪ ካስመሆን አስተማሪ ወደ መሆን መስወጡን እንረዳስን። ካሳ ወፈረ ስንልም፣ ካለመወፈር ወደ መወፈር መስወጡን እንገነዘባለን። ግሶቹ የሚገልፁት ድርጊትን ሳይሆን፣ ለውጥን ነው። ባለቤታቸውም የለውጡ ተቀባይ ወይም ተለዋጭ ነው።

ከመዋቅራዊ ባህሪ አኩዋያ ሲታዩ፣ የድርጊትና የሁነት ግሶች የተለያዩ ናቸው። የድርጊት ግሶች ከሚገልፁት ድርጊት ጋር የሚዛመድ መሙሊያ አላቸው። የሁነት ግሶች ግን አንድም መሙሊያ የላቸውም፣ ካላቸውም ከሁኔታው ጋር ሳይሆን፣ ከሁዋኙ ባለቤት ጋር የተገናዘበ ነው። ስምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ብርቱካን ሰላ 5
(ለ) ካሳ ገበሬ ሆነ

በላ የሚለው የድርጊት ግስ መሙሊያ ብርቱካን የሚለው ስም ነው። ይህ ስም የድርጊቱ ተጠቂ (ተደራጊ) ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነት የአድራጊና የተደራጊነት ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ገበሬ የሚለው ስም ሆነ የሚለው ግስ መሙሊያ ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነትም የእቻነት ነው። ሁለቱም የሚጠቁሙት እንድን ነገር ነው። ገበሬው ካሳ ነው፤ ካሳም ገበሬው ነው። በሁለቱ መካከል ልዩነት የለም።

በድርጊትና በሁነት ግሶች መካከል ያለው ሌላው መዋቅራዊ ልዩነት የሚወስዱት የመሙሊያ መጠን ነው። የድርጊት ግሶች አንድ ወይም ሁለት መሙሊያ ሊኖራቸው ይችላል። የሁነት ግሶች መሙሊያ አንድ ብቻ ነው። እሱም ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ራሱ ሁዋኙ ስማዊ ሀረግ ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [ለእስቴር ፕንዘብ ሰጣት] 6
(ለ) ካሳ [ምሳውን በላ]
(መ) ካሳ [ወታደር መስለ]
(ሰ) ካሳ [ከሳ]

ሰጣት የሚለው የድርጊት ግስ ነው። ሁለት መሙሊያዎች አሉት። እነዚህም የተሰመረባቸው ስሞች ናቸው። በላ የሚለውም እንደዚሁ የድርጊት ግስ ነው። ይሁን እንጅ መሙሊያው አንድ ስም ብቻ ነው። እሱም ምሳውን የሚለው ስም ነው። መሰለ የሚለው ደግሞ የሁነት ግስ ሲሆን፣ እሱም በላ እንደሚለው ግስ ባለአንድ መሙሊያ ነው። መሙሊያውም ወታደር የሚለው ስም ነው። በመጨረሻም ከሳ የሚለው ግስ አለ። ይህም እንደ መሰለ የሁነት ግስ ነው። ይሁን እንጅ፣ መሙሊያ የለውም[6]። በጥቅሉ ግሶችን እንደ መሙሊያቸው እይነትና መጠን መከፋፈል ይቻላል። ከዚህ ቀጥሰን የምናሳየው የሀረግ አወቃቀር ይህንን ልዩነት መሰረት ያደረገ ነው።

---


[6] ከዚህ ላይም ካሳ ራሱ መሙሊያ ነው ለማለት ይቻላል። ነገር ላለማከበድ ወደ ዝርዝሩ አንገባም።

ኢሳቢ ግሳዊ ሀረግ

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደሞከርነው፣ ግሶች *መሙሊያ* ያላቸውና የሌላቸው ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። *መሙሊያ* ያላቸው ደግሞ እንደ *መሙሊያው* ብዛት ባለአንድ ወይም ባለሁለት *መሙሊያ* እየተባሉ ሊለዩ ይችላሉ። በተጨማሪም እንደ *መሙሊያቸው* አይነት በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ይኸውም *መሙሊያቸው* ተደራጊ ስማዊ ሀረግ የሆኑና *መሙሊያቸው* ተደራጊ ስማዊ ሀረግ ያልሆኑ ብሉ በመለየት ነው። *መሙሊያቸው* ተደራጊ ስማዊ ሀረግ የሆኑት ላቢ ግሶች ሲባሉ፣ *መሙሊያቸውም* ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይባላል። *መሙሊያ* የሌላቸው ወይም *መሙሊያቸው* ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ያልሆነ ግሶች በጥቅሉ ኢሳቢ ግሶች ይባላሉ። ሀረጉም ኢሳቢ ግሳዊ ሀረግ ይባላል። የሚከተሉትን ስእብነት እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [ደነገጠ] 1
(ለ) ካሳ [ወደ ጎንደር ሄደ]

በመጀመሪያው ምሳሌ <u>ደነገጠ</u> የሚለው የሁነት ግስ *መሙሊያ* የለውም። ስለዚህም የተዋቀረው ከደንጋጩ ባለቤት ከካሳ ጋር ብቻ ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ሄደ</u> የሚለው የድርጊት ግስ <u>ወደ ጎንደር</u> ከሚለው *መሙሊያ* ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። *መሙሊያው* የጉዞውን ድርጊት መድረሻ ያመለክታል። የመድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የሁለቱን ግሶች ንዑስ ሀረግ እወቃቀር በለቆመዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




በግልፅ እንደሚታየው፣ ሁለቱ ግሶች የሚለያዩት *መሙሊያ* በመያዝና ባለመያዝ ነው። ይህ ልዩነት ግን በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ሁለቱም አቢይ ሀረጋቸውን ከተለያዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር በመቀናጀት እንደሚከተለው ይመሰርታሉ።

(ሀ) [[በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ]] 3
(ለ) [[በሀይል] [ደነገጠ]]

---

[7] መስተዋድዳዊ ሀረጎቹን በ*ንኡስ ለለ* መልክ ያስቀመጥናቸው፣ ውስጣዊ አቀነጃጀታቸው ያልታየ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ወደፊትም ሌሎች ያልተተነተኑ ሀረጎችን የምናሰየው በዚሁ መልክ መሆኑን ከወዲሁ እናስገነዝባለን።

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ በድንገት የሚለው ቅንጅት መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፥ ተግባሩ ወደ ጎንደር ሄደ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መግለፅ ነው። አገላለፁም የአካሄዱን ሁኔታ በመወሰን ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥም በሀይል የሚለው እንደዚሁ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፥ ተግባሩ የድንጋጤውን ደረጃ መግለፅ ነው። ሁለቱ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ገላጭ አነጋገሮች ሲሆኑ፥ ሁለቱ ንዑስ ሀረጎች ደግሞ ተገላጭ መሪዎች ናቸው። ከላይ በቅንፍ የሚታየውን የገላጭና የመሪ አቀማመጥ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ምሳሌ (ሀ)ን ብቻ በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



4

በግልፅ እንደሚታየው፥ ወደ ጎንደር የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የግሱ መሙሊያ ሆኖ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን መሰርቶአል። በድንገት የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግም የንዑሱ ሀረግ ገላጭ ሆኖ በመግባት አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አዋቅሮአል። ይህ አቢይ ሀረግ ተጨማሪ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ የሚከተሉትን አንመልከት።


(ሀ) [[ትናንት] [በድንገት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]] 5
(ለ) [[በድንገት] [ትናንት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]]
(መ) [[በመኪና] [ትናንት] [በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ]]

ትናንት፥ በድንገትና በመኪና የሚሉት ሀረጎች ወደ ጎንደር ሄደ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከጊዜ፥ ከሁኔታና ከማድረጊያ አኳያ ይገልፁታል። ቅደም-ተከተላቸውም ሊቀያየር ይችላል። ይህም ሀረጎቹ በተመሳሳይ ርከንና ተግባር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመለክታል። ርከናቸው አቢዩ ሀረግ ሲሆን፥ ተግባራቸው ገላጭነት ነው። ገላጭነታቸውም ለንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ነው። ይህም በስማዊ ሀረጎች ላይ ያየነውን ሁኔታ ሊያስታውሰን ይገባል።

እንደ ምሳሌ 5(ሀ) ያሉ አቢይ ግሳዊ ሀረጎች ከመጣኝ መስተዓምር ጋር በመዋቅር ዋናውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታሉ።

[[እንዴ][[በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ]]] 6

<u>አንዱ</u> የሚለው መጣኝ መስተዓምር በድንገት ወደ ጎንደር የመሄዱ ተግባር በንት ጊዜ እንደ ተፈፀመ ይገልፃል። ዕፀ-መዋቅራዊ ቅርፁን እንደሚከተለው እናሳያለን።



7

<u>ወደ ጎንደር</u> የሚለው መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ መሙሊያ በስሆነ፣ ከመሪው ግስ ጋር ተዋቅሮ፣ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) መስርቶአል። <u>በድንገት</u> የሚለው ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አዋቅሮአል። ይህ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ከመጣኙ መስተዓምር ጋር ሆኖ ዋናውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ)ን መሰርቶአል።

ይህ እንግዲህ በንዑስ ሀረግ ውስጥ የግሱንና የመሙሊያውን፣ በአቢይ ሀረግ ውስጥ የንዑሱን ሀረግና የአነላማሾቹን፣ እንዲሁም የዚህን አቢይ ሀረግና የመስተ-ዓምሩን አገባብ በተመለከተ የተገነዘብነው ነው። ይሁን እንጅ በአቢይ ሀረጉ ውስጥ ሊገኝ የሚችል ሌላም የአነላማሽ አይነት አለ። የእሱን አገባብ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

(ሀ) ካሳ [በርግጥ [በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል]] 8
(ለ) ካሳ]በፍፁም [በመኪና ወደ ትምህርት ቤት አይሄድም[ ]

በምሳሌ (ሀ) <u>በርግጥ</u> የሚለው ተውሳከ ግሳዊ አነላማሽ ነው። ተግባሩ፣ <u>በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል</u> በሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ተግባር ርግጠኝነት መግለፅ ነው። በምሳሌ (ለ)፣ <u>በፍፁም</u> የሚለው እንደዚሁ ተውሳከ

[6] <u>አንዱ</u> የሚለው የመስተዓምራዊ ሀረግ መሪ፣ <u>አንድ ጊዜ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ጉራጅ ነው። በዚህ ቅርፁ መስተዓምራዊ ነው። ሌሎቹም በዚሁ አይነት ሁለቴ፣ ሶስቴ፣ ወዘተ፣ እያሉ መጣኝ የሚሆኑበት ስርዓት አለ። በርዓቱ ሀረጎችን ወደ ተራ ቃልነት የሚለውጥ ነው።

ግሳዊ አነሳሚሽ ሲሆን፣ በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀው ተግባር ሀለት መሆኑን ይገልፃል። እንደነዚህ ያሉ አነሳሚዎች ቀደም ሲል ካየናቸው፣ እንደ በመኪና ካሉት አነሳሚሾች የተለዩ ናቸው። እንደ በመኪና ያሉት በንዑስ ሀረጉ የሚገለፀውን ድርጊት የአፈፃፀም ሁኔታ የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ እነዚህኞቹ ግን የድርጊቱን ሀለትነት ወይም ርግጠኝነት የሚያስታውቁ ናቸው። ይህ ደግሞ የቁምንቁዋው ተናጋሪዎች ስለ ድርጊቱ ያላቸውን አመለካከት የሚገልፅ እንጅ፣ የድርጊቱን ያፈፃፀም ሁኔታ የሚያሳይ አይደለም። የድርጊቱ የአፈፃፀም ሁኔታና በድርጊቱ የሚገለፀው ሀሳብ ውነትነት ወይም ሀሰትነት የተለያዩ ጉደዮች ናቸው።


እንደ በርግጥ ያሉ አነሳሚሾች ከሌሎቹ አነሳሚሾች በግብር ብቻ ሳይሆን፣ በአገባብም የተለዩ ናቸው። እንደ በመኪና ያሉት በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ ብቻ ሲገቡ፣ እንደ በርግጥ ያሉት ግን ከእቢዩ ሀረግ እልፈው ከአረፍተ ነገሩ ጋርም ሲዋቀሩ ይችላሉ። ሲዋቀሩም በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ በመግባት ነው። የሚከተለውን ለአብነት እንመልከት።


[በርግጥ [ካሳ ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል]] 9

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ በርግጥ የሚለው ገላጭ የተዋቀረው [ካሳ ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ነው። ተግባሩም አረፍተ ነገሩ ያዘለውን ሀሳብ ውነትነት መግለፅ ነው። በዚህ አወቃቀር መሰረት ገላጭነቱ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ለእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ሳይሆን፣ ለሙሉው አረፍተ ነገር ነው። ስለዚህም አረፍተ ነገራዊ አነሳሚሽ ሲባል ይችላል። ከዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም እንደ በርግጥ ያሉ አነሳሚዎች መሰረታዊ መዋቅራዊ ቦታ በተራ ቁጥር (8) እንደሚታየው፣ ከእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው? ወይስ በተራ ቁጥር (9) እንደሚታየው፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር? ተግባራቸው የአረፍተ ነገሩን ሀሳብ መግለፅ ከሆነ፣ መሰረታዊ ቦታቸውም በተራ ቁጥር (9) እንደሚታየው፣ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ መሆን አለበት። ይሁን እንጅ፣ የነገሩ ርግጠኝነት ወይም ሀለትነት በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ይዘት ላይ ከሆነ፣ መዋቅራዊ ቦታቸው በተራ ቁጥር (8) እንደሚታየው፣ በዚሁ ሀረግ መነሻ ላይ ይሆናል። ርግጠኝነቱ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀው ሀሳብ ከሆነ፣ የአነሳሚሹ መዋቅራዊ ግንኙነት ከዚሁ ሀረግ ጋር ይሆናል። ስለዚህም እንደ በርግጥ ያሉ አነሳሚሾች መዋቅራዊ ቦታ የረጋ ላይሆን ተለዋዋጭ ነው። እንዴት እንደሚለዋወጥ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል።

(ሀ) [ካሳ [በርግጥ [ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል]]] 10
(ለ) [ካሳ[ትናንት [በርግጥ [ወደ ጎንደር ሄዶአል]]]]

በምሳሌ (ሀ)፣ በርግጥ የሚለው ሀረግ የተዋቀረው ከእሱ ቀጥሎ ከሚገኘው [ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው። ርግጡም ይህ ሀረግ ያዘለው ሀሳብ ነው። በምሳሌ (ለ) ደግሞ፣ ይኸው በርግጥ የሚለው ሀረግ የተዋቀረው [ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው ንዑስ ሀረግ ጋር ነው። ርግጡም ይህ ንዑስ ሀረግ የሚገልፀው ሀሳብ ነው። የአወቃቀሩን ሁኔታ ይብልጥ ግልፅ ለማደረግ ግሳዊ ሀረጎቹን ብቻ በዕፀ-መዋቀር እንደሚከተለው እናሳያለን።





በ11(ሀ) ውስጥ፣ በርግጥ የሚሰው ሀረግ በዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር ተዋቅሮአል። ገላጭነቱም ለአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ነው። በ11(ሰ) ውስጥ ግን ይኸው ሀረግ በአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ስር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን ይገልፃል። ይህን ሊያደርግ የቻለውም ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ወርዶ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር በመዳበል ነው። በ11(ሰ) ውስጥ፣ ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር የሚታየው ነጠብጣብ፣ ሀረጉ ከመውረዱ በፊት የነበረበትን መሰረታዊ ቦታ ያመለክታል።

አረፍተ ነገራዊ ገላጮች ከመሰረታዊ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ ዕድላቸው ከሌሎች ገላጭ ሀረጎች የበለጠ ነው። ሌሎች ገላጮች የሚንቀሳቀሱት በአብዛኛው ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ ነው። አረፍተ ነገራዊ ገላጮች

ግን በተራ ቁጥር (9) ከሚታየው መሰረታዊ ቦታቸው እየተንሱ ወደ አረፍተ ነገሩ መሀል በመግባት፣ ከአቢዩም ሆነ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር የመዳበል፣ እንዲሁም ወደ አረፍተ ነገሩ መድረሻ የመዝለቅ ዕድል አላቸው። ለንፅፅር ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ [በድንገት [ወደ ጎንደር ሄደ]]] 12
(ለ) [በድንገት[ካሳ [— [ወደ ጎንደር ሄደ]]]]

(ሀ) [ምናልባት [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]] 13
(ለ) [ካሳ ምናልባት [በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]]
(መ) [ካሳ በድንገት ምናልባት [ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]]
(ሰ) [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ምናልባት [ሄዶ ይሆናል]]
(ረ) [[ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]፣ ምናልባት]

በምሳሌ 13(ሀ)፣ ምናልባት የሚለው አነሳሚሽ [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮአል። ተግባሩም አረፍተ ነገሩ ያዘለውን ሀሳብ እጠራጣሪነት መግለፅ ነው። በምሳሌ (ለ) [በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (መ) [ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (ሰ) [ሄዶ ይሆናል] የሚለውን መሪ ግስ ይገልፃል። በመጨረሻም፣ በምሳሌ (ረ) እንደገና ሙሉውን አረፍተ ነገር ይገልፃል። ይህ የገላጩ እንቅስቃሴ በምሳሌ 12(ለ) በድንገት የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ከደረገው እንቅስቃሴ እጅግ የሰፋ ነው። ይህም አረፍተ ነገራዊ ገላጮች ከግሳዊ ሀረግ ገላጮች የሚለዩበት ዋና ባህሪ ነው። እንደ ልብ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ይንሸራሸራሉ። ይህ ሁኔታ ቃለ አጋኖዎችን ሊያስታውሰን ይገባል። አነሱም አንደዚሁ የትሜ ናቸውና።

ሌላው በሁለቱ ገላጮች መካከል ያለው ልዩነት ወደ ስማዊ ሀረግነት ሲለወጡ የአዛማጅ አረፍተ ነገር መሪ ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። የግሳዊ ሀረግ አነሳሚሾች የአዛማጅ አረፍተ ነገር መሪ ለመሆን ሲችሉ፣ አረፍተ ነገራዊ ገላጮች ግን ይህን ማድረግ አይችሉም። ይህን ልዩነት ከሚከተሉት ምሳሌዎች ንፅፅር መገንዘብ ይቻላል።

(ሀ) ካሳ በመኪና ወደ ትምህርት ይሄዳል 14
(ለ) ካሳ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድበት መኪና

(ሀ) ካሳ በርግጥ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል። 15
(ለ) * ካሳ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድበት ርግጥ

በምሳሌ 14(ሀ) ውስጥ በመኪና የሚለው የግሳዊ ሀረግ ገሳጭ፣ በምሳሌ 14(ለ) የሚሄድበት መኪና ወደሚል ስማዊ ሀረግ መለወጥ ችሎአል። የሚሄድበት የሚለው

አዛማጅ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ *መሪው* <u>መኪና</u> የሚለው ስም ነው። በምሳሌ 15(ሀ) ውስጥ፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ ግን፣ በ15(ለ) ውስጥ እንደሚታየው ወደ ስማዊ ሀረግነት ሊለወጥ አልቻለም። ይህም በአረፍተ ነገራዊ ገላጮችና በግሳዊ ሀረግ ገላጮች መካከል ላለው ልዩነት ተጨማሪ ማስረጃ ነው። የግሳዊ ሀረግ ገላጮች ብቻ ወደ ስማዊ ሀረግነት የመለወጥ ችሎታ አላቸው።

እንደ <u>ምናልባት</u> ያሉ አረፍተ ነገራዊ ገላጮች፣ እንደ <u>በመኪና</u> ካሉ ከግሳዊ ሀረግ ገላጮች የሚለዩበት ሌላም ሰዋስዋዊ ባህሪ አለ። ይህም አፅንዖት ነው። የግሳዊ ሀረጎች የተለየ ባህሪ ይመለላል። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካለ ምናልባት በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ ይሆናል] 16
(ለ) <u>በመኪና</u> ነው [ካለ ምናልባት ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]
(መ) ? <u>ምናልባት</u> ነው [ካለ በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]

ምሳሌ (ሀ) በለሆሳስ (ያለአፅንዖት) የተነገረ አረፍተ ነገር ነው። ምሳሌ (ለ)፣ <u>በመኪና</u> የሚለው የግሳዊ ሀረግ ገላጭ በአፅንዖት የተነገረበት አረፍተ ነገር ነው። ሀረጉ አፅንዖት ያገኘው፣ <u>ነው</u> ከሚለው ግስ *ጋር* ተዋቅሮ በአረፍተ ነገሩ *መነሻ* ላይ በመገኘቱ ነው። በዚህም ምክንያት ይህ ሀረግ ያዘለው ሀሳብ ከሌሎቹ የበለጠ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል። በምሳሌ (መ)፣ በተመሳሳይ ሁኔታና ቦታ፣ <u>ምናልባት</u> የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ፣ <u>ነው</u> ከሚለው ግስ *ጋር* ተዋቅሮ ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ የአረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አጠያያቂ ሆኖአል። ከዚህም አረፍተ ነገራዊ ገላጮች አፅንዖታዊ *መዋቅር* እንደሌላቸው፣ ማለትም በአፅንዖት ሊነገሩ እንደማይችሉ *መገንዘብ* ይቻላል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየናቸው ሁኔታዎች የሚያመለክቱት፣ እንደ <u>ምናልባት</u> ያሉ ሀረጎች እንደ <u>በመኪና</u> ካሉት በእጅጉ የተለዩ *መሆናቸውን* ነው። ልዩነታቸው ያገባብ ብቻ ሳይሆን፣ የተግባርም ነው። እንደ <u>ምናልባት</u> ያሉት ሀረጎች የሚገልፁት፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ሁኔታ ሳይሆን፣ የድርጊቱን ውነትነት ወይም አጠራጣሪነት ነው። ይህ ደግሞ እንደየግለሰቡ ሊለያይ የሚችል የዕምነት ወይም የስሜት ጉዳይ ነው። በዚህም ምክንያት እንዱ ውነት የሚለውን፣ ሌላው ሀሰት ሲለው ይችላል። ስለዚህም እንደዚህ ያሉትን ከግል ስሜት *ጋር* የሚያያዙ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎችን ከሌሎች ሀረጎች ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ከፍ ሲል ያየነው ያወቃቀር ልዩነትም ይህን የሚያጠናክር ነው። እንደ <u>ምናልባት</u> ያሉ ሀረጎች መሰረታዊ *መዋቅራዊ* ዝምድና ከአረፍተ ነገሩ *ጋር* ሲሆን፣ እንደ <u>በመኪና</u> ያሉት ከግሳዊ ሀረጉ *ጋር* ነው። ለለዚህም በመካከላቸው የርከን ልዩነት አለ።

በዚህ ንዑስ ክፍል እስካሁን የተመለከትነው የኢሳቢ ግሳዊ ሀረግን ውስጣዊ ያወቃቀር ስርዓት ነው። ኢሳቢ ግሶች *መሙሊያ* ሀረግ ሊኖራቸው እንደሚችልና ከዚህም ሀረግ *ጋር* ንዑስ ግሳዊ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ አይተናል። *መሙሊያው* ሀረግ ድርጊት ተቀባይ ወይም ተባቢ ስማዊ ሀረግ እንደማይሆንም ተመልክተናል። ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ

ሀረጎች ጋር እየተዋቀረ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ እንደሚመሰርት ገልፀናል። አቢይ ሀረጉም በተራው ከመጣኝ መሰተዓምር ጋር ተቀናጅቶ ከፍተኛውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሲመሰርት አይተናል። በመጨረሻም እረፍተ ነገራዊ ግሳጮች ያልናቸው፣ ያንድን ሀረግ ወይም እረፍተ ነገር ሀሳብ ውነትነት ወይም ሀስትነት የሚገልፁ ሀረጎችን ባሀሪ ከግሳዊ ሀረግ ግሳጮች ጋር እያነፃፀርን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥሰን ደግሞ የሳቢ ግሳዊ ሀረጎችን ስርዓት እንመለከታለን።

ሳቢ ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ንዑስ ክፍል መግቢያ አካባቢ እንደተገለፀው፣ ሳቢ ግሶች የሚባሉት የድርጊት ግሶች ናቸው። ድርጊቱ የሚፈፀመው በአድራጊ ነው። የሚፈፀመውም በተደራጊ ላይ ነው። አድራጊና ተደራጊ በሰማዊ ሀረግ መልክ ይከሰታሉ። ተደራጊው ሰማዊ ሀረግ ተሳቢ ይባላል። ተሳቢነቱም ለሳቢው ግስ ነው። ሳቢና ተሳቢ እንድ ላይ ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግን ይመስርታሉ። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ካሳ [ልጁን ገረፈው] 1
(ለ) አስቴር [እንቁላሉን ሰበረችው]

በሠላቱም ምሳሌዎች ውስጥ፣ በየቅንፉ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች ንዑስ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። የመዋቅሮቹ መሪዎች ግሶቹ ናቸው። ሳቢ ሰለሆኑም መሙሊያዎቻቸው ተሳቢ ስማዊ ሀረጎች ናቸው። ተሳቢ ናቸው የምንልበት ምክንያት፣ ለተሳቢነት ምልክት ናቸው የሚባሉትን መስፈርቶች ስለሚያሙዋሉ ነው። መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

(ሀ) ስማዊ ሀረጉ ከሳቢ ግስ ጋር የሚዋቀር ከሆነ፣
(ለ) ከሳቢ ግስ ጋር ሲዋቀር፣ በግሱ አምድ ላይ የራሱን አፀፋ ካስከተለ፣
(መ) /-ን/ የሚለውን ምዕላድ በመድረሻው ላይ ካሳየ፣
(ሰ) ግሱ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ የዚሁ ግስ ባስቤት ሆኖ መሣባት ከቻለ፣
(ረ) በግሱ ሰተገለፀው ድርጊት ተደራጊ ወይም ተጠቂ ከሆነ።

ከነዚህ መስፈርቶች አንፃር በ1(ሀ) ውስጥ የሚታየውን፣ ልጁን የሚለውን ስማዊ ሀረግ አንመርምረው። ሀረጉ ገረፈው ከሚለው ሳቢ ግስ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። በግሱ መደረሻ ላይ /-አ/ የሚል ቅጣይ ምዕላድ አለ። ይህ ምዕላድ ልጁ የሚለው ስማዊ ሀረግ አፀፋ ነው። የሚያመሰከተው የዚህን ተሳቢ ሀረግ መሪ መደብ፣ ቁጥርና ፆታ ነው። በስሙ መድረሻ ላይ /-ን/ የሚል ቅጣይ ምዕላድ ይታያል። ይህም ስማዊ ሀረጉ ተሳቢ ስመሆኑ ምልክት ነው። ግሱ ተደራጊ ሲሆን፣ ቅርፁ ተገረፈ

የሚል ይሆናል። ልጁ የሚለው ተሳቢ ሀረግም የዚህ ግስ ባለቤት ሆኖ እንደሚከተለው ሊገባ ይችላል።

ልጁ ተገረፈ 2

በመጨረሻም፣ በምሳሌ 1(ሀ)ም ሆነ በምሳሌ (2) ልጁ የሚለው ስማዊ ሀረግ ግሱ የሚገልፀው ድርጊት ተጠቂ ነው። ርግጥ፣ ይህ መስፈርት ትርጉማዊ ነው። ስለሆነም አገደ ሌሎቹ መስፈርቶች በቅርፅ ወይም በአገባብ ሊረጋገጥ አይችልም።

በዚህ አይነት ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ስማዊ ሀረግ ሁሉ ተሳቢ ሊባል፣ ከአገደዚህ ያለ ሰም ጋር የሚዋቀር ግስም ሳቢ ይባላል። ሳቢና ተሳቢ አንድ አካል በመሆን ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ግሱ የሀረጉ መሪ ሲሆን፣ ስማዊ ሀረጉ (ተሳቢው) መሙሊያው ነው። ስለ መሙሊያ ቀደም ሲል ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ የጠቀስነውን እናስታውስ። መሪው ግስ ሙሉ ሀሳብ እንዲሰጥ የሚያደርጉ ሀረጎች ናቸው።

ከፍ ሲል ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ፦ን/ የምትለዋን ምዕላድ ሊያስከትል እንደሚችል ገልፀናል። ይህች ምዕላድ ግን ሁል ጊዜ ተሳቢን ላታመለክት ትችላለች። የሚከተለውን አንመልከት።

ካሳ አገሩን ሄደ 3

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ አገሩን የሚለው ሀረግ ሄደ ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ አገሩን ሄደ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። ፦ን/ የምትሰዋ ምዕላድም አገሩ ከሚለው ስማዊ ሀረግ መድረሻ ላይ ተቀጥላለች። ይሁን እንጅ፣ አገሩ የሚለው ስማዊ ሀረግ ተሳቢ አይደለም። ምክንያቱም ግሱ ሳቢ አይደለም። ስማዊ ሀረጉ ተሳቢ ካልሆነ፣ ምዕላድዋን ለምን አስከተለ?

ርግጥ ነው፣ ግሱ ሳቢ አይደለም። የሚያመለክተውም አንድ ሰው አንድ ድርጊት በሌላ አካል ላይ ሲፈፅም ሳይሆን፣ ራሱ የሚያደርገውን አንቅስቃሴ ነው። ስለዚህም እንደ ሄደ ያሉ ግሶች የእንቅስቃሴ ግሶች ይባላሉ። የእንቅስቃሴውን መድረሻ ቦታ የሚገልፅ ሀረግ በመሙሊያነት ይፈልጋሉ። የዚህ አይነት ተግባር ያለው ሀረግ ደግሞ ስማዊ ሳይሆን የመድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መስተዋድዳም ፦ን/ ነው። በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ ያለው ተግባር ወደ ከሚለው መስተዋድድ ተግባር ጋር አንድ ነው። ስለዚህም አገሩን ሄደ በማለት ፋንታ፣ ወደ አገሩ ሄደ ማለት ይቻላል። ከዚህ ሁኔታ ሁለት ፦ን/ዎች አንዳሉ አንረዳለን። አንዱ ተሳቢነትን የሚያመለክት ምዕላድ ሲሆን፣ ሌላው ይዋም መድረሻን የሚያመለክት

መስተዋድድ ነው[9]። ሁኔታው ሞክሼ ምዕላዶች በቁዋንቁዋው ውስጥ በብዛት እንዳሉ ቀደም ሲል የገለፅነውን ሊያስታውሰን ይችላል። ወደ ሳቢ ግሶች እንመለስ።

ሳቢ ግሶች በሁለት ይከፈላሉ። አከፋፈላቸውም በሚፈልጉት የተሳቢ ብዛትና አይነት ላይ የተመሰረተ ነው። በአንድ በኩል፣ አንድ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ የሚፈልጉ አሉ። እነዚህም ከፍ ሲል ያየናቸው እንደ <u>ገረፈ</u> እና <u>ሰደበ</u> ያሉት ሲሆኑ፣ ሁለት ተሳቢ የሚፈልጉት ደግሞ እንደ <u>ሰጠ</u> እና <u>ነገረ</u> ያሉት ናቸው። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ <u>ለተማሪዋ ገንዘብ</u> ሰጣት 4
(ለ) ካሳ <u>ለተማሪዋ ወሬ</u> ነገራት

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ የተስመረባቸው ሀረጎች ተሳቢዎች ናቸው። በቀጥታ ከግሱ በስተግራ የሚገኙት (ገንዘብና ወሬ) ስማዊ ሀረጎች ሲሆኑ፣ ከእነሱ በስተግራ የሚገኘውና <u>ለተማሪዋ</u> የሚለው ሀረግ ስማዊ ሳይሆን፣ መስተዋድዳዊ ነው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሁለቱ ሀረጎች ርቱዕና ኢርቱዕ ተሳቢዎች በመባል ይታወቃሉ። ትርጉማቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ማለት ነው። ርቱዕ የሚባለው ስማዊ ሀረጉ ሲሆን፣ ኢርቱዕ ደግሞ መስተዋድዳዊው ሀረግ ነው። ኢርቱዕ የተባለበት ምክንያት ስማዊ ሀረጉ ከግሱ ጋር ያለው መዋቅራዊ ግንኙነት በቀጥታ ሳይሆን፣ በመስተዋድዳዊው ሀረግ በኩል በመሆኑ ነው።

እንደነዚህ ያሉ ምሳሌዎች የተሙዋላ ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉት ሁለቱም ተሳቢዎች በቦታቸው ሲገኙና ከግሱ ጋር ሲዋቀሩ ብቻ ነው። ለምሳሌ ከላይ በተራ ቁጥር 4(ሀ) የሚታየውን አረፍተ ነገር እንደሚከተለው እናስቀምጠው።

?ካሳ ለተማሪዋ — ሰጣት 5

የዚህ አረፍተ ነገር ተቀባይነት አጠራጣሪ ነው ፣ ምክንያቱ ከሁለት ተሳቢዎች አንዱ በቦታው አለመገኘቱ ነው። በቦታው ያልተገኘው ሀረግ ርቱዕው ተሳቢ ነው። ባለመገኘቱም አረፍተ ነገሩ የተሙዋላ ሀሳብ ሊሰጥ አልቻለም። እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር በንግግር መካከል ሲመጣ፣ የጎደለውን ሀሳብ ከአጠቃላዩ የነገር አካሄድ ማወቅ ስለሚቻል፣ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል። የንግግር መጀመሪያ ሊሆን ወይም ብቻውን ሊነገር ግን ፈፅሞ አይችልም።

---

[9] /-ን/ መድረሻን ብቻ ሳይሆን ሌሎች መስተዋድዶችንም ወክላ ልትገባ ትችላለች። ለምሳሌ የሚከተለውን አንመልከት።

አስቴር ብዕሩን ደብዳቤ ጎረችበት

ስለዚህ ምሳሌ /-ን/ ማድረጊያ መስተዋድድ ነች። ለዚህ ማሰረጃው ይህኑ አረፍተ ነገር፣

አስቴር በብዕሩ ደብዳቤ ጎረችበት

ማለት፣ የሚቻል መሆኑ ነው። ሁኔታው /-ን/ ተውላጠ መስተዋድድ ነች የሚያሰኝ ነው።

የሁለቱ ተሳቢ ሀረጎች መሰረታዊ እገባብ በተራ ቁጥር (4) እንደሚታየው ነው። ይሁን እንጅ ይህ አገባብ ሊፋለስ ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ምሳሌ 4(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ ገንዘብ ለተማሪዋ ሰጣት 6

በዚህ ምሳሌ ውስጥ ርቱዕ ተሳቢ ከኢርቱዕ ተሳቢ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ በመሆኑ ግን የትርጉም ለውጥ አልተከሰተም። ተሳቢዎቹ ያለትርጉም ለውጥ ቦታ መለዋወጣቸው በእንድ ርከን ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ሊያሳይ ይችላል። ይህን ቀደም ሲል ስለ አጎላማሽ ሀረጎች በንወያይ ተመልክተነዋል።

ተሳቢ ሀረጎች ከአጎላማሽ ሀረጎች የሚለዩት በሁለት ሁኔታዎች ነው። እነዚህም (1) በቀጥታ ከግስ ጋር የሚዋቀሩ መሙሊያ፣ ብሌም ተሳቢ መሆናቸውና (2) ወደ ስማዊ ሀረግነት ሲለወጡ በአዛማጁ ግስ ላይ መሰተዋድዳዊ አፀፋ አለማሳየታቸው ነው። መስተዋድዳዊ አፀፋ ማሳየት የአጎላማሾች አይነተኛ ባህሪ ነው። ከዚህ እንባር በተራ ቁጥር (8) የተሰጠው አረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ሲለወጥ የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ ገንዘብ የለጣት ተማሪ 7


በተራ ቁጥር (6) ውስጥ፣ <u>ለተማሪዋ</u> የነበረው መስተዋድዳዊ ሀረግ በ(7) ውስጥ የአዛማጁ ሀረግ መሪ በመሆን ወደ <u>ተማሪ</u> ተለውጠአል። በአዛማጁ ግስ ውስጥም ምንም የመስተዋድድ አፀፋ የለም። <u>ለተማሪዋ</u> የሚለው ሀረግ አጎላማሽ ሲሆን ኖር፣ በአዛማጁ ግስ ውስጥ የመስተዋድድ አፀፋ ይታይ ነበር። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

(ሀ) ካሳ <u>ከተማሪዋ ላይ</u> ገንዘብ ወሰደ 8

(ለ) ካባ ገንዘብ የወሰደ<u>ባት</u> ተማሪ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ <u>ከተማሪዋ ላይ</u> የሚለው አጎላማሽ መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ በሚታየው የአዛማጅ ግስ ላይ /-ብአት/ በሚል አፀፋ ተመልክቶአል። ይህም፣ በአዛማጅ አረፍተ ነገር ግስ ላይ በመስተዋድድ አፀፋ መጠቀስ፣ የአጎላማሽ ሀረግ ባህሪ ነው ያልነውን ያረጋግጣል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ርቱዕና ኢርቱዕ ተሳቢዎች ከመሪ ግስ ጋር ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። አመሰራረቱን በሚከተለው ዕፀ-መዋቀር እናሳያለን።



ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። የሚገልፀውም ገንዘብ ለተማሪዋ የመስጠትን ድርጊት ብቻ ነው። የሰጭውን ማንነት፣ የአሰጣጡን ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታ፣ ምክንያት፣ ወዘተ፣ አይገልፅም። እንደዚህ ያሉትን ተጨማሪ መረጃዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ልዩ ልዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ወይም ወደፊት እንደምናየው ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ከንዑሱ ሀረግ በፊት እንደሚከተለው ማስገባት ያስፈልጋል።


[በፖስታ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት]] 10

<u>በፖስታ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ መሰረታዊው ቦታው ነው። በዚህ ቦታ ሆኖ ገንዘቡ የተሰጠበትን ዘዴ ወይም መንገድ ይገልፃል።

አንዳንድ ጊዜ ተሳቢዎቹ ሀረጎች እየቀደሙት ሊገቡ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የሀረጎቹ ቅደም- ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል።

(ሀ) ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ [በፖስታ|– – ሰጣት]] 11
(ለ) ብዙ ገንዘብ ለተማሪዋ [በፖስታ|– – ሰጣት]]

በግልፅ እንደሚታየው፣ ተሳቢዎቹ ሀረጎች በአጠቃላይ የተመለከተውን መሰረታዊ ቦታቸውን ለቀው፣ <u>በፖስታ</u> የሚለውን ግሳዊ ሀረግ በመቅደም፣ ከሀረጉ ውጭ ሆነዋል። ይህ እንቅብ በአጠቃቀም ጊዜ ለሀረጎቹ እፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ የሚታይ ነው። በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን የሀረጎቹን መሰረታዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



12


ይህ መለረታዊው የመሙሊያዎቹ (የተሳቢዎቹ) እና የአሳላጩ ሀረግ አተጋገዮ ነው[10]። መሙሊያዎቹ ይህን መለረታዊ ቦታቸውን እየለቀቁ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከሠረጉ ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በመለረታዊው አወቃቀር ደረጃ፣ ይህ አዚይ ሀረግ መጣኝ መስተዓምር ያስፈልገዋል። መስተዓምሩ የሚዋቀረው ከአዚዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር ነው። ይህ ሲሆን፣ በተራ ቁጥር (10) የሚታየው ሀረግ የሚከተለውን ይመስላል።

[ሁለት ጊዜ [በፖሰታ ስተግሪዋ ብዙ ገንዘብ ሱዛት]] 13

ይህ ያወቃቀር ስርዓት ባለፈው ንዑስ ከፍል ከየነው ከኢሳቢ ግሶች ያወቃቀር ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነት ቢኖር፣ መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ፣ እንጂ በመሙሊያው አይነትና ተግባር ላይ ነው። ሳቢ ግሶች መሙሊያ ሀረግ የግድ ያስፈልጋቸዋል፣ መሙሊያ ሀረጉም ስማዊና መስተዋድዳዊ ሊሆን፣ ተግባሩ ተሟልቶ ነው። በተራ ቁጥር (13) የተመለከተው አዚይ ሀረግ በዕፀ-መዋቅር ሊታይ የሚከተለውን ይመስላል።

---

[10] መለረታዊው አገባብ ርዕሱ ተሳቢ ቀድሞ፣ ኢርዕሱ አሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው፣ ለማለት ይቻላል። ተዋረዳዊ አቀማመጣቸውም ከዕፀ መዋቅር (9) እንደሚታየው ሶስትዮሽ ሳይሆን ሁለትዮሽ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል። ይህም ከትውረት አንፃር ነው። ለጊዜው ወደ ዝርዘሩ አንገባም።




ይህ የተሙዋላ ሀሳብ ያዘለ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ላይ ሊጨመር የሚችለው ገንዘብ የመስጠቱን ተግባር የሚፈፅመውን ሰው የሚጠቁም ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ ከዚህ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀር የምናገኘው አንደሚከተለው ያለ አረፍተ ነገርን ነው።

[ያ ልጅ [ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 15

በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው፣ አቢዩ ግሳዊ ሀረግ ነው። በውጪኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው የድርጊቱን ፈፃሚ የሚያመለክተው ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አረፍተ ነገሩ የተሙዋላ ሀሳብ ይሰጣል። ይህን ሀሳብ የሚያጠራጥር ወይም የሚያረጋግጥ ሀረግ መጨመር ይቻላል። ሀረጉም የሚዋቀረው ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ከአጠቃለዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው። ይህም ሲሆን፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር የሚከተለውን ይመስላል።

[በርግጥ [ያ ልጅ ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 16

<u>በርግጥ</u> የሚለው አረጋጋጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ ውጭ ነው። ከዚህ ቦታ ሳይ ሆኖ፣ ሙሉ አረፍተ ነገሩን ያጎላምሳል። ስለዚህም ነው ቀደም ሲል፣ አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ነው ያልነው። ከአረፍተ ነገሩ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ዝምድና እንደሚከተለው እናሳያለን።



በርግጥ ያ ልጅ ሁሰት ጊዜ በፖሰታ ለተማሪዋ በዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል

አረፍተ ነገራዊ አጎላማሾች ከግሳዊ ሀረግ አጎላማሾች የሚለዩባቸው ሁለት ባህሪያት እንዳሉዋቸው ቀደም ሲል ገልፀናል። እነዚህም ወደ ስማዊ ሀረግ ሊለወጡ አለመቻላቸውና በአረፍተ ነገሩ ውስጥ እንደ ልብ ሲንቀሳቀሱ መቻላቸው ናቸው። ይህ ሁኔታ በሚከተሉት ምሳሌዎችም ይታያል፡

(ሀ) ያ ልጅ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖሰታ</u> 18
(ለ) *ያ ልጅ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ርግጥ</u>

<u>በፖሰታ</u> የሚለው የግሳዊ ሀረግ አጎላማሽ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖሰታ</u> ወደሚል ስማዊ ሀረግ መለወጥ ሲችል፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ግን ይህን ማድረግ አንዳልቻለ፣ የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ማጣት ምልክት ነው።

የአረፍተ ነገራዊ አጎላማሾችን የእንደልብ እንቅስቃሴ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ያ ልጅ <u>በርግጥ</u> [በፖሰታ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል] 19
(ለ) ያ ልጅ በፖሰታ <u>በርግጥ</u> [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]
(መ) ያ ልጅ በፖሰታ ለተማሪዋ <u>በርግጥ</u> [ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]
(ሰ) ያ ልጅ በፖሰታ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>በርግጥ</u> [ሰጥቶአታል]
(ረ) [ያ ልጅ በፖሰታ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]፣ <u>በርግጥ</u>

በርግጥ የሚለው ሀረግ በተራ ቁጥር (16) ከሚታይበት መሰረታዊ ቦታው በመነሳት፣ ሁሉንም ሀረግ እያቁዋረጠ እስከ አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ድረስ እንደሄደ ማየት ይቻላል። በተራ ቁጥር (16) ሙሉውን አረፍተ ነገር ያካትላል። በተራ ቁጥር (19) ግን ከሚገኝበት ቦታ ቀጥሎ ያለውን ሀረግ ብቻ ያጎላምላል። በ19(ረ) ውስጥ፣ በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ቢገኝም፣ የሚያጎላምሰው ሙሉውን አረፍተ ነገር ነው። ርግጥ፣ አጎለማመሱ በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ ሆኖ እንደሚፈፅመው አይደለም፣ ጥንካሬ ይጎለዋል። ማንኛውም በመጨረሻ የሚነገር፣ አንድም መጀመሪያ ተረስቶ ድንገት ትውሰ ያለ፣ እለያም አፅንያት ሊሰጠው ያልተፈለገ ነገር ነው።

ወደ መግቢያው አካባቢ፣ ግሶችን የድርጊትና የሁኔት ብለን በሁለት ከፍለን ነበር። እሰካሁን ያየነው የድርጊት ግሶችን መዋቅራዊ ባህሪ ብቻ ነው። እነሱንም ኢሳቢና ሳቢ ብለን በሁለት ንዑስ ክፍሎች በመለየት ከንዑስ እስከ እዚይ ሀረግ ድረስ ያለውን ያወቃቀር ስርዓታቸውን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የሁኔት ግሶችን ባህሪ እንመረምራለን።

የመሆን ግስ ሀረግ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የመሆን ግስ የሚባሉት ድርጊትን ሳይሆን፣ ሁኔትን ወይም በአንድ ቦታ መገኘትን ያመለክታሉ። ባለቤታቸው ሁዋኝ ወይም ነዋሪ ስማዊ ሀረግ ነው። ሁኔትን የሚያመለክቱት ባለቤቱን ስማዊ ሀረግ በአቻነት የሚገልፅ መሙሊያ ይፈልጋሉ። ኑረትን (መኖርን) የሚያመለክቱት ነዋሪው ባለቤት የሚገኝበትን ቦታ የሚያመለክት መሰተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አበተማሪ ሆነ (1)
(ለ) ካሳ ጎበዝ ሆነ
(መ) ካሳ አስተማሪ ነው
(ሰ) ካሳ ጎበዝ ነው
(ረ) ካሳ አስተማሪ ያመስላል
(ሸ) ካሳ ጎበዝ ይመስላል
(ቀ) ካሳ ቤት ውስጥ አለ

ሆነ፣ ይመስላል እና ነው እንድ ነገር መሆንን ስለሚያመለክቱ፣ የመሆን ግስ ናቸው። አለ የሚለው በአንድ ቦታ መገኘትን ስለሚያመለክት፣ የመኖር ግስ ነው። መኖርና መሆን ተቀራራቢ ናቸው። ለምሳሌ፣ እንድን ሰው ' ናአዚ ሀ ሁን ' ስንል፣ እዚህ ቦታ ተቀመጥ ወይም ተገኝ ማለታችን ነው። እዚያ ቦታ ሲቀመጥ ወይም ሲገኝ ደግሞ፣ እዚህ አለ እንላለን። በዚህ ምክንያት ሁለቱንም እይነት ግሶች በእንድ ስም የመሆን ግሶች እንሳቸዋለን።

መዋቅራዊ ልዩነት ግን እላቸው፣ ይኸውም፣ የመኖር ግሶች ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ለመመስረት መሰተዋድዳዊ ሀረግ ሲፈለጉ፣ የመሆን ግሶች ቅፅላዊ ወይም ስማዊ ሀረግ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው። የሀረጎቹ ተግባርም እንደዚሁ ይለያያል። የመሆን

ግስ መሙሊያዎች ሁዋኙን ባለቤት በአቻነት ሲገልፁ፣ የመናር ግስ መሙሊያዎች መገኛ አድራሻውን ያመለክታሉ።

ከዚህ ላይ የመናር ግስን በሚመለከት አንድ ተጨማሪ ተጣር ማንሳት ያስፈለጋል። ይኸውም የአንድን ነገር የመናር ዓላማ የሚመለከት ነው። አንድ ነገር ዝም ብሎ ሊናር፣ ወይም ስለአንድ ሌላ ነገር ጠቃሚ ሆኖ ሊናር ይችላል። እንደዚሁ ዝም ብሎ የሚናረውን፣ ለተለየ ጥቅም ወይም አላማ ከሚናረው መለየት ያስፈልጋል። ለተለየ ጥቅም የሚናረው፣ ለማን እንደሚናር የሚያሳይ መዋቅራዊ ስርዓት አለ። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።


(ሀ) አሸዋ መንገድ ላይ አሰ 2
(ለ) አሸዋ መንገድ ላይ አለኝ

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ የአሸዋን በመንገድ ላይ መገኘት ብቻ ያመለክታል። ሁለተኛው አሸዋው ባለቤት (ባለንብረት) እንዳለው ያሳያል። "አለኝ" የሚሰውም ለው ባለንብረቱ ነው። ምሳሌ (ለ) ባለንብረቱን ጨምሮ ሲነገር ላዕላይ ቅርፁ የሚከተለውን ይመስላል[11]።

እኔ አሸዋ መንገድ ላይ አለኝ 3

ወደ ግሶቹ ያወቃቀር ስርዓት እንመለስ። የመሆን ግሶች ሰማዊ ወይም ቅፅላዊ ሀረግን መሙሊያ አድርገው ንዑስ ግሳዊ ሀረጋቸውን ይመሰርታሉ። ከላይ ከተራ ቁጥር 1(ሀ-ሸ) የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች ንዑስ ሀረግ እንደሚከተለው አጠቃሰን በአንድ ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።

ግሀ1 4



ቀደም ሲል እንዳየናቸው ግሳዊ ሀረጎች ሁሉ፣ ይህም ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ አገላማሾች ጋር እየተዋቀረ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

(ሀ) [አምና [ነበረ ነበር]] 5
(ለ) [አሁን [ቤት ውስጥ አለ]]

[11] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ባየ (1997)ን ይመልከቱ።

በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>አምና</u> እና <u>አሁን</u> የሚሉት ጊዜን የሚያመለክቱ ተውሳክ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት ንዑስ ግሳዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው አቢይን ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል። ተግባራቸው በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ሁነት ከጊዜ አንፃር እየገለፁ ንዑሱን ሀረግ ማጎላመስ ነው። ቦታቸውም ከመሙሊያው በፊት፣ ማለትም በስተግራ፣ ነው። መሙሊያውን ተከትለው ቢገቡ፣ የሀረጉ ተቀባይነት ይቀንሳል። የሚከተለውን እንመልከት።

(ሀ) * ጎበዝ [አምና[— ነበር] [6
(ለ) ገቤት ውስጥ [አሁን [--- አለ]]


<u>ጎበዝ</u> እና <u>ቤት ውስጥ</u> የሚሉት መሙሊያ ሀረጎች ናቸው። መለረታዊ ቦታቸው በንጠባጣቢ የተመለከተው ነው። ይሁን እንጅ፣ ከዚህ መሰረታዊ ቦታ ተንስተው አጎላማሾቹን ስሞች በመቅድም በአቢዩ ሀረግ መነሻ ሳይ ሊገቡ ችለዋል። ይህም በመሆኑ የሀረጎቹ ተቀባይነት በእጅጉ ቀንሶአል። ሁኔታው መሙሊያ ሀረጎች ከመሪው ግስ መለየት አይችሉም ያልነውን የሚያጠናክር ማስረጃ ነው።

ቀደም ሲል እንዳየናቸው የድርጊት ግሶች ሁሉ፣ አቢይ የመሆን ግሳዊ ሀረጎችም ከመጣኝ መስተዓምር ጋር እንደሚከተለው ሊዋቀሩ ይችላሉ።

[እንድ ጊዜ [ጎሻም ውስጥ [አስተማሪ ነበር]]] 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>አስተማሪ</u> የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ነው። <u>ጎሻም ውስጥ</u> የሚለውም ቦታን የሚገልፅ አጎላማሽ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። <u>አንድ ጊዜ</u> የሚለው ደግሞ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊሆን፣ በጎሻም ውስጥ አስተማሪ ሆኖ የናረበትን የጊዜ መጠን ይገልፃል። አጠቃላይ መዋቅሩ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሲሆን፣ በዕፀ-መዋቅር በወርድና ተዋረድ ተተንትኖ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።

8



ይህ አቢይ ሀረግ ሁዋኙን ባስቤት ከሚገልፀው ስማዊ ሀረግ ጋር እየተዋቀረ፣ ሙሉ ሀሳብ የሚሰጥ አረፍተ ነገርን ይመሰርታል። አረፍተ ነገሩም የሀሳቡን ርግጠኝነት ወይም አጠራጣሪነት ከሚገልው አረጋጋጭ ወይም አጠራጣሪ አነላማሾች ጋር እንደሚከተሰው ሊዋቀር ይችላል።

(ሀ) [ያ ሰውየ [አንድ ጊዜ ጎኛም ውስጥ አስተማሪ ነበር]] 9
(ለ) [በርግጥ [ያ ሰውየ [አንድ ጊዜ ጎኛም ውስጥ አስተማሪ ነበር]]]

የመጀመሪያው ምሳሌ [አንድ ጊዜ ጎኛም ውስጥ አስተማሪ ነበር] የሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ፣ [ያ ሰውየ] ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገር መስርቶአል። ይህ አረፍተ ነገር [በርግጥ] ከሚለው አረጋጋጭ አረፍተ ነገራዊ አነላማሽ ጋር ተዋቅሮአል። የአነላማሹ መስረታዊ ቅንጅት ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው። ይሁን እንጅ፣ ከማንኛውም የአረፍተ ነገሩ ክፍል ጋር ሊዋቀር እንደሚችል ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (19) ካየናቸው ምሳሌዎች ተረድተናል። ከማንኛውም ሀረግ ጋር ሊዋቀር፣ የሚፈፅመው ተግባር ተዋቃሪው ሀረግ ያዘለውን ሀሳብ ርግጠኝነት ወይም አጠራጣሪነት መግለፅ ነው። በዚህም የሁኔቱን <u>መቻት</u> ከሚገልፁት የግሳዊ ሀረግ አነላማሾች ይለያል።

በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። *መጀመሪያ*፣ ግሶችን የድርጊትና የሁኔት ብለን ለየናቸው። የድርጊት ያልናቸው፣ አንድ ሰው ወይም ሀይል በራሱ ወይም በአንድ ሌላ ነገር ላይ የሚፈፅመውን ተግባር የሚገልፁ ናቸው። ግሶች *መሙሊያ* ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል። እንደ *መሙሊያቸው* አይነትም ሳቢና ኢሳቢ ተብለው እንደገና በሁለት ይከፈላሉ። ሳቢ የሚባሉት ግሶች *መሙሊያ* ድርጊት ተቀባዩን ነገር የሚጠቁም ስማዊ ሀረግ ነው። ይህም ሀረግ ተሳቢ ይባላል። ግስና *መሙሊያ* ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። *መሙሊያው* ያለመሪው፣ *መሪውም* ያለመሙሊያው ብቻውን ሀረግ ሊመሰርት አይችልም። *መሪው* ያለመሙሊያው ብቻውን ቢቆም፣ ሀሳቡ-ጎደሉ ይሆናል። *መሙሊየውም* ብቻውን ቢገኝ፣ አንድ ነገርን ከመጠቆም አልፎ ግሳዊ ሀረግ ሊሆን አይችልም። ግሳዊ *መሪ* የግድ ያስፈልገዋል።

ከ*መሙሊያና* ከ*መሪ* የሚዋቀረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ገላጭ አነላማሾች ያስፈልጉታል። እነዚህ በአብዛኛው *መስተዋድዳዊ ሀረጎች* ናቸው። ተግባራቸውም በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ድርጊት ከጊዜ፣ ከመሳሪያ፣ ከዓላማ፣ ወዘተ፣ አንፃር መግለፅ ነው። ርስበርሰ ያላቸው ቅደም-ተከተላዊ ስርዓትም <u>*ዘፈቀዳዊ*</u> ነው። በዚህም ከ*መሪው* ግስ ጋር ጥብቅ ትስስር ካለው ከ*መሙሊያው* ሀረግ ይለያሉ።

ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ከአነላማሾቹ ጋር ተዋቅሮ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም አቢይ ግሳዊ ሀረግ ከመጣኝ መስተዓምሮች ጋር ተዋቅሮ ዋናውን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ሀረጉ ዋና አቢይ ሀረግ የሚባልበት ምክንያት

ያዘለው ሀሳብ ሙሉ በመሆኑ ነው። የተዋቀሪዎቹ ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

መስተዓምር- አጎላማሽ - መሙሲያ - መሪ 10

ይህ ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት ተዋረዳዊውን ዝምድናም ያንፀባርቃል። ካሁን በፊት በስማዊ ሀረግ ውስጥ እንዳየነው፣ ሀረጉ ቀኝ መሪ ነው። መሪው ግስ ሁሉንም ተዋቀሪዎቹን አስቀድሞ በቀኝ በኩል ይገኛል ማለት ነው።

ቅፅላዊ ሀረግ

እንደ ስምና እንደ ግስ ሁሉ፣ ቅፅሎችም ከተለያዩ መሙሊያዎች፣ አጎላማሾችና መስተዓምሮች ጋር በየደረጃው እየተዋቀሩ ንዑስና አቢይ ቅፅላዊ ሀረጋቸውን ይመሰርታሉ። በዚህ ንዑስ ክፍል ዝርዝር ሁኔታውን እንመለከታለን። ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት፣ ስለ ቅፅሎች በክፍል ሁለት የጠቀስነውን እዚህ ላይ እንደገና ማስታወስ እንፈልጋለን። ይኸውም የአማርኛ ቅፅሎች የስም፣ ወይም የግስ ስር ውልዶች መሆናቸው ነው። ይህ ሲባል ግን ነባር ቅፅሎች የሉም ማለት አይደለም። ርግጥ፣ ጥቂት የዚህ አይነት ቅፅሎች አሉ። እነሱም እንደ የዋሀ፣ ብልሀ፣ ትሁት፣ ደግ፣ ወዘተ፣ ያሉ ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ነባር ስማዊ ወይም ግሳዊ እቻ የላቸውም። ለምሳሌ፣ <u>ጥቂር</u> ለሚለው ቅፅል፣ <u>ጠቆረ</u> የሚል ግሳዊ እቻ እንዳለው ሁሉ፣ የዋሀ የሚለው <u>የወኸ</u> የሚል ግሳዊ እቻ የለውም። የግሳዊነት ሀሳብ የሚገለፀው ቀደም ሲል በጠቀስነው በመሆን ግስ አማካኝነት ነው። ይኸውም <u>ካሳ የዋሀ ሆነ</u> በማለት ነው። ግሳዊ እቻ ያላቸው ቅፅሎች፣ ቅፅላዊ ሀሳቡን በሁለቱም ሲገልፁ፣ ግሳዊ እቻ የሌላቸው ግን በአንዱ፣ ይኸውም በቅፅሉ ብቻ ይገልፃሉ። ለአብነት የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) ከሳ ጎበዝ ሆነ
(ለ) ካሳ ጎበዘ
(መ) ካሳ ብልሀ ሆነ
(ሰ) * ከሳ በለኸ

ግሳዊ እቻ የሌላቸው ቅፅሎች በ1(መ) እንደሚታየው፣ ከመሆን ግስ ጋር በመዋቀር ቅፅላዊ ባህሪን ይገልፃሉ። ሁኔታው ነባር ቅፅሎች በብዛት እንደሌሉ ያሳያል። ይሁን እንጅ፣ ቅፅሎችን ነባርና ውልድ ብሎ በሁለት ከመከፈል አያግደንም። ትንሽም ቢሆኑ፣ ነባር የሚባሉ ቅፅሎች አሉ።

ውልድ የሚባሉት ራሳቸው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። እከፋፈሉ ከሚወለዱበት የቃል ክፍል አኩዋያ ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ቅፅሎች ከስም ወይም ከግስ ስር ስለሚወለዱ፣ በዚሁ መሰረት ከስም የሚወለዱትን ስማዊ፣ ከግስ

የሚወለዱትን ግሳዊ ቅፅል በማለት ልንለያቸው እንችላለን። ስማዊ የሚባሉት እንደ ሆዳም፣ አመለኛ፣ አልኸኛ፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ግሳዊ የሚባሉት ደግሞ እንደ ጎበዝ፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው። የሁለቱንም ከፍሎች መዋቅራዊ ሰርዓት ከዚህ ቀጥለን በየተራ እንመለከታለን።

ስማዊ ቅፅል

ስማዊ ቅፅሎች ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከስም የሚመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። መዋቅራዊ ባህሪያቸው እንደተመሰረቱበት ስም ባህሪ ይለያያል። ለሙ መሙሊያ የሚፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ መሙሊያ ይፈልጋል። ሰሙ መሙሊያ የማይፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም አይፈልግም። ባጭሩ ውልድ ቅፅሎች የናታቸውን መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። ጉዳዩ የቅፅሎች ብቻ አይደለም፣ ስሞችም የተመሰረቱበትን ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ሁለት መፅሀፍ <u>ሸጠ</u> 2
(ለ) የሁለት መፅሀፍ <u>ሻያጭ</u>

ምላሌ 2(ሀ) ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን፣ የተዋቀረው <u>ሁለት መፅሀፍ</u> ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው። 2(ለ) ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሻያጭ</u> የሚለው ውልድ ስም ነው። የተወለደው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ከተወለደበት ስር ነው። ለለሆነም እሱም እንደ ግሱ ከመሙሊያ ጋር ተዋቅሮአል። የሁለቱ ሀረጎች ልዩነት የአይነት እንጅ ያወቃቀር አይደለም። ስማዊና ግሳዊ ከመሆናቸው በስተቀር መዋቅራዊ ይዘታቸውም ሆነ አያያዛቸው ተመሳሳይ ነው።

በዚሁ አይነት የስማዊ ቅፅሎችን መዋቅራዊ ባህሪ እንመለከታለን። ከላይ እንደተገለፀው፣ ስማዊ ቅፅል የሚባሉት ከስም ላይ የሚመሰረቱ ናቸው። እንደዚህ ያሉ ቅፅሎች መሙሊያ የሳቸውም። ሰለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት በመሪው ቅፅል አማካኝነት ብቻ ነው። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) [አልኸኛ] 3
(ለ) [አመለኛ]

የመጀመሪያው <u>አልሀ</u>፣ ሁለተኛው <u>አመል</u> ከሚለው ሰም ላይ የተመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። ለሞኝ መሙሊያ እንደማይፈልጉ ሁሉ፣ ቅፅሎቹም እንደዚሁ አይፈልጉም። የመጀመሪያውን ምሳሌ ንዑስ ሀረግ እንደሚከተለው እናሳያለን።

4

ይህ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ከአነሳሳሽ ሀረግ ጋር በመቀናጀት አቢይ ቅፅላዊ ሀረጉን እንደሚከተለው ይመሰርታል።

(ሀ) አስቴር [[እንደ አባትዋ] [እልኸኛ]] ነች 5
(ለ) አስቴር [[እንደ አባትዋ] [አመለኛ]] ነች

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ [እልኸኛ] የሚለው ቅፅል [እንደ አባትዋ] ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [እንደ አባትዋ እልኸኛ] የሚለውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ በተራው ከመጣኝ መስተጓምር ጋር ተዋቀሮ ዋናውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታል።

አስቴር [በጣም [እንደ አባትዋ እልኸኛ]] ነች 6

ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የመስተጓምር ቦታ ሁልጊዜ በሀረግ መነሻ ላይ ነው። [በጣም] የሚለው መጣኝ መስተጓምር ቦታም በመሰረቱ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ይሁን እንጅ፣ [እንደ አባትዋ] የሚለው አነፃፃሪ ሀረግ እየቀደመው ሲገባ ይችላል። ይህ ሲሆን፥ የቅፅላዊው ሀረግ ቅደም-ተከተል እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል።

(ሀ) [እንደ አባትዋ] [በጣም [— አልኸኛ]] 7
(ለ) [እንደ አባትዋ] [ሁልጊዜ [— አመለኛ]]

በግልፅ እንደሚታየው፣ [እንደ አባትዋ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በነጠብጣብ የተሸፈነውን መሰረታዊ ቦታውን ሰቆ፣ [በጣም] እና [ሁልጊዜ] የሚሉትን መጣኝ መስተጓምሮች ሰመቅደም፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ገብቶ ይገኛል። ይህ የቅደም-ተከተል ለውጥ የሚታየው፣ [እንደ አባትዋ] ሰሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ ነው። አፅንዖት መስጠት ግን እንድን ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር በጥቅም ላይ ስናውል፣ ከስሜት ጋር ተጣምሮ የሚመጣ የአጠቃቀም ባህሪ እንጅ፣ መሰረታዊ የሀረግ አወቃቀር ስርዓት አይደለም። ምክንያቱም የአንድ ሀረግ መሰረታዊ የመዋቅር ቦታ የሚወሰነው በሀረጉ ስዋስዋዊ ተግባር እንጅ፣ በሀረጉ አጠቃቀም ላይ፣ ማለትም ሀረጉ በንግግር ላይ ሲውል በተጠቃሚዎች ላይ በሚፈጥረው ስሜት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ነው። መሰረታዊ መዋቅራዊ (ሰዋስዋዊ) ተግባር የምንላቸው፣ መሪነት፣ መሙሊያነት፣ አነሳሳሽነትና መስተጓምርነት ናቸው። ያም ሆኖ፣ 7(ሀ) እና (ለ) በተራ ቁጥር (6) የተመለከተው ቅፅላዊ ሀረግ ሳዕሳይ ቅርፅ ናቸው።

ግሳዊ ቅፅል

ግሳዊ ቅፅል የሚባሉት ከግስ ሰር ላይ የሚመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። እንደሚመሰረቱበት ሰር፣ መዋቅራዊ ባህሪ መሙሊያ የሚፈልጉና የማይፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ለሰው ያዘነል 1
(ለ) የሰው አዛኝ

1(ሀ) ግሳዊ ሀረግ ሲሆን፣ *መሪው ያዝናል* የሚለው ግሰ ነው። በባህሪው *መሙሊያ* የሚፈልግ ግሰ አይደለም። ገላጭ ሀረግ ግን እንደ ማንኛውም ግሰ ይፈልጋል። ሰሰው የሚለው *መሰተዋድዳዊ* ሀረግ ለዚሁ ተግባር የገባ ነው። አዛኝ የሚሰው ውልድ ቅፅል ሲሆን፣ መሰረቱ ያዝናል የሚለው ግሰ የተወለደበት ሰር ነው። እሱም እንደ ግሱ *መሙሊያ* አይፈልግም። ገላጭ ሀረግ ግን ሊፈልግ ይችላል። የሰው የሚለው ሀረግ የገባው ለዚሁ የገላጭነት ተግባር ነው። ቅፅሉና ግሱ ከአንድ ሰር ስለተመሰረቱ መዋቅራዊ ባህሪ ሊጋሩ ችለዋል። በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ ለሰው የሚለው ገላጭ *መሰተዋድዳዊ* ሀረግ፣ በቅፅላዊ ሀረጉ ውስጥ የሰው በሚል ሰማዊ ሀረግ መልክ ገብቶአል።

ነባር ቅፅሎች *መሙሊያ* የላቸውም። ውልድ የሚባሉትም ቢሆኑ፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ *መሙሊያ* የላቸውም። ለዚህም ምክንያቱ የሚመሰረቱበት ሰር በመዋቅራዊ ባህሪው *መሙሊያ* የሚፈልግ ባለመሆኑ ነው። ከውልድ ቅፅሎች መካከል *መሙሊያ* አላቸው ሊባሉ የሚችሉት እንደ አታላይ ያሉት ብቻ ናቸው። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

[ሽማግሌ አታላይ] 2

አታላይ የሚለው ቅፅል አታ+ለለ የሚለው ግሰ ከተመሰረተበት ሳቢ ሰር የወጣ ነው። ግሱ *መሙሊያ* እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ ይፈልጋል። ይህን ፍላጎቱን ሰማሙዋላት ሽማግሌ ከሚለው ሰም ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ መሰርቶአል። ከዚህ በመነሳት፣ ግሱም ሆነ ቅፅሉ እኩል ሳቢ ናቸው ሰማሰት ይቻላል። ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ። ይህም ሰሮች ሳቢና ኢላቢ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉና ከእነሱ የሚወለዱ ሁሉ፣ ይህን የላቢነት ወይም የኢላቢነት ባህሪ የሚወርሱ መሆናቸው ነው።

ግሳዊ ቅፅል አቢይ ሀረግ ለመመሰረት ከተለያዩ አጎላማሽ ሀረጎች ጋር እንደሚከተለው ሊዋቀር ይችላል።

[እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] የለም 3

[እንደ ካሳ] የሚለው *መሰተዋድዳዊ* ሀረግ ነው። እገባቡ [ሽማግሌ አታላይ] የሚለውን ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ቀድሞ ነው። ተግባሩም ይህንኑ ንዑስ ሀረግ እያነፃፀሩ ማነላመስ ነው። ንፅፅሩ ከሌላ በግሀድ ከማይታይ ሀረግ ጋር ነው። በግሀድ ሲታይ ሀረጉ የሚከተለውን ይመስላል።

እሰቴር [እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] ነች 4


ከአረፍተ ነገሩ ትርጉም ስመረዳት እንደሚቻለው፣ ካሳ እና አስቴር አኩል [ሽማግሌ አታላይ] ናቸው። እንደ የሚለው መስተዋድድም አነፃፃሪ ነው።

[እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] የሚለው አንድ አሀዳዊ ሀረግ መሆኑን ከሚከተለው ምሳሌ ማረጋገጥ ይቻላል።

(ሀ) [እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] [አስቴር [—] ነች] 5
(ስ) አስቴር [እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] ነች፣ አልማዝሰ?
(መ) አሱዋ እንኩዋ [—] አይደለችም

በምሳሌ (4) [እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] የሚለው ሀረግ ነች ከሚለው ግስ በፊት ገብቶአል። ይህ መስረታዊ ቦታው ነው። በምሳሌ 5(ሀ) ውስጥ፣ ይኸው ሀረግ አስቴር የሚለውን የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ቀድሞ ገብቶአል። ይህን ያደረገው በተራ ቁጥር (4) የነበረበትን መሰረታዊ ቦታውን በመልቀቅ ነው። የለቀቀውም ያለ ምንም ቀሪ እንደ አንድ አካል ሆኖ ከቦታው በመንቀሳቀሰ ነው። ይህም ቅንጅቱ እንደ መዋቅር ስመሆኑ ማሰረጃ ነው። በተጨማሪም፣ በምሳሌ (መ) ውስጥ ይኸው ሀረግ ከቦታው ተገድፎአል። የተገደፈውም አሁንም ያለ ምንም ቀሪ ነው። ቅንጅቱ እንደ አሀዳዊ መዋቅር ባይሆን ኖሮ፣ የዚህ ምሳሌ ተቀባይነት አጠራጣሪ ይሆን ነበር።

የሀረጉን ውስጣዊ አቀነጃጀት እንደሚከተለው በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



እንደ በሚለው መስተዋድድ አማካኝነት የሚመሰረቱ እንደ ካሳ ያሉ ንፅፅራዊ የመስተዋድድ ሀረጎች አስቴርና ካሳ አኩል አታላይ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ይህን አቻነት የሚያሳየው እንደ የሚለው መስተዋድዳዊ መሪ ነው። ከዚህም የተነሳ ይህን መሪ አደላዳይ መስተዋድድ ልንለው እንችላለን። አደላዳይ ማለትም አኩል አድራጊ ማለት ነው። የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።


አስቴር [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]] ነች 7

ደፋር የሚለው ደፈረ የሚለው ሳቢ ግስ ከተመሰረተበት ስር ላይ የተመሰረተ ቅፅል ነው። ስለዚህም አሱም እንደ ግሱ ሳቢ ነው። በመሆኑም መሙሊያ ይፈለጋል። ስለዚህም ጨለማ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [ጨለማ ደፋር] የሚለውን ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ደግሞ [እንደ ካሳ] ከሚለው አጎላማሽ የንፅፅር መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅ [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]] የሚለውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል።

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ በጣም ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ተዋቅሮ ዋናውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ እደሚከተለው ይመስርታል።

[በጣም [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]]] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ፣ በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።



9

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ዋናው ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ) ከመጣኝ መስተዓምርና ከአቢዩ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ2) የተዋቀረ ነው። ቅፅላዊው ሀረግ የዋናው ሀረግ መሪ ነው። ይህ መሪ ሀረግ (ቅሀ2) ከአጎላማሽ መስተዋድዳዊ ሀረግና ከንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ1) ጋር ተዋቅሮአል። ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ የአቢዩ ሀረግ መሪ ነው። በመጨረሻም

ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ ጨለማ ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግና ደፋር ከሚለው ቅፅል ጋር እንደተዋቀረ እናያለን። ቅፅሉ የንዑሱ ሀረግ መሪ ነው።

እስካሁን ያየነው የአወቃቀር ስርዓት ከግሳዊ ሀረግና ከስማዊ ሀረግ ስርዓት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። በሁሉም ውስጥ መስተዓምር፣ አጎላማሽና መሙሊያ አለ። የእያንዳንዳቸው ወርዳዊና ተዋረዳዊ አገባብም አንድ አይነት ነው። በሁሉም ሀረጎች መስተዓምሩ ያቀድማል፤ ገላጩ ይከተላል፤ መሙሊያው ይቀጥልና መሪው መጨረሻ ሳይ ይመጣል። በሶስቱ የሀረግ አይነቶች መካከል ያለው ልዩነት በመሙሊያው ሳይ ነው። ይኸውም የስማዊና የቅፅላዊ ሀረግ መሙሊያ በቦታው ሊገኝ ወይም ሳይገኝ ይችላል። የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ግን የግድ በቦታው መገኘት አለበት። መስተዓምሮችና አጎላማሾች በሶስቱም የሀረግ አይነቶች ውስጥ በቦታቸው ሳይገኙ ይችላሉ። ከዚህ ስንነሳ በሶስቱም ሀረጎች ውስጥ ከቦታው መጥፋት የሌለበት የግስ መሙሊያ ብቻ ነው። ይህም ግስን ከስምና ከቅፅል የምንለይበት ዋና መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ቅፅልንም ከስም የምንለይበት መዋቅራዊ ባህሪ አለ። እሱም የአጎላማሹ አይነትና ተግባር ነው። እስተውሰን ከሆነ፣ የቅፅል አጎላማሽ ሁል ጊዜ ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው።

ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ

ባለፉት ንዑስ ክፍሎች የስማዊ፣ የግሳዊና የቅፅላዊ ሀረጎችን የአወቃቀር ስርዓት ለማየት ሞክረናል። ሁሉም ንዑስ ሀረጋቸውን ከመሙሊያ ሀረጎችና ከመሪዎች፣ አቢይ ሀረጋቸውን ከተለያዩ አጎላማሽ ሀረጎችና ከንዑስ ሀረግ እንደሚመሰርቱ ተረድተናል። አቢይ ሀረጎቹ ደግሞ በተራቸው ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ ሀረግ ሲመሰርቱ አይተናል። በሁሉም ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በስተቀኝ ነው። ይህ ያወቃቀር ስርዓት ተውሳክ ግሳዊ ሀረጎችንም ሊያጠቃልል ይችል እንደሆነ፣ ከዚህ ቀጥለን እንመረምራለን።

ደጋግመን እንደጠቀስነው፣ ተውሳክ ግስ የሚባለው ክፍል እንደሌሎቹ ክፍሎች በርካታ ቃላት የሉትም። ባንባሩ ግን የተለያዩ ተውሳክ ግሳዊ የሚባሉ በርካታ ተግባራት አሉ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

የሁኔታ
የጊዜ
የምክንያት
የማድረጊያ
የቦታ
የንፅፅር
ወዘተ

1

እነዚህ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት የሚገለፁት በአብዛኛው በስማዊ ሀረግ፣ በመስተዋድዳዊ ሀረግና በተገኘ አረፍተ ነገሮች አማካኝነት ነው። በዚህም ምክንያት፣ እንደነዚህ ያሉ ሀረጎችን ብዙ ጊዜ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች እንላቸዋለን።

በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኙት ጥቂት መደበኛ ተውሳከ ግሶች የሚከተሉት ናቸው።


(ሀ)	ቶሎ	(ለ)	ክፉኛ	2
	ገና		ግምኛ	
	እንደገና		ጅልኛ	
	መቸ		ምንኛ	

በ(ሀ) ስር ያሉት ነሳር ተውሳከ ግሶች ሲሆኑ፣ በ(ለ) ስር ያሉት ግን /-ኝኝአ/ በሚለው መለራች ምዕላድ አማካኝነት ከቅፅሎች ላይ እንደሚመሰረቱ በምስረታው ከፍል ተመልከተናል።

ተውሳከ ግሶች መመሊያ የላቸውም። ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት ሰመሪው ቃል ብቻ ነው። በዚህ መዋቅራዊ ባህሪያቸው ከሌሎቹ የቃላት ክፍሎች ይለያሉ። ቀደም ሲል በተከታታይ እንዳየነው፣ ሌሎቹ ክፍሎች በከፊልም ቢሆን፣ መመሊያ አላቸው። በግስ ክፍል ውስጥ፣ ሳቢ ግሶች ያለመመሊያ አይቆሙም። ስሞችና ቅፅሎችም ከመመሊያ ጋር ሲዋቀሩ ይችላሉ። ርግጥ፣ መመሊያዎቹ ቀሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ረገድ ተውሳከ ግሶች ልዩ ናቸው። ከሌሎቹ ጋር የሚመሳሰሉት በአቢይ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ እንደ ማንኛውም የሀረግ ክፍል ከመስተዋድዳዊ ሀረግና ከመጣኝ መስተዓምር ጋር ሲዋቀሩ ይችላሉ። መስተዋድዳዊ ሀረጉ ግን የተወሰነ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ)	እስቴር [እንደ ካሳ [ክፉኛ]] ወደቀች	3
(ለ)	እስቴር [እንደ ካሳ [ቶሎ]] ተነሳች	


በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ቅንጅቱም በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት [ክፉኛ] እና [ቶሎ] ከሚሉት ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተግባሩም የእስቴርን የአወዳደቅ ሁኔታ ከካሳ የአወዳደቅ ሁኔታ ጋር ማነፃፀር ነው። ስለዚህም ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መዋቅራዊ ሰርዓቱን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



[እንደ ካሳ] የሚለው ንፅፅራዊ ሀረግ ተግባር፣ የአወዳደቁን ወይም የአመጣጡን ሁኔታ፣ ማለትም መጥፎነቱን ወይም ፍጥነቱን፣ መግለፅ ነው። መጥፎነቱም ሆነ ፍጥነቱ የሚገለፀው ደግሞ [ከፉኛ] እና [ቶሎ] በሚሉት ተውሳከ ግሶች ስለሆነ፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጉ መዋቅራዊ ግንኙነትም ከነዚሁ ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተውሳከ ግሶቹ በሀረጉ በስተቀኝ ስለሚገኙ፣ ሀረጉ ቀኝ መሪ ነው።


ከዚህ ላይ የተውሳከ ግስንና የቅፅልን መዋቅራዊ ባህሪ ተመሳሳይነት ልብ ልንል ይገባል። የሁለቱም ገላጭ ሀረግ ንፅፅራዊ መስተዋድድ ነው። ሁለቱም ከፍሉች ገላጭ ስለሆኑ፣ የተግባር እንድነት አሳቸው። ይህ የተግባር እንድነት መዋቅራዊ ተመሳሳይነትን ሊያስከትል ችሉአል። በመካከላቸው ያለው ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ነው። ቅፅሎች መሙሊያ ሲኖራቸው፣ ተውሳከ ግሶች የላቸውም።

ቀደም ሲል ስለ ቅፅላዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ግንኙነት ከተውሳከ ግሱ ጋር ሳይሆን፣ ከእሱ ጋር ከተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው፤ ሊባል ይችላል። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው እረፍተ ነገር ውስጥ፣ [እንደ ካሳ] የሚለው ሀረግ ግንኙነት [ከፉኛ] ከሚለው ተውሳከ ግስ ጋር ሳይሆን፣ [ከፉኛ ወደቀ] ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊሆን ይችላል። ይህም ሲሆን፣ ንፅፅራዊ ገላጭነቱ በተውሳከ ግሱ ለተገለፀው <u>ሁኔታ</u> ሳይሆን፣ በግሱ ለተገለፀው <u>ድርጊት</u> ሊሆን ይችላል። የመስተዋድዳዊው ሀረግ አገባብ እሻሚ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ንፅፅራዊ ሀረጉ ግሳዊንም ሆነ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግን ሊንልፅ የሚችል መሆኑ ነው። ከተውሳከ ግሱ ጋር ያለው አቀነጃጀት ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሲሆን፣ ከግሳዊ ሀረጉ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ደግሞ ከዚህ በታች እንደሚታየው ነው።



መስተዋደዳዊ ሀረጉ የተውሳከ ግሱ ወይም የግሳዊ ሀረጉ አጎላማሽ ሊሆን እንደሚችል ዕዐ-መዋቅሮቹ ያመለክታሉ። እንደዚህ አይነቱ መዋቅራዊ እሻሚነት፣ በመዋቅር ደረጃ፣ በዚህ አይነት ሊፈታ ይችላል። ከመዋቅር ባሻገር ግን፣ ለምሳሌ፣ በንግግር ጊዜ፣ አሻሚነቱ ሊፈታ የሚችለው፣ በንግግሩ አውድ ብቻ ነው።

ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች [በጣም] ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ሊዋቀሩ ይችላሉ። የመስተዓምሩ ቦታም እንደ ማንኛውም መስተዓምር በሀረጉ መጎሻ ላይ ሲሆን፣ ተግባሩም በሀረጉ የተገለፀውን ሀኔታ ከመጠን አንፃር መወሰን ነው። ለምሳሌ፣ [ክፉኛ] ወይም [ቶሎ] ስንል፣ የፍጥነቱን ወይም የክፋቱን ደረጃ አናውቅም። ይህ የሚታወቀው [በጣም] የሚለውን መስተዓምር በመጠቀም [በጣም ቶሎ] ወይም [በጣም ክፉኛ] ስንል ነው። አቢይ ሀረጉ ውስጥ [በጣም] የሚገኘው በሀረጉ መጎሻ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተለውን እንመልከት፡



6

ዕፀ-መዋቅሩ [በጣም] የሚለው መስተዓምር ከአቢዩ ሀረግ አንጉዎ ላይ እንደሚወርድና በሀረጉ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። ይህ ግን በታህታይ መዋቅር ውስጥ የሚታይ ቅደም-ተከተል ነው። በላዕላይ መዋቅሩ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ ከቦታው እየተነሳ ወደ አቢይ ሀረጉ መነሻ ስለሚሄድ፣ መስተዓምሩ ከመሪው፣ ማለትም ከ[ቶሉ] ቀድሞ የገባ ሊመስል ይችላል። ይህ ሲሆን ሀረጉ እንደሚከተለው ይሆናል።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ቶሉ]] 7

በግልፅ እንደሚታየው፣ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በነጠብጣብ የተመለከተውን መለረታዊ ቦታውን ለቆ፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ገብቶአል። ይህ ሁኔታ በቅፅላዊ ሀረግም ይታያል። የሚከተለውን እንመልከት።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ረዥም]] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ ነው። መሪው [ረዥም] የሚለው ቅፅል ነው። የሀረጉ ታህታይ አወቃቀር እንደሚከተለው ነው።

[በጣም] እንደ ካሳ [ረዥም]]] 9

ይህ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (7) ከሚታየው ተውሳክ ግሳዊ ሀረግ ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። በሁለቱ ሀረጎች መካከል ያለው ልዩነት የአወቃቀር ሳይሆን፣ የአይነት ብቻ ነው። ይኸውም አንዱ ተውሳክ ግሳዊ ሲሆን፣ ሌላው ቅፅላዊ መሆኑ ነው። የሁለቱ መዋቅር ይህን ያህል ተመሳሳይ የሆነው ያለምክንያት አይደለም። ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ሁለቱም ገላጮች ናቸው። ተውሳክ ግሶቹ ግሰን፣ ቅፅሎቹ ስምን ይገልፃሉ። ስምና ግስ ተገላጭ፣ ቅፅልና ተውሳክ ግስ ገላጭ እንደሆኑ፣ በምዕራፍ ሁለት ስለ ቃላት ክፍል ስንወያይ ገልፀናል።

ወደ መስተዓምሩ እንመለሰና እንድ ጥያቄ እናንሳ። ይኸውም [በጣም] የሚለው መጣኝ መስተዓምር ታህታይ ቦታ በሀረጉ መነሻ ላይ ስመሆኑ ማሰረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው። ቀደም ሲል ሌሎቹን አስመልክተን እንደ ገለፅነው ሁሉ፣ አንድ መሪ ቃል ንዑስ ሀረጉን የሚመሰርተው ከመሙሊያ ጋር በመዋቀር ወይም ያለ መሙሊያ ብቻውን በመቆም ነው። ምርጫው መሙሊያ በመፈለግና ባለመፈለግ ነው። በማንኛውም መንገድ የተዋቀረ ንዑስ ሀረግ የተሰያዩ ገላጮች ያስፈልጉታል። ገላጮቹ ሀረጉን ከጊዜ፣ ከምክንያት፣ ከዓላማ፣ ከማድረጊያ፣ ወዘተ፣ አኩዋያ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት በቅርፅም ሆነ በይዘት ያጎላምሉታል። በዚህ ሁኔታ ያደገ ሀረግ መጠኑን የሚገለፅበት መጣኝ ሀረግ ያስፈልገዋል።

መጣኞቹ አንደ [በጣም] ያሉ የመጠን መስተዓምሮች ናቸው። ቦታቸውም ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በሀረጉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቦታዎች በሙሉ ሀረጉን እየሞሉና እያጎላመሉ በሚገቡት መሙሊያዎችና ገላጮች ስለሚያዙ ነው። አንድ መሪ ሀረጉን መዞና አሳድጎ የሚጨርሰው በመሙሊያዎችና በገላጭ አጎላማሾች ነው። በእነዚህ እየታጀበ ካደገ በሁዋላ መጠኑን የሚያሳይበት መጣኞች፣ የትነቱን የሚያሳይበት ጠቁዋሚዎች፣ እንዲሁም የማንነቱን የሚያሳውቅበት አገናዛቢዎች ያስፈልጉታል። እነዚህም ሊገቡ የሚችሉት በመነሻው ላይ ነው። የሀረጉን ይዘት ሊወስኑ የሚችሉት ሙሉ ሀረጉን እየቀደሙ በመነሻ ላይ ሊገቡ ነውና። ከሀረጉ መሀል ቢገኙ፣ ሊወስኑ የሚችሉት መሹውን ሀረግ ሳይሆን፣ ከሚገኙበት ቦታ ጀምሮ ያለውን የሀረጉን ከፊል አካል ብቻ ይሆናል። በሌሎቹ ሀረጎች ያየነው ሁኔታም እንደዚሁ ነበር። መስተዓምሮቹ የየሀረጉ መነሻ ናቸው። በዚህም የተውሳክ ግስን ብቻ ሳይሆን የሞና ዋናዎቹን የቃላት ክፍሎች የሀረግ አወቃቀር ስርዓት እናጠቃልላለን።

መስተዋድዳዊ ሀረግ

እስካሁን ያየነው የዋና ዋና ቃላት ክፍሎችን የሀረግ አወቃቀር ስርዓት ነው። ዋና ዋና የቃላት ክፍሎች የሚባሉት፣ ትርጉም ወይም ይዘት ያላቸው ክፍሎች ናቸው። እነዚህም የስም፣ የግስ፣ የቅፅልና የተውሳክ ግስ ክፍል ቃላት ናቸው። ሌሎቹ የቃላት ክፍሎች መሰተዋድድና መስተዓምር ናቸው። እነዚህ የይዘት ሳይሆን፣ የግብር ቃላት ክፍሎች ናቸው። ከዚህ ቀጥሰን የነዚህን ሁለት ክፍሎች ስርዓተ-መዋቅር እንመለከታለን። መጀመሪያ የመስተዋድዶችን እንመልከት።

እንደ ሌሎች የቃላት ክፍሎች ሁሉ፣ መስተዋድዶችም ንዑሰና እቢይ ሀረጎችን ይመሰርታሉ። ንዑስ ሀረጎችን የሚመሰርቱት ከመሙሊያዎች ጋር በመዋቀር ነው። መሙሊያዎቹም ሰማዊ ሀረጎች፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ናቸው።

እንደ መሙሊያቸው አያነት መስተዋድዶችን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን። ይኸውም ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋደዳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩትን በአንድ በኩል፣ ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩትን በሌላ በኩል በመመደብ ነው። ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተዋምር ይባሉ የነበሩት ናቸው። እኛ ምይ ብለናቸዋል። ምክንያቱም ተግባራቸው ማጣመር ስይሆን፣ እንደ አረፍተ ነገር በመሙሊያነት ወይም በአሳላሚነት በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ስለሆነ ነው።

በዚህ ንዑስ ከፍል የምናተኩረው ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋደዳዊ ሀረግ ጋር በሚዋቀሩት መስተዋድዶች ላይ ነው። በክፍል ሁለት እንደገለፅነው፣ መስተዋድድ የሚባለው ክፍል እንደ ሌሎቹ ክፍለ-ቃላት እንደ ስሞች፣ ግሶችና ቅፅሎች የነገሮች፣ የድርጊቶችና የባህሪያት ስያሜ አይደሉም። የግብር ቃላት ናቸው። ግብራቸውም በቀደምት ሊቃውንት በሚገባ እንደሚታወቀው፣ ማያያዝ ወይም ማዋያደ ነው። ይህን ተግባር ስመፈፀም የሚያስፈልገው የአያያዥ መጠን በሚያያዙት ነገሮችና በሚፈፅሙት ስዋስዋዊ ተግባር ልክ ይወሰናል። የሚያያዙት ነገሮች ደግሞ ስሞች፣ ግሶች፣ ቅፅሎችና ተውሳከ ግሶች ናቸው። ተግባራቱም በተውሳከ ግሱ ክፍል የተዘረዘሩት ናቸው። እነዚህን ስመግለፅ የቃላቱ ክፍል ርስበርስ ሲዋቀሩ እንዱን ተዋቃሪ ከለላው ጋር ለማያያዝ የሚያስፈልገው የአያያዥ ቃላት መጠን ጥቂት ነው። በዚህ ምክንያት በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኙት መስተዋድዶች የሚከተሉት ናቸው።

ስለ	እንደ	ጋር	እስከ	ወደ	1
ላይ	ስ-	ሰ-	በ-	ከ-	

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ መስተዋድዶች በራሳቸው ምንም ትርጉም የላቸውም። ራሳቸውንም ችለው መቆም አይችሉም፣ ሁል ጊዜ ድጋፍ ይፈልጋሉ። ባጭሩ ተስማሪ ናቸው። የሚስጠፉት መሙሊያ ሆኖ በሚገባው ሀረግ መነሻ ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና እንዛራዊ ትርጉም ያላቸው ጥቂት መስተዋድዶች አሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

አጠገብ	ባሻገር	በኩል		
በስቲያ	ድረስ	ማደ	አኩዋያ	2


እነዚህ መስተዋድዶች አንድን ነገር፣ አንድ ሌላ ነገር ከሚገኝበት ቦታ አንፃር የሚገልፁ ናቸው። ለምሳሌ፣ ወንበሩ ከጠረጴዛው አጠገብ ነው ፣ ስንል፣ ጠረጴዛው የሚገኝበትን ቦታ እንደመነሻ ወስደን፣ ወንበሩ ከዚያ መነሻ ቦታ አንፃር፣ ምን ያህል እንደሚርቅ ወይም እንደሚቀርብ መግለፃችን ነው። አጠገብ የሚለው በሁለቱ ነገሮች መካከል ያለውን ቅርበት ያመለክታል። እንደ አጠገብ ያሉ ራስ ቻይ መስተዋድዶች መመሙሊያቸውን ተክትለው ሲገቡ፣ ተለማፊዎቹ ቀድመው ይገባሉ። ይህ ግን በላዕላይ መዋቅር ደረጃ ነው።

አሁን ወደ ዝርዝር መዋቅራዊ ባህሪያቸው እንሂድ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መስተዋድዶች ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋደዳዊ ሀረግ ጋር እየተዋቀሩ ንዑስ መስተዋደዳዊ ሀረግ ሊመስርቱ ይችላሉ። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) [ወደ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] 3
(ለ) [[እስከ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] ድረስ]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ ወደ የሚለው መስተዋድድ [ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ስማዊ ሀረጉ መሙሊያ ነው። መሪው መስተዋድድ ከዚሁ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። አገባቡም ትልቅ የሚለው ተሰጣፊ በመሆን ነው። ተሰጣፊነቱ በተለይ ወደቤት ለንልና ለንዕፍ የጎላ ነው።


በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ ድረስ የሚለው መስተዋድድ [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። አገባቡ መሙሊያውን ተከትሎ ነው። የሁለተኛውን ሀረግ ያወቃቀር ስርዓት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



4

በግልፅ እንደሚታየው፣ ድረስ የሚለው መሪ መስተዋድድ ነው። [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ገብቶአል። እስከ የሚለው የመሙሊያው መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ነው። እሱም [ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ሁኔታው የሁለቱ የመነሻና የመድረሻ መስተዋድዶች አገባብ ለየቅል መሆኑን ያስረዳል። ይህም ልዩነት ከፍ ሊል እንደተገለፀው፣ ምናልባት ከመሪዎቹ መስተዋድዶች ራስን ችሎ ከመቆምና ካለመቆም የሚመጣ ሊሆን ይችላል። ራሳቸውን ችለው የሚቆሙት መሪዎች መሙሊያውን ተከትለው ሊገቡ፣ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙት፣ መሙሊያውን እየቀደሙ ይገባሉ። አገባባቸውም በተሰጣፊነት ነው። ይህ ልዩነት ግን መስረታዊ ሳይሆን፣ በመዋቅሩ ላዕላይ ገፅታ ላይ የሚከሰት የመሪና የመሙሊያ ዝምድና ነው፣ ለማለት ይቻላል። በመሰረታዊ (ታህታይ) አወቃቀር ደረጃ ላይ፣ የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ቦታ ከመሙሊያው

ዘስተቀኝ በኩል ነው፣ ብሎ ማስብ ይቻላል። በዚህም መስረት፣ በተራ ቁጥር (4) የሚታየው መዋቅር ታህታይ አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል።



ይህ መዋቅር መስተዋድዳዊ መሪዎቹ ከመሙሊያዎቹ በስተቀኝ እንደገቡ ያሳያል። ይህም የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ ስርዓት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ መሪው ከመሙሊያው እየቀደመ የሚገባው በላዕላይ መዋቅር ነው። በተራ ቁጠር (4) የሚታየውም ይኸው ነው።

የመሪው ቦታ ከመሙሊያው በልተቀኝ ለመሆኑ ማስረጃው ሌሎቹ ቀደም ሲል ያየናቸው ሀረጎች መሪ በልተቀኝ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ትልቁ ትምህርት ቤት የሚለው ሰማዊ ሀረግ መሪ ትምህርት ቤት የሚለው ጥምር ስም ሲሆን፣ ቦታውም በስተቀኝ ነው። እንደ ካሳ ሽማግሌ ደፋር የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ መሪም ደፋር የሚለው ቅፅል ሲሆን፣ የእሱም እገባብ እንደዚሁ በቀኝ በኩል ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል ያየነው የግሳዊ ሀረግ ስርዓትም እንደዚሁ ነው። ከዚህ አጠቃላይ የእገባብ ሁኔታ ስንነሳ፣ ሀረጎች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።


ከላይ የሚታዩት የንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ምሳሌ ናቸው። ከዚህ ቀጥለን የአቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን መዋቅር እንመለከታለን።

(ሀ) [ከወገብ [በታች]] 6
(ሰ) [እንደ አሳ [በባህር]]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ በታች የሚለው ከፍል ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መሪው በ የሚለው መስተዋድድ ሲሆን፣ መሙሊያው ታች የሚለው ስም ነው[12]። በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ ደግሞ ይኸው መስተዋድድ ባህር ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮአል። እነዚህ ንዑስ ሀረጎች ከወገብ እና እንደ አሳ ከሚሉት ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ መስርተዋል። ከወገብ የሚለው ገላጭ

[12] ስም ነው ከማለት ይልቅ መስተጓምር ነው ማለቱ ይቀላል። ሁኔታውን ወደሁዋላ እናየዋለን።

መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ የአንድን ነገር መነሻ ያመለክታል። መነሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ልነለው እንችላለን። እንደ የሚለው ደግሞ ቀደም ሲል ስለቅፅላዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ እነማን ነው። ሁለቱም ገላጭ ሀረጎች ከመሪዎቹ ንዑስ ሀረጎች እየቅደሙ መጣባታቸው አቢዩን ሀረግ ቀኝ መሪ ያደርገዋል። ይህም ከፍ ሲል መስተዋድዳዊ ሀረጎች እንደ ሌሎቹ ሀረጎች ሁሉ ቀኝ መሪ ናቸው ያልነውንና በተራ ቁጥር (5) ያሳየነውን አጠቃላይ ታህታይ ስርዓት የሚደግፍ ነው። ከዚሁ አኳያ የምሳሌ 6(ለ)ን ያወቃቀር ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።



7

በግልፅ እንደሚታየው፣ መመሌያዎቹ ስማዊ ሀረጎች ከመሪዎቹ መስተዋድዶች እየቀደሙ ጉበተዋል። ይሁን እንጅ መሪዎቹ ራሳቸውን ችለው ስለማይቆሙ፣ ከመመሌያዎቹ ግራ ጎን ላይ ይሰጠሩሉ። ይህን ሲያደርጉ በተራ ቁጥር (6) የሚታየውን ቅደም ተከተል ይይዛሉ።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሲነሳ ይችላል። ይኸውም ካለይ እንደሚታየው፣ እንደ አሳ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ገላጭነት በርግጥ በባህር ለሚለው መሪ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው እንደሚከተለው ያሉ መዋቅሮችን መለረት ያደረገ ነው።

ለምች እንደ አሳ በባህር ይኖራሉ 8


አግባብ ያለው ጥያቄ ነው። ምክንያቱም እንደ አሳ የሚለው ሀረግ መዋቅራዊ ግንኙነት ከላይ እንደተገለፀው፣ ብባህር ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር፣ ወይም ደግሞ በባህር ይኖራሉ ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊሆን ስለሚችል ነው። ይኖራሉ የሚለው መረ ግስ መመሌያ ያስፈልገዋል። ይህን ፍላጎት ለማሙዋላት በባህር ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር ይችላል። ይህን ሲያደርግ፣

በባህር ይኖራሉ 9

የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እናገኛለን። ይህም ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እንደ አሳ ከሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀርና፣

እንደ አሳ በባህር ይኖራሉ 10

የሚል አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ይችላል። በዚህም ምክንያት እንደ አሳ የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ የግሳዊው ሀረግ አነሳሳሽ አካል ይሆናል። አሻሚ የአወቃቀር ስርዓት አለው ማለት ነው። በአንድ በኩል፣ በ6(ለ) እንደሚታየው፣ በባህር ከሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ጋር፣ በሌላ በኩል፣ በባህር ይኖራሉ ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር ይችላል። ይህን አሻሚነት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



በግልፅ እንደሚታየው፣ በ11(ሀ) ውስጥ እንደ አሳ የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ የግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ገላጭ ሆኖ ገብቶአል። መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በ11(ለ) ውስጥ፣ ይኸው ሀረግ በባህር የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ገላጭ ሆኖ ገብቶአል። መዋቅራዊ ግንኙነቱም ከመሰተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ነው።

የዚህ አይነት መዋቅራዊ አሻሚነት የገላጭ ሀረጎች ባህሪ ነው። አንድ መዋቅር ከሌላ መዋቅር ጋር ሲቀናጅ፣ የአንደኛው መዋቅር ገላጭ ሀረግ፣ የሌላውም ገላጭ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ገላጭነቱ ለአንዱ ወይም ለሌላው መሆኑን ከሳይ በሚታየው ሁኔታ በዕፀ-መዋቅር አየለዩ ማሳየት ይቻላል።


ወደ መሰተዋድዳዊ ሀረጎቹ ውስጣዊ አወቃቀር እንመለስ። አቢይ መሰተዋድዳዊ ሀረጎች ከመጣኝ መሰተዓምር ጋር አየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ መሰተዋድዳዊ ሀረግ

ይመስርታሉ። ይህን ሲያደረጉም በገላጮች ላይ ያየነው መዋቅራዊ አሻሚነት ይከሰታል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።


(ሀ) [[እንድ ጊዜ] [እንደ አሳ በባህር]] ዋኙ 12
(ለ) [[ሁለት ጊዜ] [እንደ ወፍ በሰማይ]] በረሩ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ [እንድ ጊዜ] እና [ሁለት ጊዜ] የሚሉት መጣኝ መስተዓምሮች ናቸው። መዋቅራዊ ግንኙነታቸው [እንደ አሳ በባህር] እና [እንደ ወፍ በሰማይ] ከሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ነው። የሚያሳዩትም የባህሩን እና የሰማዩን ነገር ነው። ለምሳሌ ሁለት ጊዜ ወደ ላይ፣ እንድ ጊዜ ወደ ታች ለነል፣ መጣኝ ሀረጎቹ የሚገልፁት የላይነቱንና የታችነቱን መጠን ነው። ርግጥ ነው፣ መጣኞቹ ሀረጎች የመኖኘቱንና የመብረሩን መጠንም ሊገልፁ ይችላሉ። ይህን ሲያደረጉም መዋቅራዊ ግንኙነታቸው ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ይሆናል። ይህን አሻሚነት እንደሚከተለው እናሳያለን።

(ሀ) 13



(ለ)



በምሳሌ (ሀ) አንድ ጊዜ የሚለው መጣኝ ሀረግ ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ተዋቅሮአል። የሚገልፀውም የመዋንቱን ተግባር መጠን ነው። በምሳሌ (ለ) ደግሞ ይኸው ሀረግ፣ ከመስተዋድዳዊ ሀረጉ ጋር ተዋቅሮአል። የሚገልፀውም አንደ አሳ በባህር የመሆኑን መጠን ነው። በምሳሌ (11) እና (13) የምናየው ገላጮችና መስተ-ዓምሮች አሻሚ የሆነ መዋቅራዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ነው። መስተ-ዓምርነታቸው ለግሳዊ ሀረግ ወይም በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ለሚገኝ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል። ገላጮችም እንደዚሁ።

እስካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል ስለ መስተዋድዳዊ ሀረግ በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። መስተዋድድ በሚባለው ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቃላት አብዛኛው በመስተዋድዳዊ ሀረግ፣ ከስማዊ ሀረግና ከአረፍተ ነገር ጋር እንደሆነ አይተናል። ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተዓምር ይባሉ የነበሩት ናቸው። ተግባራቸው አንድ አረፍተ ነገር በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ነው። መስተዋድዶች ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር በመቀናጀት ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ንዑስ ሀረጎቹ ደግሞ ከገለጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር እየተቀናጁ አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ይመሰርታሉ። በንዑስ ሀረጉ ውስጥ የሚገቡት

መሙሊያዎቸ ሊሆኑ፣ በአቢይ ሀረጉ ውስጥ የሚገቡት አጎላማሾች ናቸው። አጎላማሾቹ አንደ ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ያሉ ናቸው። አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከመጣኝ ስማዊ ሀረጎች ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ይህ የመጣኙ ሀረግ አወቃቀር በርግጥ ከመስተዋድዳዊው ሀረግ ጋር መሆኑ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። ምናልባትም የመጣኙ ሀረግ ግንኙነት ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ነው የሚለው አመለካከት የበለጠ አስተማማኝ ሲሆን ይችላል። ጉዳዩን ስጊዜው በዚሁ እንተወዋለን።

በሳዕሳይ መዋቅር፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች መሪ በቀኝ ወይም በግራ ሊገኝ ይችላል። ይህም የሚሆነው በንዑስ ሀረግ ደረጃ ነው። በአቢይ ሀረግ ደረጃ፣ መሪው ምን ጊዜም በቀኝ በኩል ነው። በግራ በኩል የሚታዩት መስተዋድዳዊ መሪዎች ራሳቸውን ችለው ለመቆም የማይችሉት ናቸው። አጠቃላዩ የቁዋንቁዋው የሀረግ አመሰራረት ስርዓት መሪውን በቀኝ በኩል የሚያሳይ ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት በታሀታይ ደረጃ መስተዋድዳዊ ሀረጎችም በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው ብለን አጠቃለናል።

መስተዋድዳዊ ሀረጎች ስግሳዊ ሀረግ ወይም ስመስተዋድዳዊ ሀረግ ገላጭ እየሆኑ ስለሚገቡ፣ መዋቅራዊ ግንኙነታቸው አሻሚ ሊሆን ይችላል። ገላጩ ሀረግ ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ወይም ከግሳዊ ሀረግ ጋር መሆኑን ለይቶ በመዋቅር ማሳየት ይቻላል። መስተዓምሮችም እንደ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከግሳዊ ሀረግ ወይም ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀሩ፣ አሻሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ አይተናል። ከየትኛው ሀረግ ጋር እንደተዋቀሩ መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ማሳየት ይቻላል።

መስተዓምራዊ ሀረግ


ስስ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ እንደገለፅነው፣ መስተዓምር የሚባለው ሶስት አይነት የግብር ቃላትን የያዘ ክፍል ነው። ከፍሎቹም ጠቁዋማ፣ እገናዛቢና መጣኝ መስተ-ዓምሮች ናቸው። ጠቁዋማና አገናዛቢ መስተዓምር የሚባሉት ተውላጠ ስሞችን በሙሉ ያጠቃልላሉ። መጣኝ የሚባሉት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ የመጠንና የአሀዝ ቅፅል የሚባሉትን ይይዛሉ።

እስካሁን ድረስ በዚህ ክፍል ያየነው፣ እያንዳንዱ የቃላት ክፍል ከሌሎች ክፍሎች ጋር እየተቀናጀ ሀረግ ሊመሰርት ነው። የስም ክፍል ስማዊ ሀረግ፣ የቅፅል ክፍል ቅፅላዊ ሀረግ፣ የግስ ክፍል ግሳዊ ሀረግ፣ ወዘተ፣ ሊሆን እይተናል። ከንዑስ የቃላት ክፍልም መስተዋድድ የሚባሉት፣ መስተዋደዳዊ ሀረግን ሲመሰርቱ እይተናል። በዚሁ አካሄድ፣ መስተዓምር የሚል ንዑስ የቃላት ክፍል ካለ፣ መስተ-ዓምራዊ ሀረግ የሚል መዋቅር መመስረቱ እይቀሬ ነው። እያንዳንዱ ክፍል ሀረግ የመመስረት ችሎታ አለው ብለናልና። ሀረጉም የሚመሰረተው፣ በመስተዓምሩና ስመሙሊያዎች አማካኝነት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመለከት።

[ያ [ትልቅ]የቅኔ ተማሪ]]]

ቀደም ሲል ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ እንደተገነዘብነው ከሆነ፣ ይህ የስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። መሪው ተ<u>ማሪ</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ <u>የቅኔ</u> የሚለው የዚህ መሪ ስም መሙሊያ ነው። መሪውና መሙሊያው [የቅኔ ተማሪ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ መስርተዋል። <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅል የዚህ ንዑስ ስማዊ ሀረግ ገላጭ አጎላማሽ ነው። <u>ያ</u> የሚለው ደግሞ [ትልቅ [የቅኔ ተማሪ]] የሚለውን አቢይ ስማዊ ሀረግ የሚጠቁም መስተዓምር ነው። ይህ እንግዲህ መዋቅሩ እንደ እንድ ስማዊ ሀረግ ሲተነተን ነው።

ከላይ ባነሳነው የነገር አካሄድ መሰረት ደግሞ፣ ይህ መዋቅር እንደ ስማዊ ሳይሆን፣ እንደ መስተዓምራዊ ሀረግ ሊተነተን ይችላል። እተናተኑም፣ <u>ያ</u> የሚለውን መስተዓምር እንደ መሪ፣ [ትልቅ [የቅኔ ተማሪ]] የሚለውን አቢይ ስማዊ ሀረግ የዚሁ መሪ መሙሊያ አድርጎ በመቁጠር ነው። እንደ ማንኛውም መሪ፣ መስተዓምሩ ከመሙሊያው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን መስተዓምራዊ ሀረግ ይመሰርታል። እወቃቀሩን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



ይህ መስተዓምራዊ ሀረግ ነው። መሪው መስተዓምሩ ሲሆን፣ እገባቡም በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ሁኔታው ቀደም ሲል እንዳየናቸው እንደ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ነው። በንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ውስጥ መሪው መስተዋድድ መሙሊያውን እየቀደመ ሲገባ እይተናል። ከዚህም ሁለቱ ንዑስ የቃላት ከፍሎች የእወቃቀር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሁለቱም ስማዊ ሀረግ መሙሊያ አላቸው። በሁለቱም መሪው በሀረጉ መነሻ ላይ ይገኛል። ይህ ግን በላዕላይ መዋቅር ደረጃ ነው።


መስተዓምራዊው መሪ ከሌላ መስተዓምራዊ ህረግ ጋር ሊዋቀርና ንዑስ መስተዓምራዊ ህረግ ሊመስርት ይችላል። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

ያ ትልቅ-ኡ የቅኔ ተማሪ 3

በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሁለት መስተዓምሮች አሉ። እነሱም ያ እና /-ኡ/ ናቸው። /-ኡ/ ቅጣይ መስተዓምር ነች። ይህም ቀደም ሲል አንዳየናቸው ቅጣይ መስተዋድዶች አይነት መሆኑ ነው። የተቀጠለው ከቅፅሉ ላይ ነው። ይሁን እንጅ መስተዓምርነቱ ስቅፅሉ ሳይሆን፣ ስአጠቃላዩ ስማዊ ህረግ ነው። ይህ ውነት ከሆነ፣ መዋቅራዊ ገዘድናው ከስማዊ ህረጉ ጋር መሆን አስበት። ታህታይ አገባቡም ስማዊ ህረጉን ተከትሎ ነው። ይህ ለመሆኑ ማስረጃው ስማዊ ህረጉ ገላጭ በሌለው ጊዜ፣ መስተ-ዓምሩ የሚቀጠለው ከመሪው ስም ላይ መሆኑ ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።


ተማሪ-ው 4

መስተዓምሩ /-ኡ/ ከስሙ ላይ እንደተቀጠለ ማየት ይቻላል። ይህን መስረት በማደረግ፣ በተራ ቁጥር (3) ውስጥም የዚሁ መስተዓምር ታህታይ አገባብ ከስማዊ ህረጉ ቀጥሎ ነው፣ ስማለት ይቻላል። አወቃቀሩንም ስዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው ማሳየት የቻላል።



5


በግልፅ እንደሚታየው፣ የሁለቱ መስተጓምሮች አገባብ የተለያየ ነው። ያ በመነሻ ሲገባ፣ /-ኡ/ የሚለው ቅጣይ መስተጓምር ግን በመድረሻ ገብቶአል። ይህም ከፍ ሲል የጠቀስነውን የመስተዋድዶችን አገባብ የሚያስታውሰን ይመስላል። እንደ /ስ/ ያሉ ቅጣይ መስተዋድዶች በመነሻ ሲገቡ፣ እንደ <u>ድረስ</u> ያሉ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ መስተዋድዶች፣ በመድረሻ ላይ እንደሚገቡ አይተናል። ይሁን እንጅ፣ ከዚህ ላይ የምናየው የቅጣይ መስተጓምሩ አገባብ ከቅጣይ መስተዋድዶች አገባብ የተለየ ነው። ምክንያቱም መስተጓምሩ የሚገባው በመድረሻ ላይ በመሆኑ ነው። ቀደም ሲል፣ የስማዊ፣ የግሳዊ፣ የቅፅላዊ እና የተውላከ ግሳዊ ሀረጎች መሪ በቀኝ በኩል ስለሆነ፣ ከዚሁ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች መሪ ታህታይ ቦታም እንደ ሌሎቹ ሁሉ በሀረጉ መድረሻ ነው ፣ ብለን ደምድመን ነበር። በዚያው ድምዳሜ መሰረት፣ የመስተጓምራዊ ሀረጎች መሪም ታህታይ አገባብ በሀረጉ መድረሻ ነው ፣ ስማለት ይቻል ይሆናል። ጉዳዩ ሰፋ ያለ ጥናት ያስፈልገዋል። ከዚያ በመለስ ግን ከላይ በተራ ቁጥር (2) እና (5) የተመለከቱትን መስተጓምራዊ ሀረጎች እንደሚከተለው በአንድ ላይ አካቶ ማበቀመጥ ይቻላል።



ከዚህ ላይ <u>ትልቅ የቅኔ ተማሪ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ /-ኡ/ ከሚለው መስተጓምር ጋር በመመሊያነት ሊዋቀር ችሎአል። የመዋቅሩ ውጤት ስማዊ ሳይሆን፣ መስተጓምራዊ ሀረግ ነው። ምክንያቱም መሪው መስተጓምር ስለሆነ ነው።

ይህ መስተዓምራዊ ሀረግ ደግሞ ያ ከሚለው መስተዓምራዊ መሪ ጋር በመሙሊያነት ተዋቅሮ ንዑስ መስተዓምራዊ ሀረግ መስርቶአል። በዚህም ምክንያት ስማዊ ሀረጉ ሁለት ጊዜ ሊታመር ችሉአል፣ መጀመሪያ /-አ/ በሚለው ተራ መስተዓምር፥ ሁለተኛም ያ በሚለው ጠቁዋሚ መስተዓምር።


ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት አስብን። ይኸውም መሪው መስተዓምር ከስማዊ ወይም ከመስተዓምራዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀር የሚመስርተው ንዑስ መስተዓምሩዊ ሀረግ ከሆነ፣ አቢይ መስተዓምራዊ ሀረጉን እንዴት ይመስረታል? የሚል ነው። በሌሎቹ ሀረጎች አንዳየነው፣ አቢይ ሀረጎች ከንዑስ ሀረጎችና ከጣራጮች ይመስረታሉ። ገላጮቹ መሪው ንዑስ ሀረግ ስለሚጠቁመው (ሰለሚያመለክተው) ነገር፣ ባህሪ ወይም ድርጊት ተጨማሪ መግለጫ በመስጠት ሀረጉን ያጎላምሱታል። በመጨረሻም የተጎላመሰው ሀረግ በመስተዓምሮች አማካኝነት የትኑቱ፣ ስንትነቱና የማንነቱ ይታወቃል። ይህ አንግዲህ ቃላዊ ትርጉም ላላቸው መረዎቹና ሀረጎቻቸው ነው። መረው ቃላዊ ትርጉም ሳይሆን፣ መዋቅራዊ ግብር ብቻ ያለው ከሆነ፣ አጎላማሽና መስተዓምር ላይኖረው ይችላል። ስለዚህም የመስተዓምሩና የአጎላማሹ ቦታ ክፍት ይሆናል። በሌላ አገላለፅ፣ መስተዓምሮች ትርጉም ያላቸውን ሀረጎች ዕምር ከማድረግ ያስፈ ትርጉምም ሆነ ግብር ስለሌላቸው፣ ገላጭም ሆነ መስተዓምር አያስፈልጋቸውም። ከዚህ አንፃር የአንድን ተራ መስተዓምራዊ ሀረግ አወቃቀር እንደሚከተለው ማሳያት የቻላል።



በዋናው ሀረግ ስር በስረዝ የተሞላው ቦታ የመስተዓምር ሲሆን፥ በ(መስሀ2) ስር የሚታው ደግሞ የአጎላማሽ ቦታ ነው። በንዑሱ መስተዓምራዊ ሀረግ ስር መመሊያው

ስማዊ ሀረግ ገብቶአል። ይህም መስተዓምር መሙሊያ አንድ አነሳማሽና መስተዓምር እንደሌለው ያሳያል።

ከላይ ከሚታየው መዋቅር አሁንም አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ፣ አንድ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር እንደሚኖረውና ቦታውም ከአቢዩ ስማዊ ሀረግ ስር እደሆነ ገልፀን ነበር። አሁን ደግሞ መስተዓምሩ ከስማዊ ሀረጉ ውጭ ራሱን ችሎና ስማዊ ሀረጉን መሙሊያ አድርጎ እንደሚዋቀር እያየን ነው። እነዚህ ሁለት አመለካከቶች እይጣረሱም ወይ? የሚል ነው። መልሳችን እይጣረሱም ነው። መስተዓምሮቹን ጠቂዋሚ፣ መጣኝ እና አገናዛቢ ብለን ስለሰት ከፍሰናቸው ነበር። ከነዚህ መካከል ጠቂዋሚውና መጣኙ ከፍ ሲል በተገለፀው መሰረት ከስማዊ ሀረግ ጋር አየተቀናጁ የራሳቸውን ሀረግ ይመሰርታሉ። በዚህ አካሄድ የጠቂዋሚው መስተዓምራዊ ሀረግ አወቃቀር በተራ ቁጥር (5) እንደተመለከተው ሲሆን፣ የመጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ አወቃቀር ግን እንደሚከተለው ነው።




እንድ የሚለው መጣኝ መስተዓምር <u>ትልቅ የቅኔ ተማሪ</u> ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ ንዑሱን መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ አዋቅሮአል።

ከመጣኙና ከጠቂዋሚው መስተዓምር የሚለየው አገናዛቢው መስተዓምር ነው። ይህ መስተዓምር እንደሌሎቹ መስተዓምሮች ከስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ መስተዓምራዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም መስተዓምራዊ ሀረግ እንደገና የሌላ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር ሆኖ ይገባል። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

<u>የልጆቹ</u> የስዕል አስተማሪ 9

በዚህ ምሳሌ፣ <u>የልጆቹ</u> የሚለው መስተዓምራዊ ሀረግ ነው። መስተዓምሩም ‹-ኡ› ሲሆን መመሊያው <u>የልጆች</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። በዚህ ሀረግ መነሻ ላይ የምትታየው <u>የ</u> አገናዛቢ ምዕላድ ነች። <u>ልጆች</u> የሚለው ስም ባለገንዘብ መሆኑን ታመለክታለች። ከዚህ ግንዘቤ በመነሳት፣ ቡተራ ቁጥር (9) የተመለከተውን ስማዊ ሀረግ አወቃቀር እንደሚከተለው እናብያለን።

ስሀ 10



<u>ልጆቹ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ <u>አስተማሪ</u> ለሚለው ስም ባለገንዘብ ነው። አስተማሪው የልጆቹ ነውና። ከፍ ቢል እንደተገለፀው፣ <u>የ</u> የሁለቱ ስሞች ዝምድና የገንዘብና የባለገንዘብ መሆኑን ታመለክታለች። አገናዛቢ የተባለችውም ለዚህ ነው።


መስተዓምሩ አገናዛቢ ተውላጠ ስም ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን ከላይ የሚታየው ምላሌ የሚከተለውን ሊመስል የችላል።

<u>የእሱ</u> የስዕል አስተማሪ 11

<u>የእሱ</u> የሚለው መስተዓምር ነው። ከእሱ ጋር የሚዋቀረው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ተገድፎአል። ስለዚህም መስተዓምሩ ብቻውን ሊቆም ችሎአል። ስማዊ ሀረጉ በማይገደፍበት ጊዜ፣ አጠቃላይ መዋቅሩ የሚከተለውን ይመስላል።

<u>የእሱ ልጆች</u> የሰፅል አስተማሪ 12

በዕፀ መዋቅር ሲስፍር የሚከተለውን ይመስላል።



<u>ልጆች</u> የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ በሚገደፍበት ጊዜ፣ አገናዛቢው መስተዓምር ብቻውን ይቆማል። መሙሊያው ስማዊ ሀረግ የሚገደፈው ከመስተዓምሩ ጋር በቁጥር፣ በየታና በመደብ አንድ ሲሆን፣ ወይም የሚጠቁመውን ነገር ምንነት ከ<u>ሰውዶ ነገሩ</u> ስማወቅ የሚቻል ሲሆን ነው። ስምሳሌ፣ <u>የእሱ ሰው የሰፅል አስተማሪ</u> ብንል፣


እሱ የሚለው መስተዓምርና ስው የሚለው መሙሊያ ተመሳሳይ ነገርን ስለሚያመለክቱ፣ መሙሊያው ሊገደፍ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ መስተዓምሩም ሊገደፍ ይችላል። በዚህን ጊዜ መሙሊያው ስም የ የሚለውን የአገናዛቢ ምዕላድ በማለቀደም የልጆች የሚል ይሆናል። እጠቃላይ ሀረጉም የልጆች የበፅል እስተማሪ የሚል ይሆናል።

ከዚህ ቀጥለን ጠቁዋሚና አገናዛቢ መስተዓምሮች በአንድ መዋቅር ውስጥ ሲገኙ፣ ቅደም-ተከተላቸው ምን እንደሚመስል በሚከተለው ምሳሌ እማካኝነት እናሳያለን።


ያ የእሱ እንድ ብርሌ የገብስ ጠላ 14

የገብስ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ከፍ ሊል እንደገለፅነው የአንድ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር አገናዛቢ የሆነ ስማዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል። በዚህ መሰረት የእሱ ከሚለው አገናዛቢ መስተዓምር ጋር የተዋቀረ መሪ - አልባ ስማዊ ሀረግ አለ፣ ለማለት እንችላለን። ይህ አገናዛቢ መሪ - አልባ ሀረግ የገብስ ጠላ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር እንደሚከተለው ሆኖ ይዋቀራል።

15



ይህ አቢይ ስማዊ ሀረግ መጀመሪያ <u>አንድ ብርሌ</u> ከሚለው መጣኝ መስተ-ዓምራዊ ሀረግ ጋር ይዋቀራል። በሁዋላም <u>የእሱ</u> ከሚለው አገናዛቢ መስተዓምር ጋር ይቀናጃል። ከዚያም <u>ያ</u> ከሚለው ጠቁዋሚ መስተዓምር ጋር ይዋቀርና ዋናውን መስተዓምራዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመስርታል።



በአጠቃቀም ጊዜ <u>አንድ ብርሌ</u> የሚለው መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ <u>የእሱ የገብስ ጠላ</u> የሚለውን እገናዛቢ መስተዓምራዊ ሀረግ ቀድሞ ሊገባ ይችላል። ይህ ሲሆን የአጠቃላዩ ሀረግ ቅደም-ተከተል የሚከተለውን ሊመስል ይችላል።

ያ እንድ ብርሌ የእሱ የንብሰ ጠላ 17

በዚህ ክፍል እስካሁን በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። በክፍል ሁለት የአማርኛን ቃላት በስድስት ክፍለን ነበር። ክፍሎቹም ስም፣ ቅፅል፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው። በዚህ ክፍል፣ እነዚህ ክፍሎች እያንዳንዳቸው ሀረጋቸውን ሲመሰርቱ አይተናል። የሚመሰርቱትም ራሳቸው መሪ ሆነው፣ ሊሎቹን በመሙሊያነት፣ በዝላሞነትና በመስተዓምርነት በመውሰድ ነው። እያንዳንዱ መሪ ሌላ ቃል ነው። ሀረግ የሚሆነው ከሌላ ጋር ሲዋቀር ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ የሚመሰረተው የሀረግ አይነት በመሪው የቃል ክፍል ይወሰናል። የመሪው የቃል ክፍል ስም ከሆነ፣ የሀረጉ ክፍልም ስማዊ ይሆናል። የመሪው ክፍል ግስ ከሆነ፣ የሀረጉ ክፍልም ግሳዊ ይሆናል፣ ወዘተ ።

እያንዳንዱ ሀረግ የሚመሰረተው በወርድና በተዋረድ ከመሪው ቃል ጋር በሚዋቀሩ ሀረጎች ነው። ሀረጎቹ የመሪው መሙሊያ፣ መግለጫ እንዲሁም መወሰኛ ናቸው። መሙሊያዎቹ ስለ መሪው ቃል አይቀሬ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ። ያለነሱ መሪው የሚያስተላልፈው መልዕክት የተሙዋላ አይሆንም። ስለዚህም አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል።

መሪውና መሙሊያው ተቀናጅተው ንዑስ ሀረግ ይመሰርታሉ። ይህ ንዑስ ሀረግ ስለሚጠቁመው ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሁኔት ተጨማሪ መግለጫ ከሚሰጡ ገላጭ ሀረጎች ጋር ተዋቅሮ አቢይ ሀረግ ይሆናል። ንዑሱ ሀረግ የአቢዩ ሀረግ መሪ ነው። አቢዩ ሀረግ የሚጠቁመውን ነገር መጠን፣ የትነትና የማንነት የሚጠቁሙ ሀረጋት አሉ። እነዚህም በጥቅሉ መስተዓምራዊ ሀረጎች ናቸው። አቢዩ ሀረግ ከነዚህ ጋር ተዋቅሮ በይዘቱ ሙሉ፣ በመጠኑም ክፍተኛ ሀረግ ይሆናል።

በየሀረጉ ውስጥ ያየነውን ወርዳዊ ተዛምዶ እንደሚከተለው አጠቃለን እናለቀምጣለን።

መስተዓምር —— ገላጭ —— መሙሊያ —— መሪ 18

ይህ አጠቃላይ የቁዋንቁዋው መዋቅራዊ ባህረ ነው። በዝርዝር ሲታይ፣ መስተ-ዓምራዊና መስተዋድዳዊ ሀረጎች ብቻ በክፈል ከዚህ አጠቃላይ ስርዓት የሚያፈነግጡ ይመስላሉ። ይህም ቢሆን በላዕላይ አገባባቸው ላይ ሰናተኩር ነው። ታህታይ አገባባቸው እንደ አጠቃላዩ ስርዓት ነው፣ ብሎ ማሰብ ይቻላል። በዚህም ይህን ክፍል እንሰናበታለን።

መልመጃ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መዋቅሮች አይነትና የአወቃቀር ስርዓት ይግለፁ።

   (ሀ) በጣም ጎበዝ ወዝ አደር
   (ለ) በጣም ተሰቃየ
   (መ) በጣም በችግር ኖሩ

2. ከላይ የተሰጡትን መዋቅሮች መሪ ይጥቀሱና መሪ ስመሆናቸው ማስረጃ ይስጡ።

3. በተራ ቁጥር (1) በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ <u>በጣም</u> የሚለውን መጣኝ መስተዓምር መዋቅራዊ ዝምድና ይግለፁ።

4. <u>ተማሪ</u> ከሚለው ቃል ጋር ሊዋቀር የሚችል፡

   (ሀ) መመ.ሊያ
   (ለ) ገላጭ
   (መ) መስተዓምር

   ምሳሌ ይስጡ።

5. [ያ የእስቴር የሰዋሰው መፅሀፍ] የሚለውን ሀረግ በዕፀ-መዋቅር ተንትነው ያሳዩ።

6 በተራ ቁጥር (5) የተመለከተው ሀረግ አሻሚ ነው። አሻሚነቱ እስቴር የሚለው ስም ሙያ ላይ ነው። ስሙ የሚገልፀው የመፅሀፉን ደራሲ ወይም ያዥ (ባላደራ) ሊሆን ይችላል። ከዚህ አንፃር ሀረጉን በተለያየ ዕፀ-መዋቅር ተንትነው አሻሚነቱን ያሳዩ።

7. (ሀ) አንዳንድ ጊዜ በጠብ እንለያያለን።
   (ለ) አንዳንድ ጊዜ እንለያያለን።

7(ለ) ከ7(ሀ) ላይ የተመሰረተ ነው ብንል፡ <u>አንዳንድ ጊዜ</u> ስለሚለው መጣኝ ሀረግ አገባብ ምን ድምዳሜ መስጠት እንደሚቻል ያስረዱ።

አረፍተ ነገር

ሰዋሰው ጨዋታ አማርኛ ቅኔ
አጫውትሻለሁ እያፋታሁ እኔ።።

የማን እንደሆነ አይታወቅም።። ባገር ቤት (በገጠር) የተለመደ የዘፈን ግጥም ነው።። ምናልባት <u>ትውፊታዊ</u> ሳይሆን አይቀርም።። ከዚህ ላይ ልንጥቅሰው የፈለግነው ያለምክንያት አይደለም።። የቅኔንና የሰዋሰውን ግንኙነት የሚገልፅ ሀዝባዊ ይትበሀል ሆኖ ለላገኘነው ነው።። ቅኔ፣ በተለይም ሰምና ወርቅ የሚባለው ዘርፍ መሰረቱ ብሉም ትንታኔው አንዳንድ ጊዜ ቃላዊ፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዋሰዋዊ ነው።። ቃላዊ የሚሆነው፣ ከአንድ በላይ ትርጉም ከሚሰጥ ቃል ላይ ሊመሰረት ነው።። ከላይ በተጠቀሰው ቅኔ ውስጥ <u>አያፋታሁ</u> የሚለው ቃል የዚህ ምሳሌ ነው።። ቅኔ እየተረጎምኩ ወይም ባል አያፋታሁ ተብሎ፣ በሁለት መንገድ ሊተነተን ይችላል።። ዘፋኙ ቅኔ እየተረጎምኩ አጫውትሻለሁ የሚል መሰሉ፣ ከባልሽ ጋር አያፋታሁ እኔ አጫውትሻለሁ ይላታል።። በአንድ ቅርፅ ሁለት መልዕክት አስተላልፎአል ማለት ነው።።

ሰዋሰዋዊ የሚሆነው ቅኔው ከአንድ በላይ ያወቃቀር ስርዓት ሊኖረው ከሚችል መዋቅር ላይ ሊመሰረት ነው።። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።።


ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ
<u>በሬሳላይ</u> መጣሁ ከዚያ አስከዚህ ድረስ[1]።።

በሁለተኛው ሰንኝ ውስጥ የሚታየው <u>በሬሳላይ</u> የሚለው መዋቅር ንበት አሻሚ ነው።። አንደ ግሳዊ ወይም እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊነበብ ይችላል።። በግሳዊ ሀረግ ቅርፁ <u>በሬ ሳላይ</u> ተብሎ ይነበባል።። በዚህ መልኩ ሰውዬው ብዙ አገር አቁዋርጦ ሲመጣ፣ በሬ እንዳላየ ይናገራል።። በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው መዋቅር <u>በሬሳ ላይ</u> ተብሎ እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊነበብ ይችላል።። በዚህም ምክንያት ከመጀመሪያው ሀረግ የተለየ ትርጉም ይሰጣል።። ይኸውም ከሞጣ ጀምሮ ያለው ህዝብ ሰላለቀ፣ መንገዱ ሁሉ ሬሳ ብቻ ነው፣ የሚል ነው።። እንግዲህ አንዱ ላዕላይ መዋቅር አንድ ጊዜ እንደ ግሳዊ፣ ሌላ ጊዜ እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሆኖ ሊነበብ እና ሊተነተንም በመቻሉ የተለያየ ትርጉም ሊሰጥ ችሎአል።። ቅኔውም የተመሰረተው ከዚህ አሻሚ ንበት ላይ ነው።። ሁኔታው ባለፈው ከፍል ስለ ሀረግ ሰንወያይ ያየነውን አሻሚነት ሊያስታውሰን ይችላል።። ለምሳሌ፣ የሚከተለውን እንመልከት።።


[የጎጃም ነጭ ጤፍ አንጀራ] 1

[1] ብላቴን ጌታ ማሀተመ ስላሴ ወ.መ. (1959፡72)

ይህ ለማዊ ሀርግ ነው። የሀረጉ መሪ <u>አንጀራ</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ <u>ነጭ ጤፍ</u> የሚለው መሙሊያው፣ <u>የጎጃም</u> የሚለው ደግሞ አጎላማሹ ነው። በዕፀ-መዋቅር ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል።



በዚህ መልኩ፣ ሀረጉ ከጎጃም ስለ መጣ <u>ነጭ ጤፍ አንጀራ</u> ይገልፃል። በሌላ መልኩ ደግሞ <u>የጎጃም ነጭ ጤፍ</u> የሚለው፣ <u>አንጀራ</u> ለሚለው ስም መሙሊያ ሆኖ ሊገባ ይችላል። ይህ ሲሆን አወቃቀሩ የሚከተለውን ይመስላል።



በዚህ መልክ ሲታይ፣ መዋቅሩ ጤፉ የጎጃም መሆኑን ይገልፃል። አንጀራው የተጋገረው አዲስ አበባ ሊሆን ይችላል፤ ጤፉ ግን የጎጃም ነው። በተራ ቁጥር (2) በሚታየው ውስጥ እንጀራው የጎጃም ነው፤ ጤፉ የጎንደር ሊሆን ይችላል።

ዋናው ቁም ነገር የቃላቱም ሆነ የመዋቅሩ አሻሚነት አይደለም። ይህ የታወቀ የቁዋንቁዋ ባህሪ ነው። በሰነ-ፅሁፍ አንደውበት ይቆጠራል። ትልቁ ነገር ምንም ትምህርት የሌላቸው የቁዋንቁዋው ተናጋሪዎች፣ ይህን አሻሚነት ስመጎንዙበና ጥልቅ በሆነ ቅኔያዊ ንግግር ስመጠቀም መቻላቸው ነው። ይህ ችሎታ ባይኖራቸው ኖሮ፣ ለአባባሉ የተሰያየ ትርጉም እየሰጡ ስዛ ባሰው ሚስጥራዊ አማርኛ አይነጋገሩም ነበር። ችሎታው ራሱ ምንድን ነው? ከምንሰ ይመጣል? እንዴትስ ይገለፃል? እነዚህ የሰነ-ልሳንን ብቻ ሳይሆን፣ የሰነ-አዕምሮ ሰዎችንም ሲያነጋግሩ የኖሩ ጥያቄዎች ናቸው። በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው፣ በተሰያየ ጊዜም የተሰያየ መልስ ተሰጥቶአቸዋል። ወደ መልሶቹ አንሂድም። የአኛ ፍላጎት የችሎታውን ምንጭ ማወቅ ሳይሆን፣ ችሎታውን ራሱን በተቻለ መጠን ስመግለፅ መሞከር ነው።

ችሎታው ባለፉት ክፍሎች በተከታታይ ስማሳየት አንደሞከርነው፣ ድምፅን ከድምፅ፣ ምዕላድን ከምዕላድ፣ ቃላትን ከቃላት፣ ሀረግንም ከሀረግ ጋር በወርድና በተዋረድ እያቀናጁ የተሰያዩ መዋቅሮችን የመፍጠርና ለየመዋቅሮቹም የተሰያየ ቃላዊና ሀረጋዊ ትርጉም የመስጠት ነው። ሀሳብን በሚገባ ስመግለፅ የሚቻለው ድምፅንም ሆነ ቃላትን በተናጠል በመደርደር ሳይሆን፣ በወርድና በተዋረድ እያቀናጁ ስፋፊ መዋቅሮችን በመፍጠርና የተሰያየ ትርጉም በማላበስ ወይም በመስጠት ነው። የአንድ ቁዋንቁዋ ተናጋሪዎች የተፈጥሮ ልሳናዊ ችሎታም በመሰረቱ ይኸው ነው፤ መዋቅር። በዚህ ክፍል የምናየው በከፊልም ቢሆን፣ የዚህ አይነት ያወቃቀር ባህሪ ያላቸውን መዋቅሮች ነው። በከፊል ያልንበት ምክንያት ጉዳዩን በተሰያየ ደረጃ ባስፋት ክፍሎችም እያየነው ስለመጣን ነው።

ባለፈው ክፍል ያየነው የተሰያዩ ሀረጎችን ያወቃቀር ስርዓት ነው። እያንዳንዱ የአቢይና የንዑስ ቃላት ክፍል ከሌላ የቃላት ክፍል ጋር እየተዋቀረ ንዑስና አቢይ ሀረግ ሲመስርት አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ ከሀረግ ሰፋ ያለ ይዘት ያላቸውን መዋቅሮች ስርዓት እናያለን። እነዚህም የአረፍተ ነገር መዋቅሮች ናቸው። በዚህ ደረጃ የሚደረገው ጥናት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ስዋስው በመባል ይታወቃል። ስዚህ ነው፣ እኛም ይህን ክፍል "ሰዋስው ጨዋታ..." በሚል ስንኝ የጀመርነው። ይሁን እንጅ፣ ሰዋስው የሚለው ቃል ዛሬ የሚሸፍነው ፅንሰ-ሀሳብ ከጥንቱ የሰፋ ነው። ዛሬ፣ በጠባቡ ሲታይ፣ ቃሉ መዋቅርን ብቻ ይመለከታል። በሰፊው ሲታይ፣ እጠቃላይ የቁዋንቁዋ ትንተናን ወይም ጥናትን ያካትታል። ስለዚህም እሻሚ ነው። እሻሚነቱን ለማስወገድ፣ ቃሉን፣ ሰፊውን የቁዋንቁዋ ትንተናን ብቻ ስማመልከት እንጠቀምበታለን። ጠባቡን የመዋቅርን ክፍል ስማመልከት ስነ-መዋቅር የሚለውን ቃል

አንጠቀማለን። በዚያውም ስነ-መዋቅር የሰዋሰው፣ ማለትም የሰፈው የቁዋንቁዋ ጥናት አንድ ንዑስ ክፍል መሆኑን እናስገነዝባለን።

የአረፍተ ነገር አይነቶች

ባለፉት ሁለት ክፍሎች የቃላት ክፍሎችንና የሀረግ አይነቶችን ተመልክተናል። የሀረግ አይነቶች በቃላት ክፍሎች እንደሚመሰረቱና በነሱም እንደሚወሰኑ ተገንዝበናል። ለምሳሌ ስማዊ ሀረግ በስም ክፍል ወሰጥ በሚመደቡ ቃላት ይወሰናል። ከዚህ አኩዋያ የአረፍተ ነገር አይነት በምን ላይ ይመሰረት ይሆን?

ወደ አረፍተ ነገር አይነቶች ከመግባታችን በፊት ስለ አረፍተ ነገር ምንነት ትንሽ እንወያይ። አረፍተ ነገር በቁሙ የነገር መቁዋጫ ወይም ማረፊያ ማለት ነው። እንድ ሀሳብ ተሙዋልቶ ከተገለፀ በሁዋላ፣ ሌላ ሀሳብ አስኪመጣ ድረስ የሚደረግ ረፍት እንደማለት ነው። በቅርፁ አረፍተ ነገር የተለያዩ ሀረጎች በወርድና በተዋረድ ተቀናጅተው የሚመሰርቱት ስፊ መዋቅራዊ አሀድ ነው። ለሰነ-ልሳናዊ ትንተናም እቢዩም ሆነ ንዑስ አሀድ እሱ ነው። እንድ መዋቅር ከአረፍተ ነገር ከበለጠ፣ <u>ድርሳን፣</u> ከአረፍተ ነገር ከነሰ፣ ሀረግ ይሆናል። ሁለቱም ለስነ-ልሳናዊ ትንታኔ አይሆኑም፤ ካልቸገረ በስተቀር። ድርሳኑ ይበዛል፤ ሀረጉም የዚያኑ ያህል ሊያንስ ይችላል። ድርሳኑ በአረፍተ ነገር ደረጃ ሊታዩ የማይችሉ ባህሪያትን ያጣቅሳል። ስለዚህም ድርሳኑን በድርስት፣ አረፍተ ነገሩን በመዋቅር እየለዩ ለየብቻ ማጥናት ያስፈልጋል። ርግጥ ይህ ሲባል፣ አረፍተ ነገሩ ድርሰታዊ ዳራ አይኖረውም ማለት አይደለም። የጥናቱ ትኩረት በዳራው ላይ ሳይሆን በአረፍተ ነገሩ አወቃቀር ላይ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ከአጠቃቀም እንፃር፣ አረፍተ ነገር የተለያዩ ተግባራት አሉት። ከነዚህም አንዱ ሙሉ ሀሳብን መግለፅ ነው። ሙሉ ሀሳብ ለንል ምን ማለታችን እንደሆነ፣ በሚከተሉት ምሳሌዎች እናስረዳለን።

(ሀ) አንድ ትልቅ ልጅ 1
(ለ) በሁለት ብር
(መ) አራት እንቁላል ገዛ

እነዚህ ሶስት የተለያዩ ሀረጎች ናቸው። የመጀመሪያው ስማዊ፣ ሁለተኛው መስተዋድዳዊ፣ መጨረሻው ደግሞ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። በተናጠል ሲነገሩ፣ ሀረጋዊ ሀሳብ ይገልፃሉ። ሀረጋዊ ሀሳብ ግን ሙሉ አይደለም። ስለዚህም ጥያቄ ያስከትላል። ለምሳሌ የመጀመሪያውን ሀረግ ወስደን፣

አንድ ትልቅ ልጅ 2

ብንል፣ የሚሰማን ሰው፣

አንድ ትልቅ ልጅ ምን ሆነ ወይም ምን አደረገ? 3

ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ጥያቄውን አይቀሬ የሚያደርገው፣ <u>አንድ ትልቅ ልጅ</u> ከማለት በሰተቀር፣ ሰሰ ልጁ የተናገርነው ሌላ ነገር አለመኖሩ ነው። ባለመኖሩም የሀሳብ ጉድለት ሊከሰት ችሎአል። አንደዚሁም፣

በሁለት ብር 4

ብለን ብናቆም፣ አሁንም በሁለት ብር ምን ተደረገ? የሚል ጥያቄ ይነሳል። ጥያቄው መነሳቱ አሁንም የጎደለ ሀሳብ ስመኖሩ ምልክት ነው።

አራት አንቁላል ገዛ 5

የሚለውም አንደዚሁ በተናጠል ቢነገር፣ ማነው የገዛው? ያሰኛል። ሰስቱም ሀረጎች በተናጠል ሲነገሩ፣ <u>አይቀሬ</u> ጥያቄ ያሰከትላሉ ማለት ነው። ጥያቄ የሚነሳው የሀሳብ ጉድለት ወይም ግድፈት ሲከሰት ሰለሆነ፣ ሀረጎቹ ሀሳቡ-ጎደሉ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል።

ሀረጎቹን በተናጠል ሳይሆን፣ በአንድ ላይ ብናቀናጃቸው፣

አንድ ትልቅ ልጅ በሁለት ብር አራት እንቁላል ገዛ 6


የሚል ሰፊ መዋቅር ይሰጡናል። ይህ መዋቅር ከፍ ሲል እንደተነሱት ያሉ አይቀሬ ጥያቄዎችን አይጋብዝም። ጥያቄ አለማሰነሳቱ የሚጠቁመው የጎደለ ሀሳብ አለመኖሩን ነው። ሰሰዚህም ሙሉ <u>ሀረጋዊ</u> መዋቅር ነው። ርግጥ ሰሚያችን መቸ፣ የት፣ እንዴት፣ ከማን ጋር ገዛ? አያለ ሊመረምረን ይችላል። እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች ግን ከፍ ሲል እንደ ተነሱት አይቀሬ አይደሉም። ላይነሱ ይችላሉና። የማይነሱበት ምክንያት መዋቅሩ መያዝ ያለበትን አይቀሬ ሀሳብ አሙዋልቶ መግሰፁ ነው። አንግዲህ ከዚህ አኩዋያ ሲታይ፣ አረፍተ ነገር አይቀሬ ሀሳብን አሙዋልቶ የያዘ ሰፊ ሀረግ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ይህ ከተግባሩ አንፃር ሲታይ ነው።

ከመዋቅራዊ ቅርፁ አንፃር ሲታይ ደግሞ ለየት ያለ ብያኔ ሊሰጠው ይችላል። ለምሳሌ፣ ከላይ የተሰጠውን አረፍተ ነገር ቅርፅ ብንመለከት፣

በመጀመሪያ ደረጃ የሁለት አቢይ ሀረጎች ቅንጅት ሆኖ አናገኘዋለን። ሀረጎቹም አንድ ትልቅ ልጅ እና በሁለት ብር እራት እንቁላል ገዛ የሚሉት ናቸው። ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው፣ እነዚህ ሀርጎች ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። የስማዊ ሀርጉ መሪ ልጅ የሚለው ስም ሲሆን፣ የግሳዊ ሀረጉ መሪ ገዛ የሚለው ግስ ነው። እነዚህ መሪዎች ከመሙሊያ፣ ከገላጭ አጎላማሽ እንደዚሁም ከመስተዓምር ጋር ደረጃ በደረጃ ተዋቅረው አቢይ ሀረግ ሆነዋል። አረፍተ ነገሩን ሲመሰርቱ የሚቀናጁበት ስርዓት እንደሚከተለው ነው[2]።

[ስሀ + ግሀ] 7


ይህም ማለት ስማዊ ሀረጉ ቀድሞ፣ ግሳዊ ሀረጉ እሱን ተከትሎ ይገባል ማለት ነው። ሁለቱ ሀረጎች በዚህ ሁኔታ ተከታትለው ሲመጡ የሚፈጠረው መዋቅር አረፍተ ነገር ነው። አረፍተ ነገሩ ከሁለቱ ሀረጎች ጋር ያለውን መዋቅራዊ ተዛምዶ እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



8


መዋቅሩ፣ አረፍተ ነገር በውስጡ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን አቅፎ እንደሚይዝ ያመለክታል። ይሁን እንጅ፣ ውስጣዊ ይዘቱ በዚህ ብቻ አይወሰንም። በስማዊ ሀረጉም ሆነ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ ሌሎች ሀረጎች አሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ትልቅ ልጅ በሚለው ስማዊ ሀረግ ውስጥ ትልቅ ልጅ የሚል ሌላ ሀረግ አለ። ይህ ሀረግ ትልቅ የሚለው ቅፅልና ልጅ የሚለው ስም ቅንጅት የፈጠረው ንዑስ መዋቅር ነው። ሀሳባዊ ይዘቱም የልጁ ትልቅነት ነው። መዋቅሩ ከአንድ ሰምና ከአንድ ቅፅል ብቻ የተዋቀረ በመሆኑ ስፋቱ አንድ ትልቅ ልጅ ከሚለው አቢይ ስማዊ ሀረግ ያነሰ ነው። አቢዩ ስማዊ ሀረግ የዚህ ንዑስ መዋቅርና አንድ የሚለው መጣኝ መስተዓምር ቅንጅት ነው። በአረፍተ ነገሩ ውስጥ፣ የአጠቃላዩን ስማዊ ሀረግ ወርዳዊና ተዋረዳዊ አወቃቀር እንደሚከተለው እናሳያለን።

[2] የሀረጎቹን ታህታይ አሰላለፍ በተመለከተ ባህ (1970)ን እንዲሁም ሀድሰን (1972)ን ይመልከቱ።



9

ከዚህ ሰማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገሩን የሚመሰርተው ግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ መዋቅር ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡




10

[3] ባለፈው ክፍል ሰለ መስተዓምራዊ ሀረግ ስንወያይ፣ በዚህ ቦታ የሚገኘው አገናዛቢ መስተዓምር አንደሆነና ጠቁዋሚና መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረጎች ሰማዊ ሀረጉን መሙሊያ እያደረጉ የራሳቸውን ሀረግ እንደሚመሰርቱ ገልፀን ነበር፡፡ ከዚህ ላይ ግን ስቀላል አቀራረብ ስንል አንደተስመደው፣ ሁሉንም መስተዓምራዊ ሀረጎች በሰማዊ ሀረጉ ውስጥ እናሳያለን፡፡

በግልፅ እንደሚታየው፣ ግሳዊ ሀረጉ በውስጡ አንድ መስተዋድዳዊ ሀረግና አንድ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ አቅፎአል። ንዑሱ ግሳዊ ሀረግም አንደዚሁ አንድ ሰማዊ ሀረግና ግስ ይዞአል። ግሱ የንዑሱ ሀረግ መሪ ሲሆን፣ ሰማዊ ሀረጉ የዚሁ መሪ ግስ መሙሊያ ነው። መስተዋድዳዊ ሀረጉ የንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ገላጭ አጎላማሽ ነው። የሚያጎላምሰውም በግሱ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀሚያ (ማድረጊያ) በመግለፅ ነው።

ይህ ግሳዊ ሀረግ ከላይ በተራ ቁጥር (9) ከተመለከተው ሰማዊ ሀረግ ጋር በተራ ቁጥር (8) በተገለፀው የአወቃቀር ሰርዓት ወይም ቅደም-ተከተል መሰረት ሲቀናጅ የሚፈጠረው አረፍተ ነገር የሚከተለውን ይመሰላል።



ይህ አንግዲህ ሙሉ ሀሳብን የሚገልፅ ሙሉ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ነው። በውስጡ ሰማዊና ግሳዊ ሀረጎችን አቅፎአል። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ደግሞ በውስጣቸው ሌሎች ሀረጎችን አቅፈዋል። ሀረጎቹ የመሪ፣ የመሙሊያ፣

የአንላማሽና የመሰተዓምር ቅንጅቶች ናቸው። አቀነጃጀቱም ወርዳዊና ተዋረዳዊ ነው። ወደፊት የምናያቸው የተለያዩ አረፍተ ነገራዊ መዋቅሮች ሁሉ በዚህ መሰረት ከሀረጋት የሚዋቀሩ ናቸው። አንዱ ከሌላው የሚለየው በሚፈፅመው ተግባርና በውስጡ በሚያቅፈው የሀረግ መጠንና አይነት ነው።

ከዚህ ላይ ታዲያ አንድ ቁልፍ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም አረፍተ ነገር ከአቢይ ለማዊና ግላዊ ሀረጎች የሚፈጠር ስፊ መዋቅር ነው ካልን፣ የዚህ ስፊ መዋቅር መሪ ከሁለቱ ተዋቃሪ ሀረጎች አንደኛው መሆን አለበት። ባለፈው ክፍል ለለሀረግ ለንወያይ እንዳየነው፣ የአንድ ሀረግ አይነት በመሪው ቃል እንደሚወሰን አይተናል። የለማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው፤ የግላዊ ሀረግም ግለ ነው። አረፍተ ነገር ከፍ ሲል እንደተገለፀው ስፊ ሀረጋዊ መዋቅር ከሆነ፣ የዚህ ሀረጋዊ መዋቅር መሪ ግስ ነው? ወይስ ስም? ጥያቄው መሰረታዊ ነው። መልሱ ወደ ከፍተኛ ትውረት ይወሰደናል። ባጭሩ ግን የማንኛውም አረፍተ ነገር መሪ ግሰ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ከዚህ ሀረግ ጋር የሚዋቀረውና ባለቤት የምንለው ለማዊ ሀረግም የግላዊ ሀረጉ አድራጊ መለተዓምር ነው። በዚህ አመለካከት መሰረት፣ ከላይ በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው መዋቅር አነ ላይሆን፣ ግህ መሆን አለበት። ይህ አመለካከት ባለፈው ክፍል ስለሀረግ ለንወያይ ከጠቀስነው አጠቃላይ የሀረግ አወቃቀር መርህ ጋር ይጣጣማል። መርሁ ማንኛውም ሀረግ ስር ከመሰረተበት ዘር-ቃል የተለየ ሊሆን አይችልም የሚል ነበር። ለሩ ስም ከሆነ፣ ሀረጉ ለማዊ መሆን አለበት። በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ግን ይህን ይፃረራል። ምክንያቱም አነ የሚለው ከለማዊ ሀረጉም ሆነ ከግላዊ ሀረጉ ላይ የተመሰረተና ያደገ አይደለም። በሁለቱ ሀረጎች እናት ላይ ጉብ ያለ ባዕድ ነገር ነው። መርሁን የሚከተለው እንድም የለማዊው አለያም የግላዊው ሀረግ እፅረ ሲሆን ነው። ከሁለቱ የየትኛው እንደሆነ ለመረዳት ትርጉሙን ማየት ያስፈልጋል። አጠቃላይ መዋቅሩ ለለ እንቁላል መግዛት ለለሆነና ይህን የሚገልፀው መሪ ቃልም ግሱ ለለሆነ፣ የሀረጉ ክፉል ግላዊ መሆን አለበት። ለጊዜው በዚሁ እንተወው። የጥያቄው መልስ ግን በዚህ ብቻ አያበቃም። ግላዊ ሀረጉ ራሱ የሌላ መሪ መመሰያ ነው። ወደ ዝርዝሩ አንገባም፤ ለተነሳንበት አጠቃላይ ዓላማም ብዙ አስፈላጊ አይደለም። ስለዚህ ወደጀመርነው የአረፍተ ነገር አይነት እንመለስና የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ተግባርና የአወቃቀር ለርዓት በተለመደው አካሄድ እንመልከት።

ተራ አረፍተ ነገር

ከመዋቅራዊ ይዘት አኩዋያ አረፍተ ነገር ተራና ውስብስብ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ተራ አረፍተ ነገር የሚባለው በውስጡ አንድ ግላዊ ሀረግ ብቻ የያዘ መዋቅር ነው። የሀረጉ መሪ የሆነው ግስ ሳቢ ከሆነ፣ መሙሲያ ለማዊ ሀረግ ይኖረዋል። ለማዊ ሀረጉ የግሱ ተላቢ ይባላል። ከግሱ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን ግላዊ ሀረግ ይመሰርታል። በዚህ ሁኔታ የተመሰረተው ንዑስ ግላዊ ሀረግ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና ከመጣኝ መለተዓምራዊ ሀረጎች ጋር

ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። በዚህ አይነት ደረጃ በደረጃ የተመሰረተው አቢይ ግሳዊ ሀረግ በግሱ የተገለፀውን ተግባር የሚፈፅመውን አካል ከሚገልፅ ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ የአረፍተ ነገሩን መዋቅር ይፈጥራል። ይህ ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ይባላል።

ከዚህ አኩዋያ ሊታይ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው መዋቅር ተራ አረፍተ ነገር ነው። ምክንያቱም አንድ ግሳዊ ሀረግ ስላሰው ነው። የዚህ ግሳዊ ሀረግ መሪ <u>ገዛ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ነው። ሳቢ በመሆኑ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ያስፈልገዋል። በዚህም ምክንያት <u>አራት አንቁላል</u> የሚለው ሰማዊ ሀረግ በመሙሊያነት፣ ብሎም በተሳቢነት፣ ከዚሁ ግስ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። <u>በሁለት ብር</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የዚህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ገሳጭ አጎሳማሽ ነው። ተግባሩ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀሚያ (ማድረጊያ) በመግለፅ፣ ስለ ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ተጨማሪ መረጃ መስጠት ነው። መረጃው መሰረታዊ ሳይሆን፣ ተጨማሪ በመሆኑ ይህን መረጃ የሚገልፀው አጎሳማሽ ሀረግ ሊገደፍ ይችላል። መሙሊያው ስማዊ ሀረግ ግን ሊገደፍ አይችልም። ምክንያቱም ያለሱ ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስለ መሪው ግስ ሙሉ ሀሳብ ስለማይሰጥ ነው። ሙሉ ሀሳብ ካልሰጠ ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል። በይዘቱም ሆነ በመዋቅራዊ ቅርፁ የተሙዋላ አይሆንምና።

ከላይ እንደተገለፀው፣ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀረው ስማዊ ሀረግ ባለቤት ይባላል። ባለቤትነቱ ለአረፍተ ነገሩ ነው። አገባቡ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሲሆን፣ መዋቅራዊ አወራረዱም በተራ ቁጥር (11) ላይ እንዳየነው በቀጥታ ከአረፍተ ነገሩ አንጉዋ ላይ በመውረድ ነው። በዚህም ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ ላይ ከሚወርዱት ገሳጭ ሀረጎች፣ አንዲሁም ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ሰር ከሚወርደው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይለያል። ሁለተኛም ባለቤት ስማዊ ሀረግ እንደ መሙሊያ ሰማዊ ሀረግ አይቀሬ ነው። ሁለቱ ስማዊ ሀረጎች ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ከሚወርዱት ገሳጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች በአይቀሬነታቸው ይለያሉ። በዚህ አይነት በታህታይ መዋቅር ውሰጥ ከሚወርዱበት አንጉዋ አንፃር ሀረጎችን ባለቤት፣ አጎሳማሽ እና መሙሊያ፣ እንዲሁም አንደሚሰጡት መረጃ አይነት፣ ቀሪና አይቀሬ እያሉ በቦታቸውና በተግባራቸው መሰረት መለያየት ይቻላል። ይህ መዋቅራዊ (አገባባዊ) መለያቸው ነው።

ሌላው መለያቸው ምዕላዳዊ ነው። ባለቤትም ሆነ ተሳቢ አንዲሁም አጎሳማሽ ሀረግ በቅጣይ ምዕላዶች ይጠቆማል። ምዕላዶቹ የሚገኙት በአረፍተ ነገሩ ግስ አምድ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ነው። በመነሻ የሚገኙት አምዱ ካልዓይ አንቀፅ ሲሆን ነው። በመድረሻ የሚገኙት፣ የቀዳማይ ወይም የጨራሽ አንቀፅ አምድ ሲሆን ነው። ምዕላዶቹ አፀፋ ተውላጠ ስም በመባል ይታወቃሉ። የሀረጎቹ እጣፈ ወይም ነፀብራቅ ናቸው። ዝርዝራቸውን በርባታው ከፍል አሳይተናል። ቢሆንም ለማስታወስ ያህል፣ ብዙ ዝርዝር ውሰጥ ሳንገባ የቀዳማይ አንቅፅ አፀፋዎችን ብቻ እንደገና እናሳያለን።

ባለቤት			ተሳቢ		አጎላማሽ	
መደብ	ነጠላ	ብዙ	ነጠላ	ብዙ	ነጠላ	ብዙ
1	-ሁ	-ን	-ኝ	-ን	-ብ-ኝ	-ብ-ን
2	-ህ	-ኣችሁ	-ህ	-ኣችሁ	-ብ-ህ	-ብ-ኣችሁ
አን	-ሽ	-ኣችሁ	-ሽ	-ኣችሁ	-ብ-ሽ	-ብ-ኣችሁ
3	-ኧ	-ኡ	-ው	-ኣቸው	-ብ-ኧት	-ብ-ኣቸው
አን	-ኧች	-ኡ	-ኣት	-ኣቸው	-ብ-ኣቸው	-ብ-ኣቸው

1 የቀዳማይ አንቀፅ የባለቤትና የተሳቢ አፀፋ

እነዚህ የባለቤት፣ የተሳቢና የመስተዋድዳዊ ሀረግ አፀፋ ናቸው። ማንኛውም ባለቤት ስማዊ ሀረግ በባለቤት አፀፋ ይጠቀሳል። ማንኛውም ዕምር የሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግም በተሳቢ አፀፋ ይጠቀሳል። ማንኛውም ገሳጭ (አጎላማሽ) መስተዋድዳዊ ሀረግ በመስተዋድድ አፀፋ ይጠቀሳል። አፀፋዎቹ በተለያየ ርከን ላይ የሚገኙ ሀረጎቹን ስለሚጠቅሱ፣ በተግባራቸው መዋቅራዊ ናቸው። በቅርፃቸው ግን ምዕላዳዊ ናቸው። ስለሆኑም ከላይ እንደሚታየው፣ የሚገኙት ከየግሱ አምድ ላይ ነው። አንድ አምድ ሊይዝ የሚችለው ሁለት አፀፋዎችን ብቻ ነው። የባለቤት አፀፋ ምን ጊዜም አይቀሬ ነው። ከእሱ ቀጥሎ የተሳቢ ወይም የመስተዋድድ አፀፋ ሊመጣ ይችላል። የመስተዋድዳዊ አፀፋ /ብ-/ የሚለው መስተዋድድና የተሳቢ አፀፋ ቅንጅት ነው። ለምሳሌ /ብ-ኝ/ የሚለውን ብንመለከት፣ የመስተዋድዱ /ብ-/ እና /-ኝ/ የሚለው የአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተሳቢ አፀፋ ቅንጅት እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ አንፃር በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ ያለውን የአፀፋ ሁኔታ እንመልከት።

2

(ሀ) አስቴር ልጁን ሰደበችው (ሰደብ-ኧች-ኡ)
(ለ) አስቱር በርሳሱ ለዕሱን ሳለችበት (ሳል-ኧች-ብ-ኧት)
(መ) *አስቴር በርሳሱ ስዕሱን ሳለችውበት (ሳል-ኧች-ኡ--ብ-ኧት)

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>አስቴር</u> የሚለው የአንለታይ ዖታ ስም ባለቤት ስለሆነ፣ /-ኧች/ በሚለው የባለቤት አፀፋ ተጠቅሶአል። <u>ልጁን</u> የሚለው ዕምር ስማዊ ሀረግ ተሳቢ ስለሆነ /-ኡ/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሶአል። የሁለቱ አፀፋዎች ቅደም-ተከተል የባለቤቱ አፀፋ ቀድሞ፣ የተሳቢው ደግሞ አሱን ተከትሎ እንደሚገባ ያሳያል። ይህም ቅደም-ተከተል በመዋቅር ውስጥ ባለቤትና ተሳቢ ሀረጎች የሚከተሉትን ስርዓት ያንፀበርቃል። በመዋቅር ውስጥ ባለቤቱ ሀረግ ተሳቢውን እየቀደመደ እንደሚገባ ሁሉ፣ በግሱ አምድ ላይም የባለቤቱ አፀፋ የተሳቢውን አፀፋ እየቀደመደ ይገኛል።

በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>አስቴር</u> ከሚለው ባለቤት በተጨማሪ <u>በርሳሱ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ እና <u>ለዕሱን</u> የሚለው ዕምር ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይገኛሉ። በአፀፋ የተጠቀሱት የባለቤቱና የመስተዋድዳዊው ሀረግ ብቻ ናቸው። <u>ደብዳቤውን</u> የሚለው ዕምር ተሳቢ ሀረግ ሲጠቀስ አልቻለም። ምክንያቱም የግሱ አምድ ሲያስከትል የሚችለው ሁለት አፀፋዎችን ብቻ ነው። ሶስቱም ሀረጎች

በአፀፋ ከተጠቀሱ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አይኖረውም። ምሳሌ (መ) የሚያመለክተው ይህንኑ ሁኔታ ነው።

አንግዲህ ማንኛውም ስማዊ ሀረግ በባለቤትነት ወይም በተሳቢነት፣ እንዲሁም ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ በገላጭነት (አጎላማሽነት) መግባቱን ለማወቅ፣ መጀመሪያ ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (11) እንደተመለከተው፣ መዋቅራዊ አቀማመጡን፣ ከዚያም ምዕላዳዊ አፀፋውን መመልከት ያስፈልጋል። ሁለቱን መለያዎች መዋቅራዊና ምዕላዳዊ ልንላቸው እንችላለን። ከሁለቱ መለያዎች፣ ይበልጥ የሚያስተማምነው ምዕላዳዊው መስፈርት ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ብዛህድ ላይታይ ይችላል። ሁለተኛም በግህድ በሚታይበት ጊዜም ቢሆን፣ የሚታይበት ቦታ ሁል ጊዜ የአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይሆን ይችላል። ባጭሩ በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ የሚታይ ስማዊ ሀረግ ሁሉ፣ ባለቤት ላይሆን ይችላል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።


(ሀ) አስቴር ፊተናዋን ጨረሰች (ጨረስ-ኧች) መሰለኝ (መስል-ኧ-ኝ) 3
(ለ) አስቴር ልጆች አሉአት (አል-ኡ-አት)

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ ሁለት ግሶች አሉ፤ <u>ጨረሰች</u>ና <u>መሰለኝ</u>። ሁለት ግሶች አሉ ማለት ደግሞ፣ ሁለት ግሳዊ ሀረጎች ብሉም ሁለት አረፍተ ነገሮች አሉ፣ ማለት ነው። <u>ጨረሰች</u> የሚለው ግስ /-ኧች/ የሚል የባለቤት አፀፋ አለው። ይህም አፀፋ የሚጠቅሰው <u>አስቴር</u> የሚለውን ስም ነው። ስለዚህ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም የዚህ <u>ፊተናዋን ጨረሰች</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው። <u>መሰለኝ</u> የሚለው ግስ ደግሞ /-ኧ/ የሚል የባለቤት አፀፋ አለው። ይሁን እንጅ በዚህ አፀፋ የሚጠቀሰና ሰባተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በግህድ አይታይም። በግህድ የሚታየው ባለቤት <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ነው። እሱ ደግሞ የዚህ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም <u>መስል-ኧ-ኝ</u> በሚለው ግስ ውስጥ /-ኧ-/ የሚለው አፀፋ የሚያመለክተው ተባዕታይ ፆታ የሆነን ስም ነው። ስለዚህ የእንስታይ ፆታ ስም የሆነው፣ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም፣ የዚህ ግስ ባለቤት ሊሆን አይችልም።

በምሳሌ (ለ) ውስጥ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ የሚታየው ስም አስቴር ነው። ከግሱ አምድ ተጥሎ የሚታየው አፀፋ /-ኡ/ ነው። ሰባተኛ መደብና የብዙ ቁጥር የሆነን ባለቤት ስማዊ ሀረግ ያመለክታል። በዚህ አፀፋ ሊጠቀስ የሚችለው ስም ልጆቿ የሚለው ነው። ስለዚህም ይህ ስም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አገባቡ ግን በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ አይመስልም። በእንፃሩ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ይግባ እንጅ፣ ባለቤት አይደለም፤ ተሳቢ ነው። በተሳቢነቱም /-አት/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሰአል። ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (11) በተመለከተው ዕፀ-መዋቅር፣ ተሳቢ (መሙሊያ) ስማዊ ሀረግ ከንዑስ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ፣ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግም ከአረፍተ ነገሩ አንጉዋ እንደሚወርድ ገልፀናል። አስቴር የሚለው ስም ተሳቢ ሆኖ ሳለ፣ ከግሱ አካባቢ ርቆ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ መታየቱ፣ ከዚህ ህግ ውጭ ያደርገዋል። ይህ ግን ምሳሌዎቹን ከላይ በቀረቡበት መልካቸው ስናያቸው ነው። ይህ ደግሞ ላዕላይ አቀማመጣቸው ነው። በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው አወራረድና ድንጋጌ በሀረጎቹ ታህታይ

አቀማመጥ ላይ የተመሰረተ ነው። በታህታይ አወቃቀር፣ ከአረፍተ ነገር አንጉዋ ላይ የሚወርድ ስማዊ ሀረግ ባለቤት፣ ከንዑስ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ ላይ የሚወርድ ስማዊ ሀረግ ተሳቢ፣ እንዲሁም ከአቢይ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ ላይ የሚወርድ ማንኛውም ሀረግ ገላጭ ነው።

ይህ የአወራረድ ስርዓት ምን ጊዜም አይቀየርም። በስርዓቱ መሰረት በየቦታቸው መውረድ ያለባቸው ሀረጎችም ይወርዳሉ። ከወረዱ በሁዋላ ግን ቦታ ሊቀይሩ ይችላሉ። ቦታ ቀይረው የሚታዩበት መዋቅር ላዕላይ ይባላል። ከታህታዩ የወጣና በእሱም ላይ የተመሰረተ ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ምሳሌ 3(ለ) ከሚከተለው ታህታይ መዋቅር ላይ የተመሰረተ ላዕላይ መዋቅር ነው፣ ለማለት ይቻላል።



ይህ በተራ ቁጥር 3(ለ) የሚታየው ምሳሌ ታህታይ መዋቅር ነው። በግልፅ እንደሚታየው <u>አስቴር</u> የሚለው ስም /ለ-/ የሚለው መስተዋድድ መሙሊያና ተሳቢ ነው። አወራረዱም ከግሳዊ ሀረጉ አንጉዋ ላይ ነው። <u>ልጆች</u> የሚለው ስም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አወራረዱም ከአረፍተ ነገሩ አንጉዋ ላይ ነው። አስቴር የሚለው የመስተዋድዱ ተሳቢ ስም ቦታውን ለቆ፣ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ቀድሞ ሲገባና መስተዋድዱ /ለ-/ ከቦታው ሲጠፋ፣ አረፍተ ነገሩ

በ3(ለ) የሚታየውን ላዕላይ ቅርፅ ይይዛል[4]። ከዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የማንኛውንም ሀረግ መሰረታዊ አገባብ ለመወሰን ላዕላይ አቀማመጡን ሳይሆን፣ ታህታይ አወራረዱን መመርመር ያስፈልጋል። ካሁን በፊት እንደገለፅነው፣ ታህታይ መዋቅር ረቂቅና አዕምሮአዊ ነው። ላዕላይ መዋቅር ግህድና አንደበታዊ ነው። የመጀመሪያው በአዕምሮ የሚታሰብ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአንደበት የሚነገር ነው። በሁለቱ መካከል ሁል ጊዜ ልዩነት አለ። ይህ የማንኛውም መዋቅር ባህሪ ነው። በምዕራፍ አንድ በስነ-ድምፁ፣ ከዚያም በሁዋላ በስነ-ምዕላዱ፣ አሁን ደግሞ በስነ- መዋቅሩ አየታየ ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይህም አስቴር የሚለው ተሳቢ ስም ታህታይ ቦታውን ለቆ የሚሄደው ለምድን ነው? የሚል ነው። <u>አስቴር</u> የሚለውና <u>ልጆቹ</u> የሚለው ስም ግንኙነት የገንዛቢና የተገንዛቢ ነው። <u>አስቴር</u> ገንዛቢ (ባለገንዘብ) ስትሆን፣ <u>ልጆቹ</u> የሚለው ተገንዛቢ ነው። የዚህ አይነት ግኙነት ያላቸው ስሞች የላዕላይ አገባብ ስርዓት ገንዛቢውን ቀዳሚ፣ ተገንዛቢውን ተከታይ የሚያደርግ ነው። ባለገንዘብ ቀዳሚ፣ ገንዘብ ተቀዳሚ (ተከታይ) መሆኑ ከስው ልጅ ልዕልና ጋር የተያያዘ መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ገንዘብ ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለገንዘብ አልተፈጠረም። ርግጥ፣ ለገንዘብ ብቻ የተፈጠሩ የሚመሳሰሉ ይኖራሉ።

ወደ ጉዳያችን እንመለስ። ገንዛቢ ቀድሞ፣ ተገንዛቢ ተከትሎ የመግባቱ ነገር በማንኛውም ቁዋንቁዋ የሚታይ መዋቅራዊ ባህሪ ነው። በዚህ መሰረት፣ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ቀዳሚ ሆኖ የገባው ባለቤት ስም፣ በላዕላይ መዋቅር፣ <u>አስቴር</u> በሚለው ገንዛቢ ስም ሊቀደም ችሎአል። ሌሎችም ይህን ስርዓት የሚከተሉ መዋቅሮች አሉ።

(ሀ) አስቴርን ውሻ ነከሳት 5
(ለ) ካሳን አሾህ ወጋው


የእነዚህ አረፍተ ነገሮች ታህታይ መዋቅር አስቴርንና ካሳን ተሳቢ የሚያደርግ ነው። ግሶቹ ሳቢ ናቸውና። ውሻና አሾህ ደግሞ ነካሽና ወጊ ባለቤት ናቸው። ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ይገባሉ። ይህ ሲሆን፣ መዋቅሮቹ የሚከተውን ይመስላሉ።

(ሀ) ውሻ አስቴርን ነከሳት 6
(ለ) አሾህ ካሳን ወጋው

በዚህ አይነት በተመሰረተው ታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ ተሳቢዎቹ ስሞች ታህታይ ቦታቸውን በመልቀቅ፣ ባለቤቶቹን ስሞች አየቀደሙ ላዕላይ ቦታቸውን ይይዛሉ። ተሳቢዎቹ ባለቤቶቹን የሚቀድሙበት

[4] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት ባየ (1994፣ 1997)ን ይመልከቱ።

ምክንያት አፅንየት ነው። <u>ሰዋዊ</u> (ስውን የሚጠቁሙ) ስሞች <u>ኢሰዋዊ</u> ከሆኑ ስሞች የበለጠ አፅንየትን ይሻሉ። የበለጠ ከብርና ልዕልና ይፈልጋሉ፣ እንደማለት ነው። ይህም የሚገኘው ከሁሉ ቀድሞ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ በመሰለፍና ቀድሞም ከእንደበት በመውጣት ነው። ባጭሩ የአረፍተ ነግር ባለቤት በመሆን ነው። ከላይ እንደሚታየው፣ እንደ ውሻ ያሉ ኢሰዋዊና ኢዕምር (ያልተወሰኑ) ስሞች ባለቤት በሆኑበት መዋቅር ውስጥ፣ ሰዋዊና ዕምር (ውስን) የሆኑ ተሳቢ ስሞች አፅንየት ሲያገኙ የሚችሉት፣ ኢሰዋዊ የሆነውን ባለቤት ቀድመው ከአረፍተ ነገሩ ውጭና በላይ ሆነው በመገኘት ብቻ ነው። ይህን ሲያደርጉ የአረፍተ ነገሩ ላዕላይ መዋቅር የሚከተለውን ይመሰላል።



በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>አስቴር</u> የሚለው ተሳቢ ስም በነጠላጣብ ከተመለከተው ታህታይ ዐታው ተነስቶ <u>ውሻ</u> የሚለውን የአረፍተ ነገሩን ባለቤት በማለፍና ከአረፍተ ነገሩ ጋርም በመዋቀር የመዋቅሩን ከፍተኛውን ዐታ ሊይዝ ችሎአል[5]።

እስካሁን ያየነው የተራ አረፍተ ነገርን መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ዋናው ባህሪው ከአንድ ግሳዊ ሀረግ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ግሳዊ ሀረጉ ራሱ የተለያዩ ሊሉች ሀረጎችን በውስጡ ሊይዝ ይችላል። እነዚህም አንደ ገላጭና መሙሊያ ያሉ ሀረጎች ናቸው። ከራሱ ሀረግ ውጭ ከሆነ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገርን ይመሰርታል። ይህ ስማዊ ሀረግም ያረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። በውስጡ የተለያዩ ሀረጎችን ሊይዝ ይችላል፣ ከግሳዊ ሀረግ በስተቀር። ግሳዊ ሀረግ ከያዘ እረፍተ ነገሩ ተራ ላይሆን ውስብስብ ይሆናልና።

ከዚህ ቀጥለን የተለያዩ ተራ አረፍተ ነገሮችን እንመለከታለን። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ምልከታችን በአረፍተ ነገሮቹ መዋቅራዊ ባህሪና የዚሁ

መለረት በሆነው በተግባራቸው ላይ ያተኮረ ይሆናል። ማንኛውም አረፍተ ነገር የሚነገርበት ምክንያት ወይም ዓላማ አለው። የዓላማው አይነት የቅርፁን አይነት ሊወስን ይችላል። ከዚህም በመነሳት አንዱን አረፍተ ነገር ከሌላው መለየት ይቻላል። ከዚህ ቀጥለን የምንመለከተው ይህንኑ ነው።

ሀተታዊ አረፍተ ነገር

ሀተታዊ አረፍተ ነገር አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ፣ ግሀዳዊ ወይም ምናባዊ ለለሆኑ ነገሮች፣ ሁኔቶችና ስሜቶች ያለንን ግንዛቤ ከስሜታችን ጋር አዋህደን የምናትትበት የመዋቅር አይነት ነው። ዓላማው ማተት ነው። ሀተታውም ስለ አንድ የተወሰነ ወይም አጠቃላይ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ የራብው መንገደኛ ስለ ምግብ አያሰበ ሲጉዋዝ፣ ስዎች ስንጋ ጥለው ብልት ሲያወራዱና ጮማ ሲቆርጡ ቢያጋጥመው፣ ከሚለማው ርሀብና ካጋጠመው ትዕይንት ተነስቶ፣ ለራሱም ቢሆን፣ በአንደበቱ ወይም በልቡ የሚከተለውን ማለቱ አይቀርም።

አቦ! አንዴት ያለ ጮማ ነው! 1


ይህን በማለት ሰውየው ለለ ስጋው ጮማ መሆን ተናግሮአል ወይም አትቶአል። አነጋገሩም ስሜትን የተሳበሰ ነው። <u>አቦ!</u> አና <u>እንዴት ያለ</u> የሚሉት አባባሎች የሚያመለክቱት በለውየው አመለካከት፣ ስጋው ተራ ሳይሆን፣ ከክ የመለለ ጮማ መሆኑን ነው። አቦ! የሚለው ቃለ-አጋኖ ነው። የሰውየውን ስሜት ይገልፃል። ከዚያ ያለፈ ትርጉም የለውም። ይህን ስሜታዊ የሆነውን ክፍል ትተን፣ ተጨባጩን ነገር ብቻ ለመግለፅ ብንፈልግ፣ ከላይ የተመለከተውን አባባል አንደሚከተለው ማለት ይቻላል።

ስጋው ጮማ ነው 2

ከመዋቅር አኩዋያ ይህ ተራ አረፍተ ነገር ነው። ግሱም <u>ነው</u> የሚለው ተራ የመሆን ግስ ነው። <u>ጮማ</u> የሚለው ቅፅል የዚህ ግስ መሙሊያ ነው። <u>ስጋው</u> የሚለው ስም ደግሞ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። ግሱና መሙሊያው ተቀናጅተው ግሳዊ ሀረግ በመሆን፣ ስለ ስሙ ያትታሉ። ስሙን አንደ ርዕስ፣ ግሳዊ ሀረጉን አንደ ሀተታ-ርዕስ፣ አረፍተ ነገሩን አንደ ድርሰት አድርገን ልንመለከተው እንችላለን። መሙሊያው ከግሱ ጋር ተዋቅሮ የሚያትተው ስለ ርዕሱ፣ ማለትም ስለ <u>ስጋው</u> ነው። ግሱ ከመሙሊያው ቀፅል ጋር የሚፈጥረውን ግሳዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረጉም በተራው ከባለቤቱ ስማዊ ሀረግ፣ ማለትም ከርዕሱ ጋር ተዋቅሮ፣ የሚፈጥረውን ቅንጅት በጀመርነው አይነት በዕፀ-መዋቅር አንደሚከተለው እናሳያለን።

---

[5] ይህን ጉዳይ በሚመለከት ባየ (1994)ን ይመልከቱ።



ይህ እንግዲህ የአንድ ተራ ሀተታዊ አረፍተ ነገር መዋቅር ነው። ከዚህ አንፃር የተለያዩ ሀተታዊ አረፍተ ነገሮችን እንመለከታለን።

ሁነታዊ አረፍተ ነገር

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው፣ ሁነታዊ አረፍተ ነገር የአንድን ነገር፣ እንድ ነገር መሆን ያትታል። ከፍ ሲል በተሰጠው ምሳሌ፣ ግሱና ቅፅላዊ መሙሊያው የሚፈጥሩት ሀረግ የሚያትተው ስለ ሰጋው ጮማ መሆን ነው። መሆንን ስለሚገልፅ ግሱ የመሆን ግስ በመባል ይታወቃል። ይሁን እንጅ፣ የዚህ አይነት ሀታታዊ አረፍተ ነገር ግስ፣ መሆንን ብቻ ሳይሆን፣ ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር መለወጥንም ሊያሳይ ወይም ሊያትት ይችላል። ለዚህ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

አሰቴር አስተማሪ ሆነች 4

ይህ አረፍተ ነገር ስለ አስቴር ያትታል። የሚያትተውም አስተማሪ ካለመሆን፣ አስተማሪ ወደ መሆን ያደረገችውን ለውጥ ነው። ለውጡን የሚያመለክተው <u>ሆነች</u> የሚለው ግስ ነው። ከፍ ሲል ከጠቀስነው፣ <u>ነው</u> ከሚለው ግስ፣ የተሰየ ነው። <u>ነው</u> የሚለው ግስ የሚገልፀው *<u>ነኝነትን</u>* ነው። <u>ሆነች</u> የሚለው ግን ልውጠትን ነው የሚያሳየው፣ ስለዚህም *<u>የልውጠት</u>* ግስ ነው። አረፍተ ነገሩም የዚሁ ልውጠት ሀተታ ነው። የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

ልጆቹ ክፍል ውስጥ አሉ 5

ይህ አረፍተ ነገር የሚያትተው ልጆቹ ስለሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው። ሀተታውም ቤት ውስጥ ስለ መኖራቸው ነው። ሰሰ ሁነት ወይም ልውጠት አይደለም። በዚህም ምክንያት ግሱን ያኑረት ግስ ልንለው እንችላለን። ልጆቹ የሚለው ስም ነዋሪ ባለቤት ነው፡ ሁዋኝ ወይም ልውጥ ባለቤት አይደለም።

አስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች ሁነትን፣ ልውጠትንና ኑረትን የሚያትቱ ናቸው። የሁሉም ሀተታ ስለ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤት ነው። ከነዚህ ጋር የሚመሳሰሉ እናም በዚሁ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮችም አሉ። የሚከተለው የነዚህ ምሳሌ ነው።


ካሳ አባቱን ይመስላል 6

ይህ አረፍተ ነገር የሚያትተው ምስለትን ነው። ግሱ መስተዋድዳዊ ሀረግ መሙሊያ አለው። የሀረጉ መሪ የሆነው መስተዋድድ /-ን/ ነው። ይህ /-ን/ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን የሚያመለክተው /-ን/ አይደለም፣ ምክንያቱም ይመስላል የሚለው ግሰ ሳቢ አይደለም። ስሳልሆነም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አይፈልግም። መሙሊያ ግን ይፈልጋል። መሙሊያውም ሊሆን የሚችለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ግሳዊ ሀረጉ የሚያትተው ካሳ በሚለው ባለቤት ስምና አባቱ በሚለው መሙሊያ ስም መካከል ያለውን ምስለት ነው። ከትርጉም አኩዋያ መምሰልና መሆን ለየቅል ናቸው። ይሁን እንጅ፣ ይቀራረባሉ። እንዲያውም ክመዋቅር አንፃር ሲታዩ አንድ ናቸው። ሁሉም መሙሊያ ይፈልጋሉ። ለዚህ የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

7
(ሀ) ካሳ አስተማሪ ይሆናል
(ለ) ካሳ አስተማሪ ነው
(መ) ካሳ አስተማሪ ይመስላል
(ረ) ካሳ ረኻም ነው
(ሰ) ካሳ ረኻም ሆነ
(ቀ) ካሳ ረኻም ይመስላል

እነሆ፣ ምሳሌዎቹ ነው፣ ይመስላል እና ይሆናል የሚሉት ግሶች ቅፅላዊ ወይም መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ ሀረግን መሙሊያ እያደረጉ ግሳዊ ሀረግ እንደሚመሰርቱ ያሳያሉ። ይህን ያነባብና መጠነኛም ቢሆን፣ የትርጉም ተመሳሳይነት መሰረት በማድረግ ግሶቹን በሁነት ግስ ሰር ልናጠቃልላቸው እንችላለን። የአረፍተ ነገሮቹ መሰረታዊ አወቃቀርም አንድ አይነት ነው። ግሶቹ ከመሙሊያ ሀረግ ጋር ይዋቀራሉ። መሙሊያዎቹም ተሳቢ አይደሉም፣ ምክንያቱም ግሶቹ ሳቢ አይደሉምና።

እስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች በሙሉ የባለቤትና የመሙሊያ ቁርኝት የሚታይባቸው ናቸው። መሙሊያዎቹ ለለ ባለቤቶቹ ምንነት፣ የትነት (ኑረት) ሁነት የሚያወሱ ናቸው። ግሶቹም የሚያሳዩት ይህንን የሁለቱን ቁርኝት ነው። ለምሳሌ ከላይ በተሰጡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ (እንደ ቅደም-ተከተላቸው)፣ ካሳ እና ረዥም፣ እንዲሁም ካሳ እና አስተማሪ፣ ተቆራኝተዋል። ይኸውም በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ረዥም የሆነው ወይም የሚመስለው ካሳ ሲሆን፣ በሁሰተኛው ምሳሌ ድግሞ አስተማሪ የሆነው ወይም የሚመሰለው አሁንም ያው ካሳ ነው። በጥቅሉ አረፍተ ነገሮቹ የባለቤትን አንድ ነገር መሆን ወይም በአንድ ቦታ መገኘት ያመለክታሉ። የግሶቹም ተግባር ይህንኑ የሁለቱን ቁርኝት ማመልከት ለለሆነ፣ በጥቅሉ አቆራኝ ግሶች ልንላቸው እንችላለን። ባለቤትና መሙሊያን ያቆራኛሉ፤ ያያይዛሉ ማለት ነው። አረፍተ ነገሩም የሚያትተው ይህንኑ ነው። መዋቅራዊ ሁኔታቸውን እንደሚከተለው አድርገን በአንድ ዕፀ-መዋቅር አጠቃለን አናሳያለን።



8

በዚህ መዋቅር ከተጠቃለሉት ሁነታዊ አረፍተ ነገሮች ጋር በመጠኑ የሚመሳሰሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮችም አሉ። እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

(ሀ) ልጅቹ ባለጉ
(ለ) ሌቶቹ ሰከሩ
(መ) አስቴር ወፈረች

9

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ስለ ባለቤታቸው ባህሪ የሚያትቱ ናቸው። ግሶቹም ባህሪን የሚያመለክቱ ቅፅላዊ አቻ አላቸው። ለምሳሌ፡ ባለጌ ለሚለው ባለጌ፣ ሰካራ ለሚለው ሰካራም፣ እንደዚሁም ወፈረቾ ለሚለው ወፍራም የሚል አቻ ቅፅል አለው። ስለዚህም ልጆቹ ባለጌ በሚለው ፋንታ፣


ልጆቹ ባለጌ ሆኑ 10

የሚል ሁነታዊ አረፍተ ነገር መመስረት ይቻላል። የሌሎቹ ምሳሌዎች ባህሪም እንደዚሁ ነው። እንደነዚህ ያሉትን ስለ ባለቤት የሚያትቱ አረፍተ ነገሮችን ባህሪያዊ አረፍተ ነገሮች፣ ግሶቹን ደግሞ የባህሪ ግሶች ልንላቸው እንችላለን። ከነዚህ ጋር በአወቃቀር የሚመሳሰሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮች ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

(ሀ) ካሳ ተደሰተ 11
(ለ) አስቴር ተጨነቀች
(መ) ልጆቹ ተበሳጩ

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች የሚያትቱት ባለቤቱ የሚገኝበትን ሁኔታ ነው። ይኸውም በደስታ፣ በብስጭት፣ በጭንቀት፣ ወዘተ፣ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በመግለፅ ነው። ባለቤቱ የሁኔታው ገፈት ቀማሽ ነው። ግሶቹም ከሌሎች ግሶች በቅርፃቸው የተለዩ ናቸው። ልዩነታቸው፣ ሁሉም በ/ተ-/ የሚጀምሩ መሆናቸው ነው። ባለፈው ክፍል እንዳየነው፣ /ተ-/ የተለያየ ትርጉም አላት። ከዚህ ላይ ግሉ የሁኔታ፣ ባለቤቱም የሁኔታው ተጠቂ መሆኑን ታመለክታለች። ባጭሩ የሁኔታ ግስ መስራች ነች። ወደ ሁዋላ እንመለስባታለን።

የባህሪም ሆኑ የሁኔታ ግሶች መሙሊያ የላቸውም። ይሁን እንጅ፣ ከትርጉም አንፃር ሲታሰብ፣ መሙሊያቸው ባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ ነው፣ ሰማሰት ይቻላል። ይህ ደግሞ የዚህን ስማዊ ሀረግ መዋቅራዊ ቦታ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስር ያደርገዋል፣ መሙሊያ የሚገኘው በንዑስ ሀረግ ስር ነውና። በዚህ መሰረት፣ የባለቤቱ ቦታም ክፍት ይሆናል። ይህ በተለይ ከላይ በተራ ቁጥር (11) ስር የሚታዩት አረፍተ ነግሮች አይነተኛ ባህሪ ነው። የነዚህን ታህታይ አወቃቀር በ12(ሀ)፣ እንዲሁም ላዕላይ አቀማመጣቸውን በመዋቅር (ለ) እንደሚከተለው እናቀርባለን።



በመዋቅር 12(ሀ) ላይ በግልፅ እንደሚታየው፣ የባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (...) ነው። ካላ ተጨናቂ መመ.ሊያ ሰማዊ ሀረግ ነው። አለጨናቂው ማን ወይም ምን እንደሆነ አይታወቅም። ስለዘህም ቦታው ክፍት ነው። መዋቅር 12(ለ) ላዕላይ ነው። ካላ የዚህ መዋቅር ባለቤት ሆኖ የሚታየው፣ በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ ከሚታይበት፣ ከመመ.ሊያው ቦታ ተነስቶ ክፍት ወደ ነበረው የባለቤት ቦታ ሲሄድና ተጨናቂ ባለቤት ሲሆን ነው።

አለካሁን ያየናቸው ተራ ህተታዊ አረፍተ ነገሮች ለለ ባለቤት፣ ምንነት፣ የትነት፣ ባህሪና ሁኔታ የሚያትቱ ናቸው። ግሶቻቸው በሙሉ ኢሳቢ ናቸው። መመ.ሊያ እንጅ ተሳቢ የላቸውም። አንዳንዶቹ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ባለቤት የላቸውም። እንደነዚህ ያሉት መለያ ምልክት /ተ-/ የምትለዋ ምዕላድ ነች። ይችን የያዙ ግሶች በታህታይ መዋቅር ውስጥ መመ.ሊያ የነበረውን ሰማዊ ሀረጋቸውን በላዕላይ መዋቅር ባለቤት አድርገው ይከለታሉ። ይህም ከላይ በመዋቅር 12(ለ) እንደሚታየው ነው።

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ለለ ባለቤት ሰማዊ ሀረግ ግብር የሚያትቱትን ተራ አረፍተ ነገሮች እንመረምራለን።

ገቢር አረፍተ ነገር


እነዚህ ድርጊትን የሚያመለክት ግላዊ ሀረግ ያላቸው አረፍተ ነገሮች ናቸው። የአረፍተ ነገሩ ባለቤት የድርጊቱ ፈፃሚ ነው። ሁዋኝ ሳይሆን፣ አድራጊ ባለቤት ነው። ድርጊቱን የሚፈፅመውም በራሱ ወይም በሌላ አካል ላይ ሊሆን ይችላል። የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ለአብነት እንመልከት፡

(ሀ) ካሳ ወደ ገበያ ሄደ 1
(ለ) አስቴር ወደ ቤት ገባች
(መ) ልጆቹ ዛፍ ላይ ወጡ

እነዚህ አረፍተ ነገሮች የሚገልፁት የእንቅስቃሴ ድርጊትን ነው። የመጀመሪያው ምሳሌ፣ ባለቤቱ ካሳ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፣ ማለትም ወደ ገበያ፣ ያደረገውን እንቅስቃሴ ይገልፃል። ከዚህ የተነሳ፣ እንደ ሄደ ያሉት ግሶች የእንቅስቃሴ ግሶች ሊባሉ እንደሚችሉ ካሁን በፊት ገልፀናል። እንደነዚህ ያሉ ግሶች ዋና ባህሪ የእንቅስቃሴውን መድረሻ የሚገልፅ መስተዋድዳዊ ሀረግን በመሙሊያነት መያዝ ነው። ለምሳሌ፣ በምሳሌ 1(ሀ) ውስጥ፣ ሄደ የሚለው የእንቅስቃሴ ግስ፣ የእንቅስቃሴውን መድረሻ የሚገልፅ መሙሊያ አለው። አሱም ወደ ገበያ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የእንቅስቃሴውን መነሻ የሚገልፅ መስተዋድዳዊ ሀረግም አለው። ለምሳሌ፣ ካሳ ከትምህርት ቤት ወደ ገበያ ሄደ፣ ስንል፣ ከትምህርት ቤት የሚለው መነሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ይሁን እንጅ የመድረሻውን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ስለዚህም ሊቀር ይችላል። ሌሎቹ ግሶችም እንደዚሁ ካሉ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው ስለ እንቅስቃሴው የተሙዋላ መረጃ የሚሰጥ ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል። መረጃውን የተሙዋላ የሚያደርገው የመሙሊያዎቹ መኖር ነው። ስለዚህም መሙሊያዎቹ አይቀሬ ናቸው።

ግሱና መሙሊያዎቹ የመሰረቱት ግሳዊ ሀረግ፣ ካሳ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገሩን ሊመሰረት ችሎአል። የዚህንና ወደፊት የምናያቸውን ተመሳሳይ አረፍተ ነገሮች መዋቅራዊ አወራረድ በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።

2



በተራ ቁጥር (1) የተመለከቱት አረፍተ ነገሮች የባለቤቱን እንቅስቃሴ የሚያመለክቱ ናቸው። እንቅስቃሴው መነሻና መድረሻ አለው። ከዚህ ለየት

የሚል እንቅስቃሴም አለ። ይኸውም በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚፈፀም ነው። መነሻውም ሆነ መድረሻው አድራጊው፣ ማለትም ባለቤቱ የሚገኝበት ቦታ ነው። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ልጁ በር ላይ ቆመ 3
(ለ) አስቴር አልጋው ላይ ወደቀች
(መ) ዶሮዎቹ ቆጡ ላይ ሰፈሩ

አንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች እንድ አካል እንድ ድርጊት የሚፈፀምበትን ቦታ የሚገልፁ ናቸው። ድርጊቱ የሚፈፀምበት ቦታ በመስተዋድዳዊ ሀረግ የተገለፀው ነው። ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር፣ ልጆቹ የመቆምን ተግባር የሚፈፅሙት፣ በሩ ላይ ሲሆን፣ በሁለተኛው ደግሞ አስቴር የወደቀችው አልጋው ላይ ነው። ሁለቱም መስተዋድዳዊ ሀረጎች ሲሆኑ፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ በግሱ የተገለፀውን ተግባር የፈፀመበትን ቦታ ያመለክታሉ። በዚህም ምክንያት በቀደምት ሲቃውንት ዘንድ የቦታ ተውሳክ ግሰ በመባል እንደሚታወቁ ገልፀናል። ተውሳክ ግስነታቸው ግን የግብር እንጅ የቃል አይደለም። ምክንያቱም የቃል ክፍላቸው፣ በክፍል ሁለት እንዳየነው፣ መስተዋድድ ነውና።

እንድ ድርጊት በውጭ ሀይል ግፊት ወይም በራስ እነሳሽነት ሊፈፀም ይችላል። የሚፈፀመውም በራስ ላይ ወይም ከራስ ውጭ በሆነ ነገር ላይ ሲሆን ይችላል። ለምሳሌ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት ባለቤቱ በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ እንድ ድርጊት ሲፈፅም ነው። የፈፀመውም ምናልባት በውጭ አካል ወይም ሁኔታ ግፊት ሊሆን ይችላል። ድርጊቱ በራሱ አነሳሽነትና ተሳታፊነት እንዲሁም በራሱ ላይ የሚፈፀም ሲሆን፣ ግሶቹ ለየት ያለ ቅርፅ ይኖራቸዋል። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ከመቀመጫው ተነሳ 4
(ለ) ልጆቹ ወንበር ላይ ተቀመጡ
(መ) አስቴር አልጋ ላይ ተኛች
(ሰ) አንበሳው ተንጠራራ

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ግሶች ከፍ ሲል ካየናቸው አረፍተ ነገሮች ግሶች የተለዩ ናቸው። ልዩነታቸውም ሁሉም በ/ተ-/ መጀመራቸው ነው። /ተ-/ ደግሞ በክፍል ሁለት እንደተገለፀው፣ ምዕላድ ነች። አንድ ድርጊት በራስ አነሳሽነትና በራሰ ላይ የሚፈፀም መሆኑን ታመለክታለች። እስዋ ከሌለች ግሶቹ፣ ብሎም አረፍተ ነገሮቹ ተቀባይነታቸውን ያጣሉ። ስለዚህም፣

*ልጆቹ ወንበር ላይ ቀመጡ 5


ማለት አይቻልም። እንደዚህ የሚሉት ቁዋንቁዋውን ገና በመልመድ ላይ የሚገኙ ለዎች ብቻ ናቸው። እንደ ቀደመ፣ ቀረበ፣ ወዘተ፣ ያሉ ግሶችን አካዒድ በመከተል፣ ቁዋንቁዋውን በመልመድ ላይ የሚገኙ ህፃናትም ቀመጠ ሊሉ ይችላሉ።

የድርጊቱ መነሻ በመሰረቱ ድርጊቱን የሚፈፅመው ሰው ውስጣዊ ሰሜት ወይም የሚገኝበት የአካባቢ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። መነሻውም ሆነ መድረሻው ማለትም መፈፀሚያው፣ ሌላ አካል ሳይሆን፣ ራሱ ፈፃሚው ነው። እንደነዚህ ያሉት <u>ውስጠ-ቀር</u> ግሶች ሊባሉ ይችላሉ። ድርጊቱ ስዚያው በባለቤቱ ውስጥ የሚቀር እንጅ፣ ወደ ሌላ አካል የማይተላለፍ መሆኑን ያሳያሉና። ከላይ በተራ ቁጥር (4) የተመለከቱት ምሳሌዎች በሙሉ ውስጠ-ቀር ድርጊትን ገላጮች ናቸው።

አንድ ባለቤት ድርጊት ፈፃሚ ሳይሆን፣ ሌሎች የሚፈፅሙት ድርጊት ወይም የሚፈጥሩት ሁኔታ ተጎጅ ወይም ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) አስቴር ሽልማት ተቀበለች
(ለ) ካሳ ንብረት ተረከበ 6

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>አስቴር</u> ሽልማት የመስጠት ተግባር ፈፃሚ ሳትሆን፣ የተግባሩ ተጠቃሚ ወይም ተቀባይ ነች። ሽልማት የመስጠቱ ድርጊት የተፈፀመው በሌላ ሰው ነው። አንደዚሁም በሁስተኛው ምሳሌ፣ <u>ካሳ</u> ንብረት የመረከብ ድርጊት ፈፃሚ ነው። አሰረካቢው አሁንም ሌላ ሰው ነው። ያ ሰው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ተረካቢው ካሳ ደግሞ የግሱ መሙሊያ መሆን አለበት። አንደነዚህ ያሉትን ግሶች <u>ውስጠ-ገብ</u> ልንላቸው እንችላለን። ከአረፍተ ነገሩ ባለቤት የሚወጣውን ሳይሆን፣ ወደ ባለቤቱ የሚመጣውን ወይም የሚገባውን ድርጊት ያመለክታሉና። ይህ ከሆነ፣ የአረፍተ ነገሮቹ ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው መሆን አለበት።



7

በግልፅ እንደሚታየው፣ የባለቤቱ ቦታ ከፍት (...) ነው። በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ መሙሊያ ሆነው የሚታዩት <u>አስቴርና</u> <u>ካሳ</u> የሚሉት ስሞች ከፍት ወደሆነው ቦታ

ይሄዱና የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ይሆናሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ የአረፍተ ነገሮቹ ላዕላይ መዋቅር በተራ ቁጥር (6) የተመለከተውን ይመስላል፡፡

እነዚህንም፣ ከፍ ሲል በቅራ ቁጥር (4) እንደተመለከቱት አረፍተ ነገሮች፣ ውስጠ-ገብ ልንላቸው እንችላለን፡፡ ድርጊቱ ከሌላ ወገን ተነስተ ወደ መሙሊያው ስማዊ ሀረግ የሚገባ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ሁለቱኛም /ተ-/ የምትሰዋን ምዕላድ በግሀድ ያሳያሉ፡፡

አሰካሁን ያተኮርንባቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች አንድ ድርጊት በባለቤቱ አነሳሽነት በባለቤቱ በራሱ ላይ የሚፈፀም መሆኑን ወይም ባለቤቱ በሌላ አካል የሚፈፀም ድርጊት ተቀባይ መሆኑን የሚያትቱ ናቸው፡፡ ግሶቹን ውስጠ-ቀር እና ውስጠ-ገብ ብለናቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታ የሚያመለክት መስተዋድዳዊ ሀረግ በመሙሊያነት ይፈልጋሉ፡፡ አነዚህን ግሶች በጥቅሉ ኢሳቢ ገቢር ግሶች አንላቸዋለን፡፡ ዋናው መሊያቸው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለመፈለጋቸው ነው፡፡ ገቢር መሆናቸው ከሁኑትና ከኩረት ግሶች ይለያቸዋል፡፡ ኢሳቢ መሆናቸው ደግሞ ከነዚሁ ግሶች ጋር አንድ ያደርጋቸዋል፡

ከነዚህ ሁሉ የሚለዩት ገቢር የሆኑ ሳቢ ግሶች ናቸው፡፡ አነዚህ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋሉ፤ የግድ፡፡ የሚከተሉት ምሳሌዎች ይህን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

(ሀ) ተማሪው ደብተሩን ቀደደው 8
(ለ) ገበሬው ማሳውን አጥሮታል
(መ) አሰተማሪው ለተማሪዎች መፅሀፍ ሰጣቸው

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ቢያንስ ሁለት ስማዊ ሀረግ አላቸው፤ አንደኛው ድርጊት ፈፃሚ፣ ሁለተኛው ደግሞ ድርጊት ተቀባይ፡፡ ድርጊት ፈፃሚው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን፣ ድርጊት ተቀባዩ የግሱ ተሳቢ ነው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤቱ በግሱ የተገለፀውን ድርጊት፣ ከአሱ ውጭ በሆኑ ነገሮች ላይ መፈፀሙን ያትታሉ፡፡ ድርጊት ፈፃሚው አሱ ሲሆን፣ ድርጊት ተቀባዮቹ ሌሎች ናቸው፡፡ ስምሳሌ፣ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ብንመልከት፣ በግሱ የተገለፀውን የመቅደድ ተግባር የፈፀመው ተማሪው ሲሆን፣ የዚህ ድርጊት ተቀባይ ወይም ተጎጅ የሆነው ደብተሩ ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ፣ የተገለፀው ሁኔታም እንደዚሁ ነው፡፡ ገበሬው የፈፀመው የማጠርን ተግባር ሲሆን፣ ይህ ተግባር ደግሞ የተፈፀመው በማሳው ላይ ነው፡፡ ስለዚህም <u>ገበሬው</u> የሚሰው ሰም ባለቤት ሲሆን፣ <u>ማሳው</u> የሚሰው ተሳቢ ነው፡፡ ሶስተኛው ምሳሌ ትንሽ ለየት ይላል፡፡ ድርጊቱ የመሰጠት ነው፡፡ ስለዚህም ሶስት ነገሮችን ያጣቅሳል፡፡ አነዚህም ሰጭ፣ ሰጠታ እና ተቀባይ ናቸው፡፡ ሰጭው ድርጊት ፈፃሚው ባለቤት ነው፡፡ ሰጠታው መፅሀፍ ሲሆን፣ የዚህ ተቀባይ ደግሞ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሶስቱም ሀረጎች አይተሬ ናቸው፡፡ ሰጠታውንና ተቀባዩን የሚገልፁት ሀረጎች ተሳቢ ናቸው፡፡ ሰጠታውን የሚገልፀው ርቱዕ ወይም ቀጥተኛ ተሳቢ ይባላል፡፡ ተቀባዩን የሚገልፀው ሀረግ ኢርቱዕ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ይባላል፡፡ ቅርፃቸውም የተለያየ ነው፡፡ ርቱዑ ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ ኢርቱዑ መስተዋድዳዊ ነው፡፡ ሁለተኛም ርቱዑ ተሳቢ ብቻ፣ ተሳቢነቱን ለማመልከት /ን/ የሚል ምዕላድ ያስከትላል፡፡ ይህን


የሚያደርገው ግን ዕምር፣ ማለትም ዕውቅ ሲሆን ነው። የሚከተሉትን አያነፃፀርን አንመልከት።

(ሀ) ካሳ ለወታደሮች ገንዘብ ሰጠ /ሰኧጥ-ኧ/ 9
(ለ) ካሳ ለወታደሮቹ ገንዘቡን ሰጣቸው /ሰኧጥ-ኧ-ኣችችኧው/

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ገንዘብ የሚለው ርቱዕ ተሳቢ ዕምር ስም አይደለም። ስለዚህም የተሳቢ ምልክት የሆነችውን /-ን/ን አሳስከተለም። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ስም ዕምር ስለሆነ፣ የተሳቢ ምልክትዋን አስከትሎአል። የዕምርነት ምዕላድዋ /-ኡ/ ነች። ለወታደሮቹ የሚለው ኢርቱዕ ተሳቢ በግሱ ላይ /-ኣችችኧው/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሶአል። ይህም ሊሆን የቻለው፣ ወታደሮቹ የሚለው ሀረግ ዕምር በመሆኑ ነው። በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ይኸው ሀረግ አልታመረም፣ ስለዚህም በግሱ ላይ በተሳቢ አፀፋ አልተጠቀሰም። በተሳቢ አፀፋ መጠቀስና የተሳቢ ምዕላድ የሆነችውን /-ን/ን ማስከተል ከዕምርነት ጋር የተቆራኙ ቅርፃዊ የተሳቢ ስማዊ ሀረግ ባህሪያት ናቸው።

መዋቅራዊ የሆነው የነዚሁ ሀረጎች ባህሪ ደግሞ የርቱዑ ተሳቢ ቦታ በቀጥታ ከግሱ በፊት መሆኑ ነው። ይህንና ከሳቢ ግሳዊ ሀረጎች የሚዋቀሩ አረፍተ ነገሮችን አጠቃላይ አወቃቀር በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።

10



በግልፅ እንደሚታየው፣ ሰጣቸው የሚለው ሳቢ ግስ ገንዘቡን ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። የድርጊቱ ቀጥተኛ ተጠቃሽ ወይም ተጠቂ ስሙ ስለሆነ፣ ድርጊቱን ከሚገልፀው ግስ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው። ለዚህም ከግሱ ቀድሞ ይገባል። በቦታው ካልተገኘ፣ ግሱ ብቻውን የተሙዋላ መረጃ ስለ ድርጊቱ ሊሰጥ አይችልም። በአነጋገሩ፣ ለወታደሮቹ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ገንዘቡ የሚለውን ስም ያህል፣ ከግሱ ጋር የጠበቀ ቁርኝት፣ ብሎም ቀረቤታ የለውም። ለዚህም፣ ከግሱ ራቅ ብሎና ገንዘቡ የሚለውን ተሳቢ ቀድሞ ይገባል። መዋቅራዊ ግንኙነቱም በቀጥታ ከግሱ ጋር ሳይሆን፣ ገንዘቡን ሰጣቸው ከሚለው ንዑስ ሀረግ ጋር ነው። ከዚህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ የሚፈጥረው ሀረግም ገንዘቡን ሰጣቸው ከሚለው ንዑስ ሀረግ ትንሽ ለፋ ያለ ሌላ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። ይህም ለልጆቹ ገንዘቡን ሰጣቸው የሚለው ነው። ሁኔታው ሁለት ደረጃ ያለው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እንዳለ ያሳያል። የመጀመሪያው፣ ከግሱና ከርቱዕ ተሳቢው የሚዋቀር ሲሆን፣ ሁለተኛው የነዚህ ውጤት ከሆነው ንዑስ ግሳዊ ሀረግና ከኢርቱዕ ተሳቢ የሚዋቀር ነው። የአወራረዱና የቅደም-ተከተሉን ልዩነት ያመጣው ሁለቱ ተሳቢዎች ከግሱ ጋር ያሳቸው የቁርኝት ደረጃ ነው። ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ ኢርቱዕ ተሳቢ የርቱዕ ተሳቢን ያህል ለግሱ አስፈላጊ ሳይሆን ይችላል። ለዚህ ምልከቱ አንድ አረፍተ ነገር ከኢርቱዕ ይልቅ ርቱዑ ተሳቢውን ሲያጣ፣ የተቀባይነቱ ደረጃ የሚቀንስ መሆኑ ነው። ይህን ሁኔታ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች የተቀባይነት ደረጃ መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ካሳ ለተማሪዎቹ ገንዘቡን ከፈለ 11
(ለ) ካሳ ገንዘቡን ከፈለ
(መ) ? ካሳ ለተማሪዎቹ ከፈለ


ምሳሌ (ሀ) ሁለቱንም ተሳቢዎች ይዞአል። ለዚህም ተቀባይነቱ የተሙዋላ ነው። ምሳሌ (ለ) ኢርቱዕ ተሳቢውን አልያዘም። ይሁን እንጅ፣ ተቀባይነቱ ብዙም አልተናጋም። ምሳሌ (መ) ርቱዕ ተሳቢውን አልያዘም። ተቀባይነቱ ግን አጠራጣሪ ነው። ምን ከፈለ? የሚል ጥያቄ የግድ ያስነሳል። ይህም ኢርቱዕ ተሳቢ የርቱዕ ተሳቢን ያህል ለግሱ ተፈላጊ አለመሆኑን ይጠቁማል።

ከላይ የሚታየው የሁለቱ ተሳቢዎች ቅደም-ተከተላዊ አገባብ ሊቀየር ይችላል። ይህም የሚሆነው፣ ርቱዕ ተሳቢው መለሪታዊ ቦታውን ለቆ ኢርትዑን ተሳቢ እየቀደመ ሲገባ ነው። ይህ ሲሆን፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ ገንዘቡን ለተማሪዎቹ ከፈለ -ላቸው 12

ይህ ላዕላይ መዋቅር ሲሆን፣ ርትዑው ተሳቢ ከሁለተኛው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ለር ወጥቶ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ይዋቀራል። ይህም የሚሆነው ለዚሁ ስማዊ ሀረግ ከኢርትዑ ተሳቢ የበለጠ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ ነው። የሁለቱም

ተሳቢዎች መሰረታዊ ቦታ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስር ለመሆኑ ከአፀፋቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም ሁለቱም በተራ የተሳቢ አፀፋ በግሱ አምድ ላይ መጠቀሳቸው ነው፡፡ ርቱዑ ተሳቢ /-ኡ/ በሚሰውና በግሀድ በማይታየው ምዕላድ ፡ ኢርቱዑ ደግሞ -አቸው በሚሰው የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላድ ተመልክቶአል፡፡ የሀረጉን እንቅስቃሴ የሚያሳየውን የቦታ ለውጥ በሚከተለው ዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡



ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ገንዘቡን የሚለው ርቱዑ ተሳቢ፣ በግሀ1 ሰር፣ ከፈላቸው ከሚለው ሳቢ ግሰ በፊት ከሚታየው ክፍት ቦታ (...) ተነስቶ፣ ኢርቱዑን ተሳቢ ለማቁዋረጥ ከዋናው ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዳብሎ ገብቶአል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ከርቱዑ ተሳቢ የበለጠ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል፡፡ ከዚህም በላይ፣ ባሰቤቱን ሰማዊ ሀረግ አልፎ፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሊዋቀር ይችላል፡፡ ይህን ሲያደርግ የሚከተለውን ይመሰላል፡፡

[[ገንዘቡን]ᵢ [ካሳ[ለተማሪዎቹ [...]ᵢ ከፈላቸው]]] 14

እስካሁን ያየናቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች በአካል የሚፈፀም ድርጊትን የሚገልፁ ናቸው። ለምሳሌ የመከፈልን ድርጊት ብንመለከት፣ እጅ በመሰንዘር የሚፈፀም ተግባር ነው። አንዳንድ ግሶች የሚገልፁት ተግባር ግን ከዚህ የተለየ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ነገር አሰበአል 15
(ለ) ልጆቹ ሰሀተታቸውን አውቀዋል
(ሐ) አሰቴር ጥፋትዋን አምናለች

አንደነዚህ ባሉ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶች በአካል የሚፈፀምን ድርጊት ሳይሆን፣ በአዕምሮ ብቻ የሚወሰንን ጉዳይ የሚያመለክቱ ናቸው። በዚህም ምክንያት አንደ <u>አሰበ</u> ያሉትን ግሶች አዕምሮአዊ ግሶች ልንላቸው እንችላለን። ከነሱ ጋር በመጠኑም ቢሆን የሚመሳሰሉ ሌሎች ግሶችም አሉ። እነሱም ድርጊትን ሳይሆን ፍላጎትን፣ ምኞትን፣ ጥላቻን ወይም ውዴታን የሚገልፁ ናቸው። የሚከተሉት ምሳሌዎች አነዚህን የሚያትቱ ናቸው።

(ሀ) ልጆቹ ወተት ይወዳሉ 16
(ለ) አሰቴር ገንዘብ ትፈልጋለች
(ሐ) ካሳ ሰው ያከብራል
(ሰ) አስተማሪው ሰራ ይጠላል

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች፣ ግስ<u>ታ</u>ቸው የሚፈፅመውን ተግባር ሳይሆን፣ ሰሌላ ነገር ያለውን ዝንባሌ ወይም ፍላጎት ያሳያሉ፣ ለምሳሌ፣ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ብንመለከተው ልጆቹ አሰቴት ያላቸውን ዝንባሌ እንጅ የሚፈፅሙትን ድርጊት የሚያትት አይደለም። ስለዚህም እንደ <u>ወደደ</u> ያሉትን ግሶች የዝንባሌ ግሶች፣ አረፍተ ነገሮቻንም ዝንባሌን ገላጭ ወይም አታች በማለት፣ ድርጊት ገላጭ ከሆኑ አረፍተ ነገሮች ልንለያቸው እንችላለን።

እንደነዚህና ከፍ ሲል እንዳየናቸው ባሉት ሁለታዊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ግሶች በቀደምት ሊታወቁት ዘንድ ተሻጋሪ በመባል ይታወቃሉ። ተሻጋሪ የሚሰኙበት ምክንያት የሚገልፁት ድርጊት ወይም ሰሜት ከአድራጊው፣ ግስተም ከባለቤቱ ወደ ድርጊት ተቀባዩ ግስተም ወደ ተሳቢው፣ የሚሻገር ወይም የሚተላለፍ ስለሆነ ነው። ይህም ከትርጉም አኩዋያ ሲታሰብ ነው። ከመዋቅር አኩዋያ ሲታዩ፣ አንደነዚህ ያሉ ግሶች በሙሉ መሙሊያ ሰማዊ ሀረጎችን የግድ የሚፈልጉ ናቸው። ሰማዊ ሀረጎቹም ተሳቢ በመባል ይታወቃሉ። ከዚሁ በመነሳት ግሶቹን ሳቢ ብለናቸዋል። ሳቢና ተሳቢ ተቀናጅተው ንዑስ ግሳዊ ሀረግን፣ አልፎም አረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ። ይህ አባባል ግስ የአረፍተ ነገር መሪ ነው ያልነውን ያስታውሰናል። የማንኛውንም አረፍተ ነገር (አነ) መሪ ግሳዊ ሀረግ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል ብለን ነበር። ይህም ማንኛውም አረፍተ ነገር በሀሳብ

ይዘቱም ሆነ በመዋቅራዊ ቅርፁ የተሙዋላ ከፍተኛ ግሳዊ ሀረግ ነው አንደማለት ነው።

ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ አንድ አረፍተ ነገር ከባለቤት ስማዊ ሀረግና ከእቢይ ግሳዊ ሀረግ የሚቀናጅ አቢይ መዋቅር ነው። ስማዊ ሀረጉ የቅንጅቱ ርዕሰ ሲሆን፣ ግሳዊ ሀረጉ የዚህ ርዕሰ ሀተታ ነው። ከዚህ አባባል አንድ መዋቅር አረፍተ ነገር ለመባል የግድ ስማዊ ሀረግ ባለቤት አንደሚያስፈልገው አንረዳለን። እስካሁንም ያየነው ሁኔታ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ መዋቅሮች በግሀድ የሚታይ ስማዊ ሀረግ ባለቤት ሳይኖራቸው፣ አረፍተ ነገር የሚሆኑበት ሁኔታ አለ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

(ሀ) እግዜርን ይፈሩአል 17
(ለ) ንጉስን ያከብሩአል
(መ) ምክርን ያዳምጡአል

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ግስ ሳቢ ወይም ኢሳቢ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ሳይ የሚታዩት በሙሉ ሳቢ ናቸው። ተሳቢም አላቸው። ተሳቢዎቹ ግን ዕምር አይደሉም፣ ስላልሆኑም በግሶቹ ሳይ በአፀፋ አልተጠቀሱም። ይሁን አንጅ ለተሳቢነታቸው /-ን/ የምትለዋን የተሳቢ ምልክት አስከትለዋል። የ/-ን/ አገባብም ቀደም ሲል ስለ ተሳቢ ስማዊ ሀረጎች ስንወያይ ከገለፅነው የተለየ ነው። ያኔ /-ን/ ከዕምር ስሞች ጋር ቁርኝት አንዳላት ገልፀን ነበር። የእሁኑ አገባብዋ ይህን የሚቃረን ነው። ምክንያቱም ተሳቢዎቹ ዕምር አይደሉም።

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች አስካሁን ካየናቸው ሌሎች አረፍተ ነገሮች የሚለዩዋቸው ሌሎችም ባህሪያት አሉዋቸው። መጀመሪያ ነገር፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ባለቤት በግሀድ የሚታይና በአንደበትም የሚነገር ሀረግ አይደለም። በአፀፋ መልክ ብቻ የሚከሰት ነው። ሲከሰትም /ይ-/ እና /-አ/ ሆኖ ነው። ለምሳሌ <u>ይፈሩአል</u> የሚለውን የምሳሌ (ሀ)ን ግስ ብንመለከት፣ ታህታይ ቅርፁ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን።

/ይ-ፍሸር-አ-አልል/ 18

/ይ-/ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ እንደ ሆነች፣ በርባታው ከፍል አይተናል። /-አ-/ም የብዙ ቁጥር ምዕላድ እንደ ሆነ አይተናል። -<u>አልል</u> ጊዜን እመልካች የሆነ ረዳት ግስ ነው። መደበኛ በሆነው የምዕላዶች አገባብ፣ /-አ-/ የምትገኘውና መገኘትም ያለባት ረዳት ግሱን /-አልል/ን ተከትላ እንጅ፣ አዚህ ሳይ እንደሚታየው፣ ቀድማ አይደለም። በመደበኛው አገባብ ስትገኝ፣ የግሱ አጠቃላይ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል።

/ይ-ፍሸር-አ አልል-አ / [ይፍሸርአልልአ] ይፈራሉ 19

በሁለቱ ግሶች መካከል ያለው ልዩነት በ/-ኡ-/ አገባብ ላይ ብቻ ነው። በዚህ የአገባብ ልዩነት ምክንያት፣ የሁለቱ ግሶች ባለቤት የተለያየ ነው። እንዴት እንደሚለያይ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) እነሱ እግዜርን ይፈራሉ /ይ-ፍኧር-ኣልል-ኡ/ 20
(ለ) *እነሱ እግዜርን ይፈሩአል /ይ-ፍኧር-ኡ-ኣልል/
(መ) ---- እግዜርን ይፈሩአል /ይ-ፍኧር-ኡ-ኣልል/

ምሳሌ (ሀ) ተቀባይነት አለው። ግሱ መደበኛ የሆነ የሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር ነው። ባለቤቱ በግሀድ የሚታይ የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም ነው። ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት የለውም። ለዚህ ምክንያቱ እነሱ የሚለውን ተውላጠ ስም በግሀድ ማሳየቱ ነው። ተውላጠ ሰሙን በግሀድ በማያሳይበት ጊዜ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አለው። ይህንንም ከምሳሌ (መ) መረዳት ይቻላል።

ይህ አመሰካከት ትክክል ከሆነ፣ ሁኔታው በሌሎች አረፍተ ነገሮችም በዚሁ መልክ መከሰት አለበት። ይህም ማለት፣ ተውላጠ ስሙ በግሀድ በሚታይበት ጊዜ አረፍተ ነገሮቹ ተቀባይነት ማጣት አለባቸው። ይህ ግን የሚሆን እይመስልም፣ ምክንያቱም በአፀፋ የተጠቀሰ ባለቤት በግሀድ ላይታይ፣ በዚህም ምክንያት አረፍተ ነገሩ ላይዛባ ይችላልና። የሚከተሉት የዚህ አስረጅ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) እግዜርን ይፍሩ /ይ-ፍር-ኡ/ 21
(ለ) ንጉሰን ያክብሩ /ይ-እክብር-ኡ/


እነዚህ አረፍተ ነገሮች እንደ ቀዳሚዎቹ በግሀድ የሚታይ ባለቤት የላቸውም። በግሶቹ መነሻና መድረሻ ላይ ግን ባለቤትን የሚጠቁም አፀፋ አሰ። በአፀፋው መሰረት ባለቤቱ አሁንም እነሱ የሚለው ተውላጠ ሰም ነው። በግሀድ ሲከሰት ወይም ላይከሰት ይችላል፤ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ሳያጣ። ሰለዚህም፣

(ሀ) እነሱ እግዜርን ይፍሩ /ይ-ፍር-ኡ/ 22
(ለ) እነሱ ንጉሰን ያክብሩ /ይ-እክብር-ኡ/

ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከፍ ሲል ካቀረብነው አመለካከት ጋር የሚጣጣም አይደሰም። ክፍ ሲል ባየነው አመሰካከት መሰረት፣ እነዚህ አረፍተ ነገሮች መዛባት ነበረባቸው። ተውላጠ ስሙ በግሀድ ይታያልና። ግን አልተዛቡም። ለምን?

በአማርኛ የሶስተኛ መደብ ተውላጠ ስም ሁለት አይነት ነው። እንደኛው አይነት ሰዋዊና ዕምር ነገሮችን የሚወክል ተውላጠ ስም ሲሆን፣ ሁለተኛው አይነት ኢሰዋዊና ጥቅል ነገሮችን ወይም ሁኔታዎችን የሚወክል ነው። ሰዋዊ

የሆኑት <u>አሱና አነሱ</u> የሚሉ መደበኛ ቅርፆች አሉዋቸው። አፀፋዎቻቸውም አንደ ቅደም-ተከተላቸው /ይ-/ እና /ይ-ኡ/ ናቸው። ኢሰዋዊ የሆኑት ተውላጠ ስሞች መደበኛ ቅርፅ የላቸውም። ስለዚህም የሚታወቁት በግሱ ላይ በሚታየው አፀፋ ብቻ ነው። አፀፋው የሚታየው ከፍ ሲል አንደተጠቀሰው በዋናው ግስ መነሻና መድረሻ ላይ ብቻ ነው። የሰዋዊ ተውላጠ ስሞች አፀፋ ግን በዋናው ግስ መነሻና መድረሻ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በረዳት ግሱ መድረሻ ላይም ነው። ይህም ከላይ በተራ ቁጥር (19) እና (20) እንደሚታየው ነው። ከአፀፋዎቹ የአቀማመጥ ልዩነት የተነሳ፣ ባለቤትን የሚመለከተው የግሶቹ መዋቅራዊ ባህሪ ሊለያይ ችሉአል። አንደኛው ግሀድ ባለቤት ሲፈቅድ ሌላኛው አይፈቅድም።



23(ሀ) የኢሰዋዊ መዋቅር ነው። ስለሆነም የባለቤቱ ቦታ ክፍት ነው። 23(ለ) የሰዋዊ መዋቅር ስለሆነ፣ የባለቤቱ ቦታ <u>አነሱ</u> በሚለው ተውላጠ ስም ተሞልቶአል። በዚሁ መሰረት ግሶችን ለዋዊና ኢለዋዊ ብሎ መለየት ይቻላል። ሰዋዊ ግሶች ብቻ ባለቤት፣ ማለትም ርዕሰ አላቸው። ሁለተኛም ሀተታውን የሚገልፁት ግላዊ ሀረጎች በማንኛውም የጊዜ አይነት ሊነገሩ ይችላሉ። ኢሰዋዊ ግሶች ግን ሁል ጊዜ በኢሀላፊ ጊዜ ብቻ ይነገራሉ። ዋናው ነገር፣ ግሶች ባለ ባለቤትና ባለቤት-አልባ (በግሀድ የሚታይ ባለቤት የለላቸው) ተብለው በሁለት ሊከፈሉ የሚችሉ መሆናቸው ነው።

ማንኛውም ስዋዊ ግስ ኢስዋዊ አቻ አለው። ከኢስዋዊዎች መካከል አንዳንዶቹ /ተ-/ የሚለውን የተደራጊ ምዕላድ በመነሻቸው ላይ ያሳያሉ። የሚከተሉትን እንመለከት፡

24

/ይ-ስኽብር-ኡ/ /ይ-ስኽብር-ኡ-አልል-/ /ይ-ት-ስኽብብኽር-ኡ-አልል-/
/ይ-ግኽድል-ኡ/ /ይ-ግኽድል-ኡ-አልል-/ /ይ-ት-ግኽድድኽል-ኡ-አልል-/

በመስረቱ /ት-/ የተገብሮ ግስ መስራች ምዕላድ ነች። ከተገብሮ ግስ የሚመስረት አረፍተ ነገርም የተገብሮ አረፍተ ነግር ይባላል። አስካሁን ካየናቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች በቅርፁ ይለያል። እንዴት እንደሚለይ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ተገብሮአዊ አረፍተ ነገር

አስካሁን ያየናቸው ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ሁነታዊ፣ ኑረታዊ፣ ልውጠታዊ፣ ባህሪያዊና ገቢራዊ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ አራቱ በባለቤቱ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ከነዚህ መካከልም በአዕምሮም ይሁን በአካል የሚፈፀምን ተግባር የሚያሳየው ገቢራዊ አረፍተ ነገር <u>*ገባሪ*</u>፣ ማለትም ድርጊት ፈፃሚ አንዳለውና፣ የድርጊቱን ተቀባይ የሚሆን <u>*ተገባሪ*</u> ስማዊ ሀረግም ሊኖረው አንደሚችል አሳይተናል። ገባሪው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን፣ ተገባሪው የግስ ተሳቢ ነው። አስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች በሙሉ ስለ ገባሪው ባህሪ፣ ሁነት፣ ኑረት፣ ወዘተ፡ የሚያትቱ ናቸው። ስለዚህም ገባሪ-ተኮር ልንላቸው አንችላለን።

የነዚህ ተቃራኒ የሆኑት ስለ ተገባሪው የሚያትቱ ናቸው። ይህም የሚሆነው ተገባሪው ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን ነው። የዚህ አይነት አረፍተ ነገሮች ተገብሮአዊ ይባላሉ። ግሱም የተገብሮ ግስ ይባላል። በቅርፁም ከገቢር ግስ ይለያል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንምልከት።

(ሀ) አስቴር ተሸማለች 1
(ለ) ጫካው ተመንጥሮአል
(መ) ቡናው ተወቅጦአል
(ሰ) አገሩ ተወሮአል

የእነዚህ አረፍተ ነገሮች ባለቤት በሙሉ ተገባሪ ወይም ተደራጊዎች ናቸው። ገባሪው ማን እንደሆነ አይታወቅም። የየአረፍተ ነገሩ ሀተታ የሚያተኩረው በተደራጊው ላይ ስለሆነ፣ አድራጊው ትኩረት ሊያገኝ አናም ሊጠቀስ፣ አይችልም። ባጭሩ አድራጊው ይዋጣል ወይም ከፍ ሲል አንዳየነው ኢስዋዊ ይሆናል።


ግሶቹ የተገባሪነት ምልክት ስለሆነው /ተ-/ ይጀምራሉ። ይሁን እንጅ ቀደም ሲል እንዳየናቸው እንጂ ቴቶመስ ካሉትና በ/ተ-/ ከሚጀምሩ ሌሎች ግሶች የተሰየ ናቸው። የሚሰየትም እነዚህ ሳቢ ከሆነ አቻ ግስ ላይ የሚመሰረቱ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ፣ ታሹማለች የሚለው የተገብሮ ግስ ሹማለች የሚል ገቢርና ሳቢ አቻ አለው። ተቀመጣለች የሚለው ግስ ግን ቀምጣለች የሚል ገቢርና ሳቢ አቻ የለውም። ከዚህም በ/ተ-/ ከሚጀምር ግስ ሁሉ የተገብሮ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል። ውነተኛ የቀጉብሮ ግሶ የሚባለው ሳቢ አቻ ያለውና ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር የሚችል ነው። ለምሳሌ፣ የ1(ሀ) ሳቢ አቻ ግስ ሀረጋዊ መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።

ካሌ አስቴርን ሾሞአታል 2


በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ሾሞአታል የሚለው፣ በምሳሌ 1(ሀ) ውስጥ፣ ተሹማለች የሚለው ተገብሮአዊ ግስ ሳቢ አቻ ነው። ስለሆነም፣ አስቴር የሚለውን ስም በተሳቢነት ይዞ ግሳዊ ሀረጉን መስርቶአል። ግሳዊ ሀረጉ ደግሞ ካሳ የሚለውን ስም በእድራጊ ባለቤትነት ይዞ አረፍተ ነገሩን አዋቅሮአል። የአረፍተ ነገሩ ርዕሰም ይኸው አድራጊ ባለቤት ነው። ስለሆነም፣ ግሳዊ ሀረጉ የአሱ ሀተታ ነው።

የተገብሮ አረፍተ ነገር ባለቤት ድርጊት ተቀባይ ስም ነው። እንደዚህ አይነት ስም መሰረታዊ መዋቅራዊ ቦታው በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስር ነው። ለዚህ ምክንያቱ ግሱ በባህሪው ሳቢ ስለሆነና ተሳቢ መሙሊያ ስለሚፈልግ ነው። ከዚህ ለንነሳ፣ የምሳሌ 1(ሀ) ታህታይ አወቃቀር የሚከተለውን ይመስላል።

3



በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም <u>ተሹማለች</u> የሚለው ግስ *መሙሊያ* ነው። ባለቤቱ ለለማይታወቅ ቦታው ክፍት (---) ነው። <u>አስቴር</u> የሚለው *መሙሊያ* ስም ክፍት ወደሆነው የባለቤት ቦታ በመሄድ የአረፍተ ነገሩ ተደራጊ ባለቤትና የሀተታው ርዕስ ይሆናል። የአካሄዱን ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



ከዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚደረገው፣ በታሀታይ መዋቅር ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ፣ ክፍት ሆኖ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ነው። <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ባለቤት ሊሆን የቻለው በታሀታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ የባለቤቱ ቦታ ባዶ ስለሆነለት ነው። ወደዚያ ክፍት ቦታ በመሄድ ባለቤት ሊሆን፣ እናም አፅንዖትን ሊያገኝ ችሎአል።

ይህ እንግዲህ ስዋዊ ባለቤት ባሳቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች የሚታየው የተገብሮ አረፍተ ነገር ሁኔታ ነው። ቀደም ሲል ደግሞ ባለቤታቸው ኢሰዋዊ የሆነ አረፍተ ነገሮች እንዳሉ ምሳሌ እየጠቀስን አሳይተን ነበር። የእነዚህ አይነት አረፍተ ነገሮች ተገብሮአዊ ስርዓት ምን እንደሚመስል በሚከተሉት ምሳሌዎች አማካኝነት እናስረዳለን።

(ሀ) ንብረትን ይዘረፉአል /ይ-ት-ዝአርርአፍ-አ-አልል/ [6] 5
(ለ) ስንቅን ይነጠቁአል /ይ-ት-ንአጥጥአቅ-አ-አልል/

[6] ከዚህ ላይ የተገብሮዋ ምዕላድ ከአምዱ መነሻ ተናባቢ ድምፅ ጋር ሙሉ በሙሉ መመሳሰልዋን ልብ ይሉአል።

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ተግብሮአዊ አንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሰአል። ለዚህም /-ት-/ የምትለውን ምዕላድ ማስቀደማቸው ምልክት ነው። የገቢሩ ግስ አንቀፅ ካልዓይ ነው። ለለሆነም የባለቤት አፀፋው /ይ-/ በአምዱ መነሻ ላይ ከተገብሮዋ ምዕላድ ቀድሞ፣ የብዙ ቁጥር ምዕላድ የሆነው /-ኡ/ አምዱን ተከትሉ ገብቶአል። የተገብሮው ግሱ ቅድመ-መድረሻ አግርም ጠብቆአል። በዚህም ምክንያት የአምዱ አንቀፅ ቀዳማይ ነው ለማለት ይቻላል። የቅድመ-መድረሻው አግር ጥብቀት ግን ከተገብሮአዊነቱ ጋር የተያያዘ ነው። ማንኛውም ካልዓይ አንቀፅ ተገብሮአዊ በሚሆንበት ጊዜ ቅድመ-መድረሻ አግሩን ያጠብቃል። ለዚህ የምሳሌ 5(ሀ)ን ግስ ከገቢራዊ አቻው ጋር እያነፃፀርን ብናየው፣ ልዩነቱ ግልፅ ይሆናል።


ገቢር ፡	ይዘርፉአል	/ይ- -ዝኧርፍ-ኡ-አል/	6
ተገብሮ፡	ይዘረፉአል	/ይ-ት-ዝኧርርኧፍ-ኡ-አል/	

ከምሳሌ 5(ለ)፣ /ይ-ት--ንኧጥጥኧቅ-/ የሚለው የተገብሮው ግለ አምድ ቅድመ-መድረሻ አግር ጥብቅ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

በምሳሌ (5) ውስጥ፣ <u>ንብረትን</u> እና <u>ሰንቅን</u> የሚሉት ስሞች የየግሶቹ *መሙሊያ* ናቸው። የየአረፍተ ነገሩ ባለቤት ቀደም ሲል እንደገለፅነው ኢስዋዊ ነው። ለለዚህም ነጠላ ከሆነ፣ /ይ-/ በሚለው የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ብቻ፣ ብዙ ከሆነ ደግሞ /-ኡ-/ በሚለው የብዙ ቁጥር ምዕላድ ጭምር ይጠቀሳል (ይታወቃል) እንጅ በግሀድ ፊዕሞ አይከሰትም። *መዋቅራዊ* ቦታው ግን ከላይ በተራ ቁጥር (3) በሚታየው ዕፀ-መዋቅር ውስጥ በሰረዝ የተመለከተው ነው። *መሙሊያው* ወደዚህ ቦታ ሂዶ ባለቤት ለመሆን አይችልም። ምክንያቱም እዚህ ቦታ ከተገኘ የሀተታው ርዕስ ስለሚሆን፣ ግሀድ *መውጣት* ይኖርበታል። ግሀድ ከወጣ ደግሞ አንድም ኢስዋዊ መሆኑ ይቀራል፣ አለያም አረፍተ ነገሩ ይዛባል። ለምሳሌ የሚከተሉትን አንመልከት።

(ሀ)	በግ ይነጠቃል	/ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-አል/	7
(ለ)	--- በጎችን ይነጠቁአል	/ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-ኡ-አል/	
(መ)	*በጎች ይነጠቋል	/ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-ኡ-አል/	

ምሳሌ (ሀ) ስዋዊ የተገብሮ አረፍተ ነገር *መዋቅር* ነው። ምሳሌ (ለ) ኢለዋዊ የተገብሮ አረፍተ ነገር ነው። የባለቤቱ ቦታ ክፍት (--) ነው። ምሳሌ (መ) <u>በጎች</u> የሚለው *መሙሊያ* የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ በግሀድ የሚታይበት አረፍተ ነገር ነው። ባለቤቱ ግሀድ በመውጣቱ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን አጥቶአል። ሳዕላይ አወቃቀሩን ግን እንደሚከተለው እናሳያለን።



8

ባጭሩ ኢሰዋዊ የሆነ የገቢርም ሆነ የተገብሮ አረፍተ ነገር ባሰቤት በአፀፋ ይታወቃል አንጅ በግሀድ አይከሰትም፣ ሰሰዚህም በግልፅ አይታወቅም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። እንደነዚህ ያሉትን ባለቤታቸው በውል የማይታወቅ አረፍተ ነገሮችን ኢውሱን በማለት ባለቤታቸውን በግሀድ ከሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች መሰየት ይቻላል። ለምሳሌ፣

ነጋዴዎቹ ሰንቃቸውን ተዘርፈዋል 9

በሚሰው አረፍተ ነገር ውሰጥ፣ ባለቤቱ <u>ነጋዴዎቹ</u> የሚሰው ዕምር ሰማዊ ሀረግ እንደሆነ ከአገባቡም ሆነ ከአፀፋው መረዳት ይቻላል። <u>ሰንቅን ይዘርፉአል</u> በሚሰው ኢሰዋዊ ገቢር አረፍተ ነገር ውሰጥ ግን ዘራፊውን፣ እንደዚሁም <u>ሰንቅን ይዘረፉአል</u> በሚለው ተግብሮአዊ አቻው ውሰጥ፣ ተዘራፊውን አካል በውል ማወቅ አይቻልም። ማንኛውንም ዘረፋን ሊያካሄድ የሚችል አካልና ማንኛውንም ሊዘረፍ የሚችልን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል። ሰሰዚህም በይዘቱ ኢውሱን ነው።

እሰካሁን ካየነው ዝርዝር ሁኔታ ሁሰት አይነት ገቢርና ሁሰት አይነት የተገብሮ አረፍተ ነገሮች እንዳሉ ሰመረዳት ይቻላል። እነዚህም ሰዋዊና ኢሰዋዊ ወይም ውሱንና ኢውሱን ናቸው። ውሱኖቹ የታወቀ ገባሪ ባሰቤት ሲኖራቸው፣ ኢውሱኖቹ ያልታወቀ፣ ያልተወሰነ ተገባሪ ባለቤት አሳቸው። የየአረፍተ ነገሩ ሀተታ ትኩረትም በውሱኑ ባሰቤት ወይም መሙሲያ ላይ ነው። በመሙሲያው ላይ የሚሆነው፣ በምሳሌ 7(ለ) እንደሚታየው፣ የአረፍተ ነገሩ ባሰቤት ኢውሱን በሚሆንበት ጊዜ ነው።

መጠይቃዊ አረፍተ ነገር

አሰካሁን ያየነው የሀተታዊ አረፍተ ነገሮችን መዋቅራዊ ባህሪና ተግባር ነው። በመዋቅራዊ ባህሪያቸው ባለቤት ስማዊ ሀረግ እንዳላቸውና ይህም ባለቤት በመዋቅራዊ ቦታውና በአፀፋ እንደሚለይ፣ እንደ ግሳቸው ባህሪም መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ሊኖራቸው እንደሚችልና እነዚህም በአገባባቸውና በአፀፋቸው አይነት ከባለቤት ሀረጎች እንደሚለዩ እይተናል። ባለቤታቸው በየግሱ ሰሚጠቀስው ሁኔታ ወይም ተግባር አድራጊ፣ ወይም ተደራጊ ወይም ሁዋኝ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝበናል። ተግባራቸውን በሚመለከትም፣ ከለማቸው እንደምንረዳው፣ ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች እታች ወይም ተራኪ ናቸው። የሚተርኩት ስለ ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህም የተነሳ ባለቤት ስማዊ ሀረግን እንደ አረፍተ ነገር ርዕስ፣ ግሳዊ ሀረግን ስለዚህ ርዕስ እንደሚቀርብ ሀተታ ወይም ትረካ አድርገን ልንመለከተው እንደምንችል ቀደም አድርገን ገልፀናል።

አንድ አረፍተ ነገር ግን የሚያትት ብቻ ሳይሆን፣ በታተተው ጉዳይ ላይ ጥያቄ የሚያነሳም ሊሆን ይችላል። ጥያቄው ስለ ባለቤቱ፣ ስለ መሙሊያው፣ ስለ አጎላማሹ ወይም ስለ ድርጊቱ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ያለ አገልግሎት ያለውን አረፍተ ነገር መጠይቃዊ አረፍተ ነገር እንለዋለን። መዋቅራዊ ባህሪውን ከዚህ ቀጥለን እንደተለመደው በቅደም-ተከተል እንመረምራለን።


አንድ ሰው ጥያቄ የሚጠይቀው፣ እንድም የማያውቀውን ነገር ለማወቅ፣ አለያም የሚያውቀውን ነገር ለማረጋገጥ ነው። የማያውቀውን ነገር ለመጠየቅ፣ መጠይቅ ተውላጠ ስሞችን ይጠቀማል። የሚያውቀውን ነገር ለማረጋገጥ የማረጋገጫ ቃላትን ወይም <u>ቅላፂን</u> ይጠቀማል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት[7]።

(ሀ) ካሳ መቸ መጣ? 1
(ለ) ካሳ መጣ ወይ?
(መ) ካሳ መጣ?

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር፣ ጠያቂው፣ ካሳ የመጣበትን ጊዜ እንዳላወቀ ያሳያል። ስለዚህም ጊዜውን ለማወቅ <u>መቸ</u> የሚል መጠይቅ ተውላጠ ስም በመጠቀም፣ የጥያቄውን አረፍተ ነገር አዋቅሮአል። የዚህ አይነት ጥያቄ ዛሬ፣ ትናንት፣ ወዘተ፣ የሚል መልስ ይፈልጋል። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ ጠያቂው ካሳ እንደሚመጣ ያውቃል። በርግጥ መምጣቱን ወይም አለመምጣቱን ግን አያውቅም። ስለዚህም አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ <u>ወይ</u> የምትለዋን <u>ቃለ ጥያቄ</u>

[7] በመጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት ስለሚጠየቁ ጥያቄዎች መዋቅራዊ ባህሪ ግርማ (1992)ን ይመልከቱ። መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹ እንደ መስተጓምር ሊወሰዱና ሊተነተኑ ይችላሉ። ዝርዝሩን ወደ ሁዋላ እናየዋለን።

በመጠቀም አረጋጋጭ ጥያቄ ጠይቆአል። <u>ወይ</u> የምትለዋ ምዕላድ የአረጋጋጭ ጥያቄ ምልክት ነች። አገባበዋም በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ነው። መዋቅራዊ ግንኙነትዋ ግን ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው። አረፍተ ነገሩ ሀተታዊ ሳይሆን፣ መጠይቃዊ መሆኑን ታመለክታለች። ሁኔታውን በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



መዋቅሩ፣ <u>ካሳ መጣ</u> የሚለው ሀተታዊ አረፍተ ነገር፣ <u>ወይ</u> ከሚለው ምዕላድ ጋር ሲዋቀር፣ ካሳ መጣ ወይ? የሚል ሰፊ መጠይቃዊ መዋቅር ይፈጥራል። ይህም <u>ካሳ መጣ</u> የሚሰውን መዋቅር፣ <u>ካሳ መጣ ወይ</u> የሚለው ሰፊ መዋቅር ጥገኛ ያደርገዋል። ይህን ጥገኝነቱን የምታመለክተው <u>ወይ</u> የምትለዋ ምዕላድ ነች። እንደዚህ ያሉ አንድ አረፍተ ነገር በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ መጠጋቱን የሚያመለክቱ ምዕላዶች በጥቅሉ <u>ሞይ</u> ይባላሉ። ቅርፃቸው እንደ ጥገኛው አረፍተ ነገር ተግባር ይለያያል። እንደ <u>ወይ</u> ያሉት፣ አንድ አረፍተ ነገር መጠይቃዊ መሆኑን የመለክታሉ። በግልፅ እንደሚታየውም አገባባቸው ከመጠይቁ ተውላጠ ስም አገባብ የተለየ ነው። ተውላጠ ስሞቹ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ፣ ሰጥያቄው መንስዔ በሆነው ሀረግ መዋቅራዊ ቦታ ላይ ይገባሉ። መልሳቸውም <u>አወን</u> ወይም <u>የለም</u> የሚል ነው።

የሰሰተኛው ጥያቄ የመጠይቅ ምዕላድ የለውም። ስለዚህም መዋቅራዊ ቅርፁ ከሀተታ አረፍተ ነገር ጋር አንድ ነው። መጠይቅ መሆኑ የሚታወቀው በጥያቄ ምልክቱና በቅላፄው ብቻ ነው። የጥያቄ ምልክቱ ከፅሁፉ፣ ቅላፄው፣ ከአረፍተ ነገሩ <u>ንበት</u> ይታወቃል። መጠይቅ አረፍተ ነገር የሚነበበው ወይም የሚነገረው በ<u>አሻቃባ</u> ቅላፄ ነው። ይህም ወራጅ ወይም <u>አቆልቁዋይ</u> በሆነ <u>ቅላፄ</u> ከሚነገረው ከሀተታዊ አረፍተ ነገር የተለየ ያደርገዋል። የቅላፄው አይነት የአረፍተ ነገሩን የተግባር አይነት ይጠቁማል።

አንዳንድ ጊዜ ጠያቂው የካሳን መምጣት ወይም አለመምጣት ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ሊረዳ ይችላል። ሆኖም ግን የማረጋገጫ ጥያቄ አንዳንድ ጊዜ በግርምታ፣ ሌላ ጊዜ በሰዘብታ ሊጠይቅ ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ ቢጠየቅ፣ ጥያቄው <u>እንዴ</u> የምትሰዋን ቃለ-ጥያቄ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ያስከትላል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ካሳ መጣ እንዴ? 3
(ለ) አስቴር ምሳዋን በላች እንዴ?

እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች <u>አወን፣</u> ወይም <u>እንዲያውም</u> (የለም) በሚል መልስ ብቻ ሳያቆሙ ይችላሉ። ምነው? ለምን ጠየቅኸኝ? የሚል ሌላ ጥያቄ ሊያስከትሉ ይችላሉ። በተለይም ተጠያቂው፣ ጠያቂው ለጥያቄው መነሻ ያደረገውን <u>አውደ ነገር</u> ያልተገነዘበ እስከሆነ ድረስ። ለምሳሌ፣ በወር መጨረሻ ላይ፣ ባል እንደተለመደው፣ አንድ ጥቅል ነገር ይዞ ወደ ቤቱ ቢገባ፣ በሚስት በኩል ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፣

(ሀ) ደሞዝ ወለድክ ወይ? 4

ሳይሆን፣

(ለ) ደሞዝ ወሰድክ እንዴ?

የሚል ይሆናል። ጥቅል ይዞ መግባቱ፣ ገንዘብ የማግኘቱ ምልክት ነውና፣ ጥያቄው ይህኑ በከፊልም ቢሆን የታወቀ ነገር ለማረጋገጥ የሚነሳ ነው። ነገር ግን ባል ደሞዝ እንደሚወስድ እየታወቀ፣ ምንም ነገር ሳያንጠለጥል ቢመጣ፣ ሚስት ልትጠይቅ የምትችለው ጥያቄ፣

(ሀ) ደሞዝ ወስድክ ወይ? 5

ወይም (ለ) ደሞዝ ወሰድክ?

የሚል እንጅ፣

(መ) ደሞዝ ወስድክ እንዴ?

የሚል አይሆንም። <u>እንዴ</u> የሚለውን ቃለ-ጥያቄ መጠቀም ካለባት፣ ጥያቄውን አሉታዊ በማድረግ፣

ደሞዝ አልወሰድክም እንዴ? 6

ማለት ይኖርባታል። ከፍ ሲል ከጠቀስነው ቅላፄ በተጨማሪ <u>አውደ ነገርም</u> ስሚነሳው ጥያቄ አይነት አስተዋፅዖ ሊያደርግ እንደሚችል <u>እንዴ</u> እና <u>ወይ</u> ከሚሉት ቃለ-ጥያቄዎች አጠቃቀም መረዳት ይቻላል።

በአንድ አረፍተ ነገር ሰለ ተገለፀ ድርጊት ወይም ሁኔታ፣ ሰለ ድርጊቱ ፈፃሚ፣ ሰለ ማድረጊያው መሳሪያ ወይም ጊዜና ቦታ፣ ድርጊቱ ስለተፈፀመበት ምክንያት ወይም ዓላማ፣ ስላደራረጉ ሁኔታ ወይም ዘዴ፣ ወዘተ፣ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። እነዚህ ደግሞ የሚገለፁት በተለያዩ ሀረጎች ስለሆነ፣ ጥያቄው የሚነሳው በመሰረቱ በየሀረጎቹ ላይ ነው። ሀረጎቹ በአራት ሊጠቃለሉ ይችላሉ። እነሱም

አድራጊ፣ ተደራጊ፣ ገላጭ (አጎላማሽ) እና መስተዓምር ብለን ቀደም ሲል የገለፅናቸው የየሀረጉ ተዋቃሪዎች ናቸው። ሁሉም በግሱ ከሚገለፀው ድርጊት ወይም ሁነት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተቆራኙ ስለሆኑ፣ የዚሁ መግለጫ ከሆነው ግስ ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት አላቸው። ግንኙነቱም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የባለቤትነት፣ የመሙሊያነት፣ የአጎላማሽነትና የመስተዓምርነት ነው። ስለዚህም የሚነሳው ጥያቄ ከነዚህ በአንዱ ላይ የሚያተኩር ነው። ይህን ከዚህ ቀጥሎን በምሳሌ እያሰደገፍን እናሰረዳለን። የሚከተለውን አረፍተ ነገር እንመልከት።

[ካሳ [ከእናቱ ጋር [በተሲያት [ምሳውን በላ]]]] 7

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ሁለት ስማዊ ሀረጎችና ሁለት መሰተዋድዳዊ ሀረጎች አሉ። ሰማዊ ሀረጎቹ ካሳ እና ምሳውን የሚሉት ሲሆኑ፣ ተግባራቸውም ባለቤትነትና ተሳቢነት ነው። መሰተዋድዳዊ ሀረጎቹ ከእናቱ ጋር እና በተሲያት የሚሉት ሲሆኑ፣ ተግባራቸው ገላጭነት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከተሳቢው ስማዊ ሀረግና ከገላጮቹ መሰተዋድዳዊ ሀረጎች የተዋቀረውና ድርጊቱን የሚገልፀው ግሳዊ ሀረግ አለ። ይህም ከእናቱ ጋር በተሲያት ምሳውን በላ የሚለው መዋቅር ነው።

ጥያቄ የሚነሳው እንግዲህ እነዚህን ሀረጎች በማመለከት ሰለሆነ፣ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ማን ከእናቱ ጋር በተሲያት ምሳውን በላ? 8
(ለ) ካሳ ከእናቱ ጋር በተሲያት ምን በላ?

እነዚህ ጥያቄዎች ለማዊ ሀረጎቹን የሚመለከቱ ናቸው። መጠይቅ ተውላጠ ለሞቹም የሚገኙት ለማዊ ሀረጎቹ በሚገቡበት፣ ማለትም በባለቤትና በተሳቢ ቦታ ላይ ነው።


(ሀ) ካሳ ከማን ጋር በተሲያት ምሳውን በላ? 9
(ለ) ካሳ ከእናቱ ጋር መቸ ምሳውን በላ?

እነዚህ ጥያቄዎች ሰማዊ ሀረግን ሳይሆን፣ መሰተዋድዳዊ ሀረጎችን የሚመለከቱ ገላጭ ጥያቄዎች ናቸው። መጠይቅ ተውላጠ ለሞቹም የሚገኙት ከ ከሚለው መሰተዋድድ ጋር ነው። በመጨረሻም ራሱን ግሳዊ ሀረጉን የሚመለከት ጥያቄ እንደሚከተለው መጠየቅ ይቻላል።

ካሳ ምን አደረገ? 10

ይህ ደግሞ የድርጊት ጥያቄ ነው። አድራጊን፣ ተደራጊን ወይም ገላጭን ሳይሆን፣ ድርጊቱን ራሱን ከነምናምኑ የሚመለከት ነው። የተጠየቀውም ምን በሚል መጠይቅ ተውላጠ ስምና አደረገ በሚል ግስ አማካኝነት ነው። አደረገ የሚለው ግስ በማንኛውም የድርጊት ግስ ምትክ ሊገባ ይችላል። ምን እና ማን የሚሉት ማንኛውንም ለም ተክተው ሊገቡ እንደሚችሉና በዚህም ምክንያት መጠይቅ ተውላጠ ስም እንደሚባሉ ሁሉ፣ አደረገ የሚለው ግስም መጠይቅ ተውላጠ ግስ ሊባል ይችላል። የማንኛውም የድርጊት ግስ ምትክ ነውና። የጥያቄዎቹን ሀረጎች መዋቅራዊ አቀማመጥ በሚከተለው ዕፀ - መዋቅር እናሳያለን።

11



እንደ አደረገ ሁሉ፣ አለ የሚለው ግስም በመጠይቅ ግስነት ሊገባ ይችላል። የሚገባው ግን ድርጊትን ሳይሆን፣ ህለትን (የአንድን ነገር መባል) ለመጠየቅ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

ካሳ አመጣለሁ አለ

12

ይህ አረፍተ ነገር የሚገልፀው አንድ ድርጊት ማድረግን ሳይሆን፣ አንድ ነገር ማለትን ነው። ስለዚህም ግሱን የማለት ግስ ልንለው እንችላለን። እንደነዚህ ባሉ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ግላዊ ሀረግን የሚመለከት ጥያቄ በዚሁ ግስና ምን በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት መጠየቅ ይቻላል። ይኸውም፣

ካሳ ምን አለ 13

በማለት ነው።

ቀደም ሲል ስለ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ አንድ አረፍተ ነገር ድርጊትን ብቻ ሳይሆን፣ ሁነትንና ኑረትንም እንደሚያመለክት ገልፀን ነበር። በዚያም መሰረት እነዚህን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እንደሚከተለው አድርጎ በሁነትና በኑረት ግሶች አማካኝነት ማንሳት ይቻላል።

(ሀ) ካሳ የት አለ? 14
(ለ) ካሳ ምን ሆነ?

የመጀመሪያው የኑረት ሲሆን፣ ሁለተኛው የሁነት ጥያቄ ነው። መጠይቅ ተውላጠ ሰሞቹም የገቡት ጥያቄውን ባለከተለው ተዋቃሪ ሀረግ ቦታ ላይ ነው።

እስካሁን ድረስ ያየናቸው መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ነጠላ ጥያቄ የሚጠይቁ ናቸው። ይህም ማለት፣ አረፍተ ነገሮቹ የሚጠይቁት ስለ አንድ ነገር ወይም ድርጊት ወይም ኑረት ወይም ሁነት ብቻ ነው። መጠይቅ ተውላጠ ሰሞቹም አንዳንድ ብቻ ናቸው። ይህ አንዱ የጥያቄ አይነት ነው። ሌላው አይነት ድርብ ጥያቄዎችን የሚመለከት ነው። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ማን ምን አደረገ? 15
(ለ) ማን ከማን ጋር ምሳ በላ?
(መ) ማን ምን በላ?

የመጀመሪያው ምሳሌ ባለቤቱን ሰማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጉን፣ ግሰትም አድራጊውንና ድርጊቱን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አድራጊውን ከነአጋሩ የሚጠይቅ ነው። የመጨረሻው አድራጊውንና ተደራጊውን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ላሉ ድርብ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ድርብ ነው። ስለዚህም የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ፣

ካሳ እንጀራ በላ 16

የሚል አይነተ ይሆናል። የሌሎቹም መልስ በዚሁ ሁኔታ የሚሰጥ ነው።

አንድ መጠይቅ አረፍተ ነገር ከድርብ አልፎ ድርብርብ ሲሆን ይችላል። ይህም በአንድ ጊዜ ከሁለት በላይ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ሊመለከት ይችላል ማለት ነው። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

ማን ከማን ጋር ምን አደረገ? 17

ይህ አረፍተ ነገር አድራጊውን፣ አዳራጊውንና ድርጊቱን የሚመለክቱ መጠይቆችን ይዞአል። አድራጊውን <u>ማን</u>፣ በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም፣ አዳራጊውን <u>ከማን ጋር</u> በሚል ገላጭ መጠይቅ መሰተዋድዳዊ ሀረግ፣ እንደዚሁም ድርጊቱን <u>ምን አደረገ</u>? በሚል ግሳዊ ሀረግ በመጠየቅ ነው። ለእንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚሰጠው መልስም፣

ካሳ ከአናቱ ጋር ምሳ በላ 18

የሚል ይሆናል። አወቃቀሩ በተራ ቁጥር (16) የተገለፀው አይነት ነው። ርግጥ፣ እንደነዚህ ያሉ ድርብርብ ጥያቄዎች በአወቃቀር አንጅ በአጠቃቀም ላይ ላያጋጥሙ ይችላሉ። አብዛኛው የቁዋንቁዋው ተጠቃሚ የሚያተኩረው አንድን ነገር ብቻ በመግለፅ ወይም በመጠየቅ ላይ ነው። ይሁን አንጅ፣ የቁዋንቁዋው ጥናት በሚባለው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሚታሰበውና ሊባል በሚችሰው ጭምር የሚያተኩር በመሆኑ፣ የጥናቱን ትንተና በአብዛኛው ከአጠቃቀም ያለፈ እንዲሆን ያደርገዋል። በአጠቃቀም ላይ ብቻ የሚወሰን ከሆነ፣ ብዙ ጥያቄዎች ያለምላሽ ይቀራሉ። የብዙዎቹ ጥያቄዎች መልሰ ከሚባለው ሳይሆን፣ ከሚታሰበው፣ ማለትም አዕምሮአዊ ከሆነው የቁዋንቁዋ ችሎታ ላይ የሚገኝ ነው።

ድርብም ሆነ ድርብርብ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም-ተከተሳቸውን ሊያፋልሱ አይችሉም። ስለዚህም፣


(ሀ) ማን ምን በላ 19
(ለ) ማን ከማን ጋር ምን አደረገ?

አንጅ፣

(ሀ) ?ምን ማን በላ? 20
(ለ) ?ከማን ጋር ምን ማን አደረገ?

ግሰት አይቻልም።

ይህን የቅደም-ተከተል ገደብ ቀደም ሲል ከጠቀስነው ከሰዋዊነትና ከኢሰዋዊነት ባህሪ ጋር ማገናዘብ ይቻላል። ሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎች፣ ኢሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚገልፁ ሀረጎች የበለጠ አፅንያትን ይፈልጋሉ። ይህን የሚያገኙት፣ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሲገኙ እንደሆነ ገልፀናል። በዚህም ምክንያት ኢሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎች፣ ሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ቀድመው በላዕላይ መዋቅር ሲገቡ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያጣል። የምሳሌ (20)ን ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን።



21

ምን የሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም ክፍት ከሆነው (...) ታሀታይ ቦታው ወጥቶ፣ ማን የሚለውን ለዋዊ ባለቤት መጠይቅ ተውላጠ ስም በመቅደምና ከፍ ካለ ርከን ላይ በመቀመጡ፣ ውጤቱ ተቀባይነት የሌለው መጠይቃዊ አረፍተ ነገር ሊሆን ችሎአል።

እንግዲህ ስለ መጠይቅ አረፍተ ነገር አስካሁን በዝርዝር ያቀረብነውን እንደሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክር። መጠይቅ አረፍተ ነገር አንድ ነገርን ለማወቅ ወይም ለማረጋገጥ የሚነገር የአረፍተ ነገር አይነት ነው። መዋቅራዊ ባህሪው መጠይቅ ተውላጠ ስሞችን፣ መጠይቅ ምዕላዶችን ወይም ግሶችን በሚጠየቀው ሀረግ ቦታ ላይ ማስገባት ነው። ተውላጠ ለሞቹ ማን፣ ምን፣ መቸ፣ የት፣ እንዴት፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ምዕላዶቹ ደግሞ እንዴ እና ወይ የሚሉት ናቸው። ግሶቹም አደረገና አለ ናቸው። የሚገልፁትም እንደ ቅደም-ተከተላቸው ድርጊትንና ብለትን ነው። በመጠይቅ ተውላጠ ለሞች አማካኝነት የሚጠየቁት አድራጊ፣ ተደራጊ፣ ገላጭና መስተዓምር ናቸው። አድራጊ፣ ተደራጊና መስተዓምር ለማዊ ሀረግ የሆነ መልስ ይፈልጋሉ። ገላጭ ጥያቄዎች ለማዊ ወይም መስተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። የድርጊትና የሁኔት ጥያቄዎች ግሳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። ባጠቃላይ ጥያቄዎች በመጠይቅ ተውላጠ ስም፣ በመጠይቅ ተውላጠ ግስ፣ በቃለ ጥያቄና በቅላፄ መልክ ይከሰታሉ።

ጥያቄዎች ነጠላ፣ ድርብና ድርብርብ ሊሆኑ ይችላሉ። ነጠላ ጥያቄዎች አንድ ነገር ወይም ድርጊት የሚጠይቁ ናቸው። አንድ የመጠይቅ ተውላጥ ብቻ ይሻሉ። ድርብ መጠይቆች በአንድ ጊዜ ሁለት ሀረጎችን የሚጠይቁ ሲሆኑ፣

ድርብርብ የሚባሉት ደግሞ ከሁለት በላይ የሆኑ ሀረጎችን የሚጠይቁ ናቸው። ድርብም ሆኑ ድርብርብ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም ተከተላቸውን እይለቁም። በዚህም የመጠይቅ አረፍተ ነገሮችን ጉዳይ ለጊዜው እልባት ሰጥተን ወደሚቀጥለው ርዕሰ ጉዳይ እንሂዳለን። ለጊዜው የምንልበት ምክንያት በሌላ ቦታ በሌላ አይነት መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ስለምንገናኝ ነው።

አሉታዊ አረፍተ ነገር

አንድ አረፍተ ነገር፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የሚያትት ወይም የሚጠይቅ ብቻ ላይሆን ይችላል። የታተተውን የሚያልት (አሌ የሚል) ሊሆንም ይችላል። የሚያልተውም ቀደም ሲል በሀተታ አረፍተ ነገር የተገለፀን አንድ ሀሳብ ነው። እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው አረፍተ ነገር አሉታዊ ይባላል። በዚህ ንዑስ ክፍል የምናተኩረው በአሉ ላይ ነው። የሚከተለውን ለአብነት እንመልከት።

[ካሳ [ከእናቱ ጋር [ምሳውን በላ]]] 1


በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ሰማዊ ሀረጎች፣ እንድ መስተዋድዳዊ ሀረግና አንድ ግሳዊ ሀረግ አሉ። የነዚህ ቅንጅት የሆነው አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ እንደ አንድ ሰፊ ሀረግ የሚቆጠር ነው፣ ለዚያውም ግሳዊ። የሀረጎቹ መዋቅራዊ ዝምድና በቅንፎቹ እንደተመለከተው ነው። መጀመሪያ ግሱና <u>ምሳውን</u> የሚለው ሰማዊ ሀረግ [ምሳውን በላ] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ይህ ሀረግ ምሳ የመብላትን ፅንሰ-ሀሳብ ይገልፃል። ይህ ንዑስ ሀረግ [ከእናቱ ጋር] ከሚለው አዳራጊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ [ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። ሀረጉም ከእናት ጋር ምሳ የመብላትን ሀሳብ ይገልፃል። በመጨረሻም ይህን አቢይ ግሳዊ ሀረግ <u>ካሳ</u> ከሚለው አድራጊ ሰማዊ ሀረግ ጋር በማቀናጀት፣ [ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን ሰፊ መዋቅር እናገኛለን። ይህም የአረፍተ ነገሩ መዋቅር ነው። ሀሳባዊ ይዘቱ <u>የካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ የመብላቱ</u> ድርጊት ነው። ይህ አረፍተ ነገራዊ ሀሳብ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙት ተዋቃሪ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ውጤት ነው። የሀረጎቹ ሀሳብም እንደዚሁ በውስጣቸው የሚገኙ ንዑስ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ አንድ አረፍተ ነገር የሚነገርበት ምክንያት እንድን ሙሉ ሀሳብ ለተነጋሪ ሰማሳወቅ ወይም ለማስገንዘብ ነው። ይህን ሰማድረግ አረፍተ ነገሩ ሰዋስዋዊ፣ ማለትም የመዋቅርን ህግ የጠበቀ፣ ሙሉ ሀሳብን ያዘለና ውነትን የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፤ ውነት አንፃራዊ

ቢሆንም፡፡ አንድ አረፍተ ነገር በቅርፁ የተሰተካከለ፣ በይዘቱም የተሙዋላ ሆኖ ሳለ፣ ውነትን ግን በከፊልም ሆነ በሙሉ ላያንፀባርቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ከላይ የተጠቀሰው አረፍተ ነገር የዚህ አይነት ህፀፅ ካለበት፣ አድማጩ፣ ማለትም ተነጋሪው፣ ላይቀበለው ይችላል፡፡ ካልተቀበለው ደግሞ እንደሚከተለው አድርጎ <u>ሊያልተው</u> ይችላል፡፡

ካሳ ከአናቱ ጋር ምሳ አልበላም 2

ይህ አረፍተ ነገር ከላይ ከተሰጠው አወንታዊ አቻው የሚለየው በግሱ ቅርፀ ነው፡፡ ግሱ /አል-/ የሚል መነሻና /-ም/ የሚል መድረሻ አለው፡፡ በዚህም ምክንያት አወንታዊ የነበረው አረፍተ ነገር ወደ አሉታዊነት ተለውጦአል፡፡ የአሉታዊነቱ መንስዔ /አል-/ የሚለው ምዕላድ ብቻ ነው፡፡ /-ም/ የተራ አሉታዊ አረፍተ ነገር ምልክት ወይም ሞይ ነች፡፡ ግንኙነትዋም ከተወሰነ ሀረግ ጋር ሳይሆን፣ ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ጋር ነው፡፡ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር፣ አንደ <u>ወይ</u> ወይም <u>አንደ</u> ያለ ምዕላዳዊ ምልክት እንዳለው ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ተራ አወንታዊ የሀተታ አረፍተ ነገር ለአወንታዊነቱ የተለየ ምዕላዳዊ ምልክት ወይም ሞይ የለውም፡፡ በዚህም ከሌሎቹ ይለያል፡፡ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተሰውን ይመስላል፡፡



3

/-ም/ ሞይ ሰመሆንዋ ምልክቱ፣ አረፍተ ነገሩ ከሌላ አይነት ሞይ ጋር በሚዋቀርበት ጊዜ አሰዋ በቦታዋ ላይ አለመገኝትዋ ነው፡፡ ሁለተኛም ከላይ እንደሚታየው /-ም/ ልትቀር ትችላለች፡፡ በመቅረትዋ ግን የአረፍተ ነገሩ አሉታዊነት አይቀየርም፡፡ ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡

[አስቴር [ካሳ ከአናቱ ጋር ምሳ አንዳልበላ (<u>አንደ</u> አል-በላ)] ታውቃለች] 4


ይህ ከሁለት አረፍተ ነገሮች የተዋቀረ ሰፊ አረፍተ ነገር ነው። ተዋቃሪዎቹ አረፍተ ነገሮች በውስጠኛውና በውጫኛው ቅንፎች ውስጥ የተመለከቱት ናቸው። በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ የሚገኘው አረፍተ ነገር እሱታዊ ነው። በመሆኑም የእሱታዊ ምዕላድ የሆነችውን /እል-/ን ብቻ በግሱ መነሻ ላይ ያሳያል። ይህ አረፍተ ነገር የውጨኛው አረፍተ ነገር ተጠኒ ነው። ለዚህ ጥገኝነቱ ምልክት እንድትሆነው <u>እንደ</u> የምትሰዋን ምዕላድ በግሱ ላይ ያሳያል። /-ም/ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ እትታይም፣ ልትታይም አትችልም፤ ምክንያቱም እስዋ የተራ እሱታዊ አረፍተ ነገር ሞይ ነች።

ወደ ምሳሌው እንመለስና የታሰተውን ሀሳብ ለማየት እንሞክር። በግልፅ እንደሚታየው፣ የእሌተዋ ምዕላድ የምትገኘው ከግሱ ጋር ሰለሆነ፣ የታሰተው ሀሳብ በግሱ የተነሰፀው ምሳ የመብሳት ድርጊት ነው፣ ሰማለት ይቻል ይሆናል። ይህ አባባል ግን ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለው አይደለም። ምክንያቱም እሌቱ በግሱ ላይ ብቻ ሳይወሰን፣ በእሱ መሪነት የተዋቀረውን አቢይ ግሳዊ ሀረግም ሊጨምር ይችላል። እንዲያውም ከዚያም አልፎ በከፊልም ቢሆን፣ ከዚሁ አቢይ ሀረግና ካሳ ከማለው ሰማዊ ሀረግ የተዋቀረውን አረፍተ ነገር ጭምር ሊጠቅስ ይችላል። በሌሳ አባባል፣ አሳቹ ምዕላድ በግሱ ላይ ይለጠፍ እንጅ፣ እሌቱ ከግሱ አልፎ ማንኛውንም ሀረግ ሊሸፍን ይችላል። ሰለዚህም አረፍተ ነገሩ በቁሙ በጣም አሻሚ ነው። አሻሚነቱን እንደሚከተለው እያደረጉ ማሰወገድ ይቻላል።

(ሀ) ከእናቱ ጋር ምሳ የበላው <u>ካሳ</u> አይደለም፤ አበበ ነው
(ለ) ካሳ ምሳ የበላው <u>ከእናቱ ጋር</u> አይደለም፤ ከእህቱ ጋር ነው
(መ) ካሳ ከእናቱ ጋር የበላው <u>ምሳ</u> አይደለም፤ ራት ነው
(ሰ) ካሳ ከእናቱ ጋር <u>ምሳ አልበላም</u>፤ <u>ጠላ ጠጣ</u> እንጅ

በዚህ አይነት <u>ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ አልበላም</u> የሚለው እንድ አረፍተ ነገር ወደ አራት አረፍተ ነገሮች ሊተነተን ችሎአል። የትንተናው ውጣረት ትርጉም ሊሆን፣ የዚህም ምንጭ አሳቹ ምዕላድ ነው። ምዕላዱ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ሀረግ ሊያልት ይችላል። ይህ ግን በትንተና የሚነኝ እንጅ ከአረፍተ ነገሩ ቅርፅ የሚታይ አይደለም። ምዕላዱ በግልፅ የሚታየው በግሱ ላይ ብቻ ነው። ይሁን እንጅ፣ የምዕላዱ የዕሌት ሰፋት ወይም መጠን በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙትን ሀረጎች ሊያዳርስና በመጨረሻም ራሱን አረፍተ ነገሩን ሊሸፍን ይችላል። ከዚህም የዕሌት ዳር ድንበር ሊሰፋና ሊጠብ እንደሚችል መረዳት ይቻላል።

ቀደም ሲል በሰ መጠይቅ አረፍተ ነገር ሰንወያይ፣ የመጠይቁ ምዕላድ መዋቅራዊ ግንኙነት ከአረፍተ ነገሩ ጋር አንደሆነ ገልፀን ነበር። በዚያው አካሄድ፣ የዕሌቱ ምዕላድ መዋቅራዊ ዝምድናም አንደዚሁ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው፣ ለማለት ይቻላል። ይህንንም በዕፀ-መዋቅር አንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።




በግልፅ እንደሚታየው፣ የዕሌቱ ምዕሳድ መዋቅራዊ ግንኙነት ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው። የዕሌቱን <u>መጠነ ሰፋት</u> ከግሱ ጀምሮ፣ ወደ ላይ በመውጣት ደረጃ በደረጃ እያሰፋ፣ እስከ አረፍተ ነገሩ መዋቅር ድረስ መሄድ ይቻላል። ጠባቡ የዕሌት መጠን <u>አልበሳም</u> በሚለው ግስ ሲወሰን፣ ከፍተኛው ደግሞ <u>ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበሳም</u> እስከሚለው አረፍተ ነገር ድረስ ይሄዳል። ከዚህም የምንረዳው፣ የአንድን አሉታዊ አረፍተ ነገር ፍች ከንበታዊ ቅርፁ በቀላሉ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ነው። ፍችው በማያሻማ ሁኔታ ሊታወቅ የሚችለው፣ አረፍተ ነገሩ የተነገረበት <u>አውደ ነገር</u> ሲታወቅ ነው። ይህ አስካልሆነ ድረስ፣ አረፍተ ነገሩ በውስጡ ያለውን የህረግ መጠን ያህል ፍችው የተለያየ ሊሆን ይችላል።

ይህን የተለያየ አሉታዊ ፍች በሶስት መንገድ ማግኘት ይቻላል። አንደኛው ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ አይደለም በሚለው አሉታዊ የሁነት ግስ አማካኝነት እገሌ እንጅ፣ እገሌ አይደለም፤ በማለት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንዲታለት የተፈለገውን ሀረግ ከታሀታይ ቦታው እያነሱ፣ እላቹ ምዕላድ ጋር እንዲዋቀር በማደረግ ነው።

(ሀ) ከእናቱ ጋር ምላውን [ካሳ አልበላም] 7
(ለ) ካሳ ምላውን [ከእናቱ ጋር አልበላም]
(መ) ከእናቱ ጋር ካሳ [ምላውን አልበላም]

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ ባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ እና ተሳቢው ሰማዊ ሀረግ የዕሌቱ ምዕላድ ወዳለበት በመጠጋት ሲታለቱ ችለዋል። ሁኔታውን በዕፀ መዋቅር አንደሚከተለው እናሳያለን።



በግልፅ እንደሚታየው፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ በነጠብጣብ ከተመለከተው ታህታይ ቦታው፣ ማለትም ከግሳዊ ሀረጉ (ግሀ2) ውስጥ፣ ተነስቶ እላቹ ምዕላድ ወደሚገኝበት ወደ (እነ') በመሄድ ከምዕላዱ ጋር ተዋቅሮአል። በዚሁ አይነት ሌሎቹም ሀረጎች ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዱ ከልል ሲጠጉ እልት ይሆናሉ። ግሱም እንደዚሁ ወደ እሌቱ ምዕላድ በመሄድ ይታለትና መጀመሪያ <u>አል-በላ</u> ይሆናል። ከዚ የበለጠ ደግሞ ይሸው ዕልት ግስ ወደ ሞይዋ ምዕላድ ይወጣና <u>አልበላም</u> ይሆናል። በዚህም ቦታውን ለቆ ከሄደው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት ይፈጥራል። ይህም ማለት፣ ሁለቱም ከግሳዊ ሀረጉ ወጥተው በእነ' ጥላ ስር ከእላቹ ምዕላድ ጋር ይገናኛሉ ማለት ነው።

ይህ እንግዲህ መዋቅራዊ የሆነው የእሌት ስርዓት ነው። ሌላው ንበታዊ ነው። ይህም ሊታለት የተፈለገውን ሀረግ ከሌሎቹ ለይቶ በጎላ ቅላፄ በመናገር ነው። ይህን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

(ሀ) ካለ ከእናቱ ጋር ምላውን አልበላም 9

(ለ) ካለ ከእናቱ ጋር ምላውን አልበላም

(መ) ካለ ከእናቱ ጋር ምላውን አልበላም

እገዛሩ ያረፈባቸው ሀረጎች ደምቀው (ጎልተው) የሚነገሩት፣ እናም የሚታለቱት ናቸው።

እስካሁን የተመለከትነው /እል-/ በሚለው የእሌት ምዕላድ አማካኝነት የሚገለፀውን እሌት ነው። እንዳየነውም ይህ ምዕላድ በግሀድ የሚታየው፣ በግሱ መነሻ ላይ ነው። ስለዚህም ግሳዊ የእሌት ምዕላድ ልንሰው እንችላለን።

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስማዊ እሌትን እንመለከታለን። የሚከተሉትን ለእብነት እንመልከት።

(ሀ) ብዙ ሀፃናት ያለረዳት (የ-እለ-ረዳት) ያድጋሉ 10
(ለ) ብዙ ለምች ያለትዳር (የ-እለ-ትዳር) ይኖራሉ

በነዚህ ምላሌዎች ውስጥ፣ <u>ያለረዳት</u> እና <u>ያለትዳር</u> የሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው። መስተዋድዱ /የ/ ነው። /እለ-/ የሚለው የስማዊ ሀረግ የእሌት ምዕላድ ነው። መዋቅራዊ ግንኙቱ ከስማዊ ሀረጉ ጋር ነው። /የ/ መስተዋድድ ስመሆንዋ ማለረጃው /ከ/ በሚለው መስተዋድድ ያለምንም የትርጉም ለውጥ ልትተካ መቻልዋ ነው። ይሸውም /ከ-እለ-ረዳት/ በምንልበት ጊዜ ነው። ሁለተኛም ሀረጉ እወንታዊ ሲሆን፣ መስተዋድዱ በቦታው ይገኛል። ይህ ሲሆን 10(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል።

ብዙ ልጆች ቡ-ረዳት ያድጋሉ 11

<u>ቡ-ረዳት</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ሲታለት የ-አለ-ረዳት ወይም <u>አለ-ረዳት</u> ይሆናል። በአወንታዊው መስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ <u>ቡ</u> የነበረው መስተዋድድ፣ በአሉታዊው ሀረግ <u>የ</u> ይሆናል። ባለፈው ክፍል እንደጠቀስነው፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ የተሰያዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎች በስማዊ ሀረግ ውስጥ ሁሉም <u>የ</u> በሚል አቻ መስተዋድድ ይተካሉ።

የእሌቱ ምዕላድ የሚገኘው ከስማዊ ሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ስምላሌ ያህል የሚከተለውን እንመልከት፣

(ሀ) ያለንዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ 12
(ለ) [የ- [አለ- [የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ]]]

ምላሌ 12(ሀ) ላዕላይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ታህታይ አቀማመጡ በ12(ለ) እንደሚታየው ነው። መስተዋድዱ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ <u>የ</u> ነው። ከእሱ ጋር የተዋቀረው አሉታዊ ስማዊ ሀረግ ነው። የእሌቱ ምዕላድ መዋቅራዊ ዝምድና ከስማዊ ሀረጉ ጋር ነው። እገባቡ ደግሞ እንደ መስተዋድዱ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው።

ይህ አንዱ አይነት አገባብ ነው። ሌላው አይነት ቀደም ሲል በግሳዊ እሌት ውስጥ እንዳየነው፣ የእሌቱ ምዕላድ ከሀረጉ መሪ ጋር የሚታይበት ነው። ይህን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት አለ-መሄድ 13

ይህ አረፍተ ነገራዊ ይዘት ያለው የእልት (የታለተ) ስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። የእሌቱ ምዕላድ /አለ-/ የሚታየው የሀረጉ መሪ ከሆነው ከ<u>መሄድ</u> ጋር ነው። ይሁን እንጅ፣ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከእጠቃላዩ ሀረግ ጋር እንጅ ከመሪው ጋር ብቻ እይደለም። ይህም አገባብ በምሳሌ 12(ለ) ከሚታየው አገባብ ጋር የሚቃረን ይመስላል። በምሳሌ 12(ለ) ምዕላዱ ሀረጉን ቀድሞ ከመሰተዓምሩ ጋር ይታያል። በዚህኛው ግን ከሀረጉ መሪ ጋር በሀረጉ መጨረሻ ላይ ይታያል። ጥያቄው ታዲያ፣ የእሌቱ ምዕላድ መሰረታዊ ቦታ የትኛው ነው? የሚል ነው።


በምሳሌ (12) የሚታየው የእሌቱ ምዕላድ አገባብ፣ በምሳሌ (7) እንደሚታየው ባለ ግሳዊ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚታይ አገባብ ነው። ከዚሁ እንግር፣ የምሳሌ (13)ን አቻ ግሳዊ አረፍተ ነገር ብንመለከት፣ የሚከተለውን እንደሚመስል እንረዳለን።

እነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት አል-ሄዱም 14

በዚህና በምሳሌ (13) ውስጥ የሚታየው የእሌቱ ምዕላድ አገባብ አንድ አይነት ነው። ይሁን እንጅ፣ በምሳሌ (12) ከሚታየው አገባብ የተለየ ነው።

ከፍ ሲል የተነሳውን የእሌቱን ምዕላድ የመሰረታዊ አገባብ ጥያቄ በሁለት መንገድ መመለስ ይቻላል። አንደኛው፣ በግሀድ እንደሚታየው፣ መዋቅሮችን ለማዊና ግሳዊ ብሎ በመለየት የእሌቱን አገባብም ከዚሁ ልዩነት ጋር ማያያዝ ነው። መዋቅሩ ስማዊ ሲሆን፣ በመነሻ፣ መዋቅሩ ግሳዊ ሲሆን፣ በመድረሻ ላይ ይገባል ብሎ፣ ልዩነቱን መግለፅ ይቻላል። ይህ ደግሞ የእሌቱ ምዕላድ ሁለት ታህታይ አገባብ አለው እንደ ማለት ነው። ይህም የአገባቡን ሰርዓት አጠቃላይነት ያሳጣዋል። አንድ መዋቅር ሲገኝ የሚችሰው በመሰረቱ በአንድ ታህታይ ቦታ ብቻ ነው። ያን ታህታይ ቦታ አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ሊለቅና በሌላ ቦታ ገብቶ ሊታይ ይችላል።

የእሌቱን ምዕላድ መሰረታዊ ቦታ ለመወሰን ሁለተኛው መንገድ፣ አጠቃላዩን የቁዋንቁዋውን የሀረግ አወቃቀር ሰርዓት፣ ከመሪና ከተመሪ አቀማመጥ አኳዋያ ማየት ነው። ባለፈው ክፍል ሰለ ሀረጎች ሰንወያይ በሰፋት እንደ ተመለከትነው፣ ሀረጎቹ ቀኝ መሪ ናቸው። መሪያቸውን አንዳንድ ጊዜ በግራ የሚያስቀምጡት መስተዋድዳዊና መስተዓምራዊ ሀረጎች ብቻ ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ ይህንን የሚያደርጉት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። በሌሎቹ ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በሀረጉ መድረሻ ላይ ነው። አጠቃላይ ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ የማንኛውም ሀረግ ታህታይ አወቃቀር፣ መሪውን በቀኝ፣ ማለትም በመድረሻ፣ ላይ ያስቀምጣል፣ ብሎ ማጠቃለል እንደሚቻል ገልፀናል። በዚሁ መሰረት፣ በተራ ቁጥር (12)ና (13) የሚታየውን የተሰያየ የእሌት ምዕላድ አገባብ እንደሚከተለው አድርጎ በአንድ ላይ ማቅረብ ይቻላል።



15

[የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት መጂድ]
[የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ]

እነዚህ በቅንፍ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች፣ አረፍተ ነገራዊ ይዘት ያላቸው ስማዊ ሀረጎች ናቸው። መሪዎቹ የተሰመረባቸው ስሞች ናቸው። የሁለቱም ሀረጎች ታህታይ ቦታ ከአሌቱ ምዕላድና ከመሰተዋድዱ በፊት ነው። በተራ ቁጥር 12(ለ) እና (13) የሚታየውን ላዕላይ ቅርፃቸውን የሚይዙት፣ ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዶቹ ቀኝ ጎን ሲሄዱ ነው። የሚሄዱበት ምክንያትም ለመታለት ነው። እካሄዳቸው እንደሚከተለው ነው። መጀመሪያ መሄድ የሚለው ስም ወደ እላቹ ምዕላድ ወደ /አለ-/ ይሄድና አለ-መሄድ ይሆናል። ይህ ደግሞ በተራው ወደ /የ-/ ይሄድና ከጎንዋ ሲለጠፍ የአለመሄድ ይሆናል። ሁለተኛ፣ እነዚያ የሚለው /እለ-/ ወደሚለው አላች ይሄድና ለለ-እነዚያ ይሆናል። ከዚያ በሁዋላ ደግሞ አለእነዚያ የሚለው ወደ /የ-/ ይሄድና የ-እለእነዚያ ይሆናል። ከዚያ በሁዋላ የሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ የሚለው ክፍል እንዳለ ይሄድና በቀኝ በኩል ይሰለፋል[8]።

እስካሁን ያየነው የተራ አሌትን መዋቅራዊ ሰርዓት ነው። ከዚህ ቀጥለን የድርብ አሌትን ሰርዓት እንመለከታለን። የሚከተለውን እንመልከት።


ካሳ ያለገብሰ (የ-አለ-ገብሰ) ጠላ አይጠጣም (አል-ይ-ጠጣም) 16

ይህ ተራ አረፍተ ነገር ነው። ተራ የሚያሰኘው አንድ ግስ፣ ብሎም ግሳዊ ሀረግ፣ ያለው መሆኑ ነው። ይሁን እንጅ፣ ሁለት የአሌት ሀረጎችን ሰለያዘ የአሌት ደረጃው ድርብ ነው። የገብሰ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ /አለ-/ በሚለው ስማዊ የአሌት ምዕላድ፣ ጠጣ የሚለው ግስ ደግሞ /አል-/ በሚለው ግሳዊ የአሌት ምዕላድ ታልተዋል። የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣

ካሳ ያለገብሰ ጠላ ሌላ መጠጥ አይጠጣም 17

የሚል ነው። ሌላ መጠጥ የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ነው። ተሳቢነቱ ለአልቱ ግስ ነው። ያለገብሰ ጠላ የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ፣ የዚህ ስማዊ ሀረግ እንላማሽ ነው። የሁለቱን መዋቅራዊ ዝምድና እና የአረፍተ ነገሩን ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

[8] ዝርዝሩ ብዙ ነው፣ እንቅስቃሴውም በውነቱ ከዚህ የተለየ ነው። ለቀላል አቀራረብ ሲባል ግን በዚሁ እንወስነዋለን። ወደፊት በሌላ ፅሁፍ የተለየና የበለጠ አዋጋቢ የሚመስል ትንተና እናቀርባለን። ለአሁኑ ይህን ውነት ብለን እንቀበል፣ ነገ ውሸት ሊሆን እንደሚችል ተማምነን። ውነት አንፃራዊ ነውና፣ የዛሬ ውነት፣ የነገ ውሸት ነው።



18

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>የገብስ ጠላ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ /አለ-/ በሚለው ስማዊ አላች ምዕላድ ታልቶአል። አልቱ ስማዊ ሀረግ /የ-/ ከሚለው መስተዋድድ ጋር ተዋቅሮአል። ይህ እንደኛው እሌት ሲሆን፣ ሌላው፣ <u>ካላ ያለ ገብስ ጠላ ይጠጣ</u>

የሚለው አረፍተ ነገር ነው። ይህም የታሰተው /አል-/ በሚለው ግሳዊ የዕሌት ምዕላድ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ኢውሱን ተውላጠ ስሞችን ከስማዊና ከግሳዊ የእሌት ምዕላዶች ጋር በመጠቀም የእሌቱን ደረጃ ድርብርብ ማድረግ ይቻላል። ኢውሱን ተውላጠ ስሞች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

ማንም[9]	የትም	የማንም	አንድም	19
ምንም	መቸም	የምንም		

እነዚህ በሙሉ /-ም/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት ከየመጠይቁ ተውላጠ ስምና አንድ ከሚለው ኢውሱን ተውላጠ ስም የተመሰረቱ ናቸው። አገልግሎታቸው በመስተዓምርነት ነው። አነሱ የሚገቡበት አረፍተ ነገርም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ማንም ለማንም ምንም አይሰጥም (አል-ይ-ሰጥ-ም) 20
(ለ)* ማንም ለማንም ምንም ይሰጣል

የኢውሱን ተውላጠ ስሞቹ አገባብ በመስተዓምርነት ነው። የሚታመሩት ስማዊ ሀረጎች ማንነት ከእውደ ነገሩ ሰለሚታወቅ፣ ሊገደፉ ይችላሉ። በሚገደፉበት ጊዜ አረፍተ ነገሮቹ ከላይ የሚታየውን ቅርፅ ይይዛሉ። በማይገደፉበት ጊዜ ደግሞ የአረፍተ ነገሮቹ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል።

ማንም ሰው ለማንም ሰው ምንም ነገር አይሰጥም 21

ከምሳሌዎቹ የምንረዳው ሌላው ነገር፣ ግሳዊ ሀረጎቹ ከኢውሱኖቹ ተውላጠ ስሞች ጋር በእሌት ስምሙ መሆናቸው ነው። ይሁን እንጅ፣ ኢውሱኖቹ ተውላጠ ስሞች በተፈጥሮአቸው አልት አይደሉም። ስለዚህም፣

(ሀ) ካሳ ማንንም ያምናል 22
(ለ) ካሳ ማንንም አያምንም

---

[9] እነዚህ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች እሻሚ ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ፣ ማንም የሚለው በእንግሊዝኛው anyone ወይም no one የሚለውን ኢውሱን ተውላጠ ስም ሊተካ ይችላል። እልት ግስ የሚፈልገው no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ ነው። anyone በሚለው ትርጉሙ ከአወንታዊ ግስ ጋር ሊዋቀር ይችላል። ለምሳሌ፣

ማንም ሊመጣ ይችላል

ግለት ይቻላል። no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ፣

ማንም ሊመጣ አይችልም

ይሆናል። አንድ የሚለው ምዕላድ እንደ እሀዝ የአንድን ነገር መጠን ያመለክታል። እንደ ኢውሱን መስተዓምር ደግሞ የአንድን ነገር ዕምር ወይም ዕውቅ አለመሆን ያመለክታል። ስለዚህም እሻሚ ምዕላድ ነው።

ማለት ይቻላል። ከዚህም እንደ ማንንም ያሉ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች ጥሬ ትርጉም እሻሚ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እሱታዊነቱም ሆነ አወንታዊነቱ በግሱ ላይ የተመሰረተ ነው፤ (ማስታወሻ (9)ን ይመልከቱ።) በዚህም ባህሪያቸው፣ /እስ-/ ብሚሰው የእሌት ምዕላድ አማካኝነት ከሚታሰቱት ስማዊ ሀረጎች ይለያሉ።

ግሳዊ ሀረጉ ከእነዚህ እይነት ተውላጠ ስሞች ጋር ሲዋቀር የግድ እልት ይሆናል። ከሌሎች እልት ስማዊ ሀረጎች ጋር ሊዋቀር ግን፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፤ እልት ላይሆን ይችላል። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

ካሳ ያስትዳር ብዙ ጊዜ ኖሮአል 23

ይህም በእልት ስማዊ ሀረጎችና በኢውሱን ተውላጠ ስሞች መካከል ያወቃቀር ልዩነት እንዳለ ያሳያል። ይህ ልዩነት ግን በተራ አረፍተ ነገር ደረጃ ብቻ የተወሰነ ነው። አረፍተ ነገሩ ውስብስብ ሲሆን፣ ግሱ እልት ላይሆን ይችላል። ይህን ከሚከተለው መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል 24
(ለ) ማንም ወደ እኔ ላይመጣ ይችላል
(ሐ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል
(ሰ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም

ኢውሱን ተውላጠ ስሞች በጥሬ ነገራቸው እሻሚ የሆኑትን ያህል፣ የማያሻማ እልት ትርጉም ያለው አንድ ቃል አለ። እሱም ቀረ የሚለው ግስ ነው። ይህ ግስ የሚገኝበት አረፍተ ነገር ሁሉ እልት ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ልጆቹ መጥተው ቀሩ 25
(ለ) ነጋዴው ከሰሮ ቀረ

እነዚህ ውስብስብ አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው። ውስብስብ ያደረጋቸው ሁለት ግሶችን በውስጣቸው መያዛቸው ነው። አሉታዊ ያደረጋቸው ደግሞ ቀረ የሚለው ግስ /አል-/ የሚለውን የእሌት ምዕላድ በያዘ ሌላ ግስ ሊተካ መቻሉ ነው። ይህ ሲሆን አረፍተ ነገሮቹ እንደሚከተለው ይሆናሉ።

(ሀ) ልጆቹ አልተመለሱም 26
(ለ) ነጋዴው አላተረፈም

ቀረ የሚለው ግስ /አል-/ በሚለው የዕሌት ምዕላድ እንደገና ሊታሰት ይችላል። ይሁን እንጅ፣ ትርጉሙ አሉታዊ ሳይሆን አወንታዊ ነው።

ልጆቹ ወጥተው አልቀሩም 27

የዚህ አረፍተ ነገር ትርጉም <u>ልጆቹ ተመልሰዋል</u> የሚል ነው።

ከፍ ሲል ኢውሱን ተውላጠ ስሞች ከአልት ግስ ጋር እንደሚዋቀሩ ገልፀን ነበር። ይሁን እንጅ <u>ቀረ</u> ከሚለው አልት ግሰ ጋር አይዋቀሩም። የሚዋቀሩት <u>አል-ቀረ</u> ከሚለው ድርብ አልት ግስ ጋር ነው። የሚከተለውን እንመልከት።

(ሀ) *ማንም ለምሳ ቀረ 28
(ለ) ማንም ለምሳ አልቀረም

የምሳሌ (ሀ) ተቀባይነት ማጣት የሚያሳየው፣ የኢውሱኖቹ ተውላጠ ሰሞች ስምሙነት በተፈጥሮው አልት ከሆነ ግለ ጋር ሳይሆን፣ በ/አል-/ አማካኝነት ከታለፉ ግሰ ጋር እንደሆነ የሚያሳይ ይመስላል።

እስካሁን የተመለከትነው ህገኛ ሊባል የሚችለውን የአሌት ስርዓት ነው። ከዚህ ለየት የሚለው የሁነትና የኑረት ግሶች ባህሪ ነው። ግሶቹ አሌትን የሚያሳዩት በ/አል-/ አማካኝነት ሳይሆን፣ ቅርፃቸውን በመለወጥ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ጎበዝ ነው 29
(ለ) ካሳ ጎበዝ አይደለም
(መ) *ካሳ ጎበዝ አልነውም

<u>ነው</u> የሚለው የሁነት ግስ ነው። አሉታዊ ቅርፁ <u>አይደለም</u> እንጅ፣ <u>አልነውም</u> አይደለም። <u>አልነውም</u> የሚለው ቅርፅ ለምን ተቀባይነትን ሊያጣ ቻለ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል። ወደ መልሱ ከመሄዳችን በፊት የኑረት ግሰን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ቤት ውሰጥ አለ 30
(ለ) ካሳ ቤት ውስጥ የለም
(መ) *ካሳ ቤት ውስጥ አል-አለ-ም

<u>ነው</u> የሚለው የሁነት ግስ ከድርጊትም ሆነ ከባህሪ ግሶች የተለየ ነው። የሚለየውም በቅርፁና ከዚህም ጋር በሚያያዘው በርባታ ደረጃው ነው። ቅርፁ /ነ-/ በሚለው አንድ ተናባቢ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም ከሶስት ተናባቢዎች ከሚመሰረቱ ሌሎች ግሶች ይለያል። ሁለተኛም /ነ-/ ምንም ትርጉም የለውም። ትርጉም የሚያገኘው እሱን ተከትለው ከሚገቡ የርባታ ምዕላዶች ብቻ ነው። እነዚህም ቢሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው፣ የባለቤት አይደሉም። የተሳቢ አፀፋ የሚታየው በመሰረቱ በሳቢ ግስ ላይ ነው። ከዚህ በመነሳት /ነ-/ የርባታ ምዕላድ ለመሸከም ብቻ የሚገባ ትርጉም-የለሽ ቅርፅ ወይም ምዕላድ እንጅ፣ ግሰ አይደለም ለማለት ይቻላል። ምናልባትም የርባታ ምዕላዶቹ የተሳቢ አፀፋ የሆኑት ምዕላዱ መደበኛ ባለትርጉም ግሰ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል።

<u>የለም</u> የሚለው እልት ግስ መሰረት <u>አል</u> የሚለው የኑረት ግስ ነው። የአሌት ምዕላዱ የግዕዙ /ኢ-/ እንጅ የአማርኛው /አል-/ አይደለም የሚሉ አሉ። ስለዚህም ታህታይ ቅርፁ /ኢ-አለ-ም/ ሲሆን፣ /ኢ-/ ወደ /ይ-/ ትለወጥና፣ ቅርፁ /ይ-አለ-ም/ የሚል ይሆናል። ጉዳዩ <u>በይነ-ልሳናዊ</u> የሆነ ጠለቅ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ፣ እዚህ ላይ የምንጨምረው የለም። በጥቅሉ የኑረትና የሁነት ግሶች ሰርዓት ከሌሎቹ የተለየ ነው፣ ብለን እናልፈዋለን።

ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተቱት አረፍተ ነገሮች ሀተታን የሚያትቱ፣ ጥያቄን የሚጠይቁ ወይም ሀሳብን የሚያልቱ ሳይሆኑ፣ ትእዛዝን የሚሰጡ ናቸው። ቀደም ባለው ጊዜ ትዕዛዝ እንቀፅ በመባል ይታወቁ ነበር። የትዕዛዝን ባር የሚያሳዩ እንደግለት ነው። እኛ ግን ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ልንላቸው እንችላለን። ትዕዛዝን የሚያሳዩት አረፍተ ነገራዊ ቅርፅና ይዘት ያላቸው የመዋቅር አይነት ናቸውና። ይሁኑ እንጅ፣ ከሌሎቹ አረፍተ ነገሮች የሚለዩበት ባህሪያት ስላሉዋቸው፣ እነሱን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመረምራለን።

መዋቅራዊ ባህሪያቸው የተወሰነ፣ ግለትም የታመረ ባለቤት የሚፈልጉ መሆናቸው ነው። ይሁን እንጅ፣ ባለቤታቸው ማንኛውም እምር ስማዊ ሀረግ ሳይሆን፣ በዋናነት የሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ብቻ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ጠጅ አምጣ! 1
(ለ) ወጥ አውጪ!

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ባለቤት <u>አንተ</u> የሚለው ተውላጠ ስም ሲሆን፣ የሁለተኛው ደግሞ <u>አንቺ</u> የሚለው እንሰታይ ተውላጠ ስም ነው። ይህ ለመሆኑ ማሰረጃዎች አሉ። አንደኛውና ዋናው ሰዋሰዋዊ ሲሆን፣ ከዚሁ ላይ የሚመሰረተውና ሁለተኛው ማሰረጃ ንግግራዊ ነው። ሰዋሰዋዊውን በሚመለከት፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደሚከተለው ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

(ሀ) እንተ ጠጅ አምጣ! 2
(ለ) አንቺ ወጥ አውጪ /አውጥ-ኢ/

ከላይ ያለባለቤት የሚታዩት እረፍተ ነገሮች እዚህ ላይ ከነባለቤታቸው ይታያሉ። ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ መሆኑ በግህድ ይታያል። በተጨማሪም በሁለተኛው ምሳሌ ግስ መድረሻ ላይ የምትገኘው /-ኢ/፣ በክፍል ሁለት ሰለያታ ስንወያይ እንደገለፅነው፣ የሁለተኛ መደብ አንስታይ ያታ ምዕላድ ነች።

እነዚህ እንግዲህ ሰዋሰዋዊ ማሰረጃ ያልናቸው ሲሆኑ፣ ንግግራዊ ማሰረጃ የምንለው ደግሞ እነዚህን አረፍተ ነገሮች በሚናገረውና በሚነገረው ሰው መካከል

ባለው ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ነው። ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች አንድ ተናጋሪ ካጠገቡ ለሚገኝ አንድ ሌላ ሰው በትዕዛዛዊ ቅላፄ የሚነገሩ ናቸው። ካሁን በፊት እንደገለፅነው፣ ተናጋሪው አንደኛ መደብ ይባላል፤ ንግግር ጀማሪ ነው። ከዚህ አንፃር ተነጋሪው ሁለተኛ መደብ ይባላል፤ የነገሩ መድረሻ ነው። ተናጋሪንና ተነጋሪን የሚታዘብ ሌላ ሰው ካለ፤ ያ ሰው ሶስተኛ መደብ አንደሚባል ቀደም ሲል ተገልያለል። ከዚህ ንግግራዊ አውድ አኳያ ሲታይ፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባለቤት ሁለተኛ መደብ መሆኑ ግልፅ ነው። በአረፍተ ነገር ላይ በግሀድ የማይታየውም ለዚህ ነው፣ ዕውቅ ለለሆነ።

የማይገደፈው በአፅንያት ሲነገር ብቻ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ተው! 3
(ለ) እንተ ተው!

የመጀመሪያው መደበኛ ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን መደበኛ ብቻ ሳይሆን፣ ማስጠንቀቂያም ጭምር ነው። 'ተው ይህ ነገር አያዋጣህም' የሚል አይነት ነው። ስለዚህም አሰጠንቃቂ ትዕዛዝ ልንለው አንችላለን። ከዚህ ካለፈም አረፍተ ነገሩ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል።

(አንተ) ተው ብየሃለሁ! 4

ይህ ትዕግስቱን የጨረሰ ሰው የሚናገረው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው። ከትዕዛዝ ደረጃ ያለፈ የዛቻ አነጋገር ነው።

ሁኔታው ትዕዛዝ የተለያየ ተግባር፣ አይነትና ደረጃ እንዳለውና፣ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችም በዚሁ ላይ የሚመሰረት የተለያየ ቅርፅ ሲኖራቸው እንደሚችሉ ያሳያል[10]። እሁንም የሚከተሉትን አናነፃፅር።

(ሀ) ልብሱን እጠቡ-ው /-ኡ/ 5
(ለ) ልብሱን እጠብ
(መ) ልብስ እጠብ

ከነዚህ ምሳሌዎች መካከል የሚታይ የቅርፅ ልዩነት አለ። የመጀመሪያው ምሳሌ ዕምር ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው። የዚሁ ሀረግ አፀፋ የሆነችው /-ኡ/ም በግሱ መድረሻ ላይ ትታያለች። በሁለተኛው ምሳሌ ግን አፀፋዋ አትታይም። በሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ ዕምር አይደለም። ስላልሆነም በግሱ ላይ በአፀፋ አልተጠቀሰም። ከነዚህ የቅርፅ ልዩነቶች የመነጨ የሚመስል የትዕዛዝ ልዩነትም ያለ ይመሰላል። ይኸውም የመጀመሪያው ምሳሌ ለስለሰ ያለ ትዕዛዝን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከዚህ ከረር ያለ ትዕዛዝን

[10] በዚህ ጉዳይ ላይ ሀይሉ (1980)ን ይመልከቱ።

የሚያመለክት ይመስላል። ሶስተኛው ከሁሉም የበለጠ የትዕዛዝ መንፈስ ያለበት ይመስላል። ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ዕምርነት የመደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባህሪ ያለመሆኑን ነው። ዕምር ስማዊ ሀረግ ያለበት ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ከትዕዛዛዊነት ይልቅ ወደ ማሳሳቢያነት የሚያዘነብል ይመስላል።

የሚከተሰውን ደግሞ እንመልከት።

(ሀ) ብላ! 6
(ለ) በል ብላ!
(መ) በል ብላት!

አንድ ምግብ አልበላም አያለ የሚያሰቸግርን ልጅ ብናሰብ፣ የአነዚህን ምሳሌዎች አግባብነት በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን። የመጀመሪያው ተራ ትዕዛዝ ነው። ሁለተኛው ወላጅ ከልጁ አጠገብ ቁሞ ከዛቻ ጋር የሚሰጠው ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሶስተኛው ከዛቻ ያለፈ ሀይል የሚታይበት ትዕዛዝ ነው። ልጁ አንድም አየተመታ፣ አለያም ከተመታ በሁዋላ ምግቡን እያለቀሰ የሚበላበት ሁኔታ ነው። በሶስተኛው ምሳሌ መጨረሻ ላይ የምትታየው /-አት/ ይህን ሁኔታ የምታመለክት ምዕላድ ነች። በቅርፅዋ የሶስተኛ መደብ አንስታይ ያታ፣ የተሳቢ አፀፋ ትመሰላለች። ግን አይደለችም። ብትሆን ኖሮ፣ በሳቢ ግለ ላይ ብቻ ትገኝ ነበር። የሚከተሰውን እንመልከት።

(ሀ) በል ተኛት 7
(ለ) በል ሂዳት

<u>ተኛ</u> እና <u>ሂድ</u> የሚሉት ኢሳቢ ግሶች ሰለሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋ ሊይዙ አይችሉም። ለለዚህም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ /-አት/ በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተሳቢ አፀፋ ሳትሆን፣ የዱላ ቀረሽ ትዕዛዝ ምልክት ነች። የዛቻ ምዕላድ ልንላት እንችላለን። ሰምሳሌ፣ አንድ ልጅ አልታዘዝም ብሎ አየሮጠ ቢሄድ፣ ከአዛዡ በኩል፣

(ሀ) ቆይ ትመጣለህ! 8

ወይም

(ለ) ቆይ ትመጣታለህ! (ት-መጥ-አት-አለህ)

የሚል ዛቻ ይደርሰበታል። የመጀመሪያው ተራ ዛቻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከዚያ የከፋ ነው። /-አት/ ም የምትገኘው በዚሁ በሁለተኛው ምሳሌ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር የሚነገረው አዛዥ ወይም ገላጭ በሆነ ቅላፄ ነው። በመደበኛ የንግግር ቅላፄ ከተነገረ፣ ትዕዛዛዊ መሆኑ ይቀርና ፈቃጅ፣ ጋባዥ ወይም ተለማማጭ ይሆናል። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ጠጣ 9
(ለ) በል ጠጣ
(መ) በል ጠጣት
(ሰ) ትጠጣት

ቅላፄአቸው ካልታወቀ በስተቀር፣ አንደነዚህ ያሉ አባባሎችን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ በማየት ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው ብሎ ለመደምደም አይቻልም። ትዕዛዛዊ የሚሆኑት፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ በትዕዛዛዊ ቅላፄ ሲነገሩ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ ፈቃድን፣ ግብግን፣ ቁልምጫን፣ ወዘተ፣ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ከዚህ አኳር ሲታይ፣ የመጀመሪያው ምሳሌ፣ 'ጠላ ልጠጣ?' ብሎ ሰሚጠይቅ ልጅ የሚሰጥ ፈቃድ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ አልጠጣም እያለ ለሚያደረደር ተጋባኝ የሚነገር የግብግ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ሶስተኛው፣ 'ጠጣ አንጅ! ይቺ ደግሞ ምን አላት?' እያለ የሚጋብዝ ወይም የሚያባብል ነው። የመጨረሻውም ተጋባዡ በትዕዛዝ ሳይሆን፣ በፈቃደኛነት አንዲጠጣ የሚጠይቅ ነው። ቅርፁም የካልዓይ አንቀፅ ነው።

ሁኔታው አረፍተ ነገሮችን በሚታዩበት መልካቸው ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው፣ ለማለት እንደማይቻል ያሰገነዝባል። ትዕዛዛዊነታቸው በውል የሚታወቀው፣ ሲታዩ ሳይሆን፣ ሲባሉና በጆሮ ሲሰሙ ብቻ ነው። ባጭሩ ትዕዛዛዊነት መዋቅራዊ ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ጭምር ነው።

እሰካሁን ያየነው እንድ ሰው አንድን ሌላ ሰው ሊያዝ የሚጠቀምበትን የአረፍተ ነገር አይነት ነው። ትዕዛዙ አዛዥና ታዛዥ ፊት-ለፊት ሲገናኙ የሚሰጥ ነው። ከዚህ ለየት የሚለው ትዕዛዝ ደግሞ አዛዥ ትዕዛዙን ለታዛዡ ፊት-ለፊት ሳይሆን፣ በመልክተኛ፣ ማለትም በሶስተኛ ሰው በኩል የሚያስተላልፍበት ሁኔታ ነው። ይህም አንደሚከተለው ነው።

(ሀ) ልብሰ ትጠብ 10
(ሰ) አንጨት ትሰበር
(መ) አንጀራ ትጋግር


እንደነዚህ ያሉት ኢርቱዕ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች ሊባሉ ይችላሉ። አንድን ትዕዛዝ በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ የሚያስተላልፉ ናቸውና። ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ ሳይሆን፣ ሶስተኛ ነው። ስለሆነም ከነባለቤታቸው አንደሚከተሰው ሆነው ሊነገሩ ይቻላሉ።

(ሀ) አሰቴር ልብሰ ትጠብ 11
(ሰ) አያልነሽ አንጨት ትሰበር

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ትዕዛዝን ብቻ ሳይሆን፣ ፈቃድንም ሊያሳዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው 'አለቴር ወደ ትምህርት ቤት ትሂድ ወይ?' ተብሎ ቢጠየቅና፣

ትሂድ 12

ቢል፣ መልሱ የፈቃድ እንጅ፣ የትዕዛዝ አይሆንም። ይህም የሚያመለክተው፣ ቀደም ሲል እንደተነገረው፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነሮችን የአሻሚነት ባህሪ ነው። ትዕዛዝን ወይም ፈቃድን ሊያመለክቱ ይችላሉ። ከሁለቱ የትኛውን እንደሚያመለክቱ በውል የሚታወቀው በሚነገሩበት ቅላፄ ብቻ ነው። የትዕዛዝ ቅላፄ ከፈቃድ፣ ከመጠይቅ፣ ከእሌት እንዲሁም ከሀተታ ቅላፄ የተለየ ነው[11]። እንደዚያም ሆኖ፣ መዋቅራዊ ቅርፁን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።



በዚህ ክፍል ለንወያይ የቆየነው ለለ ተራ አረፍተ ነገሮች ያወቃቀር ስርዓትና ተግባር ነው። ተራ አረፍተ ነገሮች አንድ ግላዊ ሀረግ ብቻ ያላቸው ናቸው። ተግባራቸው ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ አሉታዊና ትዕዛዛዊ ነው። የአንዱ አወቃቀር ከሌላው የተለየ ባህሪ አለው። በሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሁነትን፣ የኑረትን፣ የነቢርና የተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መዋቅራዊ ባህሪ አይተናል።

የገቢር አረፍተ ነገር ባለቤት አድራጊ ወይም ገባሪ እንደሆነና ተገባሪ ስማዊ ሀረግ ሊኖረው እንደሚችል ገልፀናል። የተገብሮ አረፍተ ነገሮች ግስ ሳቢ የሆነ አቻ ግስ እንዳለውና ባለቤቱም ተደራጊ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ አይተናል። የተገብሮነት ምልክት የሆነችው ምዕላድም /ተ-/ እንደሆነችና አሰዋም በጥቅሉ *ማዕከላይ* ድርጊትን ከምታመለክተው ከሌላዋ /ተ-/ በአገባብዋ የተለየች እንደሆነች ገልፀናል። በጥቅሉ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብሎ በመክፈል፣ የድርጊቶቹን ደግሞ ገቢር፣ ማዕካላይና ተገብሮ ብሎ መለየት እንደሚቻል ተገንዝበናል። በመጠይቅ አረፍተ ነገር ውስጥ የተራን፣ የድርብንና የድርብርብ መጠይቅን መዋቅራዊ ሁኔታ ተመልክተናል። የመጠይቅ ምዕላዶች <u>አንዴና</u> <u>ወይ</u> እንደሆኑ፣ መጠይቅ ተውላጠ ስሞችም ለጥያቄ መነሻ በሚሆነው ሀረግ መሰረታዊ ቦታ ላይ እንደሚገቡ አይተናል። ጥያቄዎቹ ተራ ድርብና ድርብርብ ሊሆኑ እንደሚችሉም ተገንዝበናል። አሉታዊ አረፍተ ነገሮችም /አል-/ እና /አለ-/ በሚሉት ምዕላዶች አማካኝነት እንደሚመሰረቱ አይተናል። በአይነታቸውም ተራ፣ ድርብና ድርብርብ አሌትን ሊያሳዩ እንደሚችሉ አይተናል። ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችን በሚመለከት በግሰ ቅርፅ፣ በባለቤት ባህሪና በቅላፄ ሊለዩ እንደሚችሉ ተገንዝበናል። ከመዋቅር አልፈን አሰከ ትርጉም ድረሰ በመሄድ የተግባራቸውን አሻሚነትና ይህንንም አሻሚነት ለመፍታት ቅላፄ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልፀናል። በሁሉም አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግ አፀፋውን በግሱ አምድ ላይ የግድ ማሳየት እንዳለበትና በታህታይ መዋቅር ውስጥም ከሁሉም ሀረጎች ቀድሞና ከፍ ብሎ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ገልፀናል። ተሳቢ ስማዊ ሀረግም ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ ሊሆን እንደሚችልና በግሱ ላይም ከባለቤቱ አፀፋ ቀጥሎ በራሱ አፀፋ ሊጠቀስ እንደሚችል አይተናል። መስተዋድዳዊ ሀረጎችም እንደዚሁ በግሱ ላይ /ለ-/ ወይም /በ-/ በሚል መስተዋድድና በተሳቢ አፀፋ ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ተረድተናል። ግሱ ሊይዝ የሚችለው የባለቤትን፣ የርቱዕን እና የኢርቱዕን ወይም የመስተዋድድ ሀረግን አፀፋ ብቻ እንደሆነም ተግንዝበናል። በዚህም የተራ አረፍተ ነገሮችን ውይይት አንቁዋጫለን።

መልመጃ

1. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ትንታኔ በዕፀ-መዋቅር ያመልክቱ።

   (ሀ) ልጁ አስቴርን በጣም ተቀየማት።
   (ለ) ልጁ ተገረፈ።

[1] ዝርዝሩን ከዓለማየሁ (1988) ይመልከቱ

2. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተቀባይነት ሰምን አጠራጣሪ እንደሆነ ምክንያቱን ይግለፁ። ተቀባይነት እንዲያገኙ አድርገው ያዋቅሩአቸው።

   (ሀ) ? እሾህ አሰቱርን ወጋት።
   (ለ) ? ገነት አሰቱርን ወለደችባት

3. የሚከተለውን አረፍተ ነገር ተንትነው በዕፀ-መዋቅር ያሳዩ።

   ልጆቹ ምሳ አልበሉም እንዴ?

4. "እንኩዋን ለብርሃነ መሰቀሉ አደረሰህ" የሚለው አረፍተ ነገር ተግባር ምን እንደሆነ ይግለፁ። የዚህን አረፍተ ነገር ባለቤት ይግለፁ።

5. የአንድን አረፍተ ነገር ባለቤት ያለጥርጠር ማወቅ የሚቻለው በስነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ብቻ ነው። ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ።

6. "ከዚህ ጥፉ!" የሚለው መዋቅር ተግባር ምንድን ነው። ባለቤቱ በምን ይታወቃል።

7. የሚከተሉት መዋቅሮች ትርጉም አንድ አይነት ነው። ቅርፃቸው ለምን እንደተለያየ ያስረዱ።

   (ሀ) የካሳ መፅሀፍ ንባብ
   (ለ) ካሳ መፅሀፍ አነበበ
   (መ) ካሳ መፅሀፍ ማንበቡ

8. <u>ልጆቹን ጉንፋን ያዛቸው</u> የሚሰው ሁተታዊ አረፍተ ነገር ባለቤት ማን ነው? እንዴት?

9. አይነተኛ የተገብሮ ምዕላድ መለያ ምንድን ነው?

10. <u>ካሳን ደከመው</u> በሚለው አረፍተ ነገርና <u>ካሳ ደከመ</u> በሚለው አረፍተ ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዱ።

ውስብስብ አረፍተ ነገር

ውስብስብ ሀተታዊ አረፍተ ነገር

ባለፈው ክፍል ስለተራ አረፍተ ነገሮች አይነት፣ ሰርዓትና ተግባር ተወያይተናል። ተራ አረፍተ ነገሮች ከተራ ሰማዊና ግሳዊ ሀረግ ይዋቀራሉ። ተራ ሀረጎች ደግሞ ከተራ መሪ፣ ከሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽና መስተዓምር ይዋቀራሉ። ዝርዝር ሁኔታውን ቀደም ሲል ስለተለያዩ ሀረጎች ሰንወያይ ተመልክተነዋል። ለምሳሌ፣ አንድ ሳቢ ግስ ከመሙሊያ ሰማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረጉን አንደሚፈጥር፣ ያ ንዑስ ሀረግ ደግሞ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተቀናጅቶ አቢይ ሀረጉን አንደሚመሰርት፣ አቢይ ሀረጉም ከተለያዩ መሰተዓምሮች ጋር በመዋቀር ዋናውን አቢይ ሀረግ አንደማያዋቅር አይተናል። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠር ሀረግ ተራ ሀረግ ሲባል፣ ከዚህ አይነት ሀረግ የሚፈጠር አረፍተ ነገርም አንደዚሁ ተራ አረፍተ ነገር ይባላል። ተግባሩም ተራ ሀሳብን መግለፅ፣ መጠየቅ፣ ማለት (አሌ ማለት)፣ ወዘተ፣ ነው።

አንድ አረፍተ ነገር ተራ ካልሆነ ውስብስብ ነው። አንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ደግሞ ከውስብስብ ሀረጎች የሚፈጠር ሰፈ መዋቅር ነው። ውስብስብ ሀረጎች በውስጣቸው ተራ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ አረፍተ ነገራዊ የሆነ መሙሊያ አና/ወይም አጎላማሽ አላቸው። አረፍተ ነገራዊው መሙሊያ ወይም አጎላማሽ ከግሳዊ ወይም ከሰማዊ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀር፣ ከዚህ አይነት ግሳዊ ወይም ሰማዊ ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም አንደዚሁ ውስብስብ ይሆናል። ተግባሩም አንደዚያው።

የዚህ አይነት ግሳዊና ስማዊ ሀረጎች ያሉዋቸውን አረፍተ ነገሮች ሰርዓት ከዚህ ቀጥሰን አንድ በአንድ እንመረምራለን። ከዚያ በፊት ግን በሀረግ ውሰጥ ስለሚገኙ አረፍተ ነገሮች አንድ ነገር ማንሳት አለብን። ይኸውም አረፍተ ነገሮቹ ግሳዊና ስማዊ ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ነው። ግሳዊ የሚባሉት ግሳዊ ሀረግ ያላቸው ሲሆኑ፣ ሰማዊ የሚባሉት ደግሞ በግሳዊ ሀረግ ፋንታ ሰማዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን።

(ሀ)	አሰቴር [በሩን ከፈተችው] (ከፈተ-ች-ው)	1
(ለ)	አሰቴር [በሩን መክፈትዋ] (መክፈት-አ-አ)	
(መ)	የአሰቴር [በሩን መክፈት]	
(ሰ)	--------- [በሩን መክፈት]	

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ ግሳዊ አረፍተ ነገር ነው። ግሳዊ ሀረጉ በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ሲሆን፣ የዚህ ሀረግ መሪ ደግሞ [ከፈተ-ች-ው] የሚለው ሳቢ ግስ ነው። ግሱ የባለቤቱንና የተሳቢውን አፀፋ ያሳያል። በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ [በሩን መከፈትዋ] የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። የሀረጉ መሪ [መከፈትዋ] የሚለው የድርጊት ስም ነው። አርዕሰት እንደሚባል በምሰረታው ንዑስ ክፍል ተገልያአል። ይህም መሪ [-ዋ] < /ኡ-ኣ/ የምትለዋን ድርብ ምዕላድ አስከትሉአል። ይህች ምዕላድ በግሱ ላይ ከምትታየው የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ[-ች] < /-ት-ኣ/፣ ጋር በግብር አንድ ነች። ባለቤትን ትጠቁማለችና። በሁለቱ አፀፋዎች መካከል ያለው ልዩነት የቅርፅ ብቻ ነው። ይህም ልዩነት የመጣው አፀፋዎቹ ከተቀጠሉባቸው ቃላት ከፍል ልዩነት ነው። ቃላቱ ግሳዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ች] ትሆናለች። ቃላቱ ስማዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ዋ] ትሆናለች። ሁለተኛም ግሳዊ አረፍተ ነገር የባለቤትን ብቻ ሳይሆን፣ የተሳቢ አፀፋንም ሊያሳይ ይችላል። ስለንግሩ ስማዊ አረፍተ ነገር የተሳቢ አፀፋን አያሳይም። ከዚያም አልፎ ከምሳሌ (መ) እንደምንረዳው የባለቤት አፀፋንም ሳያሳይ ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ባለቤቱ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ በመነሻው ላይ ያሳያል፤ አለያም በምሳሌ (ረ) እንደሚታየው በግሀድ ከመታየት ይታቀባል።

በአጠቃላይ በአፀፋ የሚጠቀስ ሀረግ በግሀድ ላይከሰት ይችላል። ከአፀፋው ቅርፅ የየሀረጉን መደብ፣ ቁጥር ወይም ፆታ በማወቅ ይቻላል። ለምሳሌ፣ ምሳሌ 1(ሀ) እና (ለ)ን እንደሚከተለው ለማለት ይቻላል።

(ሀ) ----- [----- ከፈተቸው] (ከፈተ-ች-ው) 2
(ለ) ----- [በሩን መከፈትዋ] (መከፈት-ዋ)

በምሳሌ (ሀ) የባለቤቱና የተሳቢው ሀረግ፣ በምሳሌ (ለ) የባለቤቱ ሀረግ ብቻ ተገድፈዋል። ሰለ ስማዊና ግሳዊ አረፍተ ነገር ይህን ያህል ካልን፣ አሁን አረፍተ ነገሮቹ ወደሚገኙባቸው ሀረጎች እንመለስና መዋቅራዊ ባህሪያቸውን እንይ። ከስማዊ ሀረጎች እንጀምራለን።

ውስብስብ ስማዊ ሀረግ

ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች በውስጣቸው መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ አረፍተ ነገር አላቸው። የሁሉንም ዓይነት አረፍተ ነገሮች አገባብ ከዚህ ቀጥሎን በየተራ እንመለከታለን።

(ሀ) መሙሊያ አረፍተ ነገር


መሙሊያ አረፍተ ነገሮች የሚባሉት፣ በአንድ ስማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ከመሪው ስም ጋር አየተዋቀሩ ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሚመሰርቱና የመሪውን ስም ይዘትም ሙሉ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

[[የካሳ ቤት የመሰራት] ዓላማ] 3

ይህ ስማዊ ሀረግ ነው። የሀረጉ መሪ [ዓላማ] የሚለው ስም ነው። ይህ መሪ [የካሳ ቤት የመሰራት] ከሚለው መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ [የካሳ ቤት የመሰራት ዓላማ] የሚል ሰፊ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል።

[የካሳ ቤት የመሰራት] የሚለው መዋቅር ስማዊ አረፍተ ነገር ነው። አገባቡም <u>ዓላማ</u> ለሚለው መሪ ስም መሙሊያ ሆኖ ነው። ያለ መሙሊያው መሪው ስም ብቻ ሙሉ ሀሳብ አይሰጥም። የምን ዓላማ? የሚል አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል። ጥያቄው እንዳይነሳ ከፈለግን፣ የዓላማውን ይዘት መግለፅ ይኖርብናል። ይዘቱ የሚገለፀው በአረፍተ ነገር ስለሆነ፣ አረፍተ ነገሩ የመሪው ስም መሙሊያ ነው። ከመሪው ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ነው።

4




በግልፅ እንደሚታየው፣ [የካሳ ቤት የመሰራት] የሚለው ሰማዊ አረፍተ ነገር ከንዑሱ ሰማዊ ሀረግ (ሰሀ1) አንጉዋ በመውረድ ዓላማ ከሚለው መሪ ሰም ቀድሞ ገብቶአል። ይህ የመሙሊያዎች አይነተኛ አገባብ ነው። ግንኙነታቸው በቀጥታ ከመሪው ሰም ጋር ነው።

መሙሊያው አረፍተ ነገር የካሳ ከሚለው ባለቤትና ቤት መሰራት ከሚለው ሰማዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው። የካሳ በሚለው ሰም መነሻ ላይ የምትታየው /የ/ ካሳ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት መሆኑን የምታመለክት ምዕላድ ነች። አፀፋ ግን አይደለችም። ያለአሰዋ ካሳ የሚሰው ሰም ባለቤት መሆኑ አይታወቅም። ምክንያቱም መሰራት በሚለው መሪ ሰም ላይ ካሳን የሚጠቁም አፀፋ የለምና። በአፀፋ ያልተጠቀሰ የሰማዊ አረፍተ ነገር ባለቤት፣ አንድም ከላይ እንደሚታየው /የ/ን ያስቀድማል፣ አለያም ከቦታው ይጠፋል። ከላይ የሚታየው ሁኔታ ባለቤቱ /የ/ን አስቀድሞ በግሀድ ሲከሰት የሚያሳይ ነው። /የ/ን ባለማስቀደሙ ከቦታው ሲጠፋ ደግሞ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል።

[--- ቤት መሰራት] 5

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በሰረዝ የተመለከተው ነው። መሰራት የሚለው መሪ ላይ በአፀፋ ሰላልተጠቀሰ፣ ግንኑቱ አይታወቅም። ግንኑቱ ሰንል፣ መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው ግለታችን ነው።

ሌላው ልንገነዘበው የሚገባ ነገር [ቤት የመሰራት] በሚለው ሀረግ ውስጥ፣ መሰራት በሚለው መሪ ሰም መነሻ ላይ የምትታየውን /የ/ን ይመለከታል። ይህች /የ/ ሰማዊ አረፍተ ነገሩ ነፃ ሳይሆን፣ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን የምታመለክት ምዕላድ ነች። ጥገኝነቱም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ዓላማ ለሚለው ለሰማዊ ሀረጉ መሪ ነው። ለለዚህም ቀደም ሲል ካየናት ባለቤት አመልካች /የ/ በተግባርም ሆነ በአገባብ ትለያለች። ይህችኛዋ /የ/ ጥገኝነትን አመልካች ለትሆን፣ ያችኛዋ /የ/ ባለቤትነትን አመልካች ነች። ይህችኛዋ /የ/ በሳዕላይ መዋቅር ውስጥ፣ ከአረፍተ ነገሩ መሪ ሰም ቀድማ ለትገባ፣ ያችኛዋ /የ/ ከአረፍተ ነገሩ ባለቤት ቀድማ ትገባለች። የዚችኛዋ /የ/ መሰረታዊ አገባብ ጥገኛ ከሆነው አረፍተ ነገር ጋር ነው። ጥገኛው አረፍተ ነገር በሞይነት የገባ መሆኑን ለለምታመለክት ምደ ልንላት ችለናል። አረፍተ ነገሩንም ተሞይ ልንለው እንችላለን። መሙሊያው የጥገኛው አረፍተ ነገርና የሞይዋ ቅንጅት ሲሆን፣ አቀነጃጀቱንም እንደሚከተለው በዕፀ - መዋቅር እናሳያለን።



ይህ አንግዲህ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር ነው። አረፍተ ነገሩ ጥገኛ ሆኖ በመሙሊያነት የገባ መሆኑን ከምታሳየው ከ/የ/ ጋር የተዋቀረ ስለሆነ፣ ይዘቱ ከመደበኛ፣ ግለትም ጥገኛ ካልሆነ፣ አረፍተ ነገር ይዘት የሰፋ ነው። ይህን ሰፊ መዋቅር (አነ) በሚል <u>ምህፃር</u> እናመለክታለን። እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ሊተነተን፣ ከላይ እንደሚታየው፣ አረፍተ ነገር (አነ) እና ሞይ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የሞዩ ቦታ በግልፅ እንደሚታየው ከመሙሊያው አረፍተ ነገር በስተቀኝ ነው። /የ/ <u>መስራት</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር የሚተናጀው በላዕላይ መዋቅር፣ ግለትም በንግግር ደረጃ ነው። /የ/ ራስዋን ችላ መቆም የማትችል ምዕላድ ስለሆነች፣ ደጋፊ ያስፈልጋታል። ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ደረጃ፣ አጠገብዋ ከሚገኘው፣ መስራት ከሚለው መሪ ስም መነሻ ላይ ልትለጠፍ ችላለች። ይህን ስታደርግም መስራት የነበረው መሪ ስም ቅርፁን ለውጦ <u>የመስራት</u> ይሆናል። ካሁን በፊት፣ በእለታዊ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ግሱ ወደ አሌቱ ምዕላድ ሲሄድ አይተን ነበር። የአሁኑም <u>መስራት</u> የሚለው መሪ እካሄድ አንደዚያው አይነት መሆኑን እናስተውል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም የሞይዋ ታህታይ ቦታ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ስመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው። ስዚህ ሁስት ማስረጃዎች አሉ። አንደኛው ትውረታዊ ነው። ሞዮች የአረፍተ ነገር መሪ ናቸው ስማለት ይቻላል። አንድ አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በአነሱ አማካኝነት ነውና። አንድ መሪ ግሳዊ፣ ስማዊ፣ ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ መሆኑ የሚታወቀው፣ መሪው ግስ፣ ስም፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ሲሆን እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በጥገኝነት ምልክቱ ነው። ይህም ሞዩ ነው። ቀደም ሲል በየደረጃው ያየናቸው ሀረጎች፣ መሪያቸው የሚገኘው መሙሲያውን አየተከተለ በስተቀኝ በኩል ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሀረጎቹ በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው። ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት፣ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን መሪው፣ ማስትም ሞዩ፣ የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ ሰስተቀኝ ነው፣ ስማለት ይቻላል። ይህን በማለትም ቁዋንቁዋው በሀረግም ሆነ በአረፍተ ነገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመሪ አገባብ አንዳለው ስማሳየት ይቻላል። ይኸውም ቁዋንቁዋው ቀኝ መሪ ነው፣ የሚል አጠቃላይ መግለጫ በመስጠት ነው።

ሁስተኛው ማሰረጃ ትውረታዊ ብቻ ሳይሆን፣ ምክንያታዊ ጭምር ነው። ምክንያቱም አንደሚከተለው ያሉ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች መኖር ነው።

(ሀ) ካሳ ሰራ ይሰራ ዘንድ 7
(ስ) አስቴር ምሳዋን ትበላ ዘንድ

በቀደምት ሊቃውንት፣ አንደነዚህ ያሉ መዋቅሮች ዘንድ አንቀፅ በመባል ይታወቃሉ። ሰዚህ ምክንያቱ አንደኛ ዘንድ የሚለውን ቃል ማስከተላቸው ሲሆን፣ ሁስተኛው እንዲፈፀምልን የምንሻውን ድርጊት የሚገልፁ መሆናቸው ነው። "....ይፈፀምልኝ ዘንድ በትህትና አመለክታስሁ፣" እንደምንስው ማለት ነው።

ውስጣዊ ይዘታቸው፣ አረፍተ ነገራዊ ነው። ይሁን እንጅ፣ ቅርፁ የመደበኛ ሳይሆን፣ የጥገኛ አረፍተ ነገር ነው። ይህ ስመሆኑ ምልክቱ ዘንድ የሚለው ሞይ ነው። አሱም የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ነው። ከዚህ በመነሳት፣ በሌሎቹም ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሞዩ ቦታ አንደዚሁ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ነው፣ ስማለት ይቻላል። ዘንድ እንደ /የ/ ጥገኛ ላይሆን፣ ራሱን የቻለ ምዕላድ ነው። ስለሆነም ካጠገቡ ከሚገኘው ግሰ ወይም ስም ላይ መጠጋት አያስፈልገውም። እንደ /የ/ ያሉ ሞዮች የሚስጠፉበት ምክንያት አቅመ ቢስ ድሁር እናም ምርኩዝ ፈላጊ መሆናቸው ነው[1]።

[1] በዚህ ጉዳይ ላይ ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ። ምክንያቱ አቅመ-ቢስነት ላይሆን ይችላል። ወደ ውስብስብ ትውረት ስለሚወስደን ዝርዝር ውስጥ አንገባም።

ይህ አንግዲህ የመሙሊያ አረፍተ ነገሮችንና የሞዮችን ቅንጅት በሚመለከት ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከአጎሳማሽ አረፍተ ነገር ጋር ስለሚዋቀሩ ስማዊ ሀረጎች እንወያያለን።

(ለ) አዛማጅ አረፍተ ነገር

አዛማጅ አረፍተ ነገሮች[2] የሚባሉት አንድን ስማዊ ሀረግ በውስጣቸው ከሚገኝ ከማንኛውም ስማዊ ወይም መስተዋደዳዊ ሀረግ ጋር በማጣቀስ ይህኑ ስማዊ ሀረግ እየነለፀ የሚያጎላምሱ ውሱን መዋቅሮች ናቸው። የሚከተለው የእነዚህ ምሳሌ ነው።

[ካሳ የሸጠው [የብራና መፅሀፍ]] 1

ይህ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>መፅሀፍ</u> የሚለው ስም ነው። ይህ መሪ ስም <u>የብራና</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል። <u>የብራና</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ፣ መፅሀፉ ከምን እንደተሰራ የሚያመለክት መሙሊያ ነው። መሪውና መሙሊያው የፈጠሩት ንዑስ ስማዊ ሀረግ [ካሳ የሸጠው] ከሚለው ገላጭ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ [ካሳ የሸጠው የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ውስብስብ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል።


[ካሳ የሸጠው] 2

የሚለው መዋቅር ጥገኛ አረፍተ ነገር ነው። ስለሆነም ቀደም ሲል የጥገኝነት ምልክት ነች፣ ያልናትን /የ/ን ከግሱ ላይ ለጥፎአል። አረፍተ ነገሩ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ <u>የካሳ ቤት የመሰራት</u> እንደሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር፣ ስማዊ ሳይሆን፣ ግሳዊ ነው። ስለሆነም በግሱ መድረሻ ላይ፣ የባለቤትና የተሳቢ አፀፋዎችን አስከትሎአል። ስለዚህም ውሱን ነው። ባለቤቱ በአፀፋ ስለተጠቀሰ፣ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ አላስቀደመም።

አረፍተ ነገሩ ጥገኛ ይሁን እንጅ፣ <u>የብራና መፅሀፍ</u> ስሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ኾይደለም፣ አጎሳማሽ ነው። የመሪው ስም መሙሊያው ከላይ እንደተገለፀው፣ <u>የብራና</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። አረፍተ ነገሩ ብአጎሳማሽነቱ [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ ይዞልፃል። እንደሚንኛውም

[2] ስለ አዛማጅ አረፍተ ነገር ሀይሉ (1972)ን ይመልከቱ።

እንላማሽ፣ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከንዑስ ሰማዊ ሀረግ ጋር ነው። ይህን እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን።



ከዕፀ መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ ጥገኛው አረፍተ ነገር (አነ') የንዑስ ሰማዊ ሀረግ ገላጭ ሆኖ ገብቶአል። እወራረዱ ከእቢዩ ሰማዊ ሀረግ ስሀ(2) አንጉዋ ላይ ነው። ይህ አይነተኛ የገላጭ ሀረጎች መዋቅራዊ ባህሪ ነው።

አረፍተ ነገሩ (አነ) ከሞዩ ማሰትም ከ(የ/) ጋር ተዋቅሮ ሰፊውን ጥገኛ አረፍተ ነገር (አነ') መስርቶአል። ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ሞዩ በአረፍተ ነግሩ መድረሻ ላይ ይገኛል። አረፍተ ነገሩ ደግሞ፣ እንደ ማንኛውም ገላጭ

[3]በዚህ ምልክት (,) የሚጣቀሱ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው።

አረፍተ ነገር፣ ከስማዊ ሀረግ ባለቤትና ከግሳዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው። የግሳዊ ሀረጉ መሪ ሽጠ የሚለው ሳቢ ግስ ነው። ስለሆነም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው። ይሁን እንጅ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም። ቦታው ግን በሰረዝ (–) የተመለከተው ነው። በግሱ መድረሻ ላይ ይህንኑ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ የሚጠቁም አፀፋ አለ። አሱም /-ኡ/ ነው። ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን ያመለክታል። እንደዚህ ያለ ስማዊ ሀረግ ግን በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በግሀድ የለም። ስለዚህም ሸጠው የሚለው ግስ ተሳቢ ማነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

ተሳቢው በግሀድ የማይታይ፣ ነገር ግን መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው የሚታወቅ ስማዊ ሀረግ ነው። ሊታወቅ የቻለውም በግሱ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ ነው። ይህ አፀፋ በግሱ ላይ የግድ መታየት አለበት። ካልታየ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ ይዘት ሊታወቅ አይችልም፣ እናም አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አይኖረውም። በሌላ አነጋገር፣

*[ካሳ የሸጠ] 4

ማለት አይቻልም።

ሌላው ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፣ በአፀፋ የተጠቀሰ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ሁል ጊዜ በግሀድ አይታይም፣ ማለት ነው ወይ? የሚል ነው። በርግጥ እንደዚህ ያለ ሀረግ በግሀድ ሊታይም ላይታይም ይችላል። ወሳኙ ሀረጉ የሚገኝበት የመዋቅር አይነት ነው። መዋቅሩ ከፍ ሲል እንደሚታየው ያለ ጥገኛ አረፍተ ነገር ከሆነ፣ ሀረጉ በአፀፋ ይጠቆማል አንጅ፣ በግሀድ ሊታይ አይችልም። መዋቅሩ ቀደም ሲል እንዳየነው ያለ ስማዊ አረፍተ ነገር ወይም ከዚህ በታች እንደሚታየው ያለ መደበኛ (ጥገኛ ያልሆነ) ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ በግሀድ ሊታይ ይችላል። ስለዚህም በተሳቢ አፀፋ ላይጠቀስ ይችላል። የሚከተለውን እንመልከት።

ካሳ የብራና መፅሀፍ ሸጠ 5

እነሆ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ይታያል። በግሱ ላይም አሱን የሚጠቁም አፀፋ የለም።

ከፍ ሲል በጥገኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ ሊጠቀስ እንጅ በግሀድ ሊከሰት እንደማይችል ገልፀናል። ከዚህም ሳይ ለምን በግሀድ አይታይም? የሚል ጥያቄ አሁንም ይነሳ ይሆናል። ሀረጉ በግሀድ የማይታየው፣ በሁለት ምክንያቶች ነው። እንደኛው ሀረጉ በአፀፋ በመጠቀሱና ከዚህም ይዘቱ የሚታወቅ በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ይኸው ሀረግ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር በይዘት (ትርጉም) አንድ በመሆኑ ነው። ይህም ማለት፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ሀረግ የሚጠቁሙት አንድ ነገርን ነው። የማይታየው ተሳቢ ስማዊ ሀረግም [የብራና መፅሀፍ] የሚል ነው። ይህ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ቢወጣ፣

*[[ካሳ የብራና መፅሀፍ የሸጠው] የብራና መፅሀፍ] 6

የሚል ይሆናል። [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ሀረግ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በተሳቢነት፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ ደግሞ በመሪነት ስለተከሰተ፣ ድግግሞሽን አስከትሎአል። ይህ አይነት ድግግሞሽም ከቁዋንቁዋ ባህሪ ጋር ይጻረራል። ቁዋንቁዋ አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽን ፈፅሞ አይፈቅድም። አዕምሮም እንደዚሁ። ለዚህ ነው፣ ሀረጉ ተቀባይነት የሌለው። ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ከሁለቱ ተደጋጋሚ ስማዊ ሀረጎች አንደኛው የግድ በግሀድ እንዳይወጣ መታገድ ይኖርበታል። እንደዚህ የሚደረገው ደግሞ ማንኛውም ሳይሆን፣ በአፀፋ የሚጠቆመው ስማዊ ሀረግ ብቻ ነው። ምክንያቱም ይዘቱ ከአፀፋው አይነት ይታወቃልና። [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይዘት /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ ስለሚታወቅ፣ በግሀድ እንዳይወጣ ታግዶአል።

ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የትርጉም ብቻ ሳይሆን፣ የመዋቅርም ዝምድና አላቸው። ዝምድናውም ተሳቢውን ስማዊ ሀረግ የያዘው አረፍተ ነገር [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ስማዊ ሀረግ አጎላማሽ ሆኖ መግባቱ ነው። በአጎላማሽነቱም [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ በውስጡ ካለው ድብቅ ተሳቢ ጋር አዛምዶታል። የትኛው [የብራና መፅሀፍ] ብለን ብንጠይቅ፣ መልሱ [ካሳ የሸጠው] የሚል ይሆናል። ከዚህም ሁለቱን ስማዊ ሀረጎች የማዛመድ ተግባሩ የተነሳ፣ እንደ [ካሳ የሸጠው] ያለ መዋቅር አዛማጅ አረፍተ ነገር ይባላል።

ይህ አይነቱ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል ካየነው መሙሲያ አረፍተ ነገር የተለየ ነው። ልዩነቱ በሶስት ወገን ነው። በአንድ ወገን፣ ይሽኛው አረፍተ ነገር፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ግሳዊ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከመሪው ስም ጋር ሳይሆን፣ ከንዑሱ ሀረግ ጋር ነው። በመጨረሻም ከዚህ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በውስጡ ያለውን በአፀፋ ብቻ የተጠቆመ ድብቅ ስማዊ ሀረግ አብሮት ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ስለሚያዛምድ፣ ገላጭና አዛማጅ ነው፣ መሙሲያ አይደለም።


በአንድ አዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝን ድብቅ ሰማዊ ሀረግ ተዛማጅ እንለዋለን። የሚዛመደውም በእረፍተ ነገሩ ከሚጎላመሰው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው። ከላይ በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ ተሳቢው ነው። ተዛማጅነት ግን የተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ የተለየ ባህሪ አይደለም። ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግም ሊዛመድ ይችላል። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

[--- አስቴርን የስደቡአት (/ስደብ-ኡ-አት/) ልጆች] 7

ይህም፣ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (1) እንዳየነው መዋቅር፣ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው ልጆች የሚለው ስም ሲሆን፣ አጎላማሹ፣

[--- አስቴርን የስደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/)] 8

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። አረፍተ ነገሩ <u>አስቴርን የሰደቡአት</u> የሚል ግሳዊ ሀረግና በግሀድ የማይታይ ባለቤት ስማዊ ሀረግ አሰው። ከግሱ ላይ ከሚታየው /-አ/ ከሚለው አፀፋ፣ ባለቤቱ ሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር መሆኑን ለማወቅ ይቻላል። አዛማጁ አረፍተ ነገር ይህን ድብቅ ባለቤት ስማዊ ሀረግ <u>ልጆቹ</u> ከሚለው ከዋናው ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ጋር አዛምዶታል። ስላዛመደውም ሀረጉ በግሀድ ከመታየት ታግዶአል። በግሀድ ቢታይ ኖሮ፣ መዋቅሩ [ልጆች አስቴርን የሰደቡአት (/ሰደብ-አ-አት/) ልጆች] የሚል ይሆን ነበር። ይህ ደግሞ ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንያቱም አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽ ያሳያልና። የአዛማጁን አረፍተ ነገርና የስማዊ ሀረጉን መዋቅራዊ ተዛምዶ አሁንም በዕፀ መዋቅር አንደሚከተለው እናሳያለን።



ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም። ቦታው በሰረዝ የተመለከተው ነው። ከፍት የሆነበት ምክንያት ሀረጉ /-አ/ በሚለው አፀፋ ስለተጠቀሰና <u>ልጆቹ</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር

በትርጉም አንድ ሆኖ ስለተዛመደ ነው። ያዘግመዱም ሁኔታ ከፍ ሲል ካየነው የተሳቢ ስማዊ ሀረግ አዘግመድ ጋር አንድ ነው።


አሰካሁን ያየነው የአንድ አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤት ወይም ተሳቢ፣ በአረፍተ ነገሩ ከሚጎላመለው ስማዊ ሀረግ ጋር የሚፈጥረውን መዋቅራዊ ዝምድና ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የተዛማጅ መስተዋድዳዊ ሀረግን ሁኔታ እንመለከታለን። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

[[ልጆቹ የሄዱበት] ሀገር] 10

ይህ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሀገር</u> የሚለው ስም ነው። አጎላማሹ፣

[ልጆቹ የሄዱበት] 11

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። የዚህን አረፍተ ነገር ግስ ስንመለከት፣ /-ኡ/ እና /-በት/ የሚሉትን ቅጥያች እንዳስከተለ እንረዳለን። የመጀመሪያው ቅጣይ፣ <u>ልጆቹ</u> የሚለውን የብዙ ቁጥር ባለቤት የሚጠቁም፣ የብዙ ቁጥር አፀፋ ነው። ሁለተኛውስ? ሁለተኛው የሚጠቁመው እንድ በግሀድ የማይታይን መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ሀረጉ መስተዋድዳዊ ለመሆኑ ከግሱ ባህረ ማወቅ ይቻላል። <u>ሄደ</u> የሚለው ግስ መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግን በመሙሊያነት ይፈልጋል። የእንደዚህ አይነት መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪም <u>ወደ</u> ነው። ሀረጉ በግሀድ የማይታይበት ምክንያት፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ራሱ በመሆኑ ነው። ስለሆነም እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግ በአፀፋ ተጠቅሰአል። አፀፋውም /-በት/ ነው። ይህ አፀፋ ግን ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው። የ/በ/ እና የ/ት/ ቅንጅት ነው። /በ/ <u>ወደ</u> የሚለውን መስተዋድድ ሲወክል፣ /ት/ ከመስተዋድዱ ጋር የተዋቀረውን ስማዊ ሀረግ ትወክላለች። /-በት/ የሚለውን ውስብስብ የመስተዋድድ አፀፋ ልንለው እንችላለን። ውስብስብ ወይም ድርብ አፀፋዎችን ካሁን ቀደምም እንዳየን ያስታውሱ። ለምሳሌ፣ በስማዊ እረፍተ ነገር ውስጥ [-ዋ] የ/ኡ/ እና የ/አ/ ውሁድ፣ በግሳዊ እረፍተ ነገር ውስጥም [-ች] የ/-ት/ እና የ/-አ/ ውሁድ እንደሆነች እይተናል። ከዚህ ላይ የሚታየው /በት/ የሚለው አፀፋ አካሄድም እንደዚሁ ነው። የመዋቅሩን ተዛምዶ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናመለክታለን።



12

እነሆ፡ የግሱ መሙሊያ የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (—) ነው። ክፍት የሆነበት ምክንያትም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ሀገር ከሚለው ከስማዊ ሀረጉ መሪ ጋር በአረፍተ ነገሩ አማካኝነት ስለተዛመደና እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በአፀፉ ሳይተጠቀስ ነው። ሀገር የሚለው ስም፡ ሄዱ በሚለው ግስ ለተጠቀሰው ተግባር መድረሻ ነው። ልጆቹ ሄደው የሚደርሱበትን ቦታ ያመለክታልና። እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው ሀረግ የሚዋቀረው፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ወደ ለሚለው መስተዋድድ መሙሊያ ቢሆን ነው። ከዚህ ስንነሳ፣ በዕፀ መዋቅሩ ላይ ክፍት (-) የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ይዘት ወደ ሀገር የሚል ነው፡ ይህም የሚታወቀው /-በት/ ከሚለው ድርብ አፀፋ ነው። አፀፋው የሚያጣቅለው ይህንኑ ሀረግ ነው። ይሁን እንጅ፣ በሀረጉ ውስጥ ባለው መስተዋድድና በአፀፋው መስተዋድድ መካከል የቅርፅ ልዩነት አለ። በሀረጉ ውስጥ መስተዋድዱ ወደ የሚለው ሲሆን፣ በአፀፋው ላይ የሚታየው /-ብ/ ሆኖ ነው።

ሁኔታው በዚህ ብቻ አያበቃም፡ ለምሳሌ፣ ሀገር የሚለው መሪ ስም መድረሻ ሳይሆን፣ መነሻ ወይም መኖሪያ ቢሆን፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ

የሚጠቀሰው በተለየ ሳይሆን፣ በዚሁ /ቧ/ በሚለው አፀፋ ብቻ ነው። ልጆቹ <u>የመጡበት</u>፣ <u>የደረሱበት</u>፣ <u>የሚኖሩበት</u>፣ ወዘተ፣ ሀገር፤ ወይም ልጆቹ <u>የበሉበት</u> መሰብ፣ <u>የጠጡበት</u> ዋንጫ፣ ወዘተ፣ ብንል፣ የየሀረጉ መስተዋድድ ቅርፅ ይለያያል እንጅ፣ አፀፋው አይለወጥም። አፀፋው የተለየ የሚሆነው መስተዋድዳዊ ሀረጉ ሰዚንድ ድርጊት ተጠቃሚ መሆንን የሚያሳይ ሲሆን ነው። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

አስቴር ለካሳ ገንዘብ ላከችለት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ለካሳ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በግሱ የተገለፀው ድርጊት ፈፃሚ ሳይሆን፣ ተጠቃሚ ነው። ስለዚህም በግሱ ላይ መስተዋድዳዊው ሀረግ /-ለት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል። ይህንኑ አረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ብንለውጠው፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ የሚጠቆመው በዚሁ /-ለት/ በሚለው አፀፋ ይሆናል። ይህም እንደሚከተለው ነው።

[[አስቴር ገንዘብ የላከች-<u>ለት</u>] ሰው] 14

ከላይ በሚታየው አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ የሚታየው፣ <u>ለካሳ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በዚህ ስማዊ ሀረግ ውስጥ አይታይም። የማይታየውም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ለለሆነና እንደ ማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በግሱ ላይ ብቻ በአፀፋ ስለተጠቀሰ ነው። አፀፋውም በግልፅ እንደሚታየው፣ /-ለት/ ነው። ባጭሩ፣ ለለ መስተዋድዳዊ ሀረግ የአፀፋ ስርዓት የሚከተለውን ማለት ይቻላል። ተጠቃሚነትን ከሚያሳይ መስተዋድዳዊ ሀረግ በለተቀር፣ ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ በተዛማጅነት ሲገባ፣ የሚጠቀሰው /ቧ/ በሚለው መስተዋድድ ነው። በሌላ አነጋገር፣ /-ቧ/ እና /-ለ/ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች ናቸው፣ /-ቧ/ ለማንኛውም መስተዋድድ፣ /-ለ/ ተጠቃሚን ለሚያሳይ መስተዋድድ ብቻ።

እሰካሁን ድረስ ያየናቸው ተዛማጅ ሀረጎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ የግሱ ተሳቢ ወይም እጎላማሽ የሆኑ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ስማዊ ሀረግ እንዲት እንደሚዛመድ እንመለከታለን። ለዚህ የሚከተለውን እንይ።

[[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] ልጅ] 15

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣

[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] 16

የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። ባለቤቱ <u>አስቴር</u> የሚለው አንስታይ ስማዊ ሀረግ ነው። ስለሆነም በግሱ ላይ /-ች/ በሚለው የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ ምዕላድ ተጠቁሞአል። የግሱ ተሳቢ <u>ፀጉርዋን</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ አሱም አንደዚሁ በግሱ ላይ /-አት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል። ባለቤትም ሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ በቦታቸው አሉ፣ ማለት ነው። ከዚህ ላይ ታዲያ፣ <u>ልጅ</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ወይም የግሱ ተሳቢ ሊሆን አይችልም። አነዚህ በግሀድ ይታያሉና። ስለዚህም ተዛማጁ ሀረግ ከነዚህ ውጭ የሆነና በአፀፋም የተጠቆመ መሆን አለበት። ከባለቤትና ከተሳቢ አፀፋ ሌላ፣ በግሱ ላይ የሚታይ ምንም አፀፋ የለም። በተሳቢው ስማዊ ሀረግ መድረሻ ላይ ግን [-ዋ] </-ኡ-አ/ የምትል ድርብ አፀፋ አለች። ይህች አፀፋ የምትጠቁመው <u>ገንዛቢ</u> (ባለገንዘብ) ስማዊ ሀረግን ነው። የዚህ አይነት ስማዊ ሀረግ በተሳቢው ስማዊ ሀረግ ውስጥ በድብቅ አለ ማለት ነው። ከዚህ አንፃር አረፍተ ነገሩ ሲተረጎም፣

አስቴር ልጅትዋን ፀጉርዋን ሰራቻት 17


የሚል ይሆናል።

የተዛመደውም ይህ <u>ልጅትዋን</u> የሚለው ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ሀረግ ጋር የተገናዘበው ደግሞ <u>ፀጉር</u> የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሪ ሲሆን፣ ሁለቱን ስሞች፣ ማለትም አስቴር እና ፀጉር የሚሉትን፣ የሚያገናዝበው (የሚያገናኘው) ምዕላድ /-ዋ/ ነው። በዚህም መሰረት <u>ልጅትዋን</u> የሚለውን ስም ገንዛቢ፣ <u>ፀጉርዋን</u> የሚለውን ተገናዛቢ፣ አንዲሁም /-ዋ/ን አገናዛቢ የባለቤት አፀፋ ወይም ዘርፍ አንሳታለን። አገናዛቢዋ ምዕላድ የገንዛቢው ሀረግ አፀፋ ነች። የምትታየውም በተገናዛቢው ስም መድረሻ ላይ ነው። የባለቤት አፀፋ በመሪ ግስ ላይ አንደሚታይ ሁሉ፣ የገንዛቢ አፀፋም በመሪ ስም ላይ ይታያል፣ ማለት ነው። ሲጠቃለል፣ አፀፋዎች የሚታዩት በመሪ ሳይ ነው፣ ሲማለት ይቻላል።

ከላይ በሚታየው ምሳሌ ውስጥ፣ የተዛመደው ስማዊ ሀረግ <u>ልጅትዋ</u> የሚለው ገንዛቢ ስም ነው። ይህ ውነት ስመሆኑ ማስረጃው /-ዋ/ በሚለው ምዕላድ መጠቀሱና በግሀድ አለመታየቱ ነው። በአዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ አለመታየትና በአፀፋ መጠቀስ የተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ምልክት ነው፣ ብለናልና። ከዚህ አንፃር፣

[[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-አት] ልጅ] 18

የሚለው ስማዊ ሀረግ ውስጣዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ይሆናል።



ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ መሪ <u>ፀጉርዋን</u> የሚለው ተገናዛቢ ስም ነው። የዚህ ስም ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ደግሞ (ስሀᵢ)ነው። የተዛመደውም አሱው ነው። ስለተዛመደም ፀጉርዋን በሚለው መሪ ስም ላይ ስእፀፋ ተጠቅሶአል። ከእፀፋው ሶስተኛ መደብ፣ እንስታይ ያታ፣ ነጠላ ቁጥርና ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል።

አስካሁን በዚህ ክፍል ውስጥ ያየነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን፡፡ ለማየት የተነሳነው ውስብስብ ስማዊ ሀረጎችን ነው፡፡ ሀረጎቹ ውስብስብ የሆኑበት ምክንያት አረፍተ ነገራዊ ከሆኑ መሙሊያዎች ወይም ገላጮች ጋር ስለሚዋቀሩ ነው፡፡ መሙሊያዎቹ ስማዊ አረፍተ ነገሮች ሲሆኑ፣ ገላጮቹ አዛምጅ ግሳዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ የመሪው ስም መሙሊያ ወይም ገላጭ ሆነው በተገኙነት መግባታቸውን የሚያመለክት /የ/ የሚል ምዕላድ አላቸው፡፡ ይህም ሞይ ያልነው አሀድ ነው፡፡ መዋቅራዊ ዝምድናው ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሲሆን፣ አገባቡም አረፍተ ነገሩን ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡


የስማዊ መሙሊያ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ሊከሰት ወይም ላይከሰት ይችላል፡፡ የሚከሰተው፣ አንድም በመሪው ስም ላይ አፀፋው ሲታይ፣ አለያም /የ/ የምትለዋን ምዕላድ ሲያስቀድም ብቻ ነው፡፡

አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤቱን፣ ወይም ተሳቢውን ወይም መስተዋድዳዊ ሀረጉን ከሚያጎላምሰው ስም ጋር ያዛምዳል፡፡ የሚዛመደው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ በአፀፋ ግን አንደተለመደው ይጠቀሳል፡፡ አፀፋው የሚታየው በግሱ ላይ ነው፡፡ ከአፀፋው አይነት በግሀድ የማይታየውን ተዛማጅ ስም ይዘት ማውቅ ይቻላል፡፡ ባለቤት ወይም ተሳቢ በሆነ ስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ገንዛቢ ስማዊ ሀረግም አንደዚሁ በአፀፋ ሊዛመድ ይችላል፡፡ ሲዛመድም በግሀድ አይከሰትም፡፡ አንደ ማንኛውም ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ አፀፋው በመሪው ላይ ስለሚታይ ይዘቱ ከዚያው ይታወቃል፡፡

ውስብስብ ስማዊ ሀረግ በባለቤትነት ወይም በተሳቢነት ወይም በገላጭነት ሊገባ ይችላል፡፡ አንደዚህ ያለ ውስብስብ ሀረግን የያዘ አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ውስብስብ ይባላል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) [[የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] [ከሸፈ]] 20
(ለ) [እኔ [[የአስቴርን ቤት የመስራት አላማ] እደግፋለሁ]]

የመጀመሪያው ምላሌ [የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ባለቤት የሆነበትና ከሸፈ ከሚለው ግስ ጋር ውስብስብ አረፍተ ነገር ያዋቀረበት ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ይኸው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ እደግፋለሁ ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ፣ ብሎም ተሳቢ ሆኖ የገባበት ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው፡፡ አንደነዚህ ያሉት በውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ምክንያት ውስብስብ የሆኑ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ውስጣዊ ቅንጅታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡



ከዚህ ቀጥሰን ደግሞ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችንና በነሱ ምክንያት ውስብስብ የሚሆኑ አረፍተ ነገሮችን የአወቃቀር ስርዓት እንመለከታለን።

ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ክፍል ስስ ግሳዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ አንድ ግስ ከተራ ሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽ እና መስተዓምር ጋር እየተዋቀረ ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊመስርት ይችላል። ከዚህ አይነት ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ ነው። ይህ ግን የሁሉም ግሶች ባህሪ አይደለም። አንዳንድ ግሶች ከተራ ሳይሆን፣ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ሊዋቀሩ ይችላሉ[4]። በዚህም መስረት ግሶች

[4] ስስ መሙሊያ አረፍተ ነገሮች ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ።


ይለያያሉ። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠረው መዋቅር ውስብስብ ወይም ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

[[ካሳ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች] [አውቆአል]] 1

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፤

[አስቴር ወደ ጎንደር እንደ ሄደች] 2

የሚለው መዋቅር አረፍተ ነገራዊ ነው። አገባቡም <u>አውቆአል</u> ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ነው። ግሱ ከዚህ አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ሲቀናጅ የሚፈጥረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ አወቃቀር የሚከተለውን ይመለላል።



3

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች የሚለው አረፍተ ነገር አውቆአል ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ገብቶአል። መሙሊያው አረፍተ ነገር እንደ የሚለው መሰተዋድድና አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች የሚለው አረፍተ ነገር ቅንጅት ነው። መሰተዋድዱ፣ አረፍተ ነገሩ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ፣ የግሱ መሙሊያ ሆኖ በጥገኝነት የገባ መሆኑን ያመለክታል። ቀደም ሲል ሰለ ውስብስብ ሰማዊ ሀረግ ሰንወያይ በመሙሊያነት ወይም ባአጎላማሽነት የሚገባ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ምዕላድ እንደሚታወቅ ገልፀን ነበር። አሁንም በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምናየው ሁኔታ ይኸው ነው። እንደ የሚለው መሰተዋድድ፣

አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች 4

የሚለው አረፍተ ነገር በሞያነት መግባቱን ያመለክታል። አገባቡም እንደ ማንኛውም የዚህ አይነት ምዕላድ፣ አረፍተ ነገሩን ተከትሎ ነው። እንደነዚህ ያሉ ጥገኝነትን የሚያመለክቱ ምዕላዶች ሞይ እንደሚባሉ፣ ቀደም ሲል ገልፀናል። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መሰተፃምር ይባሉ እንደነበርም በክፍል ሁለት ሰለ ቃላት ከፍል ሰንወያይ ጠቅሰናል። መሰተፃምር የሚያሰኛቸው ከአረፍተ ነገር ጋር መግባታቸው ብቻ ነው። በሌላው ባህሪያቸው ከመሰተዋድድ እንደማይሰዩ ገልፀናል።


በሰማዊ ሀረግ ውሰጥ የሚገኝ ጥገኛ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ሞይ ሊታወቅ፣ በግሳዊ ሀረግ ውሰጥ የሚገኝ ተመሳሳይ አረፍተ ነገር ግን እንደ በሚል መሰተዋድዳዊ ሞይ ይለያል። ሁኔታው ግን በዚህ ብቻ አያቆምም። በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ አንዳንድ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችም /የ/ በሚለው ሞይ ሊታወቁ ይችላሉ። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

[[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] ይመስላል] 5

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] 6

የሚለው ጥገኛ አረፍተ ነገር ይመስላል የሚለው ግሰ መሙሊያ ነው። ሰለሆነም በግሱ ላይ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ አሰቀድሞአል። ይህችም ሞይ ምዕላድ ሰትሆን፣ ታህታይ ቦታዋ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ነው። ይህንንም ዝርዝር ውሰጥ ሳንገባ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን።



7

የአረፍተ ነገሩን ውስጣዊ ቅንጅት ከፍ ብለን ያየነው ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ አንደግመውም። ከአሱ ይልቅ <u>ይመስላል</u> ስለሚለው ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ጥቂት ገለፃ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ግስ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ንዑስ ግሳዊ ሀረጉን ይመሰርታል። እንደዚሁም ከገላጭ አረፍተ ነገር ጋር ሆኖ እቢይ ግሳዊ ሀረጉን ይመሰርታል። ይሁን እንጅ ባለቤት የለውም። ስለዚህም በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ የባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (-) ይሆናል። በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግን ቦታው አንድም ክፍት እንደሆነ ይቀራል፣ አለያም በመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ይሸፈናል። ለዚህም የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) [---[ልጆቹ [ስራ የሚሰሩ]] ይመስላል] 8
(ለ) [ልጆቹ [---[ስራ የሚሰሩ]] ይመስላሉ]

በምሳሌ (ሀ) [ስራ የሚሰሩ] የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ይህን <u>የሚሰሩ</u> ከሚለው ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው የብዙ ቁጥር አፀፋ ማወቅ ይቻላል። <u>ይመስላል</u> የሚለው የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ፣ የባለቤት ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው። ከግሱ መነሻ ላይ /ይ-/ የሚል ምዕላድ ይታያል። ይህም ስስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነን ባለቤት ይጠቁማል። ይህም <u>የአቃፊው</u> አረፍተ ነገር ባለቤት መሆን አለበት። የ<u>ታቃፊው</u> አረፍተ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው የብዙ ቁጥር ስም ነው፣

ብለናልና። ሁለተኛም <u>ይመለሳል</u> የሚለው ግስ ባለቤት እንደሌለው ከፍ ሲል ገልፀናል።

ይህ ውነት ከሆነ፣ /ይ-/ በሚለው ምዕላድ የሚጠቀስው የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። እንድ ግስ በታህታይ መዋቅር ባለቤት የለውም ሲባል፣ ድርጊት ፈፃሚ ወይም ሁዋኝ ባለቤት አይኖረውም ማለት ነው። ስለዚህም በታህታይ መዋቅር፣ የእንደዚህ አይነት ግስ የባለቤት ቦታ ከፍት ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ማንኛውም አረፍተ ነገር በላዕላይ መዋቅር የግድ ባለቤት ማግኘት አለበት። ምክንያቱም ማንኛውም አረፍተ ነገር በይዘቱ ብቻ ሳይሆን፣ በቅርፁም የተሙዋላ መሆን ስላለበት ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ባለቤት የሌለው አረፍተ ነገር ሙሉ አይሆንም ማለት ነው። ሙሉ እንዲሆን ከፈለግን፣ አድራጊም ሆነ ሁዋኝ ያልሆነ፣ ግን በባለቤት ቦታ ሊገኝ የሚችል፣ የይስሙላ ባለቤት (ለስም ብቻ የገባ) በላዕላይ መዋቅር ማስገባት አለብን። ይህም የይስሙላ ባለቤት በቦለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አፀፋ፣ ማለትም በ/ይ-/ ብቻ ይጠቀሳል። በግሀድ ግን አይወጣም። ቁዋንቁዋው የዚህ አይነት ግሀድ ባለቤት የለውምና።

እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቁዋንቁዋዎች፣ እንደዚህ ያለ የይስሙላ ባለቤት የሚሆን ተውላጠ ስም አለ። እሱም it ወይም there ነው። ይህ ተውላጠ ስም ደግሞ በአፀፋ አይጠቀስም፣ ምክንያቱም ቁዋንቁዋው የአፀፋ ምዕላድ የለውም። በህገራችን ቁዋንቁዋዎች ደግሞ እንደነዚህ ያሉ የይስሙላ ባለቤቶች፣ እንደ it ወይም there በነፃ ተውላጠ ስም መልክ አይከሰቱም። የሚከሰቱት /ይ-/ በሚለው አፀፋ ምዕላድ ብቻ ነው። በአጭሩ፣ እንደ እማርኛ ባሉ የህገራችን ቁዋንቁዋዎች it እና there መደበኛ ተውላጠ ስማዊ ቅርፅ የላቸውም። እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቁዋንቁዋዎች ደግሞ፣ መደበኛ ቅርፅ አላቸው፣ በአፀፋ ግን አይጠቀሱም።

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ይመለሳል</u> የነበረው ግስ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ <u>ይመለሳሉ</u> የሚል ሆኖአል። የብዙ ቁጥር፣ የባለቤት ስማዊ ሀረግ አፀፋ የሆነውን /-አ/ን ያሳያል ማለት ነው። ይህም የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው የብዙ ቁጥር ስማዊ ሀረግ መሆኑን ያሳያል። <u>የሚሰሩ</u> በሚለው ግስ መድረሻ ላይም ሀረጉ በዚሁ /-አ/ በሚለው አፀፋ ተጠቅሶአል። ስለዚህም ባለቤትነቱ ለአቃፊውም <u>ለዕቅፉም</u> አረፍተ ነገር ነው። ለአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ለመሆን፣ በምሳሌ (ሀ) ከሚታይበት ታህታይ ቦታው ተነስቶ፣ ከፍት ወደሆነው ወደ አቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ መሂድ አለበት። በዚያ ሆኖ የአቃፊውም ሆነ የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ሊሆን ይችላል[5]። ይህም ሊሆን የሚችለው እንደ <u>ይመስላል</u> ያሉ ግሶች በመስረቱ በባህሪያቸው ባለቤት-የለሽ በመሆናቸው ነው።

ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ደግሞ አንመልከት።

---

[5] ስለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ሁኔታ ባየ (1988፣ 1994)ን ይመልከቱ።

(ሀ) [---[ልጆቹ ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል]] 9
(ለ) [ልጆቹ [---ስራ እንዲሰሩ ይደረጋሉ]]

ይደረጋል የሚለው ግስ ተገብሮአዊ ነው። ታህታይ ቅርፁ /ይ-ት-ደረጋል/ ነው። የተገብሮ ግሶች፣ ይመስላል እንደሚለው ግስ፣ ባለቤት-የለሽ ናቸው። ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ የባለቤታቸው ቦታ ሁል ጊዜ ክፍት ነው። በላዕላይ መዋቅር ግን አረፍተ ነገሮች በቅርፃቸው ተሙዋልተው መገኘት ስላለባቸው፣ የግድ ባለቤት ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህም it የሚለው የይስሙላ ባለቤት ይገባላቸዋል። ይህም ተውላጠ ስም /ይ-/ በሚለው አፀፋ ብቻ በግሱ መነሻ ላይ ይከሰታል። ይህ ሲሆን የአረፍተ ነገሩ ቅርፅ 9(ሀ)ን ይመስላል።

በሌላ በኩል፣ ልጆቹ የሚለው የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት፣ ክቦታው ወጥቶ በአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ ሊገባና የአቃፊውም ሆነ የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ይደረጋል የነበረው ግስ የብዙ ቁጥር ቅርፅ ይይዝና ይደረጋሉ ይሆናል። ወደተነሳንበት የውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ጉዳይ እንመለስ።

ማንኛውም ሳቢ ግስ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር አየተዋቀረ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)፣ የተለያየ ተውላከ ግሳዊ ተግባር ካሳቸው አረፍተ ነገሮች ጋር እየተቀናጀ፣ አቢይ ሀረጉን ይመሰርታል። ቀከፍል ሁለት ለለ ተውላከ ግስ ስንወያይ፣ ተውላከ ግሳዊ ተግባራት በመስተዋድዳዊ ሀረጎችና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች አንደሚገለፁ፣ ለዚህም ምክንያቱ ቁዋንቁዋው በቂ መደበኛ ተውላከ ግስ ስለሌለው እንደሆነ ገልፀን ነበር። በዚያ መሰረት ከንዑስ ግሳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩና ተውላከ ግሳዊ ተግባር የሚየሳዩ ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ባሀሪ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። የሚከትሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ [[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት እንደሄደች] [ምሳውን በላ]]] 10


(ለ) [ካሳ [[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት ለለሄደች] [ተደሰተ]]]

በመጀመሪያው ምሳሌ በላ የሚለው ግስ ሳቢ ነው። ስለሆነም ምሳውን ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ምሳውን በላ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። ከዚህ ሀረግ በፊት የሚገኘው፣ ማለትም፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት እንደሄደች] 11

የሚለው ክፍል፣ ገላጭ አረፍተ ነገር ነው። ገላጭነቱም [ምሳውን በላ] ለሚለው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። ምሳ የመብላቱ ድርጊት መቸ እንደተፈፀመ ይገልፃል። ከዚህ ተግባሩ በመነሳት መዋቅሩን አረፍተ ነገራዊ የጊዜ ተውላከ ግስ ልንለው

አንችላለን፡፡ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ አንዲት እንደሚመሰርት በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡




በግልፅ እንደሚታየው፣ ገላጩ አረፍተ ነገር (አነ') ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) መሰርቶአል፡፡ የአረፍተ ነገሩ አወራረድም ከዚሁ ሀረግ እንጉዋ ሳይ ነው፡፡ ይህ የማንኛውም ገላጭ መዋቅር ባህሪ እንደሆነ በክፍል ሁለት ሰለ ሀረግ ሰንወያይ ተገንዝበናል፡፡ የአረፍተ ነገሩ ሞይ እንደ የሚለው ምዕላድ ሲሆን፣ እሱም እንደማንኛውም ሞይ አረፍተ ነገሩን ተከትሎ በሰተቀኝ በኩል ገብቶአል፡፡

በሁለተኛው ምሳሌ (10ለ) ውስጥ ያለው መዋቅራዊ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ተደሰተ የሚለው ግስ ኢሳቢ ነው፡፡ ስለዚህም ተሳቢ የለውም፡፡ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርተው ብቻውን በመቆም ነው፡፡ ይህን ንዑስ ሀረግ የሚገልፀው፣

|እሰቴር ወደ ትምህርት ቤት ሰሰሄደች| 13

የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የሚገልፀውም የደሰታውን ምክንያት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር የምክንያት ተውሳከ ግስ ይባላል፡፡ ከንዑሱ ሀረግ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነት እንደሚከተለው እድርገን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡



እስካሁን ድረስ ያየናቸው መሙሊያና አጎላማሽ (ገላጭ) አረፍተ ነገሮች፣ ግሳዊ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ግሳዊ አረፍተ ነገሮች የሚባሉት፣ ግሳዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። የነሱ አቻ የሆኑ መሙሊያና ገላጭ ስማዊ አረፍተ ነገሮችም አሉ። እነዚህ በግሳዊ ሀረግ ፋንታ፣ ስማዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። እንዳንዶቹን ስለ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ስንወያይ አይተናቸዋል። ከዚህ ቀጥሰን፣ አንደነዚህ ያሉ ስማዊ አረፍተ ነገሮችን በመሙሊያነትና በገላጭነት የሚያስገቡ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችን ባህሪ እንመረምራለን። ከዚያ በፊት ግን ነማዊ አረፍተ ነገሮች ውሱንና ኢውሱን ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ እናስነዝባለን። ውሱን የሚባሉት የባለቤት አፀፋ ያላቸው ሲሆኑ፣ ኢውሱን የሚባሉት አፀፋ የሌላቸው ናቸው። በውስኖቹ ላይ የሚታየው የባለቤት አፀፋ ዘርፍ ነው። በመሆኑም በግሱ ላይ ከሚታየው የባለቤት አፀፋ በቅርፁ ይለያል። ንፅፅሩን በርባታው ክፍል ያየነው ቢሆንም፣ ለማስታወስ ያህል አፀፋዎቹን ከዚህ በታች እንደገና እንዘረዝራቸዋለን።

	ግሳዊ	ስማዊ	15
1	ሰበር-ሁ	መስበር-እ[6]	
2	ሰበር-ህ	መስበር-ህ	
አን	ሰበር-ሽ	መስበር-ሽ	
3	ሰበር-አ	መስበር-አ	
አን	ሰበር-አች	መስበር-ዋ	
ብዙ	ሰበር-ን	መስበር-ኣችን	
	ሰበር-ኣችሁ	መስበር-ኣችሁ	
	ሰበር-ኡ	መስበር-ኣቸው	

[6] የአፀፋዎችን ባህሪና መዋቅራዊ ተግባር በተመለከተ ባየ(1988፣ 1994፣ 2001፣ 2004)ን እንዲሁም ግርማ (1994)ን ይመልከቱ።

ግሶቹ ያላፀፋዎቹ በአረፍተ ነገር ውስጥ ሊገቡ አይችሉም። ባለቤቱን የሚጠቁሙት አፀፋዎች በግሱ ላይ የግድ መገኘት አለባቸው። በተጨማሪም ግሶቹ የተሳቢ አፀፋንና ጊዜን ሊያሳዩ ይችላሉ። ለሞቹ ግን ያለያንም አፀፋ ሊገኙ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ባለቤቱ /የ/ በሚል ምዕላድ ሊለይ ስለሚችል ነው። ከዚህ የተነሳ ነው፣ እንደ <u>መሰበር</u> ባሉ ስሞች አማካ'ነት የሚመሰረቱ አረፍተ ነገሮች ውሱንና ኢውሱን ተብለው በሁለት የሚከፈሉት።

በአፀፋ የተጠቀሰ ሀረግ በግሀድ ሊከሰት ወይም ላደክሰት ይችላል። በግሀድ የሚከሰተው አንድም በአፀፋ ሲጠቀስ አለያም /የ/ በያ'ትለዋ ምዕላድ ሊደገፍ ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [[አሰጎር ወደ ጎንደር መሄድ-ዋ-ን] ስምቶአል] 16
(ለ) ካሳ [[የአሰቴርን ወደ ጎንደር መሄድ] ስምቶአል]
(መ) ካሳ [[----- ወደ ጎንደር ለመሄድ] ይፈልጋል]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ስምቶአል</u> የሚለው ሳቢ ግስ፣

[አሰቴር ወደ ጎንደር መሄድ-ዋ-ን] 17

የሚለውን ስማዊ አረፍተ ነገር በመሙሊያነት ይዞ፣ <u>ወደ ጎንደ</u><u>ር መሄድዋን ሰምቶአል</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። መሙሊያው አረፍተ ነገር የተዋቀረው <u>ወደ ጎንደር መሄድዋን</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግና <u>አሰ</u><u>ቴር</u> ከሚሰው ባለቤት ነው። <u>ወደ ጎንደር መሄድዋን</u> የሚለው ሀረግ መሪ የ'ለቤት አፀፋ ስለሚያሳይ፣ መሙሊያው አረፍተ ነገር ውሱን ነው። ከፍ ሲል እ ደተገለፀው፣ ውሱን የሆነ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ሊከሰት ይችላል። ባይከ ሰትም ይዘቱ ከመሪው ላይ ከሚታየው አፀፋ ሊታወቅ ይችላል።


በምሳሌ (ለ) ውስጥ የሚታየው መሙሊያ አረፍተ ነገር ኢ ሠ'ኑን ነው። ምክንያቱም <u>መሄድ</u> የሚለው መሪ ስም የባለቤት አፀፋ አልያዘም ። ስለዚህም <u>አሰቴር</u> የሚለው ባለቤት ስም በግሀድ ሊከሰት የሚችለው /የ/ የምትለዋ ምዕላድ ሲያሳይ ብቻ ነው። በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የምትታየው /-'/ የምትለዋ ምዕላድ አረፍተ ነገሩ ተሳቢ ሆኖ መግባቱን የምታመለክት የተሳቢ ምልክት ነች። አነባብዋ ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው፣ ከባለቤቱ አፀፋ፣ ,ወይ፯ ° /የ/ን አሰቀድሞ፣ በግሀድ ከሚታየው ባለቤት ስም ቀዋሎ ነው።

በምሳሌ (መ) <u>መሄድ</u> የሚለው ስም የባለቤት አፀፋ የለውም። ስ ነዚህም ባለቤቱ በግሀድ ሊከሰት አልቻለም። ቦታው ግን በስረዝ (---) የ'ተመለ ከተው ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ እንዳየነው፣ ባለቤቱ /የ/ን አሰቀድሞ በግሀድ ለ ከሰት ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል።

* [ካሳ [የካሳ ወደ ጎንደር (ሰ)መሄድ] ይፈልጋል] 18

ከሰዋሰው ሀግጋት አንፃር ሲታይ፣ ይህ መዋቅር ተቀባይነት አለው፡፡ ከትርጉም አንፃር ግን ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤትና <u>ይፈልጋል</u> በሚለው ግሰ የሚመራው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት የሚጠቁሙት <u>አንድን ሰው</u> በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ከመከሰት ይታቀባል፡፡ ማንነቱ ከአናቱ (ከ<u>አቃፊው</u>) አረፍተ ነገር ባለቤት ይዘት ይታወቃል፡፡

[ወደ ጎንደር ለመሄድ] በሚለው ውስጥ የምትታየው /ለ/ መስተዋድዳዊ ሞይ ነች፡፡ አገባብዋም አንደማንኛውም ሞይ መሙሊያውን አረፍተ ነገር ተከትላ ነው፡፡ የሁሉንም ስማዊ አረፍተ ነገሮችና የግሱን መዋቅራዊ ግንኙነት አጠቃለን አንደሚከተለው አናቀርባለን፡፡



19

ይህ የኢውሱኑ መሙሊያ አረፍተ ነገርና፣ ይፈልጋል የሚለው ሳቢ ግስ መዋቅራዊ ግንኙነት ነው። የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አይታይም። ቦታው በስረዝ የተመለከተው ነው። መሄድ የሚለው መሪ ስም የባለቤት አፀፋ በሚያሳይበት ጊዜ፣ ባለቤቱ በሰረዝ በተመለከተው ቦታው ላይ በግሀድ ሊከሰት ይችላል። በዚህን ጊዜ ሞዩ አይታይም። የሚታየው የተሳቢ ምልክት የሆነው /-ን/ የሚለው ምዕላድ ነው። ይህ ምዕላድ ውሱን ከሆኑ ተሳቢ ሀረጎች ጋር ቁርኝት ስላለው፣ እሱ ይከሰትና ሞዩ ከቦታው ይጠፋል[7]። ይህም የሚሆነው በላዕላይ መዋቅር ነው። ቁዋንቁዋው ሁለቱ ምዕላዶች በላዕላይ መዋቅር ተከታትለው እንዲመጡ የሚፈቅድ አይመሰልም[8]።

ከሰማዊም ይሁን ከግሳዊ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችና ከግሰ የሚመሰረቱ ንዑስ ሀረጎች ከተለያዩ አጎላማሽ አረፍተ ነገሮች ጋር በመዋቀር አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርቱ ይችላሉ። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

]አስቱር ||[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] [[ካሳ መምጣቱን] ሰማች]]] 20

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ሰማች የሚለው ሳቢ ግስ፣ [ካሳ መምጣቱን] ከሚለው ስማዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣ [ካሳ መምጣቱን ሰማች] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። መሙሊያው ሰማዊ አረፍተ ነገር አፀፋ ስላለው ውሱን ነው። ስለዚህም ባለቤቱ ካሳ በግሀድ ሊከሰት ችሎአል። ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ በተራው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] 21

ከሚለው ግሳዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣

---

[7] ከዚህ ላይ /-ን/ የተሳቢ ምዕላድ ሳይሆን፣ ሞይ መስተዋድድ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል። /-ን/ በመስተዋድድነት ሲገባ ቀደም ብለን አይተናል። እንደ ከሚለው ሞይ ጋር ተከታትሎ የማይመጣውም ለዚሁ ነው። የአንድን አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆን ለማሳየት ሁለት ሞይ አያሰፈልግም።

[8] ይህ ገደብ በሌሎች ምዕላዶችም ይታያል። ለምሳሌ /የ/ የሚለው አገናዛቢ ምዕላድ ከማንኛውም መስተዋድድ በሁዋላ ሲገባ፣ በግሀድ አይታይም። ስለዚህም ለምሳሌ፣ የ-ካሳ ልጅ የሚለው አገናዛቢ ስማዊ ሀረግ፣]ለካሳ ልጅ]፣ [ወደ ካሳ ልጅ]፣ [እንደ ካሳ ልጅ]፣ ወዘተ፣ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ቀደምት ሊቃውንት ውስጠ-የ እና ግልፀ-የ የሚል አጠራር ነበራቸው። የካሳ ልጅ በሚለው መነሻ ላይ የሚታየው /የ/ ግልፀ-የ ሲሆን፣ ከየመስተዋድዱ ቀጥሎ የሚመጣውና በግሀድ የማይታየው /የ-/ ውስጠ-የ ነው።

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደ ሄዱ ካሳ መምጣቱን ሰማች] 22

የሚለውን እቢይ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ነው። የሚገልፀው ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ነው። አገላለፁም ካሳ የመጣበትን ጊዜ በመጥቀስ ነው። ስለዚህም አረፍተ ነገራዊ የጊዜ ተውላክ ግሰ ልንለው እንችላለን። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አረፍተ ነገሩ ግሳዊ ነው። ስማዊ አቻው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው] 23

የሚል ነው። ይሁን እንጅ አገባቡ አሁንም በገላጭነት ነው። ሲገባም ከላይ በተራ ቁጥር (20) የተገለፀው ምሳሌ የሚከተለውን ይመሰላል።


[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው ካሳ መምጣቱን ሰማች] 24

በግልፅ እንደሚታየው፣ መሙሊያውም ሆነ ገላጩ አረፍተ ነገር ስማዊ ነው። ይሁን እንጅ፣ ሁለቱም ግሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ሲሆን፣ መዋቅሩ የሚከተለውን ይመሰላል።

(ሀ) [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች] 25
(ለ) ?[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች]

የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ትንሽ እጠራጣሪ ሊመስል ይችላል። ለዚህም ምክንያቱ የገላጩና የመሙሊያው አረፍተ ነገር ሞይ አንድ አይነት ቃል መሆኑ ነው። ከትርጉም አኩዋያ ሲታዩ፣ ልጆቹ እንደሄዱ እና ካሳ እንደመጣ ሰማች የሚሉት መዋቅሮች ሁለት ተከታታይ ድርጊቶችን ያመለክታሉ። ከምሳሌዎቹ ማንኛውም አይነት አረፍተ ነገር በመሙሊያነትም ሆነ በገላጭነት ሊገባ እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጅ፣ በአጠቃቀም ደረጃ፣ ገላጩ መዋቅር ግሳዊ ሆኖ መሙሊያው ስማዊ ቢሆን፣ አረፍተ ነገሩ የበለጠ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

የንዑስ ሀረጉን አወቃቀር በምሳሌ (22) እማከኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን።




እንደዚህ ያሉ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎች ቀደም ሲል እንዳየናቸው ካሉ ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ጋር ሲዋቀሩ በጣም ውስብስብ የሆነ አረፍተ ነገር ይፈጥራሉ። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

[[አስቴርን የስደበቻት ሴት] [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ [ካሳ መምጣቱን ሰማች]]] 27

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት [አስቴርን የስደበቻት ሴት] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው። ግሳዊ ሀረጉ [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ መምጣቱን

ሰማች] የሚለው ክፍል ነው። የሁለቱን አወቃቀር እንደሚከተለው እናሳያለን። የግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (26) በዝርዝር የሚታይ ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ በጥቅሉ ብቻ እናቀርበዋለን። ለግዊ ሀረጉን በዝርዝር እንመለከተዋልን።



በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሶስት ጥገኛ አረፍተ ነገሮች አሉ። እነዚህም በባለቤቱ ለማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ሰደበቻት በሚለው ግስ የሚመራው ገላጭ፣ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ፣ ሄዱ በሚለው ግስ የሚመራ ገላጭና፣ መምጣቱን በሚለው ሰም የሚመራው መሙሊያ አረፍተ ነገር ናቸው። አረፍተ ነገሩ ከዚህም የበለጠ ሊውስበስብ ይችላል። ይህን ባደረገ ቁጥር እየረዘመ ስለሚሄድ፣ ለማስታወስ ያስቸግራል። ስለዚህም የአያንዳንዱ አረፍተ ነገር የውስብስብነት ደረጃ በተጠቃሚው የማስታዎስ ችሎታ ይወሰናል። ከሰርዓት አንፃር ሲታይ ግን የማንኛውም አረፍተ ነገር መጠን ገደብ የለውም። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

> ትናንት በግ የሸጠው ነጋዴ ያመጣውን የሰንዴ ዳቦ የሰረቀውን ልጅ የገረፈችው ሴት አስቴር የምትሸጠውን የገብስ ጣላ ጠጥቶ አልከፍልም በማለት እየዛተ የሄደውን ረዥም ልጅ የሰደበችው ነች። 29

ይህ ከ(12) ግላዊና ከአንድ ሰማዊ ሀረግ በየደረጃው የተዋቀረ አንድ ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው። ከዚህም የበለጠ ሊረዝም ይችላል። ቢረዝምም መጠኑ ከአንድ አረፍተ ነገር አያልፍም። የሀረጎቹ መሪዎች የተስመረባቸው ቃላት ናቸው። ዋናው አረፍተ ነገር ነች በሚለው ግስ መሪነት ከተመሰረተው ግሳዊ ሀረግና ሴት በሚለው ለም መሪነት ከተዋቀረው ስማዊ ሀረግ የተቀናጀ ነው። በተራ መልኩ ሲቀመጥ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል።

[[.... ሴት] [.... ነች]] 30

ይህ እናት ወይም አቃፊ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ በሌሎቹ በተስመረባቸው ቃላት መሪነት በተመሰረቱት ሀረጎች አማካኝነት የተዋቀሩት አረፍተ ነገሮች በሙሉ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ አረፍተ ነገሮች ናቸው። አንዱ አረፍተ ነገር በሌላው አረፍተ ነገር ሀረግ ውስጥ እየገባ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ የሚሆንበት ለርዓት ነው። ይህን በዚህ እንተወውና ወደሌላ ጉዳይ እንሂድ። ከዚያ በፊት ግን በተራ ቁጥር (29) የተመከተውን አረፍተ ነገር ትንተና እንዲሞከሩት እንጋብዛለን።

አስካሁን ያየናቸው ውስብስብ ግላዊ ሀረጎች በቃላዊ ግስ መሪነት የሚዋቀሩ ናቸው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በምዕላድ መሪነት የሚዋቀሩ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችን ውስጣዊ ቅንጅት እንመለከታለን። ጉዳዩ በከፍል ሁለት፣ ስለ ቃላት ምስረታ ስንወያይ ካየነው ከአድራጊና ከአለደራጊ አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ጋር የሚያያዝ ነው። ያኔ አድራጊና አለደራጊ ምዕላዶች አንድ ግስ በሚፈልገው የመሙሊያ ሀረግ መጠን ላይ አስተዋፅዖ እንዳላቸው ገልፀን ነበር። ከዚያ አሳር፣ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ቡና ፈሳ 31
(ለ) አሰቴር ቡና አፈሳች
(መ) ካሳ አሰቴርን ቡና አሰፈሳት

ፈሳ የሚለው ኢሳቢ የድርጊት (ደራጊ) አምድ ነው። ኢሳቢ በመሆኑ መሙሊያ የለውም። ድርጊት ተቀባይ የሆነ ባለቤት ግን አለው። አሱም ቡና የሚለው ሰማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ኢሳቢ አምድ መነሻ ላይ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ኢሳቢና ደራጊ የነበረውን አምድ፣ ሳቢና አድራጊ ማድረግ ይቻላል። ሳቢ ግሰ ደግሞ የግድ መሙሊያ ይፈልጋል። ስለዚህም አምዱ ቡና ከሚለው ሰማዊ ሀረግ ጋር በምሳሌ (ለ) እንደሚታየው ሆኖ ይዋቀራል። አሰቴር የሚለው ሰም ለዚሁ አድራጊ ግሰ ባለቤት ሆኖ ይገባል። ከዚሁ ሳቢና አድራጊ አምድ መነሻ ላይ /አሰ-/ የሚለው ምዕላድ ሲጨመር፣ አድራጊ የነበረው አምድ አሰደራጊ ይሆናል። አሰደራጊ አምድ ሁለት መሙሊያ የግድ ይፈልጋል። ሰለዚህም አሰቴር የሚለውን ሀረግ በሁለተኛ መሙሊያነት ይወስድና በዚህ ሰም ፋንታ ባለቤት የሚሆን ሌላ ሰማዊ ሀረግ ይፈልጋል። በዚህም ምክንያት ካሳ የሚለውን ሰም በባለቤትነት ይወስድና በምሳሌ (መ) እንደሚታየው ያለ ውስብስብ አረፍተ ነገር ይመሰርታል። የምሳሌ (መ) ትርጉም፣

ካሳ አሰቴርን ቡና አንድታፈሳ (/ት-አፍኧሳ/) አደረገ 32

የሚል ነው።

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አንድታፈሳ በሚለው ላይ /አሰ-/ የሚል ምዕላድ የለም። በአሱ ፋንታ አደረገ የሚል ነባ ግሰ አለ። /አሰ-/ እና ይህ ግሰ አቻ ናቸው፣ ማለት ነው። ምክንያቱም በሁለቱ ምሳሌዎች፣ ማለትም በ31(መ) እና በዚህ ምሳሌ መካከል የትርጉም ልዩነት የለም። በሌላ አባባል፣ /አሰ-/ የሚለው አሰር ምዕላድና አደረገ የሚለው መደበኛ ግሰ በግብር አንድ ናቸው። ሁለቱም አሰደራጊ ናቸውና። የሚለያዩት በቅርፅ ብቻ ነው። ይኸውም አንደኛው አሰር ሲሆን፣ ሌላኛው ሙሉ ግሰ መሆኑና ከአሱ ጋር የሚዋቀረው አረፍተ ነገርም ሞይ ያለው መሆኑ ነው።


በአንፃሩ ካሳ አሰቴርን ቡና አሰፈሳት፣ የሚለው ተራ አንጅ ውስብስብ አረፍተ ነገር ላይመሰል ይችላል። ሞይ-አልባ መሆኑም ተራ ሊያሰኘው ይችላል። ዋናው መለኪያ ግን ሞይ አለሞኖሩ ሳይሆን፣ መዋቅሩን የሚመራው የግሰ መጠንና አይነት ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ መዋቅሩ የአንድ ደራጊና የአንድ አሰደራጊ አምድ ቅንጅት ነው። ርግጥ፣ በላዕላይ መዋቅር ሁለቱ አምዶች አንድ አካል ሰለሚሆኑና መዋቅሮቹም ሰለሚዋሀዱ ተራ አረፍተ ነገር ሊመሰሉ ይችላሉ[9]።

በዚሁ መንፈስ የምሳሌ 31(መ)ን ግሳዊ ሀረግ አቀነጃጀት በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን።

---

[9] ርግጥ፣ የቃላዊውን ግስና የምዕላዳዊውን ግስ ግንኙነት በአዕማድ ምስረታው ላይ ማየታችን ግልፅ ነው። በዚህም መስረት ምዕላዳዊ ግሶች መዋቅራዊ ቦታቸው ላይ ላይገኙ ይችላሉ። ለአቀራረብ ግልፅነት ሲባል ግን ከዚህ በታች በሚታየው መዋቅር (33) በቦታቸው ላይ እንዲታዩ ተደርጎአል።

33



ከዕፀ-መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ /አስ-/ የሚለው አስደራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው። [አስቴር...አ-ች] የሚለው አረፍተ ነገራዊ መመሪያ ነው። ሞይ የለውም፣ ስለዚህም ሞይ-የለሽ ንዑስ አረፍተ ነገር ልንለው እንችላለን። ሞይነቱ ለምዕላዳዊው ግስ ለ/አስ-/ ነው።

/አ-/ የሚለው አድራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው። አሱም [ቡና ፈላ] ከሚለው መመሪያ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህም አረፍተ ነገር [አስቴር...አ-ች] እንደሚለው መመሪያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውም። <u>ፈል-</u> የሚለው ግስ ባለቤት <u>ቡና</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ግሱ /አ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ሲዋሀድ፣ ቡና የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ የዚህ ውህድ ግስ ተላቢ ይሆናል። ውህዱ ግስ ባለቤት ያስፈልገዋል። ስለዚህም <u>አስቴር</u> የሚለውን ስማዊ ሀረግ ባለቤት አድርጎ በመውሰድ [አስቴር ቡና አፈላች] የሚለውን አድራጊ አረፍተ ነገር ይመሰርታል። <u>አፈላ</u> የሚለው ውህድ ግስ በተራው /አስ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ይዋሀድና /አስ-አ-ፈላ/ ይሆናል። /አስ-/ አና /አ-/ ተከታትለው ሲገኙ፣ /አ-/ ይገደፋል። ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግሱ [አስፈላ] የሚል ይሆናል።


<u>አስፈላ</u> የሚለው አስደራጊ ግስ ተላቢ ይፈልጋል። ስለዚህ <u>አስቴር</u> የሚለውን ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ አንደ ተላቢ አድርጎ ይወስድና፣ አንደ ማንኛውም ግስ ባለቤት የሚሆን አንደ <u>ካሳ</u> ያለ ሌላ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል።

<u>አደረገ</u> የሚለው ተራ አድራጊ ግስ ነው። /አስ-/ በሚለው አስደራጊ ምዕላድ አማካኝነት ድርብ አድራጊ ሊሆን ይችላል። በዚህን ጊዜ ቅርፁ <u>አስደረገ</u> የሚል ይሆናል። የዚህ ድርብ አድራጊ ግስ መዋቅራዊ ይዘት አንደሚከተለው ነው።

ካሳ አስቴርን ቡና እንድታፈላ አስደረጋት 34

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አራት ግሶች አሉ። አነሱም <u>ፈላ</u> ፣ <u>አ-</u> ፣ <u>አደረገ</u> አና <u>አስ-</u> ናቸው። <u>ፈላ</u> አና <u>አደረገ</u> መደበኛ ቃላዊ ግሶች ናቸው። <u>አ-</u> አና <u>አስ-</u> ምዕላዳዊ ግሶች ናቸው። ከምዕላድም አስር ምዕላድ ናቸው። በዚህም ቀደም ሲል ሰለ ምሰረታ ስንወያይ ካየናቸው ነአስር አምዶች ጋር ይመሳሰላሉ።

የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣ <u>ካሳ በአንድ ሌላ ሰው አማካኝነት አስቴር ቡና አንዲፈላ አንድታደርግ አደረገ</u> የሚል ነው። ከላይ አንደገለፅነው፣ አራት ግሶች ካሉ፣ አራት አረፍተ ነገሮች አሉ፣ ማለት ነው። አነዚህንም እንደሚከተለው እናሳያለን።


አነ
ስሀ
ግሀ
ስ
ግሀ1
ካሳ
አነ
ግ
አነ
ግ'ይ
አለ-(-አት)
ስሀ
ግሀ

ስ
ግሀ1
-
አነ
ግ
አነ
ሞይ
-ደረግ
ስሀ
ግሀ
እንሆ
ስ
ግሀ 1
አስቱር
አነ
ግ
አነ
ሞያ
ስሀ
ግሀ
ት-አ-
ስ
ግ
--
ቡና
ፈላ

ይህ በታህታይ መዋቅር የሚታየው አቀነጃጀት ሲሆን፣ በላዕላይ መዋቅር ውሰጥ፣ ፈሳ የሚለው አምድ ት-አ- ከሚለው አድራጊ ምዕላድ ጋር ይገናኝና ት-አ-ፈሳ ይሆናል። ይህም አንድ- ከሚለው ሞይ ጋር ተገናኝቶ አንድታፈሳ ይሆናል። በዚህ ግስ መሪነት የተመሰረተው ግሳዊ ሀረግ ባለቤትም አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ -ደረገ በሚለው ደራጊ ግስ መሪነት የተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ በግህድ ያልተጠቀሰውና ቦታው በነጠብጣብ የተመለከተው ነው። ደረገ የሚለው አሰር አምድ አሰ- ከሚለው ምዕላድ ጋር ተገናኝቶ አሰደረገ ይሆናል። /አሰ-/ የሚለው ምዕላድ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግሰ ሲሆን፣ ካሳ ደግሞ የዚሁ አረፍተ ነገር ባለቤት ነው። ርግጥ፣ አንደ /አሰ-/ ያለ ጥገኛ ምዕላድ እንዴት እንደ ግሰ ሊቆጠር ይችላል? የሚል ጥያቄ ማንላት ይቻላል። ዋናው መለኪያ፣ በቅርፁ አነባብ ምክንያት የሚከሰተው መዋቅራዊ ለውጥ ነው። በ/አ-/ እና በ/አሰ-/ ምክንያት፣ እንደ አስቴር ያለ፣ ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ ተሳቢ ይሆናል፣ ለባለቤትነት ደግሞ ሌላ ሀረግ አሰፈልጎአል። ስለዚህም ካሳ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል። አንድ ቅርፅ እንደዚህ ያለ መዋቅራዊ ለውጥ የሚያሰከትል ከሆነ፣ ጥገኛም ይሁን ነፃ፣ መዋቅራዊ ቦታ ይሰጠዋል። ቦታውም ከላይ እንደሚታየው የግሰ ነው።

ምሳሌ (34) አሻሚ ነው። አሻሚነቱ አስቴር በሚለው ስማዊ ሀረግ ሚና ላይ ነው። ሀረጉ አድራጊ ወይም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን ይችላል። ዕፀ መዋቅር (35) የሚያሳየው፣ ሀረጉ አድራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ ነው። ተደራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ፣ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም አስቴር ቡና እንዲፈላ አንድታደርግ ተደረገች የሚል ይሆናል። መዋቅሩም ተገብሮአዊ ነው። ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ በተራ ቁጥር (35) ከሚታየው ጋር አንድ ነው። አደረገ የሚለው ግሰ ተ-ደረገ የሚል የተደራጊ አምድ ቅርፅ ይይዛል። /አሰ-/ ከሚለው አሰደራጊ ምዕላድ ጋር ሲገናኝ፣ ግሱ /አሰ-ተ-ድ'ርር'ሽግ-/ የሚል ይሆናል። ቁዋንቁዋው የአሰደራጊና የተደራጊ ምዕላድ ክትትሎሽን ስለማይፈቅድ፣ የተደራጊው ምዕላድ /-ተ-/ ይገደፋል። ይህ ሲሆን አሰደረገ የሚለውን ላዕላይ ትርፅ አናገኛለን። ይህ ቅርፅ ነው፣ አሻሚ የሆነው።


ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ ደግሞ እንመልከት።

ካሳ አስቴርን አሰደባት 36

ይህ አረፍተ ነገር አሻሚ ነው። ከትርጉም አንፃር፣ አስቴር ሰዳቢ ወይም ተሰዳቢ ባለቤት ልትሆን ትችላለች። ርግጥ፣ በቅርፅ ደረጃ አስቴር የሚለው ስም /-ን/ የሚለውን የተላቢ ምዕላድ ስላስከተለ፣ ተሳቢ ብሎም ተደራጊ ስም ነው፣

ይባል ይሆናል። ከዚህ አኳያ ሲታሰብ፣ ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ የሚከተለው ይመስላል።

37



ከዚህ ላይ ግሱ ላቢ ስለሆነ፣ <u>አለቴር</u> የሚለውን ስም በተላቢነት ይዞአል። ግሱ ተደራጊ ስለሆነና የባለቤቱ ቦታም ክፍት ስለሆነ፣ <u>አለቴር</u> የሚለው ስም ከተሳቢ ቦታው ተነስቶ ከፍት ወደሆነው የባለቤት ቦታ ይሄዳል። <u>ተሰደብ-</u> የሚለው ተደራጊ

ግስ /አስ-/ ከሚለው ምዕላድ ጋር ሲገናኝ /አስ-ተሰደብ-አት/ ይሆናል። ቀደም ሲል አንዳየነው፣ የአስደራጊው ምዕላድ /አስ-/ እና የተደራጊው (የተገብሮው) ምዕላድ /ተ-/ ሲከታተሉ፣ /ተ-/ ትገደፋለች። ባጭሩ የማንኛውም አስደራጊ አረፍተ ነገር ታህታይ ቅርፅ ገቢር ወይም ተገብሮ ሊሆን ይችላል፤ ብሎ መደምደም ይቻላል። የአሻሚነቱም ምክንያት ይኸው ነው።

በግልፅ አንደሚታየው፣ የሞዩ ቦታ ክፍት ነው። ይህም የሚሆነው አረፍተ ነገሩ የ/አስ-/ መሙሊያ ሆኖ በሚገባበት ጊዜ ነው። <u>አደረገ</u> የሚለው መደበኛ (ነፃ) ግስ መሙሊያ ሆኖ ሲገባ፣ የሞዩ ቦታ <u>አንድ</u>[10] በሚለው ሞይ ይሸፈናል። ይህም አንደሚከተለው ሲሆን ነው።

[ካሳ [አስቴርን ሰው <u>አንድ</u>ትስድብ] አደረጋት] 38

ከዚህም ግሱ ቃላዊው <u>አደረገ</u> ሳይሆን፣ ምዕላዳዊው /አስ-/ በሚሆንበት ጊዜ፣ መሙሊያው አረፍተ ነገር ሞይ አይኖረውም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ቃላዊና ምዕላዳዊ ግሶችም በመሙሊያ አረፍተ ነገራቸው ይለያሉ። የምዕላዳዊ ግሶች መሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውምና።

በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ነው። ይሁን እንጅ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ይኸው አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ የዚሁ አቃፊ አረፍተ ነገር ባለቤት ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል።

[አስቴር [— ሰው አንድትስድብ] ተደረገች] 39

አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ መስረታዊ (ታህታይ) ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው። ይህም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ ነው። ከዚህ ቦታ ተነስቶ ወደ አቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በመውጣት [ሰው አንድትስድብ ተደረገች] ስሚለው ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ሊሆን ችሎአል። ይህ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል፣ <u>ይመስላል</u> ስለሚለው ግስ ባህሪ ስንወያይ ያስተዋልነውን ሊያስታውስን ይገባል። ያኔ የአንድ አቅፍ አረፍተ ነገር ባለቤት

[10] ሞዩ <u>አንድ</u> የሚሆነው፣ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ግስ የካልዓይ አንቀፅ ሲሆን ነው። ግሱ የቀዳማይ አንቀፅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሞዩ <u>አንደ</u> ይሆናል። ምሳሌ፣
(ሀ) ካሳ ብርጭቆ <u>አንደ</u> ሰበረ ሰማሁ
(ለ) ካሳ ብርጭቆ <u>አንዲሰብር</u> (/አንደ-/ይ-ስእብር/) አዘዘኩ

የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤትም ሊሆን እንደሚችል አይተን ነበር። ከዚህ ላይ የምናየውም ይህንኑ ሁኔታ ነው።

ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) [---]አስቴር ቡና እንድታፈላ] ይደረጋል (/ይ-ት-ድ‿ርር‿ግ-ኣልል/)] 40
[ይድድ‿ርር‿ግኣልል]

(ለ) [አስቴር]--- ቡና እንዲታፈላ] ትደረጋለች (/ት-ት-ድ‿ርር‿ግ-ኣልል-ች/)]
[ትእድድ‿ርር‿ግኣልልች]

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ይደረጋል</u> የሚለው የተገብሮ ግስ ባለቤት በግሀድ አይታይም። /ይ-/ ከሚለው አፀፋ ብቻ ስለተኛ መደብ መሆኑን መለየት ይቻላል። በግሀድ የማይከሰተው፣ ባለቤቱ መደበኛ ተውላጠ ስም ሳይሆን፣ ቀደም ሲል የይለሙላ ባለቤት ያልነው፣ <u>it</u> የሚለው ተውላጠ ስም በመሆኑ ነው። በአማርኛ፣ ይህ ተውላጠ ስም መደበኛ ቅርፅ አንደሌለውና ከላይ አንደሚታየው፣ በአፀፋ ብቻ እንደሚጠቀስ ቀደም ሲል ገልፀናል። ባለቤት ሆኖ የሚገባውም አንደ <u>ይመስላል</u> ላለ የሁኔታ ግስ እና እንደ <u>ይደረጋል</u> (ይ-ት-ደረጋል) ላሉ ተደራጊ ግሶች ነው።

እንደነዚህ ያሉ ግሶች መሰረታዊ ባህሪ አድራጊ ባለቤት አለመፈለግ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል። ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ የነዚህ ግሶች ባለቤት ቦታ ክፍት (-) ይሆናል። በላዕላይ መዋቅር፣ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤት የግድ ማግኘት አለባቸው። በቅርባቸው ሙሉ ሆነው መገኘት አለባቸውና። ባለቤት ሊሆን የሚችለው ደግሞ አንድም የይለሙላው ተውላጠ ስም፣ ማለትም <u>it</u> ፣ አለያም የአቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የሆነው ስማዊ ሀረግ ነው። የይለሙላው ተውላጠ ስም ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ምሳሌ 40(ሀ)ን እናነፃፅር። የዚህ አረፍተ ነገር ግስም <u>ይደረጋል</u> የሚል ነው። የአቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ 40(ለ)ን እናነፃፅር። ይህ ሲሆን ደግሞ፣ ግሱ <u>ት-ደረጋለ-ች</u> ይሆናል። ግሱ የለስተኛ መደብ፣ አንስታይ ያታ ምዕላድ የሆነችውን /ት-/ እና /-ች/ን ያሳያል። ከዚህም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ በርግጥ <u>አስቴር</u> የሚለው የለስተኛ መደብና የአንስታይ ያታ ስም መሆኑ ግልፅ ነው።

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን ዋናው ጉዳይ፣ በተደራጊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ ባለቤት ስማዊ ሀረግም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን የሚችል መሆኑን ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል ስለ ተራ ተደራጊ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ በታህታይ መዋቅር ተሳቢ የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ በላዕላይ መዋቅር ባለቤት ሲሆን አይተናል። ይህ ሁኔታ የሚታየው ግን በተራ

አረፍተ ነገሮች መዋቅር ነው። አረፍተ ነገሮቹ ውስብስብ ሲሆኑ፣ የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የነበረው ስማዊ ሀረግ የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ይሆናል። እንደ አቃፊው ግስ አይነትም፣ ባለቤቱ አድራጊ ወይም ተደራጊ ይሆናል። ተደራጊ የሚሆነው በምሳሌ 40(ለ) እንደሚታየው፣ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

ስለ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። ግሶች አረፍተ ነገራዊ ከሆነ መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ (ገላጭ) ጋር ሲዋቀሩ፣ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግን ይመሰርታሉ። መሙሊያው እና/ወይም አጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ወይም ስማዊ ሊሆን ይችላል። ግሳዊ አረፍተ ነገር ምን ጊዜም ውሱን ነው። የባለቤት፣ የተሳቢ ወይም የመሰተዋድድ አፀፋ ይኖረዋል። እንደ /-አልል/ ያሉ ጊዜን የሚያመለክት ምዕላድም ይኖረዋል። ሰማዊ ከሆነ ውሱን ወይም ኢውሱን ሊሆን ይችላል። ውሱን ስማዊ አረፍተ ነገር ባለቤቱን ብቻ የሚጠቁም አፀፋ ይኖረዋል። ጊዜን የሚያሳይ ምዕላድ ግን አይኖረውም። ጊዜው የሚወሰነው በአቃፊው አረፍተ ነገር የጊዜ አይነት ነው።

የግሳዊ ሀረግ የውስብስብነት ደረጃ እንደ መሙሊያው እና/ወይም አጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ ይለያያል። የመሙሊያው እና/ወይም የአጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ ውስብስብ ከሆነ፣ ዋናው ግሳዊ ሀረግ በጣም ውስብስብ ይሆናል። ከእንደዚህ አይነት ግሳዊ ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ውስብስብ ይሆናል።

የግሳዊ ሀረግ መሪ ቃላዊ ወይም ምዕላዳዊ ሊሆን ይችላል። ምዕላዳዊ የሚሆነው ግሳዊ ሀረጉ አስደራጊ ሲሆን ነው። በዚህን ጊዜ ሀረጉ /አ-/ ወይም /አስ-/ በሚለው አስደራጊ ምዕላድ መሪነት ይዋቀራል። በነዚህ መሪነት የሚዋቀረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መሙሊያ አረፍተ ነገራዊ ነው። ይሁን እንጅ ሞይ የለውም። በቃላዊ ግስ መሪነት የሚዋቀር ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ፣ ሞይ አለው። ሞዩም <u>እንደ</u> የሚለው ምዕላድ ነው። አስደራጊ ግሳዊ ሀረግ በአድራጊ ወይም በተደራጊ ግስ መሪነት ሊዋቀር ይችላል። የተደራጊ ምዕላድዋ ከአስደራጊው ምዕላድ ቀጥላ ስትገባ ትገደፋለች። በዚህ ምክንያት ሀረጉ አሻሚ ይሆናል። አሻሚነቱን ስማስወገድ በአስደራጊው ምዕላድ፣ ግለትም በ/አስ-/ ፋንታ <u>አደረገ</u> የሚለውን ቃላዊ አስደራጊ ግስ መተካት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን የተደራጊዋ ምዕላድ የሆነችው /ተ-/ በግሀድ ትታያለች፣ እናም አስደራጊው ግሳዊ ሀረግ ተደራጊ መሆኑ ይታወቃል። ወደሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እንሂድ።

ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ

አንደ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ሁሉ፣ ቅፅላዊ ሀረጎችም ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚወሳሰቡትም ከአረፍተ ነገሮች ጋር እየተቀናጁ አቢይ ሀረጋቸውን ሲመሰርቱ ነው። ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥሰን እንመለከታለን። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንይ።

(ሀ) ከአስቴር የበለጠ ወፍራም 1
(ለ) ከካሳ የባሰ አሞር

እነዚህ ቅፅላዊ ሀረጎች ናቸው። ለለሆኑም እንደ ማንኛውም ቅፅል በስማዊ ሀረግ ውሰጥ ከመሪው ስም እየቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ። ይህም እንደሚከተለው ነው።


[ከአስቴር የበለጠ ወፍራም] ሴት 2

በግልፅ እንደሚታየው፣ [ከአስቴር የበለጠ ወፍራም] የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ፣ <u>ሴት</u> የሚለውን ስም ቀድሞ በግላጭነት ገብቶአል። ይህ አይነተኛ የቅፅል አገባብ ነው። [ከአስቴር የበለጠ ወፍራም] የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ መሪ [ወፍራም] የሚለው ቅፅል ነው።

[ከአስቴር የበለጠ] 3

የሚለው ከፍል <u>ወፍራም</u> የሚለው ቅፅላዊ መሪ አነላማሽ ሲሆን፣ ተግባሩም ንፅፅርን ማሳየት ነው። ንፅፅሩ በአስቴርና በሴላ ባልተጠቀሰ ሰው መካከል ሲሆን፣ ማነፃፀሪያው ውፍረት ወይም ወፍራም መሆን ነው። [ወፍራም] የሚለው የሀረጉ መሪ <u>ወፈረ</u> የሚል ሁኔታን የሚገልፅ አቻ ግሰ አለው። አንድ ሰው የሚያደርገውን ሳይሆን፣ የሚሆነውን የሚያመለክት ለለሆነ፣ የሁነት ግሰ እንደሚባል ባለፈው ከፍል ገልፀናል። እንደዚህ ያሉ ግሶች በሙሉ መሙሊያ የላቸውም። አላቸው ከተባለ፣ መሙሊያ ሊሆን የሚችለው ራሱ ሁዋኙ ስማዊ ሀረግ ነው። ለለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚያዋቅሩት ብቻቸውን እንደ ምሰሶ እየቆሙ ነው። ከአነሱ ጋር አቻ ዝምድና ያላቸው ቅፅሎችም እንደዚሁ መሙሊያ ለለሌላቸው፣ ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት ብቻቸውን ነው። አንድ ግሰ መሙሊያ የሌለው ከሆነ፣ ከእሱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ቅፅሎችና ለሞችም እንደዚሁ መሙሊያ አይኖራቸውም። መሙሊያ የመያዝ ወይም ያለመያዝ በአንድ ከፍል ብቻ የሚወሰን ባህሪ ሳይሆን ተዛማጅ ነው።

በአቢይ ሀረግ ደረጃ [ወፍራም] የሚለው መሪ ቅፅል ከንፅፅራዊ አረፍተ ነገሮች ጋር ሊዋቀር ይችላል። የአወቃቀሩ ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን።



ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ንፅፅራዊ አረፍተ ነገር [ወፍራም] ከሚለው ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ጋር በአጎላማሽነት ተዋቅሮአል። ጥገኝነቱን የምታመለክተው /የ/ ስትሆን፣ እስዋም እንደተለመደው አረፍተ ነገሩን ተከትላ በሞዩ ስር ትገኛለች።

ከዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል። ይኸውም በስማዊና በቅፅላዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ የግሳጭም ይሁን የመሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ አንድ

አይነት መሆኑን ነው። በሁለቱም ውስጥ ሞዩ /የ/ ሲሆን፣ አገባቡም ከላይ እንደተገለፀው አረፍተ ነገሩን አየተከተለ ነው። ይህ ሞይ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ካየናቸው ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ሞይ በከፊል የተለየ ነው። እንደምናስታውሰው፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ያየናቸው የመሙሊያና የአጎላማሽ አረፍተ ነገር ሞዮች በአብዛኛው መለተዋድዶች (በጥንቱ አጠራር መስተፃምሮች) ናቸው። በአብዛኛው የምንልበት ምክንያት፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ <u>ይመለላል</u> የሚለው ግስ መሙሊያ አረፍተ ነገር /የ/ የሚል ሞይ ስላለው ነው።

ስማዊ ሀረጎችና ቅፅላዊ ሀረጎች የሚመላለሱበት ሌላም ባህሪ አለ። ይኸውም የሁለቱም መሙሊያዎች ሊቀሩ የሚችሉ መሆናቸው ነው። በዚህም ባህሪያቸው ከግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ይለያሉ። ምክንያቱም የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ሊቀር አይችልምና። ሊቀር የሚችለው አጎላማሹ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የማንኛውም አጎላማሽ ሀረግ ባህሪ ነው። የቅፅላዊና የስማዊ ሀረግ አጎላማሽ አረፍተ ነገር ምን ጊዜም ግሳዊ ነው። በዚህም ስማዊ ከሆነ አጎላማሽ አረፍተ ነገር ጋር ሊዋቀር ከሚችለው፣ ከግሳዊ ሀረግ ይለያሉ። ወደ ዕፀ-መዋቅሩ እንመለስ።

የንዕዕራዊው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አንደማይታይ አንገነዘባለን። ቦታው ስነጠብጣብ የተሸፈነው ነው። በግሱ ላይ ግን /-ኧ-/ በሚለው አፅፋ ተጠቅሰአል። ከዚህም ይዙቱ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ያታ መሆኑን አንረዳለን። ይህ ባለቤት፣ ቅፅላዊው ሀረግ በመሙሊያነት ከገባበት ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ ማለትም <u>ካሳ</u> ከሚለው ስም ጋር በትርጉም አንድ ነው። ተነፃፃሪው ስማዊ ሀረግም እሱው ነው። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) [[ካሳ] [[[--- ከአስቴር የበለጠ] ወፍራም] ነው]] 5
(ለ) [[አስቴር] [[[--- ከእኔ የበለጠች] ቀጭን] ነች]]

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ነው</u> በሚለው ግስ መሪነት የተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ <u>ካሳ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። [ከአስቴር የበለጠ] የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ባለቤትም እሱው ነው። በጥገኛው አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ ሊከሰት ያልቻለው በሁለት ምክንያት ነው። አንደኛው፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ በአፅፋ መጠቀሱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ጋር በቅርፅም ሆነ በትርጉም አንድ መሆኑ ነው። ይህ ባለቤት በግሀድ ቢታይ ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ፣

[ካሳ [[ካላ ከአስቴር የበለጠ] ወፍራም] ነው] 6

የሚል ድግግሞሽ የሚታይበት መዋቅር ይሆን ነበር። ቀደም ሲል፣ ቁጥጋጥ የማያሰፈልግ ድግግሞሽን እንደማይፈቅድ ገልፀናል። ለዚህም ነው፣ የጥገኛው አረፍተ ነገር ባለቤት የሆነው <u>ካሳ</u> በግሀድ ሲከሰት ያልቻለው።

በሁለተኛው ምሳሌ፣ ግለትም በ5(ሀ) ውስጥ የሚታየው ሁኔታም እንደዚሁ ነው። አስቴር የሚለው ሰማዊ ሀረግ የእቅፉም (ጥገኛው) ሆነ የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ነው። በሁለቱም አረፍተ ነገሮች ግሶች ላይ [-ች] በሚል የባለቤት አፀፋ ተጠቅሶአል። ከፍ ሲል የጠቀስነው የድግግሞሽ ችግር እንዳይከሰት፣ በእቅፉ አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ ከመከሰት ታቅቦአል። ከዚህም ሁኔታ የእቃፊና የእቅፍ አረፍተ ነገር ባለቤት አንድ ሲሆን፣ በግሀድ ከመከሰት የሚታቀበው የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

የንፅፅራዊ አረፍተ ነገር ግሶች የተወሰኑ ናቸው። የሚወሰኑትም በሚገልፁት የንፅፅር መጠን ነው። ንፅፅሩ እኩልነትን፣ በላጭነትን እና ተበላጭነትን ያሳያል። ግሶቹም እነዚህን ተግባራት የሚገልፁ ናቸው። በተራ አረፍተ ነገር ሲገለፅ፣ ንፅፅሩ የሚከተለውን ይመስላል።

(ሀ) ካሳ አስቴርን ያክላል 7
(ለ) ካሳ ከአስቴር ይበልጣል
(መ) ካሳ ከአስቴር ያንሳል

የመጀመሪያው ምሳሌ እኩልነትን፣ ሁለተኛው በላጭነትን፣ ሶስተኛው ደግሞ ተበላጭነትን ያሳያል። ግሶቹ ውሱን የሆኑት፣ ንፅፅሩ ውሱን በመሆኑ ነው። ቀደም ሲል እንዳመለከትነው፣ እንደዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች፣ በእነዋሪነት ከቅፅላዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀሩ፣ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

(ሀ) አስቴርን የምታክል ወፍራም 8
(ለ) ከአስቴር የበለጠች ወፍራም
(መ) ከአስቴር ያነሰች ወፍራም

በግልፅ እንደሚታየው፣ ቅፅሎቹ ከንፅፅራዊ አረፍተ ነገሮች ጋር ተዋቅረው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ መስርተዋል። ቅንጅታዊ ሰርዓታቸው በተራ ቁጥር (4) ላይ የተመለከተ ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ አንደግመውም።

ንፅፅራዊ መስተዋድዶቹ /ከ/ እና /-ን/ ናቸው። የመጀመሪያው አበላላጭ ሲሆን፣ ሁለተኛው አደላዳይ፣ ግለትም እኩልነትን አመልካች ነው። ከዚሁ ተግባራቸው በመነሳት አበላላጭና አደላዳይ መስተዋድዶች ልንላቸው እንችላለን።

አደላዳዩ አረፍተ ነገር፣ በተራ መስተዋድዳዊ ሀረግነት ሊከሰት ይችላል። በዚህን ጊዜ መስተዋድዱ <u>አንደ</u> ይሆናል። ስለዚህም <u>አስቴርን የምታክል</u> የሚለው አደላዳይ አረፍተ ነገር፣ <u>አንደ አስቴር</u> የሚል አደላዳይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይሆናል። ከቅፅሉ ጋር ሲገባም <u>አንደ አስቴር ወፍራም</u> የሚል ይሆናል። ከዚህ ላይ አስቴር የሚለውን ስም ተከትሎ የገባው /-ን/ መስተዋድድ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። መስተዋድድ በመሆኑ፣ <u>አንደ</u> የሚለው ሌላ መስተዋድድ ከስሙ ቀድሞ ሲገባ፣ /-ን/ ይጠፋል።

የውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ ግንኙነት ከስማዊ ወይም ከግሳዊ ሀረግ ጋር ነው። ከስማዊ ሀረግ ጋር በተላጭነት፣ ከግሳዊ ሀረግ ጋር በመሙሊያነት እንደሚከተለው ይገባሉ።

(ሀ) ካሳ [[ከአስቴር የበለጠች ወፍራም] ሚስት] አለችው 9
(ለ) ካሳ [[ከእኔ የበለጠ] ወፍራም] ነው

በመጀመሪያው ምሳሌ [ከአስቴር የበለጠች ወፍራም] የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ሚስት የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ገላጭ ነው። ቅፅላዊ ሀረጉ ውስብስብ ስለሆነ፣ ስማዊ ሀረጉም ውስብስብ ሊሆን ችሏል። ቅፅላዊ ሀረጉ ተራ ሲሆን፣ ባለፈው ክፍል ስለ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ ስማዊ ሀረጉም አንደዚሁ ተራ ይሆናል። በዚህን ጊዜ፣

[ከአስቴር የበለጠች ወፍራም ሚስት] 10

የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ፣

[ወፍራም ሚስት] 11


የሚል ተራ ቅፅል ብቻ የሚተነበት ስማዊ ሀረግ ይሆናል።

በሁለተኛው ምሳሌ (9ለ) ውስጥ፣ [ከእኔ የበለጠ ወፍራም] የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ <u>ነው</u> የሚለው የመሆን ግስ መሙሊያ ሆኖ ገብቶአል። በዚህም ምክንያት፣ <u>ነው</u> የሚለው ግስ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ችሏል። ቅፅላዊ ሀረጉ ውስብስብ ባይሆን ኖሮ፣ ግሳዊ ሀረጉ ውስብስብ ላይሆን፣

[ወፍራም ነው] 12

የሚል ተራ ግሳዊ ሀረግ ይሆን ነበር።

በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የተመለከትነው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ከስማዊ ሀረጉ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነት እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ - መዋቅር እናሳያለን።



[11] በታህታይ መዋቅር፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ቀኝ መሪ መሆናቸውን ልናስታውስ ይገባል። መስተዋድዱ ድጋፍ ስለሚፈልግ ከመሙሊያው ስም መነሻ ላይ የሚቀጠለው በላዕላይ መዋቅር ነው። ተለጣፊነት የለው ብቻ ላይሆን፣ የአቅመ ቢስ ምዕላዶችም ባህሪ ነው።

አንደዚህ ካሉ ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረጎች የሚዋቀር አርፍተ ነገር ውስብስብ ነው። የውስብስብነቱ ደረጃ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፣ ስማዊ ሀረጉ ብቻ ውስብስብ የሆነበት አረፍተ ነገር፣ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎቹ ውስብስብ ከሆኑበት አረፍተ ነገር ያነስ ውስብስብ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን እንመለከት።

[ገነት[ካሳ ያገባት[ሴት [ከአስቴር የበለጠች[ወፍራም[እንደሆነች[ታውቃለች]]]]]]] 14

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አንድ ውስብስብ ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ አንድ ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ እንዲሁም አንድ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ አለ። ሁሉም የሚገኙት <u>ታውቃለች</u> ስሚለው ግስ መሙሊያ ሆኖ በገባ አረፍተ ነገር ውስጥ ነው። ሀረጎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

(ሀ) ካሳ ያገባት ሴት 15
(ለ) ከአስቴር የበለጠች ወፍራም
(መ) ... እንደሆነች

<u>ካሳ ያገባት ሴት</u> የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ <u>ሆነች</u> በሚለው ግስ ስሚመራው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው። <u>ከአስቴር የበለጠች ወፍራም</u> የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ ደግሞ የዚሁ <u>ሆነች</u> የሚለው ግስ መሙሊያ ነው። ግሱና መሙሊያው ተዋቅረው፣

ከአስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች 16

የሚለውን ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል። <u>ካሳ ያገባት ሴት</u> የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ፣ የዚህ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው። ሁለቱ ሲቀናጁ፣

ካሳ ያገባት ሴት ከአስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች 17

የሚለውን መሙሊያ አረፍተ ነገር አናገኛለን። መሙሊያነቱ <u>ታውቃለች</u> ለሚለው ግስ ነው። ግሱ ከዚህ መሙሊያ ጋር ሲዋቀር የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ ያገባት ሴት ከአስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች ታውቃለች 18

<u>ገነት</u> የሚለው ስም የዚህ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው። ሁለቱ ሲዋቀሩ፣ በተራ ቁጥር (14) የተመለከተውን ውስብስብ አረፍተ ነገር አናገኛለን። ከዚህ በላይ

ባየነው ትንታኔ መሰረት የዚህኑ አረፍተ ነገር አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር ለማሳየት እንዲሞክሩ እያደፋፈርን ወደሚቀጥለው እንሂዳለን፡፡

ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረግ

ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከመስተዋድዳዊ መሪና ከውስብስብ ሰማዊ ሀረግ ይዋቀራሉ፡፡ ውስብስብ ሰማዊ ሀረግ የሚባሉትን ቀደም ሲል እይተናቸዋል፡፡ ገላጭ አዛማጅ አረፍተ ነገር እና/ወይም ሞይ አረፍተ ነገር ያላቸው ናቸው፡፡ የሚከተሉትን አንመልከት፡፡


(ሀ) ትናንት ለመጣው ልጅ 1
(ለ) ስለ ካሳ ቤት የመሸራት ዓላማ

እነዚህ ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መሪያቸው ለ እና ስለ የሚሉት መስተዋድዶች ናቸው፡፡ በተራ መስተዋድዳዊ ሀረግ መልክ ሲገኙ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

(ሀ) ለልጅ 2
(ለ) ስለ ዓላማ

በምሳሌ 1(ሀ) ልጅ የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ገላጭ አለው፡፡ ገላፊዉም ትናንት የመጣው የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ በምሳሌ (ለ)፣ ዓላማ በሚለው ስም መሪነት የተዋቀረው ስማዊ ሀረግም እንደዚሁ መሙሊያ ነው፡፡ መሙሊያነቱ ስለ ለሚለው መስተዋድድ ነው፡፡ መሙሊያው ሰማዊ ሀረግም በውስጡ የራሱ መሙሊያ አረፍተ ነገር አለው፡፡ እሱም የካሳ ቤት የመሸራት የሚለው መዋቅር ነው፡፡

የየሀረጎቹን ውስጣዊ አቀነጃጀት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡




ገላጩ አረፍተ ነገር አዛማጅ ነው። የተዛመደው ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው። ለለሆነም ቦታው በነጠብጣብ ተሸፍኖአል። የተዛመደ ሀረግ በግሀድ ሊከሰት አይችልምና። ይዘቱ በአዛማጁ ግስ ላይ ከሚታየው አፀፋና ከስማዊ ሀረጉ መሪ፣ ማለትም ልጅ ከሚለው ስም፣ ይታወቃል። አዛምጁ ሀረግ የተዋቀረው ከንዑሱ

[12] ቀደም ሲል እንደተገለፀውና መስተዋድዳዊ ሀረጎች ቀኝ መሪ ናቸው ብለን፣ ባጠቃለልነው መሰረት፣ ከዚህ ላይም መስተዋድዳዊው መሪ በስተቀኝ መገኘት እንዳለበት እናምናለን። ቢሆንም ለቀላል አቀራረብ ስንል መሪውን በግራ በኩል አስቀምጠነዋል።

ስማዊ ሀረግ ጋር ሲሆን፣ የሚመሰርተውም አቢዩን ስማዊ ሀረግ፣ ግስትም (ስሀ2) ነው። ይህ አይነተኛ የነላጭ አረፍተ ነገር መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ከንውስ ሀረግ ጋር እየተዋቀሩ አቢይ ሀረግ ይመሰርታሉ።

<u>ስለ</u> የሚለውን መስተዋድድና የመሙሊያውን አረፍተ ነገር መዋቅራዊ አገባብ ከዚህ ቀጥለን በዕፀ መዋቅር አናሳያለን።



በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>የክሳ ቤት የመሰራት</u> የሚለው ሰማዊ አረፍተ ነገር፣ <u>ዓላማ</u> ስሚለው መሪ ስም መሙሊያ ሆኖ፣ ንዑሱን ሰማዊ ሀረግ (ስሀ1)ን መስርቶአል። አረፍተ ነገሩ ሰማዊ ነው። መሪው <u>መሰራት</u> የሚለው የድርጊት ስም ሲሆን፣ እይነቱ ደግሞ ኢውሱን ነው። በመሆኑም ሰማዊ ሀረጉን፣ ማለትም <u>ካሳን</u>፣ የሚጠቅስ አፀፋ የለውም። ስለዚህም፣ ባለቤቱ በግሀድ ሊከስት የቻለው /የ/ የምትለዋን የዘርፍ ምዕላድ በማሰቀደም ነው። ይህን ቀደም አድርገን ስለ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ስንወያይ ያየነው ስለሆነ፣ እዚህ ላይ ብዙ አንገባበትም።

በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። ያተኮርነው በውስብስብ አረፍተ ነገር ላይ ነው። ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ከውስብስብ ሀረጎች ይዋቀራሉ። ውስብስብ ሀረጎች አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ (ገላጭ) ያላቸው ናቸው። ከዚህ አኳያ ውስብስብ የሆነ ሰማዊ፣ ግሳዊ፣ ቅፅላዊና መለተዋድዳዊ ሀረጎችን ተመልክተናል። በሁሱም ውስጥ፣ አረፍተ ነገሮች መሙሊያ እና አጎላማሽ (ገላጭ) እየሆኑ በጥገኝነት ሲገቡ አይተናል። አረፍተ ነገሮቹ ሰማዊና ግሳዊ ናቸው። ግሳዊ አረፍተ ነገሮች ውሱን ናቸው። ጊዜን፣ ባለቤትን እና መለተዋድዳዊ ሀረግን የሚያመለክቱ ምዕላዶች አሉዋቸው። ሰማዊ አረፍተ ነገሮች ውሱን ወይም ኢውሱን ሊሆኑ ይችላሉ። ውሱን ሰማዊ እረፍተ ነገሮች የባለቤት አፀፋ ብቻ አላቸው። ኢውሱን አረፍተ ነገሮች ምንም አፀፋ የላቸውም። ስለዚህም ባለቤታቸው አንድም በግሀድ ሊከስት አይችልም፣ ከተከለተም /የ/ የምትለዋን የዘርፍ ምዕላድ መያዝ አለበት። በግሀድ በማይከስትበት ጊዜ፣ ይዘቱ ከአቃፊው (እናት) አረፍተ ነገር ባለቤት ይዘት ለታወቅ ይችላል። ይህም በተወሰኑ መዋቅሮች ብቻ ነው።

በሰማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ ገላጭ እረፍተ ነገሮች አዛማጅ፣ በቅፅላዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮች አነፃፃሪ ሲሆኑ፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ ያግሞ አንደ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ወዘተ፣ ያሉ የተለያዩ ተውላከ ግሳዊ ተግባራትን የሚገልፁ እረፍተ ነገሮች ናቸው። ከአገባባዊ ባህሪያቸው በመነሳት፣ ገላጭ አረፍተ ነገሮችን ተውላከ ግሳዊ፣ ተውላከ ሰማዊ፣ ተውላከ ቅፅላዊ ልንላቸው እንችላለን። ይህን ክፍል በሚቀጥለው ውስብስብ አረፍተ ነገር እንለናበታለን።

> አስቴር [ትናንት በግ የሸጠላት ነጋዴ] [ክፉኛ ለላታስላት] [ከማንም የበለጠ አጭበርባሪ] መሆኑን [ሰፖሊለ በሰጠችው ቃል] አረጋግጣለች 5

በቅንፍ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች እንደ ቅደም-ተከተላቸው ውስብስብ ሰማዊ ሀረግ፣ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ፣ ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ እና ውስብስብ መለተዋድዳዊ ሀረግ ናቸው። አረፍተ ነገሩ ክዚህም የበለጠ ሊውስበስብ ይችላል። ትንታኔውን በዕፀ - መዋቅር ስማሳየት ይሞክሩ።

ውስብስብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር

ባለፉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች፣ ስለ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ተወያይተናል። ተራ አረፍተ ነገሮች ከተራ ሀረጎች፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ከውስብስብ ሀረጎች እንዴት እንደሚዋቀሩ በዝርዝር ለማየት ሞክረናል። በዚህ ንዑስ ክፍል ደግሞ ባለፈው ካየናቸው ለየት ያሉ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንመረምራለን። ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ግን ምናልባት ስለ አረፍተ ነገር ተግባር አንዳንድ ተጨማሪ ነጥቦችን እንደገና ማንሳቱና ግልፅ ማድረጉ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም። ርግጥ ጉዳዩን ቀደም ሲልም በመጠኑ አንስተነዋል። መድገሙ ጉዳት የለውም።

ማንኛውም አረፍተ ነገር የሙሉ ሀሳብ መግለጫ ነው። ቁመንቁዋም በሀሳብ መግለጫነቱ ሙሉ ወይም ከፊል ሀሳብን የሚያሰተላልፉ የቃላት፣ የሀረጎችና የአረፍተ ነገሮች ክምችት ነው። ያልተሙዋላ ሀሳብ ቢታል ወይም በሀረግ ሊገለፅ ይችላል። ሙሉ ሀሳብ ስለ አንድ ክሰተት የሚሰነዘር ሀተታ ነው። ሀተታው ስለ ክሰተቱ ድርጊት ወይም ባህሪ ወይም ሁነት ሊሆን ይችላል። አንድ አረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብን የሚገልፀው ክሰተቱንና በእሱ ላይ ሊሰዋ የሚገባውን ሀተታ አቀናጅቶ ሲይዝ ነው። ክሰተቱን ወይም ሀተታውን ብቻ በመያዝ ሙሉ ሀሳብ ሊሰዋ አይችልም። ሀሳቡ-ጎደሉ ይሆናል።

ከዚህ ሁኔታ ሊታይ፣ ካሁን በፊት እንደተገለፀው፣ አንድ አረፍተ ነገር እንደ አንድ ድርሰት ሊቆጠር ይችላል። አንድ ድርሰት ርዕስና በእሱ ላይ የቀረበ <u>ድርሳን</u> ወይም ሀተታ እንደሚኖረው ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ክሰተትና ለእሱ ላይ የቀረበ ሀተታ ይኖረዋል። ክሰተቱን እንደ ርዕስ፣ ሀተታውን እንደ ድርሳን፣ አረፍተ ነገሩን ደግሞ እንደ ድርሰት አድርጎ ማየት ይቻላል። አንድ ድርሰት የተሙዋላ ነው የሚባለው ርዕሱንና በዚያ ላይ ሊባል የሚገባውን ሁሉ፣ ከጥቅሉ አሰከ ዝርዝሩ አካቶ ሲይዝ እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም ሙሉ ነው የሚባለው፣ ክሰተቱንና በእሱ ላይ ሊቀርብ የሚገባውን ሀተታ አቀናጅቶ ሲይዝ ብቻ ነው።

አንድ ድርሰት የተለያየ ያደራረሰ ዘዴ እንዳለው ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም የተለያየ ያወቃቀር ሰርዓት አለው። ዘዴውን የሚወስነው የድርሰቱ ተግባር ነው። ድርሰቱ ተራ ሀሳብን የሚገልፅ ከሆነ፣ እደራረሱ ተራ ሊሆን ይችላል። አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ነው። ተራ ሀተታን የሚያሰተላልፍ አረፍተ ነገር አወቃቀር ተራ ነው። በአንድ ግስ መሪነት ላይ ብቻ ይመሰረታል። ባለፈው ክፍል መጀመሪያ ላይ ያየናቸው አረፍተ ነገሮች የዚህ ምሳሌ ናቸው። አረፍተ ነገሩ አፅንዖትን የተላበሰና ጥልቅ ሀሳብን የሚያቀርብ ከሆነ፣ አወቃቀሩ ከተራው አረፍተ ነገር አወቃቀር ይለያል። ከዚህ አንፃር ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

አስቴር ብርጭቆውን ሰበረችው 1

ይህ ሙሉ ሀሳብን ያዘለ ተራ አረፍተ ነገር ነው። የሀሳቡ ርዕሰ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ነው። ሀተታው <u>ብርጭቆውን ሰበረችው</u> የሚለው ክፍል ነው። ርዕሱና ሀተታው ድርሰቱን፣ ማለትም አረፍተ ነገሩን ፈጥረዋል። ከመዋቅር አኳያ፣ ርዕሱ <u>አስቴር</u> የሚለው ባሰቤት ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ ሀተታው <u>ብርጭቆውን ሰበረችው</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ ነው። የሁለቱ ቅንጅት ውጤት አረፍተ ነገሩ ነው። አረፍተ ነገሩ <u>ብርጭቆውን ሰበረችው</u> የሚለውን ግሳዊ ሀረግ ብቻ በመያዝ የተሙዋላ ሀሳብ ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህም <u>ብርጭቆውን ሰበረችው</u> የሚለውን ሀረግ የሚሰማ ሰው፣ ብርጭቆውን የሰበረችው ማን ነች? ወይም ማን ነች ብርጭቆውን የሰበረችው? ብሎ በአፅንዖት መጠየቅና የጎደለውን ሀሳብ ማግኘት ይኖርበታል። ጥያቄው የርዕሰ ጥያቄ ነው፤ የሀተታ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ <u>አስቴር</u> የሚለውን ስም ብቻ ከተናጋሪው አንደበት ቢሰማ? አስቴር ምን ሆነች ወይም ምን አደረገች? ብሎ መጠየቁ የማይቀር ነው። ይሽኛው ጥያቄ የርዕሰ አይደለም፤ የሀተታ ነው፤ ርዕሱ ተሰጥቶአልና። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ አንድ አረፍተ ነገር ሰለ አንድ ከስተት የሚያትት ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠይቅም ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገርም መጠይቃዊ አረፍተ ነገር እንደሚባል ባለፈው ክፍል ሰለ ተራ አረፍተ ነገር ስንወያይ ገልፀናል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ድርሰቱ ማለትም አረፍተ ነገሩ፣ የባለቤትና የአንቀፅ ቅንጅት ነው። ባለቤቱ <u>አስቴር</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ አንቀፁ <u>ብርጭቆውን ሰበረችው</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ ነው። ቅደም-ተከተል አገባባቸውን ስንመለከት፣ ባለቤቱ ቀድሞ፣ አንቀፁ አሱን ተከትሎ እንደገባ እንረዳለን። ከዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም፣ ቅደም-ተከተሉ ለምን እንደዚህ ሆነ? የዚህ ግልባጭ ሊሆን አይችልም ነበር ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው ሰለ ተራ አረፍተ ነገሮች አወቃቀር ስንወያይ መነሳት ነበረበት። ያኔም ይነሳ አሁን፣ መልሳችን "አወን፣ ቅደም-ተከተሉ የዚህ ግልባጭ ሊሆን ይችል ነበር፤" የሚል ነው። ሊሆን ይችል ነበር፣ የምንልበት ምክንያት፣ በግሳዊው ሀረግ የሚጀምሩና በባለቤት የሚጨርሱ ወይም በባለቤት ጀምረው በተሳቢ ስማዊ ሀረግ የሚጨርሱ ቁዋንቁዋዎች በዓለም ላይ ስላሉ ነው። ሩቅ ሳንሄድ፣ እንደ ግዕዝ ያሉ የሴም ቁዋንቁዋዎችንና እንደ አኝዋክ ያሉ የአባያዊ ቁዋንቁዋዎችን ብንመለከት፣ በባለቤት ጀምረው በተሳቢ የሚጨርሱ መሆናቸውን እንረዳለን። ይህን ከሚከተለው የግዕዝ ምሳሌ መገንዘብ ይቻላል።

እነ አነብብ መጽሐፈ 2
እኔ አነባለሁ መጽሀፍን
እኔ መጽሀፍን አነባለሁ

የአማርኛ ስርዓትም እንደዚሁ በባለቤት ጀምሮ በተሳቢ የሚጨርስ ሊሆን ይችል ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አንደ ግዕዝ ያሉ ቁዋንቁዋዎች፣ አንደ አማርኛው ስርዓት በግስ ሲጨርሱ ይችሉ ነበር። ከትውረት አንፃር ሲታይ፣ የማንኛውም ቁዋንቁዋ የአረፍተ ነገር ስርዓት በግስ መጨረስ ወይም አለመጨረስ ነው፤ ብሉ ማጠቃለል ይቻላል። ግሱ የአረፍተ ነገሩ ማሰሪያ ወይም መቁዋጭያ ስለሆነ እሱ ከሚገኝበት ቦታ አንፃር፣ የአረፍተ ነገሩን ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት ማወቅ ይቻላል።

ከዚህ አንፃር ቁዋንቁዋዎች ሁሉ ያላቸው ዕድል በግስ መጨረስ ወይም መጀመር ነው። ከዚያም አልፎ አንዳንድ የስነ-ልሳን ተዋሪዎች የቁዋንቁዋው ሁሉ ታሀታይ አወቃቀር፣ ባለቤት - ግስ - ተሳቢ ነው፣ በማለት አጠንክረው ይከራከራሉ። ወደ ዝርዝሩ እንገባም።

ትውረቱ ይህ ሆኖ ሳለ፣ አንድ ቁዋንቁዋ አንዱን ወይም ሌላውን ስርዓት የሚከተልበት ራሱን የቻለ ምክንያት አለው። ምክንያቱ አገንዛዘብ (አመለካከት) ብሎም አገላለፅ ነው። ማንኛውም ሰው አካባቢውን የሚገነዘበው እየመረጠ ነው። ሁሉንም ሊገነዘብ አይችልም። ሲናገርም ሆነ ሲሰማ እየመረጠ ነው። ሀይወት ራስዋ ምርጫ ነች። ስንመርጥ ነው የምንውለው።

ጫካ ውስጥ የገባ ሰው ጫካውን በጥቅል፣ አለያም እያንዳንዱን ዛፍ በተናጠል ይመለከታል። ከዚያም ስለ አጠቃላዩ ጫካ ወይም ስለ አንድ የተለየ ዛፍ የተገነዘበውን ይናገራል። ስለ አንድ ዛፍ የሚናገር ከሆነ፣ ንግግሩ በዛፉ አይነት ወይም መጠን ላይ ሊያተኩር ይችላል። በመጠኑ ላይ ካተኮረ፣ ትልቅ ወይም ትንሽ ብሎ ገለፃውን በቅፅል ይጀምርና ዛፍ ብሎ በስም ይጨርሳል። አጠቃላይ ገለፃውም ትልቅ ዛፍ የሚል ስማዊ ሀረግ ይሆናል። ትኩረቱ በዛፉ ላይ ከሆነ፣ ዛፍ ብሎ፣ ገለፃውን በስሙ ይጀምርና፣ ትልቅ ብሎ በቅፅል ይጨርሳል። ይህም ዛፍ ትልቅ የሚል ስማዊ ሀረግ ይሆናል። የሌሎቹ ሀረጎች ቅደም-ተከተል ስርዓትም በዚሁ አገንዛዘብ ላይ የተመሰረተ ነው ለማለት ይቻላል።

በዚህ አይነት አትኩሮትን ያገኘ ነገር አትኩሮትን ካላገኘ ነገር ቀድሞ ከአንደበት ይወጣል፣ ቀድሞም ይደመጣል። በአረፍተ ነገር ደረጃ፣ ቀድሞ የሚወጣ ነገር ደግሞ ስማዊ ወይም ግሳዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም። ሌሎቹ ሀረጎች በነዚህ ውስጥ በገላጭነት ወይም በመሙሊያነት ወይም በመስተዓምርነት የሚገኙ ናቸው። ርግጥ፣ የየራሳቸው የቅደም - ተከተል ስርዓት አላቸው። ይህም ቢሆን መሪያቸውን በመነሻ ወይም በመድረሻ የሚያስቀምጥ ነው። ከዚህ አንፃር የአማርኛ ሀረጎች መሪ መጨረሻ ላይ እንደሚገኝና በዚህም ምክንያት ቁዋንቁዋው ቀኝ መሪ እንደሆነ በከፍል ሁለት ስለ ሀገ-መዋቅር ስንወያይ ተመልክተናል።

አትኩሮት የሚያገኙ ነገሮችን የሚወስነው፣ ፍላጎት ነው። ፍላጎትን ለማሙዋላት ከፍተኛ አወንታዊ ወይም አሉታዊ አስተዋፅዖ ያላቸው ነገሮች ዋና

ናቸው። ስለሆኑም እነሰተኛ አስተዋፅዖ ካላቸው ሌሎች ነገሮች የተለየ ትኩረት ያገኛሉ፤ በተለየ አፅንዖትም ይነገራሉ። ይኸውም ከሁሉም ቀድመው ካንደበት በመውጣት፣ አለያም ከፍ ባለ ቅላፄ በመነገር ወይም ደግሞ በተለየ ምዕላድ በመጠቀም ነው። እንግዲህ አንድ ቁዋንቁዋ በባለቤት የሚጀምር ነው ስንል፣ ተናጋሪዎቹ አፅንዖት የሚሰጡት ለባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው፤ ማለታችን ነው። ስለሆነም አሱን ከሁሉ አስቀድመው ይናገራሉ። አሱን ካስተዋወቁ በሁዋላ፣ ስለእሱ ድርጊት ወይም ሁነት ወይም ባህሪ በግሳዊ ሀረጉ አማካኝነት በማተት ሙሉ ሀሳቡን ይገልፃሉ።

ሀሳቡ ሙሉ ሳይሆን ሲቀር፣ ወይም ከምናውቀው ጋር የሚቃረን ሲሆን፣ ስለጎደለው ሀሳብ የምንጠይቀው ጥያቄና ስለ*ተቃርኖው* የምንሰጠው ሀሳብ ይኖራል። ጥያቄውንም ሆነ ተቃርኖውን የምንገልፅበት አረፍተ ነገር ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው። አውዱም ከተራው አረፍተ ነገር አውድ የተለየ ነው። አንድ ሰው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ወሬ ስመጀመር የሚጠቀምበት ሳይሆን፣ ወሬ ከጀመረ በሁዋላ፣ በወሬው ላይ ስለሚነሳ አቢይ ጉዳይ አቢይ ጥያቄ የሚጠይቅበት ወይም ተቃውሞ የሚገልፅበት አረፍተ ነገር ነው። ጥያቄውም ሆነ ተቃውሞው ከፍተኛ ሰሜትን የተላበሰ ሲሆን ይችላል። እንደ ሰሜቱ ግለትም ሲያስደስት፣ ሲያስፈነጥዝ አስያም ዱላ ሲያማዝዝ ይችላል።

ጥያቄን በሚመለከት፣ ከፍ ሲል ወዳነሳነው ምሳሌ (1) እንመለስና ሁኔታውን እንመልከት።

አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው? 3


ይህ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር ነው። ይሁን እንጅ፣ ካሁን በፊት ስለተራ አረፍተ ነገር ስንወያይ እንዳየነው ያለ ተራ ጥያቄ አይደለም። ውስብስብ ነው። ተራ ቢሆን ኖሮ፣

አስቴር ምን ሰበረች 4

የሚል ይሆን ነበር። ውስብስብ ያደረገው በውስጡ አዛማጅ አረፍተ ነገርን መያዙ ነው። አዛማጁ አረፍተ ነገርም፣

አስቴር የሰበረችው 5

የሚለው ከፍል ሲሆን፣ አገባቡም ድምፅ-የለሽ የሆነ ስማዊ ሀረግን በማጎላመስ ነው። የመጠይቁ አረፍተ ነገር ታህታይ አወቃቀር፣ በዚያም ውስጥ የአዛማጁ አረፍተ ነገር አገባብና የድምፅ-የለሹ ስማዊ ሀረግ መሪ ቦታ የሚከተለውን ይመስላል።



ከዕፀ-መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት፣ <u>አስቱር የሰበረችው</u> በሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር የተጎላመሰው ስማዊ ሀረግ ነው። የዚህ

ሀረግ መሪ በግሀድ አይታይም፣ ድምፅ-የለሽ ነው። ከዚህም የተነሳ፣ ሀረጉን መሪ - አልባ ልንለው እንችላለን። ይህን ስንል ግን መጠንቀቅ አለብን። ምክንያቱም ሀረጉ ቅርፅ ሳይሆን፣ ይዘት ያለው መሪ አለውና። እሱም ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ስም ነው። ይህ ለመሆኑ ማስረጃው በአዛማጁም ሆነ በአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ላይ የሚታየው <u>ው</u> (/-ኡ/) የሚለው አፀፋ ነው። ይህ አፀፋ ካሁን በፊት ደጋግመን እንዳየነው፣ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ምዕላድ ነው። የሚጠቁመው በመጀመሪያ ደረጃ፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘውን ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአቃፊው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ የባለቤቱን ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው። <u>ምንድን</u> በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት የተጠየቀውም ይኸው መሪ ነው። በግሀድ ቢወጣ ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስል ነበር።

አስቴር የሰበረችው <u>ነገር</u> ምንድን ነው? 7

<u>ነገር</u> የሚለው ምዕላድ፣ በግሀድ የማይታየው ኢስዋዊ የሆነ ስም ተውላጥ ነው።


ከላይ በዕፀ-መዋቅሩ አማካኝነት የሚታየው ታህታይ መዋቅር አንዳንድ ጊዜ፣

ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው (ነገር) ? 8

በሚል መልክ ሊከሰት ይችላል። በሁለቱ ላዕላይ መዋቅሮች መካከል የሚታየው ልዩነት የአፅንዖት ብሉም የቅርፅ ነው።

<u>አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው</u>? የሚለው ጥያቄ የሚጀምረው <u>አስቴር የሰበረችው</u> በሚለው መሪ-አልባ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው። አፅንዖት ያገኘውም ይኸው ሀረግ ነው። <u>ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው</u>? የሚሰው ደግሞ የሚጀምረው በግሳዊ ሀረጉ ነው። በመሆኑም አፅንዖቱ ያረፈው በዚሁ ግሳዊ ሀረግ ላይ ነው። ከአፅንዖት መለያየት የተነሳ፣ አንድ መጠይቃዊ ታህታይ መዋቅር ወደ ሁለት የተሰያዩ ላዕላይ መጠይቃዊ መዋቅሮች ሊለወጥ ችሉአል። የቁዋንቁዋው ውስጣዊ አቀነጃጀት በባለቤት ስማዊ ሀረግ ጀምሮ፣ በግሳዊ ሀረግ የሚጨርስ ለለሆነ፣ <u>ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው</u>? የሚለው ላዕላይ መዋቅር፣ ከላይ ከሚታየው ዕፀ-መዋቅር ላይ በ<u>ለዎጭ ሀግ</u> አማካኝነት እንደሚከተለው ሆኖ የወጣ ነው።

9


አነ'
ግሀi
አነ
ግሀ1
ስሀ
ግሀi
ስ
ግ
ስሀ2
ነው
ምንድን
አነ'
ስሀ1
አነ
ሞይ
ስ
ስሀ
ግሀ
የ
-
ስ
ግሀ1
አስቴር
ስሀ
ግ
ስ
ስበረችው
-

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ምንድን ነው?</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ ከመሰረታዊ ቦታው ተነስቶ፣ ከአረፍተ ነገሩ በመውጣት፣ የአረፍተ ነገሩ ርዕሰ ሆኖአል። የገባበት ቦታ፣ በዕፀ መዋቅሩ ውስጥ ከሚገኙት ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛው ነው። ለለሆነም ይህ ቦታ በአፅንዖት ለሚነገሩና ወይም የየአረፍተ ነገሩ ርዕስ-ነገር የሆኑ ሀረጎች ማረፊያ ነው። ሀረጎችም እንደለው ከፍተኛ ቦታ ይፈልጋሉ ማለት ነው። ቁዋንቁዋ ተናጋሪውን እንደሚመለል ቀደም ሲል ተናግረናል።


በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ እንደሚታየው፣ <u>ምንድን ነው?</u> የሚለው ከፍል ግሳዊ ሀረግ ነው። ይህ ደግሞ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአረፍተ ነገሩ ድርሳን (ሀተታ) ከፍል ነው። የአረፍተ ነገሩ ርዕሰ ባለቤቱ፣ ማለትም <u>አስቴር የለበረችው</u>፣ የሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግ ነው። በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ አፅንዖት ያገኘውም ይኸው ከፍል ነው። በመሆኑም፣ ከሁሉም ቀድሞ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሊገኝና ከአንደበትም ቀድሞ ሊወጣ ወይም ሊፃፍ ችሎአል። ግሳዊ ሀረጉን፣ ማለትም ሀተታውን፣ በአፅንዖት ሰመግለፅ ለንፈልግ፣ ከታህታይ ቦታው አውጥተን፣ አፅንዖት እግኝቶ የነበረውን፣ ባለቤቱን ለማዊ ሀረግ አሳልፈን፣ የዕፀ መዋቅሩን ከፍተኛ ቦታ እንዲይዝ ማድረግ አለብን። ይህን ለናደርግ፣ <u>አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው?</u> ይል የነበረው መጠይቃዊ መዋቅር፣ <u>ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው?</u> ወደማል ለየት ያለ ላዕላይ መዋቅር ይለወጣል። በታህታይ መዋቅር አፅንዖት ያልነበረው ግሳዊ ሀረግ፣ በላዕላይ መዋቅሩ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ሊይዝና አፅንዖት ሊሳናፀፍ ችሎአል። ይህ ከመሆኑ፣ ማለትም ግሳዊ ሀረጉ ከመንቀሳቀሱ በፊት ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የነበረው ባለቤት ለማዊ ሀረግ፣ በፊት የነለረውን አፅንዖት ቢያጣም፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ከመሆን አይታገድም። አፅንዖት ያጣ ወይም በተራ አነጋገር ግርማ ሞገስ የራቀው ተራ ባለቤት ብቻ ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚከተለውን አይነት ላዕላይ መዋቅር ልናገኝ እንችላለን።

አስቴር ምንድን ነው የለበረችው? 10

በዚህና <u>አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው</u>? በሚለው ሀረግ መካከል ያለው ልዩነት፣ <u>ምንድን ነው</u>? የሚለው ያታፈው አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ፣ ከታህታይ ቦታው ተነስቶ ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ መሄዱ እና አሱንም ተከትሎ የአዛማጁ አረፍተ ነገር ባለቤት እንደዚሁ ከመሰረታዊ ቦታው ተነስቶ አፅንዖት ሊያገኝ ወደሚችልበት ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ መሄዱ ነው። ዝርዝሩን እንደሚከተለው እናሳያለን።

11


አነ'
ስሀ$_k$
አነ'
አስቱር
ግሀ$_i$
አነ
ምንድን ነው
ስሀ
ግሀ$_i$
አነ
ስሀ2
አነ
ሞይ$_j$
ስሀ1
ስሀ$_k$
ግሀ
የስበረችው
ስ
....
ግሀ1
ስሀ
ግ$_j$
ስ
...

በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ ስለተዛመደ፣ ቦታው በሶስት ነጥብ ተሸፍኖአል። የተዛመደ ሀረግ በግሀድ እንደማይታይ ቀደም ሲል ገልፀናልና። የዚሁ የአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ ሰበረችው የሚለው ሲሆን፣ አሱም ከቦታው ተነስቶ ወደ ሞዩ ቦታ በመሄድ ከ/የ/ ጋር ተገናኝቶአል። ምንድን ነው? የሚለው ግሳዊ ሀረግ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ታሀታይ ቦታውን ለቆ ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ በመሄድ የተሻለ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል። ይሁን እንጅ አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግም በዚሁ በአፅንዖት ምክንያት መሰረታዊ ቦታውን ለቆ፣ ምንድን ነው? የሚለውን ግሳዊ ሀረግ አቁዋርጦ በመሄድ፣ አሱም ከፍተኛውን የአፅንዖት ቦታ ሊይዝ ችሎአል። $_{ij}$አና$_{k}$ ሀረጎቹ የነበሩበትን መሰረታዊ ቦታና አሁን ያረፉበትን አፅንኦታዊ ቦታ ለማመልከት፣ እንዲሁም አፀፋዎችን ከየሀረጎቻቸው ጋር ለማጣቀስ የገቡ ምልክቶች ናቸው።

ከፍ ሲል ያየነው ጥያቄ ምንድን? የሚል ነበር። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ አነማን በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት የሚመሰረትን ውስብስብ ጥያቄ እንመለከታለን።

አስቴርን የሰድብ-ኡ-ኣት (የሰደቡዋት) አነማን ናቸው? 12


ይህ አረፍተ ነገር አስቴርን የሰደቡኣት የሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግና አነማን ናቸው? የሚለው ግሳዊ ሀረግ ቅንጅት ነው። አስቴርን የሰደቡኣት የሚለው ስማዊ ሀረግ መሪ፣ ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ በግሀድ አይታይም። ይሁን እንጅ፣ ይዘቱን ሰደቡኣት ከሚለው ግስ ላይ ከሚታየው የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ/-ኡ/፣ ማወቅ ይቻላል። ይህ አፀፋ የሶስተኛ መደብ፣ የብዙ ቁጥር የሆነ ባለቤትን ስለሚጠቁም፣ ከዚሁ በመነሳት ስማዊ ሀረጉን ከነመሪው እንደሚከተለው አድርገን በግሀድ ልናስቀምጠው እንችላለን።

አስቴርን የሰደቡኣት ልጆች 13

በዚህ ሀረግ ውስጥ፣ አስቴርን የሰደቡኣት የሚለው ከፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ ብቻ የተጠቀሰው፣ የብዙ ቁጥር ሀረግ ነው። አስቴርን የሰደቡኣት አነማን ናቸው? ስሚለው ውስጥ፣ አፅንዖቱ ያለው፣ በባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ላይ ነው። በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ የሚገኘው አሱ ነውና። ግሳዊ ሀረጉ አፅንዖትን እንዲያገኝ ከፈለግን፣ ከታሀታይ ቦታው አንስተን፣ ከአቃፊው አረፍተ ነገር በማስወጣት፣ ከፍ ሲል ባየነው የርዕስ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይኖርብናል። ይህን ስናደርግ ጥያቄው፣

አነማን ናቸው አስቴርን የሰደቡኣት...? 14

የሚል ይሆናል። <u>የሰድቡኣት</u> ከሚለው ግስ ቀጥሎ የሚታየው ነጠብጣብ የማያመለክተው፣ <u>አነማን ናቸው</u>? የሚለው ግሳዊ ሀረግ የነበረበትን መሰረታዊ ቦታ ነው። ከዚህ ተነስቶ ነው፣ የአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ሊሆን የቻለው። አካሄዱን አሁንም እንደሚከተለው በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



እስካሁን ያየናቸው ጥያቄዎች ተሳቢ ወይም ባለቤት ስማዊ ሀረግን የሚጠይቁ ናቸው። መጠይቅ ተዋላጠ ስሞቹም ምን(ድን) እና (እነ)ማን የሚሉት ናቸው። ከዚህ ቀጥለን ተውሳክ ግሳዊ ጥያቄዎችን እንመለከታለን። እነዚህም እንደሚከተለው ያሉ ናቸው።

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው ለምንድን ነው? 16

ይህ ጥያቄ አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችበትን ምክንያት ወይም ዓላማ የሚጠይቅ ተውሳክ ግሳዊ መዋቅር ነው። የተጠየቀውም <u>ለምንድን</u> በሚለው መለተዋድዳዊ መጠይቅ ሀረግ ነው። ለዚህ አይነቱ ጥያቄ የሚለጠው መልስም እንደዚሁ መለተዋድዳዊ ነው። ለምሳሌ፣ ለጥያቄው የተለጠው መልስ፣

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው <u>ለጨዋታ</u> ነው 17


የሚል ቢሆን፣ <u>ለምን</u> የሚለው መለተዋድዳዊ ጥያቄ፣ <u>ለጨዋታ</u> በሚል መለተዋድዳዊ ሀረግ እንደተመለለ እንረዳለን። መለተዋድዳዊ ሀረጎች ደግሞ፣ በሀረግ ክፍል በለፊው እንደተገለፀው፣ በግሳዊ ሀረግ ውለጥ፣ አብዛኛውን ጊዜ በአጎላማሽነት፣ እንዳንድ ጊዜ በመሙሊያነት የሚገቡ መዋቅሮች ናቸው። ይህም እንደየግሱ ባህሪ የሚወለን ነው። ከዚህ አኩዋያ ሲታይ፣ <u>አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው ለጨዋታ ነው</u> የሚለው ውስብስብ አረፍተ ነገር በተራ አረፍተ ነገር ቢነገር፣

አስቴር ለጨዋታ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች 18

የሚል ይሆናል። <u>ለጨዋታ</u> የሚለው መለተዋድዳዊ ሀረግ <u>ወደ ትምህርት ቤት ሄደች</u> የሚለውን ነዑስ ግሳዊ ሀረግ አጎላምሶ እንደገባ በግልፅ ይታያል። <u>ለምድን ነው?</u> በሚል መልክ በአፅንዖት የተጠየቀውም ይኸው መለተዋድዳዊ ሀረግ ነው።


አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው 19

የሚለው መሪ-አልባ የሆነ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። በውለጡ የተዛመደ ሀረግ አለ። ሀረጉም እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግ ድምፅ-የለሽ ነው። ይሁን እንጅ ይዘቱ <u>የሄደችው</u> ከሚለው ግለ መድረሻ ላይ ከሚታየው አፀፋ፣ ማለትም ከ <u>ው</u> (/-ኡ/) ይታወቃል። ሶለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ያታ ነው። ከባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ጋርም በትርጉም አንድ ነው። ከዚህ በመነሳት የመጠይቁን አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው አድርገን እናሳያለን።



ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት የይስሙላው ተውላጠ ስም ሊሆን አይችልም ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው

ተገቢ ነው። በርግጥም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ይህ ተውላጠ ስም ሲሆን ይችላል። ይህ ተውላጠ ስም ድምፅ-የለሽ መሆኑን መርሳት የለብንም። <u>ኑ-ው</u> በሚለው ግስ መድረሻ ላይ የሚታየው አፀፋ፣ ማለትም /-ኡ/ ይህንኑ ተውላጠ ስም ሊያመለክት ይችላል። በተጨማሪም <u>ነው</u> በሚለው ግስ ፋንታ <u>ይ-ሆን</u> የሚለውን የሁለት ግስ ብንጠቀም፣ ቀደም ሲል ያየነውን፣ /ይ-/ የሚለውን የድምፅ-የለሽ ተውላጠ ስም አፀፋ እናገኛለን። ይህ ውነት ከሆነ፣ <u>አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው</u> የሚለው መራ-አልባ ስማዊ ሀረግ፣ የግሳዊ ሀረግ አካል ነው፤ ግስት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሀረጉ ተውሳክ ግሳዊ ስም ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የአረፍተ ነገሩ ታህታይ መዋቅር የሚከተለውን መምሰል ይኖርበታል።



በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው</u> የሚለው መራ-አልባ ስማዊ ሀረግ ከግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አንጉዋ ላይ ወርዶአል። ገላጭነቱ

ለንሁሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ነው። የሚገልፀውም ከምክንያት አንፃር ነው። ሁኔታው አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው የሚለው ስማዊ ሀረግ አሻሚ አገባብ ያለው መሆኑን ያሳያል። በአንድ በኩል፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ በባለቤትነት ሲገባ፣ አዚህ ላይ ደግሞ በተውሳከ ግስነት ሲገባ ችሎአል። በተውሳከ ግስነት ለመግባቱ አንድ ተጨማሪ ማስረጃ አለ። ይኸውም ሀረጉ አንደሚከተለው ሆኖ በገሀድ ከሚታይ መሪ ጋር ሊከሰት መቻሉ ነው።

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችበት ምክንያት 22

እነሆ፣ ከፍ ሲል መሪ-አልባ የነበረው ስማዊ ሀረግ፣ አሁን ምክንያት የሚለውን ስም በመሪነት ይዞ ይገኛል። ከፍ ሲል የሄደችው የነበረው የአዛምጁ አረፍተ ነገር ግስም አሁን የሄደችበት የሚል ሆኖአል። በዚህ ግስ መድረሻ ላይ የሚታየው /-በት/ የሚለው ምዕላድ የተዛመደው መስተዋድዳዊ ሀረግ አፀፋ ነው። ተራ አፀፋ ሳይሆን ድርብ ነው። /በ/ የሚለው መስተዋድድና /-ት/ የሚለው አፀፋ ቅንጅት ነው። /ት/ የመስተዋድዱ መሙሊያ ሆኖ የገባው ስማዊ ሀረግ አፀፋ ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል። ይኸውም ስማዊ ሀረጉ ያለመሪ ሲከሰት፣ ተዛማጁ ሀረግ /-ት/-ው/ በሚል ተራ አፀፋ የሚጠቀስ መሆኑና፣ ስማዊ ሀረጉ ከመሪው ጋር ሲከሰት ደግሞ፣ ተዛማጁ ሀረግ /-በት/ በሚል ድርብ (መስተዋድዳዊ) አፀፋ የሚጠቀስ መሆኑን ነው። ግሀድ መሪ ባላቸው ስማዊ ሀረጎች ውስጥ፣ ማንኛውም ተዛማጅ መስተዋድዳዊ ሀረግ /-በት/ በሚል ድርብ አፀፋ ሲጠቀስ፣ ድምፅ-የለሽ መሪ ባላቸው ተውሳከ ግሳዊ ስማዊ ሀረጎች ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ ግን /-ው/-ት/ በሚል ተራ አፀፋ ይጠቀሳል ማለት ነው። ሁኔታውን ይበልጥ ለመገንዘብ የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

i (ሀ) አስቴር የሄደች-በት መኪና ምንድን ነው? 23
(ሰ) አስቴር የሄደች-ው በምንድን ነው?

ii (ሀ) አስቴር የሄደች-በት ምክንያት ምንድን ነው?
(ለ) አስቴር የሄደች-ው ለምንድን ነው?

iii (ሀ) አስቴር የሄደች-<u>በት ሀገር</u> የት ነው?
(ለ) አስቴር የሄደች-<u>ው ወዴት</u> ነው?

iv (ሀ) አስቴር የመጣች-<u>በት ሀገር</u> የት ነው?
(ለ) አስቴር የመጣች-<u>ው ከየት</u> ነው?

ከየጥንዱ ምሳሌ በግልፅ እንደሚታየውና ከፍ ሲልም እንደተገለፀው፣ ተዛማጁ መስተዋድዳዊ ሀረግ /-<u>በት</u>/ በሚለው አፀፋ በሚጠቀሰበት ጊዜ፣ ስማዊ ሀረጉ ከነመሪው ይከሰታል። በዚህን ጊዜም ጥያቄው በመጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት ይገለፃል። ተዛማጁ ሀረግ <u>ው</u> (/-ኡ/) በሚለው አፀፋ በሚጠቀሰበት ጊዜ፣ ስማዊ ሀረጉ ያለመሪ ይከሰታል። ጥያቄውም በመስተዋድድ ሀረግ አማካኝነት ይጠየቃል። ከዚህም የጥያቄውን አይነት የሚወስነው፣ የአፀፋው አይነት ነው ስማለት ይቻላል። አፀፋው መስተዋድዳዊው /-በት/ ሲሆን፣ ጥያቄው ስማዊ ይሆናል፣ አፀፋው ስማዊው <u>ው</u> (/-ኡ/) ሲሆን፣ ጥያቄው መስተዋድዳዊ ይሆናል። ይህ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ፣ እንደ ምሳሌ 24(ለ) እና (መ) ያለ ተቀባይነት የሌለው አረፍተ ነገር ይከተላል።

(ሀ) አስቴር የሄደችው ለምንድን ነው? 24
(ለ) *አስቴር የሄደችው ምንድን ነው?
(መ) አስቴር የሄደችበት ምክንያት ምንድን ነው?
(ለ) *አስቴር የሄደችበት ምክንያት ለምንድን ነው?

ሁኔታው ተዛማጁ ሀረግ መስተዋድዳዊ ሲሆን፣ መሙሊያው ስማዊ ሀረግ እንደሚሆን፣ እንዲሁም ተዛማጁ ሀረግ ስማዊ ሲሆን፣ መሙሊያው መስተዋድዳዊ ሀረግ እንደሚሆን ያሳያል። ከዚህም ተዛማጅ መስታወድዳዊ ሀረግና መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ተወራራሽ አገባብ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጅ፣ ይህ አይነት ተወራራሽነት የሚታየው ከላይ እንደሚታዩት ባሉ ኢሳቢ ግሳዊ ሀረጎች መሪነት በሚዋቀሩ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ነው። ግሳዊ ሀረጎቹ ሳቢ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል።

(ሀ) አስቴር የበላችው ለምንድን ነው? 25
(ለ) አስቴር የበላችው ምንድን ነው?

የመጀመሪያው መጠይቅ አረፍተ ነገር ገላጭ መሰተዋድዳዊ ሀረግን የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው መሙሊያ ሰማዊ ሀረግን የሚመለከት ነው። ሁለቱም ተቀባይነት አሳቸው። ከዚህም የኢሳቢ ግሶች መጠይቅ መሰተዋድዳዊ መሆኑን፣ የሳቢ ግሶች ግን ገላጭ መሰተዋድዳዊ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ መሙሊያ ሰማዊ ሀረግ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል። ይህም ልዩነት ከግሶቹ መዋቅራዊ ባህሪ ጋር የተያያዘ ነው። ሳቢ ግሶች ብቻ ሰማዊ ሀረግ መሙሊያ ይፈልጋሉና።

እሳካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች መጠይቅ ናቸው። ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ ጥያቄውን በአፅንዖት ለመጠየቅ የምንጠቀምበት አዛማጅ አረፍተ ነገር ራሱ ውስብስበ መሆኑ ነው። ለውስብስብ መጠይቅ ሀረጎች ወይም ለእልት ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች የሚሰጠው መልስም እንደዚሁ ያለ አፅናዖትን ለሰሚፈልግ ውስብስብ ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንመልከት።

(ሀ) እሰቱርን የሰድብናት እኛ ነን 26
(ለ) ትናንት የመጣው ማን ነው?

እንደነዚህ ያሉ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች በማንኛውም ሳይሆን፣ በተለየ አውዶ-ነገር የሚነገሩ ናቸው። አውዱም በአፅንዖት የሚጠየቅ ጥያቄ ወይም በሀሰት የሚነገር ሀተታ ነው። ጥያቄው፣


እሰቱርን የሰደባት ማን ነው? 27

የሚል ሊሆን ይችላል። ሀተታው ደግሞ፣

ትናንት የመጣሁት እኔ ነኝ 28

የሚል ሊሆን ይችላል። ከዚህ አውድ ለንነላ፣ 26(ሀ) ለ(27) የሚሰጥ መልስ ነው። (28) ደግሞ ለ26(ለ) የሚሰጥ ተገቢ ምላሽ ሊሆን ይችላል።

የእንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ቀደም ሲል ካየናቸው ውስብስብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ጋር አንድ ነው። አንድነቱን <u>እሰቱርን የሰደብናት እኛ ነን</u> ሰሚለው ምሳሌ አማካኝነት በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



ከዕፀ-ዋቅሩ እንደሚታየው፣ <u>አስቴርን የሰደብናት</u> የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። አግባቡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግን

በማነላመስ ነው። ይህ ስማዊ ሀረግም ቀደም ሲል አንዳየናቸው ሌሎች ተመሳሳይ ስማዊ ሀረጎች፣ መሪው በግሀድ አይታይም። ይሁን እንጅ፣ ይዘቱ መጀመሪያ ስደብ-ን ከሚለው ከአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ፣ ከዚያም ነ-ን ከሚለው ከአቃፊው አረፍተ ነገር የሁነት ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው የአንደኛ መደብ የብዙ ቁጥር የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ/-ን/፣ ይታወቃል። ይህ አፀፋ አንደኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር የሆነ ባለቤትን ይጠቁማልና። ከዚህም ነን በሚለው የሁነት ግስ ከሚመራው ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገሩን የመሰረተው ባለቤት፣ ይህ መራ-አልባ ስማዊ ሀረግ አንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ይህም ስማዊ ሀረግ፣ የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ከሆነው እኛ ከሚለው አህደ ጋር በትርጉም አንድ ነው። ይህም ማለት መራ-አልባው ስማዊ ሀረግና መሙሊያው ስማዊ ሀረግ የሚጠቁሙት ነገር አንድ ነው፣


በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ የተዛመደው ክፍል ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው። ስለሆነም ይህ ሀረግ በግሀድ አልተከሰተም፣ ሊከሰትም አይችልም። ማንኛውም የተዛመደ ሀረግ በአፀፋ ይጠቀሳል እንጅ፣ ግሀድ አንደማይወጣ ቀደም ሲል ገልፀናል። ስደብ-ን-አት በሚለው ግስ ላይ የሚታየው /-ን/ የሚለው አፀፋ ተግባር በግሀድ ሊወጣ ያልቻለውን ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ማንነት መጠቆም ነው። የዚህ ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ መሪ እንደ ተማሪዎች ያለ የብዙ ቁጥር የወል ስም ሊሆን ይችላል። ስሙ እኛ ከሚለው መስተዓምር ተውላጠ ስም ጋር ሲዋቀርና በግሀድ ሊከሰት የሚከተለውን ሊይመስል ይችላል።

*[[እኛ ተማሪዎች] አስቴርን የሰደብ-ን-አት] 30

ይህ ስማዊ ሀረግ ተቀባይነት የለውም። ለዚህም ምክንያቱ የተዛመደው ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ መከሰቱ ነው።

በግልፅ እንደሚታየው ስደብ-ን-አት በሚለው ግስ አምድ መድረሻ ላይ የሚታየው /-ን/ የሚለው ምዕላድ የሚጠቁመው እኛ የሚለውን የስማዊ ሀረጉን ተውላጠ ስማዊ መሰተዓምር ነው፣ ተማሪዎች የሚለውን የሀረጉን መሪ ስም አይደለም።

ከዚህ ስማዊ ሀረግ ጋር የተዋቀረውና እኛ ነን የሚለውን ግሳዊ ሀረግ በለዋጭ ህግ አማካኝነት ከመሰረታዊ (ታህታይ) ቦታው በማንሳት አፅንዖት ሊያገኝ ወደሚችልበት ቦታ መውሰድ ይቻላል። ይህ የአፅንዖት ቦታም ደጋግመን እንደገለፅነው፣ የአረፍተ ነገሩ ቅድመ-መነሻ ነው። ይህ ቦታ አፅንዖት ለማግኘት የሚንቀሳቀሱ ሀረጎች ማረፍያ ነው። በዚሁ መሰረት እኛ ነን የሚለው ግሳዊ ሀረግ ወደዚህ ቦታ ሲመጣ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (29) የተገለፀው ዕፀ-መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።



31

እነሆ፣ <u>እኛ ነን</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ በነጠብጣብ (...) ከተመለከተው ታሀታይ ቦታው ተነስቶ፣ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት አቁዋርጦ፣ ከአረፍተ ነገሩ (አነ)

በመውጣትና ከአሱም ጋር በመዋቀር፣ (አነ) የሚለውን መዋቅር ፈጥሮአል። ከዚህ መዋቅር ግራ ጎን በመግባትም ከፍተኛውን ስፍራ ሊይዝ፣ ብሉም የዕፀ-መዋቅሩ ቁንጮ ሊሆን ችሉአል።

በተራ ቁጥር (28) የተመለከተውን ምሳሌ ደግሞ አንመልከት። ምሳሌው፣

ትናንት የመጣሁት አኔ ነኝ 32

የሚል ነው።

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ <u>ነ-ኝ</u> የሚለው የሁነት ግስ <u>ትናንት የመጣሁት</u> ከሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣

ትናንት የመጣሁት ነኝ 33

የሚለውን ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ <u>አኔ</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ፣

አኔ ትናንት የመጣሁት ነኝ 34

የሚለውን አረፍተ ነገር አዋቅሮአል።

ትናንት የመጣሁት 35

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። አገባቡም ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ መሪ-አልባ የሆነን ስማዊ ሀረግ በማጎላመስ ነው። የዚህ አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አይታይም። ለዚሀም ምክንያቱ ግልፅ ነው። ተዛማጁ ሀረግ ራሱ ነው። <u>የመጣሁት</u> በሚለው ግስ ላይ /-ሁ/ የሚለው አፀፋ የሚያመለክተው ይህንኑ ተዛማጅ ባለቤት ሀረግ ነው። አንደኛ መደብ፣ ነጠሳ ቁጥር፣ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው።

ከዚህ ሳይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻሳል። ይኸውም <u>የመጣሁት</u> በሚለው ግስ መድረሻ ሳይ የምትታየው /-ት/ ምንን ታመለክታለች? የሚል ነው። በቅርፅዋ የተሳቢ አፀፋ ትመስሳለች። <u>መጣ</u> የሚለው ግስ ግን ሳቢ አይደለም። ስለዚህም ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር አይችልም። ባጭሩ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ተሳቢ ሀረግ ሊኖር አይችልም። ከሌለ፣ ስለተሳቢ አፀፋ ማንሳት አይቻልም። "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ይሆናልና።

ታዲያ ምዕሳድዋ ምንድን ነኝ ባይ ነች? ምዕሳድዋ የተሳቢ አፀፋ ትምሰል አንጅ፣ በውንስ አይደለችም። በዚች ምዕላድ ወይም የአለዋ ተለዋጭ በሆነው በ/-ኡ/ አማካኝነት የሚገለፁ የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራት አሉ። ከአነሱም መካከል ዕምርነት፣ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠሳ ቁጥር፣ አገናዛቢነት፣ የሶስተኛ

መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታነት፤ የተሳቢ አፀፋነት፣ የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላድነት፤ ተውላጠ መሪነት ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህን በሚከትሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

(ሀ) ተማሪ - ው (/-ኡ/) 36
በመስተዓምርነት

(ለ) አስቴር ተማሪውን ሰደበች-ው (/-ኡ/)
በ3ኛ መደብ፣ ነጥላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ፣ ተሳቢ አፀፋነት

(መ) ትናንት የሄድ- ኡ
በ3ኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላድነት

(ሰ) ትናንት የሄድ-ኡ-ት
በተውላጠ መሪነት

ከዚህ ላይ <u>ተውላጠ መሪነት</u> የሚለውን ቃል መግለፅ ላያስፈልግ አይቀርም። ተውላጠ መሪ የምንለው፣ አንድ በግሀድ የማይታይን መሪ ስም ተክቶ የሚገባን ጥገኛ ምዕላድ ነው። በተግባሩ እንደ ተውላጠ ስም ነው። በቅርፁ ግን እንደ ተውላጠ ስም ነፃ ላይሆን፣ ጥገኛ፣ ማለትም ቅጣይ ነው።

የአንድን አዛማጅ አረፍተ ነገር ግስ ከነዚህ ሞክሸ ምዕላዶች ውስጥ አንዱን ወይም ሁለቱን፣ በአንዳንድ ቀበልኛ ደግሞ ሶስቱን፣ ሊያስከትል ይችላል። ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ነው።

አምድ - የባለቤት አፀፋ - ተውላጠ መሪ/የተሳቢ አፀፋ - መስተዓምር 37

የባለቤትና የተዛማጅ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አፀፋ አይቀሬ ናቸው። ሌሎቹ ሊቀሩ ይችላሉ። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) እኔ [ትናንት የመጣሁት] (የመጣ - ሁ - (ት)) ነኝ 38
(ለ) እኔ [ትናንት ጠላውን የጠጣሁት] (የጠጣ - ሁ - ት) ነኝ
(መ) እኔ [ትናንት ጠላውን የጠጣሁቱ] (የጠጣ - ሁ -ት - (ኡ)) ነኝ

በየቅንፉ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች አዛማጅ አረፍተ ነገሮች ናቸው። በግሀድ የማይታይን ስማዊ መሪ ያነሳመሳሉ። በምሳሌ (ሀ) ወስጥ /-ት/ የተዛመደውና በግሀድ የማይታየው ስማዊ መሪ ተውላጥ ነች። ስሙ ሶስተኛ መደብ፣ ተባዕታይ ፆታና ነጠላ ቁጥር መሆኑን ታመለክታለች። በምሳሌ (ለ) <u>ጠላውን</u> የሚለው ተሳቢ

ስማዊ ሀረግ አፀፋ ነች። በምሳሌ (መ) /-ት/ የተሳቢው አፀፋ ስትሆን፣ ከአስዋ ቀጥላ የገባችው /-አ/ ተውላጠ መሪ ነች። የሚከተለውን ደግሞ አንመልከት።

ትናንት የሰደብኩት (የሰደብ - ኩ - ት) ልጅ 39

በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምትታየው /-ት/ የትኛዋ /-ት/ ነች? ተዛማጁን ስማዊ ሀረግ የምትጠቁመው? ተውላጠ መሪዋ? ወይስ መስተዓምርዋ /-ት/? መጀመሪያ /-ት/ የ/-አ/ ተለዋጭ መሆንዋን አንርሳ። /-አ/ ከሴላ /-አ/ በሁዋሰ ስትገኝ ወደ /-ት/ ትለወጣለች።

ተውላጠ መሪዋ /-ት/ ልትሆን አትችልም፤ ምክንያቱም መሪው ስም ማለትም ልጅ በግሀድ ይታያልና። ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ይህች ተውላጠ መሪ ምዕላድ የምትከሰተው የተዛመደው ስማዊ ሀረግ መሪ በግሀድ በማይታይበት ጊዜ ነው። ተውላጠ መሪዋ ካልሆነች፣ ልትሆን የምትችለው አንድም የተሳቢው ሀረግ አፀፋ፣ አለያም መስተዓምርዋ ት < /-አ/ ነው። መስተዓምርዋ ልትሆን አትችልም፤ ምክንያቱም መስተዓምርዋ ት ከሆነች፣ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ አልተጠቀሰም ማለት ነው። በአፀፋ ያልተጠቀሰ ተዛማጅ ተሳቢ ሀረግን የያዘ ስማዊ ሀረግ ደግሞ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህም፣

*ትናንት የሰደብኩ ልጅ 40

ማለት አይቻልም። ይህ ከሆነ፣ -ት የተዛማጁ ስማዊ ሀረግ ጠቃሽ መሆን አለባት። ርግጥ፣ ይህች ምዕላድ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ከተውላጠ መሪውና ከመስተዓምርዋ -ት ጋር በቅርፅ አንድ ነች። ስለዚህም ልንደናገር አንችላለን። ይሁን እንጅ፣ መስተዓምርዋ -ት ከተውላጠ መሪው ወይም ከተሳቢው አፀፋ ቀጥላ ትገባለች። ይህም በአንዳንድ የገጠር ቀበልኛ ነው፤ ለምሳሌ በወሎ። ይህ ሲሆን ሀረጉ፣

ትናንት የሰደብኩቱ (ሰደብ- ኩ - ት - ኡ) 41

የሚል ይሆናል።

ተውላጠ መሪዋ -ት የምትገኘው መሪ-አልባ በሆነ ስማዊ ሀረግ ውስጥ ነው ብለናል። ለዚህ የሚከተለውን ምሳሌ አንመልከት።

ትናንት የመጡት (መጥ - ኡ - ት) 42

በዚህ ሀረግ ውስጥ፣ የተዛመደው፣ ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው። በመሆኑም በግሀድ አይታይም፤ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ግን ተጠቅሰአል። ከዚህ አፀፋ ቀጥሎ የሚታየው ምዕላድ፣ ማለም -ት የሚጠቁመው አዛማጁ አረፍተ ነገር

የሚያጎላምስውን ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው። ስለዚህም የመሪው ተውሳጥ ነው። ተውሳጠ መሪ ያልነውም ስዚሁ ነው። ከሱ ቀጥሎ መስተዓምሩን /-ኡ/ በማስገባት፣

ትናንት የመጡቱ (መጥ- ኡ - ት -ኡ) 43

ማለት እንችላለን፣ ቢያንስ ከፍ ሲል በጠቀስነው ቀበልኛ።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም የመስተዓምሩን አገባብ የሚመለከት ነው። ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ፣ መስተዓምር የሚገኘው መሙሊያዎችንና አጎላማሾችን ቀድሞ በሀረግ መነሻ ላይ እንደሆነ ገልፀን ነበር። አሁን ደግሞ ከዚህ ላይ እንደሚታየው፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ አየገባ ይገኛል። አንዳንድ ጊዜ በስማዊ ሀረጉ መነሻ፣ ሌላ ጊዜ በግሱ መድረሻ ላይ ሊገባ ይችላል ማለት ነው? ስዚህ መልሳችን "አወን ይችላል" የሚል ነው። በሀረጉ መነሻና በግሱ መድረሻ የሚገባው መስተዓምር ግን አይነቱ ለየቅል ነው። በሀረጉ መነሻ የሚገባው እንደ ይህ፣ ያ፣ ወዘተ፣ ያለ ነፃ መስተዓምር ሲሆን፣ በግሱ መድረሻ ላይ የሚገባው እንደ /-ኡ/ ወይም /-ኡ/-ኢ/ (ዋ) ያለ ጥገኛ መስተዓምር ነው[13]። ጥገኛ ስለሆነ፣ ቀድሞት ከሚገኘው መሪ ቃል ላይ ይጠጋል። መሪው ቃል ገላጭ ሀረግ ካለው፣ ከገላፊው መሪ ቃል ላይ ያርፋል። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን።

(ሀ) ልጁ (ልጅ-ኡ) 44
(ለ) ትልቁ (ትልቅ-ኡ) ልጅ
(መ) ትናንት የመጣው (የመጥ-አ-ኡ) ትልቅ ልጅ


በመጀመሪያው ምሳሌ፣ መስተዓምሩ ልጅ የሚለውን ስም ተጠግቶ ገብቶአል። በሁለተኛው ምሳሌ ልጅ የሚለውን ስም አልፎ በገላፊው ቅፅል መድረሻ ላይ ይገኛል። በሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ ቅፅሉንም አልፎ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ ገብቶአል። የመስተዓምሩ ታሀታይ አገባብ ስማዊ ሀረጉን ተከትሎ ነው፤ ለማለት ይቻላል። ሀረጉ ገላጭ ሲኖረው ብቻ ወደ መጀመሪያው ገላጭ ይሸጋገራል ብሎ፣ ማጠቃለል ይቻላል፤ ለጊዜው።

ስለ ሀረግ ስንወያይ መስተዓምር ስማዊ ሀረግን በመሙሊያነት አየያዘ መስተዓምራዊ ሀረግ አንደሚፈጥር ገልፀን ነበር። በዚያ አመለካከት መሰረት፣ በተራ ቁጥር (44) የተመለከቱት መዋቅሮች ስማዊ ሳይሆኑ፣ መስተዓምራዊ

---

[13] ጉዳዩ /ኡ-/ን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን እንደ /-ኧኛ/ ያሉትን ምዕላዶችም ይጨምራል። እነዚህም እንደ፡
ይኸኛው (ይኸ-ኧኛ-ኡ) ልጅ
ይሀችኛዋ (ይኽ-ች-ኧኛ-ኡ-ኣ) ልጅ
ስንል ነው። ዝርዝር ሀኔታውን ወደፊት በሌላ ፅሁፍ እናሳያለን።

ሀረጎች መሆን አለባቸው። ይህ ከሆነ አወቃቀራቸውን እንደሚከተለው እድርገን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን።



በግልፅ እንደሚታየው፣ የመስተዓምራዊው ሀረግ መሪ /-ኡ/ ነው። እንደማንኛውም መሪ ቦታው በመሙሊያው ስማዊ ሀረግ ቀኝ ጎን ነው። ስማዊ ሀረጉ ገላጭ ሲኖረው፣ ከመጀመሪያው ገላጭ ጋር ይዋቀራል። ገላጭ ከሌለው ከመሪው ሰም ላይ ይለጠፋል። እንዲት እንደሚለጠፍ ወደፊት በስፊው እናሳያለን። ምናልባትም፣ የመስተዓምሩ ቦታ ከላይ እንደሚታየው በቀኝ በኩል ላይሆን ይችላል። ለጊዜው በዚህ እንተወው።

እንግዲህ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ስለ ውስብስብ አረፍተ ነገር በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልና እንለያይ። ውይይታችን ያተኮረው በአፅንዖታዊ አረፍተ ነገሮች ላይ ነው። እነዚህም በአንድ በተለየ አውደ-ነገር ላይ በሚነሱ ጥያቄዎችና በመልሶቻቸው ላይ የሚያተኩሩ አረፍተ ነገሮች ናቸው። ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ናቸው። ውስብስብ የሚሆኑበት ምክንያት በውስጣቸው አዛማጅ አረፍተ ነገር ስለሚይዙ ነው። የአዛማጁ አረፍተ ነገር መሪ በግሀድ ላይከሰት ይችላል። በአፀፋ ግን ይጠቀሳል። ከዚህም ይዘቱ ይታወቃል። የአፀፋው ቅርፅ ከመስተዓምሩ /-ኡ/ ጋር አንድ ነው።

በእንደዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ስማዊ ወይም ግሳዊ ሀረጎች ከመሰረታዊ (ታህታይ) ቦታቸው እያተነሱ ከአረፍተ ነገሩ በመውጣት፣ ሌሎቹን የአረፍተ ነገር ክፍሎች እየቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ። ይህን በማድረግም አፅንዖት ያገኛሉ። እንደነዚህ ያሉ ሀረጎች ተራ ሳይሆን፣ ዋና ሀሳብን ያዘሉ ናቸው። ስለዚህ የተለየ አቀራረብን፣ ማለትም የሀረግ አወቃቀርን ይጠይቃሉ። በዚህ ክፍልም ያየነው፣ ይህንኑ ከተራው ለየት ያለ የአወቃቀር ስርዓትን ነው።

በመጨረሻም፣ በዚህ መፅሀፍ፣ ከድምፅ ጀምረን፣ በቃላት ክፍሎች አድርገን፣ ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን እየተመለከትን ከዚህ ደርሰናል። በጉዞአችን ላይ ለማየት የሞከርነውን ወደሁዋላ መለስ ብለን ብናስተውሰው፣ ከአንድ ቤት ሰራ ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ቤት፣ መሰረት፣ ጣሪያና ግድግዳ ይኖረዋል። ያለመሰረቱ ግድግዳው፣ ያለግድግዳው ጣሪያው ፈፅሞ ሊታሰብ አይችልም። ሶስቱም በተናጠል ሳይሆን፣ በሀብረት ተደጋግፈው ቤቱን ማቆም አለባቸው። ከዚያ በመለስ ያለው የመልክ ጉዳይ ነው።

አረፍተ ነገሮችን እንደቤት ልንቆጥራቸው አንችላለን። መሰረታቸው ድምፅ ነው። በዚህ ረገድ በክፍል አንድ የ30 ተናባቢና የ7 አናባቢ ድምፆችን አፈጣጠርና የአቀነጃጀት ስርዓት አይተናል። እነዚህ 37 ድምፆች ተናባቢ - አናባቢ - ተናባቢ በሚል ስርዓት ሲቀናጁ፣ ቀለምና ምዕላድ እንደሚፈጥሩ አይተናል። በየቀለሙና በየምዕላዱ ውስጥ፣ እንዲሁም በየድንበሩ ላይ በሚፈጠረው የድምፆች ንክኪ ምክንያት የሚከሰቱትን ልዩ ልዩ ድምፀ - ልሳናዊ ሂደቶችና ለውጦች ተመልክተናል። ለውጦቹ በእብዛኛው የመካነ አናቶ/ወይም የባህርየ ንባብ ምሰሶሎሽ ናቸው።

በክፍል ሁለት የተመለከትነው በጥቅሉ የምዕላዶችንና፣ የቃላትን አይነትና የአፈጣጠር ስርዓት ነው። ቃላት እንደ ብሉኬት፣ ወይም እንደ ሸክላ አለያም እንደ ጠርብና ጨፈቃ ሊቆጠሩ ይችላሉ። አፈጣጠራቸው ስነ-ድምፀ - ልሳዊና ስነ-ምዕላዳዊ ነው። ስነ-ምዕላዳዊ ሰርዓታቸው በስር፣ በተለያየ አምድና ቅጣይ ምዕላዶች ላይ የተመሰረተ ነው። በማንኛውም መንገድ የሚፈጠሩ ቃላት ልዩ ልዩ የርባታ ምዕላዶችን እያሰከተሉ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀረጋትን መደብ፣ ቁጥር፣ ዖታ፣ ወዘተ፣ እንዲሁም የየግሱን የአንቀፅና የጊዜ አይነት እንዴት እንደሚያሳዩ ተግንዝበናል።

በማንኛውም ሁኔታ የሚፈጠሩ ቃላት ርስበርስ ተያይዘውና ተደጋግፈው የሚፈጥሩዋቸው ሀረጎች እንደ ግድግዳ ሊቆጠሩ ይችላሉ። የሀረጎቹን አይነትና ይዘት ያየነው በክፍል ሰስት መጀመሪያ ላይ ነው። ግድግዳውን ከሚፈጥሩት ሀረጎች መካከል ስማዊ ሀረጎችና ግሳዊ ሀረጎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ምክንያቱም ግንባር ለግንባር ተዋቅረው የቤቱን ጣሪያ የሚፈጥሩት እነሱ ናቸውና። ሌሎቹ ሀረጎች የእነዚሁ የሁለቱ አጎላማሾች ናቸው። ሀረጎቹ በቁዋንቁዋው የቃላት ክፍሎች አይነት ይወሰናሉ። ሰድስት የቃላት ክፍሎችን አግኝተናል። በየክፍሎቹ ውስጥ በሚገኙ ቃላት አማካኝነት የሚፈጠሩ ሰደስት አይነት ሀረጎችን አይተናል። እያንዳንዱ ሀረግ ከአንድ ቃላዊ መሪ፣ ከመሙሊያ፣ ከተለያዩ ግላጭ አጎላማሾችና መስተጓምሮች እንደሚመሰረት አይተናል። መሪው ቃል ሁል ጊዜ በስተቀኝ በኩል ይገኛል። በዚህም ቁዋንቁዋው ቀኝ መሪ እንደሆነ ተግንዝበናል።

አንድ ቤት ተራ ወይም ሰፊና ባለብዙ ፎቅ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆን እንደሚችል አይተናል። ይህም የሚወሰነው በውሰጡ በሚይዘው የሀረግ መጠን ነው። ብዙ ሀረግ የያዘ ውስብስብ ነው። ተግባሩም እንደዚሁ።

ከመጀመሪያ አንሰተን የቤቱን፣ ማለትም የአረፍተ ነገሩን መሰረተ ነገር የሆኑትን ድምፆች በመለየት፣ ከነዚህ የሚፈጠሩትን ምዕላድና ቃላት፣ ማለትም ብሉኬቶችን በአይነት በአይነታቸው በመመደብ፣ ወደ ሁዋላም በእነሱ አማካኝነት የሚፈጠሩትን ሀረጎች በማያያዝና አንዱን ከሌላው በማዋቀር፣ የተለያዩ ቤቶችን፣ ማለትም አረፍተ ነገሮችን፣ ስንሰራ ቆይተናል። ቤቶች ለልዩ ልዩ ተግባር እንደሚውሉ ሁሉ፣ አረፍተ ነገሮችም እንደዚሁ ለልዩ ልዩ ተግባር ይውላሉ። ማተቻ፣ ማለቻ፣ መጠየቂያ፣ ማዘዣ፣ መቃወሚያ፣ ወዘተ፣ የሆነ ተግባር እንዳላቸው በሰፊው አይተናል። እንደ ተግባራቸው ልዩነት ቅርፃቸውም ይለያያል። የመመገቢያና የማብሰያ ቤት አንድ አይነት አይሆንምና። የማተቻና የማለቻ አረፍተ ነገሮችም እንደዚሁ አንድ አይነት አይሆኑም፣ እንዳልሆኑም በዝርዝር አይተናል።

ወደፊት በሌላ ጊዜ እንገናኝ ይሆናል። እለከዚያው ግን ይህንኑ እየደጋገምን በማንበብ፣ ማንም ሰራየ ብሎ ሳያስተምረን፣ እኛም ለራየ ብለን ሳንይዘው፣ ከእድሜ ዘመናችን እጅግ ውሱን በሆነችው የልጅነት ጊዜአችን፣ ሳናውቀው ሰላወቅነውና፣ በማወቅም ያለምንም ችግር፣ እድሜ ልክ ሳይለለቸንና ሳያልቅብን፣ በማንኛውም ጊዜና ቦታ፣ ለማንኛውም ጉዳይ፣ ከማንኛውም የእኛ ቢጤ ጋር ለለምንጠቀምበት ቁዋንቁዋ፣ ያለን ዕውቀት ምን እንደሆነና፣ መጠኑም ምን ያህል እንደሆነ? እንዴትሰ እያደረግን እንደምንጠቀምበት እናሰላለል። በበኩሌ ባስብኩትና ባሰላለልኩት ቁጥር ግርም ይለኛል። ለየጥያቄው የማለበው መልለም ዛሬ ቀኝ፣ ነገ ግራ እየሆነ ያስቸግረኛል። ለለዚህም ቀኝ ነው ያልኩት፣ ግራ ከመሆኑ በፊት ተሻምቼ የያዝኩትን በትንሹ አቅርቢአለሁ። ነገ እንደምለቀው ግን በጣም ርግጠኛ ነኝ። ሌላ ቀኝ ፍለጋ... ለዚያውም ከተገኘ።

መልመጃ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ታህታይ መዋቅር ያመልክቱ።

1. እንደ ካሳ የተደለተ ሰው እለካሁን አላየሁም።
2. ማንንም እንዳላነጋገርኩ ለአስቴር ደብዳቤ ፃፍኩላት።
3. ያች ትናንት በግ የገዛችው ሴት አስቴርን ሰደበቻት።
4. ማን ነው ካሳ በግ ይገዛል ያለህ?
5. የአስቴር ቤት የመሰራት አላማ ብዙ ሰው አስደሰቶአል።
6. ልጆቹ ቤት ለመሰራት የፈለጉ ይመስላል።
7. አንተ ልጅ ተው ብየሀለሁ።
8. የት ነው አስቴር የሄደችው?
9. አቦ! ተው ክቶ አትናገር!
10. አቦ! የሚለውን ምዕላድ የቃል ክፍልና ሰዋሰዋዊ ተግባር ይግለፁ።

መዛግብተ ቃላት

ሀተታ፣ ስለ አንድ ነገር በዝርዝር የሚነገር ወይም የሚሰጥ አስተያየት፣ comment

ሁነት፣ የአንድ ነገር መሆን ወይም መከሰት፣ event

ህገ-መዋቅር፣ የሀረግና የአረፍተ ነገር የአመሰራረት ህግ ወይም ስርዓት፣ phrase structure rule

ለዋጭ ህግ፣ አንድን ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር ወደ ላዕላይ መዋቅር የሚለውጥ ህግ፣ ለምሳሌ፣ <u>ውሻው አስቴርን ነከሳት</u> የሚለውን አረፍተ ነገር <u>አስቴርን ውሻው ነከሳት ወደሚል</u> ተለዋጭ አረፍተ ነገር ለመለወጥ የምንጠቀምበት ህግ፣ transformational rule

ላንቃዊነት፣ አንድን የላንቃ ያልሆነ ድምፅ ከአጠገቡ በሚገኝ የላንቃ ድምፅ ተጋቦት ምክንያት ወደ ላንቃ ድምፅነት የሚቀይር የለውጥ ሂደት፣ palatalizainn

ላዕላይ መዋቅር፣ የሚባል፣ በአንደበት የሚነገር መዋቅር፣ surface structure

ልል፣ ጠብቆ የማይነገር ድምፅ፣ ለምሳሌ ፣[ግኧልኧብአ] <u>ገለባ</u> ሰንል፣ በግዕዘኑ ውስጥ ካሉት ድምፆች መካከል [ብ] ልል ነው። ባንፃሩ [ግኧንኧብብአ] <u>ገነባ</u> በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው [ብብ] ጥብቅ ነው። non-geminate

ልስት፣ አንድ አግድ ወይም ፍግድ ድምፅ ወደ ፈትግነት የሚለወጥበት ሂደት፣ weakening

ልምደት፣ አንድ ህፃን የአፍ መፍቻ ቋንቋውን የሚያውቅበት፣ የሚለምድበት ወይም አፍ የሚፈታበት ሂደት፣ acquisition

ልሳነ-ክልዔ፣ ሁለት ቋንቋዎ የሚናገር፣ bilingual

ልሳነ-ሳልስ፣ ሶስት ቋንቋዎ የሚናገር፣ tri-lingual

ልሳነ-ተፈጥሮ፣ ማንኛውም ሰው በተፈጠሮ ያለው የቋንቋዎ ችሎታ፣ linguistic competence

ልሳነ-ብዙ፣ በዙ ቋንቋዎ የሚናገር፣ multilingual

ልሳነ-ዋህድ፣ አንድ ቋንቋዎ ብቻ የሚናገር ሰው፣ monolingual

ልቅ፣ ከሳንባ ውስጥ የሚወጣው አየር ሳይታገድ እንደልቡ ቢወጣ የሚፈጠር የንግግር ድምፅ፣ ለምሳሌ እንደ [አ] ያለ አናባቢ ወይም አንደ [ም] ያለ ተናባቢ ድምፅ፣ non-obstruent

ልውጠት፣ አንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር የሚያደርገው የመቀየር ሂደት፣ ለምሳሌ ከቅጥነት ወደ ውፍረት የሚያደርገው ለውጥ፣ inchoative

መሙሲያ፣ አንድን ነገር በይዘቱ ሙሉ እንዲሆን የሚያደርግ ነገር፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ገደለ ብንል፣ አረፍተ ነገሩ በጥቅል፣ ግሱ ደግሞ በተለይ የሚሰጠን ሀሳብ ሙሉ አይሆንም። ሙሉ የሚሆነው፣ እንደ አንበሳ ያለ ሰማዊ ሀረግ ቀድሞት ሲገባና አረፍተ ነገሩም፣ ካሳ አንበሳ ገደለ የሚል ሲሆን ነው። ሙሉ የሚያደርገው አንበሳ የሚለው ስማዊ ሀረግ ስለሆነ፣ እንደዚህ ያለ ሀረግ መሙሊያ ይባላል። complement

መላሽ፣ ወደሁዋላ፣ ማለትም ወደ ግራ የሚመልሰ፣ አንድ ድምፅ ባህሪውን ቀድሞት ለሚገኝ ሌላ ድምፅ የሚያጋባበት የምስለሌሽ ሂደት፣ regressive

መላምታዊ፣ በመላ፣ በግምት፣ ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ አመለካከት፣ hypothetical

መስራች፣ አንድን ቃል ከሌላ ቃል ላይ የሚፈጥር ወይም የሚመሰርት ምዕላድ፣ ለምሳሌ /-ሽት/ የሚለው ምዕላድ ብልጥ ከሚለው ቅፅል ላይ ብልጠት የሚል ስም ስለሚመሰርት መሰራች ምዕላድ ነው። derivational

መስተዓምር፣ አንድን ነገር ከሌሎች ነገሮች ለይቶ የሚያሳይ ወይም የሚያሳውቅ ምዕላድ፣ specifier or determine

መቸት፣ መቸ እና የት ከሚሉት ቃላት ላይ የተመሰረተ ቃል፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፣ setting

መካነ-ናጥረት፣ በአንደበት ውስጥ፣ አንድ ድምፅ የሚፈጠርበት ቦታ፣

መዋቅር፣ ድምፅ ከድምፅ፣ ቃል ከቃል ወይም ከሀረግ፣ ወዘተ፣ ሲቀናጅ የሚፈጠረው ነገር፣ structure

መዋዋጫ፣ ምግብ ከአፍ ወደሆድ የሚወርድበት ቱቦ፣ esophagus

መጠነ-ሰፋት፣ የአንድ ነገር ባህሪ የሚሸፍነው የሀረግ መጠን፣ scope

መጠነ-ወርድ፣ የአንድ ነገር የወርድ ርዝመት ወይም መጠን፣ linear size

መጣኝ፣ የአንድን ነገር መጠን የሚያመለክት ቃል፣ ለምሳሌ ሁለት ተማሪዎች ሰንል፣ የተማሪቹን ስንትነት የሚጠቁመን ሁለት የሚለው አህዝ ነው። ስለዚህም መጣኝ መስተዓምር ነው። quantifier

ማንቁርታዊ፣ ወደ ማንቁርት ድምፅነት የተለወጠ ወይም ማንቁርት ላይ የተፈጠረ ድምፅ፣ glottalized

ማለት፣ [ምአልልኽት] በአንድ ቦታ ወይም ወቅት መገኘት፣ አለሁ ማለት፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ርሳስ አለው ስንል፣ አለው የሚለው የማለት ግስ ነው። ነገሩ አከለ ብሎ ማከል ከተባለ፣ አለ ብሎም ማለት ሊባል እንደሚችል የሚያሰረዳ ነው። verb to have

ማዕከል፣ የተለያዩ ነገሮችን አቅርና ደግፎ የሚቆም፣ nucleus

ማዕከላይ፣ በባለቤት ስም ላይ የሚፈፀምን ድርጊት የሚያመለክቱ ግሶች፣ middle voice

ማዕቀፍ፣ እቅፎ የሚይዝና ከሌላ የሚለይ፣ frame

ምህፃር፣ ሙሉውን ቃል ወይም መዋቅር አሳጥሮ የሚያሳይ ምልክት፣ abbreviation

ምዕላድ፣ አንድ ትርጉም ያለውና አነስተኛ ወደሆነ ትርጉም አዘል አሀድ ሊከፈል የማይችል ቅርፅ፣ ለምሳሌ ቤት፣ morpheme

ምስለት፣ ተነራባች ድምፆች ባህሪ የሚወራረሱበትና በዚህም ምክንያት የሚመሳሰሉበት ሂደት፣ assimilation

ምስረታ፣ አዳዲስ ቃላትን ከነባር ቃላት ላይ የመመስረት፣ የመፍጠር ሂደት፣ derivation

ምዝገባ ቃላት፣ ቃላትን በቅደም ተከተል ከነትርጉማቸው የመመዝገብና እጠቃቀማቸቀውንም የመግለፅ ተግባር፣ lexicography

ሞፈር ዘመት፣ ከመኖሪያ አካባቢ ርቆ የሚገኝ የእርሻ መሬት፣ far away farm

ሞይ፣ አንድ አረፍተ ነገር የአንድ መሪ ቃል መሙሊያ ሆኖ መግባቱን የሚያሳይ ምዕላድ፣ ለምሳሌ፣

ካሳ አስቴር እንደታመመች ስምቶአል

በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ እንደ የሚለው ምዕላድ አስቴር ታመመች የሚለው አረፍተ ነገር ስምቶአል ለሚለው ግስ መሙሊያ ሆኖ መግባቱን ያመለክታል። እንደዚህ ያለ ምዕላድ ሞይ ይባላል። complementizer

ሰበ-ነክ፣ ሰውን ብቻ ለይቶ የሚመለከት ባህሪ፣ human

ሰርን፣ ከአፍንጫ ቀዳዳ ጀምሮ እስከ እንጥል ድረስ ያለው ከፍት ቦታ፣ nasal cavity

ሰርገት፣ በሁለት ነገሮች መካከል ጣልቃ የመግባት ሂደት፣ epenthesis

ሰረ-ገብ፣ ስር በሚመሰርቱ ተናባቢዎች መካከል የሚገባ፣ root internal

ሰርጎ-ገብ፣ በሁለት ነገሮች መካከል ረልቅቆ የሚገባ፣ epenthetic

ሰርናዊ፣ አየር በሰርን በኩል አድርጎ ሲወጣ፣ አፍ ውስጥ የሚፈጠር ድምፅ፣ ለምሳሌ [ም] nasal

ሰርዓተ ቃላት፣ የቃላትን አጠቃላይ የርስበርስ ግንኙነት የሚገልፅ ህግ፣ lexical pattern or system

ስምሙ፣ በባህሪ የሚጣጣም፣ የሚስማማ፣ matching

ስር፣ መሰረት ወይም መነሻ፣ ለምሳሌ ክበደ ለሚለው ግስም ሆነ ክባድ ለሚለው ቅፅል መነሻ የሆነው /ክ-ብ-ድ-/ የሚለው

የሶስት ተናባቢዎች ቅንጅት ነው። እንደዚህ ያለ የተናባቢዎች ቅንጅት ስር ይባላል። root

ስነ-ልሳን፣ የቁዋንቁዋን ባህሪና አጠቃቀም የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፣ linguistics

ስነ-ቃላት፣ የቃላትን የአፈጣጠር ስርዓት የሚመለከት የስነ-ልሳን ዘርፍ፣ morphology

ስነ-ድምፅ፣ የአንድን ቁዋንቁዋ ድምፆች የአፈጣጠርና የአቀነጃጀት ባህሪ የሚመለከት የስነ-ልሳን ዘርፍ፣ phonetics/phonology

ስነ-አዕምሮ፣ የሰውን ልጅ ባህሪና የእንሳልን ግንኙነት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፣ psychology

ስነ-ዘዴ፣ የማስተማር ጥበብ፣ የምርምር አካሄድ፣ methodology

ሳቢ፣ የሚስብ፣ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን በመሙሊያነት የሚፈልግ፣ transitive

ሰዋዊ፣ ሰውን የሚመለከት ተውላጠ ስም፣ ስምሳሌ አንተ፣ እኔ፣ ወዘተ፣ personal

ረቢ፣ ቅርፁን እየለዋወጠ ሊረባ፣ ሊበዛ የሚችል ቃል፣ productive

ርባታ፣ ቃላት የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ባህሪያትን ለማሳየት ቅርፃቸውን በመጠኑ የሚለዋውጡበት ሂደት፣ inflection

ርዕስ፣ ለአረፍተ ነገርም ሆነ ለድርሰት መነሻ የሚሆን፣ በተለምዶ አርዕስት የምንለው ክፍል፣ topic

ርቱዕ፣ ከአንድ መሪ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስማዊ ሀረግ፣ ለምሳሌ፣ <u>ካሳ ለአስቴር ገንዘብ ሰጣት</u> በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ <u>ሰጣት</u> ከሚለው ግስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው፣ <u>ገንዘብ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ካሳ ከእጁ አውጥቶ የሰጠው ነገር እሱ ነውና። direct

ርግብግቢት· ግንቁርት ውስጥ የሚገኙ ተርገብጋቢ ጡንቻዎች፣ vocal folds

ቀለም፣ የአንድ አናባቢ፣ ወይም የአንድ አናባቢና የተናባቢ(ዎች) ቅንጅት፣ syllable

ቀለማይ፣ የአንድ ቀለም ምሰሶ ሆኖ ሊገባ የሚችል ድምፅ፣ syllabic

ቀሬነት፣ በመዋቅር ውስጥ በቦታ ሳይገኙ የመቅረት ወይም የመገደፍ ችሎታ፣ optionality

ቀጣይ፣ ሲነበብ ትንፋሽ የማያስቆርጥ፣ continuant

ቀድሞ-ገብ፣ በቃል መነሻ ላይ ከተናባቢ ቀድሞ የሚገባ አናባቢ፣ prothetic

ቃለ-ጥያቄ፣ አንድ አረፍተ ነገር መጠይቃዊ መሆኑን የሚያመለክት ምዕላድ፣ question particle

ቅላፄ፣ የድምፅ ከፍታና ዝቅታ ማለት፣ intonation

ቅምር፣ የአንድ ነገር ሂደት ወይም ውስጣዊ ቅንጅት የሚገለፅበት ሀግ፣ formula

ቅናጅ፣ የሁለት ነገሮች ቅንጅት፣ composite

ቅድመ-መድረሻ፣ ከአንድ ምዕላድ ወይም ቃል ወይም መዋቅር መጨረሻ አካል በፊት የሚገኝ ሌላ አካል፣ penultimate

ቅየራ፣ አንድ ነገር ከአጠገቡ ከሚገኝ ሌላ ነገር ጋር ቦታ የሚቀያየርበት ስርዓት፣ methathesis

በይነ-ልሳናዊ፣ በቋንቋዎች መካከል የሚታይ የጋራ ባህሪ፣ inter-lingual

ባህርየ ንባብ፣ አንድ ድምፅ የሚፈጠርበት ባህሪ፣ manner of articulation

ባለቤት-አልባ፣ ባለቤቱ በግሀድ ሊከሰት የማይችል አረፍተ ነገር፣ subjectless

ብለት፣ አለ ከሚለው ግስ ስር ሊወጣ የሚችል ስም፣ የአንድን ነገር መባል ወይም መነገር የሚገልፅ፣ ጋለ ብለን ግለት እንደምንል ሁሉ፣ አለ ብለንም ብለት ማለት እንደምንችል ለማሳየት፣ quotative, verb to say

ተርታ ተከታታይ፣ በመካከላቸው ጣለቃ ሳያስገቡ የሚከታተሉ፣ contiguous or immediately adjacent

ተሞያ፣ በአንድ መመሪያ ወይም አጎላማሽ ቦታ ላይ የሚሞላ ወይም የሚገባ መዋቅር፣ (sentential) complement

ተስተጋብሮት፣ የብዙ ነገሮች የርስበርስ ድርጊት፣ interaction

ተቃርኖ፣ ርስበርሱ የሚጋጩ አስተያየት፣ contradiction

ተነጋሪ፣ የሚነገር፣ ማለትም ነገር የሚቀበል ወይም የሚያዳምጥ ሰው፣ addressee

ተናባቢ፣ ከሳንባ የሚነሳ አየር እየታገደና አየተለቀቀ ሲወጣ የሚፈጠር የንግግር ድምፅ፣ consonant

ተናጠላዊ፣ ብቸኛ፣ የተነጠለ፣ segmental

ተገባሪ፣ የሚደረግ ወይም ድርጊት የሚፈፀምበት፣ ለምሳሌ ካሳ ተደበደበ ስንል፣ ካሳ ተገባሪ ባለቤት ነው። patient

ተገንዛቢ፣ የሚዛመድ፣ የሚገናዘብ፣ possessed noun

ተጋቦት፣ የአንድ ነገር ባህሪ ወደሌላ ነገር የሚዛመትበት ሂደት፣ influence

ተናጠላዊ፣ በተናጠል ወይም በብቸኝነት የሚገኝ ባህሪ፣ independent

ተዋረድ፣ ሽማያ፣ ማለትም ተጉዋዳኝ ሳይሆን፣ ላይና ታችነት የሚታይበት የአወቃቀር ስርዓት፣ hierarchical

ተዋቃሪ፣ አንድ ላይ የሚገናኙና መዋቅር የሚፈጥሩ አካላት፣ constituent

ተዛማጅ፣ የሚዛመድ፣ የሚጣቀስ፣ relative

ተውላጥ፣ ምትክ፣ እንድን ነገር ተክቶ የሚገባ፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል ብለን፣ እንተለ? የሚል ጥያቄ ብናሰክትል፣ እኔም እሄዳለሁ፣ የሚል መልስ ልናገኝ እንችላለን። እኔም በሚሰው መልስ መድረሻ ላይ የምትታየው /-ም/፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚለው መሰተዋድዳዊ ሀረግ ምትክ ወይም ተውላጥ ነች። pro-form

ተውላጠ መሪ፣ እንድን መሪ ቃል የሚተካ፣ የመሪ ምትክ፣ pro-head

ታህታይ መዋቅር፣ በአንደበት የሚባል ሳይሆን፣ በአዕምሮ የሚታሰብ፣ የሚታወቅ መዋቅር፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ተሰደበ ሰንል፣ ካሳን የሰደበው ሰው እንዳለ ይሰማናል። አንድ ሰው ካሳን ሰድቦታል ማለታችን ነው። ግን ማን እንደሆነ አይታወቅም። ይህን ሰሜት የሚይዝ መዋቅር ታህታይ ይባላል። ካሳ ተሰደበ የሚሰው የዚህ ላዕላይ ወይም አንደበታዊ ቅርፅ ነው። deep structure

ትናጋዊነት፣ አንድ የትናጋ ያልሆነ ድምፅ ወደ ትናጋ ድምፅነት የሚለወጥበት ሂደት፣ velarization

ትውረት፣ theory

ትውፊት ሳይፃፍ በቃል ብቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ህዝባዊ ባህል፣ folklore

ነባር፣ የነበረ፣ የኖረ፣ base

ነቢብ-ነገር፣ የሚነገር፣ ከአንደበት የሚወጣ ነገር፣ expression

ኑረት፣ የመኖር፣ በአንድ ቦታ የመገኘት ሁኔታ፣ existence

ንበት፣ አንድ ድምፅ የሚነበብበት ሁኔታ፣ pronunciation

ነዛሪ፣ ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ተርገብጋቢ ጡንቻዎች ሲነዝሩ የሚፈጠር ድምፅ፣ voiced

ነጣይ፣ አንድን ነገር ከሌሎች ነገሮች ነጥሎ፣ ማሰትም ለይቶ፣ የሚያሳይ፣ singulative

ከፍናቢ፣ ከፊል አናባቢ የሚለውን ሀረግ በማሳጠር የተፈጠረ አጭር ቃል፣ semi-vowel

ከፋች፣ የቀለም መጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ፣ onset

ከናፍራዊነት፣ የከናፍር ያልሆነ ድምፅ ወደ ከናፍር ድምፅነት እንዲለወጥ የሚያደርግ ሂደት፣ labialization

ከበት፣ ከንፈርን የመከበብ ሁኔታ፣ ለምሳሌ ሙሉ ሰንል ከንፈራችን ክብ ይሆናል፤ rounding

አሀድ፣ አንድ አካል፣ unit

አለላላሽ፣ አንድ ነገር ለሰለሰና ረጋ ባለ ሁኔታ የሚፈፀም መሆኑን የሚያመለክት ቅርፅ ለምሳሌ፣ ከፈት፣ ለቀቅ፣ ወዘተ፣ attenuative

አላች፣ የሚያልት፣ አሉ ወይም ሀሰት የሚል፣ negator

አምድ፣ ቅጣይ ምዕላድ ሊያሰከትል ወይም ሊያስቀድም የሚችል ቅርፅ፣ ለምሳሌ ውርደት የሚለውን ሰም ብንመለከት፣ ውርድ ከሚለውና /-ኧት/ ከሚለው መስራች ምዕላድ የተፈጠረ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ውርድ የሚለው አምድ ሲሆን /-ኧት/ ቅጣይ ምዕላድ ነው፡፡ stem

አሰላሳይ፣ የሚያሰላስል፣ የሚያስተውል፣ speculator, thinker

አሸቃቢ፣ ሞቅ - ደመቅ ብሎ የሚሰማ፣ ጎርናና፣ sonorant, sonorous

አቃፊ፣ ከዝቅተኛ ወይም መሀከለኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚወጣ ቅላፄ፣ rising intonation

አቀልቁዋይ፣ አንድን አረፍተ ነገር አቅፎ በውሰጡ የሚይዝ፣ matrix

አቆራኝ ከከፍተኛ ወይም መሀከለኛ ደረጃ ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የሚወርድ ቅላፄ፣ falling intonation

አበላላጭ፣ ሁለት ነገሮችን የሚያያይዝ፣ የሚያቆራኝ፣ copular

አታች፣ ሁለት ነገሮች የሚበላለጡ መሆናቸውን የሚገልፅ፣ ለምሳሌ፣ ከካሳ ይልቅ አስቴር ረዥም ነች፣ ስንል ይልቅ የሚለው አበላላጭ ምዕላድ ነው፡፡ comparative

አንድምታ፣ የሚያትት፣ ሀተታ የሚሰጥ፣ declarative

አንጉዋ፣ አንድ ነገር ሲነገር ወይም ሲፃፍ፣ በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ የሚሰጠው ወይም ሊሰጥ የሚችለው ተጨማሪ ፍች ወይም መልዕክት፣ implication

አደላዳይ፣ መለያያ ቦት፣ መንታ መንገድ፣ አንድ መዋቅር ወደ ሁለት ወይም ወደ ሶስት ከፍሎች የሚከፈልበት ቦታ፣ node

አነናዛቢ፣ ሁለት ነገሮች እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ ምዕላድ፣ ለምሳሌ ካሳ እንደ አባቱ ረዥም ነው፣ ሰንል፣ ካሳ እና አባቱ እኩልረዥም መሆናቸውን እንገልፃለን፡፡ አንደ የሚለው አደላዳይ ምዕላድ ነው፡፡ positive or equative

ባለገንዘብን ወይም ባለድርጊትን የሚያመለክት ምዕላድ፣ ለምሳሌ፣ካሳ ቤቱ ተቃጠለበት ወይም ካሳ መሄዱ ተሰማ ስንል፣በመጀመሪያው ምሳሌ፣ /-ኡ/ የሚለው ምዕላድ ካሳ የቤቱ ባለቤት መሆኑን ያሳያል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ

ደግሞ ይኸው /-ኡ/ ካሳ የመሄድ ተግባሪ ፈፃሚ ወይም ሂያጅ መሆኑን ያመለክታል። genitive

አጎላማሽ፣ የሚያሳድግ፣ የሚያጎላምስ፣ ለምሳሌ ተውሳክ ግሶችና ቅፅሎች፣ modifier

አጎላቢች የሚያጎለብት፣ የሚያጎላ፣ augmentative

አጉዋዳኙ፣ በጉዋድ፣ በጉዋድ የሚከፋፍል፣ someone and Co.

አይረቤ፣ ቅጣይ እየፈመረ የማይረባ መሀን ቃል፣ unproductive

አውደ-ነገር፣ አንድ አረፍተ ነገር የሚነገርበት ሁኔታ፣ context

አጠንካሪ፣ አንድ ነገር በጠነከረ፣ በከረረ ሁኔታ የሚፈፀም መሆኑን የሚያመለክት፣ ለምሳሌ፣
ካሳ በሩን ክፍት አደረገው፣
ለንል፣ቤቱ በሀይልና በድንገት መከፈቱን እንገልፃለን። intensive

አዛማጅ፣ የሚያዛምድ የሚያገናኝ፣ relative

አፀፋ፣ አንድን ነገር የሚጠቅስ ወይም የሚያመለክት ምዕላድ፣ ለምሳሌ የባለቤት አፀፋ፣ reflexive

አፅንያት፣ በጉልህ፣ በጥንካሬ፣ የሚወጣ ወይም የሚነገር፣ emphatic, focused

ኢሀላፊ፣ ያላለፈ ወይም ያልተፈፀመ ድርጊት፣ non-past

ኢሳቢ፣ የማይሰብ፣ ተሳቢ የማይፈልግ፣ intransitive

ኢሰዋዊ፣ ሰው ነክ ያልሆነ፣ ለምሳሌ፣ ካሳ አንደተቀየመ ግልፅ ነው፣
ለንል፣ ግልፅ ነው የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት አሱ የሚለው ሰዋዊ ተውላጠ ስም ሳይሆን፣ it የሚለው ኢሰዋዊ ተውላጠ ስም ነው። በአማርኛ ይህ ተዋላጠ ስም ድምፅ የለውም፣ በአፀፋ ብቻ ይጠቀሳል። impersonal

ኢርቱዕ፣ ቀጥተኛ ያልሆነ፣ indirect

ኢቀለማይ፣ ብቻውን ቀለም ሊመሰርት የማይችል ድምፅ፣ ለምሳሌ ተናባቢ ድምፅ፣ non-syllabic

ኢነዛሪ፣ የማይነዝር፣ ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ጅማቶች በማይርገበገቡበት ጊዜ የሚፈጠር ድምፅ፣ voiceless

ኢድምፀት፣ አንድ ነዛሪ የሆነ ድምፅ ወደ ኢነዛሪ ድምፅነት የሚለወጥበት ሂደት፣ devoicing

እሰር፣ ነፃ ያልሆነ፣ ብቻውን የማይቆም፣ ምሳሌ፣ ውፍር-፣ ድፍር-፣ ወዘተ፣ bound

እግድ፣ አየር ታግዶ በአንድ ጊዜ ሲለቀቅ የሚፈጠር ድምፅ፣ stop / plosive

አሌት፣ አሌ፣ ወይም ሀሰት የማለት ሂደት፣ negation

አልት፣ ሀሰት የተባለ ነገር፣ negated

ዕምር፣ ከሌሎች ተለይቶ የታወቀ፣ definite

ዕምርነት፣ ዕውቅነት፣ definiteness

ዕቅፍ፣ የታቀፈ፣ በሌላ ስር የሚገኝ፣ embedded

ዕፀ-መዋቅር፣ በአንድ አህድ ውሰጥ የሚገኙ ሀረጎችንና መሪዎችን ዝምድና የሚያሳይ ዛፍ-መሰል ስዕል፣ tree structure

ውሁድ፣ መሰረቱ ሁለት ሆኖ፣ በሂደት ተዋህዶ አንድ አካል የሆነ፣ unified, lexicalized

ውልድ፣ ከነባር ቃል ላይ የተመሰረተ ቃል፣ ለምሳሌ ጉልበተኛ የሚለው ቃል፣ ጉልበት ከሚለው ነባር ቃል ላይ የተመሰረተ ወይም የተወለደ ቃል ነው። derived

ውስብስብ፣ ተራ ያልሆነ፣ ጥልቅ የሆነ ሰርዓት የሚታይበት፣ complex

ውስጠ-ገብ፣ ወደ ውሰጥ የሚገባ፣ ወደራሰ የሚመለሰን ድርጊት ወይም ሁኔታ የሚያሳይ ግሰ፣ ለምሳሌ፣ <u>ካሳ ተጎዳ፤</u> ስንል፣ <u>ካሳ</u> ተጎጅ ባለቤት መሆኑን እንገልፃለን። ጉዳቱ ከሌላ ሰው ወደ እሱ የመጣ ነው። reflexive

ውሰጠ-ቀር፣ ወደ ሌላ ሰው የማይሻገር ድርጊት፣ በአድራጊው ላይ ብቻ የሚወሰን፣ ለምሳሌ፣

<u>ካሳ ተነሰ</u>

ስንል፣ የመነሳት ድርጊት በካሳ የሚፈፀምና በራሱም የሚቀር መሆኑን እንገልፃለን። auto-benefactive/malfactive

ዘረፍኒም፣ የፎኒም ዘር፣ የአንድ ፎኒም ልዩ ልዩ ቅርፅ ወይም ክሳች፣ allophone

ዘረ-ቢስ፣ ዘር የሌለው፣ ሊረባ የማይችል፣ unproductive

ዘፈቀዳዊ አንደመሰለ፣ ልብ እንደ ፈቀደ የሚፈፀም ተግባር፣ arbitrary

ዝርግ፣ ክብ ያልሆነ ድምፅ፣ ለምሳሌ <u>ሚ</u>ሚ ስንል፣ ከንፈራችን ይዘረጋል፣ ቡቡ ሰንል ደግሞ ይከበባል፣ unrounded

ገስጋሽ፣ አንድ ድምፅ ባህሪውን በቀኙ በኩል ላለ ሌላ ድምፅ የሚያጋባበት የምሰሰሉሽ ሂደት፣ progressive

ገባሪ፣ ድርጊት ፈፃሚ፣ agentive

ገንዛቢ፣ ሰእንድ ነገር ባለቤት ወይም ባለገንዘብ የሆነ፣ possessor

ግላጌ፣ ሰለ አንድ ነገር ምንነት፣ ተግባር፣ ወይም ባህሪ፣ የሚሰጥ መግለጫ፣ definition

ግብዓት፣ የሚገባ፣ የሚያገዝ፣ input

ጎነ-ሳልስ፣ ባለሶስት ጎን ግዕዘን፣ triangle

ደራራጊ፣ ወዲያው ወዲያው የሚፈፀም ተደጋጋሚ ድርጊት፣ iterative

ደጋጋሚ፣ አንድ ድርጊት ተደግሞ ተደግሞ የሚፈፀም መሆኑን የሚያሳይ ግሰ፣ frequentative

ዳራ፣ ሁዋላ፣ መነሻ፣ background

ድላንቃ፣ በድድና በላንቃ መካከል የሚገኘውን ቦታ ለመሰየም፣ ድድ እና ላንቃ ከሚሉት ቃላት የተፈጠር አጭር ቃል፣ alveopalatal

ድምፅ-የለሽ፣ ሲባል፣ በእንደበት ሲነገር የማይችል ምዕላድ፣ ለምሳሌ ካሳ ጠጅ መጠጣት ያዘወትራል፣ በሚለው ውስጥ፣ ጠጅ መጠጣት የሚለው ሀረግ ባለቤት፣ ድምፅ የለሽ ነው።። በትርጉሙ ካሳ ከሚለው ስም ጋር እንድ ነው።። ካሳ የሚለው ስም ግን ያዘወትራል የሚለው ግሰ ባለቤት ነው።። empty

ድምፀት፣ ነዛሪ ድምፆች የሚፈጠሩበት ሂደት፣ voicing

ድርሳን፣ ሰለ አንድ ነገር የሚሰጥ አስተያየት፣ comment

ድሀረ-ገብ፣ በቃል መድረሻ ላይ ተናባቢን ተክትሎ የሚገባ አናባቢ፣ syncope

ድንጋሬ፣ መደናገር፣ ግራ መጋባት፣ ድንጋጤ ቦሚለው ቃል አምሳያ የተፈጠረ፣ confusion

ዱካ፣ አንድ ነገር ቦታውን ሲለቅ የሚተወው ምልክት፣ trace

የተፀውዖ ስም፣ የአንድ ሰው የግል መጠሪያ የሆነ ቃል፣ proper noun

ጠቁዋሚ፣ አንድን ነገር ከሚገኝበት ቦታ ወይም ጊዜ አኩዋያ ከሌሎች ለይቶ የሚያመለክት፣ deictic

ጥብበ-ነገር፣ ዕውቀት፣ ስለማንኛውም ነገር ያለን ግንዛቤ፣ cognition

ጥብቅ፣ ሲነበብ ምላሰን ጫን የማድረግ ባህሪ ያለው ድምፅ፣ geminate

ጥመራ፣ ቃል ክቃል እየተቀናጀ ጥምር ቃል የሚፈጥርበት ሂደት፣ compounding

ጥምር፣ በጥመራ የሚፈጠር ቃል፣ ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር፣ compound

ጥቁምነት፣ የመጠቆም ወይም ተለይቶ የመታወቅ ሁኔታ፣ indexicality

ጨራሽ የቀለም የመጨረሻ ተናባቢ ድምፅ፣ coda

ፅንሰ-ቃላት፣ ገና ያልተወለደ፣ ያልተመሰረተ ቃል፣ potential word

ፍትግ፣ የድምፅ መውጫ ቀዳዳ ሲጠብና እየር ሲፋተግ የሚፈጠር ድምፅ፣ fricative

ፍግድ፣ እየተፋተገና እየታገደ የሚወጣ ድምፅ፣ ቃሉ ፍትግ እና እግድ ከሚሉት ቃላት ተቀናጅቶና ተጎርዶ የወጣ ነው።። affricate

ፎኒም፣ ትርጉም ለይ፣ ማለትም በሁለት ቃላት መካከል ለሚከሰት የትርጉም ልዩነት ምክንያት የሚሆን ድምፅ፣ phoneme

ዋቢ

መንግሥቱ ስማ፣ 1963፣ የአማርኛ ግጥም አይነቱ፣ ሥረቱ፣ ሥርዓቱ፣ *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት*፣ ቅፅ 1፣ ቁ. 1፣ *(133-149)*።።

በዕምነት ገብረ አምላክ፣ 1947፣ *የአንድ ቋንቋ አድገት - አማርኛ እንዴት እንደ ተሰፋፋ*፣ አዲስ አባባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።።

ባየ ይማም፣ 1984፣ ስርዓተ ፅህፈት፣ *ውይይት*፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር መፅሄት፣ መጀመሪያ ቅፅ፣ (17-41)።።

ባየ ይማም፣ 1987፣ *የአማርኛ ሰዋሰው*፣ አዲስ አበባ፣ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማተሚያ ቤት።።

ባየ ይማምና ቲም 89፣ 1989፣ ፌደል አንደገና፣ *የኢትዮጵያ የቁዋንቁዋና ሰነ ፅሁፍ መፅሄት*፣ ቅፅ 7፣ (1-23)።።

ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወ.መ. 1959፣ *አማርኛ ቅኔ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።።

ብላታ መርስዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ 1948፣ *የአማርኛ ሰዋሰው*፣(4ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።።

ብርሃኑ ገበየሁ፣ 2000፣ ምጣኔ በአማርኛ ስነ ግጥም፣ በተሾመ ይመር አበባው፣ "የአማርኛ ግጥም አይነቶች" *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት*፣ ቅፅ 33፣ ቁ. 1፣ (67-103)።።

ተክለ ማርያም ፋንታዬ፣ 1944፣ *ሆሀተ ጥበብ ዘሰነ ፅሁፍ*፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳዔ ዘጥዋዔ ማተሚያ ቤት።።

ተሾመ ይመር አበባው፣ 1997፣ የአማርኛ ግጥም አይነቶች፣ *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት*፣ ቅፅ 30፣ ቁ. 1፣ (89-118)።።

ደረጀ ገብሬ፣ 1975፣ ምት በስነ ግጥም ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ቁዋንቁዋዎችና ስነ - ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ድግፅ።።

ጌታሁን አማረ፣1990፣ *የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ*፣ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት።።

Abraham Demoz. 1968. Amharic for Modern Use. *Journal of Ethiopian Studies*. 2:1, (15-30).

---------and Haylu Fulass. 1970. The Adjectival and the Näw Clauses in Amharic *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies*, II, (81-87). Addis Ababa, Haile Selassie I University.

Aday Abebe. 1987. The Role of the Ethiopian Revolution in the Development of Amharic Vocabulary. BA thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Afeworq G.J. 1905. *Grammatica della Lingua Amarica*. Rome.

Alemayehu Haile. 1987. An Autosegmental Approach to Amharic Intonation. PhD thesis, School of Oriental and African Studies, University of London.

---------.1988. Lexical Stress in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, 20, (19-43).

---------.1990 An Autosegmental Approach to Some Amharic Declarative and Interrogative Contours. *Proceedings of the First National Conference of Ethiopian Studies*, (449-460). Addis Ababa University.

---------1991. The Morphological Structure of the Imperative Stem in Amharic. *The Ethiopian Journal of Education*, XII:1, (62-76).

---------1995.Is Syllabic Weight Distinction Relevant for Amharic Stress? *Journal of Ethiopian Studies, XXVIII:2, (15-25)*

Appleyard, D. 1972. A- and As- verb forms in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 35, (18-26).

Armbruster, C.H. 1908. *Initia Amharica, Part I, Grammar*. Cambridge: University Press.

Aster Taddese. 1981.The Syllable Structure of Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Ayele Bekerie. 1997. *Ethiopic: an African Writing System, its History and Principles*, Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press.

Bach, E. 1970. Is Amharic an SOV Language? *Journal of Ethiopian Studies*, VIII, (9-20).

Baye Yimam. 1988(a). Towards a Definition of Nominal Specifiers in Amharic. In: Taddese Beyene, (ed), *Proceedings of the Eight International Conference of Ethiopian Studies*, (599-613). Addis Ababa University.

---------1990. Raising in Amharic. *Langue Orientale Ancienne de Philologie et de Linguistique*, 2:1, (231-256).

---------1994. Unaccusative Structures in Amharic. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1238-1253). New Jersey: Red Sea Press.

---------1996. Definiteness in Amharic Discourse. *Journal of African Languages and Linguistics*, 17, (47-83).

---------1997. The Verb to Have in Amharic. In: Fukui, K. et al, (eds.), *Ethiopia in Broader Perspective: Proceedings of the Thirteenth International Conference of Ethiopian Studies*, (619-638). Kyoyo, Japan.

---------1999(a). The Verb to Say in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, XXXII: 1, (1-50).

---------1999 (b) .Root Extension and Reduction in Amharic. *Ethiopian Journal of Language and Literature*, 9 , (56-88)

--------- 2004. Agreement Phenomena in Amharic. In Verena Böl et al. *Studia Aetiopica. In Honour of Siegbert Uhlig on the Occasion of his 65th birthday*, (319-337) Wiesbaden: Harrassowitz Verlag.

……. 2006. The morphosyntactic properties of the form *bičč* in Amharic. In: Siegberg Uhlig (ed.) *Proceedings of the 15th International conference of Ethiopian Studies.* (715-26) Wiesbaden: Harrassowitz Verlag

---------2006. The Interaction of Tense, Aspect, Agreement in Amharic Syntax. In: John Mugane et al (eds.), Selected Proceedings of the 35th Annual Conference of African Linguistics. Somerville, MA.: Cascadilla Proceedings Project, (193-202), www.lingref.com, document #1309

---------(in progress) The Structure of DP in Ethiopian Semitic: Amharic.

Bender, M.L. 1974. Amharic Verbal Types from Text to Lexicon. *Folia Orientalia,* 15 (23-46).

——— et al. 1976. The Amharic Language. In : Bender et al (ed) *Language in Ethiopia.* London: Oxford University Press. (77-98)

--------- 1983. The Origin of Amharic. *Journal of the Institute of Language Studies.* Addis Ababa University, 1:1, (14-52).

Benneth, M.E. 1978. Stratificational Approach to Amharic Phonology. MA thesis, Michigan State University.

Beza Tesfaw. 1997. Causativization in Amharic. MA Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

Bliese, L. 1979. Constraints on Clitics in Amharic. F*olia Orientalia*, (113-142).

-------- 1988. A Discourse Analysis of Amharic Narratives. In: Taddese Beyene (ed) *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*, (613-621), Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

Cohen, M. 1970 (2nd Edition). *Traite de Langue Amharic.* Paris: Institut d'Ethnolgie.

Cotterell, F.B. 1964. Amharic Word Classes. *Journal of Ethiopian Studies*, II:1, (11-33).

——— 1966. The Amharic Primary Neutral Sentence. *Journal of Ethiopian Studies*, IV:2, (33-48).

——— 1973. Control in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, 7:1, (75-106).

Cowley, R. 1969. A and B Verbal Stem Types in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies.* VII:1 (1-33)

---------. 1976. The Standardisation of Amharic Spelling. *Journal of Ethiopian Studies*, V:2, (1-18)

Dawkins, C.H. 1960. *The Fundamentals of Amharic.* Addis Ababa: Sudan Interior Mission.

Degif Petros Banksira. 2000. *Sound Mutations, the Morphophonology of Chaha.* Philadelphia/Amsterdam: John Benjamins Publishing Company.

Demissie Manahlot. 1977. Nominal Clauses in Amharic. PhD Dissertation, Georgetown University.

-------- 1988. On Amharic Performative Verbs. In:Taddese Beyene (ed) *Proceedings of the Eighth International conference of Ethiopian Studies* (623-629). Institute of Ethiopian Studies.

Demeke, G. Awigichew. 2000. The Structure of IP in Amharic. A paper presented at the 14th International Conference of Ethiopian Studies, Addis Ababa University

----------2001. N-Final Relative Clauses in Amharic. Studia Linguistica, vol.55 :2, (192-216)

----------2004. The Clause Structure of Ethiopian Semitic. PhD Dissertation, University of Tromso.

Ehret, Christopher. 1988. Social Transformation in the Early History of the Horn of Africa: Linguistic Clues to Development of the Period 500 B.C. to AD 500. In: Taddese Beyene (ed.) *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*.Vol. I, (639-651), Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

Ferguson, C. 1976. The Ethiopian Language Area. In: Bender, et al, (eds.), *Language in Ethiopia.* Oxford University Press, (64-76).

Gasser, M. 1985. Amharic –m and –ss, Morphology, Theme and Assumed Knowledge. *Lingua.* 65:1/2, (56-106).

Getachew Haile. 1967. Demonstrative Pronouns in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies,* V, (9-12).

--------1971. The Suffix Pronouns in Amharic. *Papers in African Linguistics*, (101-111).

--------1972. The Copula naw in Amharic. *Proceedings of the Fourth international Conference of Ethiopian Studies,* (139-154). Rome,

--------1970. Archaic Amharic Forms. *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies,* II, (61-80), Institute of Ethiopian Studies, Haile Selassie I University.

Getahun Amare. 1995. Baye Yimam: yamariñña säwasäw (Amharic Grammar), *Journal of Ethiopian Studies*, XXVIII:2, (51-60).

Girma Halefom. 1992. An Initial Wh-filter in Amharic. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*, 2, (75-94).

--------- 1994. The Morphologically "Incomplete" Agreement Paradigms in Amharic. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1249-1260). New Jersey: Red Sea Press.

---------1994. The Syntax of Functional Categories: A Case Study of Amharic. PhD Dissertation, Montreal, Universite Du Quebec a Montreal.

Girmay Berhane. 1992. Word Formation in Amharic. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*, 2, (50-74)

Goldenberg, G. 1964. On the Amharic Tense System. *Proceedings of the Second International Conference of Ethiopian Studies,* (47-49). Manchester.

--------- 1965. Studies in Amharic Syntax. *Journal of Ethiopian Studies*, III:1 (6-22).

Habte Mariam Marcos. 1973. Regional Variation in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies.* Vol. XI:1, (113-129)

Hartmann, J. 1980. *Amharishe Grammatik.* Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.

Haylu Fulass. 1964. Derived Nominal Patterns in Amharic. PhD Thesis, UCLA.
-------- 1967. The Particle yä in Amharic. *Rassegna di studi etiopici*, 20, (103-119).
-------- 1968. Notes on the Verbal Noun and Possession Markers. *Journal of Ethiopian Studies*, 6:2, (71-76).
-------- 1972. A Pseudo-object Construction in Amharic. *Proceedings of the Fourth International Conference of Ethiopian Studies*, (115-125). Rome.
-------- 1972. Relative Clause in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 35, (497-515).
-------- 1980. On Imperatives in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, XIV, (87-96).
-------- and Bender, M.L. 1978. *Amharic Verb Morphology*. East Lansing: Michigan State University, African Studies Center.
-------- Getachew Haile, and Roger Cowley. 1976. Dialect Variation in Amharic. In: Bender et al, (eds.), *Language in Ethiopia*. London: Oxford University Press, (90-99).
Hayward, R.J. (n.d.) The High Central Vowel in Amharic: New Approaches to an Old Problem. In: Fishman, J. (ed), *From Phonology to Society*, (301-325).
--------1991. A Propos Pattern of Lexicalization in the Ethiopian Language Area. *Afrikanstische Arbeitspapiere*.
Hebo, P. A. 1955. *Grammatica Amharica*. Asmara: Scuola Tipografica Francescana.
Hetzron, R. 1966. Pronominalization in Amharic. *Journal of Semitic Studies*, 2:1, (71-76).
--------1970. Towardss an Amharic Case Grammar. *Studies in African Linguistics*, 1:3, (304-354).
--------1972. Ethiopian Semitic: Studies in Classification. *Journal of Semitic Studies*, Monograph No 2., Manchester University.
Hodson, A. and C.H. Walker. 1922. *An Elementary and Practical Grammar of the Oromo Language*. London: Society for Promoting Christian Knowledge.
Hudson, G. 1972. Why Amharic is not a VOS Language. *Studies in African Linguistics*, 3.
--------1978. Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory. *Language Miscelanea*. Institute of Ethiopian Studies.
-------- 1981. Evidence of the Nominal Origin of the Perfect in Amharic. In: Segert, Stanislav, (ed). *Ethiopian Studies*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz.
-------- 1985. The Principled Grammar of Amharic Verb Stems. *Journal of African Languages and Linguistics*, 7:1, (39-58).
Isenberg, W.C. 1842. *Grammar of the Amharic Language*. London: Church Missionary Society.
Kapeliuk, O. 1969. Auxiliaires en amharique. *Proceedings of the Six international Conference of Semitic Studies*, 1-16. Jerusalem.
-------- 1978. Particles of Concatenation and Reference in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 14, (272-282).
-------- 1980. Pseudo Questions in Amharic. *Proceedings of the Six International conference of Ethiopian Studies*, (337-341). Tel-Aviv.

--------1984. Semantic Analysis of Some Morphological Phenomena. In: Taddese Beyene (ed). *Proceedings of the Eighth International conference of Ethiopian Studies*, (697-703). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

-------- 1988 *Nominalization in Amharic*. Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.

--------1994. The Evolution of ïrswo and ïrsaccäw as Sociolinguistic Variants. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1270-1281). New Jersey: Red Sea Press.

-------- 1994. *The Syntax of the Noun in Amharic*. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag

Leslau, W. 1945. The Influence of Cushitic on the Semitic Languages of Ethiopia. A Problem of Substratum. *Word*, 5:1, (59-82).

-------- 1964. Toward a History of Amharic Vocabulary. *Journal of Ethiopian Studies*, II:2, (12-20).

-------- 1968. *An Amharic Conversation Book*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz

-------- 1995. *A Reference Grammar of Amharic*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz

Levine, D. 1974. *Greater Ethiopia*. University of Chicago Press.

Lykowska, L. 1993. Sentence Schemata for Amharic. University of Warsaw.

Mantel-Niecko, J. 1971. Palatograms of Sounds of Amharic. *Africana Bulletin*, 15, (23-41).

Messelech Melkie. 1985. Interrogative Sentences in Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Meseret Teshome. 1985. The Verb Phrase in Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Mullen, D.S. 1986. Issues in the Morphology and Phonology of Amharic: The Lexical Generation of Pronominal Clitics. PhD. Thesis, University of Ottawa.

Mulugeta Seyoum .2001. The Syllable Structure and Syllabification in Amharic. MPhil. Thesis, Norwegian University of Science and Technology.

Podolsky, B. 1977. Morphophonology of Amharic Verb. *Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies*, (91-96) Nice.

-------- 1980. The System of Verbal Stems in Amharic. *Proceedings of the Six International Conference of Ethiopian Studies*, (447-454). Tel Aviv.

-------- 1982. Some Problems in the Phonology and Morphology of Amharic. *Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies*, (17-18). Lund.

Polacek. Z. Functional Sentence Perspectives in Amharic, Preliminary Notes. In: Taddese Beyene, (ed). *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*, (567-572). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

-------- 1994. Several Notes on Amharic Syntactically – formed Adjectives. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1282-1293). New Jersey: Red Sea Press.

Richter, R.1984. On the Enrichment and Expansion of the Amharic Scientific Vocabulary. In: Taddese Beyene, (ed). *Proceedings of the Eighth International Conference of*

Ethiopian Studies, (567-572). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

---------1994. Lexicographical Notes on Amharic.In: Harold Marcus, (ed). *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1294-1301). New Jersey: Red Sea Press.

--------- 1997.Some Linguistic Peculiarities of Old Amharic Texts. In: Fukui, K. et al, (eds.). *Ethiopia in Broader Perspective: Proceedings of the Thirteenth International Conference of Ethiopian Studies,* (543-551). Kyoto, Japan.

Taddese Beyene. 1972. Aspects of the Verb in Amharic. PhD thesis, Georgetown University.

--------- 1980. Notes on Two Process Verbs in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies,* 14, (123-129).

--------- 1989. Terms of Endearment in Amharic, Their Morphological Structures and Sociolinguistic Norms. *Journal of Ethiopian Studies*, XXII, (65-75).

Taddese Tamrat. 1972. *Church and State in Ethiopia 1270-1527.* London: Oxford University Press.

--------- 1988. Ethnic Interaction and Integration in Ethiopian History: The Case of Gafat, *Journal of Ethiopian Studies,* XXI, (121-144).

Takkele Taddese. 1992. Are t' and s' Variants of an Amharic Variable: A Sociolinguistic Analysis. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*. No2, (103-121).

Titov, E. 1976. The Amharic Language. Moscow: NAUKA

Ullendorff, E. 1955. *The Semitic Languages of Ethiopia: a Comparative Phonology.* London: Tylor's Foreign Press.

Vassilevich, A. 1988. Colour Terms in Amharic. *Proceedings of the Ninth International Conference of Ethiopian Studies*, (142-148). Moscow

Voigt, R. 1980. The Amharic First Order Vowel. In: Serget, Stanislav (ed). *Ethiopian Studies: Dedicated to Wolf Leslau*, (142-148). Wiesbaden:

Wedekind, K. 1992. Which Form Predicts all Others Best? Variations on the Amharic Verb Theme. *Journal of Ethiopian Studies*, XXV, (73-92).

Zavdskaya, E. P. 1988. A Propos the Expression of Causation Category in the Amharic Language. *Proceedings of the Ninth international Conference of Ethiopian Studies*, (157-164). Moscow.